
የሩፍ ሰበበ

# የሱፍ አበባ

ሀብታሙ አለባቸው

2008 ዓ.ም

©ሀብታሙ አለባቸው፤ 2008

መብቱ በሕግ የተጠበቀ።

ሊትማን ቡክስ
አዲስ አበባ
ስልክ- +251930013422/ +25111262021

የመጀመርያ ዕትም፣ ጥር፣2008 ዓ.ም
2ኛ ዕትም የካቲት 2008 ዓ.ም

የሽፋን ቀንበር -ሐኒባል ገብረሕይወት

hannhiwot@gmail.com

ለዳዕሮ ነጋሽ

# ቅድመ-ታሪክ

ሰኞ፣ ሐምሌ 10/1961 ዓ.ም።

ከእናቴ ጋር ከባሕርዳር ወደ አዲስ አበባ የምበርበት ሰዓት እየቀረበ ነው።

"በኢትዮጵያ አየር መንገድ የ«ኢቲ-103» በረራ ወደ አዲስ አበባ ለመብረር የመጣችሁ እንግዶች የምትበሩበት «ዲሲ-3» መለስተኛ አውሮፕላን ከአዲስ አበባ ተነስቶ በመምጣት ላይ ነው። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ባሕርዳር አየር ማረፊያ ይደርሳል። እባካችሁ ለጉዞ ተዘጋጁ!" አለችን አንዲት መልከቀና አስተናጋጅ ከትኬት ማረጋገጫና ፍትሻ ክፍል ብቅ ብላ።

"እስቲ የቸር መንገድ አድርግልን!" እናቴ መስቀል በእጇ ሰርታ አማተበች። ለምን እንደሆነ እንጃ ከጧት ጀምሮ ፍርሃት ተጭኗታል። በአውሮፕላን ሄዳ ስለማታውቅ መስሎኝ ነበር፤ ስጠይቃት ግን ምክንያቷ ያ እንዳልሆነ ተረዳሁ።

"እንጃ ልጄ! ዛሬ እንዲሁ ቅፍፍ ብሎኛል፤ ነፍሱን ይማረውና ታላቅ ወንድምህ ሞተ ያሉኝ ጊዜም ጧቱኑ እንዲሁ ሲያደርገኝ ነበር።" ደግማ ደጋግማ ታማትባለች።

ላጽናናት ይገባኝ ነበር መሰለኝ። ለምን እንደሆነ እንጃ ዝም አልኳት።

በተርሚናሉ ዉስጥ በግምት20 የሚሆኑ ሰዎች ቀድመውን ደርሰዋል። በዕድሜ ትንሹ እኔ ሳልሆን አልቀርም። ባልና ሚስቶች፣ የእጅ ቦርሳ የያዙ ትልልቅ ሰዎች፣ ቦርጫም ነጋዴዎች፣ እንዲሁም ጥቂት ፈረንጆች ይታዩኛል። እኔና እናቴ አግዳሚው ወንበር ላይ ከተቀረው መንገደኛ ጋር ተቀላቅለን ተቀመጥን።

እናቴ አሁንም ለራሷ ብቻ በሚሰማ ድምጽ አንዳች ነገር ታልጎመጉምና አከታትላ ታማትባለች።

"ኧረ እማ! ይሄን ያህልስ አትፍሪ!" ሳቅኩባት።

"ፍርሃት ነው ብለህ ነው፣ልጄ!? አስቲ አንተም እመቤቴን አስታውሳት!!"

ከአፍታ ቆይታ በኋላ ስድስት ወይም ሰባት የሚሆኑ ወጣቶች እኛ ወደተቀመጥንበት አግዳሚ መጡ። ሦስት አራቱ በአፍሮ ዘዬ ያበጠሩት ፀጉራቸው ትንንሽ ጃንጥላ ይመስላል። እኔ አሥራ ሰባተኛ ዓመት ዕድሜዬን መያዜ ነው። በግምት በሰባት ወይም በስምንት ዓመት ይበልጡኛል። ሁሉም ወንዶች ሆነው በአለባበሳቸውና በሁኔታቸው ዓይን የሚስቡ ቄንጠኞች ናቸው። የባሕርዳር ፖሊቴክኒክ ተመራቂ ተማሪዎች እንደሆኑ ገመትኩ። እኔ ራሴ በዚያው ዓመት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስጄ ውጤት እየጠበኩ ነበር። ዩኒቨርስቲ የሚያስገባ በቂ ነጥብ ካስመዘገብኩ ነገ እንደ እነርሱ መሆኔ ሲታሰበኝ ከየት መጣ ያላልኩት አንዳች የደስታ ስሜት ሰውነቴን ዉርር አደረገኝ። የበለጠ አተኮርኩባቸው። ኮስተርተር ብለው በአጭር በአጭሩ ያወራሉ። እንደ ጓደኛማሞች እንኳ አይስቁም። 'ለካንስ ዩኒቨርስቲ የተማረ ሰው ብዙ አይስቅም!' አልኩ በሆዴ። እኔም እንደነሱ ኮስተርተር የምልበት ጊዜ ናፈቀኝ። ደግሞ በየንንግራቸው ጣልቃ እንግሊዝኛ ቃላት ጣል ሲያደርጉ ስሰማ የበለጠ ቀናሁባቸው።

ለእናቴ ስለነርሱ ላወራላት ስዞር እሷ በጭንቀት ተውጣ ቅዝዝ ብላለች። አሳዘነችኝ።

ከደቂቃዎች በኋላ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያዥጎረጎራት ትንሽ «ዲሲ-3» የመንገደኞች አውሮፕላን ከምዕራብ አቅጣጫ ጢዝዝዝዝ እያለች መጥታ አረፈች። ያመጣቻቸውን መንገደኞች አራግፋ ስትጨርስ እኛ በጀርባ በር በኩል በአስተናጋጆች እየተመራን ተሳፈርን። እናቴና እኔ በተሰጠን ቁጥር መሠረት ፊትና ኋላ ሆነን ተቀመጥን። መለያየታችን እንዲትም እርምጃ ቢሆን ደስ አላለንም። በተለይም እናቴ ተለያይተን መቀመጣችንን ስታውቅ ጭንቀቷ እጥፍ ሆነ።

ከኮሌጅ ወጣቶቹ አንዱ እማዬ አጠገብ በመስኮቱ በኩል ወንበር ያዘ። ሌላው ደግሞ ከእኔ አጠገብ ወንበር ቀይሮኝ ተቀመጠ። ደስ አለኝ። ጠይም፣ ረጅምና ቀጭን ነው።ሌሎቹ ከፊትና ከኋላ ብትንትን ብለው ሲቀመጡ አየኋቸው። በጥቁር ፕላስቲክ የተሸፈነው የአውሮፕላኑ ጣውላ ወንበር ሲቀመጡበት ሲጥ ሲጥ ይላል።

ስለ ዩኒቨርስቲ ሕይወት የምጠይቀው ወጣት አጠገቤ መቀመጡን ሳውቅ ቁንጥንጥ አረገኝ።

ሁሉም ተሳፋሪ መግባቱና እቃ መጫኑ ተረጋግጦ በሩ ሲዘጋ የአውሮፕላኑ ሞተር እኽኽኽኽ... ማለት ጀመረ።

ነጎኔ ከተቀመጠው ወጣት ጋር እንዴት ወሬ እንደምጀምር ማውጣት ማውረድ ጀመርኩ። በሆዴ ቃላት እየመረጥኩ ማሰካካት ያዝኩ። ስለ ዩኒቨርስቲ ሕይወት በደንብ እንዲነግረኝ ነው ፍላጎቴ። ወዲያው ግን አውሮፕላኑ ሽቅብ ወደ ከፍታው ሲበር ልቤ ፍስስ ልትል ደረሰች። ወደ እናቴ ዐየሁ። ዐይኖቿን በነጠላዋ ሸፍና ከፊት ለፊቷ ባለው ወንበር ላይ ድፍት ብላለች።

ከሴኮንድ ሴኮንድ ከመሬት እየራቅን ወደ አርያም አረግን። አውሮፕላኑ የተመደበለትን የጫማ ከፍታ ሲይዝ ትንሽ ተንፈስ አልን። ወደ እናቴ በድጋሚ ዞርኩ። ያው ናት። በጭንቀት ልትሞት ደርሳለች። 'ሰሀሊለነ ቅ--ድ--ስ--ት!' ትላለች ደጋግማ እያማተበች።

ረዳት አብራሪው እንግሊዝኛ ይሁን አማርኛ ባለየለት ቋንቋ ስለጉዟችንና ስለአየሩ ጠባይ በድምጽ ማጉያ ነገረን። አዲስ አበባ ደርሰን ቦሌ አየር ማረፊያ ለማረፍ 1 ሰዓት ከ20 ደቂቃዎች እንደሚወስድብን ተናገረ። የእናቴ ጭንቀት እንጂ እኔስ ለዘላለሙ ከአውሮፕላኑ ባልወርድ ተመኘሁ።

አሁን ደፈር ብዬ ወሬ ልጀምር ሳቀበቅብ ወጣቱ ፊት ነሳኝ። በዐይኖቼ ዐይኖቹን ስፈልጋቸው እንግዳ ነገር አስተዋልኩ። በጤናው አይመስልም። እሱ አጠገቡ ሰው የሌለ ያህል ወደ ፊትና ወደ ኋላው ቅብዝብዝ ይላል። ከመጠን በላይ ተረብሿል። ከሁኔታው አውሮፕላኑ አንዳች ብልሽት የገጠመው ነው የመሰለኝ። ወይም የሆነ ለኔ ያልገባኝ ነገር ተፈጥሯል። ይሄንኑ ወደጆሮው ጠጋ ብዬ ስጠይቀው ቀልቡ ጭራሽ አብሮት የለም። ከምንም ሳይጥፈኝ ከእናቴ አጠገብ የተቀመጠውን ጓደኛውን ተከሻው ላይ ገፋ ገፋ አደረገውና "ብርሃነ! ብርሃነ! ሬዲ?" አለው። ድምጹ ዉስጥ አንዳች ፍርሃት አለ። ወደ ፓይለቱ አቅጣጫ ዐይቶ ደግሞ ከሌላ ጓደኛው ጋር በዐይንና በእጅ ምልከት ሲሰጣጡ አስተዋልኩ።

"ብርሀነ" ብሎ ወደጠራው ጓደኛው ስመለከት እሱም ልክ አልነበረም። ቀይ ፊቱ ደፍርሶ፣ አፍሮ ጸጉሩ እንደ ምሶሶ ቆሟል። የፊቱ ምስል በጭራሽ የሚረሳ አይደለም። ገና ዐይኔን ወደርሱ ከማዞሬ ድንገት ብድግ ብሎ እናቴን በኃይል ገፍትሯት ወደ ማቋረጫው አለፈ።

"እንዴ፣ ምን ነካህ ሰውዬ?" በንዴት ጮኽኩበት።

ልብም አላለኝ ወይም ጨርሶ አልሰማኝም። አቀማመጤን አስተካከዬ እንደገና ቁጭ ስል አጠገቤ የተቀመጠው ወጣት የወገብ ቀበቶውን በጥይት ፍጥነት ፈትቶ ከወንበሩ ብድግ አለ። እጁን ከላይ ወደተጫነው ሻንጣው የጎን ኪስ ይመስለኛል እየተርበተበተ አስገባው። ወዲያው ማረሻ የሚያክል አውቶማቲክ ሰንጢ አወጣ። ድንጋጤ በተቀመጥኩበት በረዶ አደረገኝ። በፍርሀት እየተናጥኩ ቀና ብዬ ሳየው ሌላ አንድ ጓደኛቸው ከጀርባችን እየጮኸ መጣ። ወደ ፓይለቱ አቅጣጫ እየከነፈ ሲያልፍ ቀኝ

እጁን ዐየሁት። ረመጥ የመሰለና ዘለበቱ የፍየል ጆሮ የሚመስል ጀለቲና ቦንብ ይዟል። ከፓይለቱ በር ሲደርስ ፊቱን ወደ እኛ አዞሮ ቆመ።

"አንድም ሰው ንቅንቅ እንዳይል! ልብ አድርጉ! ትንሽም የተለየ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ሰው ካለ አውሮፕላኑን እናጋየዋለን!" በመጨረሻ ድምጹ ጮኾ ልብ በፍርሀት የሚያርደውን የእጅ ቦንብ ከፍ አድርጎ እጁን እያወናጨፈ አሳየን።

ልቤ ከላይ ከላይ ድው ድው እያለች ልታመልጠኝ ሆነ።ወደ እናቴ በጭንቀት ተውጬ ዐየሁ። የፊቷ ቀለም ልውጥውጥ ብሏል። ስለርሷ ሳይሆን ስለኔ እየተጨነቀች እንደሆነ ዐይኖቿ ነገሩኝ።

ሁሉም ነገር አስፈሪና ቅጽበታዊ ነበር። እኔና እናቴ አጠገብ ተቀምጠው የነበሩት ጓደኛሞች እንደደነበረ ነብር እየተምዘገዘጉ ሄደው ቦንብ የያዘ ጓደኛቸውን አለፉት። የፓይለቱን በር በቀላሉ ቷ አድርገው ከፍተውት ገቡ። "ልብ አድርጉ! አንድም ሰው ከተቀመጠበት እንዳይንቀሳቀ---ስ!!" ከጀርባችን የኦሮምኛ ቅላጼ የተጫነው ድምጽ እንደ ብራቅ ጮሆ ትእዛዝ ሰጠን። ወደ እሱ ዞር ስል ሁለት ሴት የአውሮፕላኑ አስተናጋጆች ጭንቅላታቸውን ይዘው ፊታቸውን እንዲዞሩ ተደርገው ዐየሁ። ከአንድ ሁለት ደቂቃዎች በኋላ የካፕቴይኑ የተረበሸ ድምጽ በውስጥ መነጋገሪያ በኩል መጣ።

"መንገደኞቻችን፣ አብራሪያችሁ ነኝ። ጥሩ ዜና የለኝም። አውሮፕላናችን ተጠልፏል። አሁን ከተፈቀደልኝ መስመር ወጥቼ ወደ ሱዳን ኻርቱም እንዳበር ተገድጃለሁ። ለሕይወታችንና ለደህንነታችን ስል የበረራ አቅጣጫ ቀይሬያለሁ...ፀሎታችሁ አይለየን..."

'ስሀሊለነ ቅ--ድ--ስ--ት!' እናቴ ነበረች።

ዞሬ ዐየኋት። በሚያሳሳ የወላጅ ዐይኗ ዐየችኝ። እርሷ ሞታ ነገር ግን አንድዬ ወንድ ልጇን እንዲጠብቅላት ወደ ፈጣሪ እየፀለየች እንደሆነ ገባኝ። ሀሊናዬን ልስት ትንሽ ሲቀረኝ ጭንቅላቴን ይዤ ወደ መሬት አቀረቀርኩ...

# 1

1968 ዓ.ም።

አዲስ አበባ በሙቀት የምትጠበስበት የዓመቱ አጋማሽ፤ ከፈረንሳይ ለጋሲዮን ወደ መሳለሚያ ቤት እየቀየርኩ ነው። አዲሱን ቤቴን ገና አላየሁትም። እኔ ለአንድ ወር ጅማ ሳለሁ የፖለቲካ ታማኝ ጓዴና ወዳጂ ልቤ የኾነው ኢሳያስ ምሩጽ ነው በሌለሁበት የተከራየልኝ። እሱ ነው ኮተቴን ሁሉ በአሮጌ «ኤን ዱዌ» የጭነት መኪና አስጭኖ ያደረሰልኝ። አሁን ወደዚያ መሄድ ይኖርብኛል።

ለኢሳያስ ስልክ ደወልኩለት። ያንኑ አሮጌ «ኤን ዱዌ» መኪና ላከልኝ። ይሄን ከርካሳ መኪና የምንጠቀመው ትኩረት ላለመሳብ እንደሆነ ገብቶኛል። መኪናው ከበግ ተራው ራቅ ብሎ ነው የቆመው። ወደዚያ መራመድ ከመጀመሬ በፊት ለመጨረሻ ጥንቃቄ ቆም ብዬ አካባቢዬን ቃኘሁ። ቀጥሎ ራሴን በለሆሳስ ደባበስኩ። ሁሉም በተገቢው ሥፍራ መኖሩን አረጋገጥኩ።

በጀርባዬ የጅማ ኢሕአፓ ኮሚቴን 16 ገጽ ሪፖርት ይዣለሁ። በሆዴ በኩል ደግሞ የራሴን 9 ገጽ ራፖር ከቀበቶዬ ጋር አጣብቄ ይዤዋለሁ። ሙታንታዬ ውስጥ ብልቴ ጎን አሜሪካ ሰራሽ ኮልት-38 ሽጉጤን ሽንጫለሁ። ቀልጠፍ ብዬ በአሮጌው «ኤን ዱዌ» መኪና ተሳፈርኩ።

"እንሂድ!" የሚል ምልከት ገና ከመስጠቴ ወጣቱ ሾፌር ሞተሩን ተረክ አደረገው። ልጁ ከ17 ዓመት በላይ የሚሆነው አይመስለኝም። በድርጅቱ በኩል የሚያገናኘን ምንም ዓይነት መስመር የለም። ተልእኮ እንዳለን ብንግባባ እንኳን አንድም ቃል ትንፍሽ አንልም። ድልድዩ ጋ ስንደርስ ቀና ብሎ አየኝ። አንድ

ነገር ሊናገር እንደፈለገ ጠረጠርኩ።

"ያመጣሁልህን ቱታ አለበስከውም። ኢሳያስ ለብሶት ይምጣ ነው ያለኝ..."

"እ ስጠኝ! ስጠኝ! ይቅርታ...ረስቼው እኮ ነው...።" ከተቀመጥኩበት ወንበር ጀርባ ወደተቀመጠ ጆንያ አመለከተኝ። አውጥቼ ከፈትኩት። ለአዲሱ ማንነቴ የተለገሰኝ የሕቡእ ዩኒፎርም ነው። አዲስ ጠቆር ያለ ሰማያዊ ቱታ፣ ከበድ ያለ ቆዳ ጫማና ቆብ፣ ፊትን በከፊል የሚሸፍን የብየዳ ጨረር መከላከያ መነጽር አገኘሁ። ፈጠን ብዬ ቱታውን ለበስኩና መነጽሩንም አደረኩት። አንድ ወሳኝ ነገር መኖሩን ለማረጋገጥ በድጋሚ ቱታዉን ደባበስኩ። አለ። በቱታው ኮሌታ ውስጥ ተቀብሮ አገኘሁት። 'ሲናይድ' የሚባለው የመርዝ እንክብል ነው። በኢሕአፓ ከፍተኛ ካድሬነቴ አይበለውና በአንዳች ከፉ አጋጣሚ በጠላት እጅ ላይ ብወድቅ ሲናይዷን ተጠቅሜ በቀላሉ ራሴን ማጥፋት እችላለሁ። ለምን እንደሆነ አላውቅም ሲናይዱ በራስ የመተማመን ስሜቴን ሰማይ አደረሰው።

'ከሰዓታት በኋላ ኑሮዬን መሳለሚያ በአዲሱ ቤቴ እጀምራለሁ። አዲስ ሰፈር...፣ አዲስ ሥራ...፣ አዲስ ሕይወት...፣አዲስ ጎረቤት...፣ አዲስ ተልእኮ...በድምሩ አዲስ ሰብዕና!' በረጅሙ ተነፈስኩ። ለአንድ ዓላማ መኖር መጀመርን እጅግ ናፍቂያለሁ።

የአሮጌው «ኤን ዱዌ» ቀርፋፋነት ትእግስት ይፈታተናል። እንደ ቅንቡርስ እየተጎተተ ከረፋዱ አራት ሰዓት ላይ ስድስት ኪሎ ደረሰ።

አዲስ አበባ እንደከራሞቷ ግራ ተጋብታ ወዲያና ወዲህ እየተቅበዘበዘች ጠበቀችኝ። አገር ምድሩ ይሰግድላቸው የነበሩት ንጉሷ አጼ ኃይለሥላሴ አሁን በሥልጣንም በሕይወትም የሉም። በግሌ የእሳቸውና የሥርዐተ-መንግሥታቸው መራር ተቃዋሚ ነኝ። ጉሮሮዬ እስከሚሰነጥቅ ድረስ አውግዣቸዋለሁ። የመጨረሻ የአገዛዝ ዘመናቸው እንደፈራሁት አላማረም።

'ከሞቱ አሟሟቱ!ይላል የአገሬ ሰው።'

ድፍን ኢትዮጵያ ሆ! ብላ በእሳታዊ አብዮት ከሥልጣናቸው ካወረደቻቸው ሁለት ዓመት ሞላ። ነገር ግን አገሬ እሳቸውን ሸኝታ ልትራመድ እግሯን ስታነሳ አቅጣጫው ጠፋባት። እስካሁን ድረስ እንደ ሙሴ ባሕር ሰንጥቆ የሚያሻግር መሪ ያገኘች አትመስልም። አለመታደል ኾኖ አገሬ የራሺያ አብዮት እንደፈጠረው ቪላድሚር ኤሊች ሌኒን ወይም እንደ ቻይናው አብዮታዊ መሪ ማኦ ሴ ቱንግ ዓይነት ሰው የላትም። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ያ ሰው ከድርጅቴ ኢሕአፓ እንደሚወጣ አልጠራጠርም።

###

እናቴ ባወጣችልኝ ሥም "ሰመረ ማንደፍሮ ውቤ" እባላለሁ። ድርጅቴ ኢሕአፓ ደግሞ "አላምረው" ብሎኛል። የምወዳቸው አራት ስሞች አሉ። አራቱም በ "ኢ" ፊደል የሚጀምሩ ናቸው–ኢትዮጵያ፣ ኢሕአፓ፣ ኢኮኖሚክስና ኢሳያስ። እንደ መጥፎ እድል ሆኖ ግን አራቱም ወዳጆቼ ወደፊት በምንገነባው ኮሚኒስት ሥርዐተ-ማኅበር ውስጥ አይኖሩም። ኢትዮጵያ የ"ዓለማቀፋዊ ላባደራዊነት" መርህ እውን ሲሆን ፖለቲካ ይከስማል፣ያኔ አብራ ትከስማለች። "ኢትዮጵያ ታበጽህ ኢደውሀ አበ እግዚአብሔር..." የሚሉትን አልቀበልም።

የሚጎተተው የጭነት መኪና ጊዮርጊስን አለፈ። አካባቢው እንደሁሌው ነው። እንደወቅቱ የአገሪቱ ፖለቲካ አየር ተፋፍጓል። ጭንቅላቴ ወደ ኢሕአፓና ወደ አዲሱ ማንነቴ ተመለሰ...

በድርጅቴ ኢሕአፓ ትእዛዝ ሁለት ዓመት ተኩል አካባቢ የሠራሁበትን የመንግሥት ሥራ ለቅቄያለሁ። እርሻ ሚኒስቴር ነበር የምሠራው። ከዚህ በኋላ የምኖረው ግን ሕቡዕ ገብቼ በአዲስ ማንነት ነው። በወር አገኝ የነበረውን 345 ብር ደመወዝ ትቼው መምጣቴ ነው። በምትኩ ለኑሮ መደጎሚያ ኢሕአፓ በየወሩ 40 ብር ይቆርጥልኛል።ይህ በመሆኑ እጅግ ደስተኛ ነኝ። አሁን የኢሕአፓ የሙሉ ጊዜ ካድሬ ነኝ። ሥራዬን ለድርጅት ስል መልቀቄ እቼን ያህል ቅሬታ አልፈጠረብኝም። ለኢህአፓ እንኳን ሥራዬን ራሴንም እሰጣለሁ። ያላንዳች ስስት።

እርሻ ሚኒስቴር በንጉሡ በራሳቸው ጭምር የተናቀ መሥሪያ ቤት ነበር። ዓመታዊ በጀቱ ከጠቅላላው ብሔራዊ በጀት ከ፣ ነጥብ 5 በመቶ ከፍ ብሎ አያውቅም። ለአስር ዓመታት አካባቢ ሚኒስትር ሳይሾምለት ቆይቷል። መሬት በባላባቶች በተያዘበት አገር በእርግጥም እርሻ ሚኒስቴር ምን ይጠቅማል? ሥራ የሌለው ተቋም ነበር። ረዘም ያለ ጊዜ የሠራሁት ደርግ ከመጣ በኋላ ነው። በደርጉም የተለወጠ ነገር የለም። በዚህ ላይ መኢሶን ሰርስሮት እየገባ ነው።ሥራው ባስጠላኝ ጊዜ ኢሕአፓ ገላገለኝ። የሲዳሞ ክፍለሐገርን የዓመቱን በጀት 152 ሺህ ብር አድርሰ ብለው ላኩኝ። ገንዘቡን ለድርጅቴ አስረከቤ በዚያው ብን ብዬ ጠፋሁ። ነገር ግን በፍጹም ራሴን እንደ ሌባ ዐይቼው አላውቅም።

'ይገርማል!' አልኩ ለራሴ፣ የፖለቲካ መንገዴን መነሻና መድረሻ ሳስብ።

በአጭር ጊዜ ነው የኢሕአፓን መሰላል ፋት ብዬ የወጣሁት። ኢሳያስ የመለመለኝ ኢሕአድ ገና በኢሕአፓ ሳይተካ ነበር። ለአምስት ወራት ያህል በሕዋስ ደረጃ ቆየሁ። ቀጥዬ እዛው ፈረንሳይ ኤምባሲ አካባቢ ወደ ንዑስ ሪጅን አባልነትና ጸሐፊነት ከፍ አልኩ። እዚህም ብዙ አልቆየሁም። በፍጥነት የሪጅን ሦስትን ጸሐፊነት ተረከብኩ። በወራት ውስጥ የንዑስ ዞንና የዞን ጸሐፊነት ኀላፊነቶችን ተወጥቼ አዲስ አበባ በይነቀጠናን ተቀላቀልኩ። አዳዲስ አባላት መምጣት ሲቀጥሉ አዲስ ምደባ ተደረገ። የፖለቲካ

ኮሚቴ ተጠሪ ሆኜ ተመደብኩ። ተሾምኩ አይባልም መቼም በተራማጅ ድርጅት ውስጥ። አሁን ይኸው ከማእከላዊ ኮሚቴውና ከፖለቲካ ቢሮው አፍንጫ ሥር ነኝ።

ፍቅረኛ ነበረችኝ። ያውም ለሀጩ ጠብ እስኪል ድረስ የምወዳት። ብርኪታዊት አዳነ ትባላለች። ብርኪቴ በአጭር ጊዜ ዝና ያተረፈች፣ ድፍን አገር በድምጿ የሚያውቃት የኢትዮጵያ ራዲዮ ጋዜጠኛ ናት። ለሁለት ዓመታት በፍቅር እፍ ብለን አብደናል። ስለጋብቻም ወሬ ጀማምረን ነበር። በመሀሉ ይህ ግዳጅ መጣ። ግዳጁ ለብርኪቴ ምሥጢር ነው። እንዲያውም ዶክተር ተስፋዬ ዘርዐ ከሕሸን መለያየቴን ሳይፈልጉት የቀሩ አይመስለኝም። 'ብርኪታዊት ላይ የሆነ ጥርጣሬ አሳድረው ይሆን?' በእውነት አላውቅም።

በአዲሱ ኑሮዬ አጀማመር ላይ እየጎመዘዘኝ ዋጥ ያደረኩት መራራ ሀቅም ይኸው ነው። ከብርኪት ጋር ጨክኖ መለያየት። መስዋእትነት ነው። ለምወደው ድርጅቴ ስል የከፈልኩት መስዋዕትነት። እዚህ ሄጄኩ ሳልላት ድንገት ተሰወርኩባት።

የሚንተተው «ኤን ዱዌ» ኢሕአፓንና አዲሱን ማንነቴን በሰከነ መልኩ መልሼ ለማየት እድል ሰጠኝ።

***

ከብርሃነመስቀል ረዳ ጋር የተዋወቅንበት ዕለት ልክ እንደ ሰርግ ቀን ልዩ ስሜት ይሰጠኛል። ከሁለት ወራት በፊት ሰባ ደረጃ አካባቢ በሚኖርበት ቤት አግኝቼው ነበር። ከሦስት ሰዓት በላይ ተጫወትን።

"ረዘነ...ብታምንም ባታምንም ከሰባት ዓመታት በፊት ሐምሌ 10 ቀን ሰኞ ዕለት ነው ለመጀመርያ ጊዜ ያየሁህ።" ስለው ሁልጊዜም ግርም ይለዋል። ረዘነ ነው የትግል ስሙ። ሁለቱንም ስሞቹን እወዳቸዋለሁ። እጅግ አድርጌ የማከብረው መሪዬ ነው።

"ረዜ! ልብ አድርግ! የኔና ያንተ ትውውቅ የሚጀምረው ምድር ላይ ሳይሆን ሰማይ ላይ ነው..." ይህ ንግግሬ ሁሌም ያስቀዋል፤ይገርመዋል። በእርግጥ ብርሃነመስቀል ብዙም በነገሮች የሚደነቅ ሰው አይደለም። የኔ በዚያ በጠለፈው አውሮፕላን ዉስጥ መኖር ግን ሁሌም ያስደንቀዋል።

«ከእናቴ ጋር ነበርኩ ነው ያልከኝ?»

«አዎ! ለዛውም አንተ አጠገብ...ገሬታትረሃት ስትሄድ ላንቀህ ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ነበር...»

በጭራሽ ትዝ አይለውም። ነገር ግን ግጥምጥሞሹ ፍጹም ያስደንቀዋል።

የጠለፋውን ድራማ እንስተን ስንሳሳቅ ቆየን። ቀስ በቀስ ወደ ድርጅታዊ ጉዳያችን አለፍን። በኢሕአፓ

አባልነቴ ሁሌም የሚከነከኑኝ ሁለት አወዛጋቢ ውሳኔዎች አሉ። አንደኛው በውጭ አገር ድርጅት የመመስረቱ ተግባር ነበር። ከወሬ ወሬ አነሳሁለት።

"ጓድ ረዘነ፣ ያኔ ኢሕአድ/ኢሕአፓን ለመመስረት ወደ ሱዳንና አልጀሪያ ከምትሄዱ ወደ አርማጭሆ ወይም ወልቃይት ጠገዴ መሄድ ትችሉ የነበረ ይመስለኛል።" አልኩት ዘና ብዬ።

"ጓድ አላምረው፣ ይህ መሆኑ የተደፋ ውተት ለማፈስ ከመሞከር ያለፈ ለአሁኑ ኢሕአፓ ምን እርባና አለው ብለህ ነው? ጉዳዩ የመሪ ድርጅት ፕሮግራም ከመቅረጽና የድርጅቱን አስኳል ከመፍጠር የዘለለ አይደለም። ይሄን ለማድረግ ቦታው አልጀርስ ይሁን በርሊን፣ አዲስ አበባ ይሁን አርማጭሆ ምን ይፈይዳል? ከዚያ ይልቅ ለምን ስለ አሲምባ አታነሳም?" ትንሽ ስሜታዊ የኾነ መሰለኝ።

ከብርሃነመስቀል ጋር ከደቂቃዎች በፊት የነበረን ቅርበትና መላመድ ወደ ድርጅታዊ ጉዳዮች ሲያመራ ቶሎ መልኩን ቀየረ። ቁጣውን ስመለከት ግን ልሞግተው አመነታሁ። ዝም ብዬ ሳየው «ከጳጳሱ ቄሱ...» ብሎ የተረተብኝ መሰለኝ።

የሆነ ሆኖ ኢሕአድ/ኢሕአፓ አርማጭሆ ውስጥ አልተፈጠረም። እናገኝ የነበረውን ጥቅምና ሊደርስብን ይችል የነበረውን ጉዳት አሁን መገመትም መነጋገርም አይቻልም። አገር ውስጥ ቢመሠረት ግን ቢያንስ የሥነልቦና ጥቅም ያተርፍልን ነበር ብዬ በግሌ አምናለሁ። አሁን አዲስ አበባ ቁጭ ብለን እንደ መንደር ቀላዋጭ ያፈጠጥነው ነገርም ላይፈጠር ይችል ነበር። ሁለተኛውና ልቀበለው የቸገረኝ ውሳኔ ደግሞ ድርጅታዊ ሽግግሩ ነው። በሌላ ጊዜ ብርሃነመስቀልን አነሳሁለት።

"ረዘ...በበኩሌ ኢሕአድ መታጠፍ አልነበረበትም። ከርእዮተ-ዓለም ነጻ የሆነ ሰፊ ብሔራዊ ግንባር ሆኖ ሊቀጥል ይገባ ነበር። ምክንያቱም የቀኞችንና አክራሪ ብሔረተኞችን ድጋፍ ጭምር ማግኘት ያስችለን ነበር። ኢሕአፓ ከጀርባ ሕቡእ ሆኖ ግንባር ቀደም መሪ መሆን ነበረበት። ተሳሳትኩ፣ ጓድ ረዘነ?"

የሰጠኝ መልስ አሁንም ግራ ያጋባኝና በትንሹም ቢሆን ያስደነገጠኝ ነበር...

"ይሄንን ከዘርው ከሕሸንና ከተስፋዮ ደበሳይ ጋር ብትወያይበት የተሻለ መልስ የሚሰጡህ ይመስለኛል..." ብሎ ዝም አለ።

ብርሃነመስቀል ለምን ቶሎ ስሜታዊ እንደሚሆን ግን አልገለጥልህ ይለኛል። ምናልባት ሥራ ስለሚበዛበት ይሆናል። ምናልባትም ባህሪው እንደዚያ ሊሆን ይችላል። ዞሮ ዞሮ ለርሱ ያለኝ አክብሮት እንዲች ያህል ሸርፍ አላለም።

###

በ1964 በብርሃነመስቀል የሚመራው የአልጀርስ ቡድን ኢሕአድ/ኢሕአፓን ፈጠረ። እንደ እንጨት ቆርጦ...መትሮ... ፈልጦ...ጠርቦ...አለስልሶ...ቀለም ቀብቶ የፈጠረው ደግሞ ብርሃነመስቀል ነው። እያንዳንዷን የፕሮግራሙን ቃል በእጁ የጻፋትም እርሱ ነው። የመጀመሪያው የድርጅቱ ዋና ጸሐፊ ሆኖም ተመርጧል። ወደ አገር ቤት ከገቡትም የሚቀድመው የለም። የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) ጥንስስ ይዞ ለመጀመሪያ ጊዜ አሲምባን የረገጠም እርሱ ነው።

ኤርትራ ውስጥ መንገድ ላይ ችግር ገጠመው። በኢሳያስ አፈወርቂና በሳላህ ሳቤ የሚመራው የኤርትራ ነጻነት ግንባሮች ጥምረት መንገድ ዘጋባቸው። ይባስ ብሎ ሳህል በርሀ ውስጥ የቁም እስረኛ አደረጋቸው። ጠበንጃቸውን አስረክበው አንድ ዓመት ተኩል ታገቱ። የእገታው ምክንያት "የምናሳልፋችሁ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት መሆኗን ስታምኑልን ነው። ፈርማችሁ እለፉ..." የሚል ነበር።

ብርሃነመስቀል አመነታ። በኋላ ግን ቁርጥ ያለ መልስ ሰጣቸው። ጥያቄያቸው ከርሱ በላይ መሆኑንና እርሱ ቢያምንበት እንኳ የድርጅቱን አቋም በግሉ ሊለውጠው እንደማይችል ነገራቸው። ቢሉት ቢሠሩት ፍንክች ሳይል ቀረ።

የዛሬው ድርጅቴ ኢሕአፓ እንግዲህ የዚህ ሰው ቅያስና ቅድ ውጤት ነው። እኔም፣ ሁላችንም የርሱ እቅድ ዉጤቶች ነን። አሁን እኔ ከድሮው በተሻለ ደረጃ ላይ ነኝ። እሱንም ሆነ ሌሎች መሪዎቻችንን አብሬያቸው ልውል፣ ላመሽ፣ ላድር፣ ልሠራ...በዝግጅት ላይ ነኝ። ልባዊ ኩራት ተሰማኝ።

ብርሃነመስቀልን አካሉን ያየሁት አውሮፕላን ዉስጥ ይሁን እንጂ ዉብ ነፍሱን ማንበብ የቻልኩት በጽሑፎቹ በኩል ነው። የአዲስ አበባ በይነቀጠና የኢሕአፓ ጊዜያዊ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ ስሆን በአግባቡ በአካል ተዋወቅን። በየአርባ አምስት ቀኑ ከፖሊት ቢሮና ከማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ጋር መደበኛ ስብሰባ እንቀመጣለን። ሁለት የጋራ ስብሰባዎችን ስናደርግ አንደኛውን የመራው እሱ ነው። በልጅነቱ ደሴ ወይዘሮ ስሕን ትምህርት ቤትና አዲስ አበባ ተምሯል። ለዚህ ይመስለኛል አማርኛው ጥርትና ብቅት ያለ ነው። በዚህ ችሎታው ከኢሳያስ ምሩጽ፣ ከዘርው ከሕሸን፣ከዶክተር ተስፋዬ ደበሳይና ከሌሎች የትግራይ ልጆች ይለያል።

ዓመቱ ለኢሕአፓ መቼም ከባድ የፈተና ጊዜ ነበር።

የአዲስ አበባ በይነቀጠና ኢሕአፓ ኮሚቴ ሥር በሰደደ የመረጃና የፋይናንስ ችግር ተፈትኗል። እማደርገው ነገር ችግር ብሎ ቸገረኝ። መፍትሄ ፍለጋ ከተስፋዬና ከዘርው ጋር ዋተትን። ስድስት ተከታታይ ስብሰባዎችም ብናደርግም ችግሩን ብዙም አልፈታነውም። ያካሄድናቸው ስብሰባዎች ግን

አርስ በርስ በደንብ ለመግባባት ረድተውን አለፉ። በዚህ ጊዜ ይመስለኛል ወደ ኢሕአፓ የፖለቲካ ኮሚቴ ሊያሳድጉኝ የወሰኑት።

'በእውነት መታደል ነው!!' እጅግ በጣም ደስ አለኝ። በሌላ በኩል ደግሞ ትልቅ ኃላፊነት መሆኑ እንቅልፍ ነሳኝ። በዕድሜና በልምድ እነ ብርሃነመስቀል ጋር የምቀራረብ ሰው እንዳልሆንኩ ልቤ ያውቀዋል። ምናልባት እኩል የሚያደርገን ነገር ቢኖር ለድርጅቱ ያለን ወደር የሌለው ፍቅር ነው።

እስከአሁን በአካል ያልተዋወኩት ከፍሉ ታደሰን ብቻ ነው። ከፍሉ የመጀመሪያው ትውልድ አባል ነው። እሱንም ቢሆን በዚህ በአዲሱ ሥራዬ ምክንያት በቅርቡ እንደምተዋወቀው ተስፋ አደርጋለሁ። ከጌታቸው ማሩ ጋር ግን ዩኒቨርስቲ ግቢ እያለን ጀምሮ በደንብ እንተዋወቃለን። የሁለተኛው ትውልድ አባል ስለሆነ ትንሽ ይቀድመኛል። እኔና ኢሳያስ ሦስተኛው ትውልድ ነን።

በዚህ ጊዜ እነ ከፍሉና ተስፋዬ ውጭ ሄደዋል። አሁን ሦስት ትውልዶች በመሪነት ወንበሩ ዙሪያ ተሰባስበናል። አንድ ግብ ጥለን እየሠራን ነው። መቼም የካርል ማርክስን ሥራዎች ያህል የሚያረካኝ ሥነጽሑፍ የለም። አጥር ምጥን ባሉ ቃላት ከውቂያኖስ የሰፋን ጉዳይ ጥቅልልል አድርጎ ቁጭ ያደርገዋል። "ፈላስፎች ዓለምን በተለያየ መንገድ ገልጸዋታል። ቁም ነገሩ ግን መለወጡ ላይ ነው።" ይላል። ጥሩ ብሏል። ደግሞም ትክክል ነው።

ኢትዮጵያን የመለወጡ ፋንታ የማንም ሳይሆን የኛ ነው።

***

«ሌን-ዱዌ» መኪናችን እየተንፏቀቀ ቁልቁለቱን ወርዶ ሐብተጊዮርጊስ ድልድይ ሲደርስ ጸጥ አለ። ልጅ አግሩ ሾፌር ወርዶ ሆድ እቃውን ቢነካካው...ቢጎረጉረው... ምን ቢለው ዝም ጭጭ። ከአንድ ሰዓት በላይ ጠብቄ ሳይጠግነው ሲቀር በአውቶቡስ የመሄድ ሐሳብ መጣልኝ። ሾፌሩን ነግሬው ወደ ፌርማታው ተሻገርኩ። ባጋጣሚ ደግሞ የመሳለሚያዋ አውቶቡስ እስከ ጉሮሮዋ በሰው ተጨናንቃ ደረሰች። የዩኒቨርስቲ ትምህርቴን ከጨረስኩ ወዲህ ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ በአውቶቡስ ልሄድ ነው። ቅር አላለኝም።

'ደግሞም እኮ መደባዊ አሰላለፌ ከእነዚህ ምስኪን ተሳፋሪዎች ጋር ነው።' ለራሴ ነገርኩት።

ተጋፍቼ ተሳፈርኩና እንደምንም ቦታ ይዤ ቆምኩ። አውቶቡሱ እያቃሰተ ጉዞውን ቀጠለ። ወደ አዲስ ከተማ ትምህርት ቤት ስንጠጋ ግን ችግር ተፈጠረ። ከእኔ በአንድ በሁለት ሰው ልዩነት የቆመች ሴት የአንገት ሐብሏን ተሰረቅኩ ብላ ኡኡታዋን አቀለጠችው። ከመቅጽበት በተሳፋሪዎች መሐል የጋለ

ጭቅጭቅ ተፈጥሮ አውቶቡሱ ለመቆም ተገደደ። አዚያው አካባቢ የነበሩ ሁለት ወንድና ሴት ፖሊሶች ተጠርተው መጡ። እኔ ያለሁበት የመሀለኛው በር ብቻ ተከፍቶ አንድ በአንድ ውረዱ ተባልን። ሦስተኛ ይሁን አራተኛ ሰው ሆኜ ወረድኩ...

'ጉ--ድ ፈ----ላ! ፍተሻ ሊመጣ ነው...' የምጸልይለት ታቦት ጠፍቶኝ ግግር በረዶ ሆኜ ቆምኩ፣ በድንጋጤ።

ገና አንዲት እርምጃ ሳልራመድ፣ ለድርጅቴ አንድም ቁም ነገር ሳልሠራ ሲናይድ መርዝ እንክብሉን የምውጥበት ተልካሻ አጋጣሚ መጣ ማለት ነው? እ፫፫ ድብን እልኩ። ምክንያት የሌለው ሰማእት መሆኔ እንደ እግር እሳት ጠበሰኝ። ይባስ ብሎ ደግሞ ሐብሉ የጠፋባት ሴት ወርዳ ተንደርድራ መጥታ አንገቴን አንቆችኝ። ሌላ ጉድ!

"ይሄን ልጅ ያዙልኝ! ይሄን ልጅ ያዙልኝ! እሱ ነው የሰረቀኝ... ይኸ ነው ሌባው...እእእ...!!!"ኮሌታዬን ይዛ ወዘወዘችኝ።

'ወ---ይ---ኔ!' አልኩ ለራሴ፣ ያ ሁሉ ሕዝብ በአውቶቡሱ መስኮት አንገቱን ብቅ ብቅ አድርጎ ሲያፈጥብኝ ከማጅራቴ በኩል ቀዝቃዛ ላብ ተንቆረቆረ። ኾኖም መረበሼ ፊቴ ላይ እንዲታይ አልፈቀድኩም። የሞት ሞቴን ተረጋግቼ ቆምኩ።

የውስጥ ስሜቴ እንደ ገደል ናዳ ሲል ይሰማኛል። ሁለቱ የተለያየ ካባ የለበሱት ማንነቶቼ "ሰመረና አላምረው" አዘቅት ወረዱ። ግጭት ውስጥ ገብተው አንገት ለአንገት ተናነቁ። ባለሸጉጡና የኢሕአፓው አመራር «አላምረው›› ተራ የአውቶቡስ ሌባ ሆኖ ቁጭ አለ። ባለዲግሪውና ወፍራም ደመወዝተኛው «ሰመረም» የውስጥ ከብሩና ኩራቱ እንደ ሸከላ ሰብርብር አለ። "የሴቶች አኩልነት ዛሬውኑ!" ብዬ የጮኽኩበት ጉሮሮዬ በታገልኩላት ሴት እጆች ታንቆ ተያዘ። መቼስ በጠላትንት ላያት አልችልም።

'ወይኔ፣ ሰመረ ማንደፍሮ!' እንደ ብረት ጠንከሬ ሊታያቸው የሞት ሞቴን ታገልኩ።

ሴቲ ፖሊስ ሌባ ስለመሆኔ እምስት ሳንቲም ጥርጣሬ አላደረባትም። ይሄ የለበስኩት የጋራዥ ቱታ ነው ጉድ ያረገኝ። መጥታ ረባሽ ሕጻን ልጅን በሚቀጡበት ዓይነት ጆሮዬን በንቀት ቆንጥጣ ያዘችኝ።

«ይቺ የለመደች ጨሉሌ ናት፣ ታስታውቃለች!» ጆሮዬን ይዛኝ በንቀት ስትመለከተኝ ደሜ ፈላ። ኾኖም ለመረጋጋት ሞከርኩ። ከቢሮዬ ስወጣና ስገባ የክብር ሰላምታ ይሰጠኝ የነበረ እጅ ነው ዛሬ ጆሮዬን የያዘው።

እብሯት የነበረው ወንዱ ፖሊስ ግን ትኩ---ር ብሎ ሲያየኝ ከቆየ በኋላ ጠጋ አለኝ። ምናልባት ያሳየሁት በራስ መተማመንና ቆዳዬ ላይ ያየው ምቾት ሌባ ስላለመሆኔ ጥርጥሬ ላይ ሳይጥለው አልቀረም።

ንዴትና ፍርሃቴ ብን ሲል ይሰማኛል።

"ልቀቁት፣ ሁላታችሁም ልቀቁት!" በኃይለ-ቃል ሴቶቹን አዟቸው ሲለቁኝ፣ "እስቲ መታወቂያህን አሳየኝ!" አለኝ እጁን ዘርግቶ።

ኪሶቼን ደባበስኳቸው። ኢሕአፓ ያዘጋጀልኝን የጋራዥ ሠራተኛና መሪ መካኒክ መሆኔን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ደብተር አውጥቼ ሰጠሁት። ሦስተኛ ደረጃ መንጃ ፈቃዴም አብሮ አለ። 'መሪ ሜካኒክ ሐብል የሚሰርቅበት ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ሊኖረው አይችልም።' እያሰበ ያለው ይሄንን መሆን አለበት ። በመሀሉ ግን የትኛው ታቦት እንደደረሰልኝ አላውቅም ባለ ሐብሏ ሴት፣ "ዉይ ዉይ ዉይ... በሞትኩት...ይቅርታ! ይቅርታ፣ አንተ ልጅ! አገኘሁት...በጡቶቼ መሀል ወድቆ ነው...ዉይ በሞትኩት..." መዛ አወጣችው። ሴትዮዋ ሐፍረት የምትገባበትን ጉድጓድ ሲያሳጣት ተመለከትኩ። ከመቅጽበት የሕዝቡ እርግማን ወደ እሷ ዞረ።

«ደንባራ! ለመፍረድ ምን አስቸኮለሽ? የሰው ሰው ጉሮሮ ዘለሽ ታንቂያለሽ እንዴ? ምኗ ናት ባካችሁ...» ተሳፋሪው ተረባረበባት።

መልሳ አሳዘነችኝ። ደጋግማ ይቅርታ ስትጠይቀኝ፣ «የሚያጋጥም ነገር ነው...አይዞሽ» ብዬ ይሉኝታዬን ላሳያት ሞከርኩ። ተሳፋሪዎቹ ለርሷ ባሳዩኋት ትህትናና በቁጥብነቴ ሳይገረሙ አልቀሩም፣ እንዲያውም አንድ አባት የሚቀጥለው ፌርማታ ከመድረሳችን በፊት ከተቀመጡበት ተነስተው፣ «በእውነት ትልቅ ሰው ነህ! እግዜር ይባርክህ...» ብለውኝ ወደ በሩ አለፉ።

'ሆሆሆ---ው፣ አታጣልፈኝ ነው ነገሩ!' እንደ ነብዩ ዮናስ ከአሳ ነባሪ ሆድ በሕይወት ተርፌ የተተፋሁ ነው የመሰለኝ።

ተሳፋሪዎች ተራ በተራ ቢያበረታቱኝም መረበሹ ግን ቶሎ አለቀቀኝም። ይበልጥ የረበሸኝ ተይዤ ቢሆን ኖሮ የሚለው ሐሳብ ነው። ምንም ጥርጥር የለውም፤ ለእኔም ሆነ ለኢሕአፓ ትልቅ ጥፋት ይሆን ነበር።

አውቶቡስ መነኸሪያ ፌርማታ ሲደርስ ወርጄ በእግሬ ወደ መሳለሚያ ተጠጋሁ። "ምትኩ ፋርማሲ" እና "ኑረዲን ዳቦ ቤት"ን አልፌ ወደ ግራ ታጠፍኩ። ጠባቡን መንገድ ስጨርስ የተከፈተ ትልቅ የብረት በር ታየኝ...

«እዲሱ የትግል ሜዳዬ!» አልኩ በሆዴ።

ወደ ግቢው ስዘልቅ ሐብተጊዮርጊስ ድልድይ ጋ ጥዬው የመጣሁት ቀርፋፋው ኤን-ዱዌ ግቢውን ታኮ ቆሟል። 'በየት በየት አድርጎ ቀደመኝ?'

# 2

መሳለሚያ፣ ሸዋአዲስ ጋራዥ...

ጋራዥ ውስጥ እየሠሩ የመኪና ችግር ተራ ነገር ነው። ሊጋራዥ ሥራ ተቀጥቅጣ መልኳን የለወጠች ላንድሮቨር ሽፍን መኪና ተበረከተልኝ። እኔ ብቻ የምጠቀምባት እንደሆነች ተነግሮኛል። የልጅነት ልምዴ ተጨምሮበት በአጭር ሥልጠና የያዝኩት ሥራ ነው። ከቢሮ ወደ ጋራዥ መውረዴ ቢያስቀኝም ተልእኮ ስለሆነ ከልብ አምኜ ተቀበልኩት።

በእርግጥ ይህ ግቢ የመኪና ብሎን የሚፈታበት ጋራዥ ብቻ አይደለም። የሰው ብሎንም ይፈታል። የኢህአፓ ኮሚቴ የጭንቅላት ብሎን እስኪፈታ ስብሰባ የሚያደርገው ይህን ጋራዥ ተገን አድርጎ በተሠራ መኖርያ ቤት ዉስጥ ነው። የተነፈሰው የአገሪቱ የፖለቲካ ጎማ በከሪከ ተነስቶ ንፋስ የሚሞላውም እዚሁ ጋራዥ ነው። አዲሱ መኖሪያ ቤቴ የኢሕአፓ የፖሊት ቢሮ አባላት በቡድንና በግል ይገናኙበታል። ትንንሽ የኮሚቴ ስብሰባዎችንም ያካሄዱበታል። ለደቂቃም ፋታ የሌለው ቦታ እንደሆነ ተነግሮኛል። በእውነቱ ከሆነ ዉስጥ ዉስጡን በጣም ደስ ብሎኛል። ትርጉም ላለው ዓላማ መኖር መጀመሬ አፍነከነከኝ።

ጋራዥ ውስጥ በቀኝ በኩል ከርቀት ኢሳያስን ዓየሁት። እንደኔው በዘይት የተበለሻሸ ሰማያዊ ቱታ ለብሷል። የፊት ከፍሉ ሽፋን በተከፈተ አነስተኛ መኪና ሞተር ላይ አቀርቅሯል። በዙርያው አምስት ወጣቶች ተመሳሳይ ያደፈ ቱታ ለብሰው ከብብ አድርገውታል። ኢሳያስ የሰው ኮቴ ሲሰማ ወደ መግቢያ በሩ አማተረ። እኔ መሆኔን ሲያውቅ ቀና ብሎ ደማቅ ፈገግታ መገበኝ።

"እ——ው፣ ሰመሬ መጣ!!" እንደሁሌው "ረ"ን በ "ሬ" ገድፎ ጠርቶኝ ወጣቶቹን እየመራ መጥቶ አንገቴ ላይ ጥምጥም አለብኝ።

ከሰላምታ በኋላ ከወጣቶቹ ጋር አስተዋወቀኝ። ሁሉም ሀያ ዓመት ዕድሜ እንኳ ያልደፈኑ ሊጋ ወጣቶች እንደሆኑ ገመትኩ። እኔና ኢሳያስ በስድስት ዓመታት እንበልጣቸዋለን ማለት ነው። ከጋራዥ መደበኛ ሥራና ከተነገራቸው ነገር ውጭ ዝም ጭጭ ነው። ስለእኔ አንድም ነገር ማወቅ የለባቸውም። እኔም ብሆን እንደዚያው።

'እህ...ሕቡዕነት'ኮ ሃይማኖታችን እየሆነ መጣ!' እጨነቃለሁ እንጂ ለድርጅቱ የምሥጢራዊነት ሕግ የምገዛው ከልቤ ነው።

ለደህንነት ሲባል በዚህ ሰዓት ወደተዘጋጀልኝ የኪራይ ምድር ቤት እንድገባ አይደረግም። በዚህ ቤት ውስጥ ስኖር ከሦስት የድርጅት ሰዎች በስተቀር ሌላ ማንም ሰው የድሮ ማንነቴን ሊያውቅ አይገባም። ለአከራዮቹም ቢሆን የጋራዥ መሪ ሜካኒክ ብቻ ነኝ። በቃ፣ ጥንቅቅ ያልኩ ፕሮፌሽናል ሜካኒክ። ልብሴ በበቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ዘወትር አንድ ዓይነት ነው። ከዚህ በኋላ ሁሌም በዘይት የጠቆረ ሰማያዊ ቱታ የቆዳዬ ቀለም እስኪመስል ድረስ አብሮኝ ይኖራል። ተመሳሳይ ቆብ ከጭንቅላቴ ላይ ማንሳትም አይፈቀድልኝም። ዓይኔ ላይ ደግሞ የብዬዳ መነጽር አለ። እጄም ሁሌ በብርሻቶ የጠየመና መፍቻ የማይለየው ነው።

'ሕይወቱ ተልእኮ የሌላት ሰው ምኑን ኖርኩት ይላል!?' የሰሞኑ ቋንቋዬ ይኼው ነው።

ኢሳያስ ወደተዘጋጀልኝ የመሪ ሜካኒክ ሥራ አስኪያጅ ቢሮ ወሰደኝ። ገርበብ ያለውን በር ከፍተነው ስንገባ ላዩ ላይ መዐት ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶች የተከመሩበት ጠረጴዛ ታየኝ። ከጠረጴዛው ጀርባ በግራና በቀኝ በኩል በሰው ቁመት ልክ የተሳሉ የቅድስተማርያምና የኢየሱስ ክርስቶስ ምስሎች በቆርቆሮው ግድግዳ ላይ ግራና ቀኝ ቆመዋል። እንደድሮው ቢሆን በደረቴ ተደፍቼ እጅ እነሳላቸው ነበር። አሁን በዲያሌክቲካዊ ቁሳካልነት የሚያምን ማርክሲስት-ሌኒኒስት (ማሌ) ነኝ። ዝም ብዬ ገባሁ።

ቢሮው በመለዋወጫ እቃዎችና በመፍቻ መሣሪያዎች የተጨናነቀ ክፍል ነው። የማየው ነገር ሁሉ የብረት ቁርጥራጭ፣ የማሸተው ሁሉ ላንባና ዘይት፣ የምሰማው ሁሉ የብረታብረት ቅጭልጭታ ነው።

እንደቆምኩ በበሩ በኩል እንደገና ወደ ዋናው ጋራዥ ተመለከትኩ። ዓይቼው የማላውቀው የመኪና መዓት። ገማው የነፈሰ...እፍንጫው የተገነጠለ... መስታወቱ የረገፈ... ወደ አንድ ጎኑ የተንጋደደ...ትቢያ

እስከ እንጦጦ ድረስ የዋጠው...የመኪና መዐት። የታርጋ ሰሌዳዎችን ቃኘሁ። የግል፣ የመንግሥት፣ የንግድ ድርጅት፣ የግብረሰናይ፣ የዓለምአቀፍ ድርጅት...።ጋራዡ እንደ ኖሕ መርከብ ከየዘሩ አውጣጥቶ ሁሉንም ይዟል። በርከት ያሉ ሞተር ብስክሌቶችም አሉ። ካፒታሊዝም የአርትፊሻል ሐብት አምልኮ አይደል!? እነሆ ጥርሱን አግጦ...አግሩን እንፈራጦ...ቦርጩን ዘርግፎ...ቆሞ አየሁት!

"ስሜሬ፣እዚህ የምንነጋገረው ምንም ዓይነት ድርጅታዊ ጉዳይ ሊኖርም።" ኢሳያስ ሹክ አለኝ።

ወዝበር ላይ አረፍ ስል እሱ ተመልሶ ሄደ። ምን ያህል ጊዜ እንደምቆይበት ባላውቅም የወደፊቱ የሥራ ጽሕፈት ቤቴ ግን ይህ ቢሮ ነው። በትክክል ሕቡእ ገባሁ ማለት ነው። ለነገሩ ድሮም ይሄንን ያህል ነገሬ ብሎ ሰው የሚያውቀኝ ዓይነት ፍጡር አልነበርኩም። የምፈራውም የምጠነቀቀውም ከሦስት አቅጣጫዎች ከሚመጡብኝ ሰዎች ብቻ ነው። የድሮዋ ፍቅረኛዬ ብርክታዊት አዳነ፣ ከድሮው መሥሪያ ቤቴ ሁለት ኢክስፐርቶችና በተለይ የአስተዳደር መመሪያ ኃላፊውና የቀድሞ የዩኒቨርስቲ ጓደኞቼ። ጥንቃቄዬ ትንሽም ከተጓደለ በቀላሉ የሚለዩኝ እነርሱ ናቸው። አሁን "ዓይናቸውን ይሰውርልኝ!" ብሎ ጸሎት አይሠራም። ብልጠትና ጥንቃቄ ብቻ!

ከደቂቃዎች በኋላ ኢሳያስ ተመልሶ ብቅ አለ። ጠረጴዛው ላይ ትልቅ መዝገብ እያመላከተ፣ "ይሄ ዋናው የደንበኞች ቀጠሮ መዝገብ ነው። ስለእያንዳንዱ የሚጠገን መኪና ዝርዝር መረጃ የምታገኘው እዚህ ነው። ቀጠሮ፣ የንብረት ባለቤትነት፣ የብልሽት ዓይነት፣ የጎደሉና የሚገዙ መለዋወጫዎችን ዝርዝር በሙሉ ይነግርሀል።ስለ ሒሳብም በቂ ነገር አለው።" ካለኝ በኋላ መዝገቡን ወደ ፊት ለፊቴ ገፋ አደረገልኝ።

ገለጥ ገለጥ አድርጌ ገጾችን ተመለከትኩ። የሀብታም ባለመኪናዎችና የመኪናዎቻቸው ዓይነት መረጃ ግጥም ብሎበታል። እንዳንዶቹን በዝና አውቃቸዋለሁ። የጅማው ባለጸጋ ከድር ኤባና የሶማሌው የቡና ንግድ ከበርቴ ፈታውራሪ አከሴዴ የሚጠቀሱ ናቸው። እልፎ አልፎም የፈረንጅ ስሞች አጋጥመውኛል። የትምህርትና የማስታወቂያ ሚኒስቴሮች የመስክ መኪናዎችም አሉ። የእርሻ ሚኒስቴር መኪና ይኖር እንደሆን ቃኘሁ። ከአንድ ሞተር ብስክሌት በስተቀር የሚታየኝ የለም።

"እፎ——ይ፣ ግልግል ነው!"

ኢሳያስ ፈገግ ብሎ ርክክቡን ቀጠለ። የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች፣ የጋራዡን ማኅተምና የመጻጻፊያ ሰነዶች፣ የበርና የእያንዳንዱን የሚጠገን መኪና ቁልፍ፣ የብረት ካዝናና ሌሎች ንብረቶችን ወደኔ አስተላለፈ። በሁሉም ነገር የሚያሳየው የጥንቃቄ ደረጃና ጥልቀት አስገረመኝ። ለምን እንደሆነ

አላውቅም ብቻ በውስጤ ድንበር የሌለው ኩራት ተሰማኝ።

"ድንቅ ነው!" አልኩ እንደገና።

ርክክብ ስንጨርስ ኢሳያስ በምሳ ሰዓት እንደሚመለስ ነግሮኝ ሄደ። ያለማቋረጥ ከሚትጎለጎለው የሲጋራው መአጠንት ትንሽ ተንፈስ ስል ተሰማኝ። ያም ሆኖ ኢሳያስን ከነምናምኑ እወደዋለሁ። እሱ ሲለየኝ አእምሮዬ ባገኘው ፋታ ሥራ አልፈታም። የኋሊት ተጉዞ እዚህ ቦታ ያደረሰኝን የነገሮች ሰንሰለት እንደመስታውት ቁልጭ አድርጎ ያሳየኝ ጀመር። እንደሁሌው ኢሳያስን የነገሮች ሁሉ መታጠፊያ በሆነው ፖለቲካዊ ሕይወቴ ቦታ ላይ ቆሞ አገኘሁት።

###

ኢሱ በብዙ ነገሩ የማይረሳ ልጅ ነው። ዐድዋ መዳረሻ እንትጮ የምትባል ትንሽ ከተማ አለች። እዛ ነው የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን የተከታተለው።ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ አሥመራ።

'ወ---ይ ኢ---ሳ--ያ--ስ!' አልኩ ለራሴ።

ኢሳያስ በጣም ብጭጭ ያለ ቀይ፣ ረጅምና በጣም ቀጭን ነው። ረጃጅም ቋንጃዎቹን እጥፍ ዘርጋ እያደረገ ሲሄድ ያሳዝነኛል። በሆነ ትንሽ ስህተት ድንገት ስብር ስብርብር የሚል ሁሉ ይመስለኛል። የእጆቹ ጣቶች ርዝማኔ ሁሌም ይገርመኛል። በቃ፣ የጠፍር አለንጋ። በእኔ እጆች ላይ የማላያቸው ካቦ ገመድ የሚያካክሉ ጅማቶች እሱ እጆች ላይ አሉ። በእነዚህ ጣቶቹ ታዲያ ከሦስት ነገሮች በስተቀር ሌላ ነገር ሲይዝባቸው ዐይቼ አላውቅም። እስክርቢቶ፣ ሲጋራና ብሎን መፍቻ። ሲጋራ ከመጠን በላይ ያጤሳል።

"ኢሳያ-----ስ፣ ወዲ ዐድዋ! የትግሬይቱ ልጅ!" እለዋለሁ በአንዳንድ ያልተለመዱና ደስ በሚሉኝ ባህርያቱ ስገረም።

እኔ በቁመት መካከለኛ ሆኜ ጠይም ነኝ። ከልጅነቴ ጀምሬ ብዙ ሰዎች እናቴን እንደምመስልና መልከ ቀና እንደሆንኩ ይነግሩኛል። ኢሳያስ እንዲህ ዓይነት የአካላት ወሬ አይገባውም። አካል ጠቆረ... ቀላ...ረዘመ...አጠረ...ወፈረ ቀጠነ...ጉዳዩ አይደለም። ሲጋራ የማግኘትና የማጣት ያህል እንኳን አያስጨንቀውም።አማርኛን ለመግባባት ብቻ ስለሚጠቀምበት የዘዬ ልዩነቶችን ብዙም አያውቃቸው። ተረትና ምሳሌ፣ ሰምና ወርቅ፣ ቅኔና ፈሊጥ፣ ሕብርና አሽሙር... አገራቸውን አያውቀውም። ብቻ

ቡልትፍትፍ እያለ ሲናገረው ከአፉ ማር ጠብ ይላል። ድብብቆሽ አይሆንለትም። የሚናገረው በግልጽ ነው። የመጣለትንና መናገር የሚችለውን ሁሉ ዝርግፍ ያደርገዋል። አሁን አሁን ግን የሚገድፋቸው አማርኛ ቃላት እየቀነሱ መጥተዋል። የቀሩትን ደግሞ ጆሮዬ በጣም ስለተለማመዳቸው እንደ መደበኛ ነገር ወስጃቸዋለሁ። እሱ ሲናገር የምረዳው ሙሉ በሙሉ በራሴ አነጋገር ነው።

"ኢታ ሰመሬ፣ የት ነው አገሬ ያልከኝ፣ ጎጃም ነው ጎንደር?"

መቶ ጊዜ ጠይቆኝ መቶ ጊዜ መልሼለታለሁ። ነገር ግን ወዲያው ይረሳዋል። አባቴ የፖሊስ ባልደረባና የመርሰዲስ ጭነት መኪና ሾፌር ነበር። በሥራ ዝውውር ምክንያት ያልረገጠው የኢትዮጵያ ክፍል የለም። ሁኔታው ሲፈቅድ ቤተሰቦቹም አብረነው እንጓዛለን። ጎጃም፣ ደጀን ከተማ መወለዴን አውቃለሁ። ያደኩበትን ቦታ ግን በትክክል መናገር ያስቸግረኛል። ያልተጓዝኩበት የወሎና የጎጃም መሬት የለም። ቤተሰቦቼ አሁን ደሴ ኩታ በር በምትባል ከተማ ይኖራሉ።

ይሄንኑ ደጋግሜ ነግሬዋለሁ። አንድ የተወሰነ ቦታ ስላልጠራሁለት ነው መሰለኝ ወዲያው ይረሳዋል። ከኢሳያስ ጋር መጀመሪያ የተዋወቅነው ከአራት ዓመታት በፊት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሆነን ነው። እሱ የምህንድስና ተማሪ ነበር። የንጉሡን አገዛዝ በመቃወም አብረን ሰልፍ ወጣን። ወቅቱ የአጼው መንግሥት ጨካኝ የሆነበት ጊዜ ነበር። ሁለታችንም በፖሊስ ጥይት ቆሰልን።

እሱ በርከክ በርከክ መትረየስ ደገኑ

አውሬ መሰያቸው፣

የሰው ልጅ መሆኔን ማን በነገራቸው፣

ይህ የተዘመረበት ጊዜ መሆኑ ነው። እኔ ሚጢጢቴ ላይ፣ እሱ ደግሞ ግራ ጭኑን ተመታ። የካቲት 12 ሆስፒታል ገብተን ስንታከም ተገናኘን። ከዚያማ ፖለቲካን 24 ሰዓት ሙሉ እንደ ሲጃራ ማጨስ። አንድ ወር ያህል ታክመን ስንወጣ ለካንስ መለያየት የማንችል የልብ ጓደኞች ሆነናል።ከዚያ በኋላ በተደጋጋሚ እንገናኛለን። ስንለያይ እንደገና እስከምንገናኝ ድረስ እንዴት እንደምንነፋፈቅ ይገርመኛል። የአገሬ ሰው "መወለድ ቋንቋ ነው" የሚለው እውነቱን ነው። ከጊዜ ጊዜ ልቦቻችን ተዋሀዱ። እሱ ሦስት ዓመት ስለሚማር እኔ ቀድሜው ተመርቄ ወጥቼ ሥራ ያዝኩ። አሁን የለቀኩትን ቤት ፈረንሳይ ...ደጅ መኖር የጀመርኩትም ያን ጊዜ ነበር።

ንጉሡ ወርደው ደርግ በጊዜያዊነት በተተካበት ቀን አብረን ዋልን። በዚህ ጊዜ ለካ እሱ ኢሕአፓን ተቀላቅሏል። በንግግሩ የፖለቲካ ብስለቱ ሲጨምር ታወቀኝ። ኾኖም የእኔን ያህል ርእዮተ-ዓለማዊ ጉዳዮችን ማስተንተን ይቸግረዋል። ማንበብም ላይ የእኔን ያህል ፍጥነት የለውም። ቀስስተኛ አንባቢ ነው። ፍልንትና ብሩህ ጭንቅላት ግን ሰጥቶታል። የተነገረውን ሁሉ በመልከ በመልከ አደራጅቶ ቀብ ያደርገዋል። ከዚያማ አልም አድርጎ ያላምጠዋል። መልሰን ስንነጋገርበት ታዲያ በደንብ እንግባባለን።

በተለይ እሱን በሚቸግረው የፖለቲካል ኢኮኖሚ መስክ እኔ ብዙ የተራመድኩ ይመስለኛል። ከማንበብም አልፌ መጻፍም ጀማምሬያለሁ። ይህንን ሲመለከት የበለጠ አየፈለገኝ፣ አየቀረበኝ፣ አያከበረኝ...መጣ። ጧትና ማታ መጻሕፍት ማገላበጥ ሥራችን ሆነ። አያነበቡ በቀይ እስከርቢቶ ማስመር...ማስታወሻ መያዝ...እልባት ማጠፍ።

ደርግ በመጣ በሳምንታት ውስጥ አንድ አስቸጋሪ ጥያቄ አነሳልኝ።

"ሰመሬ፣ አሁን የተፈጠረውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ፣ በተለይ፣ የደርግን መምጣትና የወደፊት ጉዞውን እንዴት ታየዋለህ?" በእንከሮ ዓይን ዓይኖቼን እየተመለከተ ጠየቀኝ።

ለዚህ ጥያቄ የሰጠሁት መልስ ወደሌላ ጉዳይ መራው። ለካንስ እየመለመለኝ ነበር። በዚያው ሳምንት ኢሕአፓን እንድቀላቀል ጠየቀኝ። ፈቃደኝነቴን የነገርኩት ያለምንም ማንገራገር ነበር። ይህ ወደ ኢሕአፓና በኢሕአፓ መዋቅር ውስጥ የተጓዝኩበትን ፈጣን መንገድ ከፈተው። በዚህ ጀምሬ ረጅሙን የማራቶን ሩጫ ተያያዝኩት። ከዚያማ ማን ይቻለኝ! በተለይ ጠጣር የርእዮተ-ዓለምና የፖለቲካ ንድፈ-ሐሳቦችን በማብራራት በኩል ብዙ ተራመድኩ። እኔ እጽፋለሁ፣ ብርከቲ ትተይበዋለች፣ ኢሳያስ ይወስደዋል...። ብርኪታዊት ታዲያ አንድም ቀን "ምንድነው? ለማን ነው?" ብላ ጠይቃኝ አታውቅም።

አንድ ዕለት ሥራዬ እንደተዋጣልኝ ዶክተር ተስፋዬ ጠቆም አደረገኝ...

"ቢፓርቲ አመሠራረትና በመደቦች አሰላለፍ ለውጥ መስተጋብር ላይ የጻፍከው ማብራሪያ ደርሶናል። በቂ ውይይት አድርገንበታል። አያያዝህና የፖለቲካ ብስለትህ ይበል የሚያሰኝ ነው!" ሲለኝ ለከፍተኛ ሥራ እየታጨሁ እንደነበር ማመን ሆንኩ።

***

ሁሉም ሠራተኞች ጥርግርግ ብለው ለምሳ ሲወጡ ጋራዡ እንደመቃብር በአርምሞ ተዋጠ። ቦታውን

ለሕቡእ ድርጅታዊ ሥራ ያስመረጠው ምሥጢር አሁን የበለጠ ጎልቶ ታየኝ። ወዲያው ኢሳያስ መጣ. . .

"ስመሬ፣ ተነስ! የምሠራውን በደንብ ተመልከት!" ብሎኝ መልሴን ሳይጠብቅ የቢሮውን በር ከዘጋ በኋላ ተመልሶ መጣ።

ከክርስቶስ ምስል በቀኝ በኩል ቋሚውንና ማገሩን እንጨት አያይዞ የተቋጠረች የኤሌክትሪክ ገመድ ፈታና ገመዱን ኪሱ ውስጥ አስገባው። ከዚያ የምስሉን የቀኝ መወጠሪያ እንጨት ይዞ ወደራሱ ሳብ አደረገው።ረዥሙ ምስል ድንገት በር ሆኖ ቦግ ብሎ ተከፈተ። ከምሥሉ ጀርባ በር ይኖራል ብዬ ፈጽሞ አልጠረጠርኩም። ምትሀት የሠራብኝ መስሎ ታየኝ። ተያይዘን በበሩ ከወጣን በኋላ መልሶ በሩን ዘጋው። እንጨቶቹን በዚያው ገመድ መልሶ አሠራቸው። በሩ ተመልሶ ሥዕል የተሠቀለበት ግድግዳ ሆነ።

'ያለ ጥርጥር ወደ ሌላ ዓለም እየገባሁ ነው!' አልኩት ራሴን በሆዴ።

ትክክል ነኝ። እንደወጣን ከፊት ለፊታችን በግምት አምስት ሜትር ርቀት ላይ የቆመ ትልቅ ቀይ የብረት በር አለ። ቀዩ በር የትልቅ መኖሪያ ግቢ የጀርባ በር ነው። የጸጥታው ጥልቀት የተለየ ነው። በሩ ከጥፋት ውኃ ወዲህ ተከፍቶ የሚያውቅ አይመስልም። አንድ የተለየ ነገር ቢኖር ግቢው ውስጥ ውሻ ሲያላዝን ይሰማኛል። በቀኝ በኩል ምንም ዓይነት የሰውም ይሁን የመኪና መንገድ የለም። ባለቤቶቹ ለምን በር እንዳቆሙ ግራ ገባኝ። ወደ በሩ ጠጋ ብሎ አንኳኳ። አከራይዋን ሊያስተዋውቀኝ መሆኑ ገባኝ። ስማቸውን በጋራዡ መዝገብ ላይ አግኝቼዋለሁ። ወይዘሮ ማስተዋል ግዛቸው ይባላሉ። ኢሳያስ ደጋግሞ አንኳኳ...

"ወ---ይ ጉ----ድ!" እላለሁ እኔ በየመሀሉ።

ከግቢው ውስጥ እየቀረበ የሚመጣ ኮቴ ተሰማን። ወዲያው ደስ የሚል ታዳጊ ልጅ ብቅ አለ። ኢሳያስ፣ "ሚካኤለ፣ እንደምን ነህ?" ብሎት ጎንበስ ብሎ ጉንጮቹን ሳመው። እኔም ተዋውቄው ግንባሩ ላይ ሳምኩት። ተያይዘን ገባን። በረጅም የሲሚንቶና የብረት ግንብ አጥር የተከለለ ትልቅ ቪላ ቤት ግቢ ነው። በሸቦ ቤት ውስጥ የታሰረ ነብር የሚያክል ውሻ ሲጮህ ምድሩን ስንጥቅ ያደርገዋል። አሁን እኔ እንግዳ ስለሆንኩበት መሰለኝ እኔ ላይ አተኩሮ ነው የሚጮኸው።

"ተ---ው፣ ዳግላ---ስ!" ብሎ ኢሳያስ ሲቆጣው ውሻው በረድ እያለ አጉረመረመ።

ሚካኤለ እየመራ ወስዶ በቤታቸው የጀርባ በር በኩል አስገባን። ዓይን የሚስብ ልእልታዊ አልፍኝ

የመሰለ ሳሎን ቤት ተቀበለን። ታዳጊው ሚካኤል እናቱን ሊጠራ ይመስለኛል ወደ ሌላ ክፍል ሄዶ ገባ። ወንበር ላይ ቁጭ ብለን ስንጠብቃቸው የአፍታ ጊዜ አገኘን። ዓይኔ ሥራ አልፈታም። ከቤቱ የግራ መስኮት በኩል በትልቅ ፍሬም ውስጥ የተሰቀለ ፎቶ አለ። ዕንቁ የመሰለች የቆንጆ ሴት ፎቶግራፍ። የብርኪታዊት ሐሳብና ትዝታ ከንፍ አውጥቶ እየበረረ መጣብኝ። ፎቶውን በቅሬታ ተውጬ እተኩሬ መረመርኩት...

'ምን ዓይነት ቁንጅና ነው፣ ባካችሁ!' አልኩ በልቤ እንደገና።

ባለ ፎቶዋ እውነትም አቻ የሌላት ቆንጆ ናት። ምስሏ ኪነጥበባዊ መልእክት ያለው ይመስላል። ፈገግ ልትል ፈልጋለች፤ ነገር ግን አልገፋችበትም። አዲስ የመውዜር ጥይት የመሰሉ የፊት ጥርሶቿን ብልጭ አድርጋ ባሉበት ትታቸዋለች። ስሜቷ በትክክል ምን እንደነበረ ለመገመት አስቸጋሪ ነው። ሁኔታዋ የሞናሊዛ ስሜት ዓይነት ውዝግብ ይጋብዛል። ከፍቷታል ሲባል ፈገግ ብላለች። ተደስታለች ሲባል አልሳቀችም። ጭል ጭል የምትል ፈገግታዋም የአንገት ትሁን የአንጀት ማወቅ አይቻልም። የቸገረ ነገር...

"ኢሱ፣ እንዲህ ዓይነት ቁንጅና አጋጥሞህ ያውቃል? ምናቸው ናት ባከህ?" በሹክሹክታ ጠየኩት።

"ልጃቸው ናት። ቢታኒያ ትባላለች..." ሲለኝ ወይዘሮ ማስተዋል የነበሩበትን ክፍል በር ከፍተውት ብቅ አሉ። ረዘም፣ ሞላና ነቃ ያሉ ጠይምና ዘንካታ የሴት ወይዘሮ። ንጣቱ ዓይን የሚያጥበረብር ነጭ ጥበብ ቀሚስ ለብሰዋል። ጸጉራቸው በጥቁር ሻሽ ግጥም ተደርጎ ታስሯል። ጸጉራቸው በከፊል በሽበት የተወረረ መሆኑ በግንባራቸው በኩል አፈትልከው በወጡ ዘለላዎች ይታወቃል። የእጆቻቸው ጀርባና ድፍን አንገታቸው በንቅሳት ተዥጎርጉሯል።

"ደህና ዋላችሁ፣ ልጆቼ?" እንከን የሌለበት እናታዊ ድምጻቸው ሲመጣ ቆመን ተቀበልናቸው።

እጆቻችንን ጨብጠው ሲያበቁ ሶፋ ላይ ተቀመጡ። ግርማ ሞገሳቸው እንደ ቤተመቅደስ መንፈስ ይጫጫናል። የፊታቸው አንዳንድ ክፍሎች ፎቶዋን ካየሁት ውብ ልጃቸው ጋር ይመሳሰላሉ። ምግብ ካልበላችሁ ብለው ያዙን። ሁላታችንም በልተናል ብለን እምቢ አልናቸው። ኢሳያስ ይብላ አይብላ አላውቅም። የእኔው እምቢታ ግን መግደርደር ነው።

'ኧረ እናቴ ምግቡን ትተው ይህችን የገነት ተክል ልጅዎን ያስተዋውቁን፣ በፈጠረዎ ጌታ ይዤዎታለሁ...' በልቤ ተማጸንኳቸው።

ምግቡን እምቢ ስንላቸው እንደገና ተረጋግተው ተቀመጡ። ኢሳያስ ስሜንና የሜካኒከነት ደረጃዬን ነግሯቸው ተዋወቅን። የጋራዡን የየቀኑን ሒሳብ 60 ከመቶ እጅ ለእሳቸው ቆጥሬና አስፈርሜ እስረክባለሁ። በአጋጣሚ እሳቸው ከሌሉ ለሴቷ ልጃቸው ቢታኒያ። የሆነ ልብ የሚያንጠለጥል ነፋስ ነገር ሽው አለብኝ። ብርከታዊትን ተሰውሬ መምጣቴ የፈጠረብኝ የውስጥ ባዶነትና ቅናት የፈጠረው ንፋስ ሊሆን ይችላል።

በቀኝ በኩል ገርበብ ብሎ ወደተከፈተው መስኮት ዘወር ስል ያልጠበኩት ሰው ያየሁ መሰለኝ። ፍቅሬ ዘርጋው! ፈጠን ፈጠን ብሎ ወደ ዋናው የፊት ለፊት በር ሄደ። ወደ ኢሳያስ ዞር ስል ያየሁትን ችላ እንድለው በዓይኖቹ ምልከት ሰጠኝ...

'ፍቅሬ ዘርጋው! የኢሕአፓ ከተማ ታጣቂ ከንፍ የአዲስ አበባ በይነቀጣና ኮማንደር... እዚህ ግቢ እንዴት ብሎ ተገኘ?'

ትውውቁን ጨርሰን ተያይዘን ወጣን...

# 3

በግምት መቶ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ከጋራዡ ጀርባ በረጅም አድሞ የታጠረ መስጊድ ይታየኛል። ቢላል መስጊድ። ጎድጓዳማውን ቦታ ወደ ግራ ትተን ጠባብ መተላለፊያ መንገድ ይዘን ሄድን። የአይጥ ጅራት የመሰለች ቀጭን የእግር መንገድ። እሷን ስንጨርስ አጭርና ትንሽ ዳገት ወጣን።

'የት ነው የሚወስደኝ?' ግራ ገባኝ።

ለዘመናት ካልተነሳ አፍንጫ ቆርጦ ከሚጥል የቆሻሻ ክምር ደረስን። ሦስት አጽማቸው ብቻ የቀረ የመኪና ቅሪቶች ከፊት ለፊታችን አሉ። ከጀርባቸው ለማንም ሊከሰት የማይችል ከድንጋይ የተገነባ የጥንት ካብ ቤት ብቅ አለ።ከእኛ በግራ በኩል የቆሻሻ ክምር...ከፊት ለፊት የመኪና ቅሪቶች...በቀኝ በኩል ኩታ ገጠሙ የቀዩ በር መኖሪያ ቤት ግቢ...ከጀርባ ጋራዥና ቢላል መስጊድ...የከበቡት ቤት። ከየትም አቅጣጫ ከሩቅ ፈጽሞ ሊታይ አይችልም። በሩ ከወፍራም ጣውላ የተሠራ ባለአንድ ገጽ መዝጊያ ነው። የሰውም ይሁን የእንስሳት ዘር አይታየኝም፣ ድምጽም አይሰማኝም። ኢሳያስ ሁለቴ ኳ ኳ አደረገ። ከሴኮንዶች በኋላ እንደገና አንዴ ኳ አደረገው፤ ኮድ መሆኑ ገብቶኛል።

"አንተ ስታንኳኳ አንድ ጨምረህ አራት ታደርገዋለህ። ሦስት በፍጥነት...አራተኛውን ዘግይት ብለህ፤ ይሄ ነው ኮድህ።" አለኝ በለሆሳስ።

በልቤ መዝግቤ ጭንቅላቴን በአዎንታ አወዛወዝኩለት። ጥቂት ቆይቶ ጣውላው በር ከውስጥ በቀስታ ተከፈተ። ሰማያዊ ካኪ ካፖርት ያጠለቀች ግዙፍ ሴት ብቅ አለች። ካፖርቱ ሥር ቀላ ያለ ቀሚስ ለብሳለች። ጸጉሯን በጥቁር ሻሽ ሸፍናዋለች። ጠይም ፊቷ በማድያት ተዥጎርጉሯል። ጡቶቿ በጣም

ከመግዘፋቸው የተነሳ ከበሮ ያክላሉ። ከውጭ ሆኜ ሳያት ገደል እከላ ታየችኝ። ዕድሜዋ በግምት ሠላሳ አምስት ይሆናል። እኔን በአንክሮ ዓይታኝ ያልተሰማኝ የሆነ ነገር ለኢሳያስ ተናገረች። እልፊናት ስንገባ በሩን ፈጠን ብላ ከጀርባዬ ዘጋችው።

"ጓድ አላምረው ይባላል። ትላንት ይመጣል ያልኩሽ እንግዳችን ነው።" አስተዋወቀኝ፤እጅ ለእጅ ስንጨባበጥ።

"እህህህ..." ብላ ማስታወሷን ለመግለጽ፤"ሽዋዬ እባላለሁ። እንኳን ደህና መጣህ!" የተመጠነ ፈገግታ አሳየችኝ።

ኢሳያስ ለወጉ ያስተዋውቀን እንጅ ስለ ሽዋዬ ቀደም ብሎ ነግሮኛል። የኢሕአፓ የፖለቲካ ኮሚቴ እንደዓይን ብሌን የሚመለከታት ፕሮፌሽናል ጋዜጠኛና አርታኢ ናት። የኢሕአፓ ዋነኛዋ ጋዜጣ ዲሞክራሲያ የመጀመሪያወቹ ቅጅዎች በእሷ የተተየቡ ናቸው። ጋዜጣዋ በአዲስ መልክ ተደራጅታ የሥራ አመራር ቦርድ ተረከባት። ያኔ የዝግጅት ቦታዋ ተቀየረ። ይሁንና እንደምታነሳው አጀንዳና እንዲያነባት እንደሚፈለገው የሕብረተሰብ ክፍል ዓይነት እየታየ አንዳንዴ እዚሁ ቦታም ትዘጋጃለች። በተለይ በርእዮተ-ዓለም ጉዳይ ላይ ስታተኩር ዲሞክራሲያ ወደ እኔ ትመጣለች። ሽዋዬ ከዚህ በተጨማሪ ሌላም ሥራ አላት። እዚህ የምትኖረው በምግብ አብሳይነት ሽፋን ነው።

"ደጀኔ አለ?" ኢሳያስ ሌላ ጥያቄ አነሳለት።

"አለ፤ ሦስተኛው ክፍል ታገኘዋለህ።" በእጇ ወደ ክፍሉ አቅጣጫ አመላከተችው።

ሽዋዬ ወደ ቀኝ እጥፍ ብላ እዛው የነበረ መጋረጃ ከፍታ ገባች። እኛ ፊትና ኋላ ሆነን ሄደን በግራ በኩል ወደ አንድ ክፍል ገባን። ጽድት ያለና በዋና ዋና የቤት እቃዎች የተሞላ ክፍል ነው። የራሱ የኢሳያስ መኖሪያ ክፍል እንደሆነ በአልባሳቱና በጫማዎቹ ወዲያው አውቄዋለሁ። እሱንም አልፈን በሩ በመጋረጃ የተከለለ ሌላ ክፍል ውስጥ ገባን። ደብዘዝ ከማለቱ የተነሳ ውስጡ በደንብ አይታይም። ኢሳያስ እጁን ሰደድ አድርጎ መብራት ሲያበራና የወንድ ድምጽ ስሙን ሲጠራው አንድ ሆነ።

"ኢሳ----ያስ!" ተብሎ ሲጠራ ሳጥናኤል አድፍጦ የጠበቀን ያህል በጎርናናው ድምጹ ደንገጥ አልኩ።

መብራቱ ሲበራ አልጋ ላይ ጋደም ያለ ሰው ታየኝ። መጽሐፍ እያነበበ ነበር። ከላይ ነጭ ኬኔትራ ብቻ ለብሷል። ያፈረጠመና ጥቁረቱ ከሰል የመሰለ ጡንቻው ቀድሞ ዓይኔ ውስጥ ገባ። በእካል እንቅስቃሴ

የዳበሩት ጡንቻዎቹ ዕይታ ይስባሉ። ጸጉሩ እንድ ሁለት ተብሎ ሊቆጠር የሚችል ያህል ከርዳዳ ነው። ፈጠን ብሎ ከተጋደመበት ተነሳ።

"እንግዳው ደርሷል!"በትህትና የእጅ ሰላምታ ሰጥቶኝ፣ "ደጀኔ እባላለሁ!" አለኝ፣ የድርጅት ስሜን ነገርኩት።

ደጀኔ፣ ወዝ የሚረጨው ሞላና ልስልስ ያለ የፊቱ ቆዳ ማቅ ይመስላል። ፈገግ ሲል እጭ የመሰሉት ነጫጭ ጥርሶቹ የውትት አረፋ መስለው ብልጭልጭ አሉ። ሲያነበው የነበረውን መጽሐፍ ሽፋኑን ገልመጥ ብዬ አየሁት።"የቬትናም አብዮትና ጸረ-ኢምፔሪያሊስት ተጋድሎው"። በሕዝብ መሀል ሆኖ ለሚደረግ የተራዘመ ሽምቅ ውጊያ ማገናዘቢያ ጽሑፍ ነው። እንደ ፍቅር ደብዳቤ ደጋግሜ እንብቤዋለሁ። የደጀኔን ከፍል አለፍን። ስለ ሁኔታው አንድ ነገር ከመገመቴ በፊት ኢሳያስ ወደ ጆሮዬ ጠጋ አለ...

"ደጀኔ ማለት ድርጅታችን ከሚተማመንባቸው የወደፊቱ ምርጥ ወታደራዊ አዛገቻችን መካከል የመጀመሪያው ነው።"

ከፖለቲካ ከፍሉ ሥራ ጋር የሚያገናኘው ነገር ምን እንደሆነ ቀስ ብዬ ጠየኩት።

"በሥራ ከ'ኛ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የለውም። እዚህ የሚኖረዉ አንድም ሕቡእ ስለገባ ነው። የአየር ወለድ አዛዥ የነበረው የኮሌኔል ዓለምዘውድ ተሰማ 'ጋርድ' ነበር። ኮሎኔሉ ሲገደል ወደዚህ መጥቶ ተሰወረ። ሁለተኛም ለፖለቲካ ቢሮውና ለፖለቲካ ኮሚቴው ወታደራዊ ጥበቃ ያደርጋል። በድርጅት ጉዳይ ግን ተጠሪነታችን ለተለያዩ ከፍሎች ነው።ከአንተ ጋር የምትነጋገሩት ነገር የለም..." ኢሳያስ ከትላንትና ወዲያ እንደዘበት የነገረኝን ነገር አሁን በቁምነገር ጠበቅ አድርጎ አስጠነቀቀኝ።

የፖለቲካ ከፍሉ ተጠሪነቱ ለተሰፋዬ ደበሳይ ሲሆን ወታደራዊ ከንፉ ደግሞ ለዘርዐ ከህሽን ነው።ወዲያው ኢሳያስ ቢጫ የቁመት ልክ መጋረጃ ገለጥ አደረገ። ከግድግዳው ጋር የሚመሳሰል ጥቁር ጣውላ በር ብቅ አለ። በሰረገላ ቁልፍ ከርችም ተደርጎ ተዘግቷል። ቁልፍ አስገብቶ ሲከፍተው ተያይዘን ገባን። ደረጃዎች ስንወርድ አነስ ያለ የምድር ውስጥ እልፍኝ ዋጥ አደረገን።

"ኢሱ፣ ወደ ግብጽ ፒራሚዶች መቃብር ቤት ነው እንዴ ያስገባኸኝ?" ፈገግ ብዬ በቀልድ ጠየኩት።

"የምን መቃብር አመጣህ? ከዚህ በኋላ የሌሊት ቢሮህም መኖሪያህም እዚህ ነው። ሕቡእ ለገባ ሰው ይሄ ቤተመንግሥት የገባ ያህል የሚመቸው ይመስለኛል።" ብሎኝ ወደ አዳራሹ መሀል እየመራኝ ገባን።

ዓይኖቼ ቀስ በቀስ ደብዛዛውን ብርሀን ሲለማመዱት አካባቢውን ልክ እንግዳ ዶሮ መስዬ ለመቃኘት ሞከርኩ። ቤቱ በአብዛኛው አና ነው። ልዩነት የታዘብኩት በቀኝ ማእዘኑ ጫፍ ላይ ተገጣጥመው የቆሙ ግዙፍ የቁም ሳጥኖችን ስመለከት ነው። ራሳቸው ትንንሽ ቤት የሚያከሉ የመሀንኒ ቁምሳጥኖች ናቸው። ከግራ ወደ ቀኝ እስከ መሀል ወለሉ ተጠጋግተው ተገጥግጠዋል። ከጀርባቸው እንድ ወፍራም የድርጅቴ ምሥጢር እንደሚኖር አልተጠራጠርኩም። ሄደን በጀርባቸው በኩል ገባን። ትክክል ነበርኩ። አራት አነስተኛ ታጣፊ የብረት ወንበሮች ከግድግዳው በተቃራኒ መደዳውን ተደርድረዋል። ከፊት ለፊታቸው በትንንሽ ጠረጴዛዎች ላይ የሙተየቢያ መሣሪያዎች ተቀምጠዋል። ወለሉ ላይ እዚህም እዚያው የወደቁ የብረት ቁርጥራጮች ይታዩኛል።

"ኢሱ፣ እውነት እሁን ያለነው በዛ የቆሻሻ ተራራ ሥር ባለ ምድር ቤት ውስጥ ነው? ለመሆኑ ምን ይሠራበት የነበረ ምሽግ ነው?" እንደ ሞኝ ፍዝዝ ብዬ እያየሁ ጠየኩት።

"አዎ፣ በዚህ በቀኝ በኩልና ወደ ላይ የቆሻሻው ክምር አለ። በዚህ በግራ በኩል የምታየው የድንጋይ ግድግዳ ደግሞ የአከራዖችን መኖሪያ ግቢ ግድግዳ ነው። ያ ቅድም ያየኸው የቀዩ በር ግቢ ማለቴ ነው። ግቢው ውስጥ ሆነህ ቆሻሻውን ስታየው ግን ሳር የለበሰ ኮረብታ ነው።ቢቃ፣ ሌላ ምንም ነገር አታይም። ከቆሻሻው አልፎ ልክ መኮንን ድልድይ የሚያቋርጠውን ወንዝ የሚመስል ሽጥ አለ። ገደል ነገር ነው። ድሮ የወይዘሮ ማስተዋል ጋራዥ እዚህ ነው የነበረው። ቦታ ገዝተው ወደ ጀርባ ሲሄዱ ባዶውን ቀረ።" በእጆቹ የአቅጣጫ ምልከት እያሳየ ሲነግረኝ በመጠኑ ገባኝ።

ወይዘሮ ማስተዋል ከኢሕአፓ ጋር የተገናኙበት መስመር ምን እንደሆነ መገመት አልቻልኩም። ኢሳያስም በትክክል የሚያውቅ አይመስለኝም። ልጠይቀውም አልፈለኩም። የውስጥ ጉብኝቴን ቀጠልኩ...

በግራ በኩል በኢሕአፓ የተለመደ አጠራር "አደፍርስ" የሚባለው የማተሚያና ማባዣመሣሪያ በትልቅ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጧል። ቀላል የእጅ ማተሚያ ነው። በዝርግ ጣውላ ላይ ናይለን ጨርቅ ተወጥሯል። ጨርቁ ላይ ቀለም ይፈስበታል። ከቀለሙ ላይ ስቴንስል ይለጠፋል። የሚባዛው ወረቀት ስቴንስሉ ላይ ይቀመጣል። ባዶ ወረቀት በናይለን ጨርቁ ላይ ተስተካክሎ ከተቀመጠ በኋላ ይዘጋል። ያኔ አርጅናሉን በቀላሉ ይቀዳዋል።ዲሞክራሲያ ጋዜጣ በዚህ መንገድ ነው የምትታተመውና የምትባዛው። ለምን "አደፍርስ" እንደተባለ ግን አላውቅም።

ከእሱ ጀርባ የእኔ እቃዎች አሉ። ሁሉም እቃዎቼ መልክ መልክ ይዘው ተቀምጠዋል። ሽቦ አልጋዬም ተነጥጥፎ ተዘጋጅቶልኛል። ጠረጴዛዬና ወንበሮቼም እንዲሁ። ቁምሳጥኖቹ የፊት ለፊት መዝጊያ ብቻ የተገጠመላቸው መስሎኝ ነበር። አሁን ሳይ ግን ከጀርባም በዓይን ለመለየት የሚያስቸግር በር አላቸው። ኢሳያስ በቁልፍ እየከፈተ ውስጣቸውን አሳየኝ። ኢሕአፓ በ1964 ዓ.ም ገና ኢሕአድ ተብሎ ሲቋቋም

ጀምሮ የተመረቱ ሰነዶቹ በሙሉ እዚህ ናቸው።

"ጉ-----ድ ነው!!" አልኩ ሳይታወቀኝ።

ኢሳያስ መልስ ሳይሰጠኝ ማስጎብኘቱን ቀጠለ። በአንዱ ቁምሳጥን የታችኛው ምሥጢራዊ ኪሶች ውስጥ ደግሞ ለየት ያሉ እቃዎች ተቀምጠዋል። ፊሊፕስ የቴፕና ሸከላ ማጫወቻወች፣ የቴፕ ከሮች፣ ፎቶ ካሜራዎችና ፊልሞች ተከማችተዋል። ወደሚቀጥለው ቁምሳጥን አለፍን። እዚህም የእቃዎች ክምችት ጠበቀን። የቀለም ቆርቆሮዎች፣ የታይፕ ማሽን ቀለሞችና መለዋወጫወች፣ የተሠራባቸውና ያልተሠራባቸው ስቴንስል የጽሑፍ ማባዣዎች...። ሌሎቹም እንዲሁ በአንድ ወይም በሌላ ዓይነት የጽሕፈት መሣሪያዎች ስብስብ የተሞሉ ናቸው። የሆነ ዓይነት የቀለም ሽታ አፍንጫዬን ቆርጦ ሊጥለው ተፈታተነኝ።

"ኢሱ፣ በጣም ይገርማል!" አልኩት የሚያሳየኝን ነገር ሁሉ በግርምት እየተመለከትኩ።

"ሰመሬ፣ አንድ ነገር ልብ በል!" አለኝ፣ ዘና ብሎ ቁልቁል ዓይን አይኖቼን እየተመለከተ፣ "እነዚህ በሙሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸው። የኢሕአፓ ዋናው የደምስር ያለው ግን በማቀፊያ ተደርገው በተያዙት ሰነዶቹ ላይ ነው። ይሄንን ለአፍታም ቢሆን እንዳትረሳ። እነዚህ ሰነዶች ጠፉ ማለት ኢሕአፓ ዓይኖቹን አጣ ማለት ነው። የሚጓዝበት መንገድ የሌለው ወይም የጨለመበት ድርጅት ሆነ ማለት ነው።" የቀኝ እጁን ሌባ ጣት ወደ እኔ ቀስሮ እያወዛወዘ የምሩን አስጠነቀቀኝ።

ፈርጠም ብዬ ሊታየው ሞከርኩ። ሆዴ ግን የተሸከምኩት ኃላፊነት ከመርግ የከበደ መሆኑን ይነግረኝ ነበር። በትክክል እንደምወጣው ራሴን ማሳመን ቀጠልኩ። አንድ ስንቅር ያለብኝ ጥያቄ ቢኖር የደህንነት ጉዳይ ነው። ኢሳያስን አነሳሁለት...

"በደህንነት ጉዳይ ሐሳብ አይግባህ። ደጆኔ ቁጥር አንድ ሥራው ይሄ ነው። ምናልባት ከእሱ አቅም በላይ ከሆነ ደግሞ ሌላ መፍትሄ አለ። ቅድም ጋራዥ ውስጥ ያየሃቸው ወጣቶች በሙሉ የከተማ ታጣቂ ክፍሉ ኮማንዶዎች ናቸው። ሕዳር ላይ በተደረሰው ስምምነት ከኤርትራ የመጡ ፈዳዩኖች (አድፍጦ ገዳዩች) አሉን። በሽጉጥ ጥይት የምትበር ጭልፊት ከሰማይ ያወርዳሉ። ያ በኤን-ዱዌው ይዞህ የመጣው ልጅ ኀይቶም ለባሲ ይባላል። ጠርናፊያቸው እሱ ነው...የሁላችንም አለቃ..." አለኝ በቀልድ እየሳቀ ተመልሰን ወደገባንበት በር መሄድ ስንጀምር።

"ጎ---ሽ!" ለምን እንዳልኩ ለጊዜው እርግጠኛ ሆኜ የማውቀው ነገር የለም። 'ያ አንድ ፍሬ ልጅ ነው ኀይቶም ለባሲ ማለት?'

ኢሳያስ የሰጠኝ መረጃ በደረጃዬ ላውቀው የሚገባ ይሁን ወይም በጓደኝነት አላውቅም። ብቻ

የሚጠረጥረውን ነገር ዝርግፍ አደረገልኝ። መውጫው በር ከመድረሳችን በፊት ወደ ግራ አቅጣጫ መራኝ። የምድር ቤቱ የቀኝ ማእዘን መሆኑ ነው። በርከክ ብሎ ማእዘኑ ሥር የሆነ የተለየ ቦታ አመለከተኝ። በርከክ ብዬ አስተዋልኩት። አራት ማእዘኖች ያሉትና መስኮት የመሰለ ቅርጽ ያለው ነገር ነው። ነጣ ነጣ ባሉ ድንጋዮች ምልክት ተደርጎበታል። በደንብ ካላተኮሩበት ምንነቱ አይታወቅም።

"ኢሱ፣ ይሄ ምንድነው?" በድንጋይ መስኮቱ ላይ እንዳቀረቀርኩ ጠየኩት።

"ስመሬ፣ ሁሉም የደህንነት ጥበቃ ጥረት ተደርጎ ከዐቅም በላይ ከሆነ ይሄ የአደጋ ጊዜ መውጫህ ነው። መጀመሪያ ሰነዶቹን ታስወጣለህ። ከዚያ አንተ ትወጣለህ። ሰነድ ሳታወጣ አንተ መውጣት አትችልም። ልክ እንደወጣህ የሚጠብቅህ ኩሽና ቤት ነው። ቅድም ወዳሳየውህ ባለቀይ በር የአከራያችን መኖሪያ ግቢ ገባህ ማለት ነው። እንደሁኔታው በቀዩ በር በኩል ወይም በዋናውና በግራ በኩል ባለው በራቸው በኩል ወጥተህ ትሰወራለህ ማለት ነው።" ብሎ መስኮቷ እንዴት እንደምትዘጋና እንደምትከፈት አሳየኝ።

'ኢሱ፣ መጀመሪያ ግን ከፉን ያርቅ በል፣ ወዳጄ!!' መለስኩለት በልቤ። 'መስኮቷ ወደ ወይዘሮ ማስተዋልና ወደ ልጃቸው ግቢ የምትወስድ መሆኗ ግን የገነት መንገድ ያደርጋታል! እስቲ አሁን የሳሎን ፎቶ ዐይቶ ሴት ማፍቀር ምን ይሉታል? ሌላ ምንም አይሉት፣ ባላገርነት ነው!' ራሴን በራሴ ሞለጭኩት።

የመሳለሚያው ሸዋአዲስ ጋራዥ የውስጥ ጉብኝቱ አበቃ።

በጉብኝቱ ማብቂያ አሁን የቆምኩበት ቦታና የጠቅላላ ጋራዡ አቀማመጥ ካርታ ገባኝ። የሰፈሬ ስም «መሳለሚያ» ይሁን እንጂ ያለሁበት ጋራዥ አንድ ራሱን የቻለ አውራጃ መሆኑን ከኔና ከድርጅቱ ሌላ ማን ያውቃል? ጉብኝቱን በልቦናዬ ዳግም ተመላለስኩበት። በደንብ ስለለው አእምሮዬ ውስጥ እንዳች ምሥል ሠራ። የ"ደ" ቅርጽ ሰጠኝ። ከላይ ያለችው ከቧ ጋራዡን ትወከላለች። የግራው እግር የወይዘሮ ማስተዋል መኖሪያ ግቢ ነው። የቀኙ ደግሞ የእኛ መኖሪያ የምድር ቤት መሆኑ ነው። አሁን ምድር ቤት ውስጥ የማያት መስኮት ሁለቱን እግሮች በአቋራጭ ታገናኛለች።

ሸዋዬ ጣውላውን በር ከፈተችልን። ተያይዘን በደጀኔ ክፍል በኩል የኢሳያስን ክፍል አቋርጠን ወጣን። ወደ ጋራዡ።

***

ኢሳያስ ወደ ጉለሌ የኢሕአፓ ፖሊት ቢሮ ጽሕፈት ቤት ለመሄድ ሞተር ብስክሌት ይዞ ሲወጣ እስከዋናው አስፋልት ድረስ ሸኝቼው ተመለስኩ።እግሬ ልክ የጋራዡን በር ሲረግጥ ግን ምድርን ያንቀጠቀጠ ፍንዳታ ተሰማኝ። ከሩቅ ይሁን ከቅርብ...ቦንብ ይሁን መድፍ...መለየት አቃተኝ። ትንሽ ቆይቶ የጥይት ተኩስ ተንፈቀፈቀ። 'እህ! የምን ተኩስ ነው?' ተመልሼ ወጥቼ ወደ ጋራዡ ሸማግሌ ዘበኛ

ተንደረደርኩ። ሽማግሌው ማደሪያ ቆጣቸው ላይ እንደቆሙ አሸጋግረው ወደ ሩቅ ቦታ ይመለከታሉ።

"ምንድነው አባት? የሚታይዎት ነገር አለ?"

"እይ...ሩቅ ነው። ወደ መርካቶ አካባቢ ይመስለኛል። ከባድ ቃጠሎ ይታየኛል..."

ከሩቀ ችግር የለውም። ወደ ጋራዥ ተመለስኩ። ቢሮዬ ገብቼ ልቀመጥ ወንበሩን ሳብ ሳደርግ እንደገና ሌላ ድምጽ መጣ። የአሁኑ የሰው ካቢድ ጩኸት ያጀበው ነው። የእኛው የጋራዡ ዘበኛ ቆጣቸው ላይ እንደቆሙ ጮኹ። ከጋራዡ ጀርባ አንድ አደጋ እንደመጣ ገመትኩ። እንደዛ ዓይነት መብረቃዊ ድምጽ ከእኚህ ኮሳሳ ሽማግሌ አልጠበቀኩም።

"ቁ———ም!! ቁም ብየ——ሃለሁ ቁም!! እመቤቴ ትፍረድብኝ፤ ጣልኩህ!"

ሽጉጤን መቼ እንደምጠቀምበት ግራ ስለሚገባኝና ለአያያዝ ስለማይመቸኝ አልያዝኩትም። ምድር ቤቴ ካርቶን ውስጥ ትቼው መጥቻለሁ። አንድ ትልቅ የብሎን መፍቻ ጉጠት አነሳሁ። እሱን እንደቆመጥ እየነቀነኩ ወደ በሩ ተንደረደርኩ...

"ጋሽ አለነ፣ ሙሴ ባልዲ ነኝ። መንገድ ጠፍቶብን ነው። እንዳይተኩሱብን!" በጭንቀት የሚለማመጥ ድምጽ ተሰማኝ።

"ሙሴ፣ ብለህ ብለህ ወደ እኔ መጣ---ህ?" እዛውንቱ በወቀሳ ድምጸት መልስ ሲሰጡ ከቅድሙ ይልቅ አሁን ቀዝቀዝ ብለዋል።

ልክ ከበሩ ስደረስ ሦስት ጠብደል ጎረምሶች የጋራዡን የብረት አጥር እንደ ፌንጣ እየዘለሉ ዱብ ዱብ ኣሉ። በዚያው ፍጥነት አፍንጫዬን ታከው ወደ ዋናው አስፋልት ሽምጥ ሮጡ። ሦስቱም ገና ሲያዩት 'ጎህት የሚለቅ ትልልቅ ጩቤ ይዘዋል። አንድ ወንጀል ሠርተው እያመለጡ እንደሆነ ሁኔታቸው ይናገራል።

"ምንድነው፣ አባት? ማነው ሙሴ ባልዲ?" ጠበንጃቸውን ዘቅዝቀው ወደ ዋናው አስፋልት ያፈጠጡትን ዘበኛ ጠየኳቸው።

"እይ ልጄ፣ ሙሴ ባልዲማ አገር ምድሩን ያስገበረ የመሳለሚያ ማጅራት መቺ ነው። መንግሥትን ያቸነፈ የከተማ ሽፍታ!"

እየተገረምኩ ተመልሼ ገባሁ...

# 4

ሕቡእ የፖለቲካ ሥራዬን በሸዋአዲስ ጋራዥ ከጀመርኩ ቀናት አስቆጥሬያለሁ። ሸዋዬ ያቀረበችልኝን የሻይና ዳቦ ቁርሴን በልቼ ወጣሁ። አሁን ረፋድ ላይ የጋራዥ ቢሮዬ ውስጥ ነኝ። በርከት ያሉ ደንበኞችን አስተናገድኩ። በሥራው የረኩት አመስግነውኝ ይሄዳሉ። አንዳንዶቹማ እስከ አስር ብር ድረስ የሻይ ሽጉጥ አድርገውልኛል። "በጣም አመሰግናለሁ!" እጃቸውን በሰላምታ ጨብጬ እወዘውዘዋለሁ። ገቢው ድርጅቴን ኢሕአፓን የሚጠቅም ስለሆነ ስቀበላቸው አልግደረደርም።

እነዚህ ሲሄዱ ሌሎች ይመጣሉ። በቀጠሮው ቀን ጥገናው ያላለቀላቸው ደግሞ ይነጫነጩብኛል። የመለዋወጫ እቃውን እጥረት፣ የሜካኒኮችን ሥራ መልቀቅ፣ የኤሌክትሪክን መቆራረጥ ሁሉ እየዘረዘርኩ ላሳምናቸው እታገላለሁ። በቃልኪዳንና በመሀላ መዐት እያግባባሁ እንደ ምንም አሸኛቸኋለው። ምን ላድርግ? የሥራው ባሕሪ ነው።

ከብዙ ወከባ በኋላ አሁን ትንሽ ፋታ አገኘሁ…

ሊቀመንበር ማኦ "አብዮታዊ ሥራህን ከመጀመርህ በፊት አካባቢህን ጠንቅቀህ እወቅ!" ይላል። ሕቡዕ ሥራዬን ከመጀመሬ በፊት አካባቢውንና ትክክለኛውን የሥራ መርሀ-ግብሬን ጠንቅቄ ማወቅ ነበረብኝ።ሁለቱን ቀናት ያሳለፍኩት ይህንኑ በማድረግ ጥረት ነው። ስለዚህም ሥራውን ስጀምር ብዙም ግራ አልተጋባሁም። በዚህ ላይ በኢሕአፓ የፖለቲካ ኮሚቴ ኃላፊነቴ ግልጽ የሥራ ስምሪት ተሰጥቶኛል። ዶክተር ተስፋዬ ከሳምንት በፊት ከእኔ ምን እንደሚጠበቅ በቃል ጠቃቅሶልኛል።

በማግስቱ ደግሞ ከፍሉ ታደሰ በታይፐ የተጻፈ 12 ገጽ የሥራ ዝርዝር በኢሳያስ በኩል ላከልኝ።

በደቂቃዎች ውስጥ ቆት አደረኩት። ወረቀቱ የተሟላ መረጃን ይዟል። ልቤ ውስጥ የተቀረጸው ግን ተስፋዬ ደበሳይ እንደቀልድ ያጫወተኝ ነገር ነው።

ለጓድ ተስፋዬ አማርኛ ከእናት እንደበቱ ሳሆና በልምድ ከሚናገረው ትግርኛ ቀጥሎ ሦስተኛ ቋንቋው ነው። እንግሊዝኛንም በሚገባ ይጠቀምበታል። አማርኛን ለመግባባትና ሐሳቡን ለመግለጽ ሲጠቀምበት ትንሽም ዝንፍ አይልም። በዚህ ላይ ዘወትር በማይለየው ነጭ የዕይታ መነጽሩ ሥር የሚንከባለሉት ዓይኖቹም የራሳቸው ቋንቋ አላቸው። ተናጋሪ ወይም ተጫዋች የሚባል ሰው ግን አይደለም። ጭምትነቱ በዛ ይላል። የፍልስፍና ምሩቅ መሆኑ በቀላሉ እንድንግባባ ያገዘን ይመስለኛል።

ፍልስፍናን እኔ እንደ ሃይማኖት ዐየዋለሁ። ብዙው የንባብ ታሪኬ ከፍልስፍና መጻሕፍት ጋር የተያያዘ ነው። ከፕሌቶ እስከ ጆን ስትዋርት ሚል ድረስ የተቻለኝን ያህል ሰልቄዋለሁ። ባነበብኩት ቁጥር ሁሌም አዲስ ይሆንብኛል።ተስፋዬ በውይይት መሀል እስቦ እስቦ አንድ ቁም ነገር ጣል ያደርጋል። እኔ ደግሞ የተናገረውን ቁምነገር የፍልስፍና ጓዳ ጎድጓዳ ወዲያውኑ ቆጭ አደረገዋለሁ።

"እ--ይ ፖለቲካ! ነገርሽ ሁሉ አስደማሚ ነው!" ያልተለመደ ነገር በገጠመኝ ቁጥር ኢሳያስን አደጋግምለታለሁ።

ዶክተር ተስፋዬ የመጣበት መንገድ ከሚገርሙኝ ነገሮች መካከል ነው። በቤተሰባዊ ሃይማኖቱ የካቶሊክ ክርስትና እምነት ተከታይ ነበር። የፍልስፍና ትምህርቱን የተማረው ስዊዘርላንድ ውስጥ ነው። እድሉን የሰጠችውና ወጭውን የሸፈነችለት ደግሞ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ናት። ካርዲናሎቹና መምህራኑ ተስፋዬን ሲያስተምሩት ከእሱ የሚጠብቁት ነገር ነበራቸው። ሲቀድስና ሲዘምር የምእመናንን ልብ ቀልጥ የሚያደርግ የካቶሊክ ቄስ ኾኖ ማየት። እሱ ግን በዚህ ቦይ አልፈሰሰም። አቅጣጫውን ቀይሮ ከፖለቲካ ጋር ተቆራኘ። ማርክሲስት በመሆኑ ካቶሊክ እምነቱን አራግፎታል።

"አሁን የሚገዛህን ማኅበራዊ ወገን ትክክለኛነት መጠራጠር ስትጀምር ያኔ መፈላሰፍ ጀምርሀል!" አርስቶትል ይማርከኛል።

አእምሮዬን ወደ አዲሱ ሥራዬና ሰፈሬ መለስኩት። የትላንቱን ሌሊት እየጻፍኩ ነው ያነጋሁት። የኢትዮጵያን ተራማጆች በተለይ ድርጅቴን የተገዳደሩትን ፈተናዎች በሁለት ከፈልኳቸው። "አዚመኛና መዘዘኛ" ብዬ። ከአዚመኛ ፈተናዎች የአንበሳውን ድርሻ የሚይዘው የመሬት ዐዋጁ ነው። በሕይወቴ ከሠራኋቸው ትልልቅ ስህተቶች ምናልባትም ዋናው የመሬት ዐዋጁን መተንበይ አለመቻሌ ነው። ብርከታዊት ወሬውን ስምታ መጀመሪያ ስትነገረኝ "የማይሆን ነገር!" እንዳልኳት ትዝ ይለኛል። አሁን

ድረስ እንደ'ሱ የሚቆጠቁጠኝ የለም። ከመዘዘኛ ፈተናዎች ደግሞ "የኤርትራ ጥያቄን" የሚስተካከል የለም።የብሔር ጥያቄ ይከተላል። የተራማጅነት አዳ ነውና ለሁለቱም ዓይነት ፈተናዎች ኢሕአፓ ቀጥተኛ የፐሮግራም መልስ ሰጥቷል። በመሀል ግን ሁኔታው ተለወጠ። እናም የተሻሻለ ፐሮግራም የመንደፍና የማጽደቅ ግዴታ አለብን።

"ማንም በቅሬታ ይዘን ወይም በደስታ ይዝለል፣ መልስ መስጠት ለድርጅቱ ግዴታ ነው።" መነሻ መርሆዬ አደረኩት።

እሁንም ቢጋራዥ ቢሮዬ ውስጥ ነኝ። የብረቱን ቅጭልጭታ እየተላመድኩት መጥቻለሁ። እንቅልፍ ማጣት የፈጠረብኝ ድካም ሊያንገላውደኝ ፈለገ። በኃይል ተንጠራርቼ እፌን በእጄ ስተመትም የቢሮዬ በር ተንኳኳ።

"ይግ---ቡ!" የደስ ደስ ያለውና የፊቱ ቅላት የዐረብ ክልስ የመሰለ ልጅ ብቅ አለ።ሚካኤለ ነው። የጋራዡ ባለቤትና የምድር ቤቱ አከራያችን የወይዘሮ ማስተዋል የልጅ ልጅ። የአራተኛ ወንድ ልጃቸው ልጅ። የፊት ቆዳው ጥራት ገና ጡት ያልጣለ ሕጻን  አስመስሎታል። ትዝ ሲለኝ የዐይኑ ሽፋሽፍት ፎቶዋን ግድግዳ ላይ ካየሁት ቆንጆዬ ሴት ልጃቸው ጋር ይመሳሰላል። ቢታኒያ! ቢታኒያ ብለው የነገሩኝን ስሟ ለምን አእምሮዬ ላይ እንደታተመ አላወቅኩም።ከሚካኤለ ጋር የተዋወቅን ቀን ትንሽ አውርተናል። ዕድሜው 12 ዓመት ሆኖ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ መሆኑን ነግሮኛል።

"ጋሼ፣ ስልክ ትፈሊጋላችሁ፣ እኛ ጋ።" ብሎኝ ሮጦ ሊመለስ ሲል..."ቆይ እንጂ..አብረን እንሂድ፣ ሚካኤለ፤ መንገዱ እንዳይጠፋብኝ..." ስለው ቆም አለ።

የጋራዡ ስልክ ተበላሽቷል። ሆን ተብሎ ይሁን ወይም ለጥገና ወረፋ አልደርስ ብሎ አላውቅም ብቻ ከተበላሸ ወራት ማስቆጠሩን ኢሳያስ ነግሮኛል። በዚህም ምክንያት ማንኛውንም ጥሪ የምንቀበለው በወይዘሮ ማስተዋል ስልክ ነው።የደወለው ሰው እንዱ የጋራጉ ደንበኛ እንደሚሆን ዐውቃለሁ። የመኪናውን ዓይነትና የጥገና ታሪኩን ግን አላውቅም። ዋናውን መዝገብ የመሸከም ያህል ይገፎ ወጣሁ። ሚካኤለ እየመራ ወሰደኝ። በዋናው የጋራዡ በር ወጥተን ወደ ግራ ታጥፈን ሁለት የቆርቆሮ በሮችን አለፍን። በግቢው የግራ ጎን ሌላ ጠባብ አረንጓዴ በር አለ። ሚካኤለ ከፍቶ ካስገባኝ በኋላ ስልኩ ያለበትን ቦታ አሳይቶኝ ወደ ዋናው ቤት ገባ።

'ማን ይሆን የደወለው?'

ከዋናውና ትልቁ ቤት ጀርባ ከሁሉም ሰፋ ያለ ሰርቪስ ቤት አለ። በመሀል ጠባብ ክፍት ቦታ አለ፡ ስልኩ የተቀመጠው ከሰርቪስ ቤቱ ጎን ባለ የመስታውት መስኮት ሥር በብረት ማስቀመጫ ላይ ነው። ገርበብ ብሎ የተከፈተው የሰርቪስ ቤቱ መስኮት በውስጥ በኩል በመጋረጃ ግጥም ተደርጎ ተሸፈኗል።ሄጄ ተከፍቶ የጠበቀኝን የስልክ እጀታ እስከማነሳ ድረስ ሰው አልታየኝም ነበር። ወዲያው ግን የአግሬን ኮቴ ሰሙ መሰለኝ ወይዘሮ ማስተዋል ከዋናው ቤት ብቅ አሉ።

"አንተ ነህ ልጄ? ደህና ዋልክ?" ትህትናቸው አንጀት ያርሳል፤ አጸፋውን ስመልስላቸው ሰላምታ ሰጥተውኝ ተመለሱ።

"አቤት፤ ሰመረ እባላለሁ ከሸዋአዲስ ጋራዥ..." አልኩ ለደወለልኝ ሰው።

በመሀሉ ከመስኮቱ የሚመጣ ጥዑም ሽቶ አፍንጫዬን አውድ አደረገው። ቤተመቅደስ በር ላይ የቆምኩ መሰለኝ።

ከወዲያኛው ጫፍ የመጣው ድምጽ የሴት እንግሊዝኛ ተናጋሪ ፈረንጅ እንደበት ነው። "'ያንኪስ፤ ጎ ሆም!" ብለን አባረናቸው የለም እንዴ!? ይህች በየት በኩል ያመለጠች ያንኪ ናት?' ራሴን ጠየኩት። ጥርት ባለ የብሪቴይን ቅላጼ ባለው እንግሊዝኛ ነው የምታነጋግረኝ። በዚህ ቦታ ለደንበኛ ጥሪ በእንግሊዝኛ መልስ ስለመስጠት ተገቢነት ጨርሶ አላሰብኩበትም። ህቡእ የገባሁ ሰው ስለሆንኩ ፈራሁ። እንግሊዝኛ መናገር ራሱ የተደበቀው ማንነቴ አንድ አካል ነው። ለአፍታ ግራ ተጋብቼ ቆየሁ። የፈረንጇ ጥያቄ ሲደጋገምብኝ ድምጼን ቀንሼ አጭር ነገር መነጋገር መረጥኩ...

"ትሰሚኛለሽ? ሊብሬ ላይ የተመዘገበውን የመኪናዋን ባለቤት ሙሉ ስምና የመኪናዋን ታርጋ ቁጥር ብትነግሪኝ..." መዝገቡን ገልጬ ሳነጋግራት ድምጼን የበለጠ ዝቅ አደረኩት፤ የተሳካልኝ አልመሰለኝም።

"የባለቤቱ ስም ጀምስ ስተርን ነው። ታርጋ ቁጥሯ ደግሞ ኮድ 2-1023...'

የመዝገቡን በኮድ ቁጥር 2 ዝርዝር የተለየ ክፍል ገጽ ገልበጥ ገልበጥ አደረኩ። ፈረንጇ ያለችውን መኪና መረጃ አገኘሁት። ምን ደረጃ ላይ እንዳለ በፍጥነት ነበብ ነበብ አድርጌ ሄሎ! አልኩ። ለማሰናበት ጠደፍ ጠደፍ እያልኩ ነው...

"መኪናዋ አራት ዓይነት ብልሽት ተገኝቶባታል። ዘይት ታፈሳለች፤ የኤሌክትሪክ ስርዐቷ ታውኳል፤ የመሪ ዘንጉ ደንብሿል፤ ነዳጅ መሳቢያውም ተበስቷል። አሁን ከኤሌክትሪክ ችግሩ በስተቀር ሁሉም

ተስተካክሏል። እሱም ቢሆን ዛሬና ነገ ጧት ያልቃል። በሚቀጥለው ሳምንት መጨረሻ ብቅ በሉ። ሁለት ሙቶ ሰባ ብር ከፍላችሁ መውሰድ ትችላላችሁ..."

የምናገረውን በእንግሊዝኛ አፍ በፍጥነትና ዝግ ባለ ድምጽ ነበር። ቀና ስል አጠገቤ ድንገተኛ ለውጥ መጣ። የሰርቪስ ቤቱ ባለመስታወት መስኮት ሲጢጢጥ ብሎ ከውስጥ ተከፈተ። በአበባ ምስሎች የተንቆጠቆጠው መጋረጃ ወደ አንድ ጎን ሰብሰብ ተደርጎ ተገለጠ። ወዲያው የመስኮቱ የግራ ተከፋች ቦግ አለ። ጠይምነቷ ቀድሞ ከልብ የሚደርስ ወጣት የምድር ቆንጆ! ጉድ! የተተኮሰ ርችት መስላ ዐይኔ ላይ ፈነዳች። ፊቷ ልክ እንደ ንጉሣን ቤተሰቦች ከግንባሯ ትንሽ ሰፋና ወጣ ብሎ ይጀምርና ከአገጯ ሲደርስ ቀለል ይላል። ከግንባሯ ወረድ ሲል ንጣታቸው መልሶ ዓይን የሚወጋ ትልልቅ ዐይኖች፤ አፍንጫዋ ደጋን መስሎ ይወርድና ስስ ከንፈሮቿን ተንተርሶ ወደ ውስጥ ይቀለበሳል። እንዳፈረች ሁሉ የፊቷ ቀለም ድፍርስ አለ።

'እ—ግ---ዚ---እ!!'

ለቅጽበት ማርከሲስትነቴን አስረሳችኝ። የዌስት ሚኒስትር ዘውዳዊ ቤተመንግሥት ልዩ ሰረገላ ቆሞ ልእልቷ የወርቅ መጋረጃዋ በደንገጡሮቿ ሲከፈትላት ብቅ ያለች መሰለኝ። ሁሌምና የትም ቦታ እንዲሁ ነኝ። ቁንጅናዋ ከመጠን ያለፈ ሴት አትመቸኝም። በድንገትም ቢሆን ስታየኝ እንደ ዛር ታስፈራኛለች። በራስ መተማመኔ እንደ ጤዛ ጥሎኝ እብስ ይላል። ይህችኛዋ ግን መስህብ ነው ያላት። 'ከዓይን ያውጣሽ፣ የኔ ቆንጆ!' በሆዴ ጸልየላት ተመልሼ ሰረቅ አድርጌ አየኋት...

'እግዚ----እ፣ ይህች እውነት ከሰው ማህጸን የተፈጠረች ናት ወይስ በስህተት ከገነት የተወረወረች ፍሬ?!'ዐይኔን የማሳርፍበት ቦታ አጥቼ ዞር ስል ልቤ ቀጥ ልትል ምንም አልቀራትም።

በቅጽበቱ እንደከከ ሰፈጨው የነበረው እንግሊዝኛም እልም ሊልብኝ ታገለኝ። ወሬዬን እንደምንም ጨርሼ ወደ መስኮቱ ዞር አልኩ። ልጅቱ የሰበሰበችውን መጋረጃ ወደቦታው እየመለሰች ነው። 'ጉድ ነው!' የዐይኖቿን ቅንድቦች ሽቅብ ሰብሰብ አድርጋ ሰላምታ ሰጠችኝ። እኔን ሰላም ማለቷን ማመን እቃተኝ። የስልኩን መነጋገሪያ ሳስቀምጥ እጄ ትክክል አልነበረም። እንከርፍፌ ዘጋሁት። እንደገና እስተካከዬው መዝገቤን እንስቼ ወደ ጆርባዬ ዞር አልኩ። ልጂቱ ከመጋረጃው ጀርባ የለችም። እንደ ቆሌ ውልብ ብላ እልም አለችብኝ። ዐይኖቼ አብረው ቦግ ብለው ወዲያው ደግሞ አብረው ድርግም አሉ።

"እድህነን ከመዐቱ ሰውረን!"በልጅነቴ የከረምት ሰማይ ድንገት ብልጭ ብልጭልጭ ብሎ እንደ መድፍ ያጓራል። ያኔ እናቴ ደረቷ ላይ አማትባ የምታደርሰው ጸሎት ትዝ አለኝ።ወደ በሩ እየሄድኩ የተበታተኑ

የአእምሮዬን ምስሎች ለመገጣጠም ሞከርኩ። ወዲያው ትዝ ያሉኝ ወይዘሮ ማስተዋል ናቸው። የተዋወቅን ዕለት ያሉኝን አስታወስኩት...

"እኔ ያው ሁሌም እዝችው ሶፋ ላይ ነኝ። ምናልባት ምናልባት ካልኖርኩ ግን ቢታኒያ የምትባል ልጄ አለች። እዚህ ሰርቪስ ቤት ነው የምትኖረው። ሒሳቡን ለእሷ ትሰጣታለህ..."

ቀጥሎ የመጣልኝ ደግሞ እሳቸውን እያዋራሁ ያየሁት ፎቶ ነው። ግድግዳው ላይ ያለምንም ይሉኝታ አፍጥጬበት ነበር። 'ቢታኒያ ማለት ይህች መሆን አለባት።' ጭራሽ ቀንጆ ዐይቼ እንደማላውቅ ሆንኩኝ። አግራሞቱ ቀዩ በር ደርሼም ቶሎ አለቀቀኝም። እንግሊዝኛን የአማርኛን ያህል መናገሬ መዘዝ ሲያስከትል ታየኝ። ቢታኒያን ምናልባት ተራ ሜካኒክ አለመሆኔን ሳይጠቁማት አልቀረም። መስኮት ከፍታ ያየችኝ ለዚህ መሆን አለበት። ድምጼ ረብሿት ሊሆን ይችላል ብዬ ማሰብ አልቻልኩም። እንዲያ ከሆነ ከድርጅት ተልእኮዬ አንጻር ትልቅ ስህተት ነው የሠራሁት። እንዲያውም ተራ ልታይ ልታይ ባይነት ሆኖ ተሰማኝ። ትንሽ ስቆይ ግን ችላ አልኩት...

'ከዚች የምድር ቀንጆ ጋር የበለጠ ለመቀራረብ ምናልባት የሚረዳኝ ከሆነስ? ይሁን፣ ምናባቱ!' ራሴን አበረታታሁት። '"ቀንጅትዬ" ብትባል ያንስባታል።' ከብርከታዊት ያለምክንያት መለያየት ያቆሰለው ልቤ ደጋግሞ አወደሳት።

***

ወደ ጋራዥ ተመለስኩ። ሰዓቱ 6:35 እስከሚሆን ድረስ ከቢሮዬ ንቅንቅ አላልኩም። ሙሉ በሙሉ ጭር ሲል ወደ ጋራዡ የሥራ ክፍል ብቅ አልኩ። በማውቀው ምክንያት ግማሽ ያህሉ ሠራተኞች የሉም።

"ደጀኔ ለኮማንዶ ስልጠና በጋራዡ ጀርባ በኩል እያሾለከ ይወስዳቸዋል። ዋናው ሥራቸው ይሄው ነው። አንተ በምንም ተአምር ጣልቃ አትገባም።" ኢሳያስ ጠበቅ አድርጎ ከማስጠንቀቂያ ጋር ነግሮኛል።

የተቀሩት ደግሞ ውድቅት ሌሊት ላይ ሥልጠና ላይ ያመሹትን ይተኳቸዋል። ኤርትራዊው የሐርነት ኤርትራ (ጀብሀ) ፈዳይን ጎይቶም ለባሲ ይረከባቸዋል። ተኩስና ቦታ አያያዝ ያስለጥናቸዋል። ደጀኔ በበኩሉ የእጅ በእጅና የከተማ ውጊያ ያስተምራቸዋል። ከጋራዥ ሥራ ውጭ በድርጅት ጉዳይ እንዳይተዋወቁ ጥንቃቄ ተደርጓል። አራት ወጣቶች በአንድ ህዋስ እየታቀፉ እንዲሰለጥኑ ነው የተደረገው።በበኩሌ ልሳሳት እችላለሁ፤ ነገሩ ግን ፈጽሞ ደስ አይለኝም። የሆነ የሰፈር ልጆች ጨዋታ መስሎ ይታየኛል።

'ኡ-ሙ፣ የከተማ ትጥቅ ትግል ብሎ ነገር!' አልኩ ለራሴ፣ 'አብዮታዊ ፓርቲ ካሉ በኋላ የከተማ ሽምቅ ውጊያ ምናምን ምን አመጣው? ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ እፈን ዳባ ዳባ አለኝ...'

ኢሳያስ ከወራት በፊት ብርሀነመስቀል ከአሲምባ መምጣቱን የነገረኝ ቀን ነው። እንደዛን ዕለት ተደናግጬ አላውቅም። "ብርሃነመስቀል አሲምባን ለቆ አዲስ አ'ባ?" ጮኽኩ። በእውነት ብርሃነመስቀል በድርጅታችን ዋና ጸሐፊነቱ የተገደለ፣ የተማረከ ወይም እጁን የሰጠ ያህል ነው የተሰማኝ። ኢሕአሠን የወደፊቱ ኢትዮጵያዊ የቀይ ጦር ጥንስስ አድርጌ ነው የማየው። እናም የፓርቲው ዋና ጸሐፊ ትክክለኛ ቦታ ገጠር በኢሕአሠ መካከል እዛው አሲምባ! ብዬ የማምነውም ለዚህ ነው።

"ይሄ ነገር የታክቲክ ጉዳይ ነው ወይስ ከጀርባው የአመለካከትና የፖሊሲ ልውጥ ይኖር ይሆን?" ስጋት ሲገባኝ ኢሳያስን ጠየኩት።

"እ--ይ፣ የድርጅቱን መለስተኛ ጉባኤ ለመምራት ነው የመጣው። ተመልሶ የሚሄድ ይመስለኛል..."

የኢሳያስ መልስ የበለጠ ግራ አጋባኝ። "የኢሕአፓ ድርጅታዊ ጉባኤ አዲስ አበባ ውስጥ? ወይስ የጫጉላ ሽርሽር አደረጉት?" መልስ አላገኜሁም። ሌኒንና ማኦ ይሄን ጉድ ቢሰሙ በሳቅ ፍንድት ብለው ይሞታሉ!"የተሰማኝን ልነግረው ካልኩ በኋላ መልሼ ተውኩት።

ከዚህ የከፋ ነገርም አለ።በብርሀነመስቀል ቦታ ተተክቶ አሲምባ የሄደው ጸጋዬ ገብረመድህን (ደብተራው) ነው። በጭራሽ አልተመቸኝም። ሲጀምር ጸጋየ በቂ የሚባል ወታደራዊ ስልጠናም ይሁን ልምድ የለውም። በፖለቲካ አቋሙም ብዙውን ጊዜ ግትር ነው። በዚህ ላይ የትግራይ ልጅ አይደለም፤ አሲምባንና አካባቢውን አያውቀውም። የአረጋዊ በርሄና የስብሀት ነጋ የትግራይ አርነት ድርጅትም አጠገቡ አለ። ኢሕአሠ በአካባቢው መኖሩ እንዳላስደሰታቸው ሰምቻለሁ። ጸጋዬ ደብተራው ይሄንን ሁሉ ውጥንቅጥ የመልከዐ ምድርና የፖለቲካ ፈተና ሲቋቋም ሊታየኝ አልቻለም። በጣም ቅር አለኝ። ይህንንም ቢሆን ግን አሁንም ከኢሳያስ በስተቀር ለማንም አልተናገርኩም።

'እእእ----ው፣ ከአፍ የወጣ አፋፍ ነው ወዳጄ!' ራሴን ነገርኩት።

በድርጅቴ ውስጥ ጥርጣሬ ለሚፈጥር ነገር ምክንያት መሆን አልሻም። ወይም አንዳች ዓይነት አሉታዊ አስተዋጽኦ ማድረግ የለብኝም ብዬ ስለማምን እጠነቀቃለሁ። የፖለቲካ ድርጅት በተለይ በድሀ አገር ትርጉሙ ለየት ይላል። እጅግ ውድ ብቻ ሳይሆን እጅግ ተሰባሪ ምርትም ሆኖ ይሰማኛል። እናም ጥንካሬው እንደ ጊዛ ብረት ነው። አንዴ ቀጭ ብሎ ከተሰነጠቀ መልሶ መጠገን አይቻልም። ድርጅትም

እንዴ ከሽ ካለ የማቋቋሙን ያህል ቀላል አይደለም። ኢሕአፓን ማጣት ማለት ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የዓይን ግርዶሽ ነው...

'ቸር ተመኝ ቸር እንድታገኝ!' ልል ፈልጌ ለራሴ ሳይንሳዊ ያልሆነ ምኞት መሆኑ ትዝ ሲለኝ መልሼ ተውኩት።

***

የከርስቶን ምስል እንስቼ ምሥጢራዊዋን በር ከፈትኩ። በዚያው ለምሳ ወጣሁ። የነቢታኒያን ቀይ በር በስርቆሽ ዐየት አድርጌው አለፍኩ።ይህንን ማድረግ ካየኋት ቀን ጀምሮ ልምድ ኾኖብኛል። ወ---ይ ቢታኒ---ያ! ደራሽ እንግዳ ስሜት ደርሶ ውርርር አደረገኝ። ጣውላውን በር በተሰጠኝ ኮድ እንኳኳሁት። ኳኳኳ ትንሽ ቆይቼ ደግሞ ኳ...።

ሸዋዬ ከፍታልኝ ተያይዘን ገባን። ኢሳያስ የለም። ከሸዋዬና ከደጀኔ ጋር ምን ይመስለ ሽሮ ወጥ ግጥም አድርጌ በላሁ። ትንሽ አረፍ ብለን ስንጫወት ቆየን። የሁለቱም ጨዋታ ለዛ አለው። ስምንት ሰዓት ላይ ለሥራ ወደ ጋራዥ ተመለስኩ።

***

ከሰዓት በኋላ ከሁለት ደንበኞች በስተቀር ብቅ ያለ ሰው አልነበረም። ይህንና ያንን ስጽፍና ስቀድ ሰዓቱ ሽው አለ። ጋራዡ ሙሉ በሙሉ ጭር ሲል ቢሮዬን ዘግቼ የዕለቱን ገቢ ገንዘብ ቆጠርኩ። 2220 ብር ከምናምን ሳንቲም። የወይዘሮ ማስተዋልን ድርሻ በቀኝ ኪሴ አስገባሁ። የቀረው የኢሕአፓ ድርሻ ነው። ሰባ ደረጃ ብቅ ብዬ ለኢሕአፓ ፋይናንስ ኃላፊ ለዮሴፍ አዳን ሰጥቼው እመለሳለሁ። ዮሴፍ የማእከላዊ ኮሚቴ አባልም ጭምር ነው። በጣም የማደንቀውና የምወደው መሪ ነው። የደስ ደስ አለው። ጨዋታው መቼም ጥርስ አያስከድንም።

'ዮ---ሴ---ፍ አዳ---ነ!' ሁለተኛው የኢሕአፓ ሰማዕት ቢኒያም አዳነ ወንድሙ ነው። እነ ብርሃነመስቀል በ1961 አውሮፕላን ሲጠልፉ ቢኒያም አንዱ ነበር። ለኔ ግን ከጠላፊዎቹ ምስል ብርሃነመስቀል እንጂ እሱ ትዝ አይለኝም። ብርሃነመስቀል ስለ ቢንያም ድፍረቱን አንስቶ አድንቆልኛል። በኤርትራ በኩል ወደ እሲምባ ከመጣው ኃይል ጋር ሲጓዝ እስም በሽታው ተቀስቅሶ እላራምድ አለው። በዚህ በጣ---ም ተበሳጭቶ ራሱን አጠፋ።

ዮሲፍን ካገኘሁት ደግሞ ለኢንጅነር ኡስማን አስረክበዋለሁ። መጀመሪያ ግን ሁልጊዜም ወደ ወይዘሮ ማስተዋል ነው የምሄደው። ብር ከተቀበሉኝ በኋላ የሚከተለው ምርቃታቸው ደስ ይለኛል።የኢየሱስን ምስል አንስቴ በማሥጠራዊው በር በኩል ወጣሁ። ቀዩን በር ሳንኳኳ ሚካኤለ ከፈተልኝ። ዋናው ቤት ገብቼ የዕለቱን ገቢ አስረከብያቸው ብድግ ልል ስል ቢታኒያ ከቤቷ ወጥታ መጣች። የእረፍት ልብስ ነው የለበሰችው። እንደገመትኩት አጭር አይደለችም። ከመካከለኛ ቁመት ትንሽ ዘለል ትላለች። ሽንጧ እንደ ሀረግ እየተመዘዘ መጥታ ገባች። የጥዑም ሽታ ጠረን ቀድሟት ገብቶ አፍንጫዬን አወደው።

"ሀ—ይ፥ በደንብ አልተዋወቅንም አይደል? ቢታኒያ እባላለሁ!" ልትጨብጠኝ መጣች።

ልቤ እንደ ዱባ ከሁለት ከሦስት ስንጥቅ ልትል ተፈታተነችኝ። እርሷን የመሰለች ሴት ልጅ በራሷ ጊዜ ትተዋወቀኛለች ብዬ ስላልጠበቅኩ ነገሩ ሁሉ ተወነባበደብኝ።የእጇ ዘይት እንዳያበላሻት ተጠንቅቄ ጨበጥኳት። "ሰመረ እባላለሁ!" የውስጥ እጅ ቆዳዋ እንደ ድመት ወዞብ ለሰለሰኝ።ዐይኖቿ በራስ መተማመኗን ሲፈታተኑት ይሰማኛል። ጸጉሯ ከሰዓት በፊት እንዳየሁት አይደለም። ዘረያውን ጠቅልላ ጎንተናዋለች። እናም ጭንቅላቷ ላይ የተጋደመ ጋሻ አስመሰላዋለች። ድምሩን ውበቷን የሚመራው የትኛው የፊት ገጿ አካል እንደሆነ መለየት አልቻልኩም። ዐይኖቼ ተብርብር አሉብኝ…

"ኢሳያስ በእኔ ቦታ ይመጣል ያለኝ ልጅ አንተ ነህ?" ድምጿን ከሥሩ ግሩም ዜማ አጅቦታል።

"አዎ፣ እኔ ነኝ።" ብዙ ተናግሬ ምናልባት በሚያመልጡኝ ቀበልኛ ቃላት እንዳትይዝብኝ ተጠንቀቅኩ።

"በል፣ ልመድ! ኢሳያስ እግሩ የማይጨበጥ ከመሆኑ በስተቀር በጣ—ም ጥሩ ልጅ ነው። ያው መኪና ሲያስፈልገን ትረዳናለህ፣ ከይቅርታ ጋር…" ፊቷን ወደ ውስጥ ቀልበስ ስታደርገው ዓይኖቿ መጠናቸው ድንገት ጨምሮ ጨረር መሰል ነገር ለቀቁብኝ።

'ለምን አሁን በዚች ሴኮንድ አይሆንም?!' ብዬ በሆዴ፣ "ምንም ችግር የለም፣ እለሁ!" ብያት ወጥቼ ሄድኩ።

'አሁን የጣዝማ ማር የመሰለ ጠይም ወዝ የሚያመነጨውን የፊት ገጽ ውበቷን የሚመራውን አካል አገኘሁት። ዐይኖቿ ናቸው፣ ዐይኗ! ቢቃ፣ ልክ የተወረወረ አዲስ ጦር!'

ልፍጠን፣ ልሩጥ፣ ልንቀራፈፍ…ሳይታወቀኝ ቀዩን በር አልፌ ጋራዥ ደረስኩ…

# 5

የጋራዥ ሥራዬን በደንብ እየተለማመድኩት መጥቻለሁ። "አንድ ሳምንት" ማለት ብዙ እንደሆነ አሁን ነው የገባኝ። ከሸዋዬና ከደጀኔም ጋር አብሮ መብላትና በአንድ ጣሪያ ሥር መኖር በደንብ እያግባባን መጣ። ኢትዮጵያውያን ለነገሩ የትም ቦታ እንደዚያ ነን። ሕይወት ሥልቷን ጠብቃ ቀጠለች። ከወይዘሮ ማስተዋል፣ ከቢታኒያና ከሚካኤላ ጋርም እንዲሁ። ገንዘብ የማስረክብበት ሰዓት ሲደርስ ያቁነጠንጠኝ ጀምሯል። በስማችን መጠራራትም ጀምረናል። የቢታኒያ ነገር አስገረመኝ። በየቀኑ ሳያት ቁንጅናዋ እያደር ይፈካል። ሌላ ነገርም አለ። የግንዛቤ ደረጃዋም ቀላል የሚባል አይደለም። ሌላ ውበት ፈጠረላት።

'ውበት እንደተመልካቹ ነው ያለው ቅብጥርጥር ማነው? መጥቶ ቢታኒያን ይያትና ያኔ ምን እንደሚል በሰማሁት!'

በሌላ በኩል ግን አንድ ያልፈታሁት ችግር አለብኝ። ብርኪታዊትን ለመርሳት የሚረዳ ነገር እስካሁን አላገኘሁም። በየሰዓቱ በዐይነህሊናዬ እየመጣች ድንቅር ትልብኛለች።ታግዬ እመልሳታለሁ። አሁን ከምሳ በኋላ ኢሳያስና እኔ እሱ መኖሪያ ክፍል ውስጥ ነን። አረፍ ብለን ፖለቲካዊ ወሬ ያዝን። የወቅቱ ፖለቲካ እሱንም እንደ እኔ አስጨንቆታል። ሸዋዬ አብራን ቁጭ ብላ በጥሞና ታዳምጠናለች። ደጀኔ የለም፤ ሥልጠና ሳይሄድ አልቀረም። ኢሳያስ በጥያቄ ጀመረ...

"ሰመረ፣ የቸገረ ነገር ነው የገጠመንኮ። ትላንት ከጌታቸው ማሩና ከዶክተር ተስፋዬ ጋር አብረን ነበርን። 'አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ አብዮት ተካሂዷል ነው የምንለው ወይስ አብዮቱ ተቀልብሷል?'። መግባባት አልቻልንም። እኔና ተስፋዬ ተቀልብሷል ብለን ተከራከርን። ጌታቸው ገና አለየለትም ብሎ ተከራከረን።

ለመሆኑ አንተ ምን ትላለህ?" ትኩር ብሎ እያየኝ ጠየቀኝ።

"ዬ----ል፣ ጥያቄ ሆነው የማይቀርቡ ነገሮች ናቸው ተነጣጥለው የተነሱት። ምክንያቱም አብዮት መካሄዱ እውነት ነው። አብዮት ሌላ ምንም ሳይሆን ገዥና ተገዥ መደቦች እንደ ድሮው አብሮ መሄድ አቅታቸው ሲጠፋፉ ነው። ይህ በአጼው አገዛዝ መውደቅ ተጠናቋል። ይሄው አብዮት መቀልበሱም የሚያጠያይቅ አይደለም።" ቀለል አድርጌ ስመልስለት ኢሳያስ ሌላ ጥያቄ አነሳልኝ።

"ጥሩ፣ በዚህ ላይ እኛም ተግባብተናል። አንድ አብዮት ተቀልብሷል የሚባለውስ ምን ሲፈጠር ነው? ማለቴ መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው?"

"ዬ---ል፣ አብዮቱን ያካሄደው ሕዝብ ቡተወካዩቹ በኩል አብዮቱን የማስቀጠል መብቱና እድሉ ሲነጠቅ አብዮቱ ተቀልብሷል። ጋና፣ ኮንጎና ቺሊ የተፈጸመው ይሄው ነው። ሲአይኤ ያሰማራቸው ወታደሮች መፈንቅለ መንግሥት አካሄዱ። አብዮቱን እንዲመሩ የተቋቋሙትን የመንግሥት መዋቅሮችና የሕዝብ ምክር ቤቶች አፍርሰው የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታን ዐወጁ። በእኛ አገር ለዚህም ሳንበቃ ደርግ ጣልቃ ገባ። ደርግ 'አብዮታዊ ነኝ' የሚለው ዘፈኑ ሊያሳስተን አይገባም..."

ቀና ብዬ ሳየው ኢሳያስ አሁንም ግራ እንደተጋባ ነው። ሽዋዬም ጭንቅ ብሏት ዝምብላ እየተመለከተችን ነው። ማስረዳቴን ቀጠልኩ...

"አንድ አብዮት ተቀለበሰ ለማለት ግን ሌሎች መስፍርቶችም አሉ። ለምሳሌ ለአብዮቱ መለኮስ ምክንያት የሆኑ የቆዩ ማኅበራዊ ቅራኔዎች ሳይፈቱ ይቀጥላሉ። የሕዝቡ የኑሮ ደረጃም ሳይሻሻል ይቀራል። መብቶች ይታፈናሉ። ይሄ ሁሉ በእኛ አገር ገና አለየለትም የሚባል ነገር አይደለም። 'መሰብሰብና ሰልፍ ማድረግ አይቻልም' ከተባለ ይሄው ሦስት ዓመት እያለፈ አይደል እንዴ?" መልሼ ጥያቄ አነሳሁ።

"እና...አላምር...አሁን የምትለን የተቀለበሰውን አብዮት ለመመለስ ሌላ ሁለተኛ አብዮት መካሄድ አለበት ነው?" ሽዋዬ ጠየቀችኝ።

"ትክክ-----ል!!" በአስተውሎቷ ተደስቼ እጇን በአድናቆት ጨበጥኩት።

ዎ፣ ትክክል ነህ። አጼ ኃይለሥላሴ 'አገር የጋራ ነው፣ ሃይማኖት የግል ነው፣ አከብር አለቃህን ተከተል ነጋሪህን...ምናምን ይል ነበር። ደርግ መጣና ደግሞ 'ኢትዮጵያ ትቅደም' አለ። የኤርትራና የኦጋዴን ጦርነቶች በዚህ ምክንያት ቀጠሉ። አሁን ደ'ሞ ትግራይ ተከተለ። አብዮቱ ባይቀለበስ ኖሮ ጦርነቱ

ይቆም ነበር። ቢያንስ የጉሮ መሻሻልም ተስፋ ይታይ ነበር..." ኢሳያስ ተስማማ።

ወሬያችንን ስንጨርስ እኔ ወደ ጋራዥ ስሄድ እነርሱ እዛው ቆዩ። በቀጭኗ መንገድ አልፌ በምሥጢራዊው በር በኩል ጋራዥ ገባሁ። ከአንዱ የሥራ ክፍል የቆየሁ መምሰል አለብኝ። የቢሮዬን በር ከፍቼ ብቅ አልኩ።

###

ጫጫታውና ቅጭልጭልታው ደምቆ ጠበቀኝ። ሰባት ባለመኪና ደንበኞችን አስተናገድኩ። ስድስቱ መኪናዎችን ለጥገና የሚያስገቡ ናቸው። ነጣ ያለ የመስከ ላንድሮቨር፣ ፔዦ 403 የቤት መኪና፣ ዶጅ ታከሲና የወባ መከላከያ ጅፕ ቦታ ይዘው ይታዩኛል። አንደኛው ደንበኛ ደግሞ ጥገናው ያለቀለትን ቤቢ ፊያት የቤት መኪናውን የሚወስድ ነው። በኀይቶም ለባሲ ድጋፍ ተመን አውጥቼ ነገርኳቸው። ሲስማሙ ገንዘቡን ተቀብዬ ደረሰኝ ቆርጬ ሰጠኋቸው። አሁን ትንሽ አረፍ አልኩ። ሰዓቱ ሲደርስ የዕለቱን ገቢ ቆጠርኩ። 'ወደ ወይዘሮ ማስተዋል!'

ሙቼም ወደ እሳቸው ቤት መሄጃ ሰዓቴ ሲደርስ ስሜቴ ሁሉ ልውጥውጥ ይላል። እንዳች ዓይነት ውስጣዊ ግፊት ቁንጥንጥ ያደረገኛል። የቢታኒያን ዓይኖች ዐይቶ የማድነቅ ጉጉት ነው ብዬ ግን ልቤን አልነገርኩትም። ራሴን ልዋሸው አልዋሸው መጠየቅ አስፈራኝ። ድርሻቸውን ቆጥሬ ይዤ በምስጢር በር በኩል ወጣሁ። በጠባቧ መንገድ አልፌ ቀዬ በራቸው ስደርስ ቆም አልኩ።ለማንኳኳት እጄን ስደድ ሳደርግ ከግቢው የሚመጣ ዜማ ነገር ተሰማኝ። እጄን ሰብሰብ አድርጌ ጆሮዬን ቀሰርኩ። ትክክል ነኝ፣ ሕጻናት እየዘመሩ ነው። በደንብ ሳዳምጠው በጣም ተወዳጅ የሆነው የድርጅታችን አብዮታዊ ኅብረ-ዝማሬ ነው...

ይፍሰስ ደሜ ላቤ ይንጠፍጠፍ፣

ይዛል ከንዴ አካሌ ይርገፍ፣

ለታረዘው...... ቀን እስካሳልፍ!

መዝሙሩን ድንገት ስሰማው እንደሁሌው ልቤ ጭልጥ ብሎ ሸፈተ። ልቦናዬ ወደ ወሎ ተሻግሮ ነጎደ። ግራ ዘመም መሆን እዳ ነው። አንዳንዴ የገበሬ ፍቅር ስሜታዊ ያደርጋል። ከሁለት ዓመታት በፊት ይልሱት ይቀምሱት አጥተው አጥንታቸው ፈጦ፣ ቆዳቸው ረግቦ፣ ዐይናቸው ዘቅጦ፣ ከጻእረሞት ጋር

እየታገሉ ያዮኋቸውን ወገኖቼን ፍሊጋ እማተረ። በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ምን ያልደረሰ መከራና ግፍ አለ! ግን እንዲህ እንደሆን አይቀርም። ሁሉም ነገር ይለወጣል...

'ትግልና ድል ለድርጅታችን ኢሕአፓ!' ሆዬ ሞቅ ያለ መፈክር አስተጋባ።

አሁንም ከማንኳኳቴ በፊት ሌላ ጥያቄ አፋጠጠኝ። 'ይህ ድምጽ ከየት ነው የሚመጣው? ከወይዘሮ ማስተዋል ቤት ወይም ግቢ ይሆን? ይህ ከሆነ ከውበት ፈርጧ ቢታኒያ ቤት መሆን አለበት። ቢድርጅታችን መረብ ተይዛለች ማለት መሆኑ ነው።ሕጻናትን እያለማመደች እንደሚሆን ገመትኩ።እንዲሁ ደስ አለኝ። አሁን ወይዘሮ ማስተዋል እንዲሰሙኝ ጠበቅ አድርጌ እንኳኳሁ። ከመቅጽበት መዝሙሩ እልም ድርግም አለ። እዛው ግቢው ውስጥ የሆነ በር ሲጢጢጥ ብሎ ሲከፈት ይሰማኛል። ወዲያው ደግሞ እየሮጠ የሚመጣ ሰው ኮቴ ተሰማኝ። በሩ ንጭጭጭ ብሎ ሲከፈት ከውስጥ ብቅ ያለው ሚካኤለ ነው።በጣም ተግባብተናል። በተገኘው ጊዜ ሁሉ ብቅ ስል እየተሳሳቅን እናወራለን።

"እንዴዴዴ! ሰመረ፣ ልክ ወደ አንተ ልመጣ ስል ከች አልክ!" ሚካኤለ በመገረም እያየኝ ፈገግ አለ።

"ከድካም አዳንኩህ ማለት ነዋ!...ስልክ አለኝ እንዴ?" ጠየኩት።

"አይ፣ ስልክ አይደለም። እህቴ ቤቲን ታውቃት የለ?"

"እ...እዎ...ቢታኒያ?"

"እሷ ፈልጋህ፣እ..እ... እንዴ ጥራልኝ ብላኝ ልመጣ ስል ነው የመጣኸው..."

"ማ...፣ ቢታኒ----ያ?" በደመነፍስ ስጠይቀው ልቤ ፀሐይ እንዳገኘው ቅቤ ቅልጥ ብላ ልትፈስ ምንም አልቀራትም።

"እ----ዎ፣ ቢታኒያ..." ሚካኤለ አረጋገጠልኝ።

"እኔን ነው ኢሳያስን?" ትክክለኝነቱን በመጠራጠር ርብትብት እያልኩ ሌላ የጭንቀትና የጉጉት ጥያቄ አነሳሁለት።

"እረ አንተን ነው። ሰመረ የሚባለውን ጠይሙን... አማራውን ልጅ ነው ያለችኝ..."

ሚካኤለ እንዳልተሳሳተ ገባኝ። በዚያችው ቅጽበት ቢታኒያ የተኮሰችው የስሜት ርችት ፈነዳብኝ።

ልትከዶኝ የምትታገለኝ ልቤ ጭራሽ ቅልጥ ቅልጥልጥ አለች። ሚካኤለ ፊቴ ላይ የስሜት መለዋወጥ እንዳይታዘብ መጠንቀቅ ነበረብኝ። የተሳካልኝ ግን አልመሰለኝም። የምናገረው ጭራሽ አልም ብሎ ጠፋብኝ። መልሴን እየጠበቀ እንደሆነ አውቃለሁ። ግራ ገባኝ...

"ለምን ፈለገችኝ?" የሞት ሞቴን ልጠይቀው ፈልጌ አፌን መልሼ እንቅ አደረኩት።

ልቤ እሱን ቀድማ ቢታኒያ ጋ ስትደርስ ሴኮንድ አልፈጀባትም። ያለፉት ቀናት ወደ አእምሮዬ መጡ። በተዋወቅን በማግስቱ ከምሽቱ 10:00 ሰዓት ላይ ስልክ ተፈልጌ ሄጄ ነበር። ቢታኒያ እንደሁሌው ቤቷ ነበረች። ስልክ ተነጋግሬ ጨርሼ ልመለስ ዞር ስል ቤቷ በር ቆማለች። እግሬ በቆመበት የድንጋይ ንጣፍ ላይ ሽርተት ብሎ የምወድቅ መሰለኝ። ዐይኖቼን እሷ ዐይኖች ላይ ለማሳረፍ ፍርሀት ያዘኝ።

"ሀይ፣ እንደምን ነህ?" ብላኝ አጸፋውን ስመልስላት፣ "ሰመረ ነው ያልከኝ አይደል፣ ስምህን?" እጆቻችን ተጨባበጠው ጠበቅ አድርጋ ስትይዘኝ እንደ ኤሌክትሪክ መላ አካሌን ነዘረው።

ስሜን ሳስታውሳት ደገመችው። መቼም የቆንጆ ሴት ፍርሀቴ መከራ ነው። ዐይኖቼ መድረሻ አጥተው ቶሎ ልለያት ቅልብልብ አልኩ። ባለፈው በእንግሊዝኛ መናገሬን አስታውሳ ምንም ነገር እንዳትጠይቀኝ ተመኘሁ። የእኛ ድርጅት ሰው (ኢ.ፒ) ከሆነች አታደርገውም። ለጊዜው ልትጠራጠረኝ እንኳን እንደማይገባ ማድረግ የነበረብኝን ግዴታ ረሳሁት። የበለጠ ትኩር ብላ ስታየኝ ከንፈሮቼ መርበትበታቸው ስለማይቀር ጭንቀቴን ያወቀችብኝ መስሎኝ ፍርሀቴ ጫፍ ደረሰ።

'ወ----ይ ቆንጆ-----ና!! አንሶላ ከተጋፈፉ፣ ከፀነሱ፣ ካረገዙ፣ ተንበርክከው ካማጡና ከወለዱ አይቀር እንዲህ ነው አሳምሮ መውለድ!' ድምጼን አውጥቼ መጮህ ብችል ደስታውን አልችለውም ነበር።

ደግነቱ ቢታኒያ አልጸናችብኝም።

"እሽ፣ በደንብ ልመድ!" ብቻ ብላ አሰናበተችኝ። ዐይኖቿ ላይ ያየሁትን ስውር መልእክት መተርጎም አቃተኝ። እጄ ላይ ቀልብ የሚነሳ የጥዑም ሽቶ ጠረኗ ቀርቷል። ይገፔው ውልቅ አልኩ። ከዚያ ወዲህ ትውውቃቸን እድገት አሳይቷል። በተለይ አሁን ቢታኒያ እኔን ማስጠራቷ ግን ያልጠበኩት ነው። የማብሰልሰያው ጊዜ አጠረብኝ። እዛው አጠገቧ በሩ ላይ አይደል የቆምኩት? የሚካኤለን እጅ ይገፔ አብረን ገባን። መጀመሪያ የሄድኩት ወደ ዋናው ቤት ወደ ወይዘሮ ማስተዋል ነው።

"እንደምን ዋላ---ችሁ?" ብዬ ወደ ሳሎን ከፍላቸው ገባሁ።

"እንደምን ዋልክ፣ ልጂ?" ወይዘሮ ማስተዋል ጋደም ብለው የጀርመን ራዲዮን የአማርኛ ዜና ይሰሙበት ከነበረው ትልቅ ሶፋቸው ተነሱ። ራዲዮኑ ሽሽሽ እያለ አስቸግሯቸዋል መሰለኝ ከናካቴው ዘጉት። እንዳይነሱ ለምኛቸው አልተቀበሉኝም። ተነስተው ቁጭ አሉ። እንደ ብዙ የአዲስ አበባ ሰው ለዜና የሚተማመኑት የጀርመን ራዲዮን እንደነበር ይገባኛል። በተለይ በዕድሜ ጠና ያሉ ጎልማሶችና አዛውንቶች እንደሱሰ ይከታተሉታል። አዳምጠው ሲዘጉት ታዲያ፣ "ጽም፣ እየ ጉድ! አገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል..." ይላሉ፣ ተሰፋ በመቁረጥና በማማረር። በብዙዎቹ አነጋገር "የንጉሡ የውሻ አሟሟትና የጨካኝ ወታደሮች መንግሥት መሆን" እንደ እግር እሳት የሚለበልብ ጸጸት ተከሎባቸዋል። ጸጸት! ጽም!

"እንዴት ነው ጤንነት?" ሁሌም ጉልበታቸው ላይ እመመኝ የሚሉትን አስታውሼ ጠየኳቸው፣ ብር አውጥቼ ለመቁጠር ሳዘጋጅ።

"ደህና ነኝ! አሁን ተሽሎኛል! ለነገሩ አገር ምድሩ እየታመሰ የኔ በሽታ በምን ትዝ አለኝ ብለህ ነው?" ወይዘሮ ማስተዋል ትክዝ አሉ።

ልቤ ወደ ቢታኒያ እየቀዘፈ አስቸገረኝ። እንደሰሞኑ እህ? እያልኩ ላዋራቸው አልቻልኩም። 'ለምን ፈለገችኝ?' ቀልቤ እየተነሳ ይፈርጣል። አንድም ነገር መገመት አልቻልኩም። ብሩን ስቆጥር ሁለቴ ተሳሳትኩ። ደግሜ ቆጥሬ ለወይዘሮ ማስተዋል ድርሻቸውን አስረከብኩ። ቀጥዬ በደረሰኝ መዝገብ ላይ አስፈረምኳቸው። እሳቸው በተራቸው ብሩን ቆጠሩ። መጨረሳቸውን ዐይቼ ተሰናብቻቸው ልወጣ ስል፣ "አንተ ልጂ፣ ሰመረ..." ጠሩኝ። ትህትና የበዛበት አጠራራቸው እንጀት ያላውሳል።

"አቤት፣ እናቴ...ፈለጉኝ?"

"እዎ፣ እዎ፣ መሸትሸት ሲል ሥራ ከሌለህ አንድ ነገር ላስቸግርህ ነው፣ ልጂ። የምትሄድበት ቦታ ወይ ሌላ ሥራ አለህ?" ከተቀመጡበት ተነስተው መጥተው እጂን ይዘው ጠየቁኝ።

ደንገጥ ብዬ ለአፍታ የምሽት ሥራ ዝርዝሬን በአእምሮዬ ለማስታወስ ሞከርኩ። የቁምነገር ሥራ የሚኖረኝ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ ነው። የኢሕአፓን የሦስት ቀናት የገቢ ድርሻ ለመስጠት ወደ ራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ እሄዳለሁ። የሚታጠፍ ቀጠሮ አይደለም። እስከዚያ ሰዓት ከሆነ ችግር የለም። ይህንኑ ገደብ ይገፎ ነጻ መሆኔን አርግጠኛ ሆኜ ነገርኳቸው።

"ኧረ ምን ነውጣህ ልጂ፣ እስከ ሦስት ሰዓት የማቆይህ በዚህ የግርግር ጊዜ?" ቆና አሉ፣ "እንግዲያውስ

ቢታኒያዬ ጥርሷን አሟት ተቸግራ ነው የዋለችብኝ። አንድ አፍታ ጊወርጊስ ዶክተር መኮንን ከንሊክ አጠገብ ዶክተር ሲንግ አሚባል ሕንድ የጥርስ ሐኪም አለ...ሮጥ ብለህ አሳክመህልኝ እንድትመጣ ልለምንህ ነው..." አሉኝ።

ውስጤ በሌላ የልብ ውስጥ ስሜታዊ የገሞራ ፍንዳታ ተናጠ። "እን----ዴ፣ ማዘር...እንኳን ጊዮርጊስ ለምን ደብረብርሀን አይሆንም?! ምንም ችግር የለም። ይንገሯት፣ ተዘጋጅታ ትጠብቀኝ። እየመሸ ስለሆነ እንድ ሰዓት ላይ መኪና ይዤ በዚህ በውጭ በር በኩል አመጣለሁ..." ምን ያህል እንደተርበተበትኩ አላውቅም።

ጥያቄያቸውን በሆነ እንዳች ዓይነት ሰይጣናዊ ግፊት ድንገት እንዳይለውጡብኝ የተውኩትን ፈጣሪ መልሼ ተማጸንኩት።

"ተባረክ፣ ልጄ! ታዲያ ተጠንቅቀህ...ሰው ዐይተህ መንገድ ላይ እንዳታቆምብኝ...መቼስ አንዳንድ ጠላት አይጠፋም..."

ጠበቅ አድርገው አደራቸውን ሲነግሩኝ ቢታኒያ ከቤቷ ወጥታ መጣች። አዲስ ጥቁር ስማያዊ ከፋይ ጅንስ ሱሪ በቀይ ስስ ሸሚዝ ለብሳለች። ነጠላ ጫማዋን እንዳደረገች ነው። ሐር የመሰለ ረጅም ጸጉሯን በካውያ የተተኮሰ ያህል ልምጥ አድርጋ አበጥራ ወደ ኋላዋ አጋድማዋለች። ከገላ መታጠቢያ መልስ እንደመጣች ሁኔታዋ ያስታውቃል። የገላ ሳሙናዋ ጥዑም ሽታ መንፈሴን ዳንኪራ አስረገጠው። በአጥበት ምክንያት ነጣ ያለውን እጇንና ፊቷን በማዋዣ ቅባት ታለሰልሰዋለች። የጉዞ ዝግጅት መሆኑን ምንም አልተጠራጠርኩም። ሆዴ ፍርስ ያለ መሰለኝ፣ ጉጉትና ድንጋጤ በፈጠረው ብርቱ ወጀብ።

"ሀይ፣ እንደምን ነህ፣ ስመረ?" ብላኝ መልስ ሳትጠብቅ፣ "ማሚ፣ እየነገርሽው ነው?" እናቷን ጠይቃቸው ስትጨብጠኝ ብድግ አልኩላት።ትንፋሼ ቀጥ እንዳይል ሰግቻለሁ።

"አዎ፣ ቤቲዬ... አንድ ሰዓት ሲሆን ይመጣልሻል። አደራ...ልጄ! ወዲያ ወዲህ ማለት የለም!" በመማጸን ቃላጼ አስጠነቀቋት።

'ይህ ተራ አጋጣሚ አይደለም፣ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት የፈጠረው መሆን አለበት...'ብዬ ለራሴ መኪና ለመምረጥና ለማዘጋጀት እንደ ሰጋር በቅሎ በመጨረሻው ፍጥነቴ እየተራመድኩ ወደ ጋራዥ ከነፍኩ።

ቢታኒያንና ቁንጅናዋን የምትመጥን ቆንጆ መኪና መረጥኩ። የአንድ ሀብታም ንብረት የሆነች ምርጥ

ቢትረን የቤት መኪና። ይህችን አልማዝ የመሰሉች የውበት ፈርጥ ጊዮርጊስ አድርሼ ለማምጣት መታደሌ የፈጠረብኝ እረፍት የሚነሳ ስሜት ከደቂቃ ደቂቃ እየናረ መጣ። ለአንድ ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩ ሲትረኗን እየነዳሁ ከጋራዥ ወጣሁ። ኢሳያስ ድንገት እንዳያገኘኝ የረሳኋቸው ታቦታት ይረዱኝ ዘንድ ልጸልይ ዳር ዳር አለኝ። ከቤታቸው በር በውጭ በኩል ትንሽ አለፍ ብዬ አቁሜ ጠበኳት።

'እስቲ ብቅ በይ አንች የዉበት ፈርጥ!' በጀርባው መስታወት የቤታቸውን በር አየሁ።

ቢታኒያ በሩን በጥይት ፍጥነት ከፍታ ወጥታ ውልብ ብላ መጣች። የገቢናውን በር ከፍቼ እንድትገባ ስጠብቃት የኋለኛውን በር በዚያው ፍጥነት ከፍታው ገባች። ተቀምጣ በሩን ከዘጋች በኋላ አካባቢውን በመስኮት መስታውቱ በኩል ቃኘት ቃኘት አደረገች። ምክንያቱን አላውቅም፣ግን ሰው እንዲያያት አለመፈለጓ ወዲያው ገባኝ። ደግሞ ቅልጥፍናዋ አስደነገጠኝ።

'ኧረ በደንብ ተደበቂልኝ፣ ቢታኒያ። የዓይን መዘዝ ብዙ ነው!' ለራሴ ከልቤ የተናገርኩት ነበር።

አጠገቤ ለመቀመጥ አለመፈለጓ ግን ከመቅጽበት አርብሽ አደረገኝ። ድንጋጤ መከረኛውን በራስ የመተማመን ስሜቴን እንደ ፍልጥ ትርትር አድርጎ ቅጥንጥን አደረገው። 'ይችን ይወዳ—ል፣ ሰመረ ማንደፍሮ!' በሆዴ የእልህ ቀረርቶ አቅራራሁ። 'ማንም ተራ ሜካኒክ መሰልኳት እንዴ??' በሆነ ዘዴ የውስጥ ጥንካሬዬንና ኩራቴን ላሳያት ፈለኩ። ከኋለኛው ወንበር አጠገቧ የተቀመጡ የመለዋወጫ እቃዎች ትዝ አሉኝ። መኪናዋ ስትንቀሳቀስ ይንጫጫሉ። ጥሩ ምክንያት እንዳገኘሁ ተሰማኝ።

"እእእ...ይቅርታ ቢታኒያ፣ እቃዎቹ ይረብሹሻል ብዬ ነው እኮ እዚህ ተቀመጭ ያ----ልኩሽ..." አፌ ቀልፍልፍ አለብኝ።

"እህ፣ ምነው ሰመረ? እሱን ቱታህን ለብሰህማ አጠገብህ አልቀመጥም..."

'ም---ምን? ም--ን? ም-----------ንድነው ያለችው?' ልቤ ትርትር አለች።

ከጀርባዬ የምገፋ ያህል በድን ሆንኩ። መኪናዋን ሳንቀሳቅሳት እጆቼና እግሮቼ ፈዘዙብኝ። ቢታኒያ በእሉታ ትናገረው በአወንታ ትርጉሙ አልም ብሎ ጠፍቶብኝ ይወዘውዘኝ ገባ። የኑረዲንን ዳቦ ቤት አልፌን ወደ አውቶቡስ መናኸሪያ ስንጠጋም የማስበው ይህንኑ ነው። "እህ፣ ምነው ሰመረ? እሱን ቱታህን ለብሰህማ አጠገብህ አልቀመጥም..." በደንብ አኘኩት። እየቆየ አዉንታዊ ጎኑ አመዘነብኝ። ትርጉሙን ለራሴ አዳልቼ ፈለኩት። "ጥሩ ለብሰህ ቢሆን ኖሮ አጠገብህ መቀመጥ አይገደኝም ነበር።"

ይሄ ለማንም ተራ ሾፌር ሜካኒክ የሚባል ነገር አይደለም። አባባሏ "ወደ እኔ ለመሮጥ ተዘጋጅ!" የሚል ፊሽካ ሆኖ ተሰማኝ። ነገር ግን እንዴት ብዬ እርግጠኛ ልሁን?

'ቢታኒ-------ያ! የቆንጆዎች እናት! ማንም አይስተካከልሽም!' ደስታም ሲቃ አለው መሰለኝ ሰቅ--ዝ አድርጎ አላናግር አለኝ።

እኔ ዝም ስል እሷ ነጻ ሆና ወሬ ጀመረች። እንደበቷ የተለየ ጣእም አለው። ምልቃቃ ግን አይደለችም። ጓደኛዬን ኢሳያስን አጀንዳዋ አደረገችው። ቤተሰቧና እሷ ኢሳያስን ከአንድ ዓመት ወዲህ ነው የሚያውቁት። ለዛውም አማርኛውን በጣም ባሻሻለበት ጊዜ መሆኑ ነው። ወይዘሮ ማስተዋል የኢሳያስ አነጋገር ግሩም መዝናኛቸው እንደሆነ ገባኝ። እሷም እንዲሁ እንደሆነች ነገረችኝ። አነጋገሩን ልቅም አድርጋ ይዛዋለች። እንደእሱ እየተኮላተፈች ለመናገር ስትሞክር እኔንም የምር አሳቀችኝ።

"አንቺ ማማ አስተውላ...እግርሽ ተሻለው? ለምን ሙቀት ልብስ በደንቢ አይታለብሽም?" ከምላ ጎደል ቁጭ አደረገችው።

ወይዘሮ ማስተዋልን ዛሬ "እርስዎ" ነገ "አንቺ" የማለቱን ልምድ ጨምራ ቀድታዋለች።ከት ከት ብዬ ሳቅኩ። ለነገሩ ምንም ዓይነት ወሬ ይሁን፤ ብቻ ለቅርርባችን ይርዳኝ እንጂ በአድርባይነትም ጭምር እንባዬ ጠብ ጠብ እስከሚል ድረስ ልስቅላት ተዘጋጅቻለሁ። ችግሩ ግን መንገዱ አጭር ነው። ጊዮርጊስ ሳደርሳት ምንም አልታወቀኝም። ይሄ በብርከታዊት ያየሁት ነገር ነው። መቼም በአዲስ የፍቅር ስሜት ሰሞን የጊዜ እጥረትን የመሰለ ጠላት የለም። ሲትረኗን ከመኮንን ክሊኒክ ፊት ለፊት ደብዘዝ ባለ ቦታ ላይ አቆምኳት። ቢታኒያ አሁንም አካባቢዋን በጥንቃቄ ከቃኘች በኋላ ወረደች። እንደ መጫኛ እየተሳበች ወደ ክሊኒኩ ተጣደፈች። ዓይኖቼ ተከተሏት።

'የኔ ቆንጆ፣ በዚህ ውብ ጥርስሽ ስቀሽ ማሳሳቅ ነው እንጅ የምን መታመም አመጣሽ!?' ሳሳሁላት።

ወደ ክሊኒኩ ገብታ ከዓይኔ ስትሰወር ዐይኖቼ እዛው ቀሩ። ወዲያው ከቆምኩበት በግራ በኩል ቆሊ የመሰለ ነገር ውልብ አለብኝ። አንድ የሆነ ሰው ከጭለማው ጠባብ መንገድ አመር ብሎ ሲወጣ ትኩር ብዬ ዐየሁት። የሐኪሞች ነጣ ያለ ግዋን ለብሷል። ጀርባውን ሰጥቶኝ ወደ ክሊኒኩ የሩጫ ያህል ሄደ። አረማመዱን ስመለከት የማውቀው ሰው መሰለኝ። አእምሮዬ ሰውዬውን ያየበትን ቦታ ፍለጋ ተንከራተተ። ዐይኔን እንደተከልኩበት የክሊኒኩን በር አልፎ ሲገባና ወደ ቀኝ ዞር ሲል በደንብ ታየኝ። ቢታኒያ ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ እጅ ለእጅ ተጨባበጡ። ተመልሰው ሁለቱም ከዓይኔ ጠፉ...

'ስዩም ከበ---------ደ!!' ለራሴ ስሙኝ ሳይታወቀኝ ሀይኔን ልጠራጠረው ፈለኩ። 'ባለፈው ደግሞ ፍቅሬ ዘርጋው!'

ስዩም ከበደ ማለት ከኢሕአፓ በተለይ ከኢሕአሠ መሥራቾች አንዱ ነው። የፍልስጤም ነጻነት ተዋጊ ድርጅትአልፈታሕ በሽምቅ ውጊያ ካሰለጠናቸው የመጀመሪያዎቹ 13 ታጋዮችም አንዱ ስዩም ነው። በሥራ ምክንያት አውሮፓ ቆይቶ አዲስ አበባ በቦሌ በኩል ነው የገባው። አሁን የኢሕአፓ የከተማ ታጣቂ ክንፍ ዋና ኮማንደር ነው። የአዲስ አበባ በይነቀጠና ኮሚቴ ጸሐፊ እያለሁ ሦስቴ ወይም አራቴ ስብሰባ ላይ ተገናኝተናል። ኮማንደር ከሆነ በኋላ ግን ለደህንነት ሲባል ከተደራቢ ኮሚቴዎች አባልነት ወጥቷል። ቢታንያ ቀጠሮ በሚመስል ግንኙነት የጨበጠችው ሰው ይህ ነው። አእምሮዬ ቅብዥርዥር አለብኝ_

'ምን አገናኛቸው? የድርጅት ሥራ? ፍቅር? ወይስ ሌላ ዝምድና?' ልቤ ስሙን በማላውቀው ረብሻ ጥልጥል አለች፤ 'የድርጅት ሥራ ይመስላል። ግ---ን እንደዚያ ከሆነ ለምን ያን ያህል መኳኳል አበዛች? አዎ፣ ፍቅረኛዋ መሆን አለበት። እኔን እያ ሞኜን እንደ አመላላሽ ሾፌር ተጠቀመችብኝ ማለት ነው። በምትኩ' ቅናት እንደ መኝገር ብልት አድርጎ በላኝ።

ከሴኮንድ ሴኮንድ እየቆየሁ ሳስበው ግን ትክክል አልነበርኩም። የቀድሞዋ ፍቅረኛዬ ብርኪታዊት አንዳንዴ በምሰራቸው ስህተቶች ንጭንጭ ብላ የምትሰጠኝ ማስጠንቀቂያ እውነት ሆኖ አገኘሁት። "ሰሙዋ፣ በናትህ ይገርሃለሁ፣ ለመፍረድ አትቸኩል!! ለመናገር አትቸኩል!! ለመቀየም አትቸኩል!! ሁሌም መጀመሪያ ላይ ለሌላ ሰው ትክክል የመሆንን እድል መስጠት ልመድ!" ትለኝ ነበር፣ ደጋግማ። ትክክል ሳትሆን አትቀርም። እንዳንዴማ የምሠራው ስህተት ገደል ጫፍ ሁሉ አድርሶኝ ለጥቂት አተርፋለሁ። አሁንም ምንም ነገር በእጄ ሳይኖር በቅናት መብሰልሰሌ መልሶ እኔኑ አሳፈረኝ።

'ምን ዓይነት ተልካሻ ፍጡር ነኝ?!' ራሴን ወቀስኩት።

መቼም ቢሆን ቅድሚያ ሰጥቼ መመልከት ያለብኝ ድርጅታዊ ሥራን ነው። በቃ፣ የቢታኒያና የስዩም ግንኙነትም ይህ ሊሆን ይችላል። ልክ እንደ እኔና ሽዋዬ ማለት ነው። ሐቁን ልድረስበት ወይም ራሴን እያጽናናሁ ይሁን ግን አርግጠኛ አይደለሁም። ብቻ ዓይኖቼ ትክክለኛውን ነገር እንደሚያሳዩኝ ተስፋ አድርጌ ወደ ክሊኒኩ እንደተከልኳቸው ቀረሁ። ወደ ፊት ሰገ---ግ፣ ወደ ኋላዬ ለጠ--ጥ እያልኩ ፈተሽኩ። ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አይታየኝም። በመሀሉ ሁለት ሰዎች ከጀርባ በኩል መጥተው መኪናዋን ተደግፈው ሲቆሙ ዕይታዬ ድርግም አለ።

'እሀ፣ ምን ለማለት ፈልገው ነው? መኪናዋ ውስጥ ሰው እንዳለ ዐይተው የለም እንዴ?'

ንድድ ብሎኝ መስኮቱን እንኳኩቼ ላነቃቸው ሞከርኩ። ወይ ንቅንቅ፣ ተገትረው ቀሩ። በጣም ተናድጄ ጥሩንባውን አስጮኸኩት። ወይ ፍንክች። ሞተር ላስነሳ እጄን ወደ ቁልፉ ሰደድ ሳደርግ ግን አንድ ድንገተኛ መረጃ ብልጭ አለልኝ። ሰፌም ከበደ እዚሁ አካባቢ ነው። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች የእሱ ጠባቂዎች ናቸው። የኢሕአፓ የከተማ ታጣቂ ከንፍ አባላት።

'እዚህም ደረጃ ተደርሷ---ል!?' መራራ የምጸት ሳቅ ከት ከት ብዬ በውስጤ ሳቅኩ።ደግነቱ ቢታኒያ ብዙ አልቆየችም። ራሴን አረጋግቼ ጠበኳት።

ስለ ጥርስ ሕመሟ እየጠየኳት እሷ እየመለሰችልኝ ወደ ሰፈራችን ተመለስን። ስንመለስ ደግሞ ጊዜው የበለጠ አጠረ። የኑረዲንን ዳቦ ቤት ስናልፍ ድንገት የድምጿ ቅላጼ ተቀየረ...

"ሰመረ፣ በጣ---ም ይቅርታ! አንድ ነገር ላስቸግርህ ነው።" ዐረፍተነገሩን እንጠልጥላ መልሴን ጠበቀች።

"ያ---ው፣ ስትነግረኝ ነዋ የማውቀው..." ትንፋሺ ከሀዲዱ ሲወጣ ታወቀኝ።

"ማከሰኞ ጠዋት ላይ ሥራ ይኖርሀል፣ እስከ ሦስት ሰዓት ባለው ጊዜ?"

'ምን ልትለኝ ይሆን፣ አምላኬ? ይሄ ነገር የምሥራች ይዞ የሚመጣ ይመስላል። "ምንጊዜም ጧት ላይ ነጻ ነኝ።" ብያት ወደ ጋራዡ ለመታጠፍ የመኪናዋን ፍጥነት ቀነስኩት።

"እንደዛ ከሆነ ሱሉልታ እንዴ ደርሰን እንድንመጣ ልጠይቅህ ፈልጌ ነው..." አለችኝ ትህትና በበዛበት ድምጽ።

'እንኳን ሱሉልታ ለምን ጎንደር አይሆንም! ቢታኒያ፣ ትቀልጃለሽ እንዴ? ተገኝቶ ነው?' ሆዴ ይሄን አስተጋብቶ፣ "ምንም ችግር የለም። ደርሰን እንመጣለን!" አልኳት።

# 6

የማከሰኞ ጧቱ የቢታኒያ ቀጠሮዬ እንደ ኤሊ ተጎተተብኝ። ሁለት ቀናት በመከራ ገድያለሁ። ገና አንድ ሙሉ ቀን ይቀራል። ምሳዬን ከሽዋዬና ከደጀኔ ጋር በላሁ። ኢሳያስ ሌሊት ጉለሌ አድሮ ነው የመጣው። የፖለቲካ ቢሮውን የስብሰባ ቃለጉባኤ ሲይዝ አንግቶ መመለሱ ነው። አልጋው ላይ በደረቱ ለሽ ብሏል። እንደዚህ ተኝቶ ሳየው ሁሌም ያሳዝነኛል። እጥፍጥፍ ብሎ አጥንት የሌለው ነው የሚመስለው።የተወልኝን መልእክት ሽዋዬ ነገረችኝ።

"ዛሬ ምሽት አንድ ሰዓት ላይ ጓድ ተስፋዬ ደበሳይና ጓድ ዘርዑ ከሕሸን ይፈልጉሀል። የምትገናኙበት መኖሪያ ቤት ከምትኩ ፋርማሲ አጠገብ ያለው ቪላ ነው። ጉዳዩ የጅማ ጭፍጨፋ ሪፖርትህ እንደሚሆን እገምታለሁ።"

እስቤበት ሰጠብቀው የቆየ ግንኙነት ነው። በሪፖርቴ ያካተትኳቸው አንዳንድ ጽንሰ-ሐሳቦችና መደምደሚያዎች ምቾት አልሰጧቸውም። ኢሳያስ በደንብ እንድዘጋጅ ነግሮኛል። ሪፖርቴን እንዴ ገረፍ ማድረግ ይኖርብኛል። ጋራዥ ትንሽ ሠርቼ ወደ ምድር ቤት እመለሳለሁ። ሽዋዬንና ደጀኔን ቻው ብያቸው ወጣሁና በቀጭኗ መንገድ ወደ ጋራዥ ተመልሼ ሄድኩ። በምስጢራዊው በር በኩል ቢሮ ገብቼ ቁጭ አልኩ። ሥራ ስጀምር ግን ሰዓቱ ከንፍ አውጥቶ ጥርግ አለ። ወደ ምድር ቤት መመለስ አልቻልኩም። በጋራዡ ዋና በር በኩል ወጣሁ። ልቤ ትክክለኛውን ፍላጎቴን አልደበቀልኝም። ወደ ወይዘሮ ማስተዋል የሄድኩት ቢታኒያን ለማየት ነው። እንደተመለስኩ ቁጭ አላልኩም።

·፡ ፡ደ ምትኩ ፋርማሲ...

አሁን መጠቀም ያለብኝ የዕለት የመስክ ጥገና የሚደረግባትን ናሚካኒክ ጉርድ ላንድሮቨር ነው። ለዚህ ተብላ በተለየ ሁኔታ የተዘጋጀች ናት። ለደርግ/መኢሶን ከተትል አተመችም። ከዓይን ወጣ ያለች ወይም በብዙ መንገድ ከዕይታ የራቀች ናት። በሚገረም ሁኔታ ብዙ የጸጥታ ሠራተኞቻቸው መኪናዋን ፈጽሞ አይጠራጠሯትም። በትክክል የጋራዥ አገልግሎት መኪና መሆኗን የሚያምኑት ገና የብረት ቅጥልጥሏንና ድምጻቸው የሚንሿሿውን መፍቻዎች ሳጥን ሲመለከቱ ነው።

ጋራዡ በምሽት ፈረቃ ሠራተኞች ተማሙቆ ጠበቀኝ። ኢሳያስ ከሠራተኞቹ ጋርም ይሁን ቢሮ ውስጥ አይታየኝም።

'ኢሱዬ፣ አሁንም እዛው ምድር ቤት ለሽ እንዳለ ነው ማለት ነው።' እንደገና አዘንኩለት።

በሩን አልፌ ወደ መሀል ገባሁ። ቅርቤ የነበሩት ጎይቶም ለባሲና አንድ ሁለት ጓደኞቹ ናቸው። በእጅ ምልክት ሰላምታ ሰጥቻቸው ወደ ላንድሮቨሯ ሄድኩ። ሞተር አስነሰቼ ወደ ደጁ ስወጣ አዲስ አበባ የጀንበር ብርሀንን አሰናብታ ድብዝብዝ ብላለች። የመንገድ አምፖሎቿን አብርታ ጠበቀችኝ። ሰማዩ ንጹህ ነው። ካፊያ ነገር ግን ብን ብን ይላል። ጉዞ ወደ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ቀጠሮ!

ወደ ቀኝ ታጥፌ ዋናውን አስፋልት ያዝኩ። ከሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት መቋቋም ወዲህ አዲስ አበባ ውስጥ ለውጥ አለ። በየቀኑ የማይከሮፎን ድምጽ ተለይቷት አያውቅም። የስብሰባ ጥሪ ብዛት እንደጎርፍ ነው...

"መላው የቀበሌያችን ነዋሪዎች በሙሉ..." ትንሽ እንደሄድኩ ትራፊክ መብራቱ ጋ ስደርስ ጆሮዬ ላይ አንባረቀብኝ።

ከዚህ የደርግ/መኢሶን ፖለቲካዊ ጋብቻ ወዲህ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ቋንቋም እየተቀየረ መጥቷል። አብዮታዊና ግራ ዘመም ቃላትና ሀረጋት አጥለቅልቀውታል። የቀድሞው ንጉሥና አገዛዛቸው የሚወገዙባቸው ቃላት ምሬታቸው እየጨመረ መጥቷል። የፍቅር ዘፈን እየቀረ በአብዮታዊ ዘፈኖች በመተካትም ላይ ነው። ብዙዎቹ ዜማዎች ደስ አይሉም። እኔና ኢሳያስ "ባዶ ጋን" በምንለው የደርግ ብሔረተኛ መፈክር "ኢትዮጵያ ትቅደም!!" መንፈስ የተቃኙ ናቸው።

መናኸሪያ ምትኩ ፋርማሲ ስደርስ መኪናዋን አቁሜ ቦታ አስያዝኳት። ለማስመሰል ያህል የመፍቻዎችን መካከለኛ የብረት ሳጥን አውርጄ በመያዝ ወደ ቀጠሮው ቤት የብረት በር አመራሁ። በትንሿ መግቢያ በር በኩል ብርድ ልብስ የተከናነቡ ሽማግሌ ዘበኛ ይታዩኛል። አካሉ ከማይታየኝ ሰው ጋር ወሬ ይዘዋል። ሳንኳኳ የማይታየኝ ሰው ተንቀሳቅሶ ሊከፍትልኝ መጣ። በሩ ተከፍቶ ስንተያይ ማንነቱን ወዲያውኑ አወኩት...

'ኦ----ው_እንበሳው ደጀኔ!' አልኩ በሆዴ።

ከደጀኔ ጋር ምሳችንን አብረን ነው የበላነው። እዚህ ስንገናኝ ግን አንተዋወቅም። ስለዚህ ሰላምታ ብቻ ሰጥቼው ወደ ግቢው ገባሁ። ቤቱ ድምጽ የሚባል ነገር አይሰማበትም። እንዲት የፊት ገጿን እስከ እፍንጫዋ በቆብ የሸፈነች አጭርና ወጣት ልጅ መጥታ ተቀበለችኝ። ሳሎኑን አብረን አቋርጠን ቀይ እምቱል የሚረጭ መብራት ወዳደበዘዘው ንባብ ክፍል ስንገባ ልጅቱ ተመለሰች።

"ሐ--ይ፣ ጓዶች እንደምን አላችሁ!" አልኩ እንደገባሁ።

ዶክተር ተስፋዬ ጀርባውን ሰጥቶኝ ቁጭ ብሏል።። ከፊት ለፊቱ ባለ ትልቅ ጠረጴዛ ጀርባ ደግሞ ዘርዑ ኪሕሸን አለ። በትግርኛ "ኪሕሸን" "ይሻለኛል ወይም ተሻለኝ" ማለት ነው። "ደበሳይ" ማለት ደግሞ "መጽናኛዬ"። ኢሱ ነው ትርጉማቸውን የነገረኝ። ዘርዑ በቁመት ረጅም ከመሆኑ የተነሳ ቁጭ ብሎም የቆመ ይመስላል። ለስላሳ ጺም የወረሰው የፊቱ ቅላት መብራቱ ሥር ይንተገተጋል። ሁለቱም አቀርቅረው ማስታወሻ ደብተሮቻቸውን ያነባሉ። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ወንበር ስቤ ዘርዑ አጠገብ ተቀመጥኩ። እኔም ሙታንታዬ ውስጥ ያስቀመጥኩትን አነስተኛ ማስታወሻ ደብተሬን አወጣሁ። ሁለት ስለሆኑ በጥያቄ ማአበል እንደሚያዋክቡኝ ገመትኩ። ወዲያው ግን በራሴው ሐሳብ መልሼ ተናደድኩ።

'ኤጭ! ምን ዓይነቱ ጥጥ ልብ እህያ ነኝ!?' አእምሮዬን በሆዴ ወርፌ ልኩን አስያዝኩት።

ያም ሆኖ በደንብ መነጋገር አለብኝ። "ሰሙየ፣ ይሄን ችኮላህን አትተውም!?" የብርከቲ መንፈስ መጥቶ በቁጣ ጮኸብኝ። ይሄን ሳስብ አንድ የሆነ ታዋቂ ሰው አባባል ትዝ አለኝ። "ንበዝ ሰው ለጥያቄዎች በሚሰጠው መልስ ይታወቃል። ብልህ ሰው ግን በሚጠይቀው ጥያቄ ይመዘናል።" ነቃ ብዬ የሚሉኝን ለመስማት ተዘጋጀሁ።

ዶክተር ተስፋዬ ስለአዲሱ ሰፈሬና ሥራዬ አጭር ነገር ሲደንቡ ያህል ጠየቀኝ። በጥቅል ጥሩ እንደሆነ ስነግረው ወደ ዋናው የተጠራሁበት ጉዳይ ገባ። ነጭ የዕይታ መነጽሩ አሁንም ዓይኖቹ ላይ ነው። የማስታወሻ ደብተሩን ገጾች ገልበጥ ገልበጥ አድርጎ አንዱ ላይ ቆመ። መናገር ሲጀምር ጉዳዩ እንደጠበኩት ነው። የጅማ ጭፍጨፋ። ቀጥታ ሄዶ የነካው የሪፖርቴን ማእከላዊ ነጥብ ነው። የጭፍጨፋው ፖለቲካዊና ርእዮተ-ዓለማዊ ትርጉም። ሪፖርቴን በአእምሮዬ ለአፈታ ጨለፍለፍ አደረኩት...

"የጅማው የደርግ/መኢሶን ጭፍጨፋ ሦስት ርእዩተ-ፖለቲካዊ ዝንባሌዎችን ያሳየናል። እነርሱም፣ የተጠቀሱት ሁለት ኃይሎች ጥምረት በአገሪቱ የማኅበራዊ ኃይሎች አሰላለፍ ላይ ለውጥ ማስከተሉን ነው። ያም የደርግ ጠበንጃና የመኢሶን ብዕር መጣመራቸውን ነው። ይህ በሌሎች የግራ ኃይሎች

ሀልውና ላይ ጥቃት መሰንዘር መጀመራቸውን ያሳያል። መኢሶን የትኛው ዜጋ ከየትኛው ፖለቲካ ድርጅት ጋር እንደቆመ የቋንቋና የርእዮት ትርጉም ይሰጣል። ደርግ ጠበንጃውን እቀባብሎ ይተኩሳል።"

ለእፍታ እሰብ አድርጌ ወደ ሁለተኛው ነጥብ አለፍኩ...

"ሁለተኛ፣ ጭፍጨፋው በአጋጣሚ የተካሄደ የፖሊስ ጸጥታ የማስከበር ተግባር አይደለም። ይልቁንም ሥር የወጋ የአስተሳሰብ መሠረት ያለው ነው። ደርግ 'የኢትዮጵያ ትቅደም'ን መንፈስና ዓላማ በማንኛውም መንገድ መቃወም አይቻልም ብሏል። ጭፍጨፋው ይህንን ውልና አቅጣጫ የለሽ መርሕ ለማስከበር ጭካኔውን ያሳየበት ነው። መኢሶን በበኩሉ፣ 'ዲሞክራሲ በገደብ' የሚል እምነቱ የማይደፈር መሆኑን ያስመሰከረበት ነው። ይህ ጥምረት በሁለት ንዑስ ከበርቴ ማኅበራዊ ቡድኖች የተፈጠረ ነው። ነገር ግን እገዛዙ ጦር መሣሪያን የሥርዐቱ ቁልፍ ዋስትና ማድረጉ አደገኛ ዝንባሌውን ይመሰክራል..."

ወደ ሦስተኛውና ምናልባትም ዋናው ነጥቤ አለፍኩ...

"ሦስተኛ፣ የሕዝቡ አመጽ በዚህ ጥምረት ጭካኔ ተቀጭቷል። ይህ ግን የሕዝቡን ደካማነትና የጥምረቱን ጥንካሬ ጨርሶ የሚያሳይ አይደለም። ይልቁንም አሁን ባለው የኃይሎች አሰላለፍ አንድ ትልቅ ቁም ነገር ያለው መልእክት አስተላልፏል። ያም የከተማ አመጽ የቱንም ያህል ጉልበት ቢኖረው ዋናው መፍትሄ አለመሆኑን ያሳያል። በግልጽ እነጋገር የከተማ አመጽ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት አይችልም። ይህ ምን ማለት ነው? ድርጅታችን በ1964 የበርሊን ጉባኤው ያጸደቀው በመስከ የተራዘመ ትጥቅ ትግል ስትራቴጅ አለን። ስትራቴጂው ከከተሞች ባህርያዊ አወቃቀር አንጻር ሳይንሳዊ መሆኑን ያሳያል..."

ከሞላ ጎደል በደንብ ያስታወስኩት መሰለኝ። ወደ እነርሱ ቀና አልኩ...

"ጓድ አላምረው..." በኮድ ስሜ ጠርቶኝ ጀመረ ዶክተር ተስፋዬ፣ "ጓድ አላምረው...ስለ ጅማ ሕዝብ ጭፍጨፋ በቂ ሥዕል ሰጥተህናል። አሁን ስለ ድርጊቱ እናንሳም። የምንጠይቅህ ማብራሪያ በጭፍጨፋው አተረጓጎምህ አንድ ሁለት ነጥቦች ላይ ነው። 'የከተሞች ባህርያዊ አወቃቀር ከኢሕአፓ ትግል ዋነኛ ሥልት ጋር አይጣጣምም' የሚለውን ነጥብህን አስረዳን እስቲ..."

ጉሮሮዬን አጸዳድቼ መናገር ጀመርኩ...

"ከዚህ ማጠቃለያ የደረስኩት በጅማ ጭፍጨፋ በተማርኳቸው የሚከተሉት አምስት ምክንያቶች ነው።" ብዬ ማስታወሻ ደብተሬ ላይ አተኮርኩ፣

"አንደኛ፣ በአሁኗ ኢትዮጵያ የሁሉም ከተሞች ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ መሠረት አነስተኛ ንግድና የመንግሥት ሥራ ናቸው። እነዚህ ሥራዎች ከጠቅላላው የገቢ ምንጭ አውታር የ75 በመቶ ድርሻ አላቸው። ይህም ማለት ጠቅላላው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የድርጅታችን አባላትና ደጋፊዎች ጭምር በመንግሥት ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጥገኛ ናቸው። ስለዚህም ረዥም ሕዝባዊ አመጽ መልሶ ለኢኮኖሚ ጉዳት ይዳርጋቸዋል..."

የማስታወሻ ደብተሬን ገጽ ገልበጥ አድርጌ ልቀጥል ስል በሩ በኃይል ተበርግዶ ተከፈተ። ተቀብላ ያስገባችኝ ሴት ብቅ አለች። "ፖሊስ!!" ሹክ አለችን። ብድግ ብድግ ብለን ስንነሳ ዘርዑ፣ "መኪና ይዘህ ነው የመጣኸው፣ አይደል?" ሲጠይቀኝ በአዎንታ መልሼለት የሚለኝን ጠበኩ። "እንግዲያውስ ጓድ ኢሳያስ እዚሁ ፋርማሲው አካባቢ ይጠብቅሃል። አንተ ወደዚህ በመምጣት ላይ እያለህ ደውዬለት አግኝቼዋለሁ። አብራችሁ ጉለሌ ቢሯችን ሂዱና ኢሳያስ ያስገባኻል። ከዚያ ወደ እናንተ የሚመጡ ንብረቶች ተዘጋጅተው ታገኛላችሁ። ጭነህ ተመለስ።"

ትእዛዙን ተቀበልኩ። ከዚህ የዘለለ የሚያቆየኝ ነገር አልነበረም። ሳላስበው የእጅ ሰዓቴን ዐየሁ። ከመጣሁ ወደ 45 ደቂቃዎች ቆይቻለሁ። ተሰናብቻቸው ወጣሁ...

***

ላንድሮቨሬን አስነስቼ ወደ ዋናው አስፋልት ስገባ ኢሳያስ ከምትኩ ፋርማሲ አጠገብ ብቅ አለ። ፖሊስ ወይም ሌላ የመንግሥት ጸጥታ ኃይል ግን አይታየኝም። መኪና ለምን እንዳልያዘ አልገባኝም።እንቅልፉን ሳይጨርስ እንደመጣ ፊቱ ላይ ይታወቃል። እንዲህ ሲሆን ዓለም አስጠልታው ቁጭ ትላለች። ማንንም አያናግርም። ፊቴን ወደ አውቶቡስ መነኸሪያ አዞርኩ...

ከእነ ዶክተር ተስፋዬ ተለይቼ ከወጣሁ በኋላ ስሜቴ ትክክል አልነበረም። የድርጅቱ ነገር ከመጠን በላይ አሳሰበኝ። የፕሮግራም ጥራት ችግር መኖሩ አሁን የበለጠ ገብቶኛል። ይህ ማለት ሕዝብን የሚያናግሩበትና የሚመሩበት ቋንቋ አጥቶ ዲዳ ከመሆን የተለየ አይደለም። ባጭሩ አጀንዳ ማጣት። አጀንዳ ማጣት ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ በጣም አደገኛ ነው ብቻ ተብሎ አይታለፍም። የህልውናው ፈተና ጭምር ነው።

የችግሩ ምንጭ ሄዶ ሄዶ አሁንም የሚያርፈው በደርግ የመሬት አዋጅ ውጤት ትንበያ ላይ ነው። የድርጅቱ የውስጥ አንድነት በአጉል አተረጓጎም እንዳይናጋ ስጋት ገባኝ። በእርግጥ የመሬት ዐዋጁ የ1964ቱን የኢሕአድ/ኢሕአፓ የበርሊን ጉባኤ ውሳኔዎች አደጋ ላይ ጥሏቸዋል። ያኔ የፕሮግራሙ መሠረት የአጼ

:ኃይለሥላሴ አገዛዝ ነው። አገዛዙ ወድቆ የተተካው በደርግ ነው። ደርግ ሆዬ መንግሥት አቋቁም ወደ ካምፑ ይመለሳል ብለን ስንጠብቅ ጨርሶ ሳይገመት መሬትን በአዋጅ የመንግሥት ንብረት አደረገው...

"ይህ ጥያቄ ከተመለሰ የትግል ትርጉሙ ታዲያ ምንድነው?" የብዙዎችን አቋም ለኾዋኾዌ ጨዋታ አጋለጠው።

በዚህ ተወስኖ ቢቀር ባልከፋ። ጥያቄው የቀሰቀሰው ማዕበል አሲምባ ደረሶ ለጋውን ኢሕአሠ ይንጠው ገባ። ብርሃነመስቀል አንጂቱ እየጤሰ ለኢሳያስ ነግሮታል። ኢሳያስ ደግሞ ለእኔ። በኤርትራ በርሀ በኩል አንድ ዓመት ተኩል ሙሉ ተጉዘውና የድሮ መልካቸውን በፀሐይ ንዳድ አቃጥለው ደረሱ። መንገድ ላይ ጀምሮ ግን የጥንስሱ ቀይሠራዊት አባላት በሐሳብ ተከፋፈሉ። ተስፋዬ መኮንን መቼም የተረገመ እርጉም ነው። የአሲምባ አስቸጋሪ የገደላገደል ሕይወት ተጨምሮበት ሆድ ባሰው። ውስጥ ለውስጥ አንድ ተስፈንጣሪ ቡድን ፈጠረና ብርሃነመስቀልን በጥያቄ ሰቅዞ ያዘው...

"መሬት የመንግሥት ሀብት ሆኖ ከታወጀ እኛ የማን ጎፈሬ ነቃሾች ነን? እዚህ ጠበንጃ ይዘን እንደ ዝንጀሮ ገደል ለገደል የምንከራተተው ለምንድነው? ነጻ የወጣን ሕዝብ ነጻ ማውጣት ብሎ ነገር አለ? እኛ በትጥቅ ትግል ሥርዐት ለመለወጥ የተነሳነው ደርግ አሁን የሠራውን ለመሥራት አይደለም? ድርጅቱ በቂ ማብራሪያ እንዲሰጠን እንፈልጋለን...።"

ብርሃነመስቀል ለራሱ ግራ ተጋብቷል። ጥያቄውን እንደ አጓጉል ንዝንዝ ተመለከተው። የእሱ ልብ ያለው ሊጠራ በዝግጅት ላይ ባለው የኢሕአፓ መለስተኛ ጉባኤ ላይ ነው። ከዚህ ጉባኤ በፊት በግሉም ይሁን በዋና ጸሐፊነቱ ለተስፋዬ መኮንን ቡድን የሚሰጠው መልስ የለም። ተስፋዬ የብርሃነመስቀልን ዝምታ አልወደደውም። እንዲያውም እንደ ትምክህት ቆጠረው። መቼም ብርሃነመስቀል ዝም ካለ ዝም ነው፤ ሐውልት መስሎ ቁጭ ይላል። በዚህ የተበሳጨው ተስፋዬ እርምጃ ወሰደ። በመከራ የተገኘውን ጠበንጃ ይዞ ከሰባት ጓደኞቹ ጋር እጁን ለመንግሥት ሰጠ። መጥቶ ቁጭ አላለም፣ ከደርግ ጋር ከርስትና ተነሳ...

'ወይ ነዶ! ገና በማለዳው እንዲህ ያለ ከህደት?!' መሀል ከተማ አስፋልት ላይ መኪና እየነዳሁ መሆኔን እስከምረሳ ድረስ ቅጥል አልኩ።

ጸጸት እንዳይመጣ ልጸልይ አማረኝ። ሁኔታው ኢሕአፓን መስቀልኛ መንገድ ላይ አቁሞታል። ይህ ሲታየኝ ፍርሀት ለእፍታ ናጠኝ። ከዚህ ያላነሰ ድንብርብር ያለብኝ ደግሞ ብርሃነመስቀል የወሰደው እርምጃ ነው። እዛው አሲምባ ወታደራዊ ፍርድ ቤት አቋቁሞ በተስፋዬ መኮንንና በጓደኞቹ ላይ ክስ መሠረተ። ለዚያውም በሌሉበት ነው የከሰሳቸው። ክሱን ያየው ፍርድ ቤት የአንድ ቀን ውሎ ምርመራ

አደረገ። በመጨረሻ የሞት ፍርድ ወሰነ...

"ሞ.........ት?! አልገባኝም፤ ኢሱ። የሞት ፍርድ ማለት ምን ማለት ነው?" ኢሳያስን በድንጋጤ ስጠይቀው ትዝ ይለኛል።

የሚያረካ መልስ አልሰጠኝም። ማንም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅት አባል የሚሆነው በፈቃደኝነት ነው። ድርጅቱን የሚተወውም በፈቃደኝነት ነው። የፖለቲካ አቋምን መለወጥ ይቻላል። ግትር የሆነ ሃይማኖትን እንደመለወጥ አይደለም። እናም "መናፍቅ" አያሰኝም። የተስፋዬ መኮንንና የጓደኞቹን ኩብላላ በበኩሌ የማየው በዚህ መነጽር ነው። ድርጊታቸውን ምናልባት "ክህደት" የሚያሰኘው ነገር ቢኖር የኢሕአሠ ንብረት የሆነውን ጠበንጃ ይዘው መኮብለላቸው ነው። ያም ሆኖ ብርሃነመስቀልን ሊያስጨንቀው ይገባ የነበረ ጉዳይ አይደለም። ከተጨነቀ የሚያስጨንቀው ሰብዓዊ የሆነው የኩብለላቸው ምክንያት እንጅ ቁሳዊ የሆነው ጠበንጃ መሆን የለበትም።

"ኢሱ፣ ትልቅ ሰው ሲሳሳት...የሚባለው ነገር እየደረሰ እንዳይሆን። ብርሃነመስቀል ጥሩ ሀልዮተኛ እንጂ ጥሩ ጀኔራል አይደለም ማለት ነው። ፍርዱ ትክክል ነው ቢባል እንኳን ሌላ ጥያቄ ይነሳበታል። ደርግ ሜጉላ ቤት የገባውን ተስፋዬን እንዴት አድርጎ ሊያስገድለው ነው?" የመገረም ጥያቄ አነሳሁለት።

"ስሜ፤ ቢቃ...የሆነው ሆኗል። የብርሐነን የሞት ፍርድ ውሳኔ ማእከላዊ ኮሚቴው አላጸደቀለትም። ተስፋዬ መኮንንን በተዘዋዋሪም በቀጥታም አነጋግረው 'ጥፋቱ የራሱ የብርሃነመስቀል አያያዝ ችግር ነው' በሚል ሻሩበት። ሙተው ይሻላል..." ኢሳያስ እንደዚህ ቀን የፖለቲካ ጉዳያችን ስልችት ብሎት ዐይቼው አላውቅም።

"ቡ-ሉ---ው!! ይሄም ሌላ አደገኛ ስህተት ነው። ብረት ይዘው መኮብለላቸው ያለቀለት እውነት ነው። ይህ ሆኖ ሳለ የብርሃነመስቀልን የሞት ፍርድ ላለማጽደቅ ሲባል ከደርግ ብብት የገቡ ሰዎችን ሄዶ ማነጋገር ማለት ምን ማለት ነው? ሞኝነት? ዲሞክራሲያዊነት? ፍትሀዊነት ወይስ ልጅነት?" ከንፈሬ በንዴት ተንቀጠቀጠ።

ይሁን እንጂ ይህ እሰጣ ገባ በድርጅቴ ላይ ያለኝን እምነት የሚነካ አይደለም። ትንሽ ቅር የሚለኝ አንድ ነገር ግን አለ። ገና በማለዳው የዚህ ሁሉ ብጥብጥ ሰበብ የመሬት ዐዋጁ መሆኑ።ደርግ ይህንን ዐዋጅ ሲያወጣ ከልብ የኢትዮጵያን ችግር ከሥሩ እነቅላለሁ ብሎ አይደለም። ከዚያ ይልቅ ኢሕአፓንና ሌሎች የግራ ኃይሎችን አጀንዳ ለማሳጣት አልሞ ነው። ሌላም አንድ አሳሳቢ መረጃ ደርሶኛል። ተስፋዬ መኮንን ስለ ኢሕአሠ መፈጠርና አሲምባ መድረስ ለሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ዝርዝር አድርጎ ነግሮታል።

ሻለቃው አራት ገጽ ደብዳቤ ጽፎ እዚያው እሲምባ ድረስ ለብርሃነመስቀል ላከለት። "እና አብዮቱን ተጋግዘን ግቡን እንዲመታ እናድርግ። በዚህ የአብዮት እፍላ ወቅት ጠበንጃ ይዛችሁ ተራራ ለተራራ መንከራተትን ምን አመጣው?" በልጅነቴ አንድ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያየሁት ሥእል ትዝ አለኝ። "ቀበሮ መሬት ላይ ሆኖ በፍርሀት አጥር ላይ የቆመውን አውራ ዶሮ "ጓደኞች እንሁን..." እያለ ሲለምነው የሚያሳይ ነው። የሻለቃው ደብዳቤ ማእከላዊ ነጥብም ይሄው ነው። ብርሃነመስቀል መልስ አልሰጠውም፣ ለማእከላዊ ኮሚቴም አላቀረበው። ለምን? መልስ የለም።ስጋት ናጠኝ...

'ደርግ እየተሳካለት ይሆን? ከተሳካለት በእኛ በኢሕአፓዎች ቀድሞ የማየት ችግር ብቻ መሆን አለበት።'

ኢሳያስ ምንም ሳያነጋግረኝ ወዲያው ወዲያው ያዛጋል። ወደ ጉለሌ የፖሊት ቢሮው ጽሕፈት ቤት እየተጠጋሁ ነው።እስካሁኗ ሴኮንድ ድረስ ይሄ መዘዘኛ ዐዋጅ አእምሮዬን አለቀቀውም። በበኩሌ የዐዋጁ መውጣት አያስጨንቀኝም። ምክንያቱም የለውጡ አንድ ገጽ ብቻ ነው። ከበድ ያለ ክርክር ይጠይቅ ይሆናል። ይህንን አዲስ ሁኔታ ተርጉሞ ከኢሕአፓ ፕሮግራም ጋር ማጣጣም ግን የማይቻል ነገር ሆኖ አልታይህ አለኝ። ይሄንን ሳስብ አንድ ያላሰብኩት ጥያቄ በአእምሮዬ ሽው አለብኝ...

'ብርሃነመስቀል እንዴት በዚህ ላይ የሚያስማማ ንድፍ-ሐሳብ እስከአሁን አልቀመረም?'

ብርሃነመስቀል ይሄንን ማድረግ እንደማይሳነው አምናለሁ። ነገር ግን አልቻለም።ስለዚህ የድርሻዬን በበቂ መጠን ከመሥራት የተሻለ ምንም አማራጭ የለኝም። ዐይኔ ጎርቦ ደም እስኪመስል ድረስ ሌሊትና ቀን እነበብኩ። በተጨማሪ ነጥቦች ራሴን ለማሰማን ሞከርኩ። የምቀርጸውን አንብሮ መቀበል አለመቀበል የእነርሱ ፋንታ ነው። ችግሩ ግን ሁሉም መሪዎች ከሌኒናዊ ፓርቲ ወጣ ወጣ ብለው በጥቃቅን የዕለት ተዕለት ጉዳዩች ተውጠዋል። የደህንነት ስጋቱም ተረጋግቶ ለማሰብ የሚያስፈልገውን አደብ ነስቷቸዋል።

'ወ------ይ ጣ----------------------ጣ!!' አልኩ ለራሴ።

ከዋናው መንገድ ወጥቼ ወደ ግራ ታጠፍኩ። ቀጭን የኮረኮንች መንገድ ስይዝ መኪናዋ ኡኡኡ ማለት ጀመረች። ጭለማው ዋጥ አደረገን። ከአንድ ትልቅ ቪላ ቤት ስንደርስ ከግቢው የጎን በር ፊት ለፊት ሞተር አጥፍቼ ቆምኩ።ኢሳያስ ወርዶ ወደ በሩ ሄዶ፣ ከዘበኛው ጋር ይመስለኛል፣ አጭር ነገር ተነጋግሮ ተመለሰ። ተያይዘን ሄደን ገባን። ዮሴፍ አዳነ በአንደኛው ክፍል ቁጭ ብሎ አገኘነው። ወደ ሌላ ክፍል ይዞን ሄዶ የተቆለፈውን በር ከፈተው። ወደ መሳለሚያ የምወስደው እቃ በሁለት ካርቶኖች ተዘጋጅቶ ወለሉ ላይ ተቀምጧል። ዮሴፍ ፈጠን ብሎ አንደኛውን ካርቶን ሲከፍተው ከብዙ አባላትና ደጋፊዎች

የተሰበሰቡ ንብረቶች ዐይኖቻችን ሥር ዝርግፍ አሉ።

የወርቅ ጉትቻዎች...የአንገት ሐብሎች...የጣት ቀለበቶች...የእግር አልቦዎች...የጥንት ማሪያቴሬዛ ሳንቲሞች...በደርዘን በደርዘን የታሸጉ ብእሮች ከነቀለም ቢልቃጦቻቸው...ሽጉጥቶች ከነመሰል ጥይቶቻቸው...የኢትዮጵያ ብር...የአሜሪካን ዶላር...የእጅ ቦርሳዎች...

የሌለ የለም። ዐይኔ በተለይ ያረፈው ግን በጣም ቀላል በሆነች አንዲት አስትሪያ ሰራሽ አውቶማቲክ ሽጉጥ ላይ ነው። እኔ የታጠኩት ኮልት-38 አሜሪካን ሠራሽ ሽጉጥ ነው። ከብደቱና ትልቅነቱ አይጣል ነው። ይዤው የማልዞረው ለዚህ ነው። ሽጉጧን አንስቼ እያገላበጥኩ አየኋት። ዘጠኝ ጥይቶች አሏት። መቀየር እንደምፈልግ ዮሴፍን ነገርኩት። ሽጉጤን ለንብረት ክፍሉ መልሼ መውሰድ እንደምችል ነገረኝ። እዛው ላይ ታጠኳት። ሁለተኛው ካርቶንም በተመሳሳይ ንብረት የታጨቀ ነው። ተሸክመን አውጥተን ላንደሮቨሬ ላይ ጫንነው። ኢሳያስ የፖሊት ቢሮ ስብሰባ ቃለጉባኤ ስለሚይዝ እዛው ቀረ። ቻው! ብያቸው ወደ መሳለሚያ ነዳሁ...

'ይሄን ይሄን ይሆናል እንግዲህ ከተማ ላይ የመሆናችን ጥቅም የሚሉት እነ ጓድ ዘርዑ!' ቅር አለኝ።

ኮረኮንቹን መንገድ ጨርሼ ዋናውን አስፋልት ያዝኩ። በማስታወቂያ ሚኒስቴር በኩል ልነዳ አስቤ ብርክታዊት ትዝ ስትለኝ ሐሳቤን ቀየርኩ። እንዲሁ መንገድ ላይ ድንገት ዐይታኝ መጥታ የምታንቀኝ የምታንቀኝ ይመስለኛል። ሌላም አስተውዬው የማላውቀው ነገር ይፈታተነኛል። መንገድ ላይ የማያቸው የአዲስ አበባ ሴቶች...። ለተንኮሉ ድሮ አስቤው ስለማላውቅ መሰለኝ ብዙዎቹ ከእሷ ጋር ይመሳሰሉብኛል። ከተማ ወጣ ባልኩ ቁጥር ስደነግጥ እውላለሁ። ጭንቀት የፈጠረው ሊሆን ይችላል። መንገዴን ቀይሬ ነዳሁ። አንዱን አንስቼ ሌላውን እየጣልኩ ጎጃም በረንዳን አልፌ የመናኸሪያን አስፋልት ያዝኩ። ልክ የመነኸሪያውን መስቀልኛ መንገድ ስይዝ ችግር መጣ። ከቀኝ አቅጣጫ የመጣ መኪና ተወርውሮ ደርሶ መንገዱን ዘጋብኝ። የሞት ሞቴን ፍሬን ስይዝ ላንድሮቨሯ ሲጢጢጢጢጥ ብላ ቆመች።

"ምን ነካ---ው ሰውዬውን?" ደራሽ ቁጣ ገንፍሎብኝ በመጨረሻው ድምጼ ጮኽኩ።

የሁለታችንም መኪናዎች አፍንጫዎች ሊላተሙ ለትንሽ ተረፍን። የአንድ ስንዝር ያህል ርቀት ብቻ ተጠጋግተው ቆሙ። በደመነፍስ እየተንዘፈዘፍኩ ወደዚያኛው መኪና እየሁ። ጥቁር ቀለም የተቀባ አዲስ የመንግሥት ላንድሮቨር መኪና ነው። ፖሊስ ወይም መከላከያ። ከሁለቱ አይወጣም። ከየት እንደመጣ የማላውቀው የድንጋጤ ላብ ግንፍል ብሎ ጀርባዬን እያራሰው ወረደ።

'ወይኔ! በቃ፣ ተከታትለው ያዙኝ ማለት ነው። ለእኔ ችግር የለውም ሲናይድ መርዜን ውጬ እሞታለሁ።

የድርጅቱን ንብረት ግን አስያዝኩት ማለት ነው።ወ–ይ—ኔ!' አጄን ሰድጄ ኮሊታዬን ስነካካ ደግሞ ሲናይድ እንከብሉ በቦታው የለም። ላቤ ወደ ውስጥ ሲንቆረቆር ተሰማኝ።

በመብራቱ ቦቃታ ወደ ሾፌሩ አቅጣጫ አማተርኩ። እሱም ወደ'ኔ። ሳይታወቀኝ የኋላ ማርሽ አስገብቼ ሸሸሁ። ተታኩሼ መሞቴ የማይቀር ሆነብኝ። ቦታ ስለቅለት ጥቂት ላንድሮቨር ቀስ ብሎ ወደ መንገዱ ገባ። የቀኝ መስመሩን ሲይዝ ሾፌሩ ወደ እኔ ዞረ...

"አንተ ሰካራም፣ ፊትህን አዙረህ ነው እንዴ መኪናውን የምትነዳው?"

እንኳን አጸፋውን ልመልስለት ማየትም አልፈለኩ። ድንጋጤ ደሜን ከቱበው አውጥቶ ይረጨዋል። ማርሹን በፍጥነት ቀይሬ "አላይም አልሰማም" ብዬ ወደፊት ተፈተለኩ። ትንፋሼ ወደ ቦታው የተመለሰው ከኑረዲን ዳቦ ቤት ስደርስ ነው። ታሪክ ራሱን ይደግማል ማለት ነው? ጌታቸው ማሩ ትዝ አለኝ። ኢሕአፓ የዛሬ ዓመት በታወጀበት ምሽት እያሱ አለማየሁን ተመሳሳይ ፈተና ገጥሞት ነበር። ወደ ግራ ታጥፌ ጭልልታ ወደ ዋጠው ጋራዥ ገባሁ...

# 7

ማከሰኞ ንጋት ላይ ቅገሪት የሚመስል እንቅልፍ ረበሸኝ። ስወድቅ...ስነሳ ብቻ ይታየኛል። እንደምንም ታማዩ ነቃሁ። ምድር ቤት መኖሪያ ክፍሌ ውስጥ ነኝ። እንደ ልጅነት ዘመኔ "በስመ.....ዐብ!" ማለት አሁን የለም። መጀመሪያ መጥቶ አእምሮዬ ውስጥ ስንቅር ያለው የቢታኒያ ቀጠሮ ነው። መጨረሻውን ማየት ንፍቅ ብሎ ናፈቀኝ። ከፍቅረኛ ገላ ከተለየሁ ወራት እየተቆጠሩ ነው። ብርኪታዊትን በህልሜ ሳላያት ሌሊቱ ነግቶ አያውቅም። ቡተለይ ድምጿን በሬዲዮ የሰማሁ ቀን አለቀልኝ። ሙሉውን ሌሊት አትለየኝም።

'ብርኪቲዬ፤ ም---ሱ---ኪ---ን!! እንደዋናዋ ብርኪታዊት ፊጣኑ ጊዮርጊስን ሆኜ ደርሸላት ነበር። አሁን ግን እንደ ይሁዳ በክህደት ድንጉት ቁጭ አድርጌያት አልም አለሁ...' ሆዴ በጣ---ም ተንቦጫበጨብኝ።

ለአፍታ እንደገና በዐይነ ልቦናዬ መጣችና መጥፋቱ ረብሿት ደጋግማ ቤቱ ብቅ ትላለች፤ ታጣኛለች። ሲቸግራት ደጋግማ ደውላ ልታገኘኝ ትሞክራለች። ደብዛዬ አልም ሲልባት ምን እንደምትልና እንደምትሆን ምስሏን በአእምሮዬ ላመጣው ሞከርኩ። ረዘም ያለው የቀይ ዳማ ፊቷ ፍም ይመስልና ለሌኮንድ የማይለያትን ነጭ የፅድታ መነጽሯን በንዴት ታወልቀዋለች። ከበድ ያሉት ከንፈሮቿ ይንዘፈዘፉና ራሷን አንድ ጥያቄ ትጠይቀዋለች። "ቢቃ፤ ሰመረየ ካደ---ኝ?!" መልሷ ምን እንደሚሆን አላውቅም። ስገምት ግን "አ---ይ፤ እኔ አንደ ሰሙዬ መቻኮል አልፈልግም። በትእግስት እጠብቀዋለሁ!" የምትል ይመስለኛል። ከዚያ የቀድሞ አከራዮቼ ቤት ዣቢታ ቅስሙ በተሰበረ አነጋገር መልእክት ስትነግራቸው ይታየኛል...

"እደራ፤ከደወለላችሁ በጣ---ም እንደምፈልገው ንገሩልኝ!"

ብርከትዬ አሳዘነችኝ። ግን ምንም ማድረግ አልችልም። እንደ አብርሐም በግ መስዋእት ያደረኳት ለሌላ ከእሷ ለሚልቅ ዓላማ ነው። ህሊናዬ ከመጠን በላይ ንጹህ ነው። ከቀን ቀን እየቀነሰ የመጣው ትዝታዋ ሊገነፍልብኝ ዳር ዳር ያለው መሰለኝ።

'ኖ-----ኖ----ኖ! ብርከቲዬ፤ ቻው! ቻው!' የሸፈነኝን ብርድ ልብስ ግልጥልጥ አደረኩት።

በተገላበጥኩ ቁጥር ሲጥ ሲጥ ከሚለው ሸቦ አልጋዬ ቀልጠፍ ብዬ ተነሳሁ። በዘይትና በብርሻቶ የተበለሻሸውን ጥቁር ሰማያዊ የሥራ ቱታዬን ለበስኩ። ቆዳ ጫማዬን ተጫማሁ። ጫማዬም እንደቱታዬ በዘይት ምክንያት አቧራ ቀም መልኩን ለውጧል። ምንም አይመስለኝም። እንዲያውም ማንነቴን ልውጥውጥ ስላደረገው ደስ ይለኛል። ጠቆር ያለ ሰማያዊ ቆቤን ደፋሁ። ከምድር ቤቴ ወጥቼ የደጀኔንና የኢሳያስን ከፍሎች አቋርጬ ጣውላውን በር ከፍቼ በቀጭኗ ምሥጢራዊ መንገድ ወደ ጋራዥ...

'ቢ--ታ---ኒ---ያ!! የቁንጅና ድንበር!!' ወደ እሷ እየሄድኩ መሆኔን ሳስበው ሆዴ በሆነ ዓይነት እንግዳ ስሜት ብር---ዝ አለ።

የእሷን ቁንጅና የሚመጥን መኪና ፍለጋ አማተርኩ። የፈረንጆቹን ፊያት 127 ተጠግና አልቃለች፣ ፈረንጆቹ ግን በዛው ብን ብለው ቀርተዋል። ተባረው እንደሚሆን እየገመትኩ መኪናዋን ከጋራዥ ይዣት ወጣሁ። ኢሕአፓ በማያውቅው ጉዞ ወደ ሉሉልታ መውጣቴ ነው። ትንሽ ቅር እያለኝ የጋራዡን በር ዘግቼ መኪናዋን ወደ ዋናው የመሳለሚያ አስፋልት ነዳኋት። በቀስታ ወደ ቀኝ ታጥፌ ከኑረዲን ዳቦ ቤት ሳልደርስ የቀኝ መስመር ይዤ አቆምኳት...

'አ----ው ቢታኒያ መኮንን...ይሄ ላንቺ በጣም ሲያንስሽ ነው!' ውስጤ ሽለላውን አቀለጠው።

ገና ጀንበር አልወጣችም እንጂ በደንብ ነግቷል። ዐይኖቼን አንዴ ፊት ለፊቴ ባለው የንጋት ትርኢት ላይ አሳረፍኩ። በዚያውም ቢታኒያን ከጀርባዬ ስትመጣ ማየት አለብኝ። የቀኙን የጎን መስታወት ሰረቅ አድርጌ እያየሁ መጠበቅ ያዝኩ። ቤታቸው ከቆምኩበት በግምት ሰባ ወይም ሰማኒያ ሜትር ያህል ይርቃል። እሷው ነች እዚህ ቦታ ቆሜ እንድጠብቃት የነገረችኝ። የሰው ክትትል የምትሸሽ ስለመሆኗ አሁን እርግጠኛ ነኝ። በሆነ ምክንያት ከፊል ሕቡእ ገብታለች። ይህንን ጥቂቶች ብቻ የታደሉትን ቁንጅና ይዛ ከክትትል መሰወር እንዴት እንደሚሳካላት ግን እንጃ። “ግመል ሰርቆ አጎንብሶ” አሉ!

'ለነገሩ ዘንድሮ ማን ሕቡእ ያልገባ ይገኛል!?' ወደፊት ለፊቴ አማተርኩ።

በጣም በርካታ ሰዎች ኑረዲን ዳቦ ቤት ፊት ለፊት ይተራመሳሉ። የዳቦ ወረፋ ነው። የአፍሪካ የዳቦ

ቅርጫት ትባል የነበረችው ኢትዮጵያ ሕዝቧን አሰልፋ ዳቦ ማደል ከጀመረች ሦስተኛ ዓመቷን መያዟ ነው። ይሄንን ሳስብ ምንጊዜም ውስጥ አንጀቴ በንዴት ይጤሳል። ድርቅ የተፈጥሮ ምክንያት አለው። ርሀብ ግን ሁሌም የተዛባ ፖለቲካዊ መስመርና ፖሊሲ ውጤት ነው። ይህ በኢኮኖሚስትነቴ የማምንበት ነው።

ዐይኔን ወደ ጎን መስታወቱ ስመልስ ቢታኒያ መኮንን! ቀስት መስላ ብርርር እያለች ስትመጣ አየኋት።

ከአንዴም ሁለት ሦስቴ ፍቅር ደርሶብኛል፣

ዛሬም በእው ላይ ነው ይጫወትብኛል!

የጥላሁን ገሠሠ ድንቅ ዜማ ነው። ለአሁኑ ሁኔታዬ የማስጠንቀቂያ ደወል ሆኖ ሲጮኽ ተሰማኝ። እንደገና የጎን መስታወቱን ተመለከትኩ። አሁን ቢታኒያ ሙሉ በሙሉ ታየችኝ። ሰማያዊ ከፋይ ጅንስ ሱሪ አድርጋለች። ቀለል ያለ ሽፍን ጥቁር ቆዳ ጫማ ተጫምታለች። ረጅምና ማበጠሪያ ሲያርፈበት ልንቀጥቀጥ የሚለው ጸጉሯ አሁን አይታየኝም። ጭንቅላቷን በቀይ ሻሽ ድብን አድርጋ አሥራ ሸፍናዋለች። ከአንገቷ እስከ አፍንጫዋ ድረስ ነጭ ስካርፍ ጠምጥማለች። ለቀቅ ያለና ቁንጠኛ የዝናብ ኮት አድርጋ ከአቁማዳ የሚፎካከር ቢጫ ቦርሳ አንግባለች። ስም ልሰጣት ከጀለኝ። መዘዘ? መለሎ? በተወለድኩበት አካባቢ በሚነገር ቃል ደግሞ "አሩጊ?" በፍጹም ቃል አይገልጻትም።

'ቢ----ታ----ኒ----ያ! ቢ---ታ---ኒ--ያ!! ይህችን የመሰለች እምቡጥ ጽጌረዳ ለምን በአይሁድ ከተማ ስም "ቢታኒያ" ብለው ሰየሟት?' ጸረ-ጽዮናዊ፣ ግራ ዘመም፣ ማርክሲስትም ስለሆንኩ፣ ክርስቲያንነቴንም ስለሰረዝኩ ስሟ ቅር አሰኘኝ።

ወይዘሮ ማስተዋል የእጹብ ድንቅ ልጃቸውን ቁንጅና የሚመጥን ስም እንዴት እንዳጡ አልገባህ አለኝ። ይህንን ሁሉ ከራሴ ጋር ሳወራ የሚገረመው በማያገባኝ ጣጣ ገብቼ መጨነቄን መርሳቴ ነው።'ይሁን፣ ምናባቱ...ቢ---ታ---ኒ---ያ ቆንጆ ናት!! የቆንጆ ሴት ነገርስ የማይመለከተው ወንድ አለ እንዴ!?' ራሴን እንደምንም አታልዬ የተነሳሳ መንፈሴን ለማረጋጋት ስታገል ቢታኒያ ደረሰች...

"ሰመረ፣ ደህና አደርክ? ወይኔ ጉዴ...አስጠብቄህ እንዳይሆን..." የገቢናውን የቀኝ በር ከፍታ በፍጥነት ገብታ ከአጠገቤ ተቀመጠች።

'ቤቲ...እንኳን ለጥቂት ደቂቃዎች ለዓመታትም ብጠብቅሽ አይከፋኝም!' አልኩ በሆዴ፣

"ሰላም ነሽ፣ ቢታኒያ? ኧረ አላስጠበቅሽኝም፣ ገና አሁን መድረሴ ነው..." ልዋሽ አልዋሽ አላውቅም።

'አጠገ---ቤ ተ-ቀመ-ጠ-ች?!' የማየው ነገር እውነት መሆኑን ማመን አቃተኝ።መኪናዋን ወደፊት አንቀሳቀስኳት። የኑረዲንን ዳቦ ቤት ስናልፍ ቀልቤን ሰብስቤ ወደ ቢታኒያ ተመልስኩ። አሁን በራሷ ምርጫ አጠገቤ ተቀምጣለች። ስለጤንነታችን አጭር ነገር አወራን። አንጠጦን እስከምንወጣ ድረስ ብዙ አልተነጋገርንም። በምናየው ነገር እየተሳብን ዝምታን እንደምንመርጥ ገምቻለሁ። ቁንጅናዋን ዘጠኜ ከማድነቅ አልፌ ሌላ ጥያቄ ለራሴ አነሳሁ...

'ለምንድነው ወደ ሱሉልታ መሄድ የፈለገችው? ምናልባት ይሄ ጃንያ የሚያክል ቦርሳዋ የዲሞክራሲያን ቁጥር 8 ዕትሞች ይዛበት ይሆን? መጀመሪያውኑ ግን በትክክል የእኛ የኢሕአፓ ሰው ነች?ለምንስ ብቻዋን ቤት ዘግታ ትውላለች?'

ለእነዚህ ጥያቄዎች በቂ መልስ ሳላገኝ እንደገና ሌላ ጥያቄ ይመጣብኛል። ቢታኒያ፣ የምድር ቅኔ! ልቤ ከብርክታዊት ጋር አንድ በአንድ ሊያወዳድራት ከጀለ። ይህንን ማድረግ ግን ደስ አላለኝም። 'በቃ፣ ቢታኒያና ብርክቲ ሁለት የተለያዩ የወንዜ የሐበሻ ቆንጆዎች ናቸው። እንደ አትሌት ይህችኛዋ ትቀድማለች፣ ያችኛዋ ትከተላለች የሚባል ነገር አይደለም!' ራሴን ገሰጽኩት።

ከፍለሐገር አውቶቡስ መናኸሪያ ስንደርስ ወደ ግራ ዞርኩ። መነኸሪያው የዓመት በዓል ገበያ መስሏል። መንገደኛው ሕዝብ ከሸኝውና ከእቃ ተሸካሚው ጋር ይርመሰመሳል። ሳንቡሳ ሻጩ...ሲጋራ ነጋዴው... ጋዜጣ አዟሪው...ለማኙና ኪስ አውላቂውም ግርግሩን የተሟላ አድርገውታል። በቀስታ ለመንዳት ስገደድ ጋዜጣ የመግዛት ሐሳብ መጣብኝ። ለወትሮው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥንቡን ጥሎ በአስር ሳንቲም ይቸበቸብ ነበር። አሁን ለምስ ያህል እንኳን ከዓይን ጠፍቷል። ምክንያቱ ለብዙ አንባቢዎች የታወቀ ነው። የኢሕአፓና የመኢሶን የርእዮተ-ዓለም ጦር ሜዳ በመሆኑ።

"ኤጭ፣ ይሄ የመናኸሪያ ትርምስ መቼ ይሆን የሚያልፍለት?" ቢታኒያ ንጭንጭ ብላ ከሰው ዓይን ላለመግባት የፈለገች ይመስለኛል ጥቁር የፀሐይ መነጽሯን ከቦርሳዋ አውጥታ አደረገችው።

"ያ---ው፣ ሕዝቡ ሲያልፍለት ነዋ፣ ቢታኒያ።" ብዬ ልመልስላት ከከንፈሬ ከደረሰ በኋላ አባባሌ ፖለቲካዊ መልእክት እንዳይኖረው ሰግቼ መልሼ ዋጥ አደረኩት። "መቼም አያልፍለት..." ብያት ዝም አልኩ።

መናኸሪያውን አልፈን ጎላ ሚካኤል አካባቢ ስንደርስ የሰው ትርምስምስ የዕለቱን ውሎ ጀምሮታል። ሰው እዚህም እዚያም በእጁ ምናምን ይዞ ከል ከል ይላል። አልፎ አልፎ የብረት ቆብ የደፉና ሙሉ ወታደራዊ የደንብ ልብስ የለበሱ ወታደሮች ይታዩኛል። ብትንትን ብለው ቆመው ወጭ ወራጁን በዐይነቁራኛ ይከታተላሉ። ውትድርና እንጀራቸው በመሆኑ ግዳጃቸውን እየተወጡ ነው ብዬ ማሰብ

ትቻለሁ። ደርግ የእነርሱ መንግሥት ስለሆነ ብቻ የሚሠሩ ሆነው ይታዩኛል። ጅማ እንዳየሁት ወታደሮቹ ሲቪሉን ሕዝብ ከመጤፍ አይቆጥሩትም። ኢትዮጵያ እኛቸው ላይ የመሆኗ ትርጉም ነው። የጅማ ወጣቶች ጥይት እያፏጨባቸው ይዘምሩት የነበረው መዝሙር ትዝ አለኝ......

*ሳንጃ ይዟል በእጁ፡ ሳንጃ ይዟል በእጁ፥*

*ወገኑን አራጁ!*

ዳገት መውጣት ስንጀምር ነፍሴ ፊቷን መልሳ ወደ ቢታኒያ አዞረች። ያደረገችው መነጽር ዐይኖቿን ስለደበቀብኝ ደስ አላለኝም።'ቢታኒያ፥ቁንጅናዋ ሰማኒያ ከመቶ ምናምን ዐይኖቿ ላይ እንዳለ አታውቅም እንዴ?' በልቤ አጉረመረምኩ።እውነቴን ነው። ዐይኗ ከአፎቱ መዥረጥ ተደርጎ የወጣ ሰይፍ መስሎ ይታየኛል። የተቃራኒ ጾታዎች ተፈጥሮ መቼም ሁሌም የሚገርም ነው። ፍርሀትና ተስፋ እየተፈራረቁ ደነከሩብኝ።'ቢ--ታ--ኒ--ያ! ያፍዝዝ ያደንዝዝ ወይስ ያስደንግጥ ያስበርግግ አባዜ ነው ያለባት ወይስ ሁለቱም?'

መኪናዋ የእንጦጦን ዳገት ስትወጣ የቀበሌ ድምጽ ማጉያ ሲጮህ ተሰማኝ። ሁለታችንም ወደ ድምጹ አተኮርን። የሕዝባዊ ስብሰባ ጥሪ ነው። ደርግ ያቀደው የአዲሱ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር ማቋቋሚያ የቀበሌ ምርጫ ነው። የአካባቢው ነዋሪ እንዲወጣ ይቀሰቅሳል። ሁለታችንም ለቅስቀሳው ፍላጎት ማሳየታችን ገረመኝ።'በቃ፥ ቢታኒያ የእኛ ሰው ናት ማለት ነው፣ አልም ያለች ኢፒ ሳትሆን አትቀርም!' አልኩኝ በሆዴ።

ዞር ብዬ እንደዘበት ጨረፍ አድርጌ ዐየኋት። ብልጭ ያለችው ጀንበር ብርሀኗን ግንባሯ ላይ አሳርፋባታለች። አዲስ መዳብ የሚመስለው የቆዳዋ ቀለም ቦግ ብሏል። የፀሐይ ብርሀኑን ለመከላከል ግንባሯን በእጇቿ ስትከልለው ቀለሟ ደበዘዘብኝ። ዛሬም የለበስኩት ያንኑ ዘይት የጠገበ የሥራ ቱታ ነው። ያለ እኔ ግብግብ አጠገቤ ስትቀመጥ ግን አላመነታችም። ትርጉሙን ማግኘት ከበደኝ። ያም ሆነ ይህ ቢታኒያ አሁን አጠገቤ አለች። ቀጥሎ ምን እንደሚመጣ አላውቅም።

'አንድ ነገር አለ ልበ-----ል?'

እንጦጦን ወጥተን ስንጨርስ ሌላ የሰው ትርምስ ተቀበለን። የመኪና መዐት ሰልፍ ሠርቶ የመንገዱን ጠርዝ ይዞ ተደርድሯል። ፍተሻው ተጧጡፏል። ፖሊሶቹ በመስክ ጃኬት ላይ ዘጠኝ ብርድ ልብስ የሚወጣው ካፖርት ደርበውም በሚጠብሳቸው ቁር ይንዘፈዘፋሉ። እኔ የትኛውንም ፍተሻ ለማለፍ ችግር የለብኝም። ዕድሜ ለብርሻቶዮ፣ የሚጠረጥረኝ የለም። ቢታኒያ ቦርሳዋን ይዛ ወረዳ እየከፈተችው

ለፍተሻ ስትቀርብ ሆዴ ፈራ። መቼም ኢሕአፓ ከሆኑት አንድ ተልእኮ ላይ መሆን አለባት። 'ዲሞክራሲያ ጋዜጣ ይዛ ይሆን?' ጠረጠርኩ።ጥያቄዬን ለሁለተኛ ጊዜ አነሳሁት። ነገር ግን ሳልጨርሰው ከቦርሳዋ የጎን ኪስ የሆነ ነገር ስታወጣ አየኋት።

አሸጋቸው ገና ያልተከፈተ የቅባት እቃና ቫዝሊን። ለፖሊሷ ሰጠቻት። የፖሊሷ ፊት በደስታ ፍልቅልቅ አለ። ቢታኒያ ቦርሳዋን ከፍታ እንድትፈትሸው ስታቀርብላት ፖሊሷ አታይም። እቃዎቹን እንደብርቅ ነገር እያገላበጠች እያየች በወሬ ይዛታለች። የተከፈተውን ቦርሳ ሳታይ እንዲሁ ገፋ አደረገችው። ቢታኒያ "ቻው!" ብላት መጥታ ተሳፈረች። ወደ ሱሉልታ...

'ሳትፈ---ተ---ሽ?' አንድ ምሥጢር እንዳላት የበለጠ ጠረጠርኩ።

ምክንያቱን በትክክል አላውቅም። እንጦጦን ካለፍን በኋላ የሁለታችንም መንፈስ ተነቃቃ። የደራ ወሬ ጀመርን። እያንዳንዱ የምትናገረውን ቃል እንደሁሌው ከሥሩ ሙዚቃዊ ቃና ያጅበዋል። በጣም የተገረምኩበት ሌላ አሁን ያስተዋልኩት ትርኢትም አለ። ስትስቅ የሚታየው ከፊት ለፊት የላይኛው ጥንድ ጥርሷ ሳቋን ጣፋጭ ያደርግላታል። ይሄንን ሳስተውል ቅናቴ ነፍስ ዘርቶ ብድግ አለብኝ። ጉድለቷን መፈለግ ያዝኩ። የውስጥ አካሏን አላውቅም፣ ከውጭ ግን አንድም ህጸጽ ማግኘት አልቻልኩም። በሰው ሠራሽ ብልሀት የተፈጠረች ሥዕል መሰላ ታየችኝ።

'ማን ይሆን ቦይ ፍሬንዷ?' ከውስጤ ገንፍሎ የመጣ ቅናት ሊጠብሰኝ ከጃጀለው። 'ኤጭ፣ ምን ዓይነቱ ሰንበሌጥ ፍጡር ነኝ?! እንዴት በተወሳሰበ የፖለቲካ ሥራ ትከሻው የጎበጠ ሰው እንደዚህ ያስባል!?' ንድድ ብሎኝ በኢሕአፓ አነጋገር "ግለ-ሂሴን" ለራሴ አቅርቤ ዋጥ አደረኩት። 'በእውነት፣ ደደብ ነኝ... አልም ያልኩ እንከፍ!' አልኩ እንደገና ለራሴ።

ፈያቷ መኪናችን ጠመዝማዛውን ሜዳ ቁ---ት እያደረገችው ከነፈች። ወደ ቢታኒያ ተመለስኩ። ቢታኒያ መኮንን!' እንደተለመደው ስለኢሳያስ እያወራችኝ ነው። ብዙ ተሳሳቅን። ወሬው ቀስ በቀስ ከኢሳያስ ወደ ወይዘሮ ማስተዋልና ወደ ቤተሰቡ ተለወጠ። ለፍቅር ካሰቧት ሴት ጋር በሳቅ ፍርስ እያሉ ለመጫወት መቼም ቤተሰብን የመሰለ አጀንዳ አይገኝም...

"በቀደምለት ማታ አድርሰህ የመለሰከኝ እኮ የኛ ክሊኒክ ነው። መኮንን ወልዴ ማለት አባቴ ነው። አሁን ለሌላ ሰው አከራይተነዋል።" አለችኝ በቁምነገር።

'እሱን ተይው ቢታኒያ፣ የኔ ቆንጆ። ብንናገር እናልቃለን እንጂ ማወቁንስ እናውቃለን!' ብዬ በሆዴ፣ "ኧረ ባክሽ? ለነገሩ ጠርጥሬያለሁ። አባትሽ አሁን የት ነው ያሉት?" በማስመሰል ጥበብ ጥያቄዬን ቤታሰባዊ

ቃና ለማስያዝ ሞከርኩ።

"ውጭ ሄዷል። በአሁኑ ፖለቲካ አልተደሰተም መሰለኝ ስደትን መረጠ። ለነገሩ እኔንና ማሚንም ከጭንቀት ገላግሎናል..." የቢታኒያ ድምጽ በአንዳች ዓይነት ውስጣዊ ቅሬታ እየረገበ ሲመጣ ይታወቅባታል።

አስተያየት መስጠት አልፈለኩም። መነጋገር ከተጀመረ ጋራዡ፣ ምድር ቤቱ፣ ወይዘሮ ማስተዋል፣ ኢሕአፓ...ሁሉም አነጋጋሪ ነው። ቀደም ሲል ፍቅሬ ዘርጋውን ግቢያቸው ውስጥ ማየቴ ትዝ ሲለኝ በጥያቄ ብዛት ብከንከን አልኩ። 'ምንድነው ግንኙነታቸው?' ከሊኒኩ ውስጥ ደግሞ ከሰዪም ከበደ ጋር መገናኘቷን ሳስታውስ ስሜቴ ርብ--ሽ ሊልብኝ ፈለገ። ያኔ ለራሴ የነገርኩትን መጽናኛ ደገምኩት። 'ያገናኛቸው የድርጅት ሥራ ነው። ፍቅር ቢሆን ኖሮ ያ ሁሉ ጥንቃቄ ምን ያስፈልጋል?' ሊንቀለቀል የሚታገለኝ ቅናቴ በረድ ሲል በመጠኑ ቅልል አለኝ። ከደቂቃዎች በኋላ ሱሉልታ ገባን።

###

ሱሉልታ ከአንቅልፏ ተነስታ ጉድ ጉድ ማለት ጀምራለች። የከተማዋን ቀበሌ ጽሕፈት ቤት አልፈን ከአንድ ትልቅ ሱቅ ስንደርስ ወደ ግራ እንድታጠፍ ነገረችኝ። የውስጥ ለውስጥ መንገድ ይዘን ሄደን ከከተማዋ የመጨረሻ ጠርዝ ደረስን። በባህርዛፍ ፍልጥ ከታጠረ ትልቅ ግቢ በር አጠገብ አስቁማኝ ቦርሳዋን ይዛ ወረደች። በፍጥነት ራመድ ራመድ እያለች ስትሄድ ከጀርባዋ አጠናኋት። በደንብ ተለኩታ የተጠረበችና ከብረቷ ጋር የተዋደደች መውዜር። "አንችን ለሰው?" ይበሉ ቆንጆ የወለዱ አባት!

በሩን አንኳኳታ ትንሽ ልጅ ሲከፍትላት ወደ ውስጥ ገብታ ከዐይኔ ተሰወረች።

'ቢታኒያ ያለጥርጥር ዲሞክራሲያን እያሰራጨች ነው። በቃ፣ የእኛ ሰው ናት!'

በነገሩ ይህንን ያህል ለምን እንደተጨነኩ አልገባኝም። አዲስ አበባ ውስጥ የተፈጠረው አባላችን በአሰር ሺዎች እንደሚገመት አውቃለሁ። ኢሕአፓነት ፋሽን ኾኗል። ወጣት ሆኖ ኢሕአፓን ያልተቀላቀለ ጤነኛ መሆኑን እስከመጠራጠርም ደርሻለሁ። የቢታኒያ እንደዚያ መሆን ያሳሰበኝ ሳይታወቀኝ ለደህንነቴ አስቤ ሊሆን ይችላል። ይህንን ከብርከቲ ያላገኘሁት ዝንባሌ መሆኑን አስታውሳለሁ።

'ብርከቲዬ፣ ከእንግዲህ ስ'ላንቺ "የቀድሞ ፍቅረኛዬ" ብዬ ላወራ ነው? ሀ---ም!' ጭንቅ አለኝ።

በግምት ከግማሽ ሰዓት በኋላ ቢታኒያ ተመልሳ መጣች። ቀጥሎ የት እንሂድ እንደምትለኝ አላውቅም፣ እኔም አልጠየኳት። ስላስጠበቀችኝ የይሉኝታ ይቅርታ አቅርባልኝ ገብታ በሩን ስትዘጋው መኪናዋን ወደ

ጀርባ አዞርኳት። ተመልሰን ወደ ዋናው መንገድ ገባን። ወደ መሀል ስንገባ ትንሿ ከተማ እንደነበረችው አይደለችም። ቀበሌ ጽሕፈት ቤቱ አካባቢ የተሰበሰበ ሕዝብ ታየን። ወዲያና ወዲህ የሚዋከቡ ዐዋቂ ሴቶች የሚበዙበት ስብሰብ ነው። ምን እንደተፈጠረ ለመገመት ተቸግረን ስንተያይ የማይክሮፎን ድምጽ መጣ። በአማርኛና በኦሮምኛ እያፈራረቀ ሕዝቡ የራዛ ዘማቾችን ለመሸኘት እንዲወጣ መልእክት ያስተላልፋል...

'እንዴ፣ እዚህም የራዛ ዘማች እየመለመሉ ነው?' በውስጤ ዘመቻው የሚመለከተው የጎንደር፣ የጎጃምና የትግራይ ገበሬን ብቻ እንደነበር አስታውሼ ጥያቄ አነሳሁ።

የ"ራዛ ዘመቻ" ኢሕአፓ አጥብቆ ያወገዘው የደርግ መንግሥት የጦርነት እቅድ ነው። እኔም በዲሞክራሲያ ቅጽ 3 ቁጥር 5 ላይ የውግዘት መዐት አውርጀበታለሁ። "ይህ ዘመቻ የንጉሣዊውን ሥርዐት ነቅሎ የጣለውን ሕዝባዊ አብዮት መንፈስና ዓላማ የሚጻረር እንባገነናዊ ድርጊት ነው!"የጽሑፌ ዋነኛ ነጥብ ነበር። ቀጥዬ፣"ዘመቻው ደርግ የአብዮቱን አቅጣጫ ያለአግባብ ጠልፎ የመጭው ጊዜ ፈላጭ ቆራጭ ጁንታ ለመሆን መቁረጡን ያሳየበት ነው። አርሶ አደሩ በዚህ የኢኮኖሚ ምስቅልቅል ወቅት ወደ ጦርነት እንዲገባ መደረጉ የባሰ መዘዝ አለው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በጦርነት የሚፈታ ችግር የሌለ መሆኑን በማመን እቅዱን መቃወም አለበት።"አጥብቄ አሳስቢያለሁ።

ደርግ በዘመቻ እቅዱ ገፋበት። ገበሬውን ለመሳብና ለማነሳሳት የተጠቀመበት ዘዴ ደግሞ እጅግ አስጠሊታ ነው። "የሰሜን ገበሬ ጠበንጃ ይወዳል" ከሚል ይነሳና "በዘመቻው ላይ የያዝከውን ምርኮኛ ለመንግሥት፣ ጠበንጃውን ለራስህ!" ሲል በግልጽ አውጇል። በደንብ ከሰለጠነና በቂ አደረጃጀት ካለው ሽምቅ ተዋጊ ጋር ያልሰለጠነ ገበሬ ተዋግቶ ይሄንን ያሳካል ብሎ ደርግ ማሰቡ ሁሌም ይገርመኛል።

ወደ ቢታኒያ ዞር ብዬ ሳይ አሷም እያየችኝ ነው። ሳንነጋገር የተግባባን መሰለኝ። ለዐመል ያህል የሆነ አስተያየት ልሰጥ ስል እሷ ቀድማ የኢንፎርሜሽን ጥያቄ አነሳችልኝ...

"ስመረ፣ ይሄን ነገር ከሁለት ወር ምናምን ወዲህ ነው የሰማሁት። ያች ብርክታዊት የሚሏት ጋዜጠኛ አለች። 'ራዛ ዘመቻ' ምናምን እያለች ትለፈልፍ ነበር። ለመሆኑ ራዛ ማለት ምንድነው?" ፊቷን በግራ መጋባት ቋጠር ፈታ አደረጋ መነጽሯን አወለቀችው።

የቀሀነት ልታሳየኝ እየሞከረች እንደሆነ ገመትኩ። የኢሕአፓ ቅጥ የሌለው ሕቡዕነት መቼም ሁላችንንም አስመሳይ አድርጎናል። ከፖሊት ቢሮ ጀምሮ እስከ ተራ አባል ድረስ እንደዚያው ነን። በየቀኑ ድራማውን ስንተውነው እንውላለን። ቢታኒያም ብርክታዊትን ስታነሳ ደግሞ ሆዴ ትርጉሙ በማይታወቅ የሆነ

ስሜት ቦ--ጭ አለብኝ። ቢታኒያ እጹብ ድንቅ! መነጽሯን ስታወልቀው የናፈቁኝ ዐይኖቿ ፓውዛ መስለው አጥበረበሩኝ። የፊቷ ቆዳ ልስላሴ ዓይን ያዳልጣል። ስለ "ራዛ ዘመቻ" ትርጉም ለመናገር አጣብቂኝ ውስጥ መግባቷ አልቀረም። ነገሩ ራሳቸው የደርግ ባለሥልጣናት በይፋ የተናገሩት ስለሆነ የሰማሁትን ነገርኳት...

"ኤርትራና ትግራይ ውስጥ ተቃዋሚዎችን ለማጥፋት የታሰበ ዘመቻ ነው። ለምን 'ራዛ' ብለው ዘመቻውን መሰየም እንደፈለጉ ግን አልገባኝም። ራዛ ማለት ሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ የምታገኘው የወፍ ዓይነት ነው። አንበጣ ተወዳጅ ምግቡ ነው። ወራትን ጠብቆ የአንበጣ መንጋ ሲመጣ ራዛ ወፍ ከች ይላል። የአፉ ምንቃር ትልቅ ነው። አንበጣውን ታዲያ እያሳደደ ይለቅመዋል። ችግሩ ግን ያለመጠን ይበላ ይበላና ያለመጠን ይኮሳል። ገበሬዎች ራዛ ወፍ 'አንበጣን መልቀሙ ጥሩ ሆኖ ሳለ የኩሱ ብዛት ግን አስመረረን' ሲሉ ሰምቻለሁ..."

ቢታኒያ የገነፈለባትን ሳቅ መቆጣጠር ወይም ለትህትና ያህል እንኳን መቀነስ የቻለች አትመስልም። በመጨረሻ ድምጿ ለቀቀችው። ካካካካ...ቂቂቂቂ...ካካካካ! ዐይኖቿ እስከሚያነቡ ድረስ ተንከተከተች። አሁን የምሯን ጠይቃኝ የምሯን ተገርማ እንደሳቀች አልተጠራጠርኩም። ከልቧ ስለሳቀችልኝ ደስ እያለኝ እኔም አጅቢያት ሳቅኩ።

"እ---ይየኝ አገ------ር... የሚያስቀው ነገር መብዛቱ! ለመሆኑ ማነው ወፉ፣ ማነው አንበጣው?" እንደገና በረጅሙ ስትስቅ መልሱም እዛው ሳቋ ውስጥ ስላለ ዝም ብያት ወደጉዧችን ጉዳይ ተመለስኩ።

የመኪናዋን ፍጥነት የማቆም ያህል ቀስ ብዬ እየነዳሁ የሚቀጥለው ፍላጎቷ ምን እንደሆነ እንድትነግረኝ እድል ሰጠኋት። የተረዳችኝ አልመሰለኝም። ወሬውንና ሳቁን ስትቀጥልበት ራሴ ጠየኳት። "የት ነን፣ ቢታኒያ?"

"እእእ......" ብላ ትንሽ አሰብ ካደረገች በኋላ፣ "ግ---ን ይቅርታ፣ ሰመረ... አንድ ነገር ላስቸግርህ ነው። የሚያስቸኩል ሥራ ነገር ምናምን አለህ?" እየተጨነቀች ጠይቃኝ ለመልሱ አፍ አፌን አየችኝ።

"ምን አስበሽ ነው? እስከ ሦስት ሰዓት ተኩል እንደዚህ ድረስ የሚያ—ጣ—ድፍ ሥራ የለኝም..." መለስኩላት የዕለት ሥራ መርሀግብሬን ለማስታወስ እየሞከርኩና ሱሉልታ መቆየታችን አንድ ጥሩ ነገር ያመጣ ይሆናል ብዬ እየተመኘሁ።

"እንግዲያውስ በጣ--ም ይቅርታ፣ ሰመረ...አስር ደቂቃ ምናምን ይበቃኛል። እንዳልረሳው መኪና ልንዳ። ግን ይቅርታ!"

'ሆሆ——ው፣ ቢታኒያ፣ ትቀልጃለሽ እንዴ?! አብሮ መቆየትን አግኝቼው ነው!?' በልቤ ደስታዬን ለራሴ አስተጋብቼ፣ "ኧረ አትሳቀቂ፣ ምንም ችግር የለ!" ትንሽም ሳላመነታ መኪናዋን እዙሬ ወደ ጎኛም መውጫ ነዳኋት።

ከተማዋ ጫፍ ላይ ስንደርስ ወደ ቀኝ ታጥፌ ዋናውን መንገድ ለቀቅኩ። ሁለታችንም ብቻውን ከቆመ የእህል ወፍጮ ቤት ጀርባ ትንሽ አግር ኳስ መጫዎቻ ሜዳ ዐይተናል። ወፍጮ ቤቱ ገና በቢት ሥራ ጀምሯል። በር ላይ ጭነታቸው የተራገፈ አህዮችና ፈረሶች በጠፍር እየታሰሩ ቆመዋል። ሜዳዋ ላይ ስንደርስ መኪናዋን አቆምኳትና ወንበር ለቅቄላት ወረድኩ። መለማመድ ስትጀምር ገና ለማጅ አለመሆኗ ገባኝ። ወደፊት ሄዳ ኳስ ሜዳዋ ጫፍ ስትደርስ ሞተር ከመጥፋቱ በስተቀር በደንብ ችላበታለች። መመላለስ ስትቀጥል እኔ አንዳንድ እያሉ መጥተው ከቆሙ ገበሬዎች ጋር ወሬ ጀመርኩ።

"አንተ፣ ጠይሙ...ሚስት አግብተሀል ወይስ ገና ነህ?" አንዱን ወጣት ድንገት ጠየኩት።

"አዎ፣ ባለፈው ጥር አግብቻለሁ..." የኦሮምኛ ቃና በሚሰማበት አማርኛ መለሰልኝ።

"እንዴት ነው፣በመሬት ከፍፍሉ መሬት አግኝተሀል ወይስ አልሰጡሀም?" ሌላ ጥያቄ አነሳሁለት።

"ኧረ ማን ሰ'ቶኝ?! መቼ የቀድሞ ሀብታም ተነካና ኖ? ራዶው ዚም ብሎ ኖ ሚያወራ..."

የወጣቱ ገበሬ አነጋገር ለእኔ በኢሕአፓነቴ ከፍ ያለ ትርጉም አለው። የመሬት ዐዋጁ በድርጅታችን ውስጥ የሐሳብ መሳከር መፍጠሩ ቀጥሏል። ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ትዝ አለኝ። ገና ውይይት ከመጀመራችን ሁለታችንም አተረጓጎም ላይ ተለያይተናል። የተሳሳትኩት እኔ እንደሆንኩ ዐሰቤ ነበር። የአሁኑ የወጣቱ አነጋገር ግን የእኔን ሐሳብ የሚያጠናክር ሆኖ አገኘሁት። "ደርግ የመሬት ዐዋጁን በፍጹም እያስፈጽመውም። ያ ማለት ኢሕአፓ አጀንዳ አላጣም ማለት ነው..."ለገበሬዎቹ ሌላ የመረጃ ጥያቄ ላነሳ ስል ቢታኒያ መኪናዋን አቁማ ከጀርባዬ በአግሯ መጣች። "እንሂድ" ልትለኝ ነው ብዬ ስገምት ቅር አለኝ። አፍ አፏን እየኋት...

"ሰመረ፣ መኪና በቅቶኛል። በአማዬ ሞት፣ እኛን ሰውዬ እንለምናቸውና ፈረስ መጋለብ አሳየኝ። ይቅርታ፣ አንዴ ብቻ ካሳየኸኝ ይበቃኛል።" ልቧ በጉጉት ስቅል ብሎ ኮርቻ የተጫነ ፈረስ ከወፍጮው ግድግዳ ጋር ወደሚያስሩ አዛውንት አመላከተችኝ።

"ፈ—ረ——ስ?! በአንዴ የሚለመድ መስሎሽ እንዳይሆን..." ካልኳት በኋላ በመገረም፣ ሐሳቧን ሳትለውጥብኝ፣ "ሰውየው እሽ ካሉን እኔ ምን ቸገረኝ...አሳይሽና ትሞክሪዋለሽ..." አልኳት፣ ልቤ ድው

ድው ማለት ጀምራለች።

እኔ እየመራኋት ወደ ባለ ፈረሱ አዛውንት ሄድን። በመለማመጥ ድምጽ ስለምናቸው ሴኮንድ አላስቸገሩኝም። የፈረሱን የታሰረ እግር እንደገና ፈትተው ከአለንጋው ጋር ሰጡኝ። ራቅ ብላ የምትታይ ዛፍ እመላከተውን ከዛ እንዳላልፍ ብቻ አስጠንቀቁኝ። አመስግኜ ፈረሱ ላይ ወጣሁ። ቢታኒያ በአዛውንቱ እርዳታ ጭምር ተደግፋ ከጀርባዬ ኮርቻው ላይ ወጣች።

"ቢታኒያ እንዳትፈሪ!" አስጠንቅቄያት ልጓሙን ለቀቅ አድርጌ ፈረሱን ስኮረኩረው መጋለብ ጀመረ፤ "ወ------ይኔ!" ባለ በሌለ ድምጽ ጮኻ ወገቤን ጥምጥም አለችብኝ። "ወ---ይኔ ያስፈራ--ል!" እንደገና ጮኸች።

ቀስ በቀስ ፍጥነቱን ስጨምረው የበለጠ አጥብቃ ያዘችኝ። ትንሽ ቆይታ እጆቿን በጎንና በጎኔ አሳልፋ ትከሻዬን አጥብቃ አቀፈችኝ። እቅፏ ሲጠብቅ ህልም ውስጥ ሆኜ ከኮከቧ ማርሊ ሞንሩ ጋር ለሆሊውድ "Love in Texas" ፊልም በመቀረጽ ላይ ያለሁ መሰለኝ። እንደገና በጣ---ም ጠበቅ አደረገችኝ። ጋልበን ጋልበን አዛውንቱ አትለፉ ካሉን ዛፍ ደረስን። ፈረሱን አዞሬ ወደ ወፍጮው ተመለከትኩ። ማንም ሰው አይታየኝም። ልቤ ግልቢያውን መቀጠል በቢታኒያ እቅፍ ውስጥ ዕድሜን ማርዘም መሆኑን ነገረችኝ። ነገር ግን ቃሌን ማጠፍ አስፈራኝ። ፈረሱን አዞሬ ቆምኩ። ለመጋለብ አሁን ተራው የእሷ ነው። ቦታ ቀይረያት ልጓሙን አስጨበጥኳት።

"ው--ይ--ኔ!! ወ---------ይኔ!! ሰመረ፣ በ'ናትህ፣ እታሩጠው! ራሴን ሊያዞረኝ ነው!"

"መሬት መሬት አትመልከች! ስለምይዝሽ ደግሞ አትፍሪ!" ፈረሱ በቀስታ ሮጥ ሮጥ ማለት ሲጀምር ወገቧን እቅፌያት ከደርቴ ጋር ጥብቅ አለች።

"አሁንስ፣ ደስ ይላል?" ጠየኳት።

"በጣ---ም! በጣ----ም! ወይኔ ካሜራ ሳልይዝ መምጣቴ!"

ፈረሱ ፍጥነት ሲጨምር ጭንቅላቷ ላይ ያሰረችው ሻሽ ከፊት ለፊት ወደ ጀርባዋ ሸሽቶ በመጨረሻ ተፈታ። ረጅም ጸጉሯ ጉንጉኑ እየተፈታ አየር ላይ መነስነስ ያዘ። እየመጣ ጉንጮቼን፣ አንገቴን፣ አፍና አፍንጫዬን ሲገርፋቸው ቀልቤን መሳት ጀመርኩ። ከአንገቷ ሥር የሚፈልስ ጥዑም ሽቶ እየመጣ ያውደኝ ገባ። ፈረሱን የበለጠ ኮረኮርኩት። ቢታኒያ በሀሴት ሲቃ እየጮኸች ዘንበል ዘንበል ማለት ስትጀምር እቅፌን ጠበቅ አደረኩት። እጆቼ ከጠጣር ጡቶቿ ሥር ሽጉጥ ብለው እንደ ካቴና እንቅ

አደረኳት። ከወፍጮ ቤቱ ልንደርስ ትንሽ ሲቀረን አዛውንቱ አንዴ ተመልሰን ደርሰን እንድንመጣ በእጅ ምልከት ፈቀዱልን።

'ይሄ እውነት አይደለም፣ አልም ያለ ቅዠት ነው!' አልኩት ራሴን።

አሁን ዐቅሌን ሸኝቼ ሙሉ በሙሉ ደመነፍስ ሆንኩ። ልክ እሷ እንዳደረገችው እጆቼን ከወገቧ ዙሪያ አንስቼ በፊት ለፊት በኩል ሁለቱንም ተከሻዎቿን እንቅ አደረኳት። ወደ ዛፏ ስንጠጋ ፍጥነት ቀንሰን በዝግታ ከጋለብን በኋላ ከመመለሳችን በፊት ለአፍታ እረፍት ቆም አልን። አቅፌን ሳላላ እሷ በደስታ እያለኸለኸች የተበተነ ጸጉሯን መሰብሰብ ጀመረች። በግራዋ በኩል የተፈላለሰውን ጸጉር ስትሰበስብ በሆነ ግፊት ጣልቃ ገባሁ። ጥቅልል አድርጌ ይዤላት በጆርባዋ ትይዩ ሳስተካክለው በከፊል ፊቷ ወደ እኔ ዘወር አለች። ልቤ እንደ እንቁር ሽቅብ ቱ---ር አለችብኝ...

"ቢ---ታ---ኒ--------ያ!!" በሚንሾካሾከና በስሜት ከስልት በወጣ ድምጽ ስጠራት ምን እንደመለሰችልኝ አልሰማኋትም።

ብቻ ከንፈሮቻችን እንደመግነጢስ በራሳቸው መንገድና ፈቃድ ተፈላልገው ግጥምጥም ሲሉ ትዝ ይለኛል...

# 8

ሰዓቱ ንጋት ይሁን ምሽት አላውቅም። የማውቀው ነገር ቢኖር ከሚጥም እንቅልፌ በሸዋዬ ተቀስቅሼ መነሳቴን ብቻ ነው፤ ቢሆንም አልተነጫነጭኩም። ጭልምልም ያሉብኝን ዐይኖቼን በእጆቼ በኃይል እያባሸሁ ለመነሳት ታገልኩ። ሸዋዬ ትንሽ ጠብቃኝ በመነሳቴ እርግጠኛ ስትሆን ሄደች። ለምን እንደቀሰቀሰችኝ ግን መገመት አልቻልኩም። ከደቂቃ ደቂቃ ሰመመንና የፍቅር ትዝታ ተቀላቅለውብኝ ወደሌላ ዓለም ሸው አልኩ። ትላንት ረፋድ ላይ ከቢታኒያ ጋር ሱልልታ!! አብሮ መሆን ብቻ አይደለም። በፍቅር ከንፈናል፤ በከንፈር ስሞሽ ከንፈራችን ባስቷል። ማመን እየቸገረኝ ጣፋጩን ቆይታዬን እንደ ፊልም ወደ ኋላ አጠነጠንኩት። ከሱሉልታ እየተመለስን ነው።

'ወ—ይ አ—ጋ—ጣ—ሚ!'

ከዚያች ሰዓት ወዲህ ሰመረ እኔ መሆኔ ቀርቶ ሌላ ሰው ሆኛለሁ። የመንታ እናት ተንጋላ ሞተች አይደል የሚባለው!? የቆንጆ ልጅና የድርጅት ፍቅር! እንዲሁ ትዝ ባለኝ ቁጥር አንዳች ዓይነት የሚያባብል እንግዳ ስሜት ውርር ያደርገኛል። እንደገና መጣችብኝ። ከንፈሮቻችን ከተጨባበጡባት የሴኮንድ ጊዜ ሽራፊ በኋላ የሁለታችንም ሁኔታ ልውጥውጥ ብሏል። ልባችንን በፍቅር ለማቆላለፍ ጊዜው የማይበቃን መሰለን። ከተያየንባት የመጀመሪያዋ ቀን ጀምሮ ለካስ እንደኛችን ቀድመን በሌላችን ልብ ውስጥ ነን። የለውጣችን ፍጥነት አስገረመኝ። ዘወር ያለ ቦታ ባገኘን ቁጥር መኪናዋን አቆማትና ፊቴን ወደ እሷ አዞራለሁ።

"ቤ—ቲ፤ የውበት ጥግ...እቻ የሌለሽ ቆንጆ!" ድምጼ በስሜት ቁርጥርጥ እያለ አፌን ወደ አፏ እስጠጋለሁ።

"እ---ር---ግ—-ጠ---ኛ ነ----------ህ?" በቁንጥ አግድም ስታየኝ ዐይኖቿን ፍልቅቅ ታደርጋቸዋለች።

"በጣ---------ም!!" ጥምጥም እልባታለሁ።

አዲስ የተላጠ ብርቱካን የመሰሉ ስስ በጣም ስስ ከንፈሮች...ጉልበቱ ልብ ድረስ ዘልቆ ስሜት የሚፈጥር ትኩስ ትንፋሽ...ጽድትድት ያሉና ከብር ዘብ መስለው የተደረደሩ ጥርሶች...። የተፈጠረውን ነገር እውነትነት አምነን እስከምንቀበለው ድረስ ተቸገርን። እየተሳሳምን መነፋፈቅ...ስስት...እንደገና መሳሳም...።

ጉዟችንን እንደገና ስንቀጥል የመኪናዋን ፍጥነት ሆን ብዬ እቀንሰዋለሁ። ልቦቻችንን ክፍትፍት አድርገን የምንተያየበት ወሬ ፈልገናል። የግል ጉዳዮቻችን ወደ ፖለቲካዊ ማንነታችን ዘልቀው ይገቡ ይሆን? ሰጋሁ። ምን ማድረግ እንዳለብን ብልጭ ያለልኝ ሐሳብ የለም። የመጣልኝን ጠየኳት...

"የወይዘሮ ማስተዋል ማህጸን ያበቀላት ይህች የምድር ቆንጆ፣ ቢታኒያ፣ ምን ዓይነት ልጅ ነች?"

"እእእእ...ሰመረ...ከባድ ጥያቄ ነው የጠየከኝ።" በዝምታ መንገዱን ቡዝዝ ብላ ስታይ ቆይታ ወደ እኔ ዞር አለች፣ "እእእ...ቢታኒያ ማለት ብዙ የፍቅር ሕይወት ያላየች...ለእውነተኛ ፍቅር ስትባዝን የቆየች... አጭሩ የልጅነት ጊዜዋ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ በጸጸትና በቁጭት የተሞላ...በጣ—ም ቀናተኛና ቁጡ ልጅ ናት! ወየሁልህ! ካካካካካ..." ከትከት ብላ ስቃ ካበቃች በኋላ፣ "ራሴን ሳከብር ጎበዝ ነኝ አይደል?" አለችኝ።

የመጨረሻውን ጥያቄዋን ብዙም ትኩረት አልሰጠሁትም። አእምሮዬ ተጠንጠልጥሎ የቀረው በንጽጽሯ ላይ ነው። "የልጅነት ጊዜዬ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ በጸጸትና በቁጭት የተሞላ ነው!" 'ምን ማለቷ ነው?' የልጅነት ታሪኳ ምን ፈተና ስላለፈ ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር እንዳነጻጸረችው እንቆቅልሽ ሆነብኝ። ትርጉሙን ጠይቄ ላስጨንቃት ግን አልፈለኩም።

"ቢታኒያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ሰፊ ነው'ኮ! እኔና አንቺ ደግሞ የተረፈ ጊዜ የለንም። በእውነት የዕድሜ ልክ መነጋገሪያ የሚሆን አጀንዳ ነው ያነሳሽብኝ..." ብያት የዩኒቨርስቲ ትምህርት ሊኖራት እንደሚችል ስገምት በተቀላቀለ ስሜት በረጅሙ ተንፍሼ ሌላ ጥያቄ አነሳሁላት፣ "በነገራችን ላይ፣ መቼም ይሄ ቁንጅናሽ እስካሁን ብዙ በጣም ብዙ ነገር አሰምቶሽ ይሆናል። ደስ ደስ የሚሉ ነገሮችን ማለቴ ነው። ወንዶች ካሉት ውስጥ በጣም የወደድሽውን ገጠመኝሽን እስቲ ንገሪኝ...?" እቅፍ አድርጌ ደረቴ ላይ ልጥፍ አደረኳት።

"ዋ-----ው፣ ምኑን ነግሬህ ምኑን እተወዋለሁ። አንድ ሙሉ መዝገብ ቤት ይወጣዋል። ለነገሩ እኔ ቆንጆ ነኝ ብዬ አምኜ አላውቅም። የአዲስ አ'ባ ጎረምሳ ለከፋና የወንድ የፍቅር ደብዳቤ መዐት ግን እንደዛ

እንዳስብ ያደረገኝ ይመስለኛል። ብቻ ከሁሉም ከሁሉም ሚስተር ሻርማ የሚባል የሕንድ አስተማሪ በየቀኑ ከፍል ውስጥ ይለኝ የነበረው አይረሳኝም። 'ቢቃ፣ ንግሥት ሳባ የምትሏት የጥንት ንግሥታችሁ ቁርጥ እንቺን መምሰል አለባት። እንቺን ካለመሰለች ግን በእውነት... ትቅርባችሁ...ዐረቦች እንደተመኟት ይውሰዷት!'' የሕንዳዊውን አባባል በሕንድ እንግሊዝኛ ስትነግረኝ የፍቅር ሳቅ ሳቅሁ።

ቤት ደርሰን ስንለያይ የሚለያየን ያ ቀይ በር የገነት ግድግዳ መስሎ ታየኝ። ሩ---ቅና ውድ ሆነችብኝ። የዕሉቱን ገቢ ለወይዘሮ ማስተዋል የማስረከብበት ጊዜ ደግሞ እንደ ዳገት ቀጥ ብሎ ቆመብኝ። እንደምንም ደርሶ ምሽት ላይ ሄድኩ። ቢታኒያ እንግዳ ጋር ነች። የሕዋስ አባላት ሊሆኑ እንደሚችሉ ጠርጥሬያለሁ። ያም ሆኖ ቅር አለኝ። ዘሚካኤል ጋር ስንጋገር ድምጼን ሰማች መሰለኝ በሩን ከፍታ ወጣች። እብሪዋ ኮከብ ጭለማውን ሰንጥቃው መጣች። ፍቅሯን በዐይኖቿ ጥቅሻ አሳየችኝ።

እንደገና በረጅሙ አዛግቼ በኃይል ተንጠራራሁ።'መቼ ነው የተኛሁት? ምሳ አልበላሁም እንዴ?' ሁሉም ነገር ድንብርብር አለብኝ።

እየተርበተበትኩ ሮመር የእጅ ሰዓቴን ስመለከት የገዛ ራሴ ሁኔታ አሳቀኝ። ከጧቱ 2: 00 ሰዓት ነው። ከደቂቃ ደቂቃ ራሴን እያረጋጋሁ ሙሉ በሙሉ ከሚያባብለው የእንቅልፍ ግፊቴ ወጣሁ። ብዙም ሳይቆይ አእምሮዬ ሞተሩን አስንስቶ ሥራውን ጀመረ። አ----ፍፍፍፍፍፍፍ! ደግሜ ከተንጠራራሁ በኋላ ተነስቼ አልጋዬ ላይ ቁጭ አልኩ። አልጋዬ አጠገብ በነበረ ወንበር ላይ የከመርኩትን ወረቀት ሳየው አስፈራኝ። እንደ ደብተራ ሌሊቱን በሙሉ ስቸከችከው አድሬያለሁ። ሰውነቴን ድቅቅ ያደረገው ሥራ ይገፎ መላ ሌሊቱን ማንጋቴን አስታወስኩ። ድካሜ ግን በውጤት ተጠናቋል። ጽፌ ጨርሻለሁ።

'ይች ሸዋዬ ቀስቅሳኝ ስታበቃ በዚያው እልም አለች እንዴ?' ወደ መምጫ በሩ ደጋግሜ ባይም ብቅ አላለችም።

እጄን ወደ ሬዲዮዬ ሰደድኩ። ስከፍተውና የብርከቲ ድምጽ ጆሮዬ ሲደርስ አንድ ሆነ። የማለዳውን ዜና በጨኸት ታንበለብለዋለች። ቢታኒያ እንደገና ትዝ አለችኝ። በድምጽ አወጣጧ ብርከቲን በጣም ትጠላታለች። ምስኪ--ን ቢታኒያ። ሌላውን ጉድ ብታውቅ ደግሞ ምን እንደምትል አላውቅም። ለነገሩ አሁን ምን የሚያሳስብ ነገር አለና!? ቢታኒያ በእጄ ነች። ብርከቲ ርእሰ-ዜና አሰምታ ወደ ዝርዝሩ ገባች...

"የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የሕዝቡን ሰላምና ጸጥታ አስተማማኝ ለማድረግ የሚያስችል አዲስ የደኅንነት አጠባበቅ ደንብ ማውጣቱ ተገለጸ። ደንቡ በተለይ በትልልቅ ከተሞች ኅብረተሰቡን ለሁከትና ለብጥብጥ የሚያጋልጡ ሕገወጥ ጽሑፎችንና በራሪ ወረቀቶችን የሚከለክል እንደሆነ ታወቋል..."

'ደርግ ሆዬ... ወዴት ወዴት፣ ጃል!?' መውጫ መግቢያቸው ጠፍቶበት ናላውን ባዞሩት በኛዎቹ የኢሕአፓ ልሳናት ዲሞክራሲያ፣ ላብ አደርና ሌሎች ጋዜጦቻችን ላይ ያነጣጠረ ደንብ መሆኑ ነው።በተለይ ዲሞክራሲያ የኢሕአፓ ተቀያሪ ቅጽል ስም ሆናለች። ደርግ፣ መኢሶንና የሰናይ ልኬው ወዝሊግ በማጣጣል ድምጸት ዲሞ ይሉናል። እኛም ዝም አላልንም።ፊዲስት እንላቸዋለን፣ ፊዳ የሚለውን የኃይሌን አባት ስም ተጠቅመን።

ወደ ብርክቲ ተመለስኩ። ዜናው አላስደነቀኝም፣ አላስጨነቀኝም ወይም አልገረመኝምም። ሌሊቱን "በደርግ ተፈጥሮ" ላይ ስጽፍ ነው ያደረኩት። "ደርግ የዲሞክራሲ መብቶችን ለቀቀ ማለት አንገቱ ላይ የታሰረውን የስቅላት ገመድ በገዛ እጁ ሳበው ማለት ነው!" ብዬ ጽፌያለሁ። አንድ ቃል በጻፍኩ ቁጥር ግን የተለመደው ቸኩላዬ ስህተት እያሠራኝ እንዳይሆን እየሰጋሁ ነበር። አሁን ነጻ ወጣሁ። ትንቢቴ ትክክለኛ አቅጣጫውን ይዞ በመሄድ ላይ ነው። ከዚህ ይልቅ የገረመኝ ድርጅቴ ውስጥ በጉዳዩ ላይ አንዳንድ ጥርጣሬ መነሳቱ ነው። መነሳቱ ሳያንስ ስፋቱም እየጨመረ መጥቷል። ጥቂት ቃላትን በምሳሌነት እየጠቀሱ ጥያቄዎቹ በግልጽ እየተንሸራሸሩ ነው...

"ደርግ ተራማጅ አይደለም ወይ? መኢሶንስ ቢሆን? ምንድነው የሚያጣላን? ሁላችንም ግራ ኃይሎች አይደለንም ወይ? ከሁለቱም ጋር ልዩነቶቻችንን ተነጋግረን ለመፍታት ለምን አንቀራረብም?" ሌላም ሌላም። የተስፋዬ መኮንን ሐቲት መርዝ ሆኖ እየተሰራጨ ነው።

"ትራ-----ሽ!" አልኩ ጮክ ብዬ፣ "መንጋ ቁንጽል!"

ብዙም ሳይቆይ ግን ሸዋዬ ተመልሳ መጣች።

"አላምር፣ይቅርታ...ቀስቅሼህ ሳበቃ በዚያው ሄጄ ቀረሁ። እንግዶች መጥተውብኝ ነው። ተነስ ተነስ... አንተን እየጠበቁ ቁርስ አንበላም ብለው ቁጭ ብለዋል..." ጥድፍድፍ አለችብኝ።

"እነማን ናቸው?" ነቃ ብዬ ጠየኳት።

"ጓድ ብርሀነመስቀልና ጓድ ጌታቸው ማሩ...ኢሳያስም አለ..." ሸዋዬ ተመልሳ በጥድፊያ ሄደች።

ትንሽ ግር ብሎኝ ቆየ። የጸጥታ ሁኔታው ጥሩ አይደለም። እነርሱ ከሚመጡ ባሉበት ቦታ ሆነው እኔንና ኢሳያስን ማስጠራት ለምን እንዳልፈለጉ አልገባኝም። የመጡበትን ምክንያትም ለመገመት ተቸገርኩ። 'ያው መዘዘኛ የመሬት ዐዋጅ ሊሆን ይችላል...' ሌላ ጥርጣሬ የለኝም። ሙሉ የሥራ ልብሴን ከለበስኩ በኋላ ማስታወሻ ደብተሬንና እስክርቢቶዬን ይዤ ሄድኩ።

ብርሃነመስቀልና ጌታቸው ድምጻቸው አይሰማኝም። ኢሳያስ መኖሪያ ክፍል በር ዘግተው መቀመጣቸውን

ያወኩት ሄጄ ስገባ ነው፡፡ አለባበሳቸውን ስመለከት ጨርሶ አነርሱ አልመሰሉኝም፡፡ ብርሃነመስቀል በተለይ ቁርጥ ገበያ የሚወርድ ገበሬ ይመስላል፡፡ የጎፈረ ጸጉሩን በአዳፋ ነጭ ጨርቅ ድብን አድርጎ ጠምጥሞታል፡፡ በበዓል ቀን ቅቤ የተቀባ የሰፈር አባወራም ይመስላል፡፡ በእድፍ የጠየመ ጋቢ ደርቦ በትር ተደግፎ ነው የተቀመጠው፡፡ አረንጓዴ ቁምጣ ሱሪ ለብሶ በተለምዶ "ኮንጎ" የሚባለውን ነጠላ ጫማ አድርጓል፡፡ በቀኝ ጎኑ ደግሞ ከረጢት ነገር አንግቧል...

"እንደምን ነህ......እእእ?" የኮድ ስሜን ለማስታወስ ሲታገል፣ ጌታቸው ደርሶ፣ "ታዲያስ አላምረው?" አለኝ፡፡

የጌታቸውም አለባበስ የተዋጣለት መመሳሰያ ካሞፍላጅ ነው፡፡ ያለቀ ብሉ ጅንስ ሱሪ በተራ ሸራ ጫማ ለብሶ ቀይ ኮፍያ አጥልቋል፡፡ ቆቡ ጠይም ፊቱን በከፊል ስለከለለው በድንብ አይታይም፡፡ እንዲሁ ሲያዩት ተደባዳቢ የሰፈር ጎረምሳ ይመስላል፡፡ እንደዚህ ተመሳስለው ማንም ሊለያቸው እንደማይችል ዐውቃለሁ፡፡ በየት በየት በኩል ተሽሎኩልከው እንደገቡ ግን ገረመኝ፡፡ አልጋው ላይ ከተቀመጠው ኢሳያስ ፊት ለፊት የእንጨት ወንበሮች ላይ ተቀምጠዋል፡፡

'የትውልዱ ፈተና እንዴት ከባድ ነው!' ችግራችን ገዝፎ ገዝፎ ተራራ አከሎ ታየኝ፡፡

ከፊት ለፊታቸው ተቀመጥኩ፡፡ አሁን የኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊና ቁጥር አንድ መሥራች፣ የነገዋ ሶሻሊስት ኢትዮጵያ  ሪፓብሊክ ፕረዚደንት... አብሮኝ አለ፤ ታጋይ ብርሃነመስቀል ረዳ፡፡ እንደሁሌው ኩራት ተሰማኝ፡፡ሽዋዬ ለቁርስ  የተቆራረሰ ዳቦና ሻይ አስቀምጣልን ወጣች፡፡ አበላላችን የተገደድን ያህል ያለ ፍላጎት ነበር፡፡ ስንጨርስ ኮስተር ብለን ወደ መጡበት ጉዳይ ገባን፡፡ ጌታቸው ቀድሞ መናገር ጀመረ...

"አላምረው፣ በኢሳያስ በኩል 'ደርግ፣ አብዮቱና እኛ' በሚል ርእስ የላከው ጽሑፍ ደርሶን አንብበነዋል፡፡አንዳንድ የሚያወዛግቡ ነጥቦች ስላሉበት ለተጨማሪ ውይይት ነው የመጣነው፡፡ ያው ደርግ አፈጣጠሩ ላይ ባሉ መሠረታዊ ዝንፈቶቹና ከተከሰተበት ማኅበረሰባዊ መዋቅር አንጻር ባጭር ጊዜ ወደ ወታደራዊ አንባገነንነት መለወጡ እንደማይቀር ገልጸሃል፡፡ ከዚህ መደምደሚያ ለመድረስ መነሻ ያደረካቸው ዲያሌክቲካዊ ጥያቄች ምንድናቸው?" አለኝ የማስታወሻ ደብተሩን እየተመለከተ፡፡

ጉሮሮዬን አጸዳድቼ መነሻ ጥያቄወቼን ዘረዘርኩላቸው...

"አንደኛ፣ ደርግ በምን ዓይነት ነባራዊና ህሊናዊ የፖለቲካና የማኅበራዊ ሁኔታ የተፈጠረ ስብስብ ነው? በራሱ ለብቻ ተወስዶ ሲታይስ ደርግ ምን ዓይነት ማኅበራዊ ክስተት ነው? ሁለተኛ፣ ደርግ ሥር ነቀል አብዮትን መርቶ ወደግቡ ለማድረስ የሚያስችል መዋቅራዊ ዐቅም ሊፈጥር የሚችል አካል ነው ወይ?

ደርግ እስከአሁን የወሰዳቸው እርምጃዎች ሥነ አመክኖያዊና ፖለቲካዊ ዳራ ምን ሊሆን ይችላል? እርምጃዎቹ በማኅበራዊ ቅራኔውና በፖለቲካ አየሩ ላይ የሚፈጥሩት ተጽእኖስ ምንድነው? ሦስተኛ፣ ደርግ ከዚህ ልዩ ተፈጥሮው አንጻር የተለየ ተፈጥሮና ታሪክ ባላት ኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥት ሆኖ የመቆም አድሉና ዘዴው ምን ይሆናል? በመጨረሻ፣ ደርግ ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችና የፖለቲካ ፕሮግራሞች ጋር ተባብሮ ለመሥራት የሚያግዝ ማኅበራዊ መሠረት አለው ወይ?"

ቀና ብዬ አየኋቸው። ሁሉም በትኩረት እየተከታተሉኝ እንደሆነ ስረዳ ወደ መልሱ ሄድኩ...

"ደርግ ከተቋቋመ ወዲህ በሚሠራቸውና በሚናገራቸው ነገሮች ሲታይ ችግር አለ። ሲጀምር ግልጽ ፖለቲካዊ አተያይ ሳይዝ የተዋቀረ ስብስብ ነው። ንጉሡን ከሥልጣን የማውረድ ጥያቄ ሊያፈርሰው ለጥቂት ነው የተረፈው።በዚህ ምክንያት አብዮቱን በሚገባ ለመምራት የሚያስችል የውስጥ ጥንካሬ የለውም። ምክንያቱም ጊዜያዊ መንግሥት እንጂ ፓርቲ አይደለም። ይሁንና እየወሰዳቸው ባሉት ርምጃዎች ሲመዘን ሥልጣኑን ላለመልቀቅ መቁረጡን ማየት ቀላል ይመስለኛል። ወደፊት የሚቋቋመው ሪፓብሊክ ሊሠራቸው የሚገቡ ግዙፍ ተግባራትን ነው በአበሰጡኝ እየሠራ ያለው። ያለ ምንም 'ሌጂቲመሲ' የሚወስዳቸው እርምጃዎች መልሰው አጣብቂኝ ውስጥ ይከቱታል..."

"ስለዚ---ህ?" ብርሃነመስቀል ወደ ማጠቃለያ እንድመጣ በመፈለግ ይመስለኛል ጣልቃ ገባ።

"ስለዚህ፣ ደርግ በምንም ተዐምር በለውጥ መንገድ ፈጽሞ አይጓዝም። ችግሩ ራሱን ከሚያይበትና ከሚተረጉምበት ነጥብ ይጀምራል።ራሱን ከማንኛውም ሊፈጠር ከሚችል የፖለቲካ ድርጅት እኩል የመግዛት መብት ያለው አካል አድርጎ ወስዷል። በአንጻሩ ግን ማሕበራዊ መሠረቱ ጠባብ ነው። እርግጥ ከሞላ ጎደል ተጠቃሚ ያልነበሩ ወታደሮችን ማሰባሰቡ አይካድም። ያም ሆኖ ለገበሬው ሕዝብ የሚወግንበት በቂ መደባዊ መሠረት የለውም። ይህ በደርጉ ላይ የአገዛዝ መብት ሳንካ ይፈጥርበታል። ጉድለቱን እንዴት ይሞላዋል? ጡንቻና ኃይልን ለመጠቀም የሚገደድበት ሁኔታ እንደሚኖር ዝንባሌዎቹ ያሳያሉ..."

ጌታቸው ከደብተሩ ሥር ወረቀት ይዟል። ጨረፍ አድርጌ ተመለከትኩት። የጽሑፌን ቅጅ ዋና ዋና የሚላቸውን ቁምነገሮች መርጦ በቀይ እስክርቢቶ አስምሮባቸዋል። መናገር ቀጠለ...

"ጥሩ፣ ጓድ አላምረው... ደርግ በኢሕአፓ ህልውና ላይ ከፍ ያለ አደጋ መፍጠሩ የማይቀር እንደሆነ የደረስከበት መደምደሚያ አለ። ነገር ግን ደርግ አሁን ወደድነውም ጠላነውም ወደ አብዮታዊነት ያዘነበለ ተቋም እየሆነ ነው የሚል ክርክርም በሌላ በኩል ይነሳል። የሚያወጣቸው ፖሊሲዎች ግራ ዘመም ናቸው። የመሬት ዐዋጁን በድፍረት አውጇል። አንዳንዶች እንዲያውም ‹አብረን ብንሠራ አይሻልም ወይ?› የሚል ጥያቄ ያነሳሉ። ይህ ሆኖ ሳለ መደምደሚያህ ይህንን ማለቱ ግራ ያጋባል።

ደስ የማይል ጥያቄ ነው። በዚህ ጉዳይ ሀዋጁን [illegible] ታላቁን ስህተቱን መድገም አልፈልግም። ብልጭ ሊልብኝ ሲፈልግ ራሴን ተቆጣጥሬ ፈርጠሆ ብዬ መለስኩለት

"ደርግ በአጭር ጊዜ ወደ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነናዊ ጁንታነት ይለወጣል። ይህ የሚሆነው በመግዛት ፍላጎቱና በመደባዊ ጉድለቱ መካከል ያለውን ቅራኔ የሚፈታበት ብቸኛ ዘዴ ስለሆነ ነው። ይህ በሆነ ቁጥር ቫዮለንስን በቋሚነት የሙጥኝ ይላል። ስለዚህም ኢሕአፓ ከደርግ ጋር እንኳንስ አብሮ መሥራት ይቅርና አብሮ ማፍረስም አይችል!"

በእርግጠኝነቴ ብዛት ይሁን አኳኋል ደረቀ ሆኖባቸው ሁለቱም በትኩረት አያዩኝ ፈገግ አሉ። ከዚህ በኋላ ቃለመጠይቅ የሚመስለው ውይይታችን አንድን ሐሳብ በሌሎች ቃላት መድገም ጀመረ። ለልቋል ማለት ነው። ማስታወሻ ደብተሮቻቸውን አጥፈው በየነበሩበት መያዙቲያ አካሎቻቸው አስገቡ። ብርሃነመስቀልን ቆሞ ሳየው ገጠር በዘመዶቼ መካከል ያለሁ መሰለኝ። ሳቁ ሲፈታተነኝ መልሺ አረቅኩት። አንዳንዴ ከመጠን ያለፈው የኢሕአፓ ሕቡዕነት ትርጉሙ ይጠፋብኛል።

'ምሥጢር በጠበቀ ቁጥር በዚያው ልክ ዲሞክራሲ ይቀጭጫል። ግንኙነታቸው እሉታዊ የመጠፋፋት መስተጋብር ነው።' እላለሁ ለራሴ፣ በምሥጢራችን መክረር ምክንያት አንዳንድ የግልጽነት ጥቅሞችን ማጣታችንን ሳይ።

ከመሰነባበታችን በፊት ብርሃነመስቀል በጎኑ ያነገበውን የጨርቅ ከረጢት ከፍቶ ጥቅል ወረቀቶች አውጥቶ ሰጠኝ። ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ የተገነጠሉ ጽሑፎች ናቸው። ተቀብዬ በጎኔ ሻጥ አደረኩት። ከሁለቱም ጋር ተሰነባብቼ ደረጃውን ወርጄ ወደ ምድር ቤቴ ገባሁ። በመሀሉ ቀደም ብሎ ልቤ ውስጥ ያልነበረ ጥያቄ መጥቶ ጭንቅላቴን ገጭ አደረገው፤ 'የብርሀነመስቀልና የጌትሽ ፍላጎት ምንድነው?'

***

ጋራዥ ሦስት ደንበኞችን አስተናግጄ ከሸኘሁ ከደቂቃዎች በኋላ ጎይቶም ለባሲ መጣ። ገና ብቅ ሲል የረሳሁት ነገር ትዝ አለኝ። ኢሕአፓ ሜክሲኮ አደባባይ አካባቢ ሌላ አነስተኛ ጋራዥ ባለቤት ሆኗል። በውርስ ይሁን በግዥ አላውቅም። ጎይቶም ከአንድ ወር በኋላ ከአምስት ጓደኞቹ ጋር ለተወሰነ ጊዜ ወደዚያው ይዛወራል። በጣም እየተለማመድን ስለነበረ ቅር አለኝ። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ አዲስ ስለገባችው መኪና ብልሽትና የጥገና ደረጃ አስረዳኝ። ቃል በቃል ዋናው መዝገብ ላይ አሰፈርኩት። ጨርሰን ጎይቶም ሊወጣ የቢሮዬን በር ሲከፍት ዋናው በር አካባቢ በኃይለኛ ቁጣ እየጮኸች የምትናገር ሴት ድምጽ ተሰማን።

"ምንድነው? ምን ተፈጠረ?" ግንባራችንን ከስክስ አድርገን ተጠያየቅን።

ተንሰተን ከመውጣታችን በፊት የሴቷ ድምጽ ቢሮዬ በር ደረሰ። ጠይም፡ ወፍራም፣ የፊቷ ገጽ ምቾት የሚታይበት፣ ንጹህ የለበሰችና ነጠላ የደረበች ሴት ናት። በመጣችበት ፍጥነት በሩን በርግዳው ገባች። መላ አካሏ በቁጣ ይንዘፈዘፋል...

"አንተ ነህ አይደል፣ የዚህ ጋራዥ ኃላፊ?" ደም በጎረሱት ዐይኖቿ ቁልቁል እያየች አፈጠጠችብኝ።

"እመቤት፣ የተቆጡ ይመስለኛል። መጀመሪያ ይረጋጉ። ይቀመጡ..." ረጋ ብዬ አጠገቧ ወደነበረ ወንበር አመለከትኳት።

"እናንተ እያላችሁ ምን መረጋጋት አለ? ደ'ሞ እኔ በሌለሁበት ቤቴ ሰተት ብለህ መጥተህ የልብህን ከሠራህ በኋላ እንደ ንጹህ ሰው ተረጋጊ ባይ ሆንክ! አሁን ችግር ሳይከተል ተነስና ወደ ሕግ ቦታ እንሂድ!" አገር ይያዝልኝ አለች።

እንደተሳሳተች ገብቶኛል። የደምፍላቷ ብዛት ግን ሊያነጋግረን አላስቻለንም። ከላይ ከላይ ስድብ እያዘነበችብኝ እንገቴን ልታንቀኝ ተገለገለች። ሐውልት መስዬ በጸጥታ ቁልጭ ቁልጭ እያልኩ እከታተላታለሁ። የጋራዡ ዘበኛ መጥተው ከጎይቶም ጋር ሊያበርዷት ታገሉ። በጄ አላለችም። ስድብና ዛቻ እየቀላቀለች ታወርድብኝ ቀጠለች...

"ባለቤቱ በሌለበት ግቢ መግባትን ማን ነው ያስተማረህ? ደ'ሞ እንደ ንጹህ ሰው እዚህ ቁጭ ብለህ ጠበከኝ። ዘውድነሽን አታውቃትምና! ወንበዴ ነህ፣ ከሙሴ ባልዲ የባሰክ እልም ያልክ የሰፈር ወንበዴ!" ቀኝ እጇን ወዲያና ወዲህ አወራጨችው።

በዝምታዬ ቀጠልኩ። ከእኔ ይልቅ ጎይቶም ግልፍ አለበት።"ዋእ! ምን ትያለሽ አንች? በቃ፣ ወይ ችግርሽ ተናገሪ ወይ አፍሽ አሳርፊ!" በቁጣ አፍጥጦ ተጠጋት።

"ፖሊስ ይዤ እመጣለሁ። የትም አትደርስም። ቀማኛ!" እየተወናጨፈች ወጥታ ሄደች።

ከጎይቶምና ከዘበኛው ጋር ግራ በመጋባት ተያየን። "በዚች ትንሽ ነገር የመጣ ፖሊስ ሌላ ጣጣ ቢፈጥርብንስ?!"

# 9

ሠራተኞች ለምሳ ሲወጡ ጸጥታ ነገሰ። የዘለፈችኝን ሴትዮ ድርጊት ወዲያውኑ ነው የረሳሁት። እንዳለችው እሷም ፖሊስ ይዛ አልተመለሰችም። ያንን ሁሉ የስድብ መዓት ስታወርድብኝ ቆይታ ማንነቴን ስታውቅ ምን እንደምትል ባይ ደስ ይለኝ ነበር። ጸጥ ብዬ ተቀበልኩት። እንዲህ ዓይነት ገጠመኝ ያለኝ ግን እኔ ብቻ አይደለሁም። ዘርዑ ከሕሸን ራሱ የዛሬ ሁለት ዓመት ያጋጠመውን ነግሮኛል።

በሚሰራበት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ነው። የማኅበሩን መጽሔት ከሚያዘጋጁት የሕዝብ ግንኙነት ባለሞያዎች አንዱ ነው። አለቃው የማኅበሩ ሊቀመንበር ከመንግሥት ጋር ተፋጠዋል። አለመግባባቱን የማኅበሩ መጽሔት ፍርጥ አድርጎ እንዲያወጣው ይፈልጋሉ። ሲያዩት ግን እንጀት የሚያርስ አይደለም። በቁጣ ቱግ ብለው ዘርዑንና ከፍሉ ታደሰን አስጠሯቸው። መጥተው ቀረቡ...

"እናንተ፣ ወጣቶች አይደላችሁም? በእናንተ ዕድሜ ያሉ የቬትናምና የአልጄሪያ ወጣቶች ስንትና ስንት ተዐምር ይሠራሉ። እናንተን ምንድንው እንደዚህ የሚያንበቀብቃችሁ?! ወደ እናቶቻችሁ ሄዳችሁ ማገዶ ብታቀብሉ ይሻላችኋል..." ወረዱባቸው።

ሊቀመንበሩ ኢሕአፓን የሚያከል ግዙፍ ድርጅት የሚመሩ ሰዎችን እያበሻቀጡ እንደነበር የሚያውቁት ነገር የለም። ከፍሉ ታደሰ በትእግስት ስድቡን ዋጥ አደረገ። ዘርዑ ግን ጨጓራው ተቃጠለ። ፈሪ አለመሆኑን ነግሯቸው ብቻ ወጣ። እኔም ሕቡዕነት ገና ብዙ እንደሚያሳየን አስታውሼ ዝምታን መረጥኩ።

ቢሮዬን ዘግቼ ለምሳ ወደ ምድር ቤት ለመሄድ ዘር ስል በሩ ተንኳኳ። ኢሳያስ ነው። ፊቱ ላይ የሆነ እንግዳ ስሜት ያየሁ መሰለኝ።

"ኢሱ፣ ምን ሆነሃል፣ ችግር አለ እንዴ?"

"ችግርማ ምን ይጠፋል ብለህ...ሰመሬ?" ..."ግን በጣም እርቦኛል፣ እዛው ሄደን እየበላን ባወራህ ይሻላል..." በምሥጢር በሩ በኩል ተራ በተራ ወጣን።

***

ከምሳ በኋላ ሸዋዬ ኢቃ አነሳስታ ስትሄድ ደምጻችንን ቀንሰን ወሬ ጀመርን። የስሜት ሕዋሶቼ ቅልብልብ አሉ። እንደተለመደው የሚገደፋቸው የአማርኛ ቃላት እንደሌሉ አድርጌ የሚነግረኝን በአንክሮ አዳምጠው ጀመር...

"ሰመሬ፣ አንተ ያላወካቸው እኔም ያልነገርኩህ ችግሮች ድርጅታችን ውስጥ ተፈጥረዋል። ምናልባት አንዳንዶቹን ከራስህ ትንተና ተነስተህ ደርሰህባቸው ይሆናል።" ሲጋራ ለኮሰ።

"ኢሱ፣ ስለመሠረታዊ የድርጅት ችግሮች ነው የምትነግረኝ ወይስ የዕለት ተዕለት እንቅፋቶች?"

"ኖኖኖ..." የሲጋራውን ጢስ በአፍንጫውና በአፉ ቡልቅ ቡልቅ አድርጎ ቀጠለ፣ "መሠረታዊ የሆኑ አሉ፣ ወደዚያው ሊያድጉ የሚችሉም ይኖራሉ። ከዚያ በፊት ግን እኔ በመጭዎቹ ቀናት አልኖርም። ሲዳሞና ሸዋ ለጥናት ሥራ እንድሄድ አዘውኛል። በመሀል የማእከላዊ ኮሚቴው ከተሰበሰበ በተለዋጭ አባልነት የምትገባው አንተ ነህ። እና አስቀድመህ ልታውቃቸው የሚገቡህ ነገሮች አሉ። ስለ ጓድ ብርሃነመስቀል በተለይ መረጃ እንደሌለህ ገብቶኛል። ካለፈው ዓመት ግንቦት ወር ምናምን ጀምሮ የፓርቲው ዋና ጸሐፊ አይደለም። እዛው ኢሲምባ እያለ ነው ያወረዱት..."

"እንዴ——ዴ...ኢሱ፣ ምንድነው የምትለኝ?" ደራሽ ድንጋጤ ወገብ ዛላየን እያቀቀው፣ "ብርሃነመስቀልን? ለመሆኑ በምን ምክንያት አወረዱት?"

"ያው ገና ፓርቲውን በርሊን ላይ ሲመሠርቱ ጀምሮ በብርሃነ ዝንባሌ ደስተኞች ያልነበሩ ይመስለኛል። ጉባኤ ተጠርቶ ውይይት ሲደርግ ማሻሻያ ሐሳብ የመቀበል ፍላጎት አላሳያቸውም። በተለይ ከዘርዑ ጋር ከበ•ርሊን ጉባኤ ጀምሮ አልተጣጣሙም። ንቀት ምናምንም ሳይታዘቡ አልቀሩም። ኢሲምባ እያለም አምባገነንነት ይታይበታል ነው አብዛኛው ክስ። እና ባለፈው ዓመት ግንቦት ላይ ነው። የድርጅቱን መለስተኛ ጉባኤ ሊመራ ከኢሲምባ መጣ። ዘርዑ ከሕሸን በእሱ ቦታ ዋና ጸሐፊ ሆኖ ጠበቀው።" ሲጋራውን ማግ ማግ አደረገ።

"ብርሃነመስቀል በሌለበት?" መንፈሴ ብርዥርዥ አለ።

"እዎ፣ እሱ ባልተገኘበት ምርጫ ነው ያወረዱት። ጉዳዩን ግን ከብርሃነመስቀል ባህርይ ጋር ማያያዝ

አልፈለጉም። የፓርቲ ዋና ጸሐፊነት ቦታ በየአገሩ ግራ ዘመም ፓርቲዎች ውስጥ ምን እንደፈጠረ አጥንተናል አሉት። እንባገነንነት የብዙዎች ችግር ሆኖ ስላገኙት እንደለወጡት ነገሩት። 'ፕሮሲጀሩ' ከበርሊኑ ደንብ ጋር እንደሚጻረር እሱም ሌሎቹም ያውቃሉ። ነገር ግን ምንም ማድርግ አልቻለም።"

"እ--ን--ዴ.--ት? እንዴት ተደርጎ ጉባኤ የሰጠው ሥልጣን በማእከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ ይወሰዳል? ይሄማ መፈንቅለ-አመራር ነው!" ኢሳያስ ተሳስቷል ብዬ የሚነግረኝን ለመጠራጠር ተቸገርኩ።

"ስመሬ፣ ቢቃ...የሥልጣን ግብግብ ገና ከአሁኑ አሳፋሪ ስለሆነበት ዝም አላቸው። በኋላ ግን አምና ኢሕአፓ በታወጀበት መለስተኛ ጉባኤ ሕጋዊ አደረጉት። ጉባኤው ለዋና ጸሐፊነት ይቅርና ለፖሊት ቢሮ አባልነት እንኳን ሳይመርጠው ቀረ። አሁን ተራ የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ብቻ ነው። አበበ ዋቅጅራ ሲጨንቀው 'የእኔ ፖሊት ቢሮ አባልነት ይሰረዝና ብርሃነመስቀል ይግባ' አለ። እንኳን እነርሱ ብርሃነመስቀል ራሱም ፈቃደኛ የሚሆን አይመስለኝም..." ኢሳያስ ሲጋራውን ሽምጥጥ አደረገው።

በበኩሌ የነገሩን ጭንቅላትና ጅራት በመለየት በኩል እእምሮዬ ተንጠልጥሎ የቀረው በመጀመሪያው ነጥብ ላይ ነው። "ብረሃነመስቀል በሌለበት ዘርዑ ከሕሸን ዋና ጸሐፊ ሆኖ ተመርጦ አገኘው!" ይህንን በምንም ምድራዊ ተዐምር አልቀበልም። ከዚያ በኋላ የተሠራውና ወደ ፊትም የሚሠራው ስህተት ሁሉ የዚህኛው ስህተት ተፈጥሯዊ ቅጥያ ነው። በጣም ቅር አለኝ...

"ኢሱ፣ እኔ ይሄን ነገር እንደቀላል ግድፈት አላየውም። በጭራሽ መሆን ቀርቶ መታሰብ አልነበረበትም። ይሄንን የምለው ለብርሃነመስቀል በመቆርቆር አይደለም። ለድርጅቱ በማሰብ ነው። ብታምንም ባታምንም በጉባኤ የተመረጠን መሪ ያለ ጉባኤ ማንሳት የለየለት ጀብደኝነት ነው። ቢቃ፣ ይሄ ሸር የድርጅታችን 'የመጀመሪያው ኩነኔ' ነው።" እጆቼን በስሜታዊነት አወናጨፍኳቸው። የመጀመርያው ኩነኔ!

ኢሳያስ ያለቀች ሲጋራውን ማጠራቀሚያ ስኒ ውስጥ ደፍጥጦ ወደ እኔ ዞረ...

"ስመሬ፣ ያው በድርጅቱ የዲሲፕሊን ገድብ ምክንያት ነው ሳልነግርህ የቆየሁት። እና ይሄ ለአንቴ አዲስ ስለሆነብህ ነው እንጂ አሁን ተረስቷል። ይልቅ አሁን ሌላ ፈተና ነው የመጣው። 'ፓርቲው ትግሉን እንዴት ይቀጥል?' በሚል ጥያቄ ላይ መግባባት አልቻሉም።"

"እና ምን እያደረጉ ነው፣ ኢሱ?"

"እ—ይ፣ አንተ ጅማ እያለህ አዳዲስ ነገሮች ተፈጥረዋል። በዝንባሌ ደረጃ የመከፋፈል ነገር አለ።ብርሃነመስቀልና ጌታቸው ማሩ አንድ ላይ ናቸው። 'ደርግንና መኢሶንን ጨምሮ ከሌሎች ግራ ኃይሎች ጋር መተባበር ያስፈልገናል' የሚል አቋም ይዘዋል። ሌሎቹ በተለይ ዘርዑ፣ ተስፋዬና ከፍሉ ታደሰ 'ይህ

የማይሆን ነው ብለዋል። በኃይል ተከራክረው ተከራክረው ለመቀራረብ ሞከሩ። 'አብሮ የመሥራት ጥያቄ በመርህ ተይዞ ከደርግ ጋር ውይይት እንዲጀመር ትላንት ተስማምተዋል። የሚሆን ግን አይመስለኝም...' ሌላ ሲጋራ ለኮሰ።

የምሰማው ሁሉ ቴሌቪዥን ላይ የምመለከተው ዓይነት ድራማ መሰለኝ። በአንድ ወር ውስጥ ይሄ ሁሉ መፈጠሩ አስደነገጠኝ። 'ከደርግና መኢሶን ጋር ትብብር?? ይሄ ቅገርት ሲንኳተት ከርሞ ከፖሊት ቢሮው ደረሰ?' ምድር ልትከደኝ ምንም አልቀረኝም።በተለይ መኢሶኖችን ሳስብ ሁሌም ደሜ በቁጣ ይንተከተካል። "መኢሶን ማለት የቤቱ ጌታ ሳይጠራው ከውጭ መጥቶ የለመደ እንግዳ ውሻ ነው።" ዘሩ ከሀሸን ያሟውተኝን አልረሳውም። መኢሶኖች አርቀው ማሰብ የተሳናቸው ፖለቲከኞች መሆናቸውን አራት ማስረጃዎች ጠቅሶ አስረድቶኛል...

"የኢሕአፓ መሥራቾች 1964 ዓ.ም ላይ 'ኢትዮጵያ ውስጥ በቅርብ ጊዜ አብዮት ይፈነዳል' ብለው ተነበዩ። ኃይሌ ፊዳና መኢሶን ይህንን ትንቢት አልተቀበሉትም። እንዲያውም 'ከ25 ዓመት ወዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ አብዮት የሚባል ነገር አትጠብቁ' አሉ። ሳይገላቸው ቀረና የ1966 አብዮት ፈነዳ። በዚህ ጊዜ ግራ ገባቸው። ሁለተኛውን ስህተት የሠሩበት ጊዜ መጣ። የአክሊሉ ሐብተወልድ ካቢኔ ቀውሱን መቋቋም ተስኖት ወደቀ።የእንዳልካቸው መኮንን ካቢኔ ተተካ።ብርሃነመስቀል፣ 'እህስ፣ የሚሆነውን ነገር እያያችሁ ነው?' ብሎ ኃይሌ ፊዳን ጠየቀው። ከኃይሌ መልስ ሲያጣ፣ 'አዲሱ ካቢኔም ይወድቃል!' አለው። የኃይሌ ፊዳ መልስ ግን አሁንም ከህደት ነበር። 'ይወድቃል ብዬ በጭራሽ አልጠብቅም፣ እንዲያውም ከአዲሱ ካቢኔ ጋር ተባብረን መሥራት አለብን' ብሎት ዐረፈው..."

"ብርሃነመስቀል ተስፋ አልቆረጠም። በሌላ ጊዜ ከኃይሌ ጋር ቀጠሮ ይዘው ተገናኙና አንድ ሐሳብ አነሳለት። 'የአገራችንን ሁኔታ እንደምታየው ነው። አብዮታዊውን ሁኔታ የሚመራ መሪ ድርጅት አልተገኘም። ስለዚህ አብዮቱ የመቀልበስ እድሉ ከፍተኛ ነው። በተራዘመ የመስከ ትጥቅ ትግል መረነቱን ጨብጠን አብዮቱን ከግብ ማድረስ አለብን' አለው። ኃይሌ በንቀት ፈገግ ብሎ፣ 'እንኳንስ የተራዘመ ትጥቅ ትግል ይቅርና የገማ እንቁላልም ቢሆን መወርወር የለብንም' አለው። ይሄው አሁን ደግሞ አራተኛውንና ትልቁን ከህደት ፈጸመ። ያለምንም ቅድመሁኔታ የደርግ አፈ-ንጉሥ ሆኖ ድርጅታችን ላይ በጠላትነት ተነሳ..."

ሳስታውሰው ልክ ገና አሁን እንደተነገረኝ ሁሉ ንድድ አለኝ። ወደ ኢሳያስ ተመልሼ ሲከነክነኝ የቆየ ጥያቄ አነሳሁለት...

"እና አመራሮቹ በተናጠል እያገኙ ሐሳባችንን ይጠይቁን የነበረው ለዚህ ነዋ?!"

"አዎ፣ በተለይ ያንተን የጅማ ሪፖርት በተለያየ መንገድ ተርጉመው ሊጠቀሙበት ሞክረዋል። ብርሃነመስቀል 'ሪፖርቱ የከተማ አመጽ ሥልት እንደማያዋጣ አሳይቶኛል' ብሎ ተረጎመው። መፍትሄው 'ከደርግ ጋር

መተባበር ነው' አለ። እነ ዘርዑ ደግሞ 'ሰላማዊ ትግሉ እያበቃለት መሆኑን አሳምኖናል፤ መፍትሄው 'ራስን መከላከል ነው' አሉት።" በረጅሙ ተነፈሰ።

ሁለቱም የእኔን የመፍትሄ ሐሳብ ሆን ብለው እንደዘለሉት ገባኝ። "መፍትሄው ድርጅቱ ከተሞችን ለቆ በገበሬው መሀል የትጥቅ ትግል ማካሄድ ነው" ማለቴ አልተዋጠላቸውም። ከመገረም አልፈ ነገሩ ፈጽሞ የተለየ አቅጣጫ መያዙ የፖለቲካ ሥነልቦናና የሥነ ዕውቀት ዝንፈት እንደሆነ ስገነዘብ በጣም አሳሰበኝ። ግልፍ አለብኝ...

"ሁለቱም እንደዚያ ካሰቡ ለምንድነው ታዲያ ኢሕአሠን እዛ ተራራ ላይ አንጠልጥለው ለአንግልት የሚዳርጉት? ለምንድነው ሸዋና ሲዳሞ አዲስ መነሻ መሠረት ፍለጋ ጥናት የሚያደርጉት? 'ከመጀመሪያው ፕሮግራማችን አልወጣንም ለማለት መረጃ ማዘጋጀታቸው ነው? እኔ ይሄ የሚዋጥልኝ ነገር አይደለም። እዚህ ከተማ ውስጥ ከደርግና ከመኢሶን አፍንጫ ሥር የመነለት ፍላጎት የፈጠረው ተራ የፖለቲካ ግብረመልስ ነው!" ቃላቴ ጠንከር ማለታቸው ለእኔም ታውቆኛል።

"ሰሙ፣ ይሄ ያልከው የችግሩን ምንጭ በመረዳት በኩል አንድ ቲዮሪ ነው። በደንብ ተዘጋጅተህ ጥናት ሥራበት። በሚቀጥለው የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ተጽእኖ መፍጠር አለብን። አሁን እኔ ልሂድ። ደብረብርሃን ገብቼ ማደር ይኖርብኛል..." ኢሳያስ ተለይቶኝ ሄደ...

ጭንቅላቴ ብጥብጥ አለ። ወደ ቢታኒያ ብረር ብረር የሚል ግፊት መጣብኝ። ቢታኒያና ፍቅሯ የተወጠረ መንፈሴን ለማርገብ እንደሚረዱኝ ግን እርግጠኛ አይደለሁም!

***

ጊዜው ወደ ምሽቱ ሲቃረብ ቢታኒያ በዐይነህሊናዬ ብቅ አለች። ጥሎ አልጣለኝም። ከዛሬ ጀምሮ ብርኩታዊትን አሰናብቼ የቢታኒያ ሆኛለሁ። መጽሐፉ "እንደ ሰንፔር ያብረቀርቃል" የሚለው ያ የከበረ ማዕድን የቤቲን ዓይን ሳይሆን ይቀራል?!'። አሁን ያ ዉበት በእጄ ገብቷል።

ከቢታኒያ ጋር በፍቅር አፍ ማለቴ በድርጅቴ ቢሰማ ምን እንደሚሉ አላውቅም። ለነገሩ ብዙዎቹ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ፍቅረኞች እንዳሏቸው ዐውቃለሁ። እንዲያውም አንዳንዶቹ ጋብቻ ሁሉ የፈጸሙም ይመስለኛል። ብርሃነመስቀልና ታደለች ኃይለሚካኤል፣ ዶክተር ተስፋዬና ፍቅርተ ገብረማርያም፣ ዘርዑና ታደለች ኪዳነማርያም፣ ፀሎተ ሕዝቅያስና ሁናይት፣ ጌታቸው ማሩና ሕይወት ተፈራ ተጣምረዋል። እኔ ላይ ሲደርስ አዲስ ነገር ሊሆን አይችልም።

እንደው አይበለውና በሆነ አጋጣሚ ግን አንድ አጣብቂኝ ገጠመኝ ልበል...

"ሰመረ፡ ወይ ቢታኒያን ወይ ድርጅትህን... ከሁለቱ አንዱን ምረጥ!" ተባልኩ። ምን ይጨጠኛል? አስብኩበት። መልሴ የማያወላዳ ነው። ልክ ብርከቷ ላይ እንዳደረኩት ቢታንያንም ሳላቅማማ ቻው! እላታለሁ። ይህ ማለት ግን ለፍቅር ግድየለሽ መሆን ማለት አይደለም። ብዙ ወንድ ፈላስፎች ስለ ሴት ልጅ ፍቅር ያላቸው አስተሳሰብ አሉታዊ እንደሆነ ዐውቃለሁ። ከብዙ ፈላስፎች ጋር እዚህ ነጥብ ላይ እንለያያለን።"ጾታዊ ፍቅር እግዜአብሔር ካለ መለኮታዊ ነው። እግዚአብሔር ከሌለም ባህርያዊ ነው! ሰው ሊያፈቅር የተፈጠረ እንስሳ ነው።" ፍንከች የማልልበት የዘወትር አቋሜና እምነቴ ነው።

ቢቷን ቶሎ ሄጄ ላያት ፈለኩ። 'አዎ፡ ትክክል ነኝ!!' ደግሜ ራሴን አሳምኜ ከወንበሬ ብድግ አልኩ፣ 'ቤቷ፣ መጭው ጊዜ ካንች ጋር ሕይወትን የማጣጥምበት ይሁንልኝ! ከኢሕአፓ ጋር ደግሞ የማይቀረውን ትግልና ድል!'በተለመደው ምሥጢራዊ በር ወጥቼ ከቀዩ በር ደረስኩ...

ኳ ኳ ኳ ኳ... ገና ከማንኳኳቴ የሚካኤል ኮቴ ወደ እኔ ሲመጣ ተሰማኝ።'ቢ—ታ—ኒ——ያ፣ መምጣቴን አውቀሻል?' ሚካኤል በሩን ከፍቶልኝ ስገባ የቢታኒያ መኖሪያ ክፍል በር መዘጋቱን በማየቴ ልቤ ሽቅብ ዘላ ተመልሳ ቁልቁል ስር——ግ አለች።

ቀጥ ብዬ ወደ ዋናው ቤት ገባሁ። ሶፋቸው ላይ ጋደም ብለው የነበሩት ወይዘሮ ማስተዋል መምጣቴን ሲመለከቱ ነቃ ብለው ተቀበሉኝ። አሁን አከራዬና ጎረቤቴ ወይም ቀጣሪዬና አሠሪዬ ብቻ አይደሉም። የፍቅረኛዬም እናት ጭምር ሁነዋል። ሳይታወቀኝ አክብሮቴና ትህትናዬ ጨመረ። የተለመደውን ሥነ-ሥርዓት ተከትዬ ገንዘቡን አስረከብኳቸው።'ማህጸን እንዲህ ነው!' በሆዴ ቀረርቶ ቢጤ ለራሴ አሰማሁት። ወይዘሮ ማስተዋልን ተሰናብቼ ከግቢው ለመውጣት ከበሩ ስደርስ ዐይኖቼን ወደ ሰርቪስ ቤቱ መስኮት ወረወርኳቸው።

'አ—ው! አፍሮዳዊቷ የሐበሻ ቆንጆ!' ቢታኒያ የመስኮቱን መጋረጃ ገላልጣ ቆማለች። ዐይኖቻችን ተፈላልገው ግጥምጥም አሉ። መቼም ዐይኖቿ የስሜቶቿ መዝገበ-ቃላት ናቸው። ያሰበችውን ፍንትው አድርገው ይነግራሉ። ቁንጅና ባይኖር ፍቅር እንዴት ጎደሎ ይሆን ነበር? በጭንቅላቷ ንቅናቄ ምልክት ሰጠችኝ። "ና!" ሄጄ ከፊት ለፊቷ ቆምኩ...

"ሰሙዬ፣" ብላ ለመጀመሪያ ጊዜ በፍቅር ቁልምጫ ጠራችኝ። መንፈሴ ደርሶ ተሰወረ፣ "ሰሙዬ፣ ጨዋታ እፈልጋለሁ፣ እሺ? ከሁለት ሰዓት እስከ ሁለት ተኩል ምናምን ያንተ ጊዜ ነው። ማሚን እንዳትፈራ፣ እጠብቅሀለሁ።ታዲያ እንዳታንኳኳ! በሩ ተከፍቶ ይጠብቅሀል። ስትሄድ ዘግተኸው ትሄዳለህ። እሺ፣ ጌታዬ?' ዓይኖቿን ስሜቷን ተከትላ ቋንቋ አናገረቻቸው።

"እሽ፣ ቤቲዬ...ቃልሽ ይፈጸማል!" እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ በቁልምጫ ጠራኋት።

# 10

ሸዋዬና ደጀኔ ለእራት እየጠበቁኝ ደረስኩ። ለምግብ ብዙ ጊዜ ሰዓት አክብረን የምንገናኘው ሦስታችን ነን። ኢሳያስ ሰዓት ብሎ ነገር አያውቅም። ሲርበው ብቻ መጥቶ ይበላል። በድርጅታችን ከሚሰጠን የኑሮ መደጎሚያ 12 ብር ብቻ ለምግብ እናዋጣለን። ኢሳያስ ግን ሲያዋጣ ዐይቼው አላውቅም። ምናልባት ሸዋዬ ከእኛ በምትቀበልበት ጊዜ እሱ ስለማይኖር ይሆናል። ሲመጣ በሲጋራ ጨርሶታል። ስንጥር ታክል ቅር አይለንም። አብረን ወሩን እንገፋዋለን።

"ጓድ አላምረው፣ አበላልህ እንዴት ነው? እማቱ ቤት የተጋበዘ ሙሽራ መሰልክኮ!"

"እኔም እንደዛ ልለው ስል ቀደምሽኝ!" ደጀኔ ከት ብሎ ሳቀ።

ቢታኒያ ጥልቅ እያለች ሐሳቤን በወሰደችው ቅጽበት አለመብላቴን አይተው ነበር እንደዛ ያሉኝ። ምሥጢሬን ግንባሬ ላይ ያነበቡብኝ መሰለኝ። እየተጎራረስን ጭምር በላን።ለኢሳያስና ለእኔ ያላቸው አክብሮት መቼም የተለየ ነው። ዕድሜያችን ዲግሪ የጫነ ሰው በወጣትነቱ ለሥልጣንና ለገንዘብ የሚሟሟትበት ነው። ከፍቅረኛ ጋር ወገብ ለወገብ ተቃቅፎ እየተንሸራሸረ የሚላላስበት ጊዜም ነው። በዚህ የዕድሜ እርከን ላይ እኛ ለድርጅት ተልእኮ ስንል እንደዚህ እንኖራለን። ይህ ሳይሆን አይቀርም እንዲወዱንና እንዲያከብሩን ያደረጋቸው።

"ሸዋዬ ግ...ን እጠይቅሻለሁ እያልኩ እየረሳሁት። ሁሌ ከኛ ጋር ነሽ። መች መች ነው ወደ ቤተሰቦችሽ የምትሄጅው?"

"አይ አላምር፣ ምን ቤት አለኝ ብለህ ነው?! ባለቤቴ ማይጨው ጦር ሰፈር የወታደር መሀንዲስ ነበር። ልጅ እምቢ ብሎን አልወለድንም። አረግዛለሁ ግን አልጨርሰውም። ከከፍለሐገር ነበር እግብቶ

ያመጣኝ። እስተምሮ አዚያው ጦር ሰፈር ሥራ አሲይዞኝ ነበር። ባለፈው ዓመት መጨረሻ አካባቢ ጠፉ ደርግን እናውቅም ብሎ ዐመፀ።ባለቤቴ ከአስተባባሪዎቹ መካከል ነበር። ደርጎች ገደሉት..."

ደስ የማይል ጥያቄ ማንሳቴ ወዲያው ነው የገባኝ። ደጀኔ ሌላ አጀንዳ አንስቶ ወሬያችንን ሲያስለውጠው ደስ አለኝ። ከደቂቃ ደቂቃ መቅበጥበጥ ጀመርኩ። እንደሰሞኑ አብረን እያወራን ለመቆየት ትእግስት አጣሁ። ወደ ቢታኒያ ለመመለስ አንድ ምክንያት መስጠት ሊኖርብኝ ነው። የሆነ ሥራ እንዳለኝ ነግሬያቸው ወደ ምድር ቤት ወረድኩ።

'እንዴት ነው የምሄደው? በደኅንነት መስኮቷ በኩል ውጥቼ ልሂድ ወይስ በጋራዥ በኩል?' ጭንቅ አለኝ።

ቁጭ ብዬ ብርሃነመስቀል የሰጠኝን ወረቀቶች ባነብ ምርጫዬ ነበር። ነገር ግን ይሄንን የማደርግበት አድብ የለኝም። በዚህ ላይ እሱ "በዛብህ በላቸው" በሚል የብእር ስም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የሚጽፋቸውን መጣጥፎች በሙሉ አንብቢያቸዋለሁ። ጥልቀትና ብስለት አላቸው። እነርሱን ይሰጠኝ ወይም ሌላ ያላየሁት ጽሑፍ ይሁን እርግጠኛ አይደለሁም። ያም ሆነ ይህ ተቀምጬ ማንበብ አልቻልኩም። ወደ ቢታኒያ ሂድ ሂድ አለኝ።

ከአንድ ሰዓት በኋላ ተመልሼ እንደምመጣ ነግሬያቸው የመኪና ቁልፌን እያንቀጫቀጭኩ ወደ ጋራዥ ለመሄድ ተነሳሁ። ሽዋዬና ደጀኔ አሁንም የምግብ እቃው እንዳለ ቁጭ ብለው እያወሩ ነው። ዐይኔን ዐይተው ምሥጢሬን የሚያውቁብኝ ስለመሰለኝ ቀና ብሎ ማየት እንኳ አልቻልኩም። የጣውላውን በር ከፍቼ የምሥጢር መንገዴን ይዤ በዝግታ ስሄድ ሐሳቤ ሙሉ በሙሉ ወደ ቢታኒያ ተመለሰ። የተዛባው የደሜ ዝውውር ተመልሶ መደበኛ ፍጥነቱን ሲይዝ ተሰማኝ። 'ቢታኒያ! ውበት በእድሎ የተቸራት የገነት ተከል!' ልቤ ደነሰች።

ቀዩ በር በትንሹ ገርበብ ብሏል።ኮቴየን እንኳ ሳላሰማ በጥንቃቄ ከፍቸው ስገባ ሌላው ቀርቶ ንቁው ውሻቸው ዳግላስ እንኳን አልሰማኝም። ለነገሩ አሁን በደንብ ለምዶኛል።የፈራሁት ወይዘሮ ማስተዋልን ነው። በሆነ ሰይጣን እየተመሩ መጥተው ከፊት ለፊቴ ድቅን ቢሉብኝስ? 'ጉድ ፈላ!' አንገቴን ሊያንቁ እየተገለገሉ በስድብ ጥንብ እርኩሴን ሲያወጡኝ ታየኝ...

"እንዴ! እንዴ! እንዴ! ጥባ ብለው የላኩት ጥጃ ሰሮ ተመለሰ አሉ! ለመካኒክነት ብቀጥርህና ቤቴን ባከራይህ ልጄን ተመኝተሀት አረፍከው? አባወራነት አማረህና በውድቅት መጥተህ ቤቴን ደፈርከው? በል፣ በል፣ በል...ነገ ወፍ ውኃ ሳትቀምስ ቁልፌንና ቤቴን አስረክበኸኝ ው---ል----ቅ!" በአሳታዊ ቁጣቸው ያንዱኛል። አሰብኩ። ከዚያማ ማኅበራዊ ቅሌቴ ፖለቲካዊ ቅሌቴን ያስከትላል። ጉዳዩ ከእነ

ታደሰ ከፍሉና ከአነ ዘርዐ ጆሮ ይደርሳል። በጥድፊያ በማእከላዊ ኮሚቴ ፊት እንድቀርብ ይደረጋል። እንደ በርበሬ በሚተንትን ሂስ እለበለባለሁ።ከዚያ ተራ አባል እንድሆንኩ መወሰኑ ይነገረኛል።

'የሞት ሞት ነው!' ጉልበቴ ንዝረት ሊሰማው ዳር ዳር አለው።

ቤቷ በር ስደርስ ሞቅ ያለ የአበበ ተሰማ አርምኛ ሙዚቃ ከሬዲዮ ተሰማኝ።ልክ እንደነገረችኝ አድርጌ የመዘጊያውን መቀርቀሪያ ቀስ አድርጌ ነካሁት። ደግሜ ስነካው ከውስጥ በግ ብሎ ተከፈተ። ቢታ---ኒ---ያ መኮንን! የገነት መጋረጃ የተገለጠ መሰለኝ። መደቡ ነጭ ሆኖ የድሙትና የጽጌረዳ ምስሎች በግ በግ ያሉበት ሙሉ በሙሉ ከጥጥ የተሠራ ሱሪና ኮት የሌሊት ልብስ ለብሳለች። ሶሉ መደብ የሚያከል ነጠላ ጫማ አድርጋለች። ቁመቷን ከፍ ያደረገው መስሎ ታየኝ። ጸጉሯን ከሁለት ከፍላ በሁለት ትልልቅ ጉንጉኖች ቁልቁል ወደ ደረቷ ለቃዋለች። የአምፖሉ መብራት ሲያርፍባት እንደ ፍም ደምቃ ታየችኝ።

"ቢ--ታ--ኒ--ያ፣ እጹብ ድንቅ የገነት ፍሬ!" በሩን ከጀርባዬ መለስ አድርጌ ሄጄ ጥምጥም አልኩባት።

"ሰመረዬ፣ አሁን ባትመጣ ኖሮ ነገ ምድር ቀውጢ ትሆን እንደነበር ታውቃለህ?" ከንፈሮቼ ከንፈሮቿን ከማነቃቸው በፊት ጆሮዬ ሥር ተጠግታ ተንሾካሾከች።

ጋዝ ጋዝ የሚሸተው ቱታዬ እኔን ስቅቅ ሲያደርገኝ እሷን ግን ምንም አልመሰላትም። የበለጠ ጠበቅ አድርጋ ጥምጥም አለችብኝ። "ባል ወደሽ ጢሙን ጠልተሽ አይሆንም..." ያለች መሰሎ ተሰማኝ። ቤቷ ከውጭ እንደሚያዩት አይደለም። ባለሁለት ሰፋፊ ከፍሎች መኖሪያ ነው። ንጹህና አዳዲስ የቤት እቃዎች ሞልተውታል። ከጀርባዬ ሙሉ የሶፋ ስብስብ አለ። በአልጋዋ ራስጌ በኩል በመጻሕፍት ጢቅ ብሎ የሞላ መደርደሪያ ይታያል። የወንጀለኛ መቅጫ፣ የፍትሐብሔር ሕግ፣ የንግድ ሕግና ሌሎች የሕግ መጻሕፍት ጎላ ጎላ ብለው ታዩኝ።

'ዩኒቨርስቲ የሕግ ተማሪ ናት ወይስ ይሄ ነገር የሌላ ሰው ነው?'

ኮሽ ባለ ቁጥር ወይዘሮ ማስተዋል ወይም ሚካኤለ የመጡ እየመሰለኝ እበረግጋለሁ። ስደጋግመው ቆጣ ብላ አረጋጋችኝ። ገና የተያየን ዕለት በመከዳጀላችን ይመስለኛል ሁኔታችን የከረሙ ፍቅረኞች ይመስላል። እጆቿን፣ እግሮቿን፣ አንገቷን ወገቧን እስከ እምብርቷ ድረስ እያሻሻሁ ወሬውን ተያያዝነው። ሳላስበው እጆቼ ከዚያም ከፍ አሉ። ጡቶቿን ስጨብጣቸው እጆቼን መልሰው ይገፈትሯቸዋል። ከብብቷ የሚወጣው ጥዑም ሽቶ የተሰላቸን ሕይወት ያድሳል። ልቤ ብርኪታዊትን አምጥቶ ሊያወዳድራት ፈለገ። አልፈቀድኩለትም...

"ቤቲዬ፣ እጅሽ ይታኮሳል። ሥራ ይዘሽ ነበር?" ድምጼ የስስት ቅላጼውን መደበቅ እንዳልቻለ ይሰማኛል።

"አዎ፣ የሆነ ነገር እየጻፍኩ ነበር..." ብላኝ ከጆርባዋ አልጋው ላይ ብትንትን ብለው የነበሩ ወረቀቶችን ሰብስብ አደረገች።

ፈጠን ብላ ትራሷ ስር ሻጥ ስታደርጋቸው ዐይኖቼ አንዱ ወረቀት ላይ አረፉ። ጎላ ተደርጎ የተጻፈ ርእስ ጨረፍ አድርጌ ዐየሁ። "ዲሲፒሊን!!" ልቤ በድንጋጤ ደ--ሽ አለች። ቢታኒያ የአ.ሕአ.ፓን የመከራ ጊዜ ያጠናቀቀች ሙሉ አባል ናት! "ዲሲፒሊን" የመጨረሻው የጥናት ሰነድ ነው። ስሜቴ ከሀዲዱ ወጥቶ ወዲያና ወዲህ ተወሊጋገደብኝ።

"ቤቲ፣ ምን ዓይነት ምትሀት ነው ያለሽ? አሚገርምሽ በጣም በሥራ ተወጥሬ ነው የዋልኩት። ግን ቀኑን በሙሉ ምስልሽ አልተለየኝም። መቼም ይህ የአዲስ ፍቅር አባዜ ሊሆን አይችልም!" አልኳት።

"እንዲያዉም ሰሙዬ! እኔ በሥራ ተወጥሬ ስላልዋልኩ ነገሩ በ'ኔ አይብስም ብለህ ነው...?" ብላኝ ፈገግ አለች።

"በነገራችን ላይ የሥነጽሑፍ ዝንባሌ ምናምን አለህ እንዴ?"

"አዎ፣ ሥነ ጽሑፍ በጣም በጣም እወዳለሁ። ግን በምን ገምተሽ ነው የጠየቅሽኝ?"

"እኔ እንጃ፣ በቃ...ልቅም ያለ አማርኛ ነው የምትናገረው። እና ደግሞ ስታዋራኝ ስሜትህን ለመግለጽ ስትቸገር አላይህም። እእእእ...ምናልባት እኔም መጻፍ ላይ ብዙ አይደለሁም እንጂ ማንበብ ስለምወድ ይሆናል።"

"ቤቲ የኔ ቆንጆ!" ግንባሯ ላይ ሳም አደረኳት፣ "ካነበብሽማ እኔ እድለኛ ነኝ። የምታነብ ፍቅረኛ ምክንያታዊ ስለምትሆን ትክክለኛ የሕይወት አጋር ናት። ለመጻፍ ደግሞ ወኔ ትሆናለች። በጣም ብቁ ከሆነች ደግሞ ራሷ ትጽፋለች። በራሷ የሥነ ጽሑፉ ታሪክ ምንጭም ትሆናለች..." የያዝኩትን እጇን ጠበቅ አደረኩት።

"ዉ--ይ፣ ሰሙ...ያንን ያህል እንኳን አትሜግንብኝ። የሥነጽሑፍ ወኔ ስፈጥር እንኳ አይታየኝም። ማንበብ ግን ስጋት አይግባህ። ድቅ---ቅ አደርግልሀለሁ..." ከት ብላ ሳቀች።

"ለምንድነው አንቺ የሥነጽሑፍ ሰበብ የማትሆኝው?' በዚች አጭር ጊዜ በፈጠርሽብኝ መነቃቃት

እየጻፍኩሽ እንደሆንስ በምን ታውቂያለሽ? እንኳን እንደዚህ በአካል ስላይዋትና እቅፊው ስለሳሟት የምድራቱ ቆንጆ ይቅርና መሬት ላይ የሌለች ሴት በምናብ ተፈጥራ ትጻፍ የለ እንዴ?"

"ስሙዬ፡ ይሄን ማመን ይቸግረኛል። እና ጽፌሻለሁ እያልከኝ ነው? በማሚ ሞት ንገረኝ!"

"ግጥ---ም አድርጌ ነዋ፤ በሰባት ገጽ ወረቀት!!" መጻፍ እንደማይሳነኝ ስለማውቅ ብቻ ዋሸኋት፤ "ግን አልጨረስኩትም። አንድ ሁለት ገጾች ይቀሩኛል። እንዳለቀ አምጥቼ እሰጥሻለሁ።"

"እምቢ፤ እምቢ...፤ የጀመርከውን አምጣልኝ..." ወዲያው ደግሞ ሐሳቧን ቀይራ፤ "እሺ፤ የጨረስከውን መቼ ተ...ታመጣልኛለህ?" እንቅ አድርጋ ያዘችኝ።

ዝም አልኳት። ልትተውኝ ግን አልቻለችም። "እኮ መቼ ታመጣልኛለህ?"

"የፍቅር ጨዋታ በምንጀምርበት ቀን!"

አስቤው አልነበረም የተናገርኩት። ድፍረቱን ከየት እንዳመጣሁትም አላውቅም፤ ብቻ አምልጦኝ የተናገርኩት ነገር ከሁለታችንም ጆሮ ደረሰ።

"ችግር የለውም። የጾታ ኩብሬን ላንተ ከመስጠቴ በፊት የፈተናውን ጊዜ እንደሁኔታው አሳጥርልሀለሁ።" ፊቷ በሆነ ውስጣዊ ስሜት ልውጥውጥ ሲል ይታየኛል። "...ምናልባት እስከ መጭው ቅዳሜ ማለፍ መውደቅህ ይነገርሃል።" ቀልድና ኀፍረት ያደመቀው ፈገግታ ብርት ብሎ ሲጠፋ ከፊቷ ተመለከትኩ።

ሁለታችንም ቀጥሎ የምንናገረው ነገር ጠፍቶን ለአፍታ ዝምታ ሰፈነ። ዐይኗ ዐይኔን እየሸሸ ነበር።

"ስሙዬ! ለማንኛውም እሑ----ድ...ሌሊት..." እንጠልጥላ ተወችው።

የተናገረችውን ማመን አቃተኝ። ልቤም ከቃሉ ጋር ተንጠልጥላ ቀረች። እሑድ! እሑድ! እሑ---ድ!! እሑድ አዲስ እንደተተለተለ መጫኛ ጠፍር... እሑድ ልክ እንደምጽዐት ቀን... እሑድ ልክ እንደ ሠርግ ቀን...እሑድ እንደ ምርቃት ቀን...የሚናፍቁት ግን የማይደርሱበት ሩ------ቅ ሩ----ቅ ሆኖ ታየኝ። የቀሩኝን ቀናት ስቆጥር እንደ ሕጻን ልጅ ተሳሳትኩ። ቅድሚያው ለፍቅር ነው።

"እ---ኬ፤ እሑ---ድ ይዘሀልኝ ትመጣለህ፤ እሺ?" ብላ እንደገና እቅፍ አድርጋ ከንፈሬን ሳመችኝ።

'እሑድ! እሑ--ድ! እውነት ብላለች ወይስ ጆሮዬ ነው? እሑድ! እሑ--ድ! ለመሆኑ ስንት ቀናት ቀሩኝ?

አዎ፣ ነገን ጨምሮ እስከ ቅዳሜ አራት ቀናት ይቀሩኛል… ' ገላዋን በዐይነ-ልቦናዬ ግልጥልጥ አድርጌ ስመለከት ጉጉቴ ጨመረ። እንደ እርጉዝ ቀን መቁጠሩን ደጋገምኩት። የሞት ሞቴን፣ "ቤቲዬ፣ የኔ ቆንጆ…እሑ---ድ! በጣም እወድሻለሁ!" የድምጽ ቅላጼዬ ተለወጠ።

እሷም ደስታዋን መደበቅ አልቻለችም። እሁድ! እሁድ! በሁለታችንም ልብ ውስጥ ሰርጎ ገብቶ ተደላደለ።

###

ከአፍታ በኋላ መተፋፈሩ ቀርቶ ዘና ብለን መጫወት ስንጀምር እሑድን የመረጠችበትን ምክንያት ነገረችኝ። ወይዘሮ ማስተዋል ዘመድ ለመጠየቅ መርሀቤቴ ይሄዳሉ። እነሰ ከተባለ ዐስር ቀናት ይቆያሉ። ያኔ ቢታኒያና እኔ ጫጉላ እንገባለን ማለት ነው። ሌሊት ተነስቼ አውቶቡስ ተራ የማደርሳቸው እኔው መሆኔንም ነገረችኝ። ጉጉቱ ሁለታችንንም ጥድፍ ጥድፍድፍ አደረገን። ወደ ሌላ ወሬ ልንገባ ስንል ሬዲዮው ትኩረታችንን ሳበው። የምሽቱ የአማርኛ ፕሮግራም ላይ ብርክታዊት ዜና ማንበብ ጀመረች። ገና ድምጿን ስሰማ ስቅቅ አልኩ።

"ኡፍ፣ ይችን ብርክታዊት የሚሏትን ጥሩንባ እንዴት እንደማልወዳት ብታውቅ!!" ቢታኒያ እጇን ወደ ሬደዮው ልካ ድርግም አደረገችው።

በሆነ ተዐምር ምሥጢሬን ደርሳበት የተናገረችው ስለመሰለኝ መደንገጤ አልቀረም። ቤቲዬ፣ ጉዱን አልሰማችምና!

ሸዋዬና ደጀኔም በሚገርም ሁኔታ እንደዚያው ናቸው። የብርክቲን ድምጽ ሲሰሙ ለምን እንደሆን አላውቅም ያንገሸግሻቸዋል። ብርክቲዬ፣ ሐሳቤን እንዳትሰርቅብኝ ቶሎ ብዬ ሸሸኋት።

'እ--ሑ---ድ!' ልቤ አፍ አውጥታ ጮኸች። እሑ---ድ! አንዱ ያልታሰበ ከልከልዩስ የአመድ ዛር ጥልቅ ብሎ እንቅፋት እንዳይሆንብኝ እንዲሁ ሰጋሁ። እሑድ ጋራዥ ለቀለም ቅብና ለጎሚስታ ሥራዎች ብቻ ነው የሚከፈተው። ሥራ አይበዛብኝም። የምፈራው ድንገተኛ የድርጅት ትእዛዝ መጥቶ ጉድ እንዳይሠራኝ ብቻ ነው። ኢሳያስ ጉለሌ ሊያድር ይችላል። ከመጣም ለጥ ብሎ ስለሚተኛ ችግር አይሆንም። ሌላ ፈተና ግን አለ። ከሸዋዬና ከደጀኔ ተልይቼ እንዴት ከምድር ቤት እንደምወጣ የታየኝ ነገር የለም። ሸዋዬን እንኳን ብዙም አልፈራትም። ደጀኔ ግን ማወቅ ይቅርና መጠርጠር እንኳን የለበትም። ይሁንና በዚህ መወዝወዝ አልፈለኩም። እስረኛ አይደለሁም፣ ቀኑ ሲደርስ በአንድ መንገድ ይፈታል። ለጊዜው ግን ልቤ ምድር ቤታችንን ከእነቢታኒያ ግቢ ጋር በምታገናኘው ምሥጢራዊዋ የደጎንነት መስኮት ላይ አረፈ።

"ሰሙ፣ እኔ ፍልስፍና በጣም እወዳለሁ። አንተስ እንዴት ነህ?" አገጩን ይዛ ጠየቀችኝ።

"እውነትሽን ነው?! እንዲያውም ራሴን ጎበዝ የፍልስፍና አንባቢ ነኝ ብዬ ዐስባለሁ። ራሴን መስቀል አይሁንብኝና ከሞላ ጎደል ሁሉንም የ'ክላሲክ' ዘመን ፍልስፍናዎች ያነበብኩ ይመስለኛል። ግን ማንበብ ብቻ ነው። ጽፌ ወይም ሂስ ሰጥቼ አላውቅም..."

የአእምሮ የበላይነት መያዝ ዩኒቨርስቲ ለቀመሰ ሰው የወንድነት ኩራት ምልከት ነው። ግቢ እያለን የሴቶችን ትኩረት ለመሳብ ስንጠቀምበት ትዝ ይለኛል። ቢታኒያ ቀጥ ብላ ወደኔ ስትመጣልኝ ልቤ ሐሴት አደረገች።

"ሰሙዬ፣ በእና—ት—ሀ፣ ነገ ስትመጣ ስለ ኒኮሎ ማኪያቬሌ ዝርዝር አድርገህ አውራኝ። አጼ ኀይለሥላሴ ማኪያቬሊስት ባህርይ አላቸው ተብሎ ልጆች ሲከራከሩ ሰምቻለሁ። በዚያ ምክንያት መሰለኝ ፍላጎት ተፈጠረብኝ። መጽሐፉ አለኝ። በጣም ላውቀው የምፈልገው ኾኖም ግን በጣም የሚጠጥርብኝ የእሱ ፍልስፍና ነው። በደንብ አድርገህ ታስረዳኛለህ አይደል?" እጆቿን በአንገቴ ዙሪያ ጥምጥም አደረገቻቸው።

'አአአ—ው፣ ይህች ልጅ የዋዛ አይደለችም!'

"ምንም ችግር የለም፣ ቤቲዬ። ከወደድሽው እንነጋገርበታለን። ሊሠራ ላይሠራ ይችላል። ግን አጼ ኃይለሥላሴን ከማኪያቬሌ አንጻር ለመረዳት መፈለግሽ በራሱ ጥሩ ነገር ነው።" ኮራ ልል ፈለኩ።

"አ—ይ፣ እሱ ብቻ አይደለም ችግሩ..." ብላ ዝም ስትል፣ "እኮ ሌላም ካለ ንገሪኝ..." ብዬ አደፋፈርኳት።

"በ—ቃ፣ ምን ልበልህ፣ ሰሙ...የአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ ዝም ብዬ ሳስበው እንዲሁ ያስጨንቀኛል። አንድ የሕግ አስተማሪ የሚደጋግመው ነገር ነበረ። 'የሰውን ልጅ በሃያኛው ዓመት ፍላጎት፣ በሠላሳኛው ዓመት ጨዋታ፣ በአርባኛው ዓመቱ ደግሞ ዳኝነት ይፈራረቁበታል...' ይለን ነበር።የዳኝነት ብቃት በትምህርት ብቻ አይገኝም።የሕይወት ልምድንም ይፈልጋል ማለቱ ነው። አሁን በእኛ አገር ሳየው ግን እየሆነ ያለው የዚህ ተገላቢጦሽ ነው። ሀያና ሠላሳ ዓመት ላይ ነን። በቃ፣ የእኛ ጓደኞች መዐት ፍላጎት የሚያረኩበት ዕድሜ ነው። ግን የትም ስትሄድ ቁምነገረኞች ሆነው ታገኛቸዋለህ። ዐዋቂዎቹ ደግሞ የሚያደርጉትን አጥተው ዝም ብለው ዳር ቆመው ያያሉ..."

'እውነትም ቢታኒያ ቀላል ሰው አይደለችም!' ድንጋጤ ሊነካካኝ ፈለገ።

የወሬያችን ርእስ በምንም ተዐምር ወደ ኢሕአፓ የሚያመራ መሆን ስለሌለበት ጥንቃቄ ማድረግ አለብኝ። የተናገረችው ግን እውነት ነው። እሷ ራሷ፣ ኢሳያስና እኔ ምሳሌ ነን።በሃያዎቹ ዕድሜያችን ወደ አመራር የተጠጋን ፖለቲከኞች ነን። ኢሕአፓን የሚያከል ግዙፍ ድርጅት ከሚመሩት ሰዎች ትልቁ ዕድሜ 33 ነው። ብርሃነመቀል፣ ተስፋይ ደበሳይ፣ ዘርዑ፣ ክፍሉ ታደሰ...ከ33 አይበልጡም። ጌታቸው ማሩ 27። በደርግ/መኢሶን ውስጥም ተመሳሳይ ነው። ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያምና ኃይሌ ፊዳ 34 ግፋ ቢል 35 ዓመታቸው ነው። ኢሳያስ አፈወርቂ 37። የትግራዮቹ አረጋዊ በርሄና አባይ ፀሐዬ 26 ወይም 27 ቢሆኑ ነው።

"ቤቲዬ፣ በጣም ትክክለኛ ነው ትዝብትሽ!"

ትዝ ሲለኝ አባባሷ ሌላም ምስል ሰጠኝ። የደርጉ ጀኔራል ተፈሪ በንቲ፣ የኤርትራው እስማኘ ሳላህ ሳቤና የትግራዩ ስብሀት ነጋ ዕድሜያቸው አነሰ ከተባለ 50 ዓመት ግድም ወይም ከዚያ በላይ ነው። ነገር ግን ለስም ብቻ የተቀመጡ መሪዎች ናቸው። ሁሉንም በተለይ ፖለቲካዊውንና ወታደራዊውን መዘውር የሚያሽከረከሩት ወጣቶቹ ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ ቅልብጭ ብሎ የሚታይ ብሔራዊ ዝንባሌ ነው። እንዴት እንደደረሰችበት ገረመኝ።

"አገርን የሚያህል ነገር በልጆች ስትመራ እያሳሰብም ታዲያ፣ ሰሙዬ?" በረጅሙ ተነፈሰች።

ለሦስት ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች ቀሩ። ቢታኒያ ልንለያይ ስንል ቅር አላት። የበሩን ቁልፍ ከቦርሳዋ አውጥታ ሰጠችኝ። ማንም ማወቅ እንደሌለበት አስጠነቀቀችኝ። ልቤ ወደ ኋላ እየተጎተተ ስሜያት በመጣሁበት አኳኋን ድምጼን አጥፍቼ ወደ ቤቴ ተመለስኩ።

"እ---ሱ---ድ! እሱ---ድ!" አእምሮዬ ዉስጥ የሚያቃጭለው ብቸኛው ድምጽ ይኸው ብቻ ነበር።

\###

ቀዩን በር ቀስ አድርጌ ከፍቼ ወጣሁ። መልሼ ዘግቼው ወደ ቀጭኗ መተላለፊያ ዞር ስል የጋራዡ መብራት ቦግ ብሎ በራ። በዚህ ሰዓት የማልጠብቀው ክስተት ነው። ደንግጬ ባለሁበት ቆምኩ። በድንግጤ በር ሲከፈትና ሲዘጋ ተሰማኝ። ድንጋጤዬ የበለጠ ጨመረ። ሽጉጤን ከውስጥ ሱሪዬ አውጥቼ ከግድግዳው ጋር ልጥፍ ብዬ ቆምኩ። ቆቅ ሆኜ ስከታተል የጋራዡ መብራት ጠፍቶ የኔ ቢሮ መብራት በራ። 'ኢሳያስ ይሆን?' እሱ ደግሞ በዚህ ሰዓት ጋራዥ ገብቶ ዐይቼው አላውቅም። ደግሞ ደብረብርሃን ሄዷል። ቀርቶ ይሆን እንዴ? ጭንቅ አለኝ። ድንገት የቢሮዬም መብራት ጠፍቶ ምሥጢራዊው በር

ተከፈተና ኢሳያስ ፈትለክ ብሎ ወጣ። ይህን ጊዜ የተዛባው የደም ዝውውሬ ወደ ቦታው መለስ ሲል ታወቀኝ። እንዳይደነግጥ ቀስ ብዬ ድምጽ አሰምቼ ስሙን ጠራሁት። አጋጣሚው ሁለታችንንም አስቆን ሽጉጣችንን እንደያዝን ለአፍታ ቆም አልን...

"ሰመሬ፡ እንዴት በዚህ ሰዓት እዚህ ተገኘህ?" በመገረም ፈገግ ብሎ ጠየቀኝ።

"እኔም የገረመኝ እሱ አይደል?! ገና መውጣቴ ነው'ኮ..." ብዬው የምዋሽበትን ቃል ማፈላለግ ያዝኩ።

"ሰመሬ ከዋሸ ከእንግዲህ ማን ሊታመን ነው?!" እየሳቀ አቀፈኝ።

"...በዚህ ስዓት ልትወጣ የምትችለው ከቀዩ በር ብቻ ነው። ከቀዩ በር በፊት ደግሞ ከቢታኒያ መኖሪያ ከፍል። ከሌላ ከየትም ቦታ ዱብ ልትል አትችልም። ቤቱን ይዘሀት ከሆነ ደስታውን አልችለውም። አልነገርኩህም እንጂ እኔም ምጽላል የምትባል የመቀሌ ልጅ ይዣለሁ!" ከት ብሎ ሳቀ።

በዝምታዬ አመንኩለት። ስለ ፍቅር ኃያልነት የገረመኝ አንድ ነገር ግን አለ። ኢሳያስ በእውነትም ሴት... ፍቅር...ቀጠሮ...ወሲብ ምናምን አስታውሶ የፍቅር ጓደኛ መያዙ። ብርሃነመስቀልም እንደዚያው። እነዚህ ሰዎች ጭንቅላታቸው ከፖለቲካ ውጭ ለማሰብ ፋታ ያለው አይመስለኝም ነበር። ለካስ ፍቅርም ፖለቲካም እውር አይደሉም! አለችኝ ልቤ። ብቻ ቢታኒያን ከዐውሬ ዐይን ይሰውርልኝ! ተማጸንኩ።

"ደብረብርሃን አልሄድከም ማለት ነው? እስኪ ደግሞ የቀረውን ቤታችን ገብተን እናውራው..." ተያይዘን ወደ ቤት አመራን።

ወደ ጣውላው በር አጥፍ ስንል የሆነ ጥላ ውልብ ሲል ያየሁ መሰለኝ። ኢሳያስን ግራ እጁን ይዤ ወደኋላ ጎተት አደረኩት። ዐይኔ ዐጽማቸው ብቻ በቀረው መኪናዎች ላይ አፈጠጠ። ትክክል ነኝ። በሦስተኛው የመኪና ዐጽም አካባቢ የሰው እንቅስቃሴ ታየኝ። በዚህ ሰዓትና ቦታ ሰው ማግኘት ፈጽሞ ሊታሰብ አይችልም። ሽጉጤን ላጥ አድርጌ ከኢሳያስ ፊት ለፊት በደረቴ ለጥ ስል ኢሳያስ ተከትሎኝ እሱም በደረቱ ተኛ። ጠላት ከሆነ ሁለታችንንም በአንድ ጥይት ሊጥለን አይገባም። ሽጉጤን ፊት ለፊት እንደወደርኩ ወደ ጎድጓዳው ስፍራ ተንከባለልኩ። አመዱንና ሳሩን ከምንም ሳልቆጥረው ተንከባልዬ ከጠላታችን ጀርባ ቦታ ያዝኩ። እንደገና ወደ መኪና ዐጽሞቹ አተኮርኩ። ምንም ነገር አልታይህ ሲለኝ የበለጠ ደነገጥኩ።

ቅብዝብዝ ብዬ አካባቢዬን ስቃኝ ኢሳያስ በደረቱ እንደ እባብ እየተሳበ ወደ ጣውላው በር ሲጠጋ

እየሁት። ትክክል አይደለም፣ ጠላት ቀድሞ ዐይቶን ስፍራ ይዞብናል። ትኩረቱን መበታተን ሲገባ ፊት ለፊት እፍጥጦ መሄድ በራስ ላይ መፍረድ ነው። በምን መንገድ ነግሬ ላስቁመው? ጭንቅ ብሎኝ ሳለ የጣውላው በር ከውስጥ ተከፈተ። ሸዋዬ ከላሸንኮቭ ጠበንጃዋን በቀኝ እጇ ቁልቁል ዘቅዝቃ ብቅ አለች። ወደ ሳባራው መኪና ዞራ የሆነ ነገር ስትናገር ደጀኔ ብቅ አለ። ልቤ ትርትርታዋን ገና አላቆመችም።

"እንዴ፣ እርስ በእርስ ልትታኮሱ ነው እንዴ?" ለካንስ ደጀኔ በትክክለኛው ኮድ ስላላነኳኳ የተፈጠረ አለመግባባት ነበር። ሸዋዬ ሳቋን መቆጣጠር አቅቷት ሣስታችንንም እየመራች ገብታ በሩን ዘጋችው። ገብተን መብራቱ ሲያርፍብን ለካንስ እኔ ዐመድ የቃመች እህያ መስያለሁ። ሌላ ዙር ሳቅ ፈነዳ!

# 11

እኩለ ሌሊት፤

ምድር ቤቴ ውስጥ አልጋዬ ላይ ነኝ። ብርሃነመስቀል የሰጠኝን የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ቅጅዎች ገና በጊዜ አንብቤ ጨርሻለሁ። ካለፈው ታሕሳስ ወር ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ገበያ ላይ የዋሉ ኅትመቶች ናቸው። ሁለቱ ርእሰ አንቀጾች ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ "አብዮታዊ መድረክ" አምድ ላይ የወጡ ሆነው አገኘኋቸው። የራሱ የብርሃነመስቀል መጣጥፎች ናቸው። ያው ሁሉንም "በዛብህ በላቸው" በሚል የብእር ሥም ነው የጻፋቸው። አንብቤ ስጨርስ የመልእከታቸውን አጠቃላይ ዝንባሌ ለመበየን ሞከርኩ። ይሄኔ ችግር ገጠመኝ።

'እህ...እንዴት ነው ነገሩ? ብርሃነመስቀል ምን እያለ ነው?'

ከታሕሳስ ወር መጀመሪያ አንስቶ እስከ የካቲት መጨረሻ አካባቢ ባለው ጊዜ ውስጥ ብርሃነመስቀል በሁለት አንኳር ጉዳዮች ላይ አተኩሯል። የ"ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" አቋም ትክክለኝትና ስለ አመሠራረቱ አንደኛው ነው። ሁለተኛው ደግሞ "ዲሞክራሲ ያለገደብ" ምን ማለት እንደሆነና ስለሳይንሳዊ መነሻዎቹ ተከራክሯል። መጋቢት ወር ላይ ሲደርስ ግን ድንገት እጥፍ ይላል። እነዚህን እርግፍ አድርጎ ትቶ "የሕብረት ግንባር ምስረታን" ብድግ አድርጓል። የጸሐፊው ስም የሌለበት የመጋቢት 9 አዲስ ዘመን ርእሰ አንቀጽ ጭብጥ ደግሞ ግልጽ የ"ግንባር እንመሥርት" ጥሪ ኾኖ አገኘሁት። ከምንም በላይ የተበሳጨሁበት ነጥብ ደርግን የበየነበት ቋንቋና ሥነዘዴ ነው...

"ደርግ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች እውቅና አለመስጠቱ በቂና አሳማኝ ምክንያት አለው ብዬ

አላምንም። ይህ መሆኑ ግን ደርግን ተራማጅ አይደለም ለማለት አያስችልም። እውነተኛ የሕብረት ግንባር እንዲፈጠር ይህ ጉድለት መሟላት ይኖርበታል። አሁን ባለው ሁኔታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የተከፈተው ዲሞክራሲያዊ የክርክር መድረክ ጉድለቱን በማሟላት በኩል አንድ አዎንታዊ እርምጃ ነው። ደርግ በውስጥ አሠራሩ መሪዎቹን በምርጫ መሰየሙና በድምጽ ብልጫ ሥርዐት መገዛቱም በጠንካራ ጎን የሚታይ ነው። ይህ እየሰፋና የሕግና የአሠራር ዋስትና እያገኘ ከሄደ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሕብረት ግንባር መፍጠራቸው ተገቢና የማይቀር ይሆናል..."

"ምን ነካው ሰውዬውን?" ድምጼ ሸዋዬ ድረስ ዘልቆ የተሰማ መሰለኝ፣ "ምንድነው ብርሃነመስቀል ከዚህ 'ግንባር' የፈለገው ነገር? ለመሆኑ ይሄ አቋም የግሉ ነው ወይስ የኢሕአፓም ጭምር ነው? የሕብረት ግንባር ከደርግ ጋር? ከመኢሶን ጋር? ከሰናይ ልኬው ወዝ ሊግና እኛን ከድተው አራት ኪሎ ቤተመንግሥት ከገቡት ከእነ ተስፋዬ ታደሰ ማሌሪድ ጋር?" ትከን አልኩ።

የአጸፋ መልስ ለማዘጋጀት የወሰንኩት ወዲያዉኑ ነበር። ምክንያቱም አንደኛ ብርሃነመስቀል ሙግቱን በሳይንሳዊ የሁኔታዎች ግምገማ ላይ አልመሰረተም። ሁለተኛ የደርግን እውነተኛ ተፈጥሮ የመበየን ሥራ በተገቢው መጠንና ጥልቀት አልሠራም። እንዲያውም ደርግ ደርሶ ቅዱስ እንዲሆንለት ነው እየጠየቀ ያለው። በመንግሥት ጋዜጣ ላይ የተከፈተን የክርክር ዐምድ የዲሞክራሲ መመዘኛ ማድረጉም አስገረመኝ። ክርክሩ 93 በመቶው ማንበብና መጻፍ በማይችልበት አገር ዲሞክራሲን የልሂቃን ጉዳይ ብቻ አድርጎታል። ለብርሀነመስቀል እሱ መጻፍ ከቻለ ዲሞክራሲ አለ።

"ሮ---ን----ግ!!" እንደገና ጮኽኩ።

ብርሃነመስቀል መኢሶን በዚህ የግንባር ምስረታ ሂደት ምን ሚና እንደሚኖረውም ፍንጭ አልሰጠም። ይህንን ሳያደርግ የግንባር ጥሪ ማድረግ ወይም መቀበል ምን ማለት ነው? ያለምንም ጥርጥር ከኢሕአፓ ጀርባ የተሰለፈውን ሕዝብ መካድ ነው። ኢሕአሠንና መላ አባላቱን መካድ ነው።ደርግ "ከኢሕአፓ ጋር ግንባር ልፍጠር" ይላል ብሎ መጠበቅስ ምን ይባላል? የበቀደሙ የጌታቸው ማሩ ክርክር መሆኑ ነው። የባሰ አስቂኝ ፖለቲካዊ እንጭጭነት ነው። "ምላሴ ይቆረጥ፣ ደርግ ይሄን ይላል ማለት ከአባብ እንቁላል እርግብ መጠበቅ ነው።" ደርግ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የፖለቲካ መስተጋብር ማየት አልቻሉም።ብርሃነመስቀልና ጌታቸው ደርግ እኛን የሚገድልበትን ጠበንጃ እየመረጡለት ነው። ብጥር አድርጌ አጽፈው ጀመር...

'ከዚያ እሑድን ቀኑን በሙሉ ለሽ ያለ እንቅልፍ አተኛለሁ። ምሽት ላይ ወደ ፍቅሬ ቢታኒያ!' ደ---ስ

አለኝ። ቀጠልኩ...

ብርሃንንና ጌታቸውን በሠላሳ ሁለቱም ፕሮሰቼ ነከሻቸው አደርኩ። የየራሳቸው ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል። ሁለቱም መሪዎች ግን ከደርግ ጋር ተባብሮ የመሥራት አጀንዳ አራማጆች ናቸው። ከደርግ ጋር አብሮ መሥራት የማይቻለው ደርግ ስላልታደለ ወይም እርግማን ስላለበት አይደለም። ትብብርን የማይቻል ፕሮጀክት የሚያደርግ መደባዊ ማንቆ ስላለበት ነው። 'ሆሆ—ሆሆው፣ ከደርግ ጋር እንተባበር?' አንድ ቃል በጻፍኩ ቁጥር ሐሳቡ እየመጣ ይፈታተነኛል። ጽሑፌን ቢደረቅ የርእዮትና የፖለቲካ ሙግት መጀመር አልፈለኩም። የማርክሲስት ሊትሬቸር አጻጻፍን ወግ ተከተልኩ። የከርከሬን ዋና ነጥብ በቀላሉ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል...

"በአንድ ወቅት አንበሳ የተፈጥሮ ጥላቻውንና ተቀናቃኝነቱን በሆነ ምክንያት ትቶ ሕይወትን ቀላልና ውጤታማ ለማድረግ ፈለገ። ለዚህ ደግሞ ከሌሎች የዱር እንስሳት ጋር መተባበር አስፈላጊ መሆኑን አመነበት። ይሄንኑ ለማድረግ ወደ ጅብ፣ ነብርና ተኩላ ሰፈር ሄደ። ባልተለመደ ትህትና አዲሱን እምነቱን ነገራቸው። ሦስቱም በጣም ተደሰቱ። የመጀመሪያውን ትብብር በአንድ ታላቅ አደን እናሳይ ተባባሉ። አንድ ላይ ሲጓዙ አርፍደው ቋጥኝ የሚያከል ጎሽ አጋጠማቸው። ተባብረው ግዳይ ጣሉት።

አንበሳ የግዳዩ ዋና አዳይና ደልዳይ ሆነ። አራቱም የተለያየ የምግብ አወሳሰድ ባህል ስላላቸው አብረው መብላት አይችሉም። ነገሩን የተረዳው አንበሳ መካፈል አለብን ሲል ወሰነ። ሦስቱም በጥርጣሬ እያዩት እሽ አሉ። አንበሳ ሥጋውን ከአራት ከፈለው። አንደኛውን መደብ 'ይህ የአራዊት ንጉሥ በመሆኔ ይገባኛል' አለ። ሁለተኛውን መደብ 'በዚህ አደን ትልቁን ሚና ስለተጫወትኩ ዋጋዬ ነው' አላቸው። ሦስተኛውን ደግሞ ድርሻዬ ነው ብሎ ወሰደ። አራተኛውን መደብ 'ይሄን የሚነካ ግን ወዮለት' አለ..."

ይህ የባህርይ ጉዳይ ነው፣ በስሜትና በበጎ ፈቃድ ሊለወጥ አይችልም። ጅብ ማንከሱን፣ አዞ ማልቀሱን፣ አባብ መላሱን... በፈቃዳቸው ሊተውት አይቻላቸውም። ወደ ደርግ ተመልሼ ትብብር ማድረግ የማያስችሉ መሠረታዊ ምክንያቶችን ዘረዘርኩ...

ብርሃነመስቀልና ጌታቸው ያዩት ኮቱን ወይም ጋቢውን ነው። ደረትን ሰንጥቆ ልብ የሚመረምር የንሥር ፖለቲከኛ ዓይን እንደጎደላቸው ተሰምቶኛል። ቢያንስ ወደ ደርግ በሚያስገባው በር ላይ ማን እንደቆመ ማየት ነበረባቸው። የኪሩቤልን ጎራዴ ይዞ የቆመው መልዐከ መኢሶን መሆኑን ማስተዋል አልቻሉም። "መኢሶንና ደርግን አሳንሶ በንቀት ከማየት የተፈጠረ የዕይታ መንሸዋረር..."

የእነርሱን ስጨርስ ወደ ሌሎቹ ዞርኩ። ዘርዑ፣ ተስፋዬና ከፍሉ ታደሰ። "ከደርግ ጋር አብሮ

መሥራት አይቻልም" ካሉ በኋላ "መፍትሄው የከተማ አመጽ ነው" ይላሉ። በጽሑፌ እነርሱንም አልማርኳቸውም። "አንተባበርም" ያለ ሰው የወፍ እገሩ ዋርካ... እንዲሉ እዚህ ምን ይጎልተዋል? ወደ ትግሉ ባለቤት የገጠሩ ሕዝብ፣ ውልቅ ማለት አለበት። ሰው ቁመቱን አይቶ ደጃፍ ይሠራል ይላሉ አበው። ወደ ደርግ አልፍኝ የሚያስገባው በር በኢ.ሕአፓ ቁመት ልክ የተሠራ አይደለም። የኛ ትክክለኛ በር ወደ አሲምባ የሚያስገባው ነው።

'ኤዲያ፣ ሁለታችሁም አትረቡም። ደርግን በመተርጎም ትለያያላችሁ። ገበሬን በመከዳት ደግሞ ትመሳሰላላችሁ!' ልጽፈው ፈልጌ የአንባቢን ስሜት ላለመጉዳት ስል መልሼ ተውኩት።

የብርሃነመስቀል ጽሑፎች ሌላም ጥርጣሬ አጭረውብኛል። አንዳንዴ ያቀረበው ሐሳብ ከፖለቲካ አስተዋጽኦ ይልቅ ሌላ የሥነልቦና ግብ ያለው ሁሉ ይመስለኛል። 'የንድፈ ሐሳብ ትንተና ብቃቱን አሳይቶ የሐሳብ የበላይነት መውሰድ! ከዚያ የተወሰደበትን የዋና ጸሐፊነት ቦታ ማስመለስ! ይሄን ለማድረግ እየጣረ ይሆን?'

በሌላ በኩል ዘርዑና ሌሎቹ ሌላው መንቻካ ናቸው። ብርሃነመስቀል ለምን ካርል ማርክስን ወይም ሌኒንን ሆኖ እንደገና አይፈጠርም! ወደ መሪነት አይመልሱትም። አንድን ገመድ ከሁለት አቅጣጫ ይዞ የመጓተቱ እልህ ሌላ ምክንያት ይኖረው ይሆን? እንደገና ተጨነኩ። ጭንቀቴ እንደገና ሌላ ስጋት ይዞብኝ ይመጣል። 'እኔ ራሴ ተሳስቼ እንዳይሆን?' ባነሳው ብጥለው ግን ስህተቴ አልታይህ አለኝ።

'አዎ፣ አውቀውትም ይሁን ሳያውቁት "የመጀመሪያው ኩነኔ" እየገፋፋቸው ሊሆን ይችላል!' ለጊዜው መላምቴ ይሄው ነው።

###

የንጋት ዶሮ ሲያኳኩል ዐይኔና ወረቀቱ ተለያዩ።የአእምሮዬን ዐውድ ከፖለቲካ ወደ ፍቅር ለማዞር ጥቂት ደቂቃዎች ወሰደብኝ። ሌሊት ላይ የቢታኒያ ቀጠሮዬ ድንገት እየቀዘፈ መጥቶ ስፍሮብኝ ነበር። ቢታኒያ መኮንን! ለእሑዱ ቀጠሮዬ ስለመዘጋጀት አሰብኩ። 'ስለ ፍቅራችን በክብር የምሰጣት ወደድ፣ ጠራ ያለና ከራሚ ስጦታ ምንድነው?' ትዝ ይለኛል ለብርከታዊት ከብር የተሠራ የጸጉር ማስያዣ ነበር የሰጠኋት። በጣም ስለወደደችው ከጸጉሯ ተለይቷት ዐይቼ አላውቅም። መቼስ በአዲሱ ፍቅር ልቤ ጠፍቶ የለ?! ለቢታኒያ ደግሞ ከዚህ ከፍ ያለ መሆን አለበት!

'ለምሳሌ፣ ምን ያህል ገንዘብ የሚያስወጣ?' ማሰላሰል ጀመርኩ።

ይህ ጥያቄ መዘዝ ይዞብኝ ከች አለ። ከስድስት ወራት በፊት ባንክ ያለኝ ገንዘብ 1 ሺህ 220 ብር አካባቢ ነው። ውድ የስጦታ እቃ ለመግዛት ከበቂ በላይ ነው። የባንክ ደብተሬን ግን የት እንዳስቀመጥኩት እልም ብሎ ጠፋብኝ። በርግጌ ተነስቼ ፍለጋ ጀመርኩ። ያልበረበርኩት ሻንጣ...ኮት...ካርቶን...በርሳ የለም። ምልከቱን አጣሁት። የትምህርት ማስረጃዎቼም የሉም።

ቀስ በቀስ አብሰልስዬ ያስቀመጥኩበት ቦታ ትንሽ በትንሽ መጣልኝ። ከስምንት ወራት በፊት ለሥራ ሐረር ሄጄ ነበር። ሙቼም የአጼ ኃይለሥላሴ የተንጋደደ የብሔራዊ ሐብት ከፍፍል ፖሊሲ ጉድ አስከትሏል። ኪስ አውላቂ፣ ማጅራት መቺና በር ሰባሪ ሠራዊት እየበረከተ ነው። እጣው እንዳይወድቅብኝ ፈራሁ። ከአከራዩቼ ቤት ብረት ሳጥናቸው ውስጥ አስቀምጬው ሄድኩ...

'እ-----ዎ፣ ትክክል ነኝ! እዛ ነው ያስቀመጥኩት። ግን እሱን ለማምጣት ተመልሼ ልሄድ ነው?' ጭንቅ መጣ።

ተመልሼ ልሄድ አልችልም። ከሄድኩ ከተደበኩበት ሕቡእ ወጣሁ ማለት ነው። በዚህ ላይ ብርከታዊት ሰፈሯ ቅርብ ነው። በሆነ አጋጣሚ ብታገኘኝ ምን ሊውጠኝ ነው? መፍትሄው አንድ ብቻ ነው። ጎይቶም ለባሲን መልሼ መላክ። ግን ደግሞ በጎይቶም ላይ ቀጥተኛ ተጠሪነት የለኝም። ለሆነ አጣዳፊ ግዳጅ ቢፈለግስ?ደጀኔ በአእምሮዬ መጣ። 'ደጀኔን እመላከቼ ብልከው ይዞልኝ ከች ይላል። ነገ እሑድ ስለሆነ ባንክ አይከፈትም።' ይሄንኑ ወስኜ አደርኩ። በሚቀጥለው ቀን በጥዋት ተነስቼ ደጀኔን የባንክ ደብተሬን ሄዶ እንዲያመጣልኝ ነግሬው ጋራዥ ውስጥ የጭነት መኪናው ቁልፍ ያለበትን ሳጥን አመለከትኩት። የቢሮዬን የበር ቁልፍም ሰጥቼው ከሸዋዬ ጋር ቁርስ በልቼ ወጣሁ።

***

ጋራዡ የረፋድ ገበያ መስሎ ጠበቀኝ። በዚህ ቦታ "አማርኛና ትግርኛ ብቻ ይፋዊ ቋንቋዎች ናቸው" ተብሎ የታወጀ ይመስላል። ሁሌም ጆሮዬ ውስጥ እነርሱ ናቸው የሚገቡት። ኢሕአፓ "የአቢሲኒያውያን የ'ታላቋ ኢትዮጵያ" ህልም ዓላሚና ተርጓሚ ነው" ተብሎ የሚነሳው ቅሬታ ትዝ አለኝ። በተለይ ትግራይና ደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ። "የብሔሮች የራስን በራስ ማስተዳደር መብት እስከመገንጠል..." የሚለውን መፈከር ቀድሞ የዘመረው ድርጅቴ በዚህ ሲወቀስ ቅር ይለኛል።በፈረንጆቹ አነጋገር "ፖዬቲክ ጀስቲስ" ነው። በአገርኛ ብሂል ደግሞ "በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት..." የደረሰብን ሆኖ ይሰማኛል። በዚህ ጉዳይ እንደ ኢሳያስ ቆዳው ስስና ተጨናቂ ግን ማንም የለም። ከአንድ ዓመት በፊት ጀምሮ ይህንኑ እንስቶልኝ መነጋገራችንን አስታውሳለሁ...

"ስመሬ፡የብሔር ጥያቄ አሳስቦኛል። የዋለልኝ መኮንን የቤት ሥራ የተሠራ አይመስለኝም። ዝም ብዬ ሳየው ሁላችንም ትኩረት ያደረግነው በአብዮቱ አንድ ገጽታ ላይ ብቻ ነው። መሬት! መሬት! መሬት! ውሎ አድሮ ይሄ ነገር ችግር እንዳይፈጥር ያሰጋኛል..."

የኢሳያስ ጭንቀት ትክክል ነበር። ከአመራሮች መካከል በዚህ ጉዳይ የጸና አቋም ያለው ብርሃነመስቀል ብቻ ነዉ። ሌሎቹ የብሔር ጥያቄን የሚያራምዱት እንዲሁ እንደተራማጅነት ማሳያ እንጅ በቁም ነገር አላተኮሩበትም። "ሁለተኛው ኩነኔ" የሚሆንበት እድል ቁልጭ ብሎ ታየኝ። በስብሀት ነጋ፣ በአረጋዊ በርሄና በአባይ ፀሐዬ የሚመራው የትግራይ አርነት ግንባር አመራር ገና በጧቱ ካርዱን ከእጃችን ላይ እንደነጠቀን እኔን ጨምሮ ትዝ አላለንም። ሐቁ ወሎየው ዋለልኝ መኮንን ትግራይ ውስጥ የፖለቲካ ትግሉ ቀያሽ መሀንዲስ ሆኗል።

በመታከት ዓይነት በረጅሙ ተንፍሼ ወደ ኢሳያስ ዞርኩ...

"እንግዲህ ምን ማድረግ ይቻላል? አዲስ ሰውና አርቲፊሻል ሰፔራንቶ ቋንቋ መፍጠር አንችልም። መጠቀም ያለብን አሁንና እዚሁ መሬት ላይ ያለውን የባህልና የቋንቋ ስብጥር ነው። የፖለቲካ ትግል ተመጣጣኝ የፖለቲካ ንቃት ይጠይቃል። ፋና ወጊ የመሆን እድሉ ያለው የተሻለ በተማርነው በእኛው በሰሜነኞቹ እጅ ነው።"

በሌላ በኩል መኢሶን ተራማጅ ኦሮሞዎች ይበዙበታል። ኃይሌ ፊዳ ራሱ አሁን በ"ኢትዮጵያ ትቅደም" ብሄረተኛ መፈክር እንዲህ ሊጠመቅ ላቲን ፊደል የኦሮምኛ መጠቀሚያ እንዲሆን ጥናት የጨረሰው አውሮፓ እያለ ነው። አሁን ግን ጭጭ አለ።

በውስጤ የተጧጧፈ ክርክር ይዞኝ ስምጥ ማለት ከመጀምሬ የቢሮዬ በር ተንኳኳ። ከእንቅልፍ የመንቃት ያህል ብንን አልኩ። ሚካኤለ በሩን ብርግድ አድርጎት ገባ። ሁሌም ሳየው የዐይኑ ሽፋሽፍቶች ከቢታኒያ ጋር ስለሚመሳሰሉብኝ ያስደነግጠኛል። ሲስቅም የእሷን የሆነ ነገሯን ያስተውሰኛል። አሁን የመጣበት ምክንያት መርዶ ሊነግረኝ እንዳይሆን ሰግቼ አፍ አፉን ዐየሁት። "የነገው ቀጠሯችን በሆነ ችግር ምክንያት አልተሳካም" ቢለኝስ? ልቤ ተነሰታ ወደቀች።

"እሽ፣ ሚካኤለ...ምን ልትነግረኝ ነው የመጣኸው?" ጠየኩት እጄን ጨብጨ ግንባሩ ላይ ከሳምኩት በኋላ።

"ደጀኔ የሚባል ሰው ስልክ ደውሎልህ ነው። ከፈረንሳይ አካባቢ ነው። 'የዘገየሁት የቁም ሳጥኑን ቁልፍ የያዙት ሴትዬዋ ወጣ ስላሉ ነው። እንደመጡ ተቀብዬ እመጣለሁ' ብሎሀል።"

ሌላ መልእክት እንዳይጨምር እየተመኘሁ አሁንም አፍ አፉን ማየት ቀጠልኩ። ሚካኤለ ትኩረቱን ግድግዳው ላይ በተሰቀለ ካሌንደር ወረቀት ላይ ሲያደርግ 'እፎ---ይ!' አልኩ በሆዴ። ቀጠሮችንን እስካሁን የገጠመው ሳንካ የለም።

ደጀኔ እስከምሳ ሰዓት ካልተመለሰ ግን ዋጋ የለውም። ከሰዓት በኋላ ንግድ ባንክ አይሠራም። ሚካኤለ ተመልሶ ሄደ። በትእግስት መጠበቄን ቀጠልኩ። በመሀሉ አንድ ሁለት ደንበኞችን አስተናገድኩ። የተጠየቁትን ገንዘብ ከፍለው የተጠገኑ መኪናዎችቻቸውን ወሰዱ። አሁን የደጀኔ መዘግየት ብዙም አያሳስበኝ። የምበደረው ገንዘብ ከበቂ በላይ አግኝቻለሁ። ነገሮች ግጥምጥም ብለው የቀጠሮዬ መንገድ አልጋ በአልጋ መሆን አስደሰተኝ።'ጎ----ሽ፣ እንዲህ ነው ሲቀና!' የቀኝ እጄን አውራ ጣት ወጣ አድርጌ በድል አድራጊነት ለራሴ አሳየሁት።

ኢሳያስ ባለፈው ሳይሄድ የቀረውን መስከ ዛሬ ወጥቷል፣ ወደ ደብረብርሃን። ወይዘሮ ማስተዋል አገር ቤት ሰንበተው ሊመጡ ነገ ሌሊት ይሄዳሉ። ሳላስበው ድንገት የሚጠራኝ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይም ትግራይ ሄዷል። እሁድ መድረስ ያለበት የተሰጠኝ አጣዳፊ ሥራ የለም። ይሄን ሳቃልል ደግሞ ገንዘብ መጣ። ማርከሲስትነቴ ባይፈታተነኝ ኖሮ የፍቅር አማልክትን አወድስና ቆሜ አሸበሽብላቸው ነበር።

በመሀሉ በርገግ ብዬ ድንገት ሮመር የእጅ ሰዓቴን አየሁ። 7 ሰዓት ከ25 ደቂቃ። ደጀኔ አልተመለሰም። ቢሮዬን ዘግቼ ለምሳ ወደ ቤቴ አመራሁ። ሸዋዬ ብቻዋን ቁጭ ብላ የማእን ቀይ መጽሐፍ ስታነብ አገኘኋት። እጅ የሚያስቆረጥም ምስር ወጥ አቀረበችልኝ። ኢሕአፓ ከገጠመው ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት አንጻር ይህ የቅንጦት ምግብ ሊባል ይችላል። ግራ ኃይል መሆን ጥቅሙ እዚህ ላይ ነው። ምግብሽ ጨው አጠረው...በርበሬ አነሰው...እንጀራው ኮመጠጠ ምናምን አናውቅም። ያገኘነውን ግጥም ነው። ከምግቡ ጋር እንደተለመደው ወሬ አብሮ ቀረበ። በጣም ከመግባባታችን የተነሳ ድርጅታችን ያሰመረውን ቀይ መስመር እያለፍን ምሥጢር መነጋገር ሁሉ ጀምረናል...

"አላምረው፣ ደጀኔን የት ብትልከው ነው እንደዚህ የዘገየው? ከአዲስ አበባ ውጭ ነው እንዴ?" ሸዋዬ ኮስተር አለች።

"ሽሬ እዚሁ ፈረንሳይ አካባቢ ነው። ምነው፣ ተፈለገ እንዴ?" ደንገጥ ብዬ ጠየኳት።

"እ--ይ፣ የደርግ አየር ወለድ ጦር አምጿል እየተባለ ነው። ምናልባት ከካምፕ ሊወጡም ይችላሉ። በግርግሩ መሀል የሚያውቁት የድሮ ጓደኞቹ እንዳያገኙት እንዲጠነቀቅ እንድነግረው መልእክት መጥቶልኝ ነው።"

ስለአየር ወለድ ጦር አመጽ መረጃው ነበረኝ። እንዲያውም የደብረዘይቱ አየር ወለድ ክፍል ሻለቃ

መንግሥቱን እንዲያነጋግሩት ጠይቆ ነበር። መድረክ ላይ እንዳለ ለማፈንና ለመግደልም አቅድ ነበረዉ። ምሥጢሩን ማን እንዳሾለከላቸው አይታወቅም። ፕሮግራማቸውን ሰረዙት። አመጹ ግን ቀጠለ። በርካታ አየር ወለዶች ኢሕአፓንና ኢሕአሠን ይቀላቀላሉ ብለንም እየጠበቅን ነው። ዞሮ ዞሮ ሁኔታው ለደጀኔ የሚያሰጋው አይደለም። ይሄንኑ ለሸዋዬ ስነግራት መልሳ ቀለል አደረገችው። ደጄኔን ወዲያው ጣል አድርጋ እኔ ላይ አተኮረች...

"ጓድ አላምረው፣ አንተም ጠንቀቅ በል። በተለይ ከተማ ሰው ይዘህ ስትወጣ ረጋ ማለት አለብህ። ከማን ጋር እንደሆንክ እያወክ መሆን አለበት..." እንደዘበት ይሆን ተናግራ የበላችበትን እቃ መሰብሰብ ጀመረች።

ድንጋጤዬ አመዴን ቡን አደረገው።'አንድ እርምጃ እንኳ ሳልሄድ ከቢታኒያ ጋር የፍቅር ጉዳይ መጀመሬ ተነቃብኝ ማለት ነው?' ሀሞቴ ፈሰሰ።

የሸዋዬ ምክር አስደንጋጭ ዱብ እዳ ሆነብኝ። እስካሁን በመኪና ሰው አሳፍሬ የወጣሁት ሦስቴ ነው። ቢታኒያን ሁለቴና ጎይቶም ለባሲን አንዴ። ስለጎይቶም በዝርዝር አውቃለሁ። ስለዚህ የሸዋዬ ምክር ያነጣጠረው ቢታኒያ ላይ መሆን አለበት። ለአፍታ የምናገረው ጠፍቶብኝ ዝም ብዬ ሳያት ቆየሁ። ነገሩ ከንከን ሲያደርገኝ ግን እንዲሁ የመጣልኝን ቀጥታ ጠየኳት...

"ቢታኒያን ማለትሽ ነው፣ሸዋዬ? ሁለት ጊዜ አንዳሳፈርኳት የማስታወሰው እሷን ነው። ሌላ ሰው አላስታውስም..." ቀና ብላ ስታየኝ ወኔዬን ሰብስቤ ዐይኖቿ ላይ ትኩር አልኩባት።

"አዎ፣ እሷን ቤቲን ማለቴ ነው። ልጅቱ በጣም ጥሩ የቤት ልጅ ናት። ጨዋ ናት። ግ—ን ትልቁ እዳ ቁንጅናዋ ነው። ከአንተ ጋር እንደዚህ የሥራ ልብስ ለብሰህ ስትታዩ ትኩረት ልትስብብህ ትችላለች። እንደገናም ከዕድገት በሕብረት ዘመቻ በሕክምና በምናምን ሰበብ አድርጋ ጠፍታ ቀርታለች። በዚህ የተናደዱባት የገዛ ጓደኞቿ አይጠፉም። በቅርቡም ይመለሳሉ እየተባለ ስለሆነ ተንኮል እንዳያስቡባት ትሰጋለች። በድርጅታችን ትታቀፍ አትታቀፍ ግን አላውቅም። ይሄንን ዐውቀህ ጥንቃቄ እንድታደርግ ነው ያነሳሁልህ..."

ልቤ ወዲያው ወደ ቦታዋ ተመለሰች። 'ቢታኒያ ፍቅሬ፣ እንኳንም አልዘመተች...እንገናኝም ነበር...ኧረ እንዲያውም አንዱ በለስ የቀናው ላስ ያደርግብኝ ነበር!' ውስጤ በደስታ ፍንጥዝ አለች። "የቤት ልጅ" እና "ጨዋ" የሚሉት የሸዋዬ ቃላት ሲታከሉ ደግሞ ፍቅሬ ጨመረ። 'ይህች ምግብ በአፏ የሚዞር የማትመስል የሳሮን ወፍ እንኳንም አልዘምትም አለች። ጭራሽ ደግሞ ከእነዚያ ምኑንም ሳያዩ ጃንሜዳ ላይ ሻለቃ መንግሥቱን 'መንጌ! መንጌ!' እያሉ የልብ ልብ ከሰጡት ደደቦች ጋር ልትዘምት ኖሯል?' ቤቲን የበለጠ ወደድኳት።

"ሸዋ...ልክ ነሽ፣ ከዘመቻ መቅረቷን አላወኩም ነበር..." ጭንቅላቴን በአዎንታ ነቀነኩ።

ከምሳ በኋላ ወደ ምድር ቤቴ ሄድኩ። የሸዋዬን ምክር ምሥጢሬን ከማወቋ የመጣ ነው በሚል መጨነቅ አልፈለኩም። ለአጭር እረፍት ያህል አልጋዬ ላይ ጋደም አልኩ። ተመልሼ ስለምሄድ እንቅልፍ አልተኛም።ጥቂት ደቂቃዎች አርፌ ወደ ጋራዥ ተመለስኩ። ደጀኔ አሁንም አልመጣም። ሰዓቱ እየበረረ ስለነበረ ቁጭ ብዬ መጠበቅ አልፈለኩም። 500 ብር ከመሳቢያ አውጥቼ ኪሴ ውስጥ አስገባሁ። ኀይቶም ለባሲን ሥራ እንዲመራ በቃል ወከልኩትና ላንድሮቨሯን አስነስቼ ወጣሁ። ወደ ቀኝ ታጥፌ የኑረዲንን ዳቦ ቤት አልፌ የመናኸሪያን መንገድ ያዝኩ። ምትኩ ፋርማሲን ሳልፍ ደጀኔ ኤን ዱዌውን እያንቀረፈፈ አለፈኝ።

###

አዲስ አበባ ያው እንደ ከራሞቷ ነች። ከሰፈረባት የግራ መጋባትና የመደነባበር አዙሪት አልወጣችም። ደርግ መቼም አንድ ጥሩ ነገር ተከልኩ የሚለው ሌላ አንድ ጥሩ ነገር ነቅሎ ነው። የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ሲወርስ በመላው ኢትዮጵያ ግንባታ ቀጥ አለ። ግንባታ ሲቆም ደግሞ ግንበኞች፣ አናጺዎችና ለሳኞች ጉሮሯቸው ተዘጋ። ልጆቻቸው ይልሱት ይቀምሱት ነገር አጡ። ሥራ ለመጠየቅ ሰልፍ ሲወጡ ደግሞ ጥይትና ቆመጥ ተበረከተላቸው። ብቻ ከሁለት ዓመታት በፊት የነበረው የሕዝብ መከራና ችግር ለዐመል ያህል እንኳን አልተነካም። መርካቶ ገብቼ ወደ ወርቅ ተራ አመራሁ።

'የቢታኒያን ቁንጅናና ፍቅር የሚመጥን ውድ ስጦታ የት ነው የሚገኘው?'

አንዱ ወርቅ ቤት ገባሁ። አምስት ስድስት የሚሆኑ ሰዎች እየተገበያዩ ነው። ከአንድ ሁለት ምርጫ በኋላ ቢታኒያ ትወደዋለች የምለውን ስጦታ ገዛሁና ማሻሻያ እንዲሠሩልኝ ሰጥቻቸው እስከሚጨርሱ ለመጠበቅ ቁጭ አልኩ። በግምት ከግማሽ ሰዓት በኋላ ተሠርቶ መጣልኝ። የተሻሻለውን ሥራ የሚከካኒከ ጥቁር መነጽሬን አውልቄ አየሁት። ግሩም ተደርጎ ተሠርቷል። መነጽሬን መልሼ አድርጌ አመስግኜ ከወርቅ ቤቱ ለመውጣት ፊቴን ሳዞር የማውቀው ሰው ከጎኔ አፍጥጦብኛል። የቀድሞ መሥሪያ ቤቴ የሰው ኃይል አስተዳደር ክፍል ኃላፊ ነው። ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ነው ያለው። ዓይን የሌለው የደርግ ደጋፊ ስለሆነ ካወቀኝ ፖሊስ ፍለጋ መሮጡ ነው። ዕይታዬን በድንጋጤ ጭለማ ሊውጠው ታገለኝ። ጨረፍ አድርጌ እንደገና ዐየሁት። ሊለየኝ ሞከሮ እንደተቸገረ ከሁኔታው ገባኝ። ርምጃዬን ጨምሬ ወደ በሩ ተንደረደርኩ...

"እቶ ሰመረ! ሰመረ! እቶ ሰመረ አይደለህም እንዴ?" ከጀርባዬ ሲጠራኝ ይሰማኛል።

የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ! እቅሌን ስቼ እንደ ሩር እየከነፍኩ ወደ ላንድሮቨሬ በረርኩ...

# 12

አሐድ ንጋት!

የደጀኔን ክፍል ሳቋርጥ በደረቱ ለጥ ብሎ ተኝቷል። ከቀድሞው ኪራይ ቤቱ ያመጣው ፕላስቲክ ቦርሳዩን አልጋው አጠገብ ወንበር ላይ ልብሶቹ ሥር አስቀምጦታል። ያለፈቃዱ መንካት አልፈለኩም። አልፌው ሄጄ በባዶው የኢሳያስ ክፍል በኩል ወደ በሩ አለፍኩ። ሸዋዬ መነሳቷን በበራው መብራት ስለገመትኩ ወጥቼ ቀጭኗን የምሥጢር መንገዴን ያዝኩ...

'ወይዘሮ ማስተዋል ተነስተው ይሆን?'

በቁልፉ ቀዳዳ በኩል እጮልቁ ወደ ውስጥ ተመለከትኩ። መነሳት ብቻ አይደለም። ነጫጭ ልብሶቻቸውን ለብሰው ከቢታኒያ ጋር ቆመው ሲያወሩ ታዩኝ። 'እእእ...ቢታኒያ! የሴትነትን ከብር ሞዴል ሆነሽ ለማሳየት የተፈጠርሽ ምድራዊት ጽጌረዳ!' የልቤ አራቱም ቧንቧዎች እጅ ሲነሷት በሮቻቸው ተከፍተው ተዘጉ። ማንኳኳትና መምጣቴን መንገር አልፈለኩም። የጋራዥ መብራት ሳበራ ይታያቸዋል። የመኪና ሞተር ሳስነሳም ይሰማቸዋል። አልፌ ሄጄ በምሥጢሯ በር ጋራዥ ገባሁ። የፈረንጆቹን ፊያት 127 ይዤ ወጥቼ ወደ ዋናው አስፋልት ስገባ መንገዱ ዳር ሲጠብቁኝ አገኘኋቸው...

"ልጄ፣ ደህና አደርክልኝ?"

ከመኪና ወርጄ እጃቸውን በቃልና በእጅ ሰላምታ መለስኩላቸው፣

"ሰመረ፣ እንቅልፍ ነሳሁህ፣ ልጄ..." አሉኝ የበዛ የእናትነት ትህትና በሚሰማበት አነጋገር።

ሆሆሆው_' አልኩ ለራሴ፡ 'ሆሆሆው_ማዘር፡ አይቀልዱ እንጂ። ይህችን የለመለመ የወይራ ቀንበጥ የሚመስሉ የውብት ፈርጥ ልጅዎን ወልደው ያስታቀፉኝ የሚስቴ እናት አይደሉም፡ እንዴ? እንኳን እንቅልፌን መተው ደምህን አካፍለኝ ቢሉኝ ዐይኔን አላሽም!' አልኩ በሆዴ።

"እረ ለተ ብዬ ነው ያደርኩት፡ ማዘር። ምንም አላስቸገሩኝም..." መሪውን ይዤ ልባዊ ፈገግታ አሳየኋቸው።

ማስተዋል ለሴኮንዶች ከቢታኒያ ጋር ተንሾካሽከው መኖተው አጠገቤ ተሳፈሩ። ቤቲ በሌሊት ልብሷ ላይ ጋቢ ደርባለች። ሌላ ሰው መስላ ታየችኝ። ደግነቱ እንኳን ጋቢ ዐይነአርግብ ብታጠልቅ ውበቷ አይሸፍንም። በሆነ መንገድ ገንፍሎ ይወጣል። ከሁሉም ከሁሉም ሁሌም የሚገርመኝ በጸጉሯና በፊቷ ገጽ መካከል ያለው ግንኙነት ነው። ጸጉሯን ስትገነጉነው መልኳ ሌላ ይሆንብኛል። ፊቷን በጸጉሯ በከፊል ስትሸፍነው ደግሞ ሌላ። በአምፑል ቅርጽ ሠርታ አናቷ ላይ ሸቅብ ስትቀሰረውም ሌላ። ውበት አንድ ነገር ነው። ራሱን በተለያየ መንገድ የሚገልጽ ውበት ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ለጥቂት ሴቶች ብቻ የታደለና ተዝቆ የማያልቅ የውብት ማእድ ይሏል የቢታኒያ ነው።

'ከእሷ ይልቅ እኔ እድለኛ ነኝ ልበል?' ልቤ በስስትና በኩራት መሀል ሽው ሽው አለች።

ሚካኤለም ለካ ከወይዘሮ ማስተዋል ጋር አብሮ ይሄዳል። ትምህርቱን እንዴት አድርጎት እየሄደ እንደሆነ መጠየቅ አልፈለኩም። የሚማረው የአውቀት ብርሀን ትምህርት ቤት ነው። መምህራኑና ተማሪዎቹ "መኢሶኖች ግቢያችን ገብተው ለምን ይቀሰቅሱናል?" በሚል ቁጣ አድማ መትተው ትምህርት ቆሟል። እሱ ተሳፍሮ መኪናዋን ላንቀሳቅስ ማርሽ ስቀይር ቢታኒያ ወደ እኔ መጣች። ጎንበስ ብላ ዐይኖቼን ፊልጋ ስታገኝ አተኮረችብኝ። ከተለመደው ወንድምና እህትነት የተለየ ግንኙነት የሌለኝ ለመምሰል ያደረኩት ሙከራ ይሳካ አይሳካ አላውቅም።

"ስሙዩ፤" በወይዘሮ ማስተዋል ፊት ጨርሶ በማልጠብቀው የቁልምጫ ስም ጠርታኝ "አቤት!" ስላት "እድርሰሀቸው የምትመጣው ኮቴቤ ከአክስታችን ቤት ነው። መኪና ስላላቸው ይምጡ ብለው ስለደውሉ ነው፡ እሺ?" ጠየቀችኝ።

መኪናዋን ወደፊት አንቀሳቀስኩ።

'ሮማንስ' ሙቼም ከንደ ብርቱ ነው። ፍቅር! በማልቆጣጠረው የውስጥ ግፊት ወደ ጀርባ የሚያሳየኝን የውስጥ መስታወት ዐየሁት። ከቢታኒያ ጋር ዐይኖቻችን ግጥምጥም አሉ። ከንፈሮቿን ገጥማ ወደ

ውጭ ምጥምጥ አድርጋቸው ስታበቃ "እ–ምጿ!" የልሳምህ ምልከት አሳየችኝ። አጸፋውን በፈገግታ መልሼላት ፍጥነት ስጨምር ከዕይታዬ ወጣች።

###

የኑረዲንን ዳቦ ቤት ስናልፍ አዲስ አበባ ለዳቦ ተሰልፋ ጠበቀችን። ፉርኖ ዱቄት የቡዳ መድኃኒት ያህል መወደዱ ምክንያት ነው ተብሎ ሰምቻለሁ። ውስጤ እንደገና ቆሰለ...

ሀ-------- ሁ ኢትዮጵያ ትቅደ---ም፣

ትባል እንዳልነበር የዳቦ ቅርጫት፣

እንዴት እናታችን ትባል ራባት?!

'ትሻልን ሰደን ትብስን ስናመጣ እንዴት እንራብ? እንዴት እንጠማ?' ልቤ ቅሬታዬን አንጎራጎረች።

አውቶቡስ ፋለጋ ወደ መናኸሪያው የሚጎርፈው ሕዝብ ለጉድ ነው። የትራንስፖርት እጥረቱ በራዛ ዘመቻ ምክንያት ብሔራዊ ስቃይ ሆኗል። በዚያው ልክ ኪስ አውላቂውና ማጅራት መቺው ከፖሊስ ቁጥር በላይ ንሯል። መተማመን ብሎ ነገር ጠፍቷል። የሌቦች አሠራረቅ ዘዴ ረቂቅነት እየተነሳ የመገናኛ ወሬ እየሆነ ነው። ጽም! "የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲንቀጠቀጡ ዐየሁ!" የነብዩ እንባቆም ትንቢት ከማርከሲዝም የበለጠ ለኢትዮጵያ የቅርብ ቅርብ ሆኖ ታየኝ።

"አይ ጉድ...ከተበላሹ አይቀር እንዲህ ነው! ጽም! አይ ጊዜ..." ወይዘሮ ማስተዋል የልቤን ያነበቡ ይመስል በሚያዩት ደስ የማይል ትርኢት አማረሩ፣ "ንጉሡ ከወደቁ አገሪቱ ገነት ትሆናለች ሲባል የነበረውንማ ዐየነው'ኮ! እ---ይ፣ ለኢኒቨርስቲ ተማሪ ዋጁን ይስጠው!" ቅሬታቸው ተባባሰ።

ምርጫዬ ዝምታ ቢሆን እወዳለሁ። ነገር ግን ወይዘሮ ማስተዋል በኢሕአፓነቴ አደጋዬ አይደሉም። በደረጃቸው የሚመጥናቸውን ወሬ ባወሯቸው ከፋት የለበትም። ለአጼ ኃይለሥላሴ መውደቅ የተማሪን ረብሻ ምክንያት ማድረግ የአገሪቱ ዋና የፖለቲካ ንቃተ ህሊና ሆኖ ማደጉን አውቃለሁ። ተማሪ ዘጠኝ መቶ ጊዜ ቢጮህ አንድ አገዛዝ እንደ እያሪኮ በጩኸት እንደማይወድቅ አምናለሁ። ከዚህ ይልቅ ንጉሡን የጣላቸው የሥርዓታቸው መበስበስ የሕዝብ አልገዛም ባይነትን መቀስቀሱ ነው። ለጨዋታ ያህል ብቻ ቀልድ የተቀባ አጸፋ መለስኩላቸው...

"ግን፣ ማዘር፣ አጼ ኃይለሥላሴንማ ብዙ ሕዝብ ጠልቷቸው ነው ለዚህ የበቁት። እርስዎ ይወዷቸዋል ማለት ነው?"

ማስተዋል ፊታቸው ከመቅጽበት ልውጥውጥ ብሎ አፈጠጡብኝ...

"ምን ምን ምን? ምን አልክ ልጄ? ትወዷ–ቸዋለሽ? ትወዷ–ቸ--ዋለሽ? ማን ለዚህ አበቃኝና ነው?! ማን በዓለም፣ በደስታ፣ በእዱኛ...እኖረኝና ነው? አ፣ አንተስ ደርስህበት የለም ወይ? በ'ሳቸው ጊዜ እንዲህ እንዳሁኑ በየቀኑ ግርግር የለ...ንትርክ የለ...ቀየው እማን፣ አገሩ ሰላም፣ ገበያው ርካሽ...የገንዘቡ በረከት... የምሰቡ ቸርነት...የሰው ፍቅር! አሁን ደ'ሞ ገዥ አለ ተብሎ ተሙቶ! መንጋ አጥረ ቀላል... ሱሪው ጅል ሁሉ! ቢበላ አይጠጋው፣ ቢለብስ አያምርበት፣ ቢናገር ጣእም የለው...! ከርባት አደረግን ተብሎ ልክ የተሰቀለ ሰው። ጡል ጡል እንደፍየል ግልገል...ኧረ ወደያልኝ አቴ! እንዲያው አታስታውሰኝ፣ ልጄ። ምነው ሸዋ?!"

የወይዘሮ ማስተዋል ቀጥተኝነትና አነጋገራቸው ጥፍጥ ብሎ ሲጣፍጠኝ መናገር እንዲቀጥሉ ሌላ መቆሰቆሻ ተናገርኩ...

"ልክ ነው፣ ማዘር። አጼ ኃይለስላሴን የሚወዱ ሰዎች ይኖራሉ። ግን የጠቅላይ ግዛት ሰው የሚለው ነገር አለ። ጃንሆይ የአዲስ አ'ባን ሕዝብ ጮማ እያስቆረጡ፣ ክትፎ በቅቤ አብልተው የስድስት ወር ድፍድፍ የማር ጠጅ እያጠጡ የወሎን ሕዝብ በርሀብ ስለፈጁ ነው..."

አቋርጠውኝ ጣልቃ ገቡ...

"ውሸት! ውሸት! ውሸት!" ንድድ ብሏቸው ቀጠሉ፣ "...ይሄ የኢኒቨርሰቲ ተማሪ ወሬ ነው። እ? ጃንሆይ ከሰንቱ ጉራንጉር እየለቀሙ ይሄን የድሀ ልጅ ሁሉ አስተምረው ሰው ስላደረጉት መልሶ እጃቸውን ነከሳቸው፣ የኢኒቨርሰቲ ተማሪ። ተምረህ ተጠቀም ብለው ጅማ ኮሌጅ ከፍተው አስገቡት። ሲጠግብ መጀመሪያ ነገር የቆሰቆሰ የጅማ ኮሌጅ ተማሪ ነው። ይልሰው ይቀምሰው ያልነበረው የድሀ ልጅ ሁሉ እንቁላል ሲያበሉት ጊዜ ሽሮ አስጠላኝ አለ፣ ጠገበ። 'ሽሮው አረረና...' ብሎ እየዘመረ ሰልፍ ወጣ። ከዚያ ወደያማ እንዴት ብሎ ይቀም?! አዲስ አ'ባ ሲደርስ ጭራሽ ገንፍሎ ቁጭ። ጧት ማታ ሰልፍ ነው...ጥይት ነው...ግርግር ነው። ብሎ ብሎ ይሄው ጣላቸው..."ትከዝ አሉ።

በስድስት ኪሎ በኩል ዳግማዊ ሆስፒታልን አቋርጠን የእንግሊዝ ኤምባሲን መንገድ ስንይዝ ፍጥነታችን አልታወቀኝም። መገናኛን ስናቋርጥ የወይዘሮ ማስተዋል የድምጽ ቅላጼ ተለወጠ።

"ይሄውልህ፣ ሸዋም አልተረጋጋም። በየደብሩ ሽፍታ ተነስቶ እያመሰው ነው። በመንዝ የራስ ብሩ ልጆች ልጅ መርእድ ብሩና ልጅ መስፍን ብሩ ተነሰተዋል በል። በ'ኛ በመርሐቤቴ ባላንባራስ ሽፈራው ሽንቅል አልገዛም ብለዋል አሉ። በመናገሻ ደግሞ ደጃዝማች ከበደ ብዙነሽ ማነው ከደጄ የሚደርስ አሉ ይባላል። እነዚህ ሁሉ ተናግረው የሚሰሙ፣ ተኩሰው የማይስቱ፣ ደግሰው የማይጎድልባቸው ባላባቶች ናቸው። እኔ እንዲያው ተፈሪ ባ'ንቴ ሰላም ማውረድ የሚሆንላቸው አይመስለኝም። እነዚህን ሳይዙ ሸዋን አይገዙትም..." እንደገና ትከ--ዝ አሉ።

የምመልስላቸው ነገር የለኝም። አገሪቱ እንደ ስኒ ወድቃ ፍርስርስ ያለች መሰለኝ። ኢሳያስ እነዚህ ሽፍቶች ወዳሉበት አካባቢ ነው የሄደው። ቸር እንዲመለስ ጸሎት ቢጤ አደረስኩለት። ወደ ኮተቤ ስንገባ ወይዘሮ ማስተዋል ዐየት አደረጉኝ። ወዲያው ደግሞ ሚካኤለን ገልመጥ ብለው አይተውት ማንቀላፋቱን ሲመለከቱ ድምጻቸውን ቀንሰው ወደ እኔ ጠጋ አሉ...

"ሰመረ፣ ልጄ...የቢታኒያን ነገር እደራ! አባካችሁ፣ ጊዜው አስቸጋሪ ነው። ሁሉንም ነገር ጠንቀቅ ብላችሁ..."

በድንጋጤ ትንፋሼ ቀጥ ሊል ምንም አልቀረው።

###

ፀሐይ ፈንጥቃ አዲስ አበባ ነቃ ብላለች። በጧት ተነስቶ ወደየሥራው የሚባትለውን ሕዝብ እያቋረጥኩ የምኒልክን ዳገት ወጣሁ። ትንሽ እንደሄድኩ አንድ ላይ ከብብ ብለው ታክሲ የሚጠብቁ ሰዎችን ዐየሁ። እነርሱን ሳልፍ አዲስ ስቴሽን ዋገን የመንግሥት መኪና ከእኔ በግራ መስመር በኩል መጣ። ታጥፎ በእኔ መስመር ያለአግባብ ቀድሞ'ኝ የቀኝ መንገዱን ያዘ። ነገሩ እናዶኝ ትኩር ብዬ በቁጣ ስመለከተው ሄዶ ከአንዲት ወጣት ሴት ፊት ለፊት ቆመ። ወጣቷ ከእግሩ እጠር ያለ ጥቁር ካኪ ሱሪና ቀላል ሱፍ ኮት ለብሳለች። ወዲያውኑ አወኳት...

'ወይኔ...ብርከታዊት! በቃ ዛሬማ ያዘችኝ......!' ቀልቤን ስቴ የፍጥነት መጨመሪያውን በኃይል ተጫንኩት።

የለበስኩት የሥራ ቱታና ያደረኩት የጨረር መከላከያ መነጽር ገጽታዬን ለዋውጦታል። ይህ ሆኖ ሳለ ለምን ያን ያህል እንደፈራሁ አላውቅም። እም፣ የፈራሁት ያልተለወጠውን የገዛ ህሊናዬን ነው። ወደ ጀርባዬ ተገላመጥኩ። ብርከታዊት ዐይታኝ ወይም በአጋጣሚ መኪናዋ እየተከተለችኝ ነው። ፍጥነት ጨመርኩ። እንበሳ ግቢ መስቀልኛ መንገዱ ላይ ደረሱብ'ኝ። አልፈው'ኝ ሲሄዱ ፈራ ተባ እያልኩ ወደ

መኪናዋ ተመለከትኩ። ብርክታዊት ከኋላ ብቻዋን ተቀምጣለች። ጸጉሯ በአፍሮ ዘዬ ፍርፍር ተሰርቶ ትንሽ ጃንጥላ መስሏል።ዐይኖቿ ላይ ጥቁር የፀሐይ መነጽር አድርጋለች። ውበቷ ጨምሮ ያየሁት መሰለኝ። መኪናዋ ውልብ ብላ ስታልፈኝ ቅናት ሊዞረኝ ፈለገ...

'ብርክቲዬ፣ ሀሊናዬ ንጹህ ነው!' ለራሴ ተንተባተብኩ።

ዐይኔ አሁንም ይከተላታል። የካቲት 12 አደባባይ ሲደርሱ ወደ ቀኝ ታጠፉ። ልቤ አብራ እጥፍ አለች። ወደ አደባባዩ ተከትዬ ስገባ መኪናዋ የለችም።'ብርክቲ ወዴት ነው የሄደችው?' ልቤ አቅጨን መልስ በጥያቄ መልክ ንግር አደረገችኝ፣ "ወዴትስ ብትሄድ ምን አገባህ!?"

***

እእምሮዬን "አደራ!" ባልኩበት ሰዓት ከእንቅልፌ ነቃሁ።

እሁድ፣ ከምሽቱ 12 ከ35 ደቂቃ። ወይዘሮ ማስተዋልን ኮተቤ አድርሼ ከመጣሁ በኋላ ለቁርስ ብቻ ነው ጊዜ ያባከንኩት። የባንክ ደብተሬ አሁን አያጓጓኝም። በብድር ስጠታዬን ገዝቻለሁ። ደጀኔን ግን አሁንም አላገኘሁትም። ሰሞኑን በአዲስ መልክ በምሥጢር ለተጀመረው ሥልጠና ቀድሞኝ ተነስቶ ወጥቷል። ከረፋዱ ሦስት ሰዓት ጀምሬ ከዓለም ሁሉ ተለይቼ መዋሌን ዐውቃለሁ። የማስታውሰውን ያህል ከጅማ ጉዞዬ መልስ ገና ዛሬ በቂ እንቅልፍ ተኛሁ። መላ አካሌንና መንፈሴን ቅልልል አለኝ። በአንድ በኩል እረፍት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከአንድ ሁለት ሰዓታት በኋላ ለሚጠብቀኝ የወሲብ ጉግስ መዘጋጀቴ ነው። ነፍስ የሚያድስ ቀዝቃዛ የደስታ ነፋስ በእርጋታ ሽ---ው አለብኝ...

'ድልና ክብር ለኢሕአፓ...ውበትና ፍቅር ለቢታኒያ!' እንደገና ደስ የሚል የሐሴት ንፋስ ሽው አለብኝ።

ምሽቱ በደንብ ሲገባ ተነስቼ በባልዲ ውኃ ገላዬን ታጠብኩ። ቀ--ስ ብዬ ነው የታጠኩት። መላ አካሌን ደግሜ ደጋግሜ እያሻሸሁ በምርጥ ሽቶ ሳሙና መታሁት። ብርሻቶ የወረሰው ቆዳዬ ሲነጻ ቆሻሻው ጥቀርሻ መስሎ ወረደ። ትልቁንም ትንሹንም እያሰብኩ ከአንድ ሰዓት በላይ ሳፋ ላይ ቆየሁ። ምንም ዓይነት የዘይትና የጋዝ ሽታ መኖር የለበትም። የምሄደው ወደ ጸአዳዋ የገነት ተክል ቢታኒያ መኮንን ነዋ! ሆዴ በሆነ ዓይነት የስስትና የጉጉት ስሜት ብር--ዝ አለብኝ። የረጠበ ሰውነቴን ለማዳረቅ እንደገና ከአርባ ደቂቃ በላይ ወሰድኩ። መላ አካሌን የቆዳ ማለስለሻ ቅባት እልም አድርጌ አሸሁት። ለስላሳው ጸጉሬን በቅባት አዋዝቼ ጥሩ አድርጌ ሳበጥረው የዝሆ ጉንጉን መስሎ ለጥ አለ...

ቢታኒያ ባትኖር ኖሮ የቀድሞ ሰመረነቴ፣ ለጊዜዛዛ አጥቼው ልቀር ኖሯል!' አልኩ ለራሴ።ንግግሬ የኢሕአፓን ደንብ ጥሼ አዲስ የገዛሁትን ቀይ ከፋይ ጅንስ ሱሪና ነጭ ሸሚዝ ስለብስ የተፈጠረብኝን የውስጥ ጭንቀት ለማርገብ እንደሆነ ታውቆኛል።

አዲስ ቀላልና ጥቁር ቆዳ ጫማዬን አደረኩ። ሽንቀጥቀጥና ቀጠንጠን የሚለው አካሌ እንደተላገ ጣውላ ተስተካክሎ ሲቆም ታወቀኝ። ከወራት ወዲህ ያልተለየኝን ቁታዬን ስጥል በጭራሽ አዲስና የተለየ ሰው ሆንኩ። የሰው ልጅ አካል ምንድነው? እም፣ የማሰብ ችሎታው ተራ ነጸብራቅ ብቻ ነው። እንጂ የራሱ ህልውና የሌለው መሆኑን እንደዚህ ምሽት ተገንዝቤው አላውቅም። የብብቴን ሥር አፍንጫ ቆርጦ የሚጥል ዲዮድራንት ረጨሁት። ደንበኛ ምዕራባዊ ሆንኩ። ይሉኝታ እየመጣ አንገት አንገቴን ሲያንቀኝ ዝምብሎ የሆነ ሰው ተደብቆ የሚያየኝ ወይም ድንገት ዘው ብሎ የሚመጣብኝ መሰለኝ።

'እስቲ መጨረሻውን ያሳምረው!' ይሉኝታ ደርሶ ጸሎተኛ አደረገኝ።

ሸዋዬን ለአራት አልመጣም ስላልኳት ትመጣብኛለች ብዬ አልሰጋም። በዚህ ላይ በእነ ብርሃነመስቀል ላይ የጻፍኩትን ሂሳዊ ጽሑፍ እንድትተይብ ስጥቻታለሁ። አሥራ አራት ገጽ ወረቀት ነው። ተያይዛው እንደሚሆን እርግጠኛ ስሆን ነጻነት ተሰማኝ። ወደ ምሥጢራዊዋ የአደጋ ጊዜ መውጫ መስኮት ከመንቀሳቀሴ በፊት የቀረኝ ነገር አለ። ለቢታኒያ የገዛሁላትን ወርቅ የእጅ አንባር ስጦታ ኪሴ ውስጥ አስገባሁ። ቅዱስ እቃ መስሎ ታየኝ። ሰንሰለቱን መሀል ላይ የሚያያይዘው አንድ ሳንቲም የሚያክል ዘለበት ነው። በልብ ቅርጽ አሰርቼ በሁለቱም ገጹ በማሻሻያ ስማችንን አጽፌበታለሁ፣ "ሰመረ ለ ቢታኒያ!" የሚል።

የጻፍኩላትን ሰባት ገጽ ድርሰት ጥቅልል አድርጌ በጀርባ የሱሪ ኪሴ አስገባሁ።ሁሉንም ነገር መጨረሴን አረጋገጬ ወደ ድብቅ መውጫ መስኮቴ ስራመድ ለተዋናይነት ምርጫ የአካል ብቃት ፈተና ላይ ያለሁ መሰለኝ። አራት ማዕዘን የድንጋይ መስኮቱን በጥንቃቄ ከግድግዳው አላቀቅኩት። ከሥር የተጠማጠመበትን ገመድ ሳ—ብ ሳደርገው መውጫ ሽንቁሩ ከፍት አለ። መሬት ላይ ጋዜጣ አንጥፌ በደረቴ ተስቤ ወጣሁ። የድንጋይ መስኮቱን ገመድ መልሼ ስጎትተው መስኮቱ ድርግም አለ። ሐሳቡን ያመነጨውን ሰው አደነኩት። እንደጠበኩት ዳግላስ ባለመደው አቅጣጫ ድምጽ በመስማቱ ምድርን ቀውጢ አደረጋት...

'ዳግላስ፣ ከዚህ በኋላ ልመደው። በዚች የፍቅር መጨባበጫ መስኮት ደግሜ ደጋግሜ እመላለሳለሁ!' አልኩት ውሻውን።

የውሻውን ድምጽ ስትሰማ ቢታኒያ እየመጣሁ መሆኔን እንደምታውቅ ገመትኩ።የተቀበለኝ በመዐት የባህርዛፍ እንጨት ፍልጥ፣ በከሰል ከምርና በማብሰያ ኢቃዎች የተሞላ ኩሽና ነው። በበሩ የላይኛው ህዳግ ስንጥቅ በኩል ወደ ቢታኒያ ከፍል አጮለኩ። ግምቴ ትክክል ነው። የቤቷን በር ከፍታ ገርበብ አድርጋው መለስ ስትል አየኋት...

'ቢ--ታ--ኒ---ያ! ኢሕአፓ በኪነጥበቡ ወይም በምድራዊ ተዐምረኝነቱ ሰበብ ሆኖ የሰጠኝ አንቺ የገነት ተክል! ከፍቅርሽ ማር ልቋደስ እየመጣሁልሽ ነው...'

የኩሽናውን በር የውስጥ መቀርቀሪያ ከፍቼው በፍጥነት ወጣሁ። ጥቂት ሜትሮች ራቅ የሚለውን አቋራጭ ወለል የዝላይ ያህል ተራምጄው ከቢታኒያ በር ደረስኩ። ለደንቡ ያህል ኳኳ አድርጌ ገባሁ። ቤቷ ትልቁ ሶፋ ላይ ጋደም ብላ መጽሐፍ ታነባለች። የመጽሐፉን ርእስ ሳየው የኒዩ ማኪያቬሊ "ልዑሉ" የሚለው የፍልስፍና ሥራ ነው። ተነጋግረንበታል...

'ቢታኒያ ሆዴ፣ መጣመር ይሉሻል ይሄ ነው!' ራሴን ነገርኩት።

ከከፈተችው ሬዲዮ የሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ንግግር ተሰማኝ። ገና ጥቂት ቃላታቸውን ስሰማ ምን እያወሩ እንደሆነ ወዲያውኑ ገመትኩ። ኢሕአፓ በአንክሮ ሲጠብቀው የነበረውን "የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም" ነው። ደስ አላለኝም።«ሰይጣን ለብልሁቱ መጽሐፍ ቅዱስን ይጠቅሳል» ይላሉ። ሰውየው በዚህ ሰዓት ምርጫዬም አልነበሩ። የልጅነት ዘመኔ ወፈኝነት ውል ብሎ መጣብኝ...

'ምን ዓይነት መጥፎ ወፍ ነው፣ በዚህ የፍቅር ሰርግና ምላሽ ምሽት ይሄን ሰውዬ ያመጣብኝ!'

ቢታኒያ ቀና ብላ አይታኝ ደንግጣ ተነሳች። ዐይኖቿ ዐይኔ ላይ እንደ ወስፈንጠር የሚወረወሩ መስለው አተኮረችብኝ። "አንተ ማነህ? እውነት ዛሬ ለፍቅር ጨዋታ የቀጠርኩት ፍቅረኛዬ ሰመረ ነህ ወይስ ሌላ?!" እያለች እንደሆነ ዐይኖቿ ላይ ስገምት እንግዳ ስሜት እንደፈጠርኩባት አልተጠራጠርኩም። ሄጄ ጥምጥም አልኩባት። ነገር ግን ያቀፍኳት እኔ ብቻ ነኝ። ምንም ዓይነት አጸፋ ሳትመልስልኝ ሴኮንዶች አለፉ። ሲጨንቀኝ እጆቿን ይዤ ፊቷን አየሁት። በጸጥታ ተውጣ በመገረም ትመለከተኛለች።

"ቤቲዬ የኔ ፍቅር፣ ምንድነው እሱ፣ ችግር አለ እንዴ?" ሕጻን ልጅ በማባበል ዓይነት ከንፈሮቿን ለላ አድርጌ እየሳምኩ ጠየኳት።

"ምን ባህ፣ የዐረብ ልዑል መስለህ መጥተህ የምታስደነግጠኝ?" በስስትና በፍቅር ከስልቱ የወጣ ለስላሳ ድምጽ ከጆሮዬ ደረሰ።

" ልውጥውጥ አልኩብሽ አይደል፣ ቤቲዬ?" እንዳቀፍኳት ሶፋው ላይ ወደቅንበት።

"የምን መለዋወጥ አመጣህ? እንደገና ተወለድኩ ብትል አይቀልህም?"

እኔ መላ ትኩረቴ ፍቅር ላይ ነው። ቢታኒያ በበኩሏ በእኔ ምኞት መጠበቅ ላይ አተኮረች። እሷም እንደ እኔ በሁሉም ነገሯ ጽድትድት ብላ ነው የጠበቀችኝ። እምቢ እያልኳት እራት ልታመጣ ወደ ዋናው ቤት ሄደች። ከእጆቼ ወጥታ ስትሄድ ከጀርባዋ አየኋት። እንደ ታሸ ወርቅ ታንጸባርቃለች። የለበሰችውን የአረፍት ልብስ ዐይቼው አላውቅም። ብርቱካናማ ሆኖ በጣም ስስ ነው። በጣም ስስ። የላይ ሽሚዝና ጉልበቷ ላይ ሲደርስ የሚቀር ቁምጣ መሳይ ነገር ነው። ውድ መሆኑን ጥራቱ ይናገራል። የጡት ማስያዣዋና የውስጥ ሱሪዋ ሕልም መስለው ይታዩኛል።'ቤቲዬ፣ የሚጎድልሽ አንድም ነገር የለ!' ምራቄን ዋጥኩ።

ከነጠላ ጫማዋ ጀርባ አሞጥሙጠው የወጡት ተረከዞቿ ትኩስ የበግ ኩላሊት መስለው ታዩኝ። ቅንዝሬ ግንፍል ብሎ አንደቋያ አነደደኝ። ብቻ እሁኑኑ እሁኑኑ እንደ ሙዝ ላጥ አድርገህ ዋጥ አድርጋት የሚል ግፊት መጣብኝ። ለጥቂት ደቂቃዎች መታገስ መበለጥ መስሎ ተሰማኝ። ከበሩ ስትደርስ ቆም ብላ ወደ እኔ ዞረች። ዐይኖቼን ሳልነቅላቸው እጅ ከፍንጅ ስትይዘኝ የሀፍረት ፈገግታ ላሳያት ሞከርኩ...

"ሰ---ሙ---ዬ፣ ድርስቱን...እ?...አንድ ምክንያት አላውቅልህም። እዘጋጅተህ ጠብቀኝ!" ፈገግታ በፈገግታ ሆና የቀኝ እጇን ሌባ ጣት ወደ እኔ እቅጣጫ ቀሥራ በማስጠንቀቅ ዓይነት ወዘወዘችው።

"ቤቲዬ፣ ቃልሽ ይፈጸማል!" የፈገግታ አጸፋ መለስኩላት።

ባለፈው ምሽት ጨዋታችን በስሜት ተውጣ የነገረችኝ ነገር አለ። የሆነ ነገር ብላኝ ወይም ጠይቃኝ "ቃልሽ ይከበራል ወይም ቃልሽ ይፈጸማል" ስላት ነፍሷ አይታው የማታውቅ እርካታ ታገኛለች። ይሄን ስላለችኝ ግን እንደ ጅል በሽንገላ መደጋገም የለብኝም። ትክክለኛው ቦታ ላይ ስኬት ማድረግ ተገቢዬ ነው። የጠይም ፊቷ ገጽ ፍክ---ት ሲል ታየኝ። መደሰቷ አስደሰተኝ። ወጥታ ሄዳ ከደቂቃዎች በኋላ ትልቅ በዳንቴል የተሸፈነ ሞሰብ ይዛ እየተንገዳገደች መጣች። ሮጥ ብዬ ሄጄ ተቀበልኳት። ከፊት ለፊቴ ሳስቀምጠው ከዳኑን አነሳችው። በሆነ ትል---ቅ ባለጸጋ ወይም ባለሥልጣን ድግስ ላይ የተገኘሁ ያህል ተሰማኝ...

"ቤቲዬ፣ ይሄ ሁሉ መዐት ምንድነው?" ዐይኖቼን በምግቡና በእሷ መካከል እያፈራረኩ በመገረም ጠየኳት።

ማር የመሰለ ሽንብራ ዓሳ...የአዞ ግልገል የሚያከል አሳ ጥብስ...ንጣቱ ከጨው የሚፎካከር አልበት... ሽሮ ተጋቢኖ...የቀረ የጾም ምግብ ዓይነት አይታየኝም። የጤፍ እንጀራው ጥራት የሙብላት ፍላጎትን ይጠራል። ማርከሲስት-ሌኒኒስት (ማሌ) በመሆኔ ጊዜው ኩዳዴ ጾም እንደነበረ ረስቸዋለሁ። ከሁኔታዋ ስታዘብ ቢታኒያም ቅልጥ ያለች ማሌ ናት። በተሳሳምን ቁጥር ደረቷን አየዋለሁ። ትልቅ የወርቅ ሀብል በዋሊያ ቅርጽ ጌጥ አላት። ከታብ ግን አላሰረችም። መብላት ስትጀምርና ስትጨርስም አትጸልይም።እጂ ምግቡን አልነካም። ለሁለታችን አጉራሽ ሆኜ በደንብ በላን። ስብሐት ለዐብ! መጸለይ ገና ድሮ ድሮ ትቻለሁ፣ መሶብ አነሳች።

"የፍቅር አምላክ በዚህ ሰዓትና ቦታ ካንተ ከሰመረ ጋር ስላስቀመጠኝ አመሰግነዋለሁ! ብል ኩራት እንዳይሰማህ!" ሳቀችብኝ።

"ቤቲዬ፣ ልቤን እያነበብሽ ነው የተናገርሽው ወይስ በአጋጣሚ? ሁለታችንም እያሰብነው እያለ ነው የተናገርሽው!?" አባባሌ ያሳስቀን እንጂ ከእንጀቴ የተናገርኩት ትክክለኛ ስሜቴ ነው።

ሶፋው ላይ ብዙ መቆየት አልፈለግንም።ስጦታዬን አበረከትኩላት። ብዙ ገንዘብ በማውጣቴ ተናደደች። እምባሩን ግን ወደደችው። ወዲያው ግራ እጂ ላይ አድርጋው ከንፈሬን ሳመችኝ። ተቃቅፈን ወደ አልጋው በረርን። ጫማዎቻችንን አሽቀንጥረን ጣልናቸው። ስጋደምላት በጀርባዋ ሙሉ አካሏን ደረቴ ላይ አስተኛችው። እጇን ወደ ጡቶቿ ስሰድ "አ ኣ...መጀመሪያ ድርስቱ--ን!" አለችኝ።ከሱሪዬ የጀርባ ኪስ አውጥቼ ሰጧት። በፍጥነት ገላልጣ ማንበብ ስትጀምር እኔም አሷን ተከትዬ እንደ አዲስ ነገር ማንበብ ያዝኩ። የተገናኘንበትንና ወደ ፍቅር የገባንበትን የስሜትና የድርጊት ሰንሰለት በአጭር ልብ ወለድ ወግ ነው የጻፍኩት። አካሏንና መልኳን እንደ ፎቶ ልቅም አድርጌ ስዬዋለሁ። ቀጥዬ ባህርይዋንና እንደበቷን፣ወይዘሮ ማስተዋልንና ሚካኤለን። ከቃል ቃል ምስጥ እያለች ሄደች...

"...በዚህች ቀን ቢታኒያ ልቤ ውስጥ ገባች። የተሳብኩት በውብ ሴትነቷ ስለሆነ ቀኗ ለእኔ የተለየ ትዝታ አላት። ከዚያ በኋላ ደግሞ በጣፋጭ አንደበቷና ብዙ ቦታ እንደልብ በማይገኘው ጥልቅ ግንዛቤዋ ወደድኳት። ውበትና ዕውቀት ሲዋሃዱ ሥነውበት (ኤስቴቲክስ) የተሟላ ቅርጽ እንደሚይዝ የተረዳሁት በቢታኒያ ነው። ይህ በተራው መግነጢሳዊ ስህበት ፈጠረብኝ። መሳቤ ወደ ማተኮር አደገ። ሂደቱን ጠብቆ ጣፋጭ ፍቅሯ መጣ። ልቤ ምቷን ቀይራ ትኩረቴ ወደ መተሳሰብ ተለወጠ። ፍቅር ለዘላለም ይኑር..."

ለነዳንዴ ህም...ወዲያው ደግሞ ፈገግ...ቀጥላ ከት ብላ እየሳቀች ልቅም አድርጋ አነበበችው። ወደ መጨረሻው ገጽ ስትሄድ እኔም ሽሚዜንና ጡት ማስያዣዋን ፈትቼ ዐወለኩት። የበሰሉ የሾላ ፍሬዎች ዐይኖቼ ላይ ዱብ ዱብ አሉ። ቀ--ስ እያልኩ ጉርዷን አወለኩት። ሙታንታዋን አላስነካኝ አለች። እንብባ እስከምትጨርስ መጠበቅ ነበረብኝ። በመሀሉ የድርጅቱ ኢሕአፓ ሹል ጥፍሮች በዐይነህሊና ብቅ ብቅ አሉብኝ። የኢሕአፓን ተልእኮ ሁለቴ ሰርገሽ እብሬያት እንደተኛሁ ዐውቃለሁ። ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ የመመሳሰል ግጼታዬን ችላ ብያለሁ። ከዚህ የከፋው ግን የድርጅቱ ውድ ሰነዶች ያሉበትን ማእከል ትቼ ውጭ ማደሬ ነው። ነገሩ ሊረባብሸኝ ከጀጀለው። ታግዬ ባለበት ሳቆመው ልቤ ሌላ መልእክት አስተላለፈችልኝ...

"ሰመረ፣ አንተ ፍቅር እውር አይደለም ብለህ እንደምታምን ዐውቃለሁ። ወዳጄ ሆይ... ሞኝ አትሁን! ፍቅር፣ ወሲብ፣ ምናምን ቀድሞ የተዘጋጀ ቀመር የለውም። የምክንያትና የሎጅክ ጣጣም አያውቅ። ድንገት ብቅ ይላል፣ ሀሴት አዝንቦልህ መልሶ ይሰወራል። እንደገና ትናፍቀዋለህ። ይሄንን የተፈጥሮ ሕግ እንኳንስ አንተ የፍቅር አማልከት ሊለውጡት አይችሉም።በል፣ እንደ ነፋሱ ንፈስ፣ እንደ አገሩ ደንስ፣ እንደ ጅረቱ አቅጣጫ ፍሰስ! ጉያህ ውስጥ ያለችውን ይህችን የምድር ቆንጆ ፍቅር አቀዳጃት!" የቢታኒያ ድምጽ ከጉዞዬ መለሰኝ...

"ሰሙዬ፣ እውነቱን ልንገርህ አይደል? ጉደኛ ነህ! በቃ፣ እንጀራህ ይሄ ነው!"

ወረቀቱን አጥፍጥፍ አድርጋ ትራስጌዋ ላይ አስቀመጠችውና ዞር ብላ አቀፈችኝ። በደመነፍስ ዓይነት እንቅስቃሴ ጥምጥም አልኩባት። ከንፈሮቻችን ሲገናኙ እንደ አቶኑ ምድጃ ግዬ ግዬ መንደድ ጀመርኩ። የሚነደው እሳት በቅጽበት ወደ ቋያነት ተለወጠ።"ቤ----ቲ-----ዬ!" ስላት "ሰ----ሙ----ዬ!" እያለች እንሽካሽካችልኝ። ቀስ በቀስ ሁለታችንም ወደ ጥልቅ ሰመመን ሽርተት ሽርተተተት እያልን በቀስታ ገባን።

እርቃን ገላዎቻችን አቻዎቻቸውን እየፈለጉ ተዋሀዱ። የፍቅር ጨዋታ አታሞውን ጎስሞ ጉግሱን አስጀመረው። ወደረጅም የጠፈር ጉዞ ይዞን ጥርግ አለ። ጭር ያለ ህዋ። ጆሮ የሚጋረፍ ቀዝቃዛና ረጋ ያለ የስሜት ነፋስ...። ቀስ በቀስ ደግሞ በስም የማውቃቸው የምድሪቱ ድንቅ ፈላስፎች ብቅ ብቅ አሉ። ፊትና ኋላ ሆነው እግራቸውን እየጎተቱ ሲመጡ አየኋቸው። መጀመሪያ ያገኘሁት ፕሌቶን ነው...

"ሰመረ፣ 'በሴትና በወንድ መካከል ወሲብ የሌለበት የቅርብ ጓደኝነት ሊኖር ይችላል' አልኩ። እናንተ ይሄንን ጓደኝነት 'ፕሌቶኒክ ፍቅር' አላችሁት። አሁን አንተን ሳይ የጻፍኩት ስህተት መሆኑን ተረድቻለሁ። ይህንን ቃሌን ለዓለም ንገርልኝ..."

ሓርስቶትል ተከተለ፣ "ሰመረ፣ 'ወንዶች የተፈጠሩት ለአዳባባይ፣ ሴቶች ደግሞ ለአልጋ ነው' ብዬ በመጻፌ ምነው ያን ያህል ዘለፍከኝ? ከዚህ በኋላስ ትደግመዋለህ?" ብሎኝ ሄደ።

ቁሱ ፈላስፋ አውጎስቲን ብቅ አለ። "ሰመረ፡ እንደጨረስከ እፈልግሃለሁ። ከእግዚአብሄር ከተማ ወደ ኃጢያት ከተማ የምትወስድልኝ ደብዳቤ አለ..." ሲለኝ መሳቅ ነበረብኝ።ስሜት አንቆ ስለያዘኝ አልቻልኩም።

ከጀርባው የሚመጣው የጀርመኑ ፈላስፋ ኢማኑኤል ካንት አጠገቤ ደረሰ። ድንግልነቱን እንደጠበቀ ስለሞተ ሳየው ሰቅቅ አልኩ። "ሰመረ፡ የምሬን ልንገርህ! አሁን እያደረከው ያለሽውን ነገር ሳልሞከረው መምጣቴ በጣም ቆጭቶኛል። ጥሩ አደረክ!"

ጉዞው ማለቂያ ላይ ካርል ማርክስን አገኘሁት፣ "ሰመረ፣ የተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ሕግ በተግባር ይሄ አሁን የያዛችሁትን ይመስላል። አለመሳሳቱን ለደርግና ለመኢሶን ንገርልኝ!" ብሎኝ አልፎኝ አብስ አለ።

# 13

ጧት ወደ ሥራ ስወጣ በፍቅርና በፖለቲካ ሁነቶች የጦዘው መንፈሴ አልተረጋጋም። በቢታኒያ ቅገፔት በሚመስል የጣፋጭ ፍቅር ትኩስ ትዝታና በሚጠብቀኝ የፖለቲካ ተግባር መካከል እየባዘንኩ ነው። ሌሊቱ ነግቶ ከቢታኒያ ጋር መለያየታችን የጊዜ ሕግ ነው። የቱንም ያህል ብንጠላው ልንለውጠው አንችልም። አሁን ሲገባኝ እንደ ጊዜ አጥረት የፍቅር ጠላት የለም። ነገር ግን ጊዜ ጅረት ነው። የሚያልቀው የእኛ ፍላጎት እንጂ እሱማ ሁሌም አለ። እናም ምሽት ሲደርስ እንደገና አገኛታለሁ።

ከሸዋዬ ጋር ስንገናኝ የአዳሬን ነገር ዐይነ ውኃዬ ላይ የምታውቅብኝ መሰለኝ። ሰላም ብያት ለቁርስ ስንቀመጥ ደጀኔ መጣ። ደጀኔ ከአካል ልምምድ ሲመለስ ከወገቡ በላይ መታጠብ ልምዱ ነው። ሰውነቱን አደራርቆ መጥቶ ሰላምታ ተለዋወጥን። አጠገቤ ተቀመጠ። ያመጣልኝን መልእክት ሊሰጠኝ ፈልጎ ሰዓታችን ባለመገጣጠሙ እንዳልሰጠኝ ሳንነጋገር ተግባብተናል። አሁንም ሳንጠፋፋ ሊሰጠኝ ወሰነ መሰለኝ ወዲያው ብድግ ብሎ ወደ ክፍሉ ገብቶ ተመለሰ። ዳጎስ ያለ ካኪ ፖስታ ይዞ መጣ። ተቀብየ አመሰገንኩት። ያው እኔው ያስቀመጥኳቸው የራሴ ሰነዶች እንደሆኑ ስለገመትኩ አልከፈትኩትም።

ሸዋዬ ቅንጬ አቀርባልን መመገብ ስንጀምር የግራ እጇን ሰዳ ጠረጴዛ ላይ የነበረውን ሬዲዮ ከፈተችው...

'ሬዲዮ ከመጣ ብርኩቲ መጣች ማለት ነው...' በሆዴ መሳቀቄን ለራሴ ነገርኩት።

ኢጋጣሚ እንዳልሆነ ይገባኛል። ብርኩታዊት በድምጿ ከተፍ ብላ የሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያምን የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ደግማ እያነበበች ነው። ትላንት ከቢታኒያ ጋር ሆኜ ስሰማው የጥያቄ ማእበል ቀስቅሶብኛል። የመጀመሪያውና ቀላሉ ጥያቄ ሻለቃ መንግሥቱ መግለጫውን

ጋዜጠኞች እያሉ እሱ ራሱ ለምን ስቱዲዮ ገብቶ አነበበው? ሁለተኛ፣ የመንግሥትን ሥልጣን ተጠቅሞ የፕሮግራሙን መድረክ ለፓርቲዎች ማመቻቸት እንጂ እሱን ምን ጥልቅ አድርጎት ጥሪ አቅራቢ ሆነ? ሦስተኛ፣ በዚህ ፕሮግራም ለየትኛው ፓርቲ ነው ጥሪውን ያቀረበው? ሕቡዕ የገባውን ኢሕአፓንና ጠበንጃ ያነሱ ድርጅቶችን ይጨምራል? አራተኛ፣ ሻለቃ መንግሥቱ የጥሪውን ትርጉም በትክክል ዐውቆታል?

"ምንድነው የሚያወራው?" ቤቲ እንደእኔው ግራ ተጋብታ ጠይቃኝ ነበር።

"ቤቲዬ፣ እንኳን እኛ እሱ ራሱስ ያውቀዋል ብለሽ ነው? ከዚህ የበለጠ የገረመኝ ደግሞ የጋዜጠኞችን ሥራ ነጥቆ እሱ ማንበቡ ነው። ምን ለማለት እንደፈለገ አልገባኝም።" ወሬያችንን እንደማንኛውም ዜጋ ዓይነት አድርጌ ነበር የማዋራት።

"እሱማ አንድም ሥልጣን አለቅም ማለቱ ነው፣ ሁለተኛም ዐዋቂ መስሎ ለመታየት ነው። የበታችነት ስሜት የሚፈጥረው ፍርኃት ይመስለኛል።" አለችኝ ፊቷ ላይ ግልጽ ንቀትና ማጣጣል እያሳየችኝ።

"ከአፍሽ ማር ጠብ ይላል፣ ሆዬ!" ከንፈሮቿን በከንፈሬ ምጥምጥ አደረኳቸው።

"ምን የተለየ ነገር ተናግሬ ነው፣ ስሙዬ?"

ከቁርስ በኋላ ወደ ጋራዥ ልሄድ ብድግ ስል ካልጠበኩት አቅጣጫ ድምጽ ተሰማኝ። የውጭው ምሥጢራዊ የጣውላ በር ተንኳኳ። ከእኛ ሌላ ሰው ሲያንኳኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያጋጥመኝ ነው። በርጋግ ብዬ ሽዋዬን አየኋት። ቶቅ መስላ ጆሮዋን ወደ በሩ ደግናለች። በጥንቃቄ አዳምጣ ኮድ መሆኑን ስታውቅ ፊቷ መልሶ ደ—ብ አለ። የሁላችንንም ኮድ እሷ ብቻ ስለምታውቀው እኔም ተረጋጋሁ።

"ሰላም ነው...የኛው ሰዎች ናቸው!" ብላ ልትከፍትላቸው ተነስታ ሄደች።

በሩን ስትከፍተው ቀድሞ ብቅ ያለው ኢሳያስ ነበር። በመስከ ሥራው ላይ አደጋ ገጥሞት የተመለሰ መስሎኝ በድንጋጤ በድን ሆንኩ። ኢሱ የተፈጠረብኝን ስሜት ግንባሬ ላይ ወዲያው አንብቦታል። "ሰላም ነው!" ብሎ አረጋጋኝ። ከእሱ ጀርባ የእሱን እጥፍ የሚያክል ረጅም ሰው ይታየኛል። ወደቤት ሲገባ ጎንበስ አለ። ዘርዑ ከሀሸን ነው። ተቀምጩ ስላየሁት ጭምር መሰለኝ ወጋግራ መስሎ ታየኝ። ብርሃነመስቀልን በ"መጀመሪያው ኩነኔ" ከቦታው ካነሱት ጀምሮ የወቅቱ የኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ዋና ጸሐፊ ነው። ትዝ ሲለኝ ደራሽ ቅሬታ ጠቅ አደረገኝ። ዘርዑ ሲገባ ቀጠን ያለና መካከለኛ ቁመት

ያለው ሰው ተከተለው። በጨረፍታ ሳየው ዮሴፍ አዳነ ነው። ከኢሳያስ ጋር ተጨባብጠን ተሳሳምን...

"ሃይ፣ አላምረው?! የሶማሊ ተራው ድብቅ ሚካኒክ..." ልንሳሳም ስንል ዘርዑ ከት ብሎ ሳቀ ።

"አዳነ ይሙት፣ ስትስቅ ብቻ ነው አላምረው መሆንህን ያወኩት...አይገርምም?" ዮሴፍም በአለባበስ ለውጤና በመመሳሰሌ ብዛት በመገረም እየሳቀ ተጨባብጠን ተሳሳምን።

ዮሴፍ ሲጫወት ሁሌም የተለየ ለዛ አለው። ስማእቱ ወንድሙ ቢኒያም አዳነም እንደዚያው ነበር ሲባል ሰምቻለሁ።

"ከ'ኔው መመሳሰል የእናንተው የበለጠ አያስገርምም?" በተራዬ ሳኩ።

ዘርዑና ዮሴፍ የኢዲሱ ሠራተኞች ማኀበር አርማ ያለበት ቆብ አድርገዋል። ነጋዴዎች የሚለብሱትን ካኪ የሥራ ካፖርት ደርበዋል። ዘርዑ ጽዳቱ እንደነገሩ የሆነ ቆዳ ጫማም ተጫምቷል። ዮሴፍ ደግሞ ፕላስቲክ ጫማ። ሁለቱም ልክ ከአህል በረንዳ ወጥተው የመጡ ነጋዴዎች ይመስላሉ። መቼም በመመሳሰል ጥበብ እንደ ኢሕአፓ ሰዎች የተዋጣለት ያለ አይመስለኝም። አንዳንዴ ሳስበው ከመጠን በላይ የሆነው የአራት ዓመታት የሕቡዕነት ባህላችን ውጤት ሆኖ ይሰማኛል።

'ጥንቅቅ ባለ የገበሬ አገር ውስጥ እንደ ከንቲባ ከተማ ውስጥ የተጎለተ ድርጅት ከ'ኔው ኢሕአፓ ሌላ ይኖር ይሆን?!'

"አላምሮ፣ ወ'ዳንተ ምድር ቤት ናቸው። እንሂድ!" ብሎ ኢሳያስ መልሴን ሳይጠብቅ ሁላችንንም እየመራን ወጥተን ወደ ደጀኔ ማደሪያ ከፍል ስንገባ ዘርዑ ከደጀኔ ጋር ወደ ኋላ ቀረ።

'ጉ--ድ ፈ--ላብህ፣ ሰመረ!' ድንጋጤ እንደመጥረቢያ ፈለጠ'ኝ።

ማእከላዊ ኮሚቴው እዚህ ቦታ ሕቡእ አስገብቶ ያስቀመጠኝ ለከባድ ድርጅታዊ ተልእኮ ነው።ይህ ሆኖ ሳለ ቤቴን ትቼ ከቢታኒያ ጋር ማደሬ የተሰማብኝ መሰለኝ። የመጡት ነገሩን ሰምተው በሂስ ሊጠርቡኝ እንዳይሆን ሰጋሁ። ሳስበው ግን የሚሆን ነገር አይደለም። «ቂጡ ላይ ቁስል ያለበት ውሻ...»ዓይነት አባዜ ስለያዘኝ ነው። ዘና ብዬ ተከተልኳቸው። ትንሽ ቆይታ ሽዋዬ ተከተለችን። እሷን ሳይ የመጡበት ጉዳይ ከምላ ጎደል ገባኝ። በ "አደፍርስ" ሊያባዙት የፈለጉት ወረቀት አለ ማለት ነው። ዘርዑ ከደጀኔ ጋር የቀረው ደግሞ ሁለቱም ወታደራዊ ከንፍ ውስጥ ስላሉ ነው። የሚሰጠው መመሪያ አለ ማለት ነው።

ግምቴ ትክክል ነው። ዮሴፍ በውስጥ ሱሪው ሥር ተጣጥፎ የተቀመጠ አንድ ገጽ ወረቀት አወጣ። በአራት መቶ ቅጅዎች እንድታባዛው ነግሮ ለሸዋዬ ሰጣት። ሸዋዬ ቀድማን ወደ እኔ ማደሪያ ክፍል ስትሄድ እኛ በዝግታ እየተከተልናት ወሬ ጀመርን...

"ጌታቸው ማናን ለሆነ አጣዳፊ ሥራ ፈልጌው ነበር። ላገኘው አልቻልኩም..." አልኩት ዮሴፍን ተጠሪዬ የነበረው ተስፋዬ ወደ ትግራይ በመሄዱ ከፖሊት ቢሮው ጋር ለጊዜው የሚያገናኘኝ ጌታቸው መሆኑን እንደሚያስታውስ እየገመትኩ።

"እእእእ...ሳይነግርህ ሄደ እንዴ? አንድ የተንዛዛ የውህደት ሥራ አለ። እሱን ለመጨረስ ወሎ ሄዷል። ምናልባት በዚህ ሦስት አራት ቀን ውስጥ የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ስላለ መምጣቱ አይቀርም..." አለኝ ጭንቅላቱን በምናልባት እያወዛወዘ።

ለነገሩ የነገረኝ ዜና አዲስ አልነበረም። ያልነገረኝን ውህደት ከነ ጣጣው ሰምቻለሁ። ቀይ ባንዲራ ከሚባል ቡድን ጋር የተደረገና ያልተጠናቀቀ ውህደት ነው። የቡድኑ መሪ ጌታሁንና ሌሎች አራት ሰዎች ተዋህደው አብቅተዋል። እናም በልዩ ልዩ ቦታዎች ላይ ተመድበዋል። የቡድኑን የወሎ ቅርንጫፍ ከወሎ የኢሕአፓ በይነቀጣና ጋር ለማዋሃድ ሲሞከር ግን ኢሕአፓዎች አይሆንም አሉ። ምክንያታቸው ቡድኑን በደርግ ሰላይነት መጠርጠራቸው ነው።

እርግጥ ውህደት ከማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ አመሰራረት ዘዴዎች አንዱ መሆኑን ዐውቃለሁ። ነገር ግን መኢሶን ስላስፈራኝ "ውሕደት ለኢሕአፓ ትክክለኛ የአመሰራረት መንገድ አይደለም" የሚል አቋም ነበረኝ። በተግባር ሲታይ ግን በጣም ተሳስቻለሁ። ቀደም ብሎ ጌታቸው ማሩ ራሱ አብዮት የተባለ ቡድን ነበረው። እሱን ይዞ ነው የተዋሀደው። የውህደት ሥራው እየሰፋ ሲሄድ ግን ስጋቴ ተመልሶ ምቾት አልሰጥህ አለኝ። በተዋሃዱት ቡድኖች መካከል የደበዘዘች ቀጭን መስመር እየታየችኝ ታስቸግረኛለች። ምናልባት እጉል ተጠራጣሪም ሆኜ ይሆናል።

"እ–ይ፣ ይህንን ያህል እንኳን አጣዳፊ አይደለም። ጽሑፍ ልሰጠው ፈልጌ ነው።" መልሼ ቀለል አደረኩት።

"ከዘገየብህ ደግሞ ክፍሉ ታደሰን ልታገኘው ትችላለህ። እንዲያውም መቼ'ለት ነው እስካሁን አለመተዋወቃችሁ ገርሞት እየነገረኝ ነበር። ከቤት ስለማይወጣ ጉለሌ ሄደህ አግኘው..."

በሐሳቡ መስማማቴን ስነግረው ዮሴፍ ከወሬ ወሬ ሌላ የረሳውን ነገር አስታወሰ...

"ውህደቱ አዳዲስ ሰዎችን አምጥቶልናል። አንድ ሻለቃ ሽታዬ ደስታ የሚባል አዲስ አባል ለፋይናንስ ኮሚቴው ተመድቦልናል። ገዙ በሚል ኮድ ነው የሚታወቀው። እኔና ዑስማን ሥራ ስለሚበዛብን የዕለት ገቢ እሱ እንዲቀበል አድርገናል። ለሚቀጥለው የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ስትመጣ አስተዋውቅሀለሁ..."
ሲለኝ ማስታወሻ ያዝኩ።

"ጥሩ አድርጋችኋል!" ሰውየውን ስለማላውቀው ሌላ አስተያየት አልሰጠሁም።

ወሬያችንን ሳናቋርጥ ሄደን ወደ ማደሪያ ክፍሌ ገባን። ልክ እግሬ መግቢያውን ሲረግጥ በዚያችው ቅጽበት ረስቻቸው የነበሩ ሁለት ስጋቶች በአንዴ ድንገት መጥተው አንቅ አደረጉኝ። ትላንት ምሽት ወደ ቢታኒያ ስሄድ የለበስኩት ልብስ...። ቅድም ሥራ ልሄድ ስል አውልቄ አልጋዬ ላይ ጣል አድርጌው መውጣቴ ትዝ አለኝ።

'ወይኔ፣ ምን ዓይነቱ ዝርክርክ ነኝ!'

ዮሴፍ ልብሱን ሲያየው ምን እንደሚል መገመት አቃተኝ። ደስ የማይል ስሜት እንደሚሰማው ግን የሚጠፋብኝ ነገር አይደለም። ሁለተኛው ስጋቴ ደግሞ ዮሴፍ ራሱ ነው። የሦስቱን ቀናት የጋረዥ ገቢ የኢሕአፓ ድርሻ ቢጠይቀኝስ? የድርጅቱ የፋይናንስ ክፍል ተጠሪ ነው። ከመጣ አይቀር በዚሁ መውሰድ ይፈልግ ይሆናል። ደጀኔ የባንክ ደብተሬን ለማምጣት ሄዶ ስለዘገየብኝ ለቢታኒያ ስጦታ መግዣ ብር ቀንሼበታለሁ። በድርጅቴ ኢሕአፓ በጣም ከምኮራባቸው ባህሎቻችን አንዱ ፍጹም ታማኝነት ነው። በፈፀምኩት ተግባር ከፍርሀት ይልቅ ሀፍረት ተሰማኝ። ሳልዘጋጅ ደረሰብኝ ማለት ነው።

'ምን ዐይነት የከብት ከብት ነኝ!' ራሴን ወቀስኩት።ልክ እኔ ማደሪያ ክፍል እንደገባን ዐይኖቼን ወደ አልጋዬ ወረወርኳቸው። ምን ተዐምረኛ ወፍ መጥታ ከጉድ እንዳወጣችኝ አላውቅም። አልጋዬ ላይ ነጭ ሸሚዝና ቀይ ጅንስ ሱሪ አይታየኝም። ሳይታወቀኝ ሻንጣ ውስጥ እንዳስገባሁት ጠረጠርኩ። 'እፎ---ይ! የፍቅር አምላክ ደርሶ አዳነኝ...' ተረጋጋሁ።

በሥራ ወደ ተወጠረችው ሽዋዬ ተጠጋን። እስከምትጨርስ ድረስ ለመጠበቅ አጠገቧ ቆምን። የወሬው ርእስ ተቀይሮ ኢሳያስ የመስከ ሥራ አቋርጦ የመጣበትን ምክንያት ነገረን። ሰሜን ሸዋ ውስጥ ለኢሕአሠ ወታደራዊ እንቅስቃሴ የሚያመች ስፍራ ለማጥናት ነበር የሄደው። ነገር ግን በሐሳብ የተዘጋጀውን የንድፍ ወረቀት አለመያዙን ያወቀው ደብረብርሃን ሲደርስ ነው። አሁን ከዘርው ጋር አብረው የመጡት ወረቀቱ ከደጀኔ ይኖር እንደሆን ለመፈለግ ነው። ዘርዑና ደጀኔ ከጀርባችን መጥተው ሲቀላቀሉን ወረቀቱን ይዘውታል። ዘርው ገላልጦ ኢሳያስን እያሳየ ገለጻ ያደርግለት ጀመር።

ጨርሶ አላምንበትም። አሲምባን በወታደራዊ መናኸሪያነት የመረጡበትን ምክንያት ብርሃነመስቀል ነግሮኛል። ቦታው ከኤርትራ ኩታ ገጠም ነው። በችግር ጊዜ የማፈግፈጊያ የጀርባ በር ለማግኘት ነው። አንድ የገረመኝ ነገር ግን አለ። ገና ኢሕአሠ አንዲትም ጥይት ሳያጮህ "ማፈግፈጊያ በር" የሚለው ነገር መምጣቱ። ሥነልቦናዊ መዘዙን ያጤኑት አልመሰለኝም። ቅድሚያ መውሰድ የነበረበት ኢሕአሠ "የጸና ነጻ ቀይ ከልል ፈጥሮ እያሰፋ መሄድ አለበት" የሚለውን ነጥብ ነው። ስለ አሲምባ መመረጥ ይሄን ካሉ በኋላ ስለ ሰሜን ሸዋ ሲናገሩ አባባላቸው እርስ በእርሱ ተቃርኖ ቁጭ አለ። ሲጨንቀኝ ኢሳያስን ከወር በፊት ጠየኩት...

"ኢሱ፣ ሰሜን ሸዋን በእነርሱ መሥፈርት ምን ማፈግፈጊያ የጀርባ በር አለውና ነው ለጥናት የመረጡት?"

"ሰመሬ፣ ተዋቸው። ይሄ ሁሉ ከአዲስ አ'ባ ላለመውጣት የሚቀርብ ምክንያት ነው። ወይም ቢያንስ ከአዲስ አ'ባ ላለመራቅ ተፈልጎ ነው። ያ ካልሆነ ደግሞ ምናልባት ደርግ በሆነ ድንገት ሥልጣን ቢለቅ ቶሎ መጥቶ አራት ኪሎ ቤተመንግሥት ለመግባት ነው። ግን ምንም ማድረግ አንችልም። የእርምት ንቅናቄ እናደርጋለን እያሉ ነው፣ ያኔ እናነሳዋለን..."

ሰሜን ኢትዮጵያ ተወልጄ ያደኩ የፖሊስ ልጅ ነኝ። ሳይታወቀኝ አንድ የማውቀው ነገር ውስጤ አለ መሰለኝ። ዝምብዬ ሳስበው እቅዱ አስቂኝ ይሆንብኛል። ከሰሜን ሸዋ ሌላ ሲዳሞም ተመርጧል። ይሄ ምርጫም ከሰሜን ሸዋ የከፋ ችግር አለበት። ነገሩ ትዝ ሲለኝ አጋጣሚውን ለመጠቀም ወደ ዮሴፍ ዞር አልኩ...

"እንዴት ነው፣ ጆስ፣ አዲሱ የፖለቲካ ሁኔታ የሲዳሞን ምርጫ አያስቀረውም ብላችሁ ነው በእቅዱ የገፋችሁበት?" የድምጼ ቃላጼ ከመቃወም ወይም ተለዋጭ ሐሳብ ከማቅረብ ይልቅ "አልገባኝም" የሚል መልእክት እንዲኖረው ለማድረግ ሞከርኩ።

"አዎ፣ ትክክል ነህ። ሲዳሞን ለሽምቅ ውጊያ መነሻ ይሆናል ብለን የመረጥነው 1964 በበርሊኑ የመመስረቻ ጉባኤ ነው። እዛ በጊዜው ብሔራዊም መደባዊም ጭቆናው የከፋ ነው። እና አብዮቱ መጀመሪያ የሚፈነዳበት ቦታ ይሆናል የሚል ግምት ነበረን። ሌላው ምክንያታችን ኬኒያን የ'ሎጅስቲክስ' በር አድርገን መጠቀም ያስችለናል የሚል ነው። እንዳልከው የመጀመሪያው ግምታችን አልሠራም። ከገመትነው ጊዜ በፊት አብዮቱ ፈነዳ። ደርግ መጣና እንዱን ችግር...የመደብ ቅራኔውን... ከመሠረቱ ፈታው። አሁን ሲዳሞን ይዘን የቀጠልነው ለሁለተኛው ጥቅሙ ነው።ኬኒያ..." አለኝ ዮሴፍ እንዴ እኔን

ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ዘርዑና ወደ ኢሳያስ ዐይኖቼን እያፈራረቅ።

እንደ አሲምባ "የጀርባ ማፈግፈጊያ በር" አለማለቱ አስደስቶኛል። መልሱ ግን ፃምናምኒት አላረካኝም። ሲዳሞን የሰሚን ኢትዮጵያን ያህል ስለማላውቀው ይሆናል ብዬ መጨነቅ አልፈለኩም። ኢሕአሠን እዛ መትከል የዋዛ ሥራ አይደለም። ሁላችንም ልንከዳቸው የማንችላቸው ትልልቅ ፈተናዎች አሉብን። ዮሴፍ እነሱን አላነሳቸውም ወይም ሊያነሳልኝ አልፈለገም። የማላውቀው የውስጥ ግፊት ተናገር ተናገር አለኝ...

"እኔ ግን ሌሎች ያልታዩ መሰናከሎች አሉ የሚል ሐሳብ አለኝ..." ብዬ ቀና ብዬ ዐየሁት።

"ለምሳሌ?" ዮሴፍ ጆሮውን ይበልጥ ወደ እኔ አስጠጋው።

"ሦስት ምሳሌዎችን ልስጥህ። ሽምቅ ውጊያ ከመውጫና መግቢያ የጀርባ በር እኩል ተስማሚ የውጊያ ቶፖግራፊ ይፈልጋል። ለመንግሥት ጦር እንቅስቃሴ በተለይ ለጀት ድብደባና ለከባድ መሣሪያ ጥቃት የማይመች ተራራማ ቦታ መሆን አለበት። በሕዝብ መሀል እንንቀሳቀሳለን ብንል እንኳን ሰፊ ነጻ መሬት እስከምንፈጥር ድረስ መዋጋታችን የማይቀር ነው። ይህ የገደላገደል ስፍራን ጠቃሚነት የበለጠ ቅድሚያ እንድንሰጥ ያደርገናል። ሁለተኛ፣ በኛ ኢሕአሠና በሲዳሞ ሕዝብ መካከል ያለው የብሔር ስብጥር ልዩነት ነው። በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ኢሕአሠ ውስጥ አማርኛ ተናጋሪ መብዛቱ አይቀርም። ሲዳሞ ገብተን 'እኛ ከድሮዎቹ ነፍጠኞች የተለየን ነን፣ የመጣነው የነጻነታችሁ ባለቤት ለማድረግ ነው' ብለን ለማሳመን ከሽምቅ ውጊያው የበለጠ ፈታኝ ይሆንብናል። በአዋሳ በኩል ያባረሩትን ነፍጠኛ ከጀርባቸው በያቤሎ በኩል እንዳስገቡ ሊሰማቸው ይችላል። እና..."

ዮሴፍ እንደጨረስኩ በመገመት ይመስለኛል ጣልቃ ገባ...

"እዎ፣ ይሄንንም ማየት ይኖርብናል። የደርግ መሬት ዐዋጅ የተሻለ ነገር ላያመጣ ብዙ ፈተና ውስጥ ነው የጨመረን..."

ወሬውን ሳይጨርስልኝ ሸዋዬ ያባዛችውን ቅጅ በካኪ ፖስታ አድርጋ ለጠችው። ኢሳያስና ዘርዑ እሷን ሲያዩ ለመውጣት ተንቀሳቀሱ። ሁለቱንም ተሰናብቻቸው እዛው ቀረሁ። ዮሴፍና ዘርዑ ግድ አይሰጣቸው ይሆናል። ነገር ግን ድርጅቱ ሳይፈልገው በየት በኩልና በምን ቀዳዳ ሾልከው እንደሚገቡና እንደሚወጡ ማየት የለብኝም። ሸዋዬም እንደዚያው። ከኢሳያስና ከደጀኔ ጋር ሆነው ከምድር ቤታችን ወጡ። ደጀኔ ከቀድሞ ቤቴ ያመጣልኝ ካኪ ፖስታ አሁንም እጄ ላይ ነው። አልጋዬ ላይ ጣል አድርጌው

ልመለስ ዞር ስል ሸዋዬ ወደ እኔ ስትመጣ አየኋት...

"አንተ አላምረው፡ ምን ነካህ? እንደዚህ ግድየለሽ አትመስለኝም ነበር" አጠገቤ ስትደርስ የፈራሁትን ነገር የመቆርቆር ድምጸት በሚሰማበት የእህትነት ቁጣ ጠየቀችኝ።

"ሸዋ፣ ምን አግኝተሽ ነው?" አንድም የግዴለሽነት ምሳሌ የሚሆን ስህተት ነገር የማላስታውስ ለመምሰል ሞከርኩ።

"አንደኛ፣ ፊትህንና ጸጉርህን በመስታዎት እንኳ ተመልከተው። እንድም 'ካምፍላጅ' (መመሳሰያ) አልተጠቀምክም። ጺም የለ፣ ናፍጣና ዘይት የለ፣ ምን የለ። ቁጭ ጫጉላ የገባ ሙሽራ መስለሀል።"

ወደ ቢታኒያ ስሄድ ያደረኩት ጥንቃቄ አለ። ማንነቴን ቀይሬ ነበር። ምኑንም ሳልለውጠው ወደ ሥራ ልወጣ እንደነበር ትዝ ሲለኝ ደነገጥኩ። ሸዋዬ ትክክል ናት። ዮሴፍና ዘርዑ የመጡት እሷና ደጀኔ ስለ እኔ እያወሩ እያሉ ነው። "እንተ ንገረው፣ አንቺ ንገሪው" ተባብለዋል። እነ ዮሴፍ ቤቴ ስላገኙኝ ችግሩ አይታያቸው ይሆናል። ይህ ግን ሊያጽናናኝ የሚገባ ነገር አይደለም። ወደ ብርሻቶ ቆርቆሮ ሄጄ ፊቴን ልቀበባ ስል ሸዋዬ ሁለተኛውን ስህተቴን ልትነግረኝ እጄን ያዘችኝ...

"ሁለተኛ፣ ለብሰኸው ያደርከውን ይሁን ያመሸኸውን ንጹህ ልብስ የት ነው የምታስቀምጠው? እሌጋህ ላይ ዘርግፈኸው ነው የወጣኸው። ሕቡዕ የገባ ሰው ዓይነት አይደለም ጥንቃቄህ።"

በሐፍረት ዝም አልኩ።

"...ወጣ ብለህ ማደሩ ችግር የለውም። ግን በመሀል ምን እንደሚፈጠር አይታወቅም። ቁታህን በፌስታል ምናምን ይዘኸው ውጣ!"

"ወ—ጣ ብ—ለ—ህ ማ——ደ——ር??" የሰማሁትን ማመን አቅቶኝ እንደ እንጨት በቆምኩበት ደርቄ ቀረሁ...

***

ጋራዥ ገብቼ ሥራ መሥራት ጀምሬም የሸዋዬ ቃላት አለቀቁኝም።

"ወጣ ብለህ ማደር!" እንድ የሆነ ጊዜ ያነበብኩት ወይም የሰማሁት አባባል ትዝ አለኝ። "ምሥጢር በትክክል ምሥጢር የሚሆነው የአንተ እስረኛ ሲሆን ነው። ሌላ ሰው ጆሮ ከደረሰ ግን አንተ የምሥጢርህ

አስረኛ ትሆናለህ!" በእኔ ጉዳይ ግን ይህ አይሠራም። እኔም ሆንኩ ቢታኒያ ለማንም አልተናገርንም። ሽዋዬ እንዴት ደረሰችበትና የምሥጢሬ አስረኛ ሆንኩ? ፍጭጭ ያለልኝ መልስ የለም። ጥናቡግም ቢሆን ይሄው ነው! ይላል የአገሬ ሰው። ሴትዩዋ ሽዋዬ... ጉዳዩ ደግሞ ፍቅር ሆነ አንጅ ሌላም ቢሆን ይሄው ነው። ይሄንኑ ሳኝክ ቆይቼ ከሐሳብ የወጣሁት ጎይቶም ለባሲ የቢሮዬን በር ከፍቶ ሲገባ ነው።

"ጋሽ ሰመረ፣ በቀደም'ለት መጥታ እዚህ ስትሳደብ የነበረችው ሴትዩ አሁን ጧት ላይ ፖሊስ ይዛ መጥታ ነበር። ሲያጡህ ጊዜ ተመልሰን እንመጣለን ብለው ሄዱ። ምንድነው ነገሩ፤ የት ነው የምታውቅህ?" ብሎኝ ፈገግ አለ።

ወዲያው ግራ ገባኝ። ሳስበው ነገሩ ከመንገዱ እየወጣ ነው። ለሁለተኛ ጊዜ ስትመጣ ይሄው ጎይቶምም ሌላ ነገር ጠረጠረ። የት እንደምታውቀኝ ጠየቀኝ። እኔም ፈገግ ብዬ ቀና አልኩ...

"የትም አታውቀኝም። ምክንያቷን ግን ምንም አልተናገረችም?" መልሼ ጐይቶምን ጠየኩት።

"እሷ አልተናገረችም። የእኛ ዘበኛ ግን ወሬውን ሰምቶውታል። ላዳ ታክሲ አላት። ልጁ ባለጌ ነገር ነው መሰለኝ የሠራውን ገንዘብ ይጨፍርበታል። በዚህ ስትናደድ ላዳዋ በትንሽ ብልሽት ግቢ ውስጥ ቆመች። ሴትዩዋ አረፍኩ አለች። አሁን 'አንድ ጠይም ሜካኒክ ከልጁ ጋር ተመሳጥሮ እኔ በሌለሁበት ግቢዬ ገብቶ ጠገነለትና አስነስቶ ጠፋ' ነው የምትለው። ቅርብ ያለው ጋራዥ ይሄ ስለሆነ እኛን ጠረጠረች..."

ነገሩ ቀላል ይመስላል። ፖሊስ ሲጨመርበት ግን ቁም ነገር ሆኖ ቁጭ ሊል ይችላል። ወቅቱ ደግሞ አስቸጋሪ ነው። በዚህ ግርግር መሀል ስህተት ሊሠራ ይችላል። እዛው ፖሊስ ጣቢያ ሄጄ ለምን እንደፈለጉኝ መጠየቅ ፈለኩ። ከሴትዩዋ ጋር ድጋሚ መፋጠጥ ሌላ መዘዝ ያስከትል ይሆናል። ሄዶ ቁርጥ ያለ ነገር ይዞ መምጣት ሳይሻል አይቀርም። ለመሄድ ወሰንኩ...

"ፖሊሱ ከየትኛው ፖሊስ ጣቢያ እንደመጣ ነግሮሃል?" ጎይቶምን ጠየኩት።

"እዚሁ አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ ነው። በዚህ በኩል ሄደህ ጎዳም በረንዳን አልፈህ ከትራፊክ መብራቱ ስትደርስ ወደ መርካቶ ከሚወስደው መንገድ መገንጠያ ላይ ነው። ሄደህ የምታነጋግራቸው ከሆነ እኔም ጥሩ ይመስለኛል። ሴትዮዋ ነገር ወፈፌ ስለሆነች እየተመላለሰች ትረብሸናለች።" መከረኝ።

ላንድሮቨሬን እያንጫጫሁ ጎይቶም የሰጠኝን ምልክቶች ተከትዬ ሄድኩ። ብዙም ሳልቸገር አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ ደረስኩ። ከበሩ አጠገብ መኪናዋን አቁሜ ወደ ተረኛ ዘቦች ሄድኩ። የቀድሞ ትምህርት

ቤት ይመስላል ጣቢያው። ጭንቅንቅ ብለው በግራና በቀኝ የተደረደሩ ትንንሽ ክፍሎች። መሀል ላይ ከጣውላ ብቻ የተሠራ ትልቅ ቤት አለ። አካባቢው የሲአል ጓሮ መስሎ ታየኝ። ተረኛ ዘቡን ጉዳዬን ስነግረው መታወቂያዬን ተቀብሎ አስገባኝ። የምርመራ ሹሙን ቢሮ ሲጠቁመኝ ወደዚያው አመራሁ። በክፍሎቹ ረጅም በረንዳ ላይ የሚማግና የቀበቶ መዐት ፍስስ ብሏል፡የእስረኞች ነው። ደረጃ ወጥቼ ወደ ቀኝ ተመለከትኩ። "የምርመራ ሹም" የሚል ጽሑፍ ያለበት ቢሮ ሳይ ወደዚያው ሄድኩና በሩ ላይ ቆሜ ወደ ውስጥ ተመለከትኩ...

'እህ፡ ሰው የለም እንዴ?' ጭር ሲልብኝ ጊዜ ዙሪያውን ዐይኔ እንዲሁ ቆምኩ።ትንሽ ቆይቶ ራቅ ካለ ክፍል ድምጽ ተሰማኝ። የወንዶች ንግግር ነው። ወደዚያው አማተርኩ። አንድ ወፍራምና ረጅም የፖሊስ መኮንን ብቅ አለ። የሸሚዙን እጅጌ ሽቅብ ሰብስቦታል። ሁኔታው በጣም ያስፈራል...

"ሄይ፡ ማነህ! ምን ፈልገህ ነው?" በጩኸት ጠየቀኝ።

"እ...ትፈለጋለህ ተብዬ..." የምናገረው ጠፋብኝ።

"ታች ሄደህ ሰባት ቁጥርን አነጋግር። እዚህ ሥራ ይዘናል፤ ዞር በል!" በቀኝ እጁ ከዚህ ጥፋ ምልክት አሳየኝ።

ደንገጥ ብዬ እግሬን ሳነሳ ከመኮንኑ ጀርባ ሰዎች ዐየሁ። ሁለት ፖሊሶች አንድ ወጣት ግራና ቀኝ ተሸክመው ከአንዱ ክፍል ሲወጡ በጨረፍታ ተመለከትኩ። ወጣቱ በግርፋት መላ አካሉ ድቅቅቅ ብሏል። ልክ አሳት የበላው ጨርቅ። እጆቹና እግሮቹ እንደ ከር ጥቅልል ብለው ደም ይተፋሉ። ዐይኖቹ ተጨፍነዋል። ከእሱ ጀርባ ሌሎች ሁለት ፖሊሶች ሌላ የተገረፈ ወጣት ደግፈው ወጡ። የሩጫ ያህል ተንደርድሬ ደረጃውን ወረድኩ። በሩን አለፍ ብዬ ስቆም ፖሊሱ መጣ። እዛው በሩ ላይ እንደቆመ ወደ ዋናው በር እያየ "ያን የመርካቶ ቦንብ ተኳሽ ላከልኝ!" አለ። የሁለቱን ጽዋ ሊሰጠው እንደሆነ ገባኝ።

እግር ያመጣል እዳ!

'አንዲት እብድ ስለረበሸችኝ እሱቷ ምን ብዬ ነው እዚህ የገሐነብ እርሻ የመጣሁት?!' ወደበሩ ተመለስኩ። መታወቂያዬን እስከምቀበል ዓለም የምትጠፋ ሁሉ መሰለኝ። መኪናዬን አስነስቼ በረርኩ። የሚገርመው ደግሞ ጋራዥ ስደርስ ሴትዮዋ ከጎይቶም ጋር ስታወራ አገኘኋት። ሰላማዊ ወሬ የያዙ ነው የሚመስሉት።

"ይቅርታ፣ የኔ ወንድም። ተሳስቼ ነው እዚህ የመጣሁት!" እጄን ጨበጠችኝ።'ወ---ይ ሕቡዕነት የፈጠረው ጣ----ጣ!' ብዬ በልቤ ይቅርታዋን ተቀብዬ ሸኘኋት።

# 14

ቀናት ከንፍ አውጥተው እየበረሩ ነው። ሚያዚያ ሳይታወቀኝ ከግማሽ በላይ ቅምጥል ብሏል። የቢታኒያ ፍቅር ሲያነሳ ሲጥላት የነበረችው ልቤ እረፈት አላገኘችም። ይህ በረድ ሲልልኝ ደግሞ ሌላ ተተካ። ለመጀመሪያ ጊዜ የምሳተፍበት የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ። ው---ል ሲልብኝ ከረመ። ሥራው ግን ንቅንቅ አላለም። የሚታሰበው ብዙ፣የሚሠራው ትንሽ! እንዲህ ሆኖብኝ ነው በጋው እየከነፈ በመሄድ ላይ ያለው። "ፈጣን ነው ባቡሩ!" አለ የደርግ ኪነት። እውነትነት እንዳለው መካድ አይቻልም።

እዝነልቦናዩ በልጅነቴ ከማውቃቸው ብዙ ባሕታውያን ድምጽ አንዱን አስታወሰኝ። "ንስሐ ግቡ፣ ምጽዐት ደርሷ-----ል!!" የሚያስፈሩኝ ቃላት ነበሩ። አሁን ሕቡዕ የገባና ጊዜ እየቀደመው ጭልጥ የሚልበት ፖለቲከኛ ሆኜ ሳስበው የተቀለደብኝ ይመስለኛል። ቅር የሚለኝ ነገር አለ። ድርጅቴ ከጊዜው ጋር እኩል መራመዱን ማናችንም እርግጠኞች አይደለንም። እንዲያውም ጥርጣሬያችን ተቀድመናል የሚል ነው...

"እረ የትንፋሽ ያለ---ሀ!" ጌታቸው ማሩ ያለው ነው ብሎ ዶክተር ተስፋዬ ነግሮኛል። እውነቱን ነው። ያስብላል።

ምሳዬን ከሽዋዬና ከደጀኔ ጋር በልቼ ጋራዥ ገባሁ። የትንሳኤ በዓል ስለተቃረበ ነው መሰለኝ ደንበኛው ሁሉ እልም ብሏል። በማርክሲስትነቴ የትንሳኤ በዓል የሚሰጠኝ ትርጉም የለም። በአብዮታዊነቴ እንደ ማር የሚጣፍጠኝ ቃል "መስዋእት" መሆን ነው። ትንሳኤ የሌለው መስዋእትነት! በእውነት ዓላማ ያለው ሰው መሆን እንዴት ደስ ይላል?! የሚኖሩለት ዓላማ አለ ማለት ከእንስሳዊ ተፈጥሮ እየወጡ... እየራቁ...እየመጠቁ መሄድ ማለት ነው።

ብርሀንመስቀል ረዳ...ኢትዮጵያዊው ፊደል ካስትሮ!' ብዙ ጊዜ እንደማሞካሸው ዛሬም ልደግመው ፈልጌ የሆነ ነገር መጥቶ ልሳኔን ደረገመው።

ፖለቲካ ብቻ አይደለም እጁ ላይ ያለው ቅዱስ አጀንዳ። ፍቅርም አለ፤ ፍቅር ከቢታኒያ። የሰነበትንበትን ያልታወጀ የጫጉላ ሽርሽር ሁለታችንም መቼም እንረሳው። የደስታችን ምንጭ ተራ ወሲባዊ እርካታ አይመስለኝም። የማይዳሰሰው የመንፈስ ውህደታችን ነው። እርገታችንም በመፈጠር ሂደት ላይ መሆኑን ከመረዳት የሚቀዳ ሆኖ አግኝተነዋል። በፕሌቶ አነጋገር ወደ "ፍጹማዊ መሰናሰል" (ፐርፌክት ሀርመኒ) የሚወስደውን እጅግ ረጅም መንገድ ሀ ብለን ጀምረን እየተጓዝን ነው። ደ---ስ እለኝ! የየግል ምሥጢሮቻችን ግን ችግር ገጠማቸው። የፍቅርን ወረራ መቋቋም አቅቷቸው መንገዳገድ ጀምረዋል...

"ቤቲዬ፤ እውነቱን ንገሪኝ፤ የዩኒቨርስቲ ትምህርት ቀምሰሻል፤ አይደል?" ፈራ ተባ እያልኩ ከሳምንት በፊት ጠየኳት።

"ምን አባክ ትጠይቀኛልህ? ሞርን! አብሮ የሚያድር ፍቅረኛ ከሚያየው ተነስቶ የሚገምተው ነገር መኖሩ ጠፍቶብህ የተደበቀ ምሥጢር ፈልፍዬ ደረስኩበት ልትል ነው? ወሬኛ!" ብላ የቀኝ ጡቴን በጥርሷ እንቅ አድርጋ ስትነክሰኝ ኡኡኡ...ብዬ አስለቀኳት።

ቤቲ በዘመቻው ምክንያት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሁለተኛ ዓመት ትምህርቷን አቋርጣለች። እኔም በኢኮኖሚክስ ዲግሪ መያዜን ልደብቃት አልቻልኩም። እሷም የዋዛ አይደለች። የተማርኩትን ትምህርት ለመገመት ከመቸገሯ በስተቀር ሐቁን ደርሳበታለች። እስካሁን ግልጽልጽ አድርገን ያልተነጋገርንበት ኢሕአፓ ውስጥ ያለንን ትክክለኛ ቦታ ብቻ ነው። እዚህ ነጥብ ላይ ስንደርስ አፋችን ድንገት ይለጎማል። ያም ሆኖ ሕቡዕ የገባን ሰዎች መሆናችንን ሳንነጋገርበት ሁለታችንም ተግባብተንበታል። ነገስ ምን ይፈጠር ይሆን? ለጊዜው የምናውቀው ፍቅርና የፖለቲካ ዓላማ ወደር የሌለው ጣእም የሰጡን መሆኑን ብቻ ነው።

'ፍቅርና ኢሕአፓ ለዘላለም ይኑሩ!' የሰሞኑ መፈክሬ ነው።

አንድ እስካሁን ደፍሬ ልጠይቃት ያልቻልኩት ሌላ ጥያቄም አለ። ከሱሉልታ ጉዟችን መልስ ያለችኝ ነው። "አሞኑ የልጅነት ታሪኬ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ በጸጸትና በቁጭት የተሞላ ነው!" ምን ማለቷ ነው? ሊተረክ የሚችል ታሪክ አይኖራትም ብዬ ገምቼ ልጠይቃት አስባለሁ። ወዲያው ግን ፍርሀት ድንገት ዱብ ብሎ እንደበቴን ጥርቅም ያደርገዋል።'ሆሆው...የቅልብልብ አማት ሲሶ በትር አላት! አፈን በዳቦ፤ ወዳጄ...' አንድ ልቤን አረፍት የሚነሳና ቅናት የሚለቅብኝ ታሪክ እንዳትነግረኝ ነው ፍርሀቴ።

'አፍ ይጹም!' ብዬ በሆዴ ጸጥ አልኩ።

ከስዩም ከበደና ከፍቅሬ ዘርጋው የሚያገናኛት አጀንዳ ያለጥርጥር ፖለቲካ መሆኑን ስለደረስኩበት መጠየቅ አላስፈለገኝም። ከዚህ በተረፈ አያንዳንዱ የፍቅር ሌሊት ሁሌም አዲስና አጓጊ ነው። እሷ በምትወድው የፍልስፍና ወሬ እናጣጥመዋለን። በአንደኛ ዓመት ትምህርቷ ስላለፈችበት ጥሩ ግንዛቤ አላት። የእሷ ፍላጎት ትንሽ ለየት ይላል። ከአንድ የወሲብ ግብግብ በኋላ የትላንት ሌሊት ርእሳችን ይሄው ነበር...

"ሰሙዬ፣ እኔ'ኮ የፈላስፎች ነገር ግርም ድንቅ ይለኛል..." ብላኝ ቀጠለች፣ "እሽ...ፈላስፎች ያንን ያህል መፀት ነገር ተፈላሰፉ። ከዚያ በኋላ የተፈላሰፉትን ነገር የራሳቸው ሕይወት አድርገው ይኖሩታል? ወይስ እኛ እንድንኖርላቸው ነው የሚፈልጉት?" ድምጿ የመደመምና የመጨነቅ ቅላጼውን ቁልጭ አድርጎ አሰማኝ።

ጥያቄዋ ግሩም ድንቅ ርእስ ሆኖ ተሰማኝ። የምሰጣት መልስ ለፍቅራችንና ለፖለቲካ ዓላማችን የሚጠቅም ቢሆን ደስ ይለኛል። ስላልተዘጋጀሁበት እርግጠኛ መሆን ግን አልቻልም። እየነገርኳት ይሄንኑ ማሰብ እንደሚሻል አሰብኩ። አንድ ሁለት ፈላስፎችን ምሳሌ አድርጌ ላጫውታት የአእምሮዬን መዝገብ ቤት ፈታተሽኩት።

"ቤቲዬ፣ ምን መሰለሽ? እያንዳንዱ ፈላስፋ፣ ፈላስፋ መሆን ስለፈለገ ብቻ ይሆናል ማለት አይደለም። እርግጥ መፈላሰፍ የግል ብቃትን ይጠይቃል። ነገር ግን ሄዶ ሄዶ መጨረሻ ላይ ሁሉም ፈላስፋ በኖረበት ጊዜ የነበረው የሕብረተሰብ ቅራኔ ውጤት ነው። ፕሌቶ በማርክስ ዘመን ሊወለድ አይችልም፣ እናም በግልባጩ። ወደ ጥያቄሽ ልመለስና ብዙ ፈላስፎች የፈጠራቸውን ቅራኔ ሲመረምሩ ብዙውን ጊዜ ከሌላው ሕዝብ ርቀው ይሄዳሉ። በዚህ ምክንያት የራሳቸው ደሴት ይፈጥራሉ።"

ቢታኒያ አስቀማኝ ጣልቃ ገባች...

"ሰሙዬ፣ ይሄ በጣም ትክክል ነው። ያልገባኝ ግን አንድ ነገር አለ። ለምሳሌ፣ ዘፋኞችን ውሰድ፣ አትስረቁ፣ አትዋሹ፣ አትካዱ... ምናምን ብለው ይዘፍናሉ። ያ ማለት እነርሱ ሌላውን ሰው የመከሩትን ሁሉ ይኖሩታል ማለት አይደለም። የዘፋኞች እንደዚህ ከሆነ የፈላስፎችስ?" ደረቴ ላይ ያንተራሰቻውን ጭንቅላቷን ስታስተካክል ጸጉሯ ፊቴን እንደ ጭራ ጨርፎት አለፈ።

አሁን ጥያቄዋ በጣም ገባኝ። የመጀመሪያውን የበለጠ ግልጽ አድርጋ ነው የጠየቀችኝ። በእውነተኛ

·ዜ መመለስ ነበረብኝ። ከጥንቶቹ መካከል ለዛሬ ግሪካዊውን ዜኖን መረጥኩ...

አዎ፣ አብዛኞቹ የሚፈላሰፉትን ይኖሩታል።በአንድ ወይም በሌላ ጊዜ ለፍልስፍናቸው ሲሉ በርሀብና ነጉስቁልና የኖሩ አሉ። በጣም ብዙዎቹ ለመሰደድ ተገደዋል። ብዙዎቹ ሀብት፣ ውርስ፣ ቤተሰብ...ጨርሶ የላቸውም። የአብዛኞቹ ሕይወት በገለልተኝነትና በችጋር የተፈተነ ነው። ደስታቸው አካላዊ ከመሆን ይልቅ መንፈሳዊ ስለሆነ ግን እንግልቱ ምንም አይመስላቸውም። ከፈላስፎች ውስጥ በገንዘብ የተደደለለ ፈላስፋ ስም አታገኝም። አንዳንዶቹ ተለምነው ሥልጣን ይይዛሉ። ነገር ግን በማግስቱ ስትሄድ ወይ ለቀዋል ወይ ደግሞ ታስረዋል..."

ቢታኒያ ቅልብልብ ብላ ሌላ ጥያቄ አነሳችልኝ፣ "እሽ፣ ይሄ ከሆነ ፍልስፍና ያልቃል አያልቅም?" ተነስታ ቁጭ አለች።

"ፍልስፍናማ ያልቃል፣ አንጂ ቤቲዬ። ግን መቼ? እንዳትይኝ። በቃ፣ የሕብረተሰብ እድገት ኮሚኒዝም ደረጃ ላይ ሲደርስ ፍልስፍና ያበቃለታል። ምክንያቱም ያኔ ሁሉም ማኅበራዊ ቅራኔዎች ይፈታሉ። የሰው ልጅ ተፈጥሮን የሚገዛትን ሕግ ይደርስበታል። የሁለቱ ችግር መፈታት የፍልስፍናን ፍጻሜ ያረጋግጣል..."

ምን ማለት እንደፈለኩ ገብቷታል። ነገር ግን አልረካችበትም። ኢሕአፓ በመሆኗ ኮሚኒዝምን ልትጠራጠር አልሞከረችም። ዝምታን መርጣ ዓይን አይኔን ስታየኝ እኔ ደግሞ የፍቅር ጨዋታን መረጥኩ። እንደገና አቅፍቅፍ ብለን ወደ ሌላ ዓለም መጋለብ ጀመርን።

ፍቅራችን የቱንም ያህል ብንጠነቀቅ ምሥጢር ሆኖ አልቀረም። ሸዋዬና ደጀኔ በየራሳቸው መንገድ ደርሰውበታል። መካድ ሞኝነት ሆነብኝ። በሳቅና በተዋዛ ወሬ አመንኩላቸው። ሁሉቱም አልተከፉብኝም። ሸዋዬ እንዲያውም የቢታኒያ ዋና ምሥጢረኛ ሆና ቢታኒያ ድንገት በፈለገችኝ ጊዜ ሁሉ መልእክት አድራሽ ሆነችልን። እሷም ሆነች ደጀኔ ምሽት ላይ ሹልከ ብዬ እንደምሄድ ዐውቀውታል። ድርጊቴን አሁን መደበኛ ጉዳይ አድርገውታል። ምግብ ሲቀርብም በሹከሹከታም ቢሆን አልፎ አልፎ ይነሳል...

"አላምር፣ ከአንተና ከቢታኒያ የተወለደ ልጅ ምን እንደሚመስል ለማየት ዕድሜውን ይስጠኝ!" ትለኛለች ሸዋዬ።

ይሄኔ ልቤ በሀሴት ቁንጥንጥ ትላለች። እኔና ቤቲ በፈንጠዝያ ያሳለፍናቸው ሌሊቶች ግን ከሁለት ቀናት በኋላ ችግር ሊገጥማቸው ነው። ወይዘሮ ማስተዋል መምጫቸው ደርሷል። በጣም ስለማከብራቸው

ጭምር መጠንቀቅ ይኖርብኛል። ሲጨንቀኝ ምን እንዳሰበች ቢታኒያን ጠየኳት።

"እርሳው ባክህ...! አትጨነቅ! የፍቅር አምላክ መፍትሄውን ይነግረናል..." ብላኝ ከንፈሬን ጎረሰችው።

\#\#\#

"አሏ----ሁ አከበ--ር! አሏ----ሁ አከበ--ር!"

"አሽሀዱ አላሕ ኢለላህ!! አሽሀዱ አላሕ ኢለላህ!!"

ከወንበሬ ንቅንቅ ሳልል የአዲስ አበባ መስጊዶች የአሱር ሰላት ጥሪ አዛን አሰሙ። ካርል ማርክስ አዲስ አበባ ሰማይ ላይ ከመንበሩ ወርዶ በአላህ ተተካ። ሰዓቴን ሳይ 10፡00 ይላል። ሠራተኞች ለሕቡዕ መደበኛ ስልጠና ስለወጡ ጋራዡ ጭር ብሏል። በቀሪው ሰዓት የምሠራቸውን ተግባራት አስታወስኩ። 'አ-------ው፣ ለ'ካ በጣም አስፈላጊ ቀጠሮ አለኝ!' አልኩ ለራሴ።

ከቻልኩ ምሽት 12፡00 ሰዓት ላይ ጉለሌ ወደ ከፍሉ ታደሰ እሄዳለሁ። ጠበቅ ያለ ውይይት እንደሚኖረን ገምቼ ተዘጋጅቻለሁ። ሌላ አንድ የረሳሁት ሥራም አለ። ከባንክ ብር አውጥቼ ከድርጅቴ ያጎደልኩትን መከፈል አለብኝ። በየቀኑ እሄዳለሁ እያልኩ የባንክ ደብተሬን የያዘውን ካኪ ፖስታ ይገፎ እወጣለሁ። በሆነ ባልሆነ ምክንያት ግን ሳልሄድ እቀራለሁ። ከትላንት ወዲህ እንዲያውም ፖስታዉን እዚሁ ቢሮዬ መሳቢያ ውስጥ አስቀመጥኩት። ባንክ እስከ 10፡30 ይሠራል።

'ልፍጠን! ዛሬ ፈጽሞ መቅረት የለብኝም...'

መሳቢያዬን ከፈትኩና ካኪ ፖስታዉን አንስቼ የባንክ ደብተሬን ለይቼ ለማውጣት መበርበር ጀመርኩ። ወረቀቶችን እየለየሁ ስፈልገው ዐይኔ ባልጠበኩት አንድ ወረቀት ላይ አረፈ። በደንብ የታሸገና ዳጎስ ያለ ነጭ መደበኛ ፖስታ። 'የማን ነው?' ራሴን የምጠይቀው ነገር ጠፋብኝ። ልቤ እንዳች መጥፎ ዜና እየጠረጠረ ፖስታውን አውጥቼ እያገላበጥኩ ዐየሁት። በአንደኛው ገጹ ላይ ብቻ የላኪና የተቀባይ ስም በአጭሩ ተጽፏል። "ብርከታዊት አዳነ- ለሰመረ ማንደፍሮ..."

ለምን እንደሆነ አልገባኝም፣ መንፈሴ እንዲሁ እርብሽብሽ አለብኝ። ደጀኔ እንዴት ሳይነግረኝ እንደቀረ እየተገረምኩ አሽጉን ቀደድኩት። የፍቅር መወድስ የምጠብቅበት ደብዳቤ ሊሆን አይችልም። ብርከቲ ያለምንም ጥርጥር ከአንጀቷ አዝናብኛለች። በቃላት ቢላዋ ከትፍትፍ ልታደርገኝ ደብዳቤውን ለቀድሞ አከራዩቼ እንደሰጠቻቸው ግልጽ ነው። ትንፋሼ ከሆዴ ወጥቶ እያረገረገ የተጣጠፈውን ደብዳቤ

ዝለጥኩትና የመጀመሪያውን ገጽ ማንበብ ጀመርኩ...

"ውድ ፍቅረኛዬ ሰመረ ማንደፍሮ፣

በሕይወት ትኖራለህ ብዬ በማመን ባለህበት ቦታ ሁሉ ሰላሙን እመኝልሀለሁ። አዎ፣ በሙያዬ 'ከፉ ዜና የሚቀድመው የለም' ተብዬ መማሬን አስታውሳለሁ። ድንገት ተለይተኸኝ ስትሰወር ከፉ ነገር ስለገጠመው ነው ብዬ የማላምነው ለዚህ ነው። በየትኛውም ምክንያት ጥለኸኝ ጥፋ። በሕይወት መኖርህ ግን ፍላጎቴ ብቻ ሳይሆን የጧትና የውድቅት ጸሎቴም ጭምር ነው። በዚህ ደብዳቤዬ ለምን ጥለሽኝ እንደጠፋህ ልጠይቅህ አልፈልግም። ቢቃ፣ አንድ ልትከደው የማይቻልህ እውነት አለ። አንተና ፈጣሪ ብቻ በምታውቁት ምክንያት ከእኔ መለየት መርጠሀል። እናም ምንም ፍንጭ ሳትተውልኝ ትተኸኝ ተሰውረሀል። በዚህ ጨርሶ ይሆናል ብዬ በማልጠብቀው ውሳኔህ ለሳምንታት እረፍት ማጣቴን ልደብቅህ አልችልም። ምርጫህ በመሆኑ አንተ ደግሞ ነጻነት እንዳጣጣምክ እምነቴ ነው..."

'ብርክቲዬ፣ በዚህ ትህትና ጀምረሽ በመጨረሻ በሀሲና መጋዝ ልትገዘግዢኝ ነው አይደል?' ፍርሀቴ ጨመረ።

"ሰሙዬ፣ በፍቅር በቆየንባቸው ዓመታት ብዙ ጊዜ 'እወድሀለሁ' ብዬህ ነበር። ይህ ለአንተ በቸርነት ያቀረብኩልህ ስጦታ አይደለም። ወይም አንተ ከሌሎች ወንዶች ሁሉ በተለየ እድለኛ ስለነበርክም አይደለም። 'እወድሀለሁ' የሚለው ቃሌ ከደም ሥሮቼ የሚመነጭ እውነተኛ ስሜት እንደነበረ አሁን ከጎኔ በሌለህበት ጊዜ የበለጠ ግልጽ ሆኖልኛል። ይህም ብቻ አይደለ። የወደድኩህ የተቃራኒ ጾታ ተፈጥሮዊ ፍላጎታችንን ስናረካ በሚሰማኝ ዓይነት ግንፍል ስሜት ውስጥ ሆኜ አልነበረም። እወድህ የነበረው ከምንም በላይ በሰመረነትህ ነው። ለብርክቲ በሰጠሃት ትክክለኛ ቦታና በከፈልከላት ሲጋስ ዋጋ ነው። ልብ በል፣ በከንቱ እያሞካሸሁህ ወይም ተመልሰህ እንድትመጣልኝ እየለመንኩህ አይደለም..."

'ጉድ ፈላ! ብርክቲየ፣ የፈራሁትን ተኩስ ጀመረችው...' ልቤ ድው ድው እያለ ወደ ሚቀጥለው አንቀጽ አለፍኩ።

"ሰሙ፣ እንዳልኩህ ድንገት ብቻዬን ትተኸኝ መጥፋትህ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት ለእኔ መራራ ዱብ እዳ ነበር። እናም ማንም ሰው እንደሚሆነው አዝኛለሁ፣ ተከዝያለሁ፣ አልቅሻለሁ...። የተደፋብኝን ጭለማ እንዴት እንደምገላልጠው ብልጭ ያለልኝ ነገር ግን አልነበረም። ቤተክርስቲያን ሄጄ ምልጃ ለመጠየቅ ሁሉ አስቤ ነበር። በተለይ በተለይ ሳላውቅ ለመሰወር ምክንያትህ የሆንኩበትን ጥፋቴን እንዲገልጥልኝ ተማጽኜም ነበር።ከምንም በላይ የሚቀጥለውንና አንተ የሌለህበትን ጉዞዬን እንዴት

እንደምጀምረው ጭልምልም ብሎብኝ ነበር። ብቻ በእጅ የያዙት ወርቅ... ብዬ መተረት አልፈልግም እንጂ መለያየት መራራ አጋጣሚ ነው።"

'ብርክቲየ፣ በቃ... በጣም ጎድቻታለሁ!'

አፌን ይገኝ ዝም አልኩ። ጭንቅላቴ ወደ ኒኬልነት እንደተለወጠ ሁሉ እንዴ ጮኾ የጩኸቱን ድምጽ መልሶ እንደ ማሚቶ አስተጋባው። የብርክቲ ቃላት እንደ ፈንዲሻ እየፈነዱ እረፍት አሳጡኝ። ወደ ሁለተኛው ገጽ ሳልፍ ስል ሰዓቴን ዐየሁ። ሁለቱም ቀጠሮዬ አልፏል-የባንክ ቤትም የታደሰ ከፍሉም። የብርክቲ ደብዳቤ እንደ ከኒን እየመረረኝም ማንበቤን መቀጠል ነበረብኝ። በመሀሉ ግን የጋራዡ ዘበኛ አዛውንት ድምጽ ቀጥ አድርጎ አቆመኝ። ከሰው ጋር ተነጋገረው የዋናውን በር ትንሿን መዝጊያ ከፈቷት። የመጣውን ሰው ለማየት ብድግ ብዬ ሄጄ የቢሮዬን በር ከፈትኩት፣ "አ----ው፣ ኢሳያስ ነፍ--------ሴ!!"

በአንድ በኩል የጓደኛዬ ናፍቆት በሌላ በኩል ደግሞ ብርክቲ የፈጠረችብኝ ሆደባሻነት ተዳምረው አስጮሁኝ። በዚህ ሰዓት የምታስፈልገኝ ትክክለኛ ሰው ቢታኒያ ነች። ኢሳያስ ቀደማት። ለዓመታት እንደተለያዩ ቤተሰቦች ተቃቅፈን ተሳሳምን። ወዲያው ግን ቅዝቅዝ አለብኝ።

"ኢሱ፣ ሰላም አይደለህም እንዴ? ምን ችግር ገጠመኽ?" ዓይን ዓይኑን እያየሁ ስጠይቀው፣ "አ--ይ፣ ቀላል 'አብስታክል' ነው። ችግር የምትለው ዓይነት አይደለም። ምድር ቤት እረፍ ብለን ብናወራው ይሻላል።" እጅ ለእጅ ተያይዘን ወደ ቢሮዬ ከሄድን በኋላ መብራት አጥፍተን በሥዕለ ክርስቶሱ የምሥጢር በራችን በኩል ወጣን።

ሸዋዬ በሩን ከፍታልን ገብተን ኢሳያስ ከእሷና ከደጀኔ ጋር እየተሳሳመ እያለ አእምሮየ ሌላ ቦታ ስግሯል። ወደ ቢታኒያ ሹልክ ብዬ የምሄድባት የድንጋይ መሰኮት! ቁጥር አንድ ጭንቀቴ። ለድርጅት ሥራና ለደህንነት ብለው ነው መስኮቷን ያስረከቡኝ። እኔ ለፍቅር ተጠቀምኩባት። ወሬው ልክ ከሸዋዬ ጆሮ እንደደረሰ ሁሉ ከእነ ዘርዐ ጆሮም ደርሷል ማለት ነው። በረዶ ዘነበብኝ።

"አ---ሽ ኢሱ፣ ምን አዲስ ነገር አለ?" ሸዋዬ ጠይቃው ራት ለማምጣት ሳህን አነሳች።

"ሾዋ፣ ምንም ደስ የሚል ነገር የለም። የምትሰሚው ነገር ሁሉ ስጋት የሚያመጣ ነው። ኢሕአፓ እዚህ መሀል ከተማ እስረኛ አድርጎ ሊያስፈጅን ነው። ደርግም ምህረት የሌለው የምድር ጭራቅ እየሆነ ነው።"

"እንዴት? ምን አዲስ ነገር ሰማህ?" ቆሞ ያዳምጥ የነበረው ደጀኔ ቁጭ አለ።

"እእእ...አባቴ ዐድዋ ነበር የሚኖረው። ለግል ሥራው ወደ አዲስ አ'ባ እየመጣ እያለ ደርግ መቀሌ ላይ ይዞ አሰረው..."

"ተ------ው አን-------ጇ!!" በተለይ ሽዋዬ በድንጋጤ ከው አለች።

"በዚህ ስብሳጭ" ኢሳያስ ቀጠለ፣ "በዚህ ስብሳጭ ደ'ሞ ሌላ ነገር መጣ። ዛሬ የወጣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ገዛሁ። 'ሰመረ ማንደፍሮና ሽዋዬ ገብረማርያም በመንግሥት ይፈለጋሉ' የሚል ማስታወቂያ አወጣ። የሰመረ ፎቶግራፍ ግን ተሳስቶ የሆኑ ሽማግሌ ሰውዬ ነው የወጡት።" ብሎ ጋዜጣውን ሊያሳያን እጆቹን ወደ ጀርባው ሰደድ አደረገ።

ከሽዋዬና ከደጀኔ ጋር ተያየን፣ "ኤዲያ፣ ደርግን ፈስ በለው። የትም ቢቆፍር እኔንም ሆነ ሰመረን አያገኘንም። የትም አያገኘንም!" ሽዋዬ አጣጣለችው። 'ብቻ ቢታኒያ እንዳትሰማ ተጠንቀቅ!' ልቤ ሹክ አለኝ።

# 15

አዲስ አበባ አሁንም ነውጥ ውስጥ ነች።

የአዲስ አበባ እድገት በሕብረት ዘማቾች ረብሻ...የራዛ ዘመቻ...የሽፍታ ጥቃት ማየል...የትርፍ ቤቶች ውርስ አፈጻጸም የቀሰቀሰዉ ዉዝግብ...የከፍተኛ ወረዳዎች ምርጫ...በኢሕአፓና በመኢሶን መካከል አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የነደደዉ ቁርቋሶ...ደርግ ውስጥ የሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም እየፈረጠሙ መምጣት...የሰሞኑ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ መርሀግብርና የጋራ ግንባር ጥሪያቸው...የአየር ወለድ ጦር ተቃውሞ...እሳት የሆነው የኑሮ ውድነትና የወንጀል መበራከት...የደርጉ የለውጥ ሐዋሪያት በየመሥሪያ ቤቱ የፈጠሩት ችግር...። ጭንብል አጥልቀው በዋና ዋና ጎዳናዎች ላይ የሚዘዋወሩ የደርግ ወታደሮችም ጥሩ ስሜት አልፈጠሩም። ሰው በጥርጣሬ አያያቸው ያልፋል።

'ኢትዮጵያ ከአብዮቱ ማግስት ይሄንን መምሰል ነበረባት?'

የጋራዥ ላንድሮቨሬን እየነዳሁ ወጥቼ ኑረዲን ዳባ ቤትን አለፍኩ። በቀጥታ ወደ ፒያሳ፣ አራዳ ጊዮርጊስ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ እንደምሄድ ነግሬያቸዋለሁ። ኢሳያስ ጓዶች ስለሚመጡ ፈጠን ብዬ እንድመለስ አስጠንቅቆኛል። እነማን እንደሆኑ ግን አላውቅም። ያው የፖሊት ቢሮ አባላት እንደሚሆኑ ገምቻለሁ። የደርግ ክትትልና ወከባ እየጨመረ ሲመጣ አማራጭ ማየት ጀመሩ። የእኛን ምድር ቤት ለደኅንነታቸው የተሻለ ሆኖ ሳያገኙት አልቀረም። ይሄንኑ ትላንት ምሽት ከኢሳያስ ጋር ተነጋግረንበታል። ሁለታችንም ደስተኞች አይደለንም። ምክንያታችን የተለመደው ነው...

"ኢሱ...ለደኅንነታቸው መጠንቀቃቸው ጥሩ ነው። ነገር ግን በከተማ ሕንጻዎች ሥር መሹሎኩለክ

ለማጅራት መቺዎች ነው መተው ያለበት። ከተማ የቡና ቤት ባለቤቶችና ባለ ታክሲዎች ብቻ ነዉ።"
አልኩት ፈርጠም ብዬ።

"ትክክል ነህ፣ ሰመሬ። እንኳንስ አዲስ አባ እንሄድበታለን የሚሉት ሰሜን ሸዋም ለእኔ ከተማ ነው። የተያዘው ቀልድ ነው። ያሁኑ አንጻራዊ መረጋጋት የሚቀጥል መስሏቸዋል!" ሲል ሐሳቤን አጠናከረው።

ችግሩ ሁሉም የፖሊት ቢሮ አባላት ይሄንን በመርህ ይቀበሉታል። የተግባር ጊዜ ግን ወገባቸው ይደቃል። በበኩሌ በዚህ ሰሞን ሌላ ጥርጣሬ ብልጭ ብሎብኛል። ዘርዑ ከህሸን ባለፈው የመጣ ጊዜ ነው። ስለ ወቅቱ ሁኔታ አጭር ነገር ተነጋግረን ነበር።

"እስከመቼ ነው ኢሕአፓ አዲስ አበባ ውስጥ የሚቆየው?" እንደዘበት ጠየኩት።

"አላምረው፣ እንደምታየው ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ግልጽ 'ፓወር ቫኪውም' አለ። አግሩን መሬት ላይ የተከለ መንግሥት የለም። ገጠርም ስትሄድ እንደዚያው ነው። የመሬት ዐዋጁ ባላባቶችን ከጨዋታ ውጭ አድርጓቸዋል። ተጽእኗቸውን ግን ሊያስቀረው አልቻለም። አዲስ ሕዝባዊ አመራር አልተፈጠረም። ይሄ ውዥንብር እስከሚሰከን ድረስ እዚሁ ብንቆይ የምንጠቀም ይመስለኛል። ዘለን ገጠር ከገባን ምናልባት ከንቱ መስዋእትነት ልንከፍል እንችላለን..."

የዘርዑ አባባል ጥቅል ነው። ትርጉሙ ላይ ግን በደንብ ተግባብተናል። "አዲስ አበባን ከለቀቅን በኋላ ምናልባት በመሀሉ ሥልጣን የምንረከብበት ሁኔታ ቢፈጠርስ? እዚሁ መቆየት አለብን..."

'እንዴ! እንዴ! እንዴ! ጉዳዩ የካስትሮን የሞንካዳ...የሌኒንን የጥቅምት...የማኦን ሕዝባዊት ቻይና... አብዮቶች ኢትዮጵያ ውስጥ የመድገም ጥያቄ አይደለም። ይህ መሆኑ ቀርቶ ሥልጣን በጓዳ በር የማግኘት ጉዳይ ሆኖት አረፈው!?'

አውቶቡስ መነኸሪያ ስደርስ ፍጥነቴን ጨመርኩ። የትንሳኤ በዓል ዋዜማ የበግና የዶሮውን ገበያ አጡፎታል። በንጉሡ ዘመን ቀኑን ሙሉ በገና ይደረደርበት የነበረው አርባ ጾም ከቀረ ሁለተኛ ዓመቱን መያዙ ነው። የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጳጳስ እስር ቤት ወርደዋል። ስለዚህ ያለ ጳጳሱ ቡራኬ የሚከበር በዓል መሆኑ ነው። በዓሉ ከላባደሩ ዓለምአቀፍ በዓል በአንድ ቀን ልዩነት የሚከበር ነው። ይህ መሆኑ በደራው የበግ ገበያ መሀል የማይክሮፎን ድምጽ ጎልቶ እንዲሰማ አድርጎታል።

'ሰይጣናዊው የደርግ/መኢሶን ጥምረት!' አልኩ የድምጽ ማጉያውን ስሰማ።

አለምርዬ እንዴት አቅጣጫውን ስቶ ቅልብስ እንዳለብኝ አላውቅም። ብርከቲ በሐሳብ አከናፍ ላይ እየበረረች መጥታ ድንገት ስንቅር አለችብኝ። ሁለት ፋሲካዎችን አብረን አከብረናል። አሁን አጠገቧ የለሁም። እንደ ጥሩ እድል ሆኖ እኔ አጠገብ ግን ቢታኒያ አለች። ስሜቴ ድብልቅልቅ አለብኝ። በዓሉ ወይዘሮ ማስተዋልን ስለሚያመጣብኝ ደስ አላለኝም። ቢታኒያ የዋዜማው ሌሊት ቤታቸው አረፍት እንደማይኖረው ነግራኛለች። ዶሮውና በጉ ይታረዳል። ስጋው ታጥቦ ሲበለትና ሲበሰል ሌሊቱ ይነጋል...

'ከቤቲዬ አቅፍ ወጥቼ ላድር?!' ጭንቀት ገና ከወዲሁ ወዘወዘኝ።

አራዳ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በተገልጋይ ጢቅ ብሎ ሞልቶ ጠበቀኝ። ወረፋ መያዝ ፈልጌ ነበር። ነገር ግን ኢሳያስ እንደነገረኝ ቶሎ መመለስ አለብኝ። ምናልባት ብዙ ከመቀመጥ የሚያውቀኝ ሰውም ሊያጋጥመኝ ይችላል። ተመልሼ ወደ መሳለሚያ ነዳሁ። ግራ ቀኝ ሳላይ በቻልኩት ፍጥነት ነዳሁ። ኮረዲን ዳቦ ቤት ስደርስ ደጀኔን መንገድ ዳር ቆሞ አየሁት። ውልቅልቅ ያለ የጋራዥ ሞተር ብስከሌት አጠገቡ ቆሟል። ጓዶች ቤታችን ስለመጡ ጥበቃ አያደረገ መሆኑ ገባኝ። ጋራዥ እንደደረስኩ ቢሮ አልቆየሁም። በአንድ እግር ቀጥ ብዬ በምሥጢራዊዋ መተላለፊያ በኩል ወደ ምድር ቤቴ ሄድኩ።

"አላምረው፣ ከመቼው ብን ብለህ ጠፋኸብኝ?" ሸዋዬ በሩን ስትከፍትልኝ በመገረም አፏን ይዛ በለሆሳስ ጠየቀችኝ።

"የመጡ ጓዶች አሉ፣ ሸዋ?" ደንገጥ ብዬ ጠየኳት፣ "ባንክ ቤት ሄጄ መምጣቴ ነው። ለዚያውም ምንም ሳልሠራ..."

"እዎ፣ መጥተዋል። አንተ መኝታ ክፍል ነው ያሉት። እኔ እንኳን የፈለኩህ ሚስትህ ላግኘው ብላ ልካብኝ ነው። አትዬ ማስተዋልን ከኮተቤ እንድታመጣቸው ፈልጋ ነበር። ስትዘገይ ጊዜ የኮንትራት ታክሲ መያዛቸውን ደውለው ነገሯት።"

ሸዋዬ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቢታኒያን "ሚስትህ' ብላ መጥራት ለምዶባታል። እኔም አልከፋኝም። እንዲያውም የሆነ ነገር ኩራት ይሰማኛል። ከሌሎች ወንዶች ሁሉ በተለየ የታደልኩ ይመስለኛል።

"በቃ፣ ዋናው መምጣታቸው ነው።" ሸዋዬን አልፌያት ገባሁ።

በደጀኔ ቤት በኩል አቋርጩ ደረጃውን ስወርድ የመጡት እንግዶች ታዩኝ። ከተለመደው ቁጥር ከፍ ብለው ነው የመጡት። ሦስቱ በአንዱ ታይፕ መጻፊያ ፊት ለፊት ወንበሮች ላይ ኩብብ ብለው

ተቀምጠዋል። ረድሙ የዘርዑ ከሕሽን አካል ጎልቶ ዐይኔ ውስጥ ገባ። ሌሎቹን የሆነ ቦታ ምናልባት ከጌታቸው ማሩ ወይም ከተስፋዬ ደበሳይ ጋር ሆኜ ዐይቻቸዋለሁ መሰለኝ። ከእነርሱ ትንሽ አለፍ ብሎ ሌሎች ሁለት ሰዎች ዐየሁ። አልጋዬ አጠገብ ትንንሽ ዱካዎች ላይ ፊት ለፊት እየተያዩ ቁጭ ብለዋል። ጀርባውን ሰጥቶኝ የተቀመጠው ኢሳያስ ነው። መምጣቴን በሚቅጨለጨለው የጋራዥ ኮተቴ ሲያውቁ ዞር ዞር ብለው አዩኝ።

'አዎ፣ ትክክል ነኝ። ከዘርዑ ጋር ያሉትን ሰዎች ዐውቃቸዋለሁ። ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ምሽት ላይ ነው የተዋወኳቸው።' ጓድ ብርሀነ ሀ እና ብርሀነ ለ በሚል ስም ነው እንዲያውም የተዋወኳቸው...' በቅድሚያ እነርሱን ጨበጥኩ።

እንደምንተዋወቅ ዘርዑን ነገሩት። በትክክለኛው ማንነታቸው የደርግ አባላት የሆኑት ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤልና ሻምበል ወልደመድህን አብርሃ ናቸው። በደርግ ውስጥ በቅርቡ የተቋቋመው የኢሕአፓ ኮሚቴ አባላት ናቸው። ድምጻቸውን ቀንሰው በትግርኛ ነበር የሚያወሩት። ሰላምታውን ስንጨርስ ወደእነ ኢሳያስ ዞር ብዬ ሄድኩ። አብሮት ያለውን ሰው አላውቀውም። በእንግዳ አተያይ ትኩር ተባብለን ተያየን። አጠር ብሎ ቀጠን ያለ ሲሆን ሲጋራ አከታትሎ ያጤሳል። ሄጄ ስጨብጠው እና ልክ የኮድ ስሙን ሲነግረኝ ትክክለኛ ማንነቱን ዐወኩት። የፖሊት ቢሮ አባሉ ክፍሉ ታደሰ (የአሜሪካው) ነው።

'እ...ው፣ ከአንጋፋ የድርጅታችን መሥራች፣ ክፍሉ ታደሰ የአሜሪካው!'በሆዴ አሞገስኩት።

ሌላኛው ሞክሺው ክፍሉ ታደሰ የመኢሰማው ነው። ይሄኛውየሠራተኛ መሪው ክፍሉ ወደ ማእከላዊ ኮሚቴ አባልነት የመጣበት አኳኋን የተለየ ነበር። የአምናው የኢሕአፓ ምሥረታ ዐዋጅ "ድርጅታችን የላብአደሩ መሪ ፓርቲ ነው" ሲል ፕሮግራሙን ይፋ አድርጓል። ይሄንኑ በተግባር ለማሳየት የማእከላዊ ኮሚቴው ጥንቅር ላባደሮችን እንዲጨምር ተፈለገ። በዚህ ውሳኔ ክፍሉ እንዲሳብ ተደረገ። ሰውየው ክፍሉ ይሁን አበበ ተቃውሞ የለኝም። ነገር ግን ውሳኔው የቆመበት አስተሳሰብ እጅግ ከልብ ያስገረመኝ የልጆች ዓይነት ጨዋታ ነበር...

"ኢሱ፣ ሰዎቹ የሚሠሩትን እያየህ ነው? እንኳንስ በእኛ አገር ይቅርና በራሺያና በቻይናም ቢሆን ሀቁ አንድ ነው። እውነተኛው ላብአድር ገና ለፓርቲ መሪነት አልበቃም። ምክንያቱ ግልጽ ነው። 'ላባደራዊ እምባገነነትን' መፍጠር የሚያስችል ራሱን የቻለ ላባደራዊ መደብ ገና አልተፈጠረም። የተማረው የኅብረተሰብ ክፍል ነው በላባደሩ ስም መሪነቱን የሚይዘው። ነገር ግን ይሄ አደራ ብቻ ነው። እንጂ የግድ ላብአደር መሆን አያስፈልግም..." አልኩት።

"ስመሬ፡ ምን ይሄ ብቻ? ኢሕአፓ የብሔር ጥያቄን እንደምታየው ጨከኖ አልያዘውም። እንደገባኝ 'የብሔር ጥያቄ በኢሕአፓ አመራር ውስጥ የብሔር ሚዛንና ጥንቅር ሲጠበቅ ያኔ ይፈታል' ብለው እያሙኑ መሰለኝ። እና ድርጅታችን ይሄንን ያሚላል ለማለት ሲባል ብቻ አሮምኛ ተናጋሪውን አበበ ዋቅጅራን ወደ ፖሊት ቢሮ አባልነት አምጥተውታል። ውስብስቡን ጥያቄ በዚህ መንገድ ፈታነው አሉ። በጣም ነው የተገረምኩት..." ኢሳያስ ጭንቅላቱን በቅሬታ አወዛወዘ።

መላ ትኩረቴን ወደ ከፍሉ ታደሰ መለስኩ። አብሬያቸው ልቀመጥ ወንበር ለማምጣት ሄጄ ስል ኢሳያስ ተነሳ። የሆነ መረጃ ፋይል ውስጥ ለመፈለግ ስለሚሄድ ወንበሩን ለቀቀልኝ። ልክ እንደተቀመጥኩ ከፍሉ ጥያቄ አንስቶልኝ ወሬ ጀመርን...

"ይቅርታ አላምረው፣ መስፍን ሐብቱ የሚባል ሰሜን አሜሪካ ይማር የነበረ ልጅ ታውቃለህ?"

"መስፍን ሐብቱ? መስፍን ሐብቱ? ስሙ ለጆሮዬ አዲስ አይደለም። ብርሃነመስቀል ወ--ይ--ም ዮሴፍ አዳነ፡ እርግጠኛ አይደለሁም፣ በሆነ ምክንያት ያነሱልኝ ይመስለኛል..." አልኩት ለማስታወስ ምክሬ እያቃተኝ።

"ዌ--ል፤ መስፍን ሐብቱ የደቡብ ትግራይ አካባቢ ልጅ ነው። አንተ እዛ አልመሰልከኝም..." ሲያጤሰው የቆየውን ሲጋራ ቁራጩ መሬት ላይ ጥሎ ረገጠው።

"አ--ይ፡ አይደለሁም፤ አማርኛ ተናጋሪ ነኝ።" መለስኩለት።

"ግን የኛ የሐበሾች መልክ ያስገርመኛል። ያንተና የመስፍን ደግሞ ይብሳል። ገና ልክ እንዳየሁህ የሆነ መንታ ወንድሙ ነበር የመሰለከኝ። የሚገርምህ ዓለም ሐብቱ የሚባል የእናት የአባት ልጅ አለ። በመልክ ይመሳሰላሉ። ዓለም ያንተን ያህል ግን አይጠጋውም..." ፈገግ አለ።

"መስፍን ማለት ግን የሆነ የተለየ ታሪክ አለው ልበል?" ሁሌ እንደሚሆነው ስለ ትልልቆቹ የማወቅ ፍላጎቴ ብድግ ብሎብኝ ጠየኩት።

"አ---ዎ..." ብሎ ከፍሉ ትረካውን ጀመረልኝ ወደ መሬት አቀርቅሮ፣ "...በሰሜን አሜሪካ የተማሪዎች ማኀበር ፕረዚደንት አድርገን መርጠነው ይሠራ ነበር። በጣም ንቁ ተራማጅ ልጅ ነበር። ያኔ በተለይ በዚህ መዘዘኛ የኤርትራ ጥያቄ ምክንያት በተማሪው መሀል የአቋም መከፋፈል የተፈጠረበት ጊዜ ነው። በጣም 'ሲሪየስ' መናቆር ተከተለ። በመሀሉ እነ ብርሀነመስቀል አልጀሪያ ሆነው ፓርቲ ለማቋቋም

እየመከሩ ነው። ከአሜሪካ እኔንና መሰፍንን ኮንታክት አድርገውናል። የኔ ግንኙነት በግሌ ስለሆነ ብዙም ችግር አልነበረውም። መሰፍን ግን የተለያየ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ያቋቋሙትን ማኅበር ነበር የሚመራው። የሆኑ በርባሪ ተማሪዎች በምሥጢር የጀመረውን ግንኙነት ከነመረጃው ደረሱበት። 'መሰፍን በከሀደት እንደ እቃ ገበያ አውጥቶ እየቸበቸበን ነው' ብለው አወሩበት..."

"ግና ምንም ተሳትፎ ሳይኖረው፣ ደግሞስ መብቱ አይደል፣ እንዴ?" ገርሞኝ ጠየኩት።

"ገና ምኑም ሳይጀመር ነው። ከዚያ ለመጀመሪያው የኢሕአድ ጉባኤ ዝግጅት ወደ አውሮፓ ሄድን። መሰፍን በጣም ተበሳጭቷል፣ ሆድ ብሶታል፣ አዝኗል...። ወደ አሜሪካ የመመለስ ፍላጎትም አልነበረውም። በዚህ መጥፎ ስሜት ውስጥ እንዳለ ከብርሃነመስቀል ጋር ተገናኙ። ያው ብርሃነን ታውቀዋለህ። ማኅበራዊ ጉዳይ ለእሱ ምኑም አይደለም። መሰፍን ስለሚያከብረው የሆነ ነገር ያማክረኛል ብሎ አስቧል። የደረሰበትን መገለልና ብስጭት ዘርዝሮ ነገረው። ብርሃነመስቀል ግን ከምንም ሳይቆጥረው ዝም ብሎት የጉባኤ ዝግጅት ሥራውን ይሠራል። መሰፍን የበለጠ ተበሳጨ፣ ከፋውም። ወደ አሜሪካ እንደተመለሰ ከድሮው የበለጠ ስም ማጥፋት ዘመቻ እንደሚደረግበት ዐውቋል። ጉባኤውን ሳይጨርስ ሄደ። ከማንም ጋር መገናኘት አልፈለገም። ቤቱን ቆልፎ ብቻውን ቁጭ አለ። ጓደኞቹ የት ገባ ብለው ይፈልጉታል..."

"እ——ሽ?" አልኩት የታሪኩን መጨረሻ ለመስማት ጉጉት ቅብጥብጥ እያደረገኝ።

"ከዚያማ ቤቱን ሰብረው ሲገቡ ራሱን አጥፍቶ ተገኘ። መጀመሪያ ሰው የገደለው መስሎን ነበር። ማስታዎሻ ምናምን አልተወም። በኋላ ግን ከአንድ ቀን ቀደም ብሎ ሲመለከተው የነበረውን ፊልም አልዘጋውም ነበርና ሲያዩት 'የሱፍ አበባ' (ሰን ፍላወር) የሚል ርእስ ያለው ፊልም ሆኖ ተገኘ። የሱፍ አበባ' ማለት፣ ታውቀው ይሆናል። አንድ ቫን ጎህ የሚባል የዳች ታዋቂ ሠዓሊ ለአንድ የሥዕል ሥራው የሰጠው ስም ነው። በጣም ዝና ያተረፈ ሥዕል ነው። ሠዓሊው ግን በርሀብና በችጋር ሲሰቃይ የኖረ ነው። በመጨረሻ የሕይወትን ፈተና መቋቋም አቅቶት ቫን ጎህ ራሱን በራሱ ገደለ። መሰፍን ያየው ፊልም እንግዲህ የዚህ ሠዓሊ የሕይወት ታሪክ መሆኑ ነው..."

'ታሪኩ አሳዘነኝ። ...የሱፍ አበባ?! የሱፍ አበባ?! የሱፍ አበባ?! ሠዓሊው ሞልቶ ከተረፈው ነገር ሁሉ በተለይ የሱፍ አበባን ለምን መረጠ?' አሰብ አድርጌ ከፍሉን ልጠይቀው ስል ኢሳያስ ትልቅ ጥራዝ ይዞ መጣ። "አገኘሁት" ብሎን ተቀላቀለን። 'የሱ——ፍ አበ——ባ?!' አልኩ ለራሴ ሳይታወቀኝ በውስጤ ከአንዳች ዓይነት አደጋ ጋር እያያዝኳት። 'የሱፍ አበባ?!'

ከፍሉ ጥራዙን ከኢሳያስ ተቀብሎ ገጾችን እየገለጠ በንባብ ስምጥ አለ። ባገኘሁት አጋጣሚ ጆሮዬን ወደ እነ ዘርዑና ሻምበል ሞገስ ውይይት ጣል አደረኩ። ውይይታቸው በቀላሉ የሚቋጭ አይመስልም።

አሁንም በትግርኛ ስለሚነጋገሩ የገባኝ ነገር የለም። ሦስቱም ግን በተናገሩ ቁጥር "ሻለቃ መንግሥቱ" የሚለውን ስም ሲደጋግሙት ተሰማኝ...

'ይሄ ጣጠኛ ሻለቃ የሁሉም ራስ ምታት ሆነ ማለት ነው?'

ከእነ ዘርዑ ትኩረቴ ተመልሼ ቀና ስል ከኢሳያስ ጋር ዐይን ለዓይን ተገጣጠምን። ወደ ላይ ቤት አብረን እንድንወጣ በዐይኖቹ ጠቀስ አደረገኝ። ራቅ ማለታችንን የፈለገው ሥራ ስላልነበረን የራሳችንን ጉዳይ እንድናወራ ፈልጎ እንደሆነ ገመትኩ። ወደ ደረጃው አመራን። ሽዋዬ ማብሰያ ከፍሏ ዉስጥ ነች። ከእሱ መኖሪያ ቤት እንደገባን ብቻችንን መሆናችንን አረጋግጠናል። ኢሳያስ ድምጹን ዝቅ አድርጎ ወሬ ጀመረልኝ...

"ስመሬ፣ እነዚህ ደርጎች ዘርዑን ምን እያሉት እንደሆነ ታውቃለህ?" ወደ ጆሮዬ በጣም ተጠጋ።

"ኧረ አንድም ቃል አልሰማሁም። ምን እያሉት ነው?" የመረጃ ዘንጎቼ ከመቅጽበት ቀጥ አሉ።

"ደርግ ውስጥ የአመራር ቀውስ እየተፈጠረ ነው ብለው ጀመሩለት። 'ቀውሱ በመኢሶንና በመንግሥቱ ኃይለማርያም ጥምረት ምክንያት የተፈጠረ ነው። አብዛኛዎቹ የደርግ አባላት ደርግ የሆነ ዓይነት ርእዮተ-ዓለም እንዲኖረው አይፈልጉም። ይሄን የጠሉትን ነገር መኢሶን ይዞባቸው ስለመጣ ቅሬታ አድሮባቸዋል። ይህ መሆኑ ደግሞ ደርጉን የዳር ተመልካች አድርጎታል። ለዚህ ቀውስ ተጠያቂ የሚያደርጉትም ሻለቃ መንግሥቱን ነው። መንግሥቱ ደርግን ማግለሉ በአንድ በኩል ለሥልጣን ግብገቡ ጥሩ ነገር ነው። በሌላ በኩል የመኢሶንን ድጋፍ ከደርግ መንግሥትነት ጋር ማጣጣም ከቻለ ወላ ደርግ ራሱ፣ ኢሕአፓ፣ አብዮቱም ጭምር አደጋ ላይ መውደቃችን ነው...' አሉና..."

"እና ኢሕአፓ ምን ያድርግ አሉ?" መጨረሻውን የመስማት ጉጉት ጥድፍ አደረገኝ።

"ሻለቃ መንግሥቱ እንደምንም ተብሎ መገደል አለበት ነው የሚሉት። እሱ ከተወገደ ደርግ ያለምንም ጥርጥር ኢሕአፓን የግንባር ጥሪ ያቀርብለትና መኢሶንን ያሰናብታል። ስለዚህ የኢሕአፓ አመራር ሰውየውን ለማስወገድ ትኩረት ይስጥ። እንዲህ አድርጎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥያቄ መመለስ አለበት።' ሲሉት ሰማሁ..." ብሎኝ ኢሳያስ ሲጋራውን ማ--ግ አደረገ።

"'ኮልድ ብለድ ኪሊን-------ግ'! እንዴት ይሆናል? መፍትሄው አድፍጦ ወይም አድብቶ ግለሰብን መግደል ነው የምትለኝ?" ጆሮዬን ማመን አቅቶኝ በደመነፍስ ጠየኩት።ኢሳያስ ጭንቅላቱን በአዎንታ ነቀነቀልኝ። በድንጋጤ ዝምብለን ስንተያይ ከፍሉ ታደሰ በደጀኔ መኖሪያ ከፍል በኩል ብቅ አለ...

# 16

ወደ ኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ለመሄድ እየተጣደፍኩ ነው። እስሬ የእጅ ሰዓቴን ዐያለሁ። ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት ላይ ለሚጀመረው ስብሰባ ከጧት ጀምሬ ሳወጣ ሳወርድ ነው ቀኑ ያለፈው። የኮሚቴው ድምጽ ያለው አባል አይደለሁም። የተዘጋጁ ሐሳቦችን ግን ማቅረብ እችላለሁ። ወገቤን ጠበቅ አድርጌ በብርሃነመስቀል "የጋራ ግንባር" እና በዘርዑ ከሕሸን "የከተማ ትጥቅ ትግል" ሙግቶች ላይ ሰይፌን መዝገርባቸዋለሁ። ሰዓቱ መድረሱን በጉጉት የምጠብቀውም ለዚሁ ነው። ኢሳያስ ትላንት ከእነ ከፍሉ ጋር እንደወጣ አልተመለሰም። አዋሳ ለአንድ ሁለት ቀናት እንደሚሄድ ነግሮኛል። በሆነ ምክንያት ካልሄደ ግን ስብሰባው ላይ እንገናኛለን። የምንለያይባቸው ቀናት እየጨመሩ በመምጣታቸው ቅር ብሎኛል።

'ምን ማድረግ ይቻላል? ለድርጅቴ ሲባል ብርክቲንስ እሰናብቼ የለ?' በረጅሙ ተንፍሼ የቢሮዬን መብራት አበራሁ።

ብቻዬን ነኝ። የጋራዡ ሠራተኞች ገና በጊዜ ጥርግርግ ብለው ወጥተዋል። የሰምኑ ወታደራዊ ሥልጠናቸው የተለየና ጥብቅ እንደሆነ ከሁኔታው ተረድቻለሁ። በተለይ የደጀኔና የጎይቶም ለባሲ የፊት ገጾቻቸው በልምምድ ብዛት ልውጥውጥ ብለዋል። ደስ ባይለኝም ቻል አድርጌው የዕለቱን ገቢ መቁጠር ጀመርኩ። በመሀል አንዴ ኢሳያስ፣ ወዲያው ደግሞ ብርክቲና ቢታኒያ ዐይነህሊናዬ ላይ እየተፈራረቁብኝ ቆጥሬ ጨረስኩ። በቅድሚያ ወደ ድሮዋ አከራዬ አሁን ደግሞ ወደ እማቴ ቤት እሄዳለሁ።

'ፍቅር ለዘላለም ይኑር! ቢታኒያ ፍቅር ናት፣ ፍቅርም ቢታኒያ!' በሆዴ መፈክሩን ደግሜ ተነሳሁ።

በጠባቧ መንገድ ሄጄ ከቀዩ በር ደረስኩ። አሁን በቀዳዳ በኩል ማጮለቅ የለብኝም። ረጅም ዕድሜ

ለቢታኒያ ማገር ወለላ ፍቅር። ቤተሰብ ስለሆንኩ የበሩ ቁልፍ እጄ ላይ አለ። በሩን ከመከፈቴ በፊት ግን ጆሮዬን ወደ ግቢው ውስጥ ደቀንኩ። ቢታኒያ የኢሕአፓን መዝሙሮች ሕጻናትን ሰብስባ እያለማመደች ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከበግና ከዳግላስ ጩኸት በስተቀር የሚሰማኝ ነገር የለም። ከፍቻው ስገባ ደግሞ የሒሩት በቀለ ተወዳጅ የፍቅር ዜማ ከሸከላ ይንቆረቆራል።

ዓይኖችህን ሳ—ይ ከብለል ከብለል ሲሉ፣

በደስታ ይረካል ሰውነቴ ሁሉ!

ከእሷ መኝታ ክፍል የሚመጣ እንደሆነ አልተጠራጠርኩም። ለእኔ የተዘፈነልኝ እስኪመስለኝ ድረስ ልቤን ስር—ቅ አደረገው። ወደ መኖሪያ ክፍሏ ሰረቅ አድርጌ ተመለከትኩ። መጋረጃው ግጥም ብሎ ስለተዘረጋ ምንም ነገር ማየት አልቻልኩም። ግቢው አውዳመት አውዳመት ይሸታል። ቀንዶቹ ሐረግ መስለው የተጠማዘዙ ቀይ የበግ ሙክት ኩሽናው በር ላይ ታስሯል። ሁለት ሴት የቀን ሠራተኞች ኩሽና ውስጥ ሽር ገድ ይላሉ። እግሮቻቸው የታሠሩ ነጫጭ አውራ ዶሮዎች ጥሬ ይለቅማሉ...

'ማስቴ፣ መምጣትዎ ጥሩ ነበር፤ ከቤቲዬ ጋር ባይነጣጥሉን ኖሮ!' አልኩ ለራሴ፤ ወዲያው ግን ፍቅር በገዛ ቤታቸውና ልጃቸው ምን ያህል ራስ ወዳድ እንዳደረገኝ ሳስብ በራሲው ሐሳብ ተገረምኩ።

ወደ ዋናው ቤት ገብቼ ከወይዘሮ ማስተዋልና ከሚካኤለ ጋር ተገናኘሁ። ልክ ለዓመታት እንደተለያየ ዘመድ ሰፍ ብለው ተቀበሉኝ። እንቅ አድርገው ይዘው ጉንጮቼን አገላብጠው ሳሙኝና እየመሩ ወደ ውስጥ ይዘውኝ ገቡ። በሆነ ነገራቸው ከእሳቸው ጋር የሚመሳሰሉ ሴት እንግዳም ሳሎን ውስጥ ነበሩ። ሁለቱም ነጭ ትውፊታዊ ቀሚሶች ለብሰዋል። መመገቢያ ከፍል ውስጥ ገብተን አረፍ እንዳልን የዕለቱን ገቢ ድርሻቸውን አስረከብኳቸው። ማስተዋል እንደዚህ ቀን ደስ ብሏቸው ዐይቻቸው አላውቅም። ለበዓሉ የተዘጋጀውን ጠላ በትልቅ ጽዋ ይዘው መጡና ካልቀመስክ ብለው ያዙኝ። መድኃኒት እየወሰድኩ መሆኔን ዋሽቼ ስነግራቸው ነው በጄ ያሉት።

'ቤቲዬ የለችም ማለት ነው?' መንፈሴ ድፍርስርስ አለ።

ልወጣ ቤቱ በር ስደርስ ድምጼ እንዲሰማት ብዬ እንደገና "ደህና እደሩ!" አልኳቸው። ዐይኖቼን ወደ መኖሪያ ከፍሏ መስኮት ወርወር አደረኩ። ጭንቀቴና ፐርጣሬዬ የቢታኒያን ቅንነትና ፍቅር የሚመጥን አልነበረም። የሙዳዩ ከዳን ተነስቶ ጠይሟ ዕንቁ ወጥታለች። ቤቲ የመስኮቱን መጋረጃ በከፊል ገለጥ አድርጋ በስስት እየተመለከተችኝ ነው። በምን የሥነ ውበት ሕግ እንደምትገዛ አላውቅም። ሁሌም በመስኮት ብቃ ብላ ሳያት አረበሻለሁ። የቅናት ዘር ሊያስደነክረኝ እስከሚፈታተነኝ ድረስ የውብ ውብ

ትሆ"ንብኛለች። ቅንድቦቿን ቋንቋ አናግራ በምልከት ቀጭን ትእዛዝ ሰጠችኝ...

"ና ግባ ወደ እኔ ቤት...እፈልግሀለሁ!"

ወይዘሮ ማስተዋል እያሉ ወደ እሷ ከፍል መግባት እኔን ያስፈራኝን ያህል እሷ እንዴት እንደደፈረች አስገረመኝ። ልክ ከፍችኝ እንደገባ ሌባ እየተቅበዘበዝኩ ሾልከ ብዬ ገባሁ። መሀል ወለሉ ላይ ቆማ ጠበቀችኝ። የአረፍት ልብስ ለብሳ የተበጠረ ጸጉሯን ጀርባዋ ላይ ለቃዋለች። ምን እንደማደርግ ጨንቆኝ ትኩር ብዬ ዐየኋት። ፋታ ሳትሰጠኝ ጥምጥም ብላብኝ ወደ ሁለተኛው ከፍሏ ወሰደችኝ። ሶፋ ወንበሯ ላይ ተያይዘን ቁጭ አልን። ስታነበው የነበረውን መጽሐፍ እንደተከፈተ በአፉ ደፍታዋለች። ፈጠን ብዬ ርእሱን እየሁት። የእንግሊዛዊው ደራሲ የቻርልስ ዲከንስ "የሁለት ከተሞች ወግ" ሂሳዊ ልቦለድ ነው።

"አንተ ሞርን፣" አለችኝ ሰሞኑን በጀመረችው የቀልድ ስድብ፣ "አንተ ሞርን፣ ማሚ ስለመጣች ሰላም ሳትለኝ ልትወጣ ነበር?" ጉንጬን በቁንጥጫ ይዛ ወደ ራሷ ጎተት አደረገችኝ።

"ቤቲዬ፣ አሁንምኮ ልክ አይደለንም። እሳቸው ወይ ሚካኤለ ድንገት ቢመጡስ?" በጭንቀት በር በሩን እያየሁ ጠየኳት።

"ሰሙዬ፣ ማስቴ'ኮ እንደዚያ ዓይነት አስፈሪና አስጨናቂ እናት አይደለችም። እኔ አከብሮቴን ላሳያት ፈልጌ ነው እንጂ በምርጫዬ ጣልቃ የምትገባ ጨቅጫቃ እናት አትምሰልህ። እንዲያውም ብቸኝነቴን ስለምትጠላው ትጨነቃለች። የወንድ ጓደኛ መያዜን ጋሻ እንደማግኜት ሁሉ ልትቆጥረው ትችላለች..."

"እየቀለድሽ ነው ወይስ የምርሽን?"

"የምሬን ነው። ምንም መሳቀቅ የለብህም። በማስቴ መምጣት የምንለውጠው ነገር ቢኖር አንድ ነገር ብቻ ነው። አንተ የምትመጣበትን ጊዜ በአንድ ወይም በሁለት ሰዓት ማራዘም። ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ወደ አምስት ሰዓት። ለዛሬ አመሻሽ ላይ ማስቴም ሚካኤለም ቤተከርስቲያን ሄደው ይመለሳሉ። እኔ ሳሎን እሄድና እየተጫወትን እናመሻለን። ከአምስት ሰዓት በኋላ ስመጣ ተኝተህ አገኝሀለሁ። በቃ፣ ይሄው ነው።" አንገቴን ይዛ ሳብ አድረጋኝ ስታበቃ ነጻ ሆና ከንፈሬን ሳመችኝ።

የሚለመድ ነገር አልመሰለህ አለኝ። በዚህ ላይ እናቶች ይህንን ያህል ለዘብተኛ ይሆናሉ ብዬ ማመን ከበደኝ። የሆነ ሆኖ የመጨረሻው ውሳኔ ግን በቢታኒያ እጅ ነው። በመሀል የዛሬ ምሽቱ የኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ትዝ አለኝ። ሌሊቱን በሙሉ ነው የሚደረገው። በመሀል መውጣትና መግባት አይፈቀድም። ስለዚህ እዛው ማደሬ የማይቀር ነው። ስጓጓለት የከረምኩት የሞት የሽረት ስብሰባ ነው። መቼም በግልጽ አልነግራትም። ባይሆን ደበስበስ አድረጌ ስጠቁማት ይገባታል ብዬ ገመትኩ...

"ቤቲዬ፣ ዛሬ የሌሊት ሥራ አለብኝ። ልለውጠው የማልችለው ነው። እንደምትፈቅጅልኝ እርግጠኛ ስለሆንኩ ነው ቀድሜ ያልነገርኩሽ..."

አላስጨረሰችኝም። ፊቷ በቅጽበት ልውጥውጥ አለና ከተቀመጠችበት ተስፈንጥራ ተነሳች። ዓይኖቿ በዚች አጭር የጊዜ ትከታ ውስጥ እንዴት ደም እንደጎረሱ ግራ ገባኝ...

"አንተ ሞርን፣ ምን እባህ እያልክ ነው? የኔ እናት ሰው የምትበላ ጭራቅ መሰለችህ፣ አንዴ? በቃ፤ ከዚች ደቂቃ ጀምሮ ከዚህ ቤት ንቅንቅ አትልም!" የቀኝ እጇን ሌባ ጣት በቁጣ ማስጠንቀቂያ ዐይኔ ስር ወዘወዘችው።

ያልጠበኩት ፈተና ገጥሞኝ ቁጭ አለ። ሁኔታዋ አስፈራኝ። በእናቷ መምጣት ምክንያት ፈርቼ የወሰንኩት ውሳኔ እንዳልሆነ ለማሳመን ፍዳዬን አየሁ። በእናቴ ብምል በአባቴ... ጆሮዋን አልሰጠኝ አለች። ልቆጣ ብሞክርም ከቁብ አልቆጠረችኝም።

'ምናባቴ ይሻለኛል?!' አንድ ማምለጫ ዘዴ እንደምንም ለማግኘት ትንሽ አብሰለሰልኩ።

"እናትዬ፤" አልኳት ከምንም በላይ በምትወደው የቁልምጫ አጠራሬ፤ "እናትዬ፣ ችግሬን ተረጅልኝ። ከፈለግሽ ኢሳያስ አብሮኝ ስለሚያድር የቤቱን ስልክ ልስጥሽ። እሱን ልታነጋግሪው ትችያለሽ..." አሁንም አላስጨረሰችኝም፤ ከአስካሁኑ የበለጠ ቱግ ብላ ጣልቃ ገባች...

"ሽ—ት አ—ፕ! ይሄ ሁሉ ማስመሰያ ቀደም ብሎ የታሳበበት ነው። ቢታኒያ መኮንን ጡጦ የምጠባ ልጅ መሰልኩህ!?" አፈጠጠችብኝ።

ቁጣዋን በቅንነት ሳየው የፍቅራችን እድገት ያመጣው የሁለታችንም ስስት ነው። ወጥቼ ሳድር ታይቷት እንደማያውቅ ገባኝ። የአሁኑ ውሳኔዬ ይሄንን ያልተደፈረ ሞኖፖሊዋን እንደተጋፋባት ቆጥራዋለች። ፍቅር ዋናውን ተልእኮዬን እንዳስረሳት እየታዘብኩ ነው። አሁን አንድ ሁለት እርምጃ ሄድ ብዬ መናገር አለብኝ። ከቆመችበት የሐሳብ ጥግ ጎትቼ ላመጣት እንደሚገባኝ ተሰማኝ...

"ፍቅሬ፤ ዞሮ ዞሮ እኔና አንች መጨረሻ ላይ ሁለት የተለያየን ሰዎች መሆናችንን አትርሺ። ባንቺ በኩል አላውቅም። እኔ ግን ሁሉንም ምሥጢሬን ዝርግፍግፍ አድርጌ እንድነግርሽ ልትገፋፊኝ አይገባም። ይሄን ያህልስ ለምንድነው የተጠራጠርሽኝ? አንችን የምዋሽበት ምን ግፊት ይኖርበታል ብለሽ ብትገምች ነው? ትክክለኛው ጊዜ ሲደርስ በምታውቂው ምሥጢር ነው የምሄደው..."

በተቆጣችበት ፍጥነት መልሳ ስትሰክን የፊቷ ገጽ ነገረኝ። ከምንም በላይ ግን ዐይኖቿ ናቸው የእኔ ስሜት

መለኪያ መሣሪያዎች። አሁን ትክክለኛ ባልሆነ መንገድም ቢሆን ኢሕአፓነታችን ትዝ ብሏታል። ቀና ብላ ዐየችኝ...

"ምን'ባህ ነው ታዲያ እንደዚያ ብለህ ለመናገር አፍህን የዘጋህ፣ ሞሮን!" ደረቴ ላይ ልጥፍ አለች።

ፈቃዷን የገለጸችልኝ በአንድ ዙር የከንፈሮቻችን ፍትጊያ ነው። ቅር እያለኝ ተለይቻት ወደ ጋራዥ ሄድኩ።

***

ጉለሌ የደረስኩት ላንድሮቨሩን በጎጃም በረንዳ በኩል ነድቼ ነው። የማእከላዊ ኮሚቴው ስብሰባ በኢንጅነር ዑስማን ስም በተመዘገበ መኖሪያ ቤት ውስጥ ነው የሚካሄደው። አካባቢው ስደርስ ምሽቱ ገፍቶ የጎዳና መብራት በራ። አንድ አነስተኛ ግሮሰሪ ስድረስ ወደ ቀኝ ታጥፌ አምስት መቶ ሜትር ያህል ወደ ሰፈር ውስጥ መንዳት አለብኝ። ከዚያ በፊት ግን እዛው ግሮሰሪ አጠገብ በነበረ ምግብ ቤት ውስጥ ቀጠሮ ይዣለሁ። በሁለት ምክንያቶች ዮሴፍ አዳነን ወይም ዑስማንን ማግኘት አለብኝ። ከሰሞኑ የጋራዥ ገቢ የኢሕአፓን ድርሻ አስረከባለሁ። ወደ ስብሰባው ስገባም በጓሮ በር በኩል የሚያስገባኝን ኮድ የሚያወቀው ዮሴፍ ነው። ኾኖም ምግብ ቤቱ ውስጥ ከአንዲት አስተናጋጅ በስተቀር ሰው የለም። ገብቼ ለስላሳ አዘዝኩ። አስፋልቱ በመስኮቱ በኩል በደንብ ይታየኛል...

'በዛሬ ስብሰባ አንድ ነገር መሥራት አለብኝ!' የሰሞኑ አልሄ መጣብኝ።

በዚህ ሐሳብ መሐል ቀይ ቮልስ ቫገን የግል መኪና መጥታ ምግብ ቤቱ በር ላይ ቆመች። ሾፌሩ በደንብ ይታየኛል። ጸጉሩ በአጭሩ የተቆረጠ ሆኖ ትከሻው ከበድ ያለ ነው። ነጣ ያለ ካኪ ጃኬት እስከአንገቱ ቆልፎ ለብሷል። የቀኙ በር ተከፍቶ አንድ ሰው ወረደ። ሰውየው በጎፈረ ጸጉሩ ላይ ከብ ኮፍያ ጣል አድርጓል። በደንብ ሳየው ዮሴፍ አዳነ እንደሆነ አረጋገጥኩ። በሾፌሩ በኩል መጥቶ እጅ ለእጅ ከተጨባበጡ በኋላ ተሰነባበቱ። ይሄኔ መኪናዋ ወደ ፊት ተንቀሳቀሰች። የቮልሷ ሾፌር ማንነት ዮሴፍ ባለፈው ምድር ቤቱ የመጣ ጊዜ የነገረኝ ሰው መሰለኝ።

'አዎ፣ ማን ነበር ያለኝ?' የነገረኝ የኮድ ስሙ ኢልም አለብኝ።

ዮሴፍ ወደ ምግብ ቤቱ የሚያመጣውን ደረጃ ወጥቶ በረንዳው ላይ ተቀመጠ። በመስኮቱ በኩል ስለተቀመጠ ጭንቅላቱ ይታየኛል። ወዲያው ዞር ብሎ ወደ ምግብ ቤቱ ገልመጥ ሲል በእጄ "እዚህ ነኝ" የሚል ምልክት አሳየሁት።

"አላምረው፣ ቀድሜህ የመጣሁ መስሎኝኮ ነው።"

"እንደዚያ አንዳሰብክ ገምቻለሁ"

"ያመጣኝን ሰውዬ ዐይተኸዋል። ባለፈው ከቀይ ባንዲራ ቡድን ጋር ባደረግነው ውሕደት 'ጆይን' ያደረገን ሰው ነው። እኛ ጋ ፋይናንስ ኮሚቴ ውስጥ ተመድቧል። ሻለቃ ሽታዬ ደስታ ወይም በኮድ ስሙ ገዙ ይባላል። ላስተዋውቅህ ነበር ያመጣሁት፣ ያልደረስክ መስሎኝ ተላለፍን..."

"በደንብ ዐይቸዋለሁ...የጊዜና የቦታ ቀጠሮ ከሰጠኸን እኔው ራሴ እተዋወቀዋለሁ።" በዚሁ ተስማማን።

የሰሞኑን ገቢ እንደዘበት ቆጥሬ ሰጠሁት። በላንድሮቨሯ ተሳፍረን ረዘም ያለ የጠጠር መንገድ ሄድን። አንድ ጾጥ ያለና ከድሮ ጣውላ የተሠራ ትልቅ ግቢ ስንደርስ ወረድን። ምሽቱ ገፍቶ ደንዘዝ ስላለ ሰውን በማየት መለየት አይቻልም። የግቢው ዋና በር በፊት ይሁን በጀርባ አላውቅም። ዮሴፍ ቀድሞኝ ሄዶ የጣውላ በሩን አንኳኳው። በተመሰጠረ ኮድ እንደሚያንኳኳ ገብቶኛል።

"ማ----ን!!" የሚል ድምጽ ለዐመል ያህል ከውስጥ ተሰምቶ በሩ ተከፈተ።

ትልቅ ብርድ ልብስ የተከናነበ ዘበኛ ብቅ አለ።ተራ በተራ ዐይቶን ከፊት ለፊት ተጠግቶት የቆመውን ዮሴፍን በሹክሹክታ አናገረው። ግቢው ውስጥ ስንገባ ከውጩ የባሰ የጾጥታ አዘቅት ተቀበለን። በጀርባ በኩል አልፈን ወደ ቤቱ ፊት ለፊት ሄድን። በጎን በኩል ከሳጠራ የተሠራ ባዶ ጋራዥ ዉስጥ የተቀመጡ የሁለት ሰዎች ጭንቅላት ዐይኔ ውስጥ ገባ። የቤቱ በረንዳ በሸራ ተሸፍኗል። ወደዚያው እየሄድን እያለን የኮድ ስሜ ከጀርባዬ ዝቅ ባለ ድምጹ ተጠራ...

"አላምር! እታ አላምር!"

ዞር ብዬ ከማየቴ በፊት የማን ድምጽ እንደሆነ ወዲያው ለየሁት። ኢሳያስ ነው። ከመስከ ቀርቷል ማለት ነው። ጭለማ ውስጥ ስለተቀመጠ በደንብ ዐይታየኝም። ሄጂ ስቀላቀል ከፍሉ ተፈራም አብሮት ነው። ከፍሉ የኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ አባልና የደህንነት መዋቅሩ ኃላፊ ነው። ሁለቱም ሲጋራ ያጤሳሉ። ሄጂ ስቀላቀል ከፍሉ ተነስቶ ሳመኝ። የአዲስ አበባ በይነቀጠና ኮሚቴ ዋና ጸሐፊነትን ከመልቀቄ በፊት አንድ ወር ቀድም ብሎ ተገናኝተናል። ከዚያ በኋላ ተገናኝተን አናውቅም። ባዶውን ያገኘሁትን አሮጌ የእንጨት ወንበር ስቤ ተቀመጥኩ። ስለ እድገት በኅብረት ዘማቾችና የመንግሥት አታካራ እያወሩ እንደነበረ ወሬውን ሲቀጥሉ ገባኝ። ከፍሉ አሁን ሁለታችንንም ስለ ቀውሱ ይነግረናል...

"ደርግ የዘማቾቹን ልዩ ልዩ የፖለቲካ ጥያቄዎች በጥቅሉ 'ብሔራዊና አብዮታዊ ኃላፊነት የጎደለው

ተግባር' ብሎ ወንጅሎ በቴሌቪዥን ማሳየቱንና በሬዲዮ ማስነገሩን አልተገረምኩበትም። ያናደደኝ ግን በሬዲዮ የተነገረበትን አኳኋን ነው።" አለ።

"እንዴት አድርገው አስተላለፉት ነው?" ኢሳያስ ጠየቀው።

"ያች ብርኪታዊት የምትባል አሉባላቢት ጋዜጠኛ አለች...ራሷ የጻፈችው አስመስላ ዘማቾቹን ስትወርድባቸው አመሸች። እኔማ ለምን እንደሆነ አላውቅም ገና ድምጿን ስሰማው ደሜ ይፈላል!" ከፍሉ ተፈራ በንዴት ሞለጯት።

ኢሳያስና እኔ ተያየን።ነጻነት የሌለው ጋዜጠኛ ጽፈው የሰጡትን ማንበብ ሥራው እንደሆነና ብርኪታዊትም ከዚህ ውጭ ልትሆን እንደማትችል ኢሳያስ ቀለል አድርጎ ጠቆመው።ጥቆማውን ተከትሎ ግን ከፍሉ ሌላ ያልታሰበ ዱብ እዳ ዜና ይዞብኝ መጣ...

"አይ፣ ጤነኛ አትምስለኝም። ሰሞኑን እዛ አራት ኪሎ አካባቢ የተከፈተ ተራማጅ መጻሕፍት መደብር በተደጋጋሚ አያታለሁ። በኋላ መኢሶንን ሳትቀላቀል እንዳልቀረች አንዲት የምታውቃት ልጅ ነገረችኝ።" መልእክቱ በእኔና በኢሳያስ ላይ የፈጠረው ድንጋጤ ከፍሉን አልታየውም።

'ኢሱ፣ጉድ ፈላልህ!' ቀና ብዬ ሳየው እሱም በተረበሸ አተያይ መልሶ ዐየኝ።

ብርኪታዊት ሥራ የገባችበት የመጻሕፍት መድብር ባለቤትነቱ የመኢሶን ነው። ጅማ ሄጄ ከተለያየን ወዲህ የተፈጠረ ለውጥ መሆኑ ገባኝ። በዝንባሌዋ ብርኪቲ ፖለቲካን በሚገባ ትረዳለች። ይሄንን ሳስብ አንድ እንደቀልድ ጣል ያደረገችልኝ ወሬ እንደ ወረንጦ ድንገት መጥቶ ጠቅ አደረገኝ። ከመኢሶን መሥራቾች አንዱ የሆነውን ዶክተር ፍቅሬ መርእድን በታላቅ ወንድሟ ምክንያት እንደምታውቀው ነግራኛለች። ያኔ ግን "ፍቅሬ" የሚለውን ስሙን ከመኢሶን ጋር አገናዝቤ አልተረዳሁትም። ድንጋጤ አካሌን ጨው አደረገው።

'የቀድሞ ፍቅረኛዬን መኢሶን ጠለፋት ማለት ነው?' ኢሳያስን በደፈረሰ ስሜት ውስጥ እንደሆንኩ ቀና ብዬ ዐየሁት። 'አላምር፣ ድሮ ልትጠራጠር ፈልገህ ነበር?!' የሚል የቅሬታ መልእክት ዐይኖቹ ላይ ያነበብኩ መሰለኝ።

ብርኪቲ ተራማጅ መጻሕፍት መደብር ከሠራች በትርፍ ጊዜዋ ተቀጥራ እንደሚሆን ገመትኩ። ያ ማለት ደግሞ መኢሶን አባሉ ላልሆነ ሰው ይሄንን የሚያክል ምሥጢሩን ሊያሳውቅ አይችልም። የቤተ መጻሕፍቱን የመኢሶን ባለቤትነት ደርግም እንደማያውቅ ተስፋዬ ደበሳይ ከአንድ ሁለት ወር በፊት ነግሮኛል። ከቀናት በኋላ እኔና ኢያሱ አለማየሁ ተልእኮ ተሰጠን። የደርግ አባል የነበረውን የጌታቸው

ማሩን ታላቅ ወንድም መለሰ ማሩን አገኘነው። እያሱ ስለዚህ ቤተመጻሕፍት አነሳለት። መለሰ ከነስሙም እንደማያውቀው ነገረን። እንዴት? ትዝ ሲለኝ ያኔ ደርግና መኢሶን ለካስ የጎሪጥ ነው የሚተያዩት። ተገርመን ተመለስን...

'ወቼ ጉ---ድ! ጆሮ አይሰማው የለም...' ከኢሳያስ ጋር እንደገና ተያየን።

አብሬያት ብሆን ኖሮስ? በአንድ ነገር እርግጠኛ ነኝ። ብርከቲ እኔን ሳታማክር እንደዚህ ዓይነት አወዛጋቢ ውሳኔ ላይ አትደርስም። መኢሶንን ተቀላቅላ ከሆነ የምር ከልቤ ማዘኔ አይቀርም።'ቡ---ል ሽ-----ት!!' እየቆየሁ ስሄድ ቅጥል አልኩ።አእምሮዬ የቀድሞ ፍቅረኛዬን ነክሶ አለቅም አለ። ከብርከቲ ጋር ከወራት በፊት የነበረ ታሪካችን ሌላ ነው። አልጋ ላይ ተቆላልፈን በፍቅር ጨዋታ የምናብድ ፍቅረኞች ነበርን። አሁንም የተለየኋት በጥል ወይም ፍቅሬ ስለቀነሰ አይደለም። አሁን ከፍሉ ተፈራ የነገረን ዜና እውነት ከሆነ መኢሶንን የተቀላቀለችው ብርከቲ እንግዲህ ይህች የድሮ የልብ ፍቅረኛዬ ነች።

በመሀሉ ከፍሉ ተፈራ ሰዓቱን ዐይቶ ብድግ አለ። ለስብሰባ የሚመጣ ሰው በር ላይ ለማስገባት ሄደ። ኢሳያስ ወዲያው ወደ እኔ ጠጋ ብሎ አፉን ወደ ጆሮዬ አቀረበው...

"ስመሬ፣ እውነቱን ንገረኝ። ስለብርከቲ የሰማኸው ነገር በጣም ቅር አሰኝቶሃል፣ አይደል?" በቁምነገር ጠየቀኝ።

"ኢሱ፣ ምን ማለትህ ነው? ቅር ማሰኘት ብቻ አይደለም፣ አንገብግቦኛል..."

"ምናልባት አንተ ወደ ጋራዥ እንድትመጣ የተፈለገበትም ምክንያት ይሄው ሊሆን ይችላል። መለያየት..." እንደዘበት ነገረኝ።

"ነ----ው እንዴዴ፣ ኢሱ?" አንዳች ዓይነት ደማሚት ዐይኖቼ ላይ የፈነዳ መሰለኝ።

ከዚህ ያለፈ ነገር መነጋገር አልቻልንም። ዲ--ሲ-ፒ--ሊ--ን!! የአንደኛችን ዓይን ከሌላኛችን ሳይነቀል የቪላ ቤቱ በር ከውስጥ ተከፈተ። ዲሲፒሊን!! እንደ ካቴና ቆልፎ ያዘኝ። ጌታቸው ማሩ ከተከፈተው በር ወጥቶ ጣደፍ ጣደፍ እያለ ወደ እኛ መጣ።

"ጓዶች፣ ልንጀምር ነው፤ ወደ ውስጥ ግቡ..."

# 17

ኢሳያስና እኔ በፊት ለፊት በር ገባን። ስብሰባው የሚደረገው በቤቱ ሰፋ ያለ ሳሎን ውስጥ ነው። ጣሪያው መሀል ላይ የተገጠመው ጋን የሚያክል አምፖል ከሥሩ በቀይ ወረቀት ተከልሏል። መብራቱ ደብዛዛ ደም የመሰለ ጨረር ይረጫል። ሰውን በቀላሉ መለየት አይቻልም። አራቱን ማዕዘናት የቤቱን ግድግዳ ተከትሎ ሰፋ ወንበሮች ተደርድረዋል። ሰፋው ሥር የሰፋው ስፖንጅ መቀመጫዎች ከብ ሠርተው ተደርድረዋል። ተሰብሳቢዎች ሰፋውን ተደግፈው ስፖንጅ ትራሶቹ ላይ ተቀምጠዋል። ሄደን ክፍት ባገኘናቸው ቦታዎች አጠገብ ለአጠገብ ተቀመጥን። ሁለታችንን ጨምሮ አሥራ ሦስት ሰው ተገኝቷል። ሁሉም ማስታወሻ ደብተር ገልጦ ነው የተቀመጠው። እኛም እነርሱን መሰልን።

ለአመል ያህል ካቀረቀርኩበት የማስታወሻ ደብተሬ ቀና ብዬ ግራና ቀኙን ለማየት ሞከርኩ። በግራዬ በኩል የተቀመጠው ሰው ፈካ ያለ ቀይ ፊት...አፍንጫው ሥር ጺሙና የጭንቅላቱ ጸጉር የጎፈረ...በደብዛዛው ብርሃንም ውስጥ ሆኖ የፊቱን ገጽ ቅጭም አድርጎ መኮስኮሱ የሚታወቅበት ወጣት ተቀምጧል። ዝም ብሎ ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ይመለከታል። ብርሃነመስቀል ነው። ስለ ብርሃነመስቀል የነበረኝ የድሮው ክብር፣ ግንዛቤና አስተሳሰብ አሁን በቦታው ይኑር አይኑር እርግጠኛ አይደለሁም።

በእርግጥ አከብሮቴ እንዳለ ነው። ያ የቀድሞ ተጽእኖው ግን በውስጤ እንዳለ አይሰማኝም። ስለ ዘርዑና ተስፋዬ ደበሳይም እንደዚያው ነው የሚሰማኝ። የመጀመሪያውን ኩነኔ በመሥራት የ"እርምት ፖለቲካ ባህል" በፓርቲዩ ዉስጥ በወጉ እንዳይበቅል አድርገዋል ብዬ ስለማምን ይመስለኛል።

የዘርዑ ከህሸን ቀጠን ያለ ድምጽ ሲሰማ ጸጥታ ሰፈነ። ዘርዑ ከፊቴ ለፊቴ ትንሽ ራቅ ብሎ መሀል ላይ ነው የተቀመጠው። አጠገቡ የተቀመጠች ሴት ያየሁ መሰለኝ። የጸጉሯ ብዛትና የጆሮዋ ጌጥ በትክክል የሴት ነው። በዚህ የአመራር ደረጃ የማውቃት ሴት ግን የለችም። በጾታ ተዋጽኦ ኮታ አምጥተዋት

እንደሚሆን ገመትኩ። ከእሷ በቀኝ በኩል ሲጋራ የሚያጤስ ሰው ይታየኛል። ከፍሉ ታደሰ እንደሚሆን ገመትኩ። እሱን ሳስብ ያለፈው ጊዜ ወሬያችን ትዝ አለኝ...

"የሱ---ፍ አበ-------------ባ!" ለምን እንደሆን አላውቅም፣ ከፍሉ ያወራልኝ የሱፍ አበባ ታሪክ ባሉፉት ቀናት በፍጹም ከአእምሮዬ አልወጣ ብሎኛል። "የሱ--ፍ አበ----ባ!!"፣"የሱ--ፍ አበ----ባ!!"፣"የሱ--ፍ አበ----ባ!!"

ከሀሳቤ ያወጣኝ የዘርዐ ድምጽ ነው...

"ጓዶች፣ ኮረም ተሟልቷል፣ ስብሰባችንን ጀምረናል። የዛሬ አጀንዳዎቻችን የመረጃ ልውውጥ፣ በወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ ላይ መወያየትና አቋም መውሰድ እንዲሁም ላጋጠሙን ችግሮች የመፍትሄ ሐሳቦችን መለየትና መወሰን የሚሉ ናቸው። በናንተ በኩል የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ልንወያይበት ይገባል የምትሉትና የምታስይዙት አጀንዳ ካለም መድረኩ ከፍት ነው።" አለ፣ የትግርኛ ቅላጼ በሚጎላበት አነጋገር።

ለአፍታ ጸጥታ ሰፈነ። የተለየ አጀንዳ የሚያሲይዝ አባል የለም ማለት ነበር ዝምታው። ዘርዐ ይሄንን በአጭሩ ገልጾ በቀጥታ በእሱ በኩል ወደቀረቡት አጀንዳዎች አለፈ። የመረጃ ልውውጡ ቀደመ። ዮሴፍ አዳነ እድል ተሰጠው። ኢሕአፓ የገጠመውን ከፍተኛ የፋይናንስ ቀውስ በስታትስቲካዊ መረጃ አስደግፎ አቀረበ። ቀጥሎ ከእኔ በስተግራ በኩል አለፍ ብሎ ከተሰፋዬ ደበሳይ አጠገብ የተቀመጠው ከፍሉ ተፈራ እጁን አወጣ። በደህንነት ጉዳይ መረጃ እንደሚያቀርብ ግልጽ ነበር። የደርግ መንግሥትና መኢሶን በጥምረት የኢሕአፓ አባላትን ማሳደድ መቀጠላቸውን...በደርግ ውስጥ የአመራር ቀውስ እየጨመረና እየተወሳሰበ መምጣቱን...ደርግና መኢሶን የአብዮት ጥበቃ ቡድኖችን ለማቋቋምና ለማጠናከር ማቀዳቸውን አስረዳ። በበኩሌ የሚነገረውን ሁሉ በደንብ እየተከታተልኩ ልቤ ግን ሌላ ቦታ ዘምቷል...

'እነዚህ ሰዎች እንዴት እንዴት ነው የሚያስቡት? ኢሕአፓ አዲሳ'ባ ውስጥ ቁጭ ብሎ "ገንዘብ ቸገረኝ፣ ሰላይ ተላከብኝ፣ ደርግ ተተራመሰ..." ቢል ምን ይፈይዳል?' "የሱ--ፍ አበ----ባ!!"።

ድርጅቱ በአንግድነት ባልተጋበዘበት የሌላ ሰው ቤት ዘው ብሎ እንደገባ ዓይነት ሆኖ ተሳለብኝ። የመረጃ ልውውጡ ይህንኑ መንፈስ ይዞ ቀጠለ። ጸሎተ ሕዝቅያስ ተራውን ወሰደ።የድርጅቱን መዋቅር መስፋትና የአባላት በብዙ እጥፍ መበራከት ገለጸ። ተስፋዬ ደበሳይ ስለ ዲሞክራሲያ ኅትመት፣ ስርጭትና ግብረመልስ ከበይነቀጠና ኮሚቴዎች የደረሱትን ሪፖርቶች አቀረበ። የሁሉም ፓርቲ ኮሚቴዎች አገናኝ የሆኑ አባላት መረጃቸውን አቀረቡ። ኮሚቴዎችን ወክለን የመጣነው እኔ፣ ሴቷ አባልና ሌሎች ሁለት

ተሳታፊዎች ብቻ አልተናገርንም። የኢሳያስ ደረጃ በተለዋጭ የማእከላዊ ኮሚቴ አባልነት ስለሆነ ሪፖርት ማቅረብ አለበት። በሰሜን ሸዋ ወታደራዊ ጥናቱ ወቅት ስለታዘባቸው ነገሮች አስረዳ። በመጨረሻ መድረኩ ወደ ዘርዐ ተመለሰ...

"በመረጃ ልውውጡ ከሰማናቸው ነገሮች ግልጽ ያልሆነ ነገር ካለ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል።" ብሎ ተሰብሳቢዎችን ዙሪያውን በዐይኑ ቃኝቶ እጅ አለመውጣቱን ሲመለከት አጭር አስተያየት ሰጥቶ ወደ ሁለተኛው አጀንዳ አለፈ።

የወቅታዊ ፖለቲካ ሁኔታ ግምገማ...። አንድ ነገር እሠራበታለሁ ያልኩበት አጀንዳ ነው። ቅብጥብጥ አልኩ። ወደ ቀኝ አቅጣጫ ዞር ስል ከኢሳያስ ጋር ተያየን። ቅንድቦቹን ሽቅብ ሰብሰብ ያደረገልኝ መሰለኝ። ነገሩ "ተዘጋጅ" መሆኑ ገባኝ። ዘርዐ ተናጋሪ ሲጋብዝ ፈጠን ብዬ እጄን አወጣሁ። በተለይ ብርሃነመስቀል፣ ጌታቸው ማሩና ዶክተር ተስፋዬ እንዲቀድሙኝ አልፈለኩም። የስብሰባውን መንፈስ ወደራሳቸው አቅጣጫ እንዳይጎትቱብኝ ነው ስጋቴ። ዘርዐ የኮድ ስሜን ጠርቶ ፈቀደልኝ...

ጉሮሮዬን አጸዳድቼ መናገር ጀመርኩ...

"በእኔ በኩል የተዘጋጀሁትና የምናገረውም የወቅቱን ግምገማ ከፖለቲካ ሁኔታዎች ዕድገትና ለውጥ አንጻር ነው። ግምገማዬን የማደርገው ከጥቅል ወደ ዝርዝር በመመርመር ዘዴ ነው። ስለዚህ ብሔራዊ ሁኔታውን አስቀድማለሁ።" ብዬ ተንደርድሬ ቀና ብዬ ሳይ ደብተሩ ላይ ካቀረቀረው ብርሃነመስቀል በስተቀር ሁሉም እተኩረውብኛል። ተበረታትቼ ቀጠልኩ፣ "ለመነሻ እንዲሆነኝ ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት የሚታየውና መታየት የቀጠለው ፖለቲካዊ ለውጥ እንደምን ይገለጻል? አብዮታዊ ለውጥ ተካሂዷል ወይ? ድርጅታችን በ964ቱ የበርሊን መመሥረቻ ፕሮግራሙ የነደፈውና ያቀደው ሥር ነቀል ለውጥ ነው ወይ? ለእነዚህ ጥያቄዎች የምሰጠው መልስ የፖለቲካ ኮሚቴው የግምገማ ምሶሶ ይሆናል..."

ከማስታወሻ ደብተሬ ላይ ቀና ብዬ እንደገና ተመለከትኩ። አሁን የግማገማ ነጥቦቼን አስቀድሞ ከማያውቋቸው ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ ማስታወሻ እየያዙ ነው። ለጥያቄዎቼ መልስ መስጠት ጀመርኩ...

"አብዮት በእርግጥ ተካሂዷል ወይ? የሚለውን ጥያቄ እናስቀድም። ትንተናውን በጣም ቀላል ለማድረግ የፖሊቲካል ሶሾሎጂ መሥሰፈርቶችን መጠቀም ተገቢ ይመስለኛል። በእኔ በኩል ያለምንም ጥርጥር አብዮት ተካሂዷል። ምክንያቱም ለውጡ ሦስት መሠረታዊ የማሕበራዊ የአብዮት መሥፈርቶችን በሚገባ አሟልቷል። እነርሱም፣ የፖለቲካ እሴቶች ሥር ነቀል ለውጥ፣ የመሠረታዊ ተቋማት መፍረስና

በመጨረሻ የማኅበራዊ ኃይሎች አሰላለፍ ለውጥ ናቸው..."ብዬ ቀና ስል ሁሉም በንቃት እየተከታተሉኝ ነው።

እኔም ባገኘሁት ትኩረት የበለጠ ተበረታትቼ ትንተናዬን ገፋሁበት...

"ይህ ግን የምስሉ አንድ ገጽ ብቻ ነው። የአብዮቱና የአዲሱ ወታደራዊ አገዛዝ እጣ ፋንታስ ምን ይሆናል? ይህ ደግሞ ሌላው ውስብስብ ጥያቄ ነው። የሚቀጥለው ምን እንደሚሆን ለመተንበይ አሁንም የሶሾሎጂ መሥፈርቶችን መጠቀም ሊኖርብን ነው። አንድ ሥር ነቀል ማኅበራዊ አብዮት በየትም ጊዜና በታ የሚያልፍባቸው ሰባት ደረጃዎች አሉ......"

ወደ ጌታቸው ማሩ ገልመጥ አልኩ። ለተቃውሞ እንዲመቼው ወይም የምናገረው አዲስ ስለሆነበት ይመስለኛል አንድም ቃል እንዳያመልጠው ጥድፍድፍ አያለ ይጽፋል። እኔም ተረጋግቼ ገለጻዬን ቀጠልኩ...

"የመጀመሪያው ደረጃ የሕዝብ መነሳሳት ነው። ሁለተኛው ደረጃ፣ ሪፎርም ነው። ገዥዎች መነሳሳቱን ለማስተንፈስ የሕግና የመዋቅር ማሻሻያ ያደረጋሉ። ሕዝቡ አይቀበለውም። ወደ ሦስተኛው ደረጃ ያድጋል። ውጥረት የሚባለው ነው። አራተኛ ደረጃ ላይ አሮጌው አገዛዝ ይወድቃል። አዲስ የአብዮታውያን አመራር ቡድን ሥልጣን ይረከባል። ኮሚቴ ወይም የሆነ ቡድን ሊሆን ይችላል። አምስተኛው ደረጃ ላይ በአዲሱ አገዛዝ ውስጥ የአመራር ቀውስ ይከሰታል። ይህ አመራር አዲስና ሁሉንም የሚያግባባ ወጥ አስተሳሰብ ለመፍጠር ሲሞክር እርስ በእርስ ቅራኔ ውስጥ ይገባል።"ብዬ ቀና አልኩ።

ዘርው ጭንቅላቱን በአዎንታ ሲነቀንቅልኝ ያየሁት መሰለኝ።

"ስድስተኛው ደረጃ ላይ የአመራሩ ልዩነት ወደ ደም መፋሰስ ያድጋል። አንዱ ወገን ሌላውን ቡድን ፈጅቶ በአሸናፊነት ብቅ ይላል። በሰባተኛው ደረጃ ስክነት ወይም ቴርሚዶር ይመጣል። ፖለቲካው ይረጋጋና ሰላማዊ የሽግግር ወቅት ይጀመራል። ይህ ሽግግር በተራው አራት ደረጃዎችን ማለፍ አለበት። የመጀመሪያው የጸጥታ ማስከበር ጊዜ ነው። አዲስ የተፈጠረው ሁኔታ ወደ ብሔራዊ ብጥብጥ እንዳያመራ ለአጭር ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ይታወጃል።

"ይህ ዐዋጅ በዛ ከተባለ ከአርባ አምስት ቀናት መብለጥ የለበትም። ሁለተኛው፣ አስቸኳይ ጊዜ ዐዋጁ ይነሳና የመነጋገር ደረጃ ወይም የሽግግር ጊዜ ይፈጠራል። ይህ ጊዜ መብቶች ተከብረው አነሰም በዛ

ሰላም ይወርዳል። በፖለቲካ ቡድኖች መካከል ክርክር ይደረጋል። ግፋ ቢል ከሦስት ዓመት መብለጥ የለበትም። ሦስተኛው ደረጃ የምርጫ ጊዜ ሲሆን አራተኛው አዲሱ ሪፖብሊክ የሚቋቋምበት ይሆናል።" ቀና ስል ብርሃነመስቀል አፍጥጦብኛል።

የወቅታዊ ሁኔታ ግምገማ ዓላማዬ በሚቀጥለው አጀንዳ ላይ ጠንከር ያለ ተጽእኖ ማሳረፍ ነው። የደርግ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምና የግንባር ምሥረታ ጥሪን ኢሕአፓ እንዳይቀበለው ማድረግ ነው። ቀጥሎ ኢሕአፓ ወደ ትክክለኛ ተፈጥሯዊ ቦታው ገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንዲወጣ ማሳመን ይሆናል።" የብርሃነመስቀልን ትኩረት ስመለከት የተሳካልኝ መሰለኝ። ቀጠልኩ...

"...የደርግን መንግሥት በዚህ መሥፈርት ስንመዝነው ደርግ ይህንን ጉዞ አልፎ ለሪፓብሊኩ ቦታ ሲለቅ ፈጽሞ አይታየኝም። ይልቁንስ ደርግ በሥልጣን ለመቀጠል ይሄንን ሂደት መቀልበስ ብቸኛ አማራጩ ይሆናል። በዚህ ብቻ ግን አይወሰንም። ይሄንን ፍላጎቱን በሚጻረሩ ኃይሎች ላይ ርህራሄ የጎደለው እርምጃ መውሰዱ የማይቀር ነው።የጥቃቱ ቁጥር አንድ ኢላማ ደግሞ ድርጅታችን እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው። በተግባርም እየታየ ያለው ይሄው ነው።"

እዚህ ስደርስ ወደሚቀጥለውና ከስድሳ አራት ሺህ ዶላሩ ጥያቄ ወደሚልቀው ታላቁ አጀንዳዬ አለፍኩ። የገጠር ሥምሪት...

"ድርጅታችን ለዚህ የማይቀር የድምሰሳ እርምጃ ምን ያህል ተዘጋጅቷል? መልሴ ጨርሶ አልተዘጋጀም ብቻ ሳይሆን አላሰበበትም የሚል ነው። 'አለመዘጋጀት' ማለት ደግሞ ራስን በትክክለኛው ቦታ ላይ አለማስቀመጥ ማለት ነው። ኢሕአፓ በአንድ በኩል ትልቁ ብሔራዊ ተቃዋሚ ድርጅት ሆኗል። በሌላ በኩል ማእከላዊ ኮሚቴውና ፖሊት ቢሮው ግን በትልቁ የገጠር ሕዝብ መሀል አይደሉም።"

ግምገማዬን ገጠር መውጣት መፍትሄ መሆኑን አስረግጠ አበቃ። ሁኔታውን ሳይ የተሳካልኝ መሰለኝ። ወደ ዘርው ተመለስኩ...

"ጓድ አላምረው ያቀረበውን ሐሳብ 'ለሞሽን' ከማቀርበው ይልቅ ለሚቀጥለው አጀንዳችን እንደመንደርደሪያ ብንወሰደው የሚል ሐሳብ አለኝ። የተለየ ሐሳብ ካለ እድል እሰጣለሁ።" ብሎ የወጣ እጅ መኖር አለመኖሩን ዐየ።

የተለየ ሐሳብ አለመኖሩን ሳይ ድንጋጤ ገጭ አደረገኝ። 'ወቅታዊ ግምገማ ማለት አልገባኝም ማለት ነው?' የምጠይቀው ሰው የለም። "ሰሙየ፣ ስማኝ...ስትቸኩል ያለጥርጥር ትሳሳታለህ! ባከህ አትቸኩል...

"የብርክቲ ቃላት መጡብኝ። ነገር ግን ካልገባኝ ገለጻዬን ማስቆም ወይም ትርጉሙን መንገር የእነርሱ ፋንታ ነው። መልሼ ራሴን አረጋጋሁት። ዘርዑ የእኔን ግምገማ መነሻ አድርጎ ወደሚቀጥለው አጀንዳ ሲያልፍ ደግሞ የበለጠ ተረጋጋሁ። የሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም የሕብረት ግንባር ጥሪ...። እውነት ለመናገር ከነበርኩበት የአእምሮ ሁኔታ አንጻር ከፋኝ። አጀንዳው እንደ አባ ጨጓሬ ኮሰኮሰኝ።

ቀድሞ እጅ ያወጣው ብርሃነመስቀል ነበር...

"እኛ በፖለቲካ ፕሮግራማችን ላይ የሰፈረ ዓለማ አለን። ዓላማችንን በሰላማዊ መንገድ የምናሳካበት የፖለቲካ ሁኔታ ከተፈጠረ ከጥይትና ከጠበንጃ ምን አለን?" ብሎ ጠይቆ መልስ ሰጠ፣ "ጓድ አላምረው ያነሳው ነጥብ አለ። 'ይሄንን አጀንዳ ራሱን አንስቶ ለመወያየት ገጠር መግባት አለብን' ያለውን ነጥብ በመርህ እቀበለዋለሁ። ችግሩ ግን በዚህ ሰዓት የድርጅታችን ቁልፍ የነበረው የመሬት ጥያቄያችን በመሬት ዐዋጁ ምክንያት ወደ መለስተኛ ደረጃ ወርዷል። ይህ እውነት በሆነበት አገራዊ ሁኔታ ውስጥ ነን። ሌሎቹን ጥያቄዎቻችን በጠበንጃ ተጽእኖ ፈጥረን የምናስመልሳቸው አይደሉም። በብሔራዊ ትብብርና በሰላማዊ 'ዲያሎግ' ልናሳካቸው እንችላለን። ደርግና መኢሶን ግራ ኃይል ተራማጆች ነን ብለዋል። በቃ፣ ይሄንን በተግባር የማሳየቱ እዳ የእነርሱ ነው። የእኛ ድርሻ ከልባቸው መሆኑን በከርከር መፈተን ነው።"

ዘርዑ በብርሃነመስቀል ሐሳብ ላይ ተጨማሪ ወይም ድጋፍ ካለ ጠየቀ። ጌታቸው ማሩ ፈጥኖ እጅ አወጣ። ተፈቀደለት...

"የጋራ ብሔራዊ ግንባር ከመፍጠር ውጭ ኢሕአፓዎች ሌላ ምንም አማራጭ የለንም። ሦስት ምክንያቶች አሉኝ። እኛ አቋማችን 'ጸረ-ፊውዳሊዝም፣ ጸረ-ኢምፔሪያሊዝምና ጸረ-ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም ነው' አልን። የደርግ የመሬት ዐዋጅ በመሀሉ ወጣ። ጸረ-ፊውዳል አቋማችን በቂ መልስ አገኘ። ጥቂት ወራት ቆይቶ ደርግ የግል ማምረቻ ድርጅቶችን ወረሰ። የውጭ ባለ ሀብቶች ያለ ካሳ ተባረሩ። ቀደም ብሎም ደርግ ሶሻሊዝምን መቀበሉን ዐወጀ። በዚህ እርምጃው ጸረ-ኢምፔሪያሊስት አቋማችን መልስ አገኘ። ወዳያው ደግሞ ደርግ 'ሥር ነቀል የመዋቅር ለውጥ ለማድረግ የሽግግር ሥርዐት እዘረጋለሁ' አለ። መቼስ እኛም ሥልጣን ብንይዝ ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝምን በሽግግር ነው የምናስወግደው። በዚህ ምክንያት ሦስተኛው አቋማችን መልስ አገኘ። ስለዚህ ደርግን የምንዋጋበት አጀንዳ ምንድነው?"

'በቃ፣ ጌታቸው ደርግን ህጋዊ መሪ አድርጎታል። ጁንታ የትም ቦታ የቀውስ ውጤት እንጅ ቀውስን መፍታት የሚችል ተፈጥሯዊ ብቃት እንደሌለው አልተገነዘበም። ዞሮ ዞሮ ዋናው ምክንያት የአዲሳባ ፍቅር ነው...' ተቃጠልኩ።

ጌታቸው ለራሱ ጥያቄ ራሱ መልስ ሰጠ...

"አጀንዳ አለን ካላችሁ አስረዱኝ። የእኔ መልስ ግን ምንም አጀንዳ የለንም የሚል ነው። ሌላው የዓድ አላምረው የሁኔታ ግምገማ ነው። ግምገማው ከነባራዊው ሁኔታ ጋር የማይጣጣም ነው። በበርሊኑ ፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ከዚያ ወዲህ ያለውን ለውጥ አላገናዘበም። እርግጥ ገጠር መግባት በመርሕ ትክክል ነው። ነገር ግን ዳዱ የሚለው ዓይነት ገበሬ ስለማግኘታችን እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ያም ቢሆን የግንባር ምሥረታው ካልተሳካ የሚታይ ነው። ደርግም ቢሆን በተመሳሳይ ሁኔታ የሕብረት ግንባር ከመመስረት ውጭ እድል የለውም። ይህንን እድል መጠቀም ይኖርብናል..."

ሐሳቤን እንዴት እንዴት አድርጎ ጠምዝዞ ከሕብረት ግንባር ጥሪው ጋር እንዳያያዘው ገረመኝ። መልስ መስጠት አልፈለኩም።ዘርዐ የሚቀጥለውን የመናገር እድል ለአሜሪካው ከፍሉ ታደሰ ሰጠ። "የሰፍ አበባ" በዐይነ ህሊናዬ ድቅን አለችብኝ። ከፍሉ አቀማመጡን አስተካከሎ መናገር ጀመረ...

"እኔ የ 'ሕብረት ግንባር እንፍጠር'ሐሳብን በመቃወም ነው የምናገረው። መጀመሪያ ነገር የዓድ አላምረው ትንተና 'የጋራ ግንባር እንፍጠር' ለሚል ሐሳብ ማጠናከሪያ የሚሆን አይመስለኝም። ደርግ በባህርይው የጋራ ግንባር የመፍጠር ዝንባሌ በተፍጥሮው እንደሌለው ነው የተናገረው። እኔም መቶ በመቶ እስማማበታለሁ። የ 'ጋራ ግንባር' ለመሆኑ ምን ማለት ነው? ግንባሩን የሚፈጥሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ቢያንስ ቢያንስ በዋና ዋና የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ በመርህ መግባባት አለባቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን የሕጋዊ መንግሥት አመራርና የዲሞክራሲ...የብሔርና የሃይማኖት እኩልነት...የኤርትራ... ወ.ዘ.ተ. ጥያቄዎች አሉ። በቃ፣ ደርግ'ኮ ለጥያቄዎቹ አንድ ጥቅል መልስ ሰጥቷል። 'ኢትዮጵያ ትቅደም... ይሄንን መርሕ የሚቃወም አፈሙዝ ይጠብቀዋል...' ብሏል። ታዲያ ከዚህ መንግሥት ጋር ነው የጋራ ግንባር የምንፈጥረው?" ጥያቄውን ከፍት አድርጎ ጨረሰ።

ዘርዐ የሚቀጥለውን የመናገር እድል ለኢሳያስ ሰጠው...

"እኔ ዳዱ የሚለውን ተቃውሜ ነው የምናገረው..." ኢሳያስ ወደ ጌታቸው ማሩ በአገጩ አመልክቶ ቀጠለ፣ "ቅድም ዓድ አላምረው ስለደርግ ሲናገር ሦስት መሠረታዊ ነጥቦችን አንስቷል። የመጀመሪያው 'ደርግ የቀውስ ውጤት ነው' የሚለው ነው። ሁለተኛ፣ 'ደርግ የሌላ መደብ ተቀጽላ እንጂ በራሱ መደብ አይወከልም' ብሏል። ሦስተኛ፣ 'ደርግ በተፈጥሮው ትብብር አይፈልግም' ። መጀመሪያ ይሄ ሙግት ትክክል ነው ወይስ አይደለም? በዚህ ላይ ሳንስማማ በሕብረት ግንባር መመስረት ጉዳይ ላይ መስማማት አንችልም።ይህ እንደገና ምን ማለት ነው? ደርግ እንኳንስ በእኛ ጥያቄ ይቅርና በራሱ ጥያቄም ቢሆን

ልንተባበረው የሚያስችለን አቋቋም የለውም ማለት ነው። ይሄ ስብሰባ'ኮ የኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ነው። የደርግ/መኢሶን ስብሰባ አይደለም። ደርግን ወክለን 'ደርግም ቢሆን ከመተባበር ሌላ አማራጭ የለውም' ማለት የምንችለው እንዴት ነው? ትክክል አይደለም..."

ዶክተር ተስፋዬና ዮሴፍ አዳነ በኢሳያስ ሐሳብ ላይ ተጨማሪ ሐሳብ ሰጡ።

ክርክሩ ከኢሳያስና ከክፍሉ ታደሰ የሲጋራ ጢስ ጋር ተዋህዶ መንደድ ጀመረ። ለእኔ ሁለቱም ወገኖች አልተመቹኝም። አዲስ አበባ ከተማ እምብርት ላይ ሆነው እስከተከራከሩ ድረስ ነጥባቸው ምንም ይሁን ምን ትክክል አይደሉም። ጌታቸው ማሩ በከፊል ወይም በቅድመ ሁኔታ ተቀብሎታል። ክርክሩ ግን ቀጠለ። እኩለ ሌሊት ላይ የማእከላዊ ኮሚቴው ጥቅል ዝንባሌ እየለየ መጣ። "የሕብረት የግንባር ጥሪውን እንቀበል" የሚለው ወገን ጎልቶ ወጣ።

ብስጭቴን ለራሴ የምገልጽበት ቋንቋ ሳፈላልግ ዊሊያም ጀምስ ትዝ አለኝ። አንድ ግሩም አባባል አለው። በእንግሊዝኛ ሲነገር የተሻለ መልእክት ይሰጣል መሰለኝ። "We are shaped and fashioned by what we love!""የሰው ልጆች ባህርይ የተቀረጸው በሚያፈቅሩት ነገር ነው።" እንደማለት። ወደ ኢሕአፓ አመጣሁት። 'የድርጅታችን የወቅቱ ፖሊሲና ዓላማ የተቀረጸው ለከተማ ኑሮ ባለን ፍቅር ነው!' የእሁኑ ውሳኔም ከዚህ ውጭ ሌላ ምንም አይደለም። ውሳኔው ግን ተመልሶ የሌላ ክርክር መነሾ ሆነ።

"ለሕብረት ግንባር ጥሪው ፈቃደኛ መሆናችንን እንዴት እንግለጽ?"

ዋናው ጉዳይ መስመሩን ስቶ ስለሄደ ለዚህኛው ክርክር ብዙም ፍላጎት አልነበረኝም።ብርሃነመስቀል እጁን አወጣ። አሁን ፊቱ ፈካ ብሎ ታየኝ። ክርክሩ በተወሰነ ደረጃ ተቀባይነት በማግኘቱ እንደተደሰተ ምንም ጥርጥር የለውም።

"ሸለቃ መንግሥቱ በሕብረት ግንባር ጥሪ ንግግሩ ያቀረበውን መርሐግብር መነሻ ወለል አድርገን መቀበላችንን በዲሞክራሲያ መግለጽ እንችላለን። ምክንያቱም የቀረበው መርሐግብር ጥቅል በመሆኑ ድርጅታዊ ነጻነታችንን አይነካም።" ፈርጠም አለ።

"እንዴዴ? ሰውየውን ምን ነካው? ብርሃነመስቀል አበደ እንዴ?" ግራ በመጋባት እርስ በእርሳችን ተያየን። ዘርዑ አሁን ትእግስቱ ያለቀ ይመስላል። ለሌላ ተናጋሪ እድሉን መስጠት አልፈለገም...

"ጓድ ረዘነ..." ብርሃነመስቀል ላይ አፈጠጠበት፤ "...ጓድ ረዘነ ምንድነው እያልከን ያለኸው? ደርግና

መኢሶን በአብዮቱ የተገኙ ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችን በዐዋጅ አግደዋል። የኢርትራን ጥያቄ በጦርነት ለመፍታት ራዛ ዘመቻን ዐውጀዋል። ያለ ምንም ሕግ ዜጎችን በኮሚቴ ውሳኔ እየገደሉ ነው። የሠራተኞችን የመብት ጥያቄ አንቀበልም ብለው በግልጽ አሳውቀዋል። ይህንን ለማሳየትም በአየር መንገድ ሠራተኛ ተወካዮችና በድሬዳዋ ላብአደሮች ላይ ጥይት ተኩሰዋል። ሕዝቡ በራሱ ያደራጃቸውን የአስተዳደር አካላት በግፍ አፍርሰዋል። ወጣቱ ያለምንም የፍርድ ሂደት በየቀኑ እየተያዘ በየእስር ቤቱ እየታጎረ ነው። ዜጎች ምን እንዳጠፉ ሳይነገራቸው እየተገደሉ ነው። ይህንን ግፍና በደል እኛም ትክክል ነው ብለን ተቀብለን ነው የደርግን መግለጫ የምንቀበለው?"

'መንጋ ከተማ አምላኪ...እውደልዳይ ሁሉ!' ጭስስ አልኩ።

ዘርዑ ያነሳው ክርክር ለሦስተኛ አቋም በር ከፈተ። አበበ ዋቅጅራና ዮሀንስ ብርሀኔ በቅደም ተከተል ተናገሩ። የሕብረት ግንባር ጥሪውን የምንቀበለው በቅድመ-ሁኔታ መሆን አለበት።" አሉ።አቅለሸለሸኝ። ብቻ አንድ ትንሽ የተጽናናሁበት ነገር አለ። ወደ ገጠር የመውጣት ጉዳይ በሚቀጥለው የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ በስፋት እንዲታይ መወሰኑ ነው። ከጥርጣሬ ጋር ተቀበልኩት። በተረፈ ሌሊቱ በገፋ ቁጥር ከርከሩ ስልችት አያለኝ ሄዶ ልቤ ወደ ፍቅረኛዬ አዘነበለ።

ንጋቱን የሚያበስረው የወፎች ጫጫታ ሲሰማ የክርከሩ ድምጸት ተቀይሯል። በግንባር ጥሪው ቅድመሁኔታዎች ላይ ስምምነት ተደርሷል። "ያለቅድመ ሁኔታ ጥሪውን እንቀበል" የሚለው የብርሃነመስቀል ሐሳብ ውድቅ ተደርጓል። አልምቀኝም፣ አልበረደኝም። ሁለቱም ወገን ተከራካሪዎች የእኔና የኢሳያስ አይደሉም። ማጠቃለያ ላይ መጭው የላብአደሮች ዓለምአቀፍ በዓል ተነሳ። ኢሕአፓ ለላባደሮች ድምጽ መሰማት የራሱን ድርሻ እንዲወጣ ተወሰነ። ይሄም ስሜት አልሰጠኝም። ንጋት ላይ ስብሰባው ሲያበቃ በየአቅጣጫው ሹልክ ሹልክ ብለን ተበታተን።

\###

ከኢሳያስ አንድ ላይ ሄደን ላንድሮቨሯ ላይ ስንሳፈር ዘርዑ እየሮጠ መጥቶ እግረመንገዳችንን ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አካባቢ የጽሕፈት እቃዎችን ጭነን እንድንሄድ አዘዘን። እቃው በሁለት ካርቶኖች መዘጋጀቱን፣ ትክክለኛውን ቦታና የሚያስረክበንን ሰው ማንነት ከኮድ መተዋወቂያ ቃል ጋር ሰጥቶናል። ቀጥ ብለን ወደ ጊዮርጊስ አመራን። ጮራዋ ፈንጥቃለች። ቤተክርስቲያን የሚሳለመው ሕዝብ እንደጎርፍ ይፈሳል። ወደ ሰሜን ሆቴል በሚወስደው መንገድ ከእሳት አደጋ መከላከያ ፊት ለፊት ከመንገድ ወዲህ ቆምን፤ ከደቂቃዎች በኋላ የሆነ እንቅስቃሴ ዐየን። በግራ በኩል ከአንድ አነስተኛ ኪዩስክ በር ላይ ከበሩ

ገባ ብሎ ሁለት ካርቶኖች ተቀምጠዋል። የሥራ ልብስ የለበሰች ወጣት ሴት አንደኛው ካርቶን ላይ ተቀምጣለች። ወደሷ ለመጠጋት መኪናዋን ወደ ኪዩስኩ አቅጣጫ አንቀሳቀስኳት።

ኢሳያስ ከመኪናዋ ወርዶ ልጂቱን ለሴኮንዶች አነጋገራት ብዙም ሳይቆይ አንዱን ካርቶን እሱ ሌላኛውን እሷ ይዘው መጡ። ፈጠን ብዬ ወርጄ የጀርባውን በር ከፍቼላቸው እቃው ተጫነና በሩን ስቆልፍ ልጂቱ ተመለሰች። እኔ ከተሳፈርኩ በኋላ ኢሳያስ እጁን እጸዳድቶ ሊሳፈር እግሩን ሲያነሳ፣

"ኢሳ—ያ—ስ! ኢሳ–ያ—ስ! አትሰማ—ም እንዴ!"የሚል የሴት ድምጽ ተሰማ።

የማውቀው ድምጽ መሰለኝ። ዞር ብዬ ሳይ የኔዋ ጉድ ብርክታዊት ናት...! ...እየሮጠች መጣች። ልትደርስበት ትንሽ ሲቀራት ኢሳያስ ዘሎ ተሳፈረ። በሩን እስከሚዘጋ አልጠበኩትም። እንደ ጥንግ በረርኩ_

# 18

የተፈጥሮ ሕግ ይለወጥ ወይም የኔ ስሜት ይፍጠረው አላውቅም። ቀናት እንደ እሳት አጥፊ ቀልብ ስተው ይበራሉ። በኢሳያስ አነጋገር 'ድሮ የምናውቀው ካላንደር ተቀይሮ ሳምንት ወደ ቀን የተለወጠ' ያህል ተሰማን፣ ፍጥነቱ። ግንቦት ቦታውን ለሰኔ አስረከቧል። ሰኔና ሰኞ የገጠሙበት ዓመት ስለሆነ በርካታ ኢትዮጵያውያን ቅር ብሏቸዋል ሲባል ሰምቻለሁ። ሰኔም ትእግስት የለው። ተጣድፎ ሮጦ ሐምሌን እየጠራ ነው። ሰኔና ሰኞ! ትውፊቱ ማርከሲዝም ሌኒንዝም ገና ብዙ ፈተና እንዳለበት አስታወሰኝ። ፈተናውማ ብዙ በጣም ብዙ ነው።

'ዋናው ነገር ተስፋ አለመቁረጥ ነው እንጂ...' በረጅሙ ተነፈስኩ።

ቢታኒያ ደረቴን ተንተርሳ ስለተኛች መገላበጥ አልቻልኩም። እልም ስምጥ ብላ ጥልቅ እንቅልፍ ተኝታለች። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጣ ልምድ ነው። ቀድሚያት ነቅቼ ከጭለማ ጋር ተፋጥጫለሁ። ውድቅት ላይ መጣል የጀመረው ዝናብ አሁንም አለ። ወይ አይጨምር ወይ አይቀንስ እኘኘኘ... እያለ ይወርዳል። እንቅልፌ ተመልሶ እንደማይመጣ ዐውቃለሁ። ቅጥቃጤውን ስለምፍራ ተመልሶ እንዲመጣም አልፈልግም። አእምሮዬ ያለፉት ወራት ኸጉርጉር ገጠመኞቼን እያበጠረ ይከካ ገባ።

'እናትዬ፣ ፍቅሬ...ቢታኒያ! የዕድሜ ልክ ጣጣ የሚተው ጭንቀት እየሆንሽብኝ ነው።' ተጠንቅቄ ግንባሯ ላይ ሳምኳት።

ከሚያዚያው የኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ማግስት ነበር፣ ዕለቱ። ለስድስት ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች ይቀራሉ። ጋራዡ በዓለምአቀፉ የላብ አደሮች በዓል ምክንያት ተዘግቶ ሠራተኞቻችን በሙሉ

አብዮት አደባባይ ወርደዋል። ደጀኔም ቁርስ አብረን ስንበላ ወደዚያው እንደሚሄድ ነግሮናል። ኢሕአፓን የመታው የበጀት ድርቅ የኑረዲንን ቢልቢላ ዳቦ በውኃ እንድንበላ አደረገን። ይሉኝታ እየያዘኝ ነው እንጅ እኔ እንኳን ችግር የለብኝም። ምግቤም አዳሬም ምኔም ከቢታኒያ ጋር ከሆነ ቆይቷል። ማንንም ተመልካች የሚያስገርመው የሁለታችን መተሳሰብ ሊደበቅ አልቻለም። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ የእናቷን ልብ አሸነፈው።

"አትሳቀቅ፣ ልጄ። ቢታኒያየን ወለድኳት እንጅ አልፈጠርኳትም። መፍጠር የእግዚአብሔር ነው። ገንት ጋር ከየትም ከየትም አምጥቶ ያገናኘን ፈጣሪ ነው። አንድ ያዘጋጀላችሁ መልካም ነገር ቢኖር ነው።" ካሉኝ በኋላ፣ "ልጄ፣ ላም ቀንዷ አይከብዳትም ይባላል። ከቢታኒያ ጋር አንድ ላይ ስትበሉ ሳይ በላችልኝ ብዬ ቅልል ይለኛል። አደራ፣ ስመረዬ...ባልወልድህም ከአሁን ወዲያ ልጄ ነህ። ተሳቀህ ወይ ደ'ሞ በይሉኝታ አንዲት ጉርሻም ብትሆን ጥለኻት ከበላህ ልጄ አይደለህም..."

የሐሳብ ቀዘፋዬን አቅጣጫ ወደ ጋራዥ መለስኩት...

እኔና ኢሳያስ ብቻ ቢሮ ቁጭ ብለናል። እሱም ብዙ አልቆየም። የድርጅት ተልእኮ እንዳለበት ነግሮኝ ተለይቶኝ ወጣ። ወደ በዓሉ እንደሄደ ዐውቃለሁ። እሱ ከሄደ በኋላ አንድ ነገር ትዝ አለኝ። አብዮት አደባባይ በበዓሉ ሥነ ሥርዐት ላይ ኢሕአፓ ደርግንና መኢሶንን ያወግዛል። ይሄንን ለማስፈጸም የአዲስ አበባ ኢሕአፓ በይነቀጠና ኮሚቴ ታዟል። ስለዚህ የጋራዡ ሠራተኞች በሙሉ የሄዱት ለዚህ ተልእኮ መሆኑ ገባኝ። ከፖሊስ ጋር ግጭት እንደማይቀርም ገመትኩ። ልክ ይሄንን ሳስብ መንፈሴ ድንገት እርብሽ አለ...

"ቢ--ቲ--የስ?" ቅፍፍፍ ብሎኝ ከወንበሬ ተሸቀንጥሬ ተነሳሁ፣ "ሄዳብኝ ይሆን?" ጭንቅላቴ እንደጉሽ ጠላ ድፍርስ አለ።

የከርስቶስን ምስል ሳነሳው ፍጥነቴ ሌላ ነው። ቀዩ በር ለመድረስ እርምጃዬ የኤሊ ጉዞ መስሎ ታየኝ። በፍጥነት ከፍቸው ገባሁ። ግቢው ውስጥ የሚሰማኝ የዳግላስ ጩኸትና የወይዘሮ ማስተዋል የሳል ኪርኪርታ ብቻ ነው። ወደ ቢታኒያ መኖሪያ ክፍል ዐየሁ። ግጥም ተደርጎ በሰረገላ ቁልፍ ተቆልፏል። ወይዘሮ ማስተዋልን ይደነግጣሉ ብዬ ስለፈራሁ አላነጋገርኳቸውም። ተመልሼ ወጥቼ በሩ ላይ ወገቤን ይዤ ቆምኩ። ምን እንደምል...የት እንደምሄድ...ምን እንደማደርግ ግራ ግብት አለኝ። ለደቂቃዎች ቆሜ ቆይቼ ወደ ጋራዥ ለመሄድ ራመድ ስል ከጀርባዬ በር ሲከፈት ተሰማኝ። የግቢው ዋናው የፊት ለፊት በር ነው። ቆም ብዬ ጆሮዬን ደቀንኩ። ትክክል ነኝ፣ የቢታኒያን መኖሪያ ቤት በር ድምጽ ጠንቅቄ ነው

የማውቀው። የሩጫ ያህል እየከነፍኩ ሄጄ እንደገና ገባሁ...

'አዎ፣ ልክ ነኝ_ፍቅሬ መጥታለች። ሰልፍ ሄዳ ነበር ማለት ነው?' ልቤ በድንጋጤ ትር ትር አለች፣ መልስ ግን አልነበረኝም።

በሄድኩበት ፍጥነት ኳኳ አድርጌ ወደ ቤቷ ዘው አልኩ። ከመጀመሪያው ከፍል አልጋው አጠገብ ቆማ ልብሷን ስትቀይር ደረስኩ። ሁለት ጅንስ ሱሪዎች ደራርባ ለብሳ እንደነበር በተዘበራረቀው ልበናዬ አስተዋልኩ። እጆቿንም በውስጥ በኩል የደም ግፊት መመርመሪያ በሚመስል ሽራ ነገር ሸፍናቸዋለች። ሰላምታ እንኳን አልሰጠኋትም። ፊቴ በጥያቄ ማእበል ተመትቶ ልውጥውጥ ብሎባት እንደሚሆን ገምቻለሁ። ፊት ለፊቷ ቆሜ ግዳይ እንደጣለ ዐውሬ አፈጠጥኩባት...

"ምናባህ ሆንከ? ሞሮን! የት ቆይቼ የመጣሁ መስሎህ ነው?" የራሷ ባልሆነ ድምጽ ጉዳዩን የግላችን ልታደርገው ሞከረች።

የበለጠ አፈጠጥኩባት። የፊቷ ገጽ ትክክል አይደለም። ጠቆር ብላለች፣ ጸጉሯ ፍልስልስ ብሎ አቧራ ቅሟል። በዚህ ላይ ተረብሻለች። ሁኔታዋ ልክ ሲሰርቅ የተያዘ ሰው ዓይነት ሆነብኝ። ግራ እጇን የሸፈነችበትን ሽራ ልታነሳ ስትሞክር ደግሞ በኃይለኛ የሕመም ስሜት ፊቷን ጭምድድ አድርጋ አአአአ... አለች። ስቃይዋ የበለጠ ጉልበት ጨምሮ መንፈሴን እንደጦር ወጋው። በሁለት እግሯም በትክክል መቆም አልቻለችም። እያነከሰች እንደሆነ ገባኝ። የሀሞት ከረጢቴ በንዴትና ከድንበሩ በወጣ ቁጣ ቷ ብሎ የፈነዳ መሰለኝ...

"ነገሪ---ኝ፣ የት ነው ቆይተሽ የመጣሽ---ው?" መላ ሰውነቴ እየተንዘፈዘፈ ተጠጋኋት።

ቢታኒያ የቁጣዬን ጥልቀት በደንብ ተረድታዋለች። ነገር ግን ነገሩን ማባባስ የፈለገች ፟ትመስልም። በፈገግታም በቀልድም በምንም ብላ ቀላል ልታደርገው ስትጥር ዓይኗ ላይ አነበብኩት።

"ምናባህ ልትለኝ ነው? ኧረ ይሄ ሞሮን! ሆሆ--ው፣ የተጋባን ጊዜማ ሽመልህን ይዘህ ነው የምትጠብቀኝ... ።"ወዲያው ደግሞ ሐሳቧን ቀይራ "ናማ ጌታዬ፣ አንዴ ልደገፍህ..." ስትለኝ ከላይ ከላይ እያናፋሁ ሄጄ ደረቷን ያዝኳት።

ልብሶቿን ከውስጥ ሱሪዋና ከጡት ማሲያዥዋ በስተቀር ውልቅልቅ አደረገቻቸው። አሁን ምሥጢሯን መደበቅ አልቻለችም። በዓሉ ላይ ተገኝታለች። የእኛን ጋዜጦች ዲሞክራሲያንና ላባደርን ስትበትን ውላ

መምጣቷን በተዘዋዋሪ አመነችልኝ። ቅጥል... ንድድ... ጭስስ አልኩ። ጥይት ተተኩሶ ሰልፉ ሲበተን ሀ'ገሬ. መሀል በተደጋጋሚ ወድቃለች። በመጨረሻም ከፖሊስ ቆመጥ አላመለጠችም። ባለፈው የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ብዙም ትኩረት ያልሰጠሁት ማሳሰቢያ በዘርው ክህሽን ሲነገር ሰምቻለሁ። ወዲያውኑ የመጣልኝ እሱው ነው...

"ኢሕአፖ አጠቃላይና ብሔራዊ ለሆነ የከተሞች ሕዝብ አመጽ ራሱን ማዘጋጀት አለበት።"

ምሳ አልበላም ብዬ ብዙ ለምናኝ ነው የተቀመጥኩት። የድርጅቴ አመራር አምስት ስድስት ጊዜ ስህተት ሰርቶ ታየኝ። ቅሬታዬን በተደባላለቀ መንፈስ ውስጥ ሆኜም ላደራጀው ሞከርኩ...

'የከተማን ሕዝብ በተለይ ወጣቱን ለአመጽ ማነሳሳት ምን ማለት ነው? አዲስ አበባ ውስጥ ደጋፊውና ተቃዋሚዋው ተለይቶ አይታወቅም። የዕለት ኑሮውን ለመደጎም ደፋ ቀና የሚል ሕዝብ ነው የሚኖርበት። ድርጅቴ ይሄንን ሕዝብ አነሳስቶ በደርግ ላይ ጫና ለማድረግ እየሞከረ ነው። የምኝነት ሁሉ ትልቁ ምኝነት ነው። የትም አብዮት የተካሄደበትን የብዙኃን ገበሬ አገር ማንም ሊመለከት ይችላል። የከተማ ሕዝብ ተሳታፊና ደጋፊ እንጂ ታሪክን የሚያራምደው ገበሬ ነው። ድርጅቴ ታዲያ ይሄንን የተሳሳተ ውሳኔ የወሰነው ለምንድነው? በቃ፣ ምክንያቱ ከደርግ አፍንጫ ሥር አንድ ከተማ ውስጥ አብሮ ስለሚኖር ነው።'

እንደ ፍም የሚጠብሰኝ ብስጭቴ ጉልበት ጨምሮ ተመላለሰብኝ። ዐይኔን እያጉረጠረጥኩ ወደ እሷ ተመለከትኩ...

"ቤቲ፣ ለምን? እንዳትይኝ። በዛሬው ውሎሽ በጣም ቅር ብሎኛል። በዚህ ለውጥ የሚመጣ ቢሆን ኖሮ ለመሞት የሚቀድመኝ አይኖርም ነበር። ትክክል አይደለም። ከዚህ በኋላ ምን እንደሚያሠሩሽ..." ጭርሼ መናገር አቅቶኝ እንጠልጥዬ ተውኩት።

"እንጃባህ፣ ሞሮን! ማንም የፈለገውን የሚያሠራኝ እንስሳ መሰልኩህ እንዴ?!" የውሽት ቁጣ ልትቆጣብኝ ፈለገች።

ቀጥታ ባናነሳውም ከድርጅታችን የትግል ስልት የተለየ አቋም እንዳለኝ ሳትረዳው አልቀረችም። ደፍረን ፍርጥርጥ አድርገን ሐቁን መነጋገር ግን አልቻልንም። የምንግባባው ሁሉንም ነገር በጥቅል እያወራን ነው። ሁለታችንም የኢሕአፓን ሕቡእነት ሕግ መድፈር ከህይት ሆኑብን።

"ያ—ሳ--ዝ—ና—ል!!" ብዬ ረጅም የመከፋት ትንፋሽ እንደገና ተነፈስኩ።

ከሰዓት በኋላ ወደ ጋራዥ አልተመለስኩም። ብከንከን እያልኩ የቢታኒያን የተጋጋጡ የሰውነቷ ቦታዎች...የፖሊስ ዱላ ያረፈበትን የጀርባዋን አካባቢ...ስነካካት ሕመም የሚፈጥርባትን አካሏን ሁሉ... በሞቀ ውኃና በመታሻ ቅባት ሳሻት ዋልኩ። ነገሩ በዚህ ቢያበቃ ባልከፋኝ ነበር። ከዚያ ወዲህም ቅሬታ የሚፈጥርብኝ ነገር መጣ። ቢታኒያ በሳምንት አንድ ወይም ሁለት ቀናት ከሰዓት በኋላ አልም ብላብኝ ትውላለች። ምሽት ላይ ስትመጣ ታዲያ ሰውነቷ ድቅቅ ብሎ ትዝላለች። ፊቷም ጥቁርቁር ይልና የደረቀ ላብ ግንባሯና ማጅራቷ አካባቢ አያለሁ። ገላዋን መታጠብ ሁሉ እየደከማት እኔ እጥባታለሁ። ማታ ስንተኛ ታዲያ በቁመቷ ልክ ዥው ብላ ትወድቃለች። የእንቅልፏ ጥልቀት አንዳንዴ ኮማ የገባ ህመምተኛ ትመስላለች...

'ወታደራዊ ሥልጠና እየሰጧት ይሆን?' ብዬ አስብና፣ "ቤቲዬ፣ እኔ'ኮ በጣም እየተጨነኩ ነው። በጣም ግራ እየገባኝም ነው። የት ቆይተሽ ስትመጭ እንደዚህ እንደምትሆኚ ሊገባኝ አልቻለም..." ትከ--ዝ እልባታለሁ።

"እዚህ የወጣቶች የአካል ልምምድ ማእከል አለ'ኮ። እዛ ቆይቼ መምጣቴ ነው።ሰሙ-ዬ፣ አትጠራጠረኝ..."

አልቀበላት ስል በአባቷ...በእናቷ...በሚካኤለ የመህላ መዐት ትምልልኛለች። በመጨረሻ "ስመረን ያሳጣኝ!!" የእጇን መዳፍ ትመታዋለች። እንዲህ ስትለኝ መለስ ይልልኝና ጨዋታ እንጀምራለን። በድርጅቴ ላይ እምነቴ የተወሰኑ ግራሞች ተሸራርፈው መቀነሱ ግን አልቀረም። ያም ሆኖ እኔም ሆንኩ ኢሳያስ ለራሳችን የተገባባነው ቃል አለ። ኢሕአፓ የቱንም ያህል ይሳሳት፣ ታማኝነታችንና ታዛዥነታችን ሁሌም ይቀጥላል። በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ያለ ድርጅት መኖር አንችልም። የእርምት ጥረታችንን በልዩ ልዩ ዘዴ እንገፋበታለን።

###

ቢታኒያ አሁንም ደረቴ ላይ ለጥ እንዳለች ነው። ዝናቡም መጣሉን ቀጥሏል። ከቢታኒያ ወደ ሌሎች ያለፉት ወራት የፖለቲካ ከራሞቴና ገጠመኜ ቅኝቶች አለፍኩ።

የቀድሞዋ ፍቅረኛዬ ብርከታዊት ታወሰችኝ። ለመናገር የገፋፋኝን ባላስታወስውም ብርኪቲ ጮኛዬ እንደበረችና አሁን ላንገናኝ በድርጅት ትእዛዝ መለያየታችንን ለሸዋዬ ሹክ ብያት ነበር። የከፍሉ ተፈራ ዜና ምሥጢሩን እንዳወራት ሳያደፋፍረኝ አልቀረም። ሸዋዬ ትመነኝ አትመነኝ ግን ትዝ አይለኝም።

ባለፈው ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ኢሳያስን እንዴት እንደለየችው እንቆቅልሽ ሆኖብናል። በመመሳሳል ሥራው ላይ አንድ ጉድለት እንደነበረ ተግባብተናል። መቼም በአካሄዱ ብቻ ልታውቀው አትችልም። ያም ሆነ ይህ ከዚያ ቀን ወዲህ ቅር ብሎኝ ሰነበተ። ቅሬታዬ ግን በትክክል ምን እንደሆነ አላውቅም። ምናልባት መኢሶንን መቀላቀሏ ሊሆን ይችላል።'ብርከቲዬ፣ እውነት የመኢሶን ካድሬ ሆነሻል? ከልብ አምነሽበት ነው ወይስ እኔን ለመበቀል?' መልስ ያላገኘሁለት ጥያቄ ነው።

እርግጥ ነው፣ ፍቅራችን አከትሞለታል። ቢሆንም ከአንጀቴ በቀላሉ ቁርጥ አድርጌ አውጥቼ ልጥላት ያልቻልኩበትን ምክንያት ጠየኩ። አሁንም መልስ የለኝም። የብርከቲ ነገር ሌላ ነገር አስታወሰኝ።

ሸዋዬ ከቀናት በኋላ አዲስ ነገር ይዛብኝ መጣች።ኢሕአፓ በገጠመው ከባድ የበጀት ቀውስ ምክንያት ሠርታ የምታቀርብልን ነገር አጣች። ባንክ ሄጄ ካወጣሁት ገንዘብ ብድሬን ከፍያለሁ። የቀረውን አስቤዛና የታይፕ ወረቀት እንድትገዛበት ሰጠኋት። ደስ ብሏት ተቀብላኝ ወዲያውኑ ገበያ ሄደች። ደጀኔ ኤን ዱዌ የጭነት መኪናውን አስነስቶ አትከልት ተራ ወሰዳት። እዛ ቆይተው አራት ኪሎ ሄዱ። ኢሳያስ የጨጓራ ህመም ስላለበት ለእሱ የሚስማማ ምግብ ለመግዛት ሱፐር ማርኬት ፍለጋ ነው አካሄዳቸው። በጊዜ ተመለሱ። ምሽት ላይ ለመመሳሰል ያህል አብሬያቸው ለአራት ቁጭ አልኩ። ጥሩ ምግብ አዘጋጅታለች። በልቼ ከሄድኩ የቢታኒያን ቁጣ እፈራለሁ። "አብሬያችሁ ነኝ" ለማለት ያህል ብቻ ጥቂት ጉርሻዎችን እየወሰድኩ እናወራለን...

"አንተ አላምረው፣ ጎ--ሽ፣ የረሳሁት ነገር ትዝ አለኝ።" ብላ ሸዋዬ ደጀኔንና እኔን ተራ በተራ እየት እየት አድርጋ፣ "ያች ብርከታዊት የምትባል ጋዜጤኛ እውነት ጓደኛህ ነበረች?" ጠበቅ አድርጋ ጠየቀች።

"እውነት ልበል ሐሰት...?" እያልኩ ሳመነታ ደጀኔ በወሬው ነቃ ብሎ ጣልቃ ገባ።

"እንዴ! እንዴ! ዛሬ አራት ኪሎ 'ብርከቲዊት አዳነ ማለት ይህች ናት' ብላ እንዲት ባለ ሱቅ አሳየችን'ኮ። እኔ'ኮ የሆነች አጭር፣ ጠይም፣ ጎረድራዳ ምናምን ነበር አድርጌ የምስላት። በጣም ቆንጆ ሆና አገኘኋት። ከቢታኒያ ግን አትደርስም። አይደል፣ ሸዋ?" ብሎ የሸዋዬን ድጋፍ ለማግኘት ወደ እሷ ዘወር ብሎ ጠየቃት።

ደጀኔ ወሬውን ከየት እንዳገኘው መጠየቅ አልፈለኩም። የባንክ ደብተር እንዲያመጣልኝ የላኩት ቀን አንድ ሱቅ ውስጥ ከሰፈር ሰዎች ጋር እያወራ መዋሉን ነግሮኛል። ከብርከቲ ጋር ጧትና ማታ ተጣብቀን

ስለምንሄድ ብዙ ሰው ያውቀናል። ይሄንን ያየች እንዷ የሰፈር ልጅ ልትነግረው እንደምትችል መገመት አልቸገረኝም። ችላ ብዬው እኔም ወደ ሸዋዬ ዞርኩ...

"መኢሶን መሆኗ አበሳጨኝ እንጂ በጣም ቆንጆ ናት። የኪዩባ ወታደር ቱታ ለብሳለች...ማአ ኮፍያ አድርጋለች...ትልቅ የወገብ ቀበቶ አሥራለች...ሽጉጧን ወገቧ ላይ ሰክታለች...። ከመኪና ወርዳ ተራማጅ መጻሕፍት ቤት ስትገባ ሰው ግልብጥ ብሎ አያት። ከምንም ሳትቆጥረው አልፋ ገባች። የሆነ መጽሐፍ የእሥራኤል ጅት አብራሪ ሴት ወታደር ሥዕል አይቼ ነበር። ልክ እሷን..."

ፊቴ ላይ ይነበብ አይነበብ አላውቅም። ወሽመጤ ቁርጥ አለ። የወንድ ጓደኛ ይዛም እንደሚሆን አልጠተራጠርኩም። ከዚህ ያዝ ለቀቅ ከሚያደርገኝ ቅናት የበለጠ የቆረቆረኝ ግን ሕዝብ የሚያየው መኢሶን መሆኗ ነው። ከንከን አድርጎ ከነከነኝ። መኢሶንን በብዙ ምክንያቶች ልክ የአባቴ ጉዳይ ደመኛ ያህል እጠላዋለሁ። በጥልቅ ማሳ ላይ የበቀለ አረም መስሎ ይታየኛል...

'መንጋ ጥንብ እንሳ ሁሉ! ከአነርሱ ዲግሪ የየኔታ ጥምጣም ይሻለኛል...' ብስጭት አልኩ።

ኢትዮጵያ ሰማይ ላይ በዚህ ወቅት የተሳከረ የፖለቲካ አየር ነግሶበታል። መኢሶን ደግሞ ግራ የተጋቡና የተድበሰበሱ ሐሳቦችን እያቀረበ ሕዝቡን የበለጠ ግራ በማጋባት ከፍ ያለ ድርሻ ወስዷል። ዘርው ከነገረኝ ታሪክ በተጨማሪ ይህንን በደንብ የተረዳሁት አዲስ ዘመን ጋዜጣ በደራሲና ጋዜጠኛ ብርሀኑ ዘሪሁን በሚዘጋጀው "የአብዮት መድረክ" ላይ የመኢሶንን ክርክር ከተመለከትኩ በኋላ ነው።

'መንጋ ከሀዲ!' ከዚያ ወዲህ መኢሶንን የምጠራበት ስም ነው።

ኢሕአፓ "የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥትና ዲሞክራሲ ያለገደብ" የሚሉ መፈክሮቹ ትክክል መሆናቸውን ገልጿል። የእኛው ብርሃነመስቀል ረዳ በብእር ሥም ጋዜጣው ላይ ተነተነ። የጽሑፉ ሥነ-አመክንዮአዊና ሥነ-ዕውቀታዊ ብቃት እጅግ አስደማሚ ጉልበት ነበረው። መኢሶኖች በጽሑፉ ሳይደናገጡ አልቀሩም፤ "እውነቱ ፈረደ" በሚል የብእር ሥም አጸፋ መስጠት ጀመሩ። በተለይ "ዲሞክራሲ ያለ ገደብ" መፈክርን የተቃወሙበት አቀራረብ ጨጓራዬን አቁስሎታል...

"የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይነቃ፣ ሳይደራጅና ሳይታጠቅ የዲሞክራሲ መብቶችን መልቀቅ እጅግ አደገኛ ነው።የሚጠቀመው ቢኖር ለሥልጣን ያቆበቆቡ አናርኪስቶችን ነው። እውነተኛ አብዮታውያን ኃይሎች በዚህ ወቅት መጠየቅ ያለባቸው ሕዝቡን ስለማንቃትና ስለማደራጀት እንጂ በጊዜያዊ መንግሥት ላይ ጊዜያዊ መንግሥት እንዲቋቋም መሆን የለበትም። ...ሕዝቡን በማንቃት ተግባር ላይ እንቅፋት የሚሆኑ

ኃይሎች መታሰር ይገባቸዋል..."

ይህንን መልስ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም አየር ላይ ቀብ አደረጉት። በየፋብሪካው እየዞሩ ሰበኩት። የሰሞኑም የደርግ ፀረ-ኢሕአፓ ፕሮፓጋንዳ የየዕለቱ ድግምት ይሄው ሆነ።

'መንጋ ከሀዲ!' አሁን ራሱ በዚህ ሰዓት ሳስበው ብልጭ አለብኝ።

'የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ከቆየ ሥልጣኔውና ባህሉ ጋር አዛምዶና አጣጥሞ መጠቀም የማይችል የከብት መንጋ መሰለው እንዴ? ለመሆኑ ዲሞክራሲ እንደ ግድብ ውኃ ታቁሮ "አሁን ልቀቀው!" ተብሎ የሚፈስ የቁጠባ ምርት አደረገው እንዴ? የኢትዮጵያ ሕዝብ በደቡብና በመሀል የጥንታዊው የገዳ ሥርዐት ባለቤት አይደለም፣ እንዴ? በሰሜን የጥንታዊ ፍትሀነገሥትና የነጻ ዳኝነት ሥርዐት ፈጣሪና ባለቤት አይደለም? በአምስቱ ዓመቱ የጠላት ወረራ ወቅት የጦር አበጋዞቹን በምርጫ እየሰየመ የተዋጋና አገሩን ነጻ ያወጣ ሕዝብ መሆኑ ቀረ? አሁንስ ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘጠና በመቶውን ችግሮቹን የሚፈታው በአካባቢ ሽምግልናና ዳኝነት መሆኑን መኢሶን አያውቅም?'

ብስጭቱ ይበልጥ እየናረ እንደ ካውያ አጋለኝ። ከመኢሶን ጋር የገባሁትን የሐሳብ ጦርነት በውስጤ ቀጠልኩ...

'ለመሆኑስ መኢሶን ከሀዲው "ሕዝቡ መጀመሪያ ይንቃ" የሚለው 32 ሚሊዮን ሕዝብ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን እስከሚያጠናቅቅ ነው ወይስ ዩኒቨርስቲ እስከሚገባ? ሕዝቡ መንቃቱንስ "ኤክስ" ወይም "ራይት" እያለ የሚለካውና ያኔ የተገደበው ዲሞክራሲ እንዲለቀቅ የሚወስነው ማን ነው? የአብዮቱ ባለቤት የሆነው ራሱ ሕዝቡ መሆን የለበትም? የኢትዮጵያ ሕዝብ በታላቅ ጨዋነት ሥር ነቀል አብዮት አካሂዶ ሥርዐት የለወጠው ደርግና መኢሶን መርተውት ነው? የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ከቆዩ እሴቶች ጋር እያዛመደ ከቀን ቀን ይለማመደዋል እንጂ እንዴት እንደ ኳስ ጨዋታ ወይም እንደ ሩጫ ውድድር የዲሞክራሲ ፊሽካ እስከሚነፋ ጠብቅ ይባላል?' ንድድ አለኝ።

'እና ብርከቲዬ ጨክነሽ የእነዚህ ባንዳዎች አባል ሆንሽ?' በጣም ከፋኝ።

###

መኢሶን ከከፍተኛች ምርጫ በኋላ "የአብዮት ጥበቃ" ኮሚቴዎችን በየቀበሌው እያደራጀ ነው። ደርግ በተለምዶ "አፈ. ሾል ጓንዴ ወይም ዲሞትፈር" የሚባል ጠበንጃ ከሕንድ አገር ገዝቶ አስገብቷል።

የአብዮት ጥበቃ አባላት በሙሉ እሱን ታጠቀዋል። ከሦስት እስከ አምስት ሳምንታት የዘለቀ ወታደራዊ ሥልጠናም ተሰጥቷቸዋል። ምልምላው ገና የሚቀጥል ይመስላል።

አሁን ዝናቡ እየቀነሰ ነው። ቢታኒያ ብትት ብላ ከተወራጨች በኋላ አቅፌ ውስጥ ገባች። አልፎ አልፎ መቃዤትም ይፈታተናታል። የምትናገረው ግን በደንብ አይሰማኝም።የሒሳብ ቀዘፋዬ ትኩረቱን ቀየረ። ባለፉት ሁለት ወራት አካባቢ የኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ አላደረገም። የጸጥታ ሁኔታው ከቀን ቀን እየከፋ መምጣቱ ነው ይፋዊ ምክንያቱ።ብርሃነመስቀል በበኩሉ ይህንን አይቀበልም። ከእኔ ጋር ተራርቀናል። ኢሳያስን "መግለጫ የሰጠንበትን የሕብረት ግንባር ጥሪ ሂደቱን የማዘግየት ቢሮክራሲያዊ ዘዴ ነው..." ብሎታል።

ቢታኒያ እንደገና ብትት ብላ ስትነቃ ትኩረቴን ወደ እሷ አዞርኩ። በዳበሳ ፈልጋኝ ሆዴን ስትነካው ዞር ብላ ጥምጥም አለችብኝ። ሰሞኑን እየደከማት ስለምትመጣ የፍቅር ጨዋታ ቀንሰናል። እንዲያውም ትተናል ቢባል ይቀላል። አሁን ልታካክስልኝ ሳይሆን አይቀርም። በጣም ጥብቅ አድርጋ ይዛኝ ትስመኝ ጀመር። የአእምሮ ሁኔታዬን አስተካክዬ አጸፋውን መለስኩላት። በቀዘቀዘው አየር ሥር ሁለታችንም መጋል ጀምረን ደስ የሚል የፍቅር ጨዋታ ውስጥ ገባን።

እኛኝ... የሚለው ዝናብ ሳይቆም ንጋት ሆነ። ቀድሚያት ተነስቼ ልብሴን ስለባብስ እሷም ፈጠን ብላ ተነሳች...

"ሆድዬ፣ ወዴት ነው በዚህ ቅዝቃዜ?" እንደቀልድ ጠየኳት።

"በምትኩ፣ አንድ ሥራ ነበረኝ ረስቼው። ስሙዬ፣ ልቤን አጠፋኸው'ኮ! በል መኪና ይዘህ ና፤ ፒያሳ አድርሰህ ትመልሰኛለህ። ቶሎ በል፣ሆዴ...በጣ---ም ዘግይቻለሁ..." ጥድፍድፍ አለች።

የድርጅት ሥራ መሆኑን መገመት አልከበደኝም። ፍቅረኛዬን ለአደጋ እያጋለጡብኝ ነው። ግን ምን ላድርግ? ትካዜ ገባኝ። አብረን እንድንሄድ ስትጠይቀኝ ትንሽ ይሻለኛል። መሣሪያ ቢደግኑባት ቀድሜ እጥልላታለሁ። ብትወድቅ አነሳታለሁ። ብታመልጥ ይዣት እሰወራለሁ። መኪና ለማምጣት ወደ ጋራዥ ሄድኩ። «ፊያት-127ቷን» እየነዳሁ ስመለስ በግቢው የጎን በር በኩል ጠበቀችኝ። ወደ ፒያሳ...

የኑረዲንን ዳቦ ቤት ስናልፍ ዝናቡ ጨመሮ አስፋልቱ ውኃ ተኛበት። ፒያሳ ስንደርስ ወደ ጣይቱ ሆቴል ታጥፈን ወደ ፊት ለፊት ሄደን አንድ ቪላ ቤት በር ስንደርስ ቆምን። ቢታኒያ ልትወርድ በሩን ከከፈተች በኋላ በድንጋጤ "ወይኔ ጉዴ!" ብላ መልሳ ዘጋችው።

"ምንድነው፣ ፍቅሬ? ምን ተፈጠረ?" ብዬ በእሷ በኩል ባለው የመስኮቱ መስታወት ወደ ውጭ

ተመለከትኩ።

ትልቅ ቪላ ቤት ነው። የግቢው አረንጓዴ በር እስከ እንጦሉ ተከፍቷል። አስር የሚሆኑ ፖሊሶች በሩ ላይና ግቢው ውስጥ ይተራመሳሉ። እጆቻቸው በካቴናና በሰንሰለት የታሠሩ ሁለት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ቤቱ በረንዳ ላይ ተደርድረው ቆመዋል። በረንዳው ላይ ሁለት አደፍርስ ማባዣዎችና አራት የታይፕ መጻፊያዎች ተቀምጠዋል። ለሥርጭት የተዘጋጀ የዲሞክራሲያ ጋዜጣ ክምር ታየኝ። 'ልጆቻችን ተበልተዋል!' በድንጋጤ ሞተር አስነስቼ ማርሽ ሳስገባ አንደኛው ፖሊስ ከሌሎቹ መሀል ነጠል ብሎ መጣብን...

"ማነህ፣ ቁም፣ እንዳትንቀሳቀስ!" የለበሰውን የዝናብ ልብስ ከጉንጮቹ አካባቢ እየሰበሰበ በጩኸት አዘዘኝ።

አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ ራሴን ነገርኩት። ስጋቴ ሕቡዕነታችን ይጋለጣል የሚል አይደለም። ለምን በዚህ ቦታና በዚህ ሰዓት እንደተገኘን ለማወቅ ሊይዙን ይችላሉ። ቢታኒያ ቢጫ ቦርሳ ውስጥ ምን እንዳለ አላውቅም። እኔ ሽጉጥ ይዣለሁ። ፍተሻ ካደረጉ ሁለታችንም ጥብስ መሆናችን ነው። የእሳት እራት! "አንድም ቃል ትንፍሽ እንዳትይ!" በማስጠንቀቂያ አፈጠጥኩባት።

ፖሊሱ መጀመሪያ በእሷ በኩል ያለውን በር አስከፈተ። ትኩር ብሎ በአንግዳ አተያይ ተመለከታት። ቢታኒያ ምንም ሳይመስላት መልሳ አተኮረችበት። ቁንጅናዋንና አለባበሷን ሲያይ ምናልባት ያልጠበቀው ዓይነት ሰው ሳትሆንበት አልቀረችም። መታወቂያ ሲጠይቃት የቀበሌ መታወቂያዋን ሰጠችው። አገላብጦ ዐይቶ እንደገና ቀና አለ...

"በዚህ ሰዓት እንዴት ወደዚህ መጣሽ? ማለቴ ምን ልትሠሪ መጣሽ?" ኮስተር ለማለት ሞከረ።

"ጋራዥ አለኝ። እሱ የጋራዤ ሠራተኛ ነው።" ወደ'ኔ አመለከተችው፣ "የመኪና መለዋወጫ እቃ ግዥልኝ ብሎኝ ልገዛ መጣሁ። ያ ነበር ሱቁ፣ ተዘግቶ ስናየው ጊዜ ቆምን..." በጣም ተረጋግታ መለሰችለት።

ከጭንቅላቷ እስከ እግር ጥፍሯ ብጥር አድርጎ ካያት በኋላ ቀ—ስ አድርጎ መታወቂያዋን መልሶላት ዞር አለ።

ክርስቶስ ተመረመረ፣ ዲያቢሎስ ታሰረ! ዐይኔ ያየውን የነጻነታችንን መመለስ ማመን አልቻልኩም። ወደ ግራ ታጥፌ መኪናዋን እንደ ጥይት አስወነጨፍኳት...

# 19

ቀናት እየነጎዱ ነው።

ከሰዓት በኋላ ኢሳያስን መኖሪያ ከፍሉ ትቼዉ ወደ ምድር ቤት ወረድኩ። ለአጭር እረፍት አልጋዬ ላይ ጋደም እንዳልኩ ወዲያዉ ልብ የሚያሸብር ዝናብ መጣል ጀመረ። አዲስ አበባን የጥፋት ዉሃ የሚመስል ዶፍ ይነርታት ይዟል። ሐምሌ ከባድ ክረምት ይዞ እንደሚመጣ ወይዘሮ ማስተዋል ከልምዳቸዉ ነገረዉናል። ከነገር ነገር የሐሳብ ማአበል ይዞኝ ጥርግ አለ። ለእኛ ኢሕአፓዎች ከአየር ጸባዩ ይልቅ ፈተናችን ፖለቲካዉ ነው። ጨርሶ ምቾት አይሰጥም። በደርግና በመኢሶን በኩል የሚያበሳጭ ነገር አለ። ኢሕአፓን ችላ ብለዉ በቀበሌና ክፍተኛ ማኅበራት ማደራጀት ላይ ሙሉ ትኩረት አድርገዋል።

ባለፈው የሚያዚያ የማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ መሠረት ለኅብረት ግንባር ጥሪ በዲሞክራሲያ በኩል መልስ ሰጠን። አምስት ቅድመ ሁኔታዎች አስቀድመናል። "እነርሱ ከተሚሉልን ልንተባበር ዝግጁ ነን" አልን። የተሰጠን መልስ የዕድሜ ልክ ጸጸት ሆኖ ቁጭ አለ።መኢሶን ቀደመ...

"ኢሕአፓን ለሕብረት ግንባር ጥሪዉ ማን ጋበዛትና ነዉ ተኳኩላ የቀረበችዉ? ይህ የኢሕአፓ ፖለቲካ ቅልዉጥና የግንባር አመሠራረት ሂደቱ ምን እንደሚመስል ካለመረዳት የመጣ ችግር ነዉ..." ከሰማሁበት ቀን ጀምሮ ሕመምተኛ ሆኛለሁ።

ደርግማ ጭራሽ ከምንም ሳይጥፈን ዝግት ነው ያደረገን። ስህተት ነው የተሠራው። የግንባር ጥሪዉ ኢሕአፓን እንደማይመለከት ለማወቅ ነብይ መሆን አያስፈልግም። የሻሊቃ መንግሥቱ ኃይለማርያምን የሰሞኑን ዥግግር ሙተንተን የሚችል ማንም ሰዉ በቀላሉ ሊደርስበት አያዳግተዉም። ኢሕአፓን ልክ እንደ ግል ጠላት ነከሰዉ ይዘዉታል። ከደርግና ከመኢሶን ይልቅ ያበሳጨኝ ግን የራሳችን ሰዎች ናቸዉ።

በተለይ ብርሃነመስቀልና ጌታቸዉ ማሩ ብግን ነዉ ያደረጉኝ።ይህንን ተራ ሀቅ መስማትም መቀበልም አልፈለጉም። እናም የመኢሶን መሳቂያና መሳለቂያ አድርገዉ አዋረዱን። "ላገባህ አልፈልግህም፣ ባለትዳር ነኝ..'' ብላ እምቢ ያለችን ሴት ካላገባሽኝ ብሎ ሙዝዝ ያለ ጅላጅል ጎልማሳ ሆነዉ ታዩኝ። የሚገርመዉ ነገር አሁንም ድረስ ደርግ ከእኛ ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ ይሆናል ብለዉ ማመናቸዉ ነዉ።

'መንጋ ነፈ--ዝ!' ንዴቴ አገረሸብኝ።

በእኔና በኢሳያስ ዓይን ዘርዑ ከህሸንና ከፍሉ ታደሰም ከወንጀሉ አያመልጡም። ድርጅቱን ከተማ ዉስጥ አግተዉ የደርግን ዓይንና ጥርስ እያየ የሚያድር ደካማ ተቋም አድርገዉታል። ደርግ ኮስተር ሲል ሊፈጀን ነዉ ይላሉ። ፈገግ ሲል ደግሞ ኢሕአፓዎች፣ የፈራን ይመስላቸዋል። እንደ እንጀራ ልጅ የአሳዳሪን ፊት ዐይቶ ማደር አስቀያሚ ባህርይ ነዉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እኔም ሆንኩ ኢሳያስ ሌላ ጥርጣሬ እየተሰማን ነዉ። "እነዚህ ሰዎች ምናልባት በየራሳቸዉ መንገድ አሲምባ መሄድ ሳያስፈልገን እዚሁ በአጭር መንገድ ለሥልጣን እንበቃለን ብለዉ በምሥጢር ድርድር ጀምረው ይሆን?''

ይህንን እንድንጠረጥር ያደረገን አንድ በቂ ምክንያት አለን። በሁለቱም በኩል በየጊዜዉ የምናየዉ የአቋም መዋዠቅ ነዉ። ብርሃነመስቀል ለምሳሌ እነ ተስፋዬ መኮንን ኢሕአሠን ከድተዉ ሲመጡ የሞት ፍርድ እንዲወሰንባቸዉ አድርጓል። እሱ ይዘዉት በገቡት ጠበንጃ አሳበበ። ደርግም በበኩሉ የባሰዉ ጅል አይደል!? ከልብ ገብተዋል የሚላቸዉ ከነጠበንጃቸዉ ከኩዱ ነዉ።

"ይህ ከሆነ ታዲያ ብርሃነመስቀል ዛሬ ምን ተዐምር ዐይቶ ነዉ ደርግ እቅፍ ውስጥ ካልገባን የሚለዉ?"

ምንም የሚያሳምን ምክንያት ማግኘት አልቻልንም። በሌላ በኩል የዘርዑ፤ የተስፋዬ ደበሳይና የክፍሉ ሦስት ማዕዘን አመራርም ፍላጎቱ በትክክል ምን እንደሆነ ማወቅ ከበደን። ከደርግ ጋር አብሮ መሥራት አለመቻላችንን ርእዩተ-ዓለማዊ መሠረት አለዉ ብለዉ አምኑ እንበል። ይህ ከሆን ታዲያ ማእከላዊ ኮሚቴዉ አዲስ አበባ ዉስጥ ያሸመቀዉ የማንን ድስት እያማሰለ ነዉ? ደርግን ለኢሕአፓ ተጽእኖ ማንበርከክ የሚቻለዉ በኢሕአሠ በኩል ብቻ መሆኑ ለምን አይታያቸዉም? ለዚህ ጥያቄ መልስ ማጣታችን ነዉ እንግዲህ ወደ ሌላ ጥርጣሬ የወሰደን።

"ወደ ቤተመንግሥት ዘዉ ብሎ የሚያስገባ ከፍት መስኮት ታይቷቸዉ በምስጢር ድርድር ይዘው ይሆን?" እንደገና ተጨነቅን።

የአሻጥር ንድፈ-ሐሳብ የሁልጊዜ ንቃተ-ህሊና ተደርጎ መያዝ የለበትም። ኢሕአፓን የሚያከል ግዙፍ

የፖለቲካ ድርጅት ምክንያታዊነትንና መረጃን የአስተሳሰቡ ምሰሶ ማድረግም ይኖርበታል። አንዳንዴ ግን የፓርቲ ፖለቲካ ልምዳችን ማነስ የሚፈጥረዉ የግንዛቤ እጥረት ይኖራል። በዚህ ጊዜ የአሻጥር ንድፈ-ሐሳብ አይጠቅምም ማለት ሞኝነት ነዉ። ወደ እዉነት ሊመራ የሚችልበት እድል እንዳለ ማየት ደግሞ ተገቢ ነዉ።

"ያልጠረጠረ ተመነጠረ ነዉ፤ ወዳጄ!" ከኢሳያስ ጋር በቀላሉ ነው የተግባባነዉ።

ዝናቡ ትንሽ ጋብ እያለ ሲመጣ ሥራ ለመግባት ተነሳሁ። ጫማዬን እያደረኩ እያለሁ ግን ኢሳያስ ወደ እኔ ለመምጣት ደረጃዉን ሲወርድ ዐየሁት። ሲጋራዉን እያቦነነ ነዉ የሚመጣዉ። ሰዉነቱ ተለዋውጧል። የበለጠ ተጎሳቁሎና ጥቁርቁር ብሎ ታየኝ። እረፍት ማጣት፤ ለምግብ አለመጨነቅና ሲጋራ ተባብረዉ አዳክመዉታል። ለእሱ ይሄ ምኑም አይደለም። ለእሱ ዋናዉ ነገር ኢሕአፓ ነዉ። ቅልጥሞቹን እጥፍ ዘርጋ እያደረገ መጥቶ ስሜን እየጠራ አልጋዉ ላይ አጠገቤ ቁጭ አለ...

"እኔ'ኮ ምን ማድረግ እንደምንችል ግራ ገባኝ..." ብሎኝ ምን አዲስ ነገር እንደተፈጠረ ስጠይቀዉ ወደ ጉዳዩ ገባ፤ "አንተ ወደዚህ እንደመጣህ ዘርዑና ዮሴፍ አዳነ ከሁለት ደርጎች ጋር መጥተዋል። በደርግ የኢሕአፓ ኮሚቴዎች መሰሉኝ። ወርሀዊ ስብሰባ ሳይሆን አይቀርም። ምን እየተነጋገሩ እንደሆነ ታዉቃለህ?" ሲጋራዉን ማግ ማግ አደረገ።

"ያዉ ያ ቀፋፊ አሻጥራቸዉ ይሆናላ!" ሻምበል ሞገስና ሻምበል አምሀ እንደሚሆኑ እያሰብኩ ከተጋደምኩበት ቀና አልኩ።

"ኧረ ከዚያም በላይ እየሄዱ ነዉ ሰዎቹ! 'የደርግን መዋቅር ሻለቃ መንግሥቱን ለመቆጣጠርና ለኢሕአፓ አመች እንዲሆን አድረጋችሁ እንደገና አዋቅሩልን' ብለዉ ፕሮፖዛል በቁምነገር ጽፈዉ ሰጧቸዉ።" አለኝ በቅሬታ።

ንዴቴ ብልጭ ያለብኝ ወዲያዉኑ ነዉ።

"ኢሱ፤ እኔም እንዳንተ ጨንቆኛል። እነዚህ ሰዎች ድርጅታችንን ወዴት እየመሩት ነዉ? ተመልከት፤ በአንድ በኩል ደርግና መኢሶን ሊፈጁን ብለዉ የጦርነት ዝግጅት አጀንዳ ለስሞኑ ስብሰባ ይዘዋል። በሌላ በኩል 'ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉልን ከደርግ ጋር አብረን መሥራት እንችላለን' የሚል ይፋዊ መግለጫ ሰጥተዋል። ይሄዉ አሁን ደግሞ የደርግን መዋቅር እንለዉጥ እያሉ ነው። ይሄ ሁሉ የሚሠራዉ እንግዲህ የመጀመሪያዉ 'ሕዝባዊ ጦርነት' የሚለዉ ዓላማ ተረስቶ ነዉ። ኢሕአሠ ተረስቶ ነዉ። ጥቂት

የደርግ አባላትን ስለመለመልን ቀስ በቀስ ሁሉንም ይዞን መንግሥት ለመመሥረት እንጋበዝ ይሆናል የሚል ጅላጅል ምኞት ይዘዉ ነዉ..." በቁጭት ተጠበስኩ።

"ኢሕአሠንማ መጫዎቻ አሻንጉሊት አድርገዉታል። ሲጀምር ልክ እንደ ከፋ ቀን መደበቂያ ነዉ የሚያዩት። እዚህ ከተማ ላይ ሞክረን ካልተሳካልን እማራጭ ይሆንናል ነዉ ነገሩ። ሁለተኛ፤ አባላት ወደ ኢሕአሠ የሚሄዱት እንዴት ነዉ? ጦርነት የፖለቲካ ዓላማ ማስፈጸሚያ አንድ ሥልት ነው በሚል እምነት ነዉ? ለወታደራዊ ተልእኮ ብቃት አላቸዉ ወይ? እየተባለ እንደ አንዱ የፓርቲዉ ተግባር እየታየ ነዉ ሰዎች የሚላኩት? አይደለም። ከተማ ደርግ የነቃባቸዉን ነው እየላኩ ያሉት..." ኢሳያስ ረስቴዉ የነበረዉን ብሶቴን ቀሰቀሰዉ።

"ትክክል ነህ! ኢሕአሠን እንደ ቀይ ጦር አስኳል አላዩትም። ብርሃነመስቀል በለዉ ዘርዑ ወላ ተስፋዬ ደበሳይ ሁሉም አንድ ናቸዉ። እንደ መጠለያ ጣቢያ ነዉ የቆጠሩት። ተመልከት፤ አሁን ደግሞ የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥም ኢሕአሠ የወልድያን ንግድ ባንክ እንዲዘርፍላቸዉ አቅድ አዉጥተዋል። ጓድ ተስፋዬ ይሄን ሊያስፈጽም መሄዱ ነዉ። አንተ ሲዳሞ ሄደህ አልነበርከም መሰለኝ፤ የሆነ የመንግሥት ጠበንጃ ግምጃ ቤት እንዘርፋለን ብለዉም ዐቅደዋል። ሰንዳፋ ያለ መሰለኝ። እነ ደጀኔ ሀያ አራት ሰዓት ሙሉ ሥልጠና ላይ ናቸዉ..."

"ሕዝባዊ ጦርነት አድርገዉ በጀግንነት መማረካቸዉ ነዋ! ይሄም እንዳልከዉ ከተማ ውስጥ ከመዘፍዘፍ የመጣ የስንፍና እቅድ ነዉ። በግርግር መሀል አንዱ ቢያዝ፤ አለቀ..." ኢሳያስ የነደደ ስሜቱን ተቀላቀለ።

በኢሕአሠ ጉዳይ ማእከላዊ ኮሚቴው ስለሚከተለው ፖሊሲ ቅሬታዬን አነሳሁለት...

"በጣም የሚያናድደኝ ደግሞ እነርሱ ኢሕአሠ የሚሉት ጦር ከከተሞች ሄዶ ጠበንጃ የታጠቀውን ኃይል ነው። አማርኛ ሲናገር የእንግሊዝኛ ቃላትን የሚሰነቅረውን የከተማ ልጅ ነው። የአካባቢውን ገበሬ ወደ ሠራዊቱ ድርሽ እንዳይል አድርገውታል። ያለ ገበሬ ሠራዊት ኢሕአፓ እግሩ የተሰካ እሾህ መንቀል አይችልም። እኔ ለማን ነጻነት እንደምንታገል ቸገረኝኮ።" ምርር ብዬ ተናገርኩ።

የማስታዉሰዉን ያህል እኔና ኢሳያስ የመሪዎቻችንን ስም እየጠራን እንደዚህ አምተን አናዉቅም። ይህንን የጀመርነዉ እነርሱ በአዲስ አበባ ጉዳዩች ተጠምደዉ ኢሕአሠን መርሳትና ስለ ጋራ ግንባር ማዉራት ከጀመሩ ወዲህ ነዉ። እኔ በተደጋጋሚ አዲስ አባን የመልቀቅ ሐሳብ ማንሳቴም ደስ እንዳላሰኛቸዉ ዘርዑ ኢሳያስን ፍንጭ ሰጥቶታል። ብዙም አልተጨነኩም። ቅሬታችንን ይዘንም ቢሆን ከኢሳያስ ጋር ደጋግመን ቃል የተገባባንበት ስምምነት አለን።

"በጭራሽ በጭራሽ እንጃ እንፈፐርም። አይፈጠርም ብለንም ተስፋ እናደርጋለን። ከተፈጠርም እናወግዛለን እንጅ ማንንም አንቀላቀልም። ድርጅታችን መሳሳቱን ኢያወቅንም ቢሆን ድምጽ ብልጫ ያገኙን ዉሳኔ እናስፈጽማለን። እንጃ ማለት ሁለት ሦስቴ መሞት ነዉ።" የማይለወጥ ቃላችን ነዉ።

አሁን አሁን ግን ስጋት እየገባኝ ነዉ። አንድ ግዙፍ ድርጀት ከተማ ዉስጥ እንደ ትራፊክ መብራት ተተክሏል። ይህ መጎለት መዘዙ ብዙ እንደሚሆን በብርሃንመስቀል አቋም መዋዠቅ እያየሁት ነዉ። ብርሐነን ሳውቀው እንዲህ ዓይነት ሰው አልነበረም። ሁለት ሦስቴ በዲሞክራሲያ ታትሞ የሚወጣ መጣጥፍ ሳዘጋጅ አማክሬዋለሁ። በሦስቱም ጊዜ ያላገናዘብኳቸው አደገኛ የጽንሰ-ኃሳብ ስህተቶች ሠርቼ ነበር። ስህተት ያሠራኝን የግንዛቤ ጉድለት ሲያስርዳኝ በብቃቱ ተደንቄያለሁ። አሁን ያ ብቃት ደብዝዞ አልታይህ አለኝ።በዘርው ወደ አራት ኪሎ ቤተመንግሥት ማንጋጠጥ እየታዘብኩት ነዉ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ስለ እንጃ ከስጋት የዘለለ ስወዘወዝ መከረም አልፈልግም።

***

ሸዋዬ ወደ እኔ ቤት በሚያመጣዉ በር በኩል ብቅ ብላ "ትፈለጋላችሁ" ምልከት በእጆቿ አሳየችን። ኢሳያስ ፈጠን ብሎ ሄደ። ኢሳያስ ሲሄድ እእምሮዬ ወደ ቢታኒያ ተሻገረ። "እጭሩ የልጅነት ሕይወቴ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ በጸጸትና በቁጭት የተሞላ ነዉ!"

በሰሞኑ ለዉጧ በጣም ተከፍቻለሁ። በላባአደሮች በዓል ላይ እንድትገኝ ካደረጓት ወዲህ እምነት አጥቻለሁ። የአካል እንቅስቃሴ ብላ የምትሄደዉን ነገርም አልተወችም። ፖለቲካዊ ዓላማ ያለዉ መሆኑን ግን እስካሁን አላመነችልኝም። ሌላ የጸጸት ገፈት እንዳልጋት ፈራሁ።

"ብርክቲን ባጣ ቢታኒያን አገኛቻለሁ" ብዬ ራሴን አታልዬ የማልፈዉ ነገር ሊሆን አይችልም።

ሸዋዬም ሲታያት መቼም እንደበቷ ማር ያዘንማል። ከእኔም ከቢታኒያም የታዘበችዉ ነገር አለ። ሲመቻት ለእሷም ለእኔም በተናጠል ምክር ቢጤ ጣል ታደርግልናለች። ያለችንን ስንነጋገር ያዝናናናል...

"እናንተ ሁለት ቀንጆዎች፣ አያያዛችሁ አልተመቸኝም። በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ እንዲህ በፍቅር አብዳችሁ በኋላ አብረን እንሙት እንዳይመጣ..." ከፊል ድርጅታዊ አነጋገር መሆኑ ነዉ።

በበኩሌ እንደ ሟርት አላየዉም። ደህንነታችን በድርጅታችን ብቃት እንደሚወሰን ይገባኛል። የመስፍን ሐብቱ የሱፍ አበባ ገጠመኝ ጊዜዉ አልፏል ብዬ አምናለሁ። እዚህ ነጥብ ላይ ስደርስ እእምሮዬ ዘጠና

ዲግሪ ታጠፈ። በሚገርም የትኩረት ጥልቀት የሱፍ አበባ ተከል ላይ ሐሳቤ ሁሉ ተጠምጥሞ አልወርድ አለ።

የሱፍ አበ-----------ባ!!

'የሱፍ አበባን በልጅነቴ በደንብ ዐዉቃታለሁ።የራሷ መለያ ባሕርያት አሏት። በቁመቷ ከሌሎቹ የአገዳ ሰብሎች በጣም ረጅሟ ናት። በዚያዉ መጠን ግን በጣም ቀጭንም ናት። የአበባዋ ከፍል ፀሐይን ተከትሎ ከምሥራቅ ወደ ምእራብ እንቅስቃሴ ያደርጋል። እንዲያዉም ዋናዉ መለያዋ ይሄ ሳይሆን ይቀራል? አዎ፤ በበኩሌ እንዲህ ዓይነት ባህርይ ያለዉ ሌላ ተከል አላዉቅም። የሰዓሊዉ ቫን ጎህን ትኩረት የሳበዉም ይሄ መሆን አለበት። የሱፍ አበባ የሱፍ ጥሬንም ታመርታለች። ጥሬዉም አበባዋን አጅቦና በአበባዋ ተከልሎ ፀሐይን ይከተላል። የሱፍ ጥሬ ራሱ ይበላል። ተጨምቆም ዘይትን ይሰጣል። ታዲያ ከሞት ጋር ምን አገናኛት?'

ያነሳሁትን ጥያቄ በቅጡ ሳላጤነዉ ሸዋዬ ብቅ አለች። ቀና ብዬ ሳያት ፈገግ አለች። ወይ ስለቢታኒያ ወይም ስለ ብርከታዊት አንድ ነገር ልትለኝ ነው ብዬ ገመትኩ።

"አንተ አላምረው፣ ይሄ የድርጅት ሥራ ባለትዳር መሆንህን አስረሳህ አይደል?"

"ምነው፣ ምን ተፈጠረ?"

"እንዴ...መልስህ ደግሞ ትጠይቀኛለህ? ቢታኒያ 'ለምሳ አልመጣህም' ብላ አብድ ሙር እየሆነችልህ ነው። ለሥራ ከተማ ወጥቶ ነበር ብላት ባታልላት አልሰማም አለችኝ። ፍልጥ ይዛ እየጠበቀችህ ነው፣ ስታንጎራድድህ ይታየኛል።" ሸዋዬ ከልቧ ሳቀች፣ "በል አንድ አፍታ ብቅ ብለህ 'ይቅርታ!' በላት። ለእንክብካቤ የማትመች አስቸጋሪ ባል ነህ፣ ጃል!"

አሁን ዝናቡ በጣም ቀንሷል። መጀመሪያ ወደ ጋራዥ መሄድ ለኖርብኝ ነው። በአንገቴ ዙሪያ ፎጣ ጠምጥሜ ወጣሁ። በዚያችው የምሥጢር መንገድ ተሽሎኩልኬ ሄድኩ። ከቀዩ በር ስደርስ በቀዳዳ አጮልቄ ወደ ቢታኒያ ቤት ጎንበስ ብዬ ዐየሁ። ቢታኒያ ከሆነች ትልቅ ኮት በጨርቅ ሱሪ ከለበሰች አጭር ልጅ ጋር ናት። ከቤቷ ወጥተው በዋናው በር በኩል ስትሸኛት አየኋት። ከጀርባቸው እያወዳደርኩ ሳያቸው ቢታኒያ ልእልት መስላ ታየችኝ። ስስት ከውስጤ ግንፍል ብሎብኝ ደግሜ ዐየኋት። በአረፍት ልብሷም ሆና ሽንጧ እንደ ቁጠማ እጥፍ ዘርጋ ይላል...

'ቤቲዬ፣ እንኳን የኔ ሆንሽልኝ...ከዓይን ያውጣሽ!'

የምትሸኛትን ልጅ በሆነ አንድ ነገሯ የማውቃት መሰለኝ። የት እንደሆነ ግን የማስታውሰው ነገር የለም። ለጊዜው ችላ ብያት ወደ ጋራዥ አመራሁ። ጋራዥ ስገባ በድንጋጤ ልቤን ትርትር ያደረገ ትርኢት ገጠመኝ። እስከ አፍንጫዋ ድረስ ከምር ጭቃ የዋጣት የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ኒሳን ሽፍን መኪና ገብታ ቆማለች። ታርጋዋን ገልመጥ አድርጌ አየሁት። ሲዳሞ ከፍለሀገር መሆኑን ሳይ ልቤ ወደ ቦታዋ ተመለሰች። ከምጠላው መኢሶን በስተቀር ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከማይዛቸው አዲስ መኪናዎች አንደኛዋ ናት። ያልጠፋው ሞተሯ ገግ ገግ ገግ.. ይላል። ጎይቶም ለባሲ በኢንጋጣሚ ከሜክሲኮ መጥቶ መኪናዋ ሥር ገብቶ ይመረምራታል።

ከደቂቃዎች በኋላ ጎይቶም የኒሳኗን ሾፌር እየመራ ቢሮ ይዞት መጣ።

'እህ፣ የእነ ሰው በላው ሾፌር!' አልኩት በሆዴ።

ጎልማሳው ሾፌር እንደ ባለሥልጣኖቹ ሁሉ ደረቱን በአብረት ነፋቶ ያየሁት መሰለኝ። የደርግ ካድሬዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደደንብ ልብስ የሚለብሱትን ቡላ የኩባ ወታደራዊ ቱታ ለብሶ፣በተለምዶ ማኦ የሚባለውን ቆብ ጭንቅላቱ ላይ ደፍቷል። ልክ ካድሬዎቹን ራሳቸውን መሰሏል።ሰላምታ ተለዋወጥን። ወደ አሁኑ ሥራ ከመግባቱ በፊት የግለሰብ ሾፌር እያለ የጋራዡ ደንበኛ እንደነበረ ነገረኝ። ፊቴን ወደ ጎይቶም ስመልስ ስለ መኪናዋ ይነግረኝ ጀመር...

"ጋሽ፣ መኪናዋ ሦስት ብልሽት አለባት። አሚዘሬተሯ ከጥቅም ውጭ ነው። የፍሬን ሸራዋ ተቃጥሏል። አብዛኛው የማርሹ ጥርስ ረግፎ ስፓናቶ ኾኗል። የነዳጅ መሳቢያውና የኤሌክትሪክ ሥርዐቱ በሙሉ ተዛብቷል። ኮረቸራው መቀየር አለበት። " ጎይቶም ሌሎች ብልሽቶችን ጨምሮ ከነገረኝ በኋላ፣ "እቃዎቹ በሙሉ በአዲስ የሚቀየሩ ናቸው። ችግሩ ግን መለዋወጫቸው በቀላሉ አይገኝም። ስለዚህ በረጅም ቀጠሮ የሚሠራ ነው።" አለኝ።

"የአስር ወራት ቀጠሮ ብሰጥህ ትስማማለህ?" ሾፌሩን ጠየኩት።

"አሁን በጀት መዝጊያ ነው። በኋላም ቶሎ አይደርስም፣ እዚሁ ብትቆይ ይሻላል። ይሄንኑ ለአለቆቹ እነግራቸዋለሁ።" አለኝ።

የደረሰኝ ካርኒ ቆረጥኩለትና ቁልፍ አስረከቦኝ ተሰናብቶኝ ወጣ። በጥላቻ ከጀርባው ዐየሁት። 'ማን ያውቃል? እስከ አስር ወር ድረስ እየፈነጫችሁብን አትቆዩ ይሆናል። ድል ለኢሕአፓ!' አልኩ በሆዴ።

# 20

ከሚያዚያ ወዲህ ተገናኝቶ የማያወቀው የኢ.ሕ.አ.ፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ዛሬ ይሰበሰባል። ሳምንት ሙሉ የተዘጋጀሁበትን ጽሑፍ አስቀድሜ አሰራጭቻለሁ። ከምሳ በኋላ ሰዓቴን ወዲያው ወዲያው ማየት ጀመርኩ። ውጭ እንደማይደር ቢታኒያን መንገር አስፈርቶኛል።

'ዛሬማ ለፓርቲዩ ሕልውና አንድ ነገር ሠርቼ መምጣት አለብኝ።'

የሰኔ ወር ወደ መጨረሻዎቹ ቀናት እየተጣደፈ ቢሆንም ማእከላዊ ኮሚቴው ለዚህን ያህል ረጅም ጊዜ ያልተሰበሰበው የጸጥታ ሁኔታው እየተበላሸ በመሄዱ ነበር። ክፍሉ ታደሰ ቤቱ ሄጄ  በነበረበት ጊዜ ይህንኑ ነግሮኛል። በሰዎቻችን ላይ እየደረሰ ያለው አፈናና እንግልት በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። ክፍሉ እንዳሳየኝ ከሆነ ባለፉት ሁለት ወራት የደርግና የመኢሶን ጥምረት ጭካኔውን አፋፍሞታል። ጅማ፣ ድሬዳዋና ሐረር ግልጽ ጭፍጨፋዎች ተካሂደዋል።ይህ ስሜት በዛሬው ስብሰባ ላይ አዚሙን ሊጥልበት እንደሚችል ተሰምቶኛል። ከርክር እስካለ ድረስ ግን ስሜታዊነት የበረዘው ውሳኔ አልጠብቅም።

'ግ--ን ምኑ ይታወቃል!?' አልኩ ለራሴ ብርሃነመስቀል ያለ አግባብ ከጸሐፊነት የተነሳበት "የመጀመሪያው ኩነኔ" ትዝ ሲለኝ።

የዛሬ ሌሊቱ ስብሰባ ሰባ ደረጃ አካባቢ በዮሴፍ አዳነ ቤት ውስጥ ነው የሚደረገው። ምስኪን ዮሴፍ! ያለች የሌለችውን ንብረት ሁሉ ለኢ.ሕ.አ.ፓ አስረክቧል። በጸጥታው መበላሸት ምክንያት የሁለት ሳምንት የድርጅቱን ገቢ ስላላስረከብኩት ዛሬ አገኘዋለሁ። አዲስ የተመደበውን ሻለቃ ሽታዬ ደስታን አግኝቼ መተዋወቅ እንኳ አልቻልኩም። የጸጥታው ችግር በተራው የድርጅቱን የፋይናንስ ቀውስ አባብሶታል። ዮሴፍ የነገረኝ መራራ ታሪክ ትዝ አለኝ...

"የገንዘብ እጥረት እንዳሰቃየን ሲታወቅ በድርጅት ደረጃ መፍትሄ መፈለግ ነበረብን። አንተ ወደ ፖለቲካ ኮሚቴው ከመጣህ በኋላ የአዲስ አበባው በይነቀጠና ኮሚቴ ችግሩን ለአባላት አስታወቀ። ብዙ ልጆች ምን እንዳደረጉ ታውቃለህ? በጥቂት ቀናት ውስጥ በየግላቸው መጠነኛ ገንዘብ አመጡ። ይሄ ነገር ምንድነው ብለን ስናጣራ የሚያስደነግጥ ወሬ ሰማን። የወላጆቻቸውን ወርቅ ቀለበትና ጉትቻ እየሰረቁ ሸጠው ነው ያመጡት። ወዲያው ትእዛዝ ሰጥተን አስቆምነው..."

ዮሴፍ ቅሬታ እኔ ደግሞ ብርቱ ድንጋጤ ተሰማን። ስሜቴን ለመንገር የሚከብደኝ ሰው አይደለም...

"ጆስ፣ ይሄ የከተመኝነታችን አንዱ አስከፊ ዉጤት አይመስልህም? የትግራይ ሸምቅ ተዋጊዎችን ውሰድ። ከተቋቋሙ ሦስት ወር ባልሞላ ጊዜ አክሱም ንግድ ባንክን ሰብረው በቂ ብር ወሰዱ። ማየት ያለብህ ብሩን ብቻ አይደለም። የደፈጣ ጥቃት ልምድ አገኙበት። የሕዝቡን በራስ መተማመን ከፍ አደረጉበት። በጠበንጃ አጥቅተው ስለወሰዱት መንግሥት ማንንም ይዞ ማሰርና ማሰቃየት አልቻለም። የወሰዱትም ብር ወደ ምሽጋቸው ስላሸሹት መንግሥት ሊደርስበት ቀርቶ ዱካውን መከተል ኢቃተው። ይሄ ሁሉ ድል ድርጅታቸው ገጠር መኖሩ የሰጣቸው ነጻነት ውጤት ነው።" እየተናገርኩ ድርጅታዊ ቅናት ሊጠብሰኝ ዳር ዳር አለኝ።

"አላምረው፣ ትክክል ነህ። ብዙ ገንዘብ ከፈለክ ወደ ብዙው ሕዝብ መሄድ ነው። ከተማ ውስጥ ብዙ ገንዘብ ቢኖርም በጥቂት ሰዎች እጅ ነው ያለው። ከሁለት የከተማ ሰዎች ሺህ ብር ከምታገኝ ከአንድ ሺህ የገጠር ሰዎች አስር ሺህ ብር ብታገኝ ይቀላል።"

ዮሴፍ ይህን ይበለኝ እንጂ በተግባር ጥያቄ ላይ እሱም ያው ነው። ኢሕአፓ አዲስ አበባን ሲለቅ አይታየውም። ደርግ ስለገጠመን ችግር መረጃ አለው። መኢሶኖች ችግሩን ለፕሮፓጋንዳ ዓላማቸው ተጠቀምን ብለው ትዝብት ላይ የጣላቸውን ስህተት ሠሩ...

"ኢሕአፓ ከፍተኛ የፋይናንስ ቀውስ ገጥሞታል። ይህንን ችግሩን ለማቃለል በኢድገት በሕብረት የዕውቀትና ሥራ ዘመቻ ላይ የሚገኙ ሴት አባላቱን በሴተኛ አዳሪነት አሰማርቶ ገንዘብ እንዲያመጡለት እያደረገ መሆኑ ተደርሶበታል።" ብለው አሰወሩ።

መኢሶኖች በራሳቸው "የሰፊው ሕዝብ ድምጽ" ጋዜጣም ይህንኑ ፀያፍ ሀሜት አወጡት። በኢሕአፓነቴ እንዲህ ዓይነት ተግባር ሊፈጸም ቀርቶ ሊታሰብ አይችልም። በአገራችን ባህል የደርግና የመኢሶን መግለጫ እጅግ ነውረኛ ነው። ለሴቶች ንቀታቸውን ያሳዩበት ጸያፍ መንግሥታዊና ድርጅታዊ ትንሽነት ሆኖ ተሰምቶኛል። ወዲያው ትዝ ያለችኝ ብርከታዊት ነበረች...

'ብርክቴ፡ ይሄንን ስትሰማ ምን ብላ ይሆን?' መገመት ከበደኝ። በግልባጩ ግን ድርጅቷ መኢሶን ከፍ ያለ በጀት በደርግ ተመድቦለታል። ሰርገው የገቡ አባሎቻችን ለማን ምን ያህል እንደሚከፈለው መረጃ ልከዋል። በእውነት በጣም ያስደነገጠኝ ዝርፊያ እየተካሄ ነው።

'በዚህ በኩል ድርጅቴ ሰባራ ሳንቲም አይታማም። ኢሕአፓ ሆኜ መቶ ጊዜ ብራብና ብጠማ ይሻለኛል።' ኩራት ተሰማኝ።

የድርጅታችን የገንዘብ እጥረት ኢሳያስንም ነክቶታል። የሲጋራ መግዣ ሁሉ እያጣ እኔ መሸፈን ነበረብኝ። በዚህ ላይ ወጭ የሚጠይቀው የሰሜን ሸዋ ወታደራዊ ጥናት ጉዞው አላለቀም። ሁለታችንም የማናምነበት ጥናት ቢሆንም ቅሉ...

"እኔኮ በዚህ የሰሜን ሸዋ ጥናት ሥራ ግራ ተጋባሁ። በቃ፣ ሳይነገረኝ ወደ ወታደራዊ ክንፉ ተዛውሬያለሁ ማለት ነው?" አለኝ የሲጋራ መግዣና የጉዞ አበል ቆጥሬ ከሰጠሁት በኋላ።

"ኢሱ፣ እንደዛም ሆኖ ውጤት ቢኖረው ጥሩ ነበር። ከአዲስ አበባ ወጥቶ ሰሜን ሸዋ መግባት ለመሆኑ ምን ማለት ነው? ከዳር ወደ መሀል በሚደረግ ሕዝባዊ ጦርነት ኢሕአሠ ምናልባት ከአስር ዓመት በኋላ የሚይዘውን ቦታ አሁን ሄዶ መያዝ ትርጉሙ ሊገባኝ አልቻለም።" ጭንቅላቴን በአሉታ ወዘወዝኩ።

"ሰመሬ፣ እንኳን ሰሜን ሸዋ ሲዳሞም ያው ነው። ነጻ መሬት በውጊያ እንጂ በሰፈራ አይያዝም።" ኢሳያስ ንድድ አለው።

"ኢሱ ሙት፣ ተወው፣ ሁለቱም እውር ቢሸፍት ከዳራው ናቸው..." ስለው ኩት ብሎ ስቆ ተረቱን ሁለት ሦስቴ አስደገመኝ።

ከመስክ ተመልሶ ሲመጣ ተረቱ ቃል በቃል ጠፍቶበታል።

"'እውር በዳሮ ሸፈተ...' ነው ያልከኝ?" እየሳቀ ሲጠይቀኝ እንደገና ነገርኩት። የተረቱ ፍካሬያዊ ትርጉም ኢሕአፓን በትክክል ሊገልጽ መቻሉ አስገርሞታል። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ትእዛዙን አልቀበልም ሊል አይችልም። እንዲያውም በሙሉ ፈቃደኝነት እየሠራዉ መሆኑን ሳይ እኔም ደስ ብሎኛል። አሁንም ስብሰባ ላይ የማይገኘው ስለሄደ ነው። በእኔ ጽሑፍ ላይ የሚደረገውን ውይይትና የሚተላለፈዉን ውሳኔ ለማየት አለመቻሉ ደስ አላለውም። ከቢሮ ከመውጣቴ በፊት ጽሑፉን አንዴ ልመለከተው ስለፈለኩ ከውስጥ ሱሪዬ አወጥቼ ዘረጋጋሁት...

***

የጽሑፌ ዋና ጉዳይ በኢሕአፓ ከተማ-ተኮርነት ላይ ሂስ ማቅረብ ነው። "ገበርዲኒዝም" ደግሞ ትንተናዬን የሠራሁበት ማእዘን ነው። "ገበርዲኒዝም"ን የፈጠርኩት "ገበርዲን" ከሚለው የአማርኛ ቃል ነው። በኮት ሥር የሚለበስ አጀቢ የውስጥ ልብስ ነው። በከተሞች አካባቢ የሚዘወተር ልብስ ስለሆነ የከተመኞች ፋሽን ነው። ምን ያህል የውስጥ ብሶቴን እንደሚገልጽልኝ እርግጠኛ አይደለሁም። ሰሜን ኢትዮጵያ ገጠር ውስጥ ገበሬዎች "ገበርዲን"ን የሚጠቀሙበት አባባል አለ። እሱን ወስጄ ርእዮተ-ዓለማዊና ድርጅታዊ ቅርጽ ሰጠሁት...

"ገበርዲኒዝም!"

ብዙ ገበሬዎች ላይማሩ ይችላሉ። ልቦናቸው ብሩህ የሆኑ ገበሬዎች ቁጥር ግን ቀላል አይደለም።በከተማውና በገጠሩ ሕዝብ መካከል ያለዉን የአስተሳሰብ፣ የአኗኗር፣ የሥነልቦናና የልማድ ልዩነት ጠንቅቀው ያውቁታል። ብዙ ብዙ ልዩነት አለ። ገበሬ በጥብቆው ላይ ጋቢ ይደርባል፣ ትከሻው ላይ ዱላ ጣል ያደርጋል። ከተሜ ኮት ወይም ጃኬት በሸሚዝ፣ እንደሁኔታው በከራባት፣ ብቻ ለብሶ ይሄዳል። ዱላ አይዝም። ሽፍን ጫማ በካልሲ ይጫማል። ከዚህ ተነስተው የገጠር ነዋሪዎች የሰዎችን ማንነት ይወስናሉ። ታዲያ ትላንት አብሯቸው የነበረ ገጠሬ ጠፍቶ ቆይቶ ሲመለስ ከተሜን ከመሰለ ሌላ መለያ አላቸው...

"እሱማ ኮተኛ ሆነ ወይም እሱማ ገበርዲን ለባሽ ሆነ ይላሉ።" በሌላ አነጋገር የተባለው ሰው የቀድሞ ማኅበራዊ ሥፍራውን ቀየረ ማለታቸው ነው። ትንሽ ትንሽ ምጸትም አለበት። "ገበርዲኒዝም" ለዓላማዬ ተስማሚ ሆኖ አገኘሁት።

የገጠሩ ሕዝብ የሞራል ሕግጋት አሉት። ያለበቂ የኢኮኖሚ ወይም ሌላ ምክንያት እንዲሁ በባዶው ከተማ ለከተማ የሚንገላወድ ሰው ደስ አይላቸውም። ከከተማ በዚህ መንገድ ኮት ለብሶ የተመለሰ ገበሬንም አያልፉትም። ገበርዲንን ጠቅሰው ሸንቆጥ ያደርጉታል። አንዳንዴ ብድግ ብሎ ከተማ መመላለስን እንደ አውደልዳይነትም ያዩታል። ገበርዲን ለባሽነትን ለዚህ ሁሉ የስሜት መግለጫ ይጠቀሙበታል። ጽሑፍን ከመጀመሬ በፊት ኢሳያስን ትርጉሙን አስረዳሁት። ምን እንደሚያስብ ስጠይቀው በጣም እንደወደደው ደጋግሞ ነገረኝ። ይሄኔ ደስ አለኝ። የትንተናዬ ምሰሶ አድርጌው መጻፍ ጀመርኩ...

"ገበርዲኒዝም፣ የድርጅታችን ኢሕአፓ ዋነኛ በሽታ..." አልኩት ርእሱን።

"ገበርዲኒዝም" በሁለት ምክንያቶች የድርጅታችን ጉዳይ ህመም ነው። በአንድ በኩል ገበሬውን ወይም የገጠሩን ሕዝብ ሥርዐት የመለወጥ ዐቅም አሳንሶ ከማየት ይመነጫል። በሌላ በኩል የፖለቲካ ግንዛቤንና

የማድረግ ዐቅምን ከአስር በመቶ ለማይበልጠው የከተማ ሕዝብ ይሰጣል። ከሕዝቡም ደግሞ ጥቂት ልሂቃንን ይመርጣል። ልሂቃኑ ሐሳብ ያመነጫሉ፣ ወጣቱ ይፈጽማል። "ገበርዲኒስቶች" ገጠርን ለአጣዳፊ ፖለቲካዊ ፍላጎት ምንም ጥቅም የሌለው የሩቅ ሩቅ አድርጎ የማየት ግፊትም አለባቸው። በሌላ በኩል ራሳቸውን ለከተማ ኑሮ የተፈጠሩ አድርገው ይወስዳሉ። ይህ ከተማ የሁሉም መልካም እድሎች የሰበት ማእከል አድርጎ የማመንን አደገኛ ዝንባሌ ያመለክታል።"

እስካሁን አንጀቴ አልራሠም። በተጨማሪ ለከርከሬ ጥልቀት መስጠት እንዳለብኝ ተሰማኝ። ርእዮተ-ዓለማዊ ገጽታ ካላስያዝኩት ትኩረት የማይስብ እንደሚሆን ዐውቃለሁ። ሊብራሊዝምን ብድግ አደረኩት...

"ይህም ማለት 'ገበርዲኒዝም' በገበሬ አገር የገበሬውን ሕዝብ ብቃት ከመጠራጠር ያለፈ መሠረታዊ ችግር አለበት ማለት ይሆናል። የገበሬዉን በተለይ ድህውን ገበሬ የመካድ አተያይም ጭምር ነው። እዚህ ላይ አንድ ቁም ነገር ልብ ሊባል ይገባል። ገበሬው ሕዝብ የአብዮቱ ዋነኛ የኃይል ምንጭ ነው ስል ከተሞች ምንም አስተዋጽኦ የላቸውም ማለቴ አይደለም። የማይናቅ የራሳቸው ሚና አላቸው። ይሁንና ገበሬዉን ጨርሶ መተካት አይችሉም። ይህንን ስታትስቲካዊና ሶሾሎጅካዊ ሀቅ አለመቀበል ማለት 'ጥራዝ ነጠቅ ሊብራሊዝም'ን ከማራመድ ሌላ ስም ሊሰጠው አይችልም። ከዚህ አንጻር 'ገበርዲኒዝም' በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የተያዘን ሊብራል አድርባይነትንና ያልዘሩት በቀልነትን ያመለክታል..."

እዚህ ነጥብ ላይ ስደርስ ወደ ድርጅቴና አገሬ መመለስ እንደሚኖርብኝ ገባኝ። ዋናው የጽሑፌ ግብም ይሄው ነው። አሁን ትኩረቴ ኢሕአፓ ከተማ ዉስጥ በመጎለት ለውጥ አመጣለሁ ብሎ አስቦ ከሆነ ይህ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ መሆኑን አጥብቄ ማስረገጥ ነው። ከቻልኩ በገበርዲኒስት የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ላይ የኃፍረት ስሜት መፍጠር አለብኝ። ቀጠልኩ...

"እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ላንሳ። የድርጅታችን መስመር 'ሕዝባዊና አብዩታዊ' የሆነው ለምንድነው? ሌላ ምንም ሳይሆን ሊብራል ካልሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅለን ሊብራል መሆን ስለማንችል ነው። ይህ ከሆነ ኢሕአፓ አዲስ አበባ ውስጥ የተቀመጠው ምን ተዐምር ለመሥራት ነው? ምክንያታችን 'የገጠሩ ሕዝብ ጥያቄ በመሬት ዐዋጁ ስለተመለሰለት ቦታ አይሰጠንም' የሚል ከሆነ ይህ ጥሩ መልስ ነው። የዚህ መልስ ትልቁ ጉድለት ግን ከተማ ላይ ተሁኖ የተሰጠ መሆኑ ነው። ባጭሩ፣ ይህ ግልጽ 'ገበርዲኒዝም' ነው። ወደ ገጠር ገብተን 'ሕዝቡ ምንም አትረዱኝምና ዘወር በሉ...' ካለን ያኔ ኢሕአፓ መፍርስ ይኖርበታል። ለማን ቆምንና?"

ቀጥዬ የገጠሩ ሕዝብ ከደርግ የበለጠ ኢሕአፓን የሚቀበልበትን ምክንያት ወደ ማስረዳት ሄድኩ...

"ገጠሩ አይደግፈንም እንዳይባል ይህ የማይመስል ነው። በዚህ ላይ ቀደም ብለን የተግባባንባቸው ነጥቦች አሉ። ደርግ በራሱ መዋቅራዊ ማነቆ ምክንያት የመሬት ዐዋጁን በተግባር እንደማያውለው ተስማምተናል። ይህ ብቻም አይደለ። ደርግ ገበሬውን የዐዋጁ ባለቤት አድርጎ አይመለከተውም። እናም የምርቱ ነጻ ተጠቃሚ ያደርገዋል ተብሎ አይታሰብም። ደርጎች መሬት ከመውረስ አልፍው ሄደው ሀብታም ገበሬ የሚፈጠርበትን ፖሊሲ ይነድፋሉ ማለት ዘበት ነው። ንብና ጥንዚዛ ቦታ ተቀያየሩ ማለት ነው። ይህ ማለት እንግዲህ ኢሕአፓ የተራዘመ ሽምቅ ውጊያ ለማድረግ በቂ ምክንያት አለው ቢባል ያስኬዳል። ከመሠረቱ ደርግ የከተማው ሕዝብ ጠንቅ ከሆነ ለገጠሩ ሕዝብ ደግ ሊሆን የሚያስችለው ልብ ኩቶ ሊኖር አይችልም።"

ምን ያህል ጠንካራ ክርክር እንደጻፍኩ አሁንም እርግጠኛ አይደለሁም። ምናልባት ለውይይት ሲቀርብ ያኔ የሚከሰትልኝ የሥነ ዘዴ ስህተትም ሠርቼ ሊሆን ይችላል። ብርሐነመስቀልና ጌታቸው አይለቁኝም። ይሄን ፊርቼ ግን አልተወውም፣ እንደተለመደው ትምህርት አገኝቼበት አልፋለሁ። በመጨረሻ ገጠር መሄዳችን ለኢሕአፓ የሚያስገኛቸውን አስር ስትራቴጅካዊና ታክታካዊ ጥቅሞች በመረጃ ተደግፌ ዘረዘርኩ። በመጨረሻ መደምደሚያ አበጀሁለት።

"ድል ለኢሕአፓና ለሰፊው ሕዝብ! እናቸንፋለን" የመጨረሻውን ቃል ሳሰፍር ልዩ የደስታ ስሜት ተናነቀኝ።

***

የጋራዡ በር ትንሿ መተላለፊያ ስትከፈት ድምጽ ተሰማኝ። በሩጫ የሚመጣ ቀላል የእግር ኮቴ። የልጅ ኮቴ እንደሆነ ስጠረጥር ሚካኤለ እንደሆነ ስለገመትኩ ደንገጥ ብዬ ሄጄ በሩን ከፈትኩት። ግምቴ ትክክል ነው። የሚካኤለ ሁኔታ ግን ጥሩ አይደለም...

"ማይከ፣ ምን ተፈጠረ? ምን ሆነህ ነው?" ጥድፍድፍ ብዬ በጩኸት ጠየኩት።

"ቤቲ...ቤቲ ከሰው ጋር ተጣልታ። ከሙሴ ባልዲ ጋር ተጣልታ መንገድ ላይ አላሳልፋት ብሎ..." እያለኸለኸ ተኮለታተፈ።

"ሙሴ ባልዲ" ሲሉ በስም ደጋግሜ ሰምቻለሁ። ዘበኞችን ናቸው መጀመሪያ የነገሩኝ።"ሙሴ ድፍን

መሳለሚያ የሚያውቀው በዘኔ ነው። ማጅራትም ይመታል፣ ሴቶችን በተለይ ጌጣ ጌጥ ቀምቶ ይሮጣል።"በደንብ ሳስታውሰው ነፍስ ልስት ምንም አልቀረኝም። ከጩቤ የሚበልጥ ስለት ያለው የመኪና ጎማ መቀርደጃ ከወንበሬ ስር ብድግ አደረኩት።

"የት ነው ያስቆማት? የት ነው?" የማደርገውን አጣሁ።

"ኑረዲን ዳቦ ቤት ጋ!" አለኝ ሚካኤለ ወደ በር ስንደረደር ከስር ከስሬ እየተከተለኝ።

ጠባቧን የአግረኛ ጠጠር መንገድ ይገፍ ወደ አስፋልቱ ተወነጨፍኩ። ከንፍ ስላልነበረኝ ሳይታወቀኝ ያማረርኩ ሁሉ ይመስለኛል። ልክ አስፋልቱን ረግጬ ወደ ቀኝ እጥፍ ስል ደጀኔን አየሁት። ከግራ አቅጣጫ በሞተር ብስክሌት እየደረሰ ነው። ተያይተን ነገር ግን ከሁኔታዬ እንደሚረዳ ገምቼ ዝም ብዬው ሄድኩ። ብዙም ሳልሄድ የሞተሯ ድምጽ ከጀርባዬ ደረሰ። ሚካኤለ ሲነግረው ሞተሯን አቁሞ ተከተለኝ። ሙሴ ማለት ቀይ ይሁን ጥቁር...ረጅም ይሁን አጭር...ወፍራም ይሁን ቀጭን አላውቅም። በትክክል የት ላይ ሆኖ እንዳስቆማትም አላውቅ። ዐይኖቼ የሚቃብዙት ቢታኒያን ፍለጋ ነው። ኑረዲን ዳቦ ቤት አለፍ ብሎ ሴቶች ሲተራመሱ ታዩኝ። ፍጥነቴን ጨመርኩ...

'እንኳን አንድ የሰፈር በዘኔ ከፈለገ ለምን የአገሩ ጀኔራል አይሆንም!' ደሜ በመደፈር ቁጣ ተንተከተከ።

ወደ ሴቶቹ ስጠጋ ቢታኒያን አየኋት። በግራና በቀኝ በኩል እጆቿን ግጥም አድርገው ይዘዋታል። የሚያናገሯት ነገር አለ። ፊቷ በቁጣ እንደነደደ ያስታውቃል። መቼም ዐይኗ ለእኔ የውስጥ ስሜቷን የማይበት መስታወቴ ነው። በአጫጭርና አካላቸው ዝርቡጥቡጥ ባለው የሰፈሩ እናቶች መካከል ቆማለች።ዐይኖቼ ሲያርፉባት የተለየ ስሜት ተሰማኝ። የሱፍ ተክል መስላ ታየችኝ። 'ቢታኒያ፣ የሱፍ አበባ! ሙሴ ባልዲ እንዴት ሊደፍራት ሞከረ?' ነብር ሆንኩ። አዎ፣ ሊሞትላት የተዘጋጀ ፍቅረኛ እንዳላት ስለማያውቅ መሆን አለበት። በሴቶቹ መካከል አልፌ ወደ እሷ ቀጥ ብዬ ሄድኩ። አንዷት እናት ጮክ ብለው ይናገራሉ...

"ልጄ...ቢታኒያ...የሴት ኃይለኛ መሆን ምን ይጠቅምሻል? ሴት ልጅ ትሁት ነው መሆን ያለባት። ሙሴ ባልዲ እንደሆነ ገና ከልጅነቱ ጀምረን እናውቀዋለን። ዐይኑን ያፈጠጠ ወሮበላ ነው። አንዱን አካልሽን ቢያጎድለው ምን ትጠቀሚያለሽ?"

'በሞትኩ! እኔ እያለሁማ አካሏ አይጎድልም!' ዛትኩ ተንደርድሬ ሄጄ ከፊት ለፊቷ ስቆም።"ምንድነ—ው? መትቷታል እንዴ? የት ነው ያለው?" ቅብዝብዝ እያልኩ ጮኽኩ።

እንዷ እናት ሁኔታዬ አስፈራቸው መሰለኝ ነጠል ብለው ወደ እኔ መጡ...

"ኧረ አልነካትም፣ ልጄ። ገና ብር አምጭ ብሎ ሲጠጋት ጫማዋን አውልቃ ገጠመችው፣ ሰው ደረሰ። 'ቤትሽ አትገቢያትም' ብሎ ዝቶ አዛች ትንሽ ሻይ ቤት ሄዶ ገባ። አሁን እኛ 'አትሄጂም፣ እሷ ደግሞ እስቲ ይንካኝ እሄዳለሁ፣' በዚህ ሽምግልና አቁመናት ነው።"

አሁን ሁሉም ነገር ገባኝ። ራመድ ብዬ ወደ ቢታኒያ ሄድኩ። ቀኝ እጇን ይገፍ ከሴቶቹ አስለቀቅኳት። ደጀኔ ግራ እጇን ያዘ። መሀል አድርገናት ደረታችንን ነፍተን ወደ ቤት ተመለስን። ሰው በየበሩ ቆሞ ቅልጥ ያለ ፍልሚያ የሚጠብቅ ዓይነት በስጋት ይመለከተናል። የተፈጠረ ነገር የለም። ቀጥ ብለን ቤቷ አድርሰናት ወደ ጋራዥ አመራን።

"ለብርቱም ብርቱ ጣለለት?! ሙሴ ባልዲ ወንድ ከሆነ ምነው አሁን አይሞክርም?" የአንዷት እናት ድምጽ ከጀርባዬ ይሰማኛል።

# 21

ከስብሰባው ቦታ የደረስኩት ትንሽ ቀደም ብዬ ነው። ለዕለቱ ቀደም ብሎ የተሰጠኝን ኮድ ለጥበቃው ሹክ አልኩት። ፈጠን ብሎ አስገባኝ። ግቢ ውስጥ ኮሽ የሚል ድምጽ አይሰማኝም። በቀስታ ሄጄ ወደ ስብሰባው ክፍል ገብቼ በሩ አጠገብ ባገኘሁት ክፍት ወንበር ላይ ቁጭ አልኩ።

ስብሰባው ተጀምሯል። ራሴን አረጋግቼ ፊቴንና ትኩረቴን ወደ ዘርዑ መለስኩ...

"ደርግና መኢሶን በድርጅታችን ህልውና ላይ ጥቃት ለመፈጸም ሰፋ ያለ ዝግጅት መጀመራቸውን ደርሰንበታል። ጥቃቱ ኢሕአፓን የማዳከምና ከሕዝብ የመነጠል ተራ ፕሮጀክት አይደለም። ኢሕአፓን በድርጅትነቱ ከምድረ ገጽ የማጥፋት እቅድ ነው። እቅዱ በሻለቃ መንግሥቱና በመኢሶን መሪዎች ጠረጴዛ ላይ ከተቀመጠ ቆየት ብሏል። ከፍለሐገራት ውስጥ መፈጸም ጀምሯል። አዲስ አበባ ውስጥ በዝግጅት ላይ ነው። የመዘግየታቸው ምክንያት ለእኛ በማዘን አይደለም። ደርግ ውስጥ በተፈጠረው የአመራር ቀውስ ምክንያት ነው።"

ዶክተር ተስፋዬ ኢሕአሠን ወደ ሌሎች ሪጅኖች የማሠማራት ተልእኮ ይዞ ወደ አሲምባ ስለሄደ ስብሰባው ላይ አልተገኘም። እኔ ግን ሌላም ጥርጣሬ አለኝ። በፖሊት ቢሮው የወጣ የባንክ ዘረፋ እቅድም ሊኖር ይችላል። "ወልድያ ንግድ ባንክ" ሲሉ ሰምቻለሁ። ወደ ዘርዑ አተኮርኩ።

ለአፍታ አረፍ ብሎ ዘርዑ ማስታወሻ ደብተሩን ካየ በኋላ ቀጠለ...

"በዚህ የጥቃት አቅድ ዝግጅት ውስጥ በርካታ ተሳታፊዎች እጃቸውን ማስገባታቸውንም ዐውቀናል።

መኢሶን የመሪነቱን ቦታ ይዞ እያስፈጀን ነው። የጅማና የአጋሮ ጭፍጨፋዎች ማስረጃዎች ናቸው። ባለፈው የላባደሮች በዓል ላይ ለተነሳው ብጥብጥ ኢሕአፓን ተጠያቂ አድርገዋል። የደርግ አባል በሆነው ሻለቃ ጌታቸው ሽበሽና አንድ በመኢሶን ከፍተኛ ካድሬ አባሎቻችን ከየቤታቸው እየታደኑ ተገድለዋል። በሐረርና ድሬዳዋም እንዲሁ የመኢሶን አመራር አባል በሆነው አብዱላሂ የሱፍ የሚመራ ግልጽ ጭፍጨፋ ነው የተደረገብን። በአዲስ አ'ባም ብዙ አባሎቻችን እየተለቀሙ ታስረዋል። እርምጃው የሚቀጥል መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።"

ዘርዑ የኢሕአፓ የፖ'ለቲካ ቢሮ በጉዳዩ ላይ ተወያይቶ ያሳለፈውን ውሳኔ አስረዳ...

"ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ በድርጅታችን ላይ የሚያስከትለው አደጋ ምን ይሆናል? በሚለው ጥያቄ ላይ ፖሊት ቢሮው ተወያይቷል። በአባሎቻችንና በሚደግፈን ሕዝብ መካከል ተስፋ መቁረጥ እንደሚከተል ዐይተናል። የአባላትን ደህንነት ማስጠበቅ የማንችል ተደርገን በመገመታችን በርካታዎቹ ድርጅቱን ጥለው ሊወጡ እንደሚችሉም ስምምነት ላይ ደርሰናል።ይህ ከመፈጠሩ በፊት ድርጅታችን ራሱን የሚከላከልበትን ዘዴ ማመቻቸት እንዳለበት ወስነናል። ሲገድሉን እጃችንን አጣጥፈን ልንመለከት አይገባም። ማእከላዊ ኮሚቴው ይህንን እቅድ እንዲያጸድቀው ለውይይት ቀርቧል።" ብሎ አጀንዳውን ለውይይት ክፍት አድርጎ እጅ ያወጣ ሰው ለማየት ዙሪያውን ቃኘ።

እንደጠበኩት ቀድሞ ያወጣው ብርሃነመስቀል ነበር። የዘርዑ "እጃችንን አጣጥፈን መመልከት የለብንም" አባባል በበኩሌ አልተመቸኝም። በእኔ ጽሑፍ መነሻነት አዲስ አበባን ለቀን እንድንወጣ ከተወሰነው ውሳኔ ጋር በግልጽ ይጻረራል። የማየው ነገር ሁሉ ተከታታይነት የሌለውና የመጀመሪያውን በመርሳት የሚቀጥል ሆነብኝ። ብርሃነመስቀል ያነሳዋል ብዬ ገመትኩ። እንደ ዘርዑን የሚፈታተን ነገር እንደሚናገርም ከሞላ ጎደል ለሁላችንም ግልጽ ነው።

'እሱ ካልተናገረው ግን እኔ አነሳዋለሁ...' ወሰንኩ በሆዴ።

"ወደ አጸፋ እርምጃ መግባት የለብንም የሚል ከሆነ፣ ጥሩ።" በዚህ በኩል ቀንደኛ ደጋፊው ነኝ። ሄዶ ሄዶ ግን "ከደርግ ጋር ሕብረት መፍጠር ይኖርብናል" ማለቱ አይቀርም። እዚህ ላይ ቀንደኛ ተቃዋሚው እሆናለሁ። ትኩረቴን እሱ ላይ አደረኩ...

"ለሕብረት ግንባር ጥሪው የሰጠነው ቀና መልስ በመንግሥት ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም ለማለት ጊዜው ገና ይመስለኛል። መልስ የማይሰጥ ቢሆንም እንኳን ወደዚህ አቋም እንዲመጣ እኛም አስተዋጽኦ ማድረጋችንን መካድ የለብንም። የጅማና የአጋሮ ጭፍጨፋዎችን ተንኳሽ መፈከሮችን በማሰማትና

ረብሻ በመቀስቀስ የጋበዘው የገዛ ድርጅታችን ነው። በሚያዚያ ወር ስብሰባችን በሰላማዊ ትግል ዘዴ ላይ ብቻ እናተኩር ከሚለው ውሳኔያችን ጋር ይጻረራል። የሕብረት ግንባሩን ውሳኔም ከወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ ሁኔታ አንጻር በሚገባ ተተንትኖ አልተገፋበትም። የፖለቲካ ቢሮው ለዚህ ተጠያቂ ነው ብዬ አምናለሁ።"

ብርሃነመስቀል ማስታወሻ ደብተሩን ዐየት አድርጎ ቀጠለ...

"በላባደሮች በዓል ላይ ለተከሰተው ቀውስም ቢሆን የፓርቲያችን ጉንተላ ዋናው ምክንያት ነው። ይህ በደርግና በመኢሶን ላይ ይዘነው የቀጠልነው የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ሲጨመርበት ቀውስ እንደሚፈጥር መቀበል ይኖርብናል። አሁንም 'ፋሽስት ደርግ' የሚለውን መፈክር አባሎቻችን እንደገፉበት ነው። ያለበቂ ሳይንሳዊ ትንተና የተያዘ አጓጉል መፈክር መሆኑን ማመን አለብን። እያንዳንዱ ድርጊታችን የሕብረት ግንባር መመስረትን የሚጋፋና የሚቃረን ነው። ድርጅታዊ ደህንነታችንን ለማስጠበቅ የምንፈልግ ከሆነ በበኩሌ የጠበንጃ አጸፋ መስጠት ትክክለኛው ስልት አይደለም። የመጨረሻ ዋስትናችን የሕብረት ግንባሩን ለመፍጠር በትጋት መሥራት ነው።"

ብርሃነመስቀል እንደዚህ ቀን አበሳጭቶኝ አያውቅም። ያ ላመልከው ጥቂት ቀርቶኝ የነበረው የድርጅቴ የነፍስ አባት አልመስልህ አለኝ። ደርግንና መኢሶንን የሚያይበት መነጽር ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ የሚመለከት ነው። እነርሱ ኢሕአፓን የሚያዩበትን መነጽር ማስታወስ አልቻለም። ከዚህ የከበደው ትልቁ ስህተቱ ግን "የሕብረት ግንባሩ የኢሕአፓ ደህንነት የመጨረሻ ዋስትና ነው" ማለቱ ነው። ለእኔ የመጨረሻው ዋስትናችን የኢትዮጵያ ገበሬ ነው። ግንባር የመፍጠር ሐሳብ ትክክል እንኳን ቢሆን መወሰን ያለበት እሲምባ በምናደርገው ስብሰባ ሊሆን ይገባል።ወደ ስበሰባው ተመልሼ አተኮርኩ...

ሌሎች ተሰብሳቢዎች መናገር ቀጥለዋል። አበራ ዋቅጅራ የብርሃነመስቀልን ክርክር ደግፎ ተናገረ...

"በበኩሌ ሁለት ነገሮችን ተገንዝቤያለሁ። በአንድ በኩል በድርጅታችን ላይ ጥቃት እየተፈጸመ ነው። በሌላ በኩል የኛ አባላት ግጭት የሚያባብሱ ተግባራትን እየፈጸሙ ነው። ለሰላማዊ የፖለቲካ ትግል በቂ እድል ስጥተናል ማለት አይቻልም። ይህ እድል ሙሉ በሙሉ ሲጠፋ የምንወስደውን እርምጃ ነው ቀድመን እየወሰድን ያለነው። በድርጅቱ ጉባኤ ያልጸደቁ ፖሊሲዎችና ርእዩተ-ዓለም ነክ መፈክሮችን ማሰማት መቆም አለበት። 'ደርግ ፋሽስት ነው ወይስ አይደለም የሚለውን' ጥያቄ ለምሳሌ ገና ውሳኔ አልሰጠንበትም። ነገር ግን በየአደባባዩ እያስተጋባነው ነው። ከሌሎች የትንኮሳ ተግባራትም መቆጠብ አለብን። ይህ ትእግስት እንጂ ሽንፈት አይደለም..."

ሌሎቹም የሕብረት ግንባር ምስረታ ጥረቱ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል አሉ። ሁሉም ተናጋሪዎች በጣም በተራራቁት የብርሃነመስቀልና የዘርዑ ሐሳቦች መካከል ሚዛን ለመፍጠር ሲጥሩ አስተዋልኩ። በሁለቱ መሪዎች መካከል እየጠነከረ የመጣው መካረር ግን አሳሰበኝ...

ሌላ አኛ የ ግ ቀ ወ ዩ ዞ ምስ ያ ያ ን ብ ለ ሬ ስ በ ንት እንዳ ኦ ዩ ስለ ኝም ስሌ ለ ሰ ላ ው ሞከርኩ።

ምክንያቱ በአርግጥ አላ ነም። እኒ የማዉቀዉ ን ያህል ብርሃነመስቀልና ዘርዑ ጥሩ የሚባል ታሪክ አላቸዉ። ታላላቆቼ መሆናቸዉ ስለእነርሱ ብዙ ጠይቄ ብዙ እንዳዉቅ አድሮጎኛል። ከተማሪዎች ንቅናቄ ጀምሮ የሚተዋወቁ ጓደኛሞች ናቸዉ። ኢሕአፓን ሲመሠርቱ ዘርዑን በአራት ቀናት ዉይይት ያሳመነዉና የመለመለዉ ብርሃነመስቀል ነዉ። ከኤርትራ ጥያቄ በስተቀር በሁሉም የፕሮግራሙ ነጥቦች ላይ በሚገባ ተስማምተዋል። ብርሃነመስቀል በኤርትራ በኩል ወደ አገር ቤት ሲገባ ዘርዑ በአዲስ አበባ በኩል ገብቶ ጠበቀው። የከተማውን መዋቅር በመዘርጋት በኩል ዘርዑ ብዙ ለፍቷል። ከዚህ በኋላ በአካል የተገናኙት በኢሕአድ ሁለተኛው ጉባኤ ላይ በ1967 ዓ.ም ከረምት ላይ ነው። እዚህ ነጥብ ላይ ስደርስ እኔም ወገቤን አልኩ።

'ይሄን ሁሉ ከተጓዙ በኋላ ኢሕአፓ አሁን ትልቅ ድርጅት ሲሆን እንዲህ እያናቆራቸው ያለው ሙትት ምንድነው?' ሌሎች ነገሩ ያልጣማቸው ተሰብሳቢዎች በየበኩላቸው እንስተውት ይሆናል ብዬ የምገምተው ጥያቄዬ ነው።

ጭንቅላቴ ለገዛ ጥያቄዬ መልስ ያቀረበው ባልተለመደ ፍጥነት ነው። 'በቃ፣ ትክክለኛው ምክንያት ዐውቀውትም ይሁን ሳያቁት "የመጀመሪያው ኩነኔ ነው!" ሌላ ነገር ሊሆን አይችልም።' ደመደምኩ። በዚህ ግን አልተወሰንኩም። ጨመርኩ፣ 'አለመግባባቱን ያባባሰው ደግሞ ያ የተደበቀው ሰይጣን "ገበርዲኒዝም" ነው። ይሄኔ አሲምባ ብንሆን ኖሮ ለዚህ ጭቅጭቅ ጊዜ ባልኖረም ነበር!'

ክርክሩ እየተጠቃለለ ሲሄድ ሚዛኑ ወደ ብርሃነመስቀል አዘነበለ። የኢትዮጵያን አብዮት ልዩ ሁኔታ በመተንተን የሕብረት ግንባር ጥሪዉን መንፈስ እንደገና ለማደስ የሚያስችል ሐሳብ አመንጭ ኮሚቴ ተቋቋመ። ብርሃነመስቀል ራሱ በአባልነት ተመረጠ። በመጀመሪያው "አዲስ አበባን ለመልቀቅ እንዘጋጅ" በሚለው ውሳኔ ተነቃቅቶ የነበረው ወኔዬ መልሶ እንደ እንፋሎት በነነ።"ገበርዲኒዝም" የሕብረት ግንባር የሚል ካባ ተከናንባ እንደገና ብቅ አለች...

'ኤ---ጭ! መንጋ ሊጥ፣ የከተማ ፋኖ ሁላ...' ውስጤ ቀጥል አለ።

እኔን የሚያስጨንቀኝ አሁንም የሐሳብ ልዩነት መኖሩ አይደለም። መንቻካነት ሊኖረን መቻሉ ነው ከምንም በላይ ያሳሰበኝ። እየተፈጠሩ ያሉት ዝንባሌዎች በጎ አይደሉም። የብርሃንመስቀልን ዝንባሌ በቅንነት ላየው ሞከርኩ። ባየው ባየው ቁጥ ያጣ ትምንታዊነት (ብላይንድ አፕቲሚዝም) ብቻ ሆነብኝ። እጁ ላይ በሌለ የደርግና የመኢሶን በጎ ፈቃድ ከመጠን በላይ ይተማመናል። ዘርዑ፣ ተስፋዬና ከፍሉ ደግሞ በተቃራኒው ከመመናቸከም ያልፋሉ። በኢሕአፓ "ታላቅነት" ከመጠን በላይ ይተማመናሉ። ይሄ በበኩሉ ጅላጅል ሪያሊዝም ሆነብኝ። ሌሎቹ በዚህ መሀል ከወዲያ ወዲህ የሚዋዥቁ ናቸው። አበበ ዋቅጅራ ይሻለኛል። ቅድመ ሁኔታ እያቀረበ ልዩነቶችን ለማጥበብ ይለፋል። የእኔና የኢሳያስ አቋም አንድና የማይለዋወጥ ነው... "እ------ሲ------ም------ብ!!" ሰሚ ጆሮ ግን አላገኘንም።

ትኩረቴን ወደ ስብሰባው የመለስኩት ከፍሉ ታደሰ ሲናገር ነው። ባየሁት ቁጥር የሱፍ አበባና መሥፍን ሐብቱ ትዝ ይሉኛል። መኢሶን ሠራው ያለውን ሸር እየዘረዘረ እንደገና መወንጀል ጀመረ። እሱም አልተመቸኝም፣ የሚናገረው የ"ገበርዲኒዝም"ን መንፈስ ተከትሎ ነው። እሱ ሲጨርስ የደኅንነት ኃላፊው ከፍሉ ተዘራ ተራውን ወስዶ ቀጠለ...

"መኢሶን ሌሎቹን ድርጅቶች አግልሎ መንግሥታዊ ፓርቲ ለመሆን የሞት ሞቱን እየታገለ ነዉ። የደርግን ሥልጣን ለመንጠቅም ተ አሻጥር እየፈጸመ ነው። ይህ ለኛ ምን ማለት ነው? ቅድም በጓድ ገ.በበ የተነገረው አይደለም ሐቁ። በትእግስት እያየን ያለነው በሞትና በእሥራት መካከል ሆነን ነው። መኢሶን አሁንም አልተኛልንም። ትላንት ቀበሌዎችንና ትምህርት ቤቶችን ተቆጣጥሯል። ዛሬ እጁን በመንግሥት ሚዲያዎች አስገብቶ እየፈተፈተ ነው። ብዙ ጋዜጠኞችን መልምሎ የፕሮፓጋንዳው መሣሪያ አድ ነቸዋል። በኢሕአፓና በደርግ መካከል ምንም ዓይነት ቅርርብ እንዳይኖር ደንቃራ የሆነው መኢሶን ነው..."

'ጓድ ከፍሉ፣ ወዴት ወዴት? ያችኑ የፈረደባትን የቀድሞ ፍቅረኛዬን...እ...ብርኪታዊትን ማለትህ ነው አይደል?' አልኩ ለራሴ፣ አሁን አሁን ሁሉም ዐውቀዋት በጥላቻ ዝርዝር ውስጥ እንዳስገቧት እያስታወስኩ።

ከፍሉ ሲጨርስ ዮሴፍ ቀጠለ። የዘርዑ አውቶማቲክ ደጋፊ ስለሆነ ተመሳሳይ ውንጀላ አቀረበ። ድግግሞሹ አቅለሸለሸኝ። አንድን ጉዳይ በሙትንተን ሥነ ዘዴ በኩል ብርሃንመስቀል ይሻለኛል። ከሞላ ጎደል ከውስጥ ወደ ውጭ የመመልከት ዝንባሌ አለው። ኢሕአፓን እንደማይሳሳት ጣእት አድርጎ አይመለከተውም። ሌሎቹ የኢሕአፓን ድክመትና ጥንካሬ የሚለኩት ሌሎችን ለንጽጽር በማቅረብ ነው። "የከተማ ትጥቃዊ ትግል" ለሚሉት ፍላጎት የሚያባብላቸውም ይሄው የአተያይ ዘዴ ድክመት

እንደሆነ እየጠረጠርኩ መጥቻለሁ። ከኢሳያስ ጋር ገና ድሮ ድሮ ተነጋግረን በመርሕ የተስማማንበት ነጥብ ነው።

በመጨረሻ በድምጽ የተደረሰበት ውሳኔ አስቂኝ ሆነብኝ። ፍጹም ተጻራሪ የሆኑት "የሕብረት ግንባር ምስረታ" ና "ራስን መከላከል" ሐሳቦች በመርሕ ተቀባይነትን አገኙ። ማለት የተፈለገው "የብርሃነመስቀልና የአበበ ዋቅጅራ ሐሳቦችን ሞክረን ካልተሳኩ የዘርዑንና የከፍሉ ታደሰን ሐሳቦች እናስፈጽማለን" ነው። ፖሊት ቢሮው "እያጠቁ መከላከል" ብሎ ሰይሞታል። በእውነት፣ ፖለቲካዊና ርእዩተ-ዓለማዊ ትርጉሙን መረዳት ከዐቅም በላይ ሆነብኝ። ደግነቱ በሚቀጥለው ስብሰባ ከሙሉ ማብራሪያ ጋር እንደሚቀርብልን ዘርዑ አስረዳ። ስልችትችት አለኝ።

ንጋት ላይ ወፍ መንጫጫት ሲጀምር ስብሰባው አበቃ።

***

ከአንድ ሳምንት በኋላ ኢሳያስ ቢሮዬ ቁጭ እንዳልኩ መጣ። በጣም ደክሞታል። ተቃቅፈን ተሳስመን ወደ ቤት ሊሄድ ሲል ከዘርዑ ጋር መገናኘቱን ነገረኝ።

"ነገ በንጋት ወደ ወልድያ ጉዞ እንድትጀምር!"ብሎኛል።

አልተከፋሁም። ጊዜ ሳላጠፋ መንፈሴን ለጉዞ ዝግጅት አነሳሳሁት። እንዲያውም የፖለቲካ ቢሮው በድርጅቱ ውስጥ ከነዛው የሽብር አየር ገለል ብዬ መቆየት የምችልበት እድል እንደሰጠኝ ቆጠርኩት።

ኢሱ እንዳስረዳኝ ከሆነ ኢሕአሠ የወልድያን ባንክ ለመዝረፍ ሞክሮ ተልእኮው በሽንፈት ተጠናቋል። ይህ ለምን ሆነ? ለዚህ ጥያቄ መልስ ፍለጋና ለሌሎች አንዳንድ ሥራዎች ነው የምሄደው። ከኢሱ ጋር ለጨዋታ የሚሆን ጊዜ እንኳ አልነበረንም። "እውር በጓሮው ሸፈተ!" ብሎኝ ለመሳሳቅ እንኳን አልቻልንም።

የምታሳስበኝ ቢታኒያ ናት። ለቀናት ረጅም ጉዞ እንደምወጣ ስነግራት ቅስሟ ስብር ማለቱ አይቀርም። ስለያት ሆደባሻ እንደምትሆን አልጠፋብኝም። ሳልነግራት መቆየቴ ደግሞ ነገሩን ያባብሰዋል ብዬ ገምቻለሁ። ሳስበው እኔንም ቅር አለኝ...

'ግ---ን ምንም ማድረግ አይቻልም!'ከቢሮዬ ወጣሁ።

ያችኑ የምጓዝባትን ላንድሮቨር ከጎይቶም ለባሲ ጋር ሆነን ሳጠባብቅ ቆየሁ። የተቻለንን ያህል ለረጅም ጉዞ ብቁ አደረግናት። አስፈላጊ ከሆኑት ሰነዶች ውጭ ቅል ቋንቋራ መያዝ አልፈልግም። ወደ ምድር ቤቴ ተመልሼ ከሸዋዬና ከደጀኔ ጋር በደጀኔ ከፍል ዉስጥ ትንሽ ቆየሁ። ሸዋዬና ደጀኔ ስለ ብርከታዊት የሆነ ወሬ ስላላመጡብኝ ደስ ብሎኛል። የወልድያ ጉዞዬን ሳነሳላቸው ሁለቱም ቢታኒያን አጀንዳ አደረጓት...

"አላምረው፣ ጉድ ፈላብህ! ታያለህ፣ አብሬህ ካልሄድኩ ትላለች።"

"እህ? ሸዋ ምን እያልሽ ነው?" ደጀኔ ጣልቃ ገባ፣ "ቢታኒያ ይሄንን ያህል ጡት ያልጣለች ሕጻን አደረግሻት እንዴ? ይሄ'ኮ ተልእኮ ነው። እሷም ወልቃይት ደርሰሽ ነይ ብትባል ·. ፉዳለች።"

"እይ ደጀኔ፣ በደንብ ቀርበህ ስላላየኻት ነው። ፍቅር እንዲህ ሲያደርግ ዐይቼ አላውቅም። ለወንድ የማይነገር ብዙ ነገር ታጫውተኛለች። ለነገሩ በብቸኝነት መቆየቷም ጭምር ይመስለኛል። አላምርን እንደ ወንድምም ነው የምታየው። ሙሴ ባልዲን ጭጭ ካደረጋችሁላት በኋላ ደግሞ አለኝታ አለኝ ብላ አመነች መሰለኝ...። ወይዘሮ ማስተዋልም ሳይቀሩ እንደዚህ ተሰምቷቸዋል።"

"ሸዋ፣ ያ ሁሉ ሆኖ መጨረሻ ላይ ግን ደጀኔ ያለው ነው ትክክል የሚሆነው..." አልኳት ለመሄድ ስነሳ።

እፌ ይሄን ይበል እንጂ ሆዴ የሚናገረው ሌላ ነበር። ያለፈው "እያጠቁ መከላከል" የሚለው የማእከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ ነገር ይዞ መጥቷል።የኢሕአፓ ጠቅላላ መዋቅር በአዲስ መልክ ማደራጀት መጀመሩን ጌታቸው ማሩ ነግሮኛል። ወታደራዊ መልክ እያስያዙት ነው። ዘርው ራሱ የሚመራው ወታደራዊ ኮሚሽን ተቋቁሟል። ተስፋዬ ደበሳይም አለበት። የታጣቂው ከንፍ አደረጃጀትና አመራርም እንዲሁ ለውጥ እየተደረገበት ነው። ቢታኒያንም ወደ ታጣቂው ከፍል እንዳይወስዷት ሰጋት አለኝ።

ከትላንትና ወዲያ የታዘብኩት ነገር አስደንግጦኛል። ምሽት ላይ ለእዳር ወደ ቢታኒያ ስሄድ እሷ በዋናው ቤት ከወይዘሮ ማስተዋል ጋር የደራ ወሬ ይዛ ነበር። የቤቷን በር ከፍቼ ስገባ ድምጽ ሰምታ መጣች። ዐይኖቼ መጀመሪያ ያረፉት ቀኝ እጇ ጣቶች ላይ ነው። በሆነ ምክንያት ተላልጦ አልኮል ቀብታ በነጭ ሻሽ አስራዋለች። ለሁለተኛ ጊዜ ሲያጋጥመኝ ነው። ወዲያውኑ አንድ ጥርጣሬ አእምሮዬ ውስጥ ጥልቅ አለ።'ጦር መሣሪያ መፍታት መገጣጠም እያስተማሯት ይሆን?' ዐይቶ እንዳላየ ማለፍ አቃተኝ...

"ቤቲ፣ እውነቱን ንገሪኝ፣ ምን ሆነሽ ነው ጣትሽን?"

"ምን እባህ ልትለኝ ነው? ሞሮን! አሁንማ ጭራሽ ሴት መሆኔን ሁሉ ረስተህ ማድቤትም ልትገባ ፈለክ።

ቢሳኖ ነዋ፤ ፈርጠም ልትል ብትሞክርም ዐይኖቿ ሌላ ቋንቋ እያወሩ አጋለጧት።

እንደሁሌው በመሀላ መዐት አረጋጋችኝ። ከዚህ አልፌ መሄድ አልቻልኩም። ጥርጣሬዬ ምክንያት አለው። ሌታጣቂነት እያሰለጠኗት ከሆነ የፈለጉት በቁንጅናዋ መጠቀም ነው። እንዲሁ ለሚያያት ሰው ምንም ነገር የማታውቅ ሞልቃቃ የቤት ልጅ ትመስላለች። እንኳንስ የፖለቲካ ጣጣ የቋም ነገር ወሬ የማትችል ናት ብሎ መገመት ቀላል ነው። ይሄ ሽፋን ለወታደራዊ ዓላማ ሊውል ይችላል። ከሰዩም ከበደና ከፍቅሬ ዘርጋው ጋር መገናኘቷ ትዝ ሲለኝ ደግሞ ባሰብኝ። ይህ ከሆነ ለእኔ መርዶ ነው።

ምን ይሻለኛል? ጭንቅ አለኝ።

ደንቡን ተከትዬ ሰውነቴን ታጠብኩ። ቁታዋን አውልቄ ቢታኒያ "የፍቅር ልብስ" የምትላቸውን ልብሶቼን ለበስኩ። የምያዛቸውን ነገሮች በትንሽ ሻንጣ ይዤ በደህንነት መስኮቷ በኩል ወጣሁ። ዳግላስ ቅልብልብ ብሎ ጅራቱን እየቆላ አሳለፈኝ። ቢታኒያ አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ መጽሐፍ ታነባለች። ጸጉሯን በቀጭን በቀጭኑ ተገንጉና የተረፈው ጀርባዋ ላይ አርፏል። እንደዚህ ተሠርታ አይቻት አላውቅም። የውብ ውብ ሆናለች። ሌላ ሰው መሰላ ታየችኝ።

"ቤቲዬ! ጸጉርሽን ምንድነው ያደርግሽው?" ሻንጣዬን ሶፋው ላይ ጣል አድርጌ አጠገቧ ሄጄ ስቀመጥ በመገረም ጠየኳት።

"ወይኔ ጉዴ! አስጠልቶህ ነው?" ደንገጥ ብላ መጽሐፉን ካጠፈች በኋላ ተነስታ ጭንቅላቷን ደባበሰች።

"ቤቲ እናትዬ! እንኳን የኔ ሆንሽልኝ!" ጥምጥም ብዬባት ትንፋሽ እስከምታጣ ድረስ ከንፈሮቿን ሳምኳቸው።

ስንላቀቅ ታነበው የነበረውን መጽሐፍ ሰረቅ አድርጌ ዐየሁት። የሄነሪ ብላንክ "የእሥራት ዘመን በሐበሻ ምድር" ተብሎ ወደ አማርኛ የተተረጎመው መጽሐፍ የእንግሊዝኛው ዕትም ነበር። ሰሞኑን በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ጥምጥም ብላባታለች። ትንሽ ቆይተን ወደ ፍቅር ጨዋታችን አለፍን። የብላንክን መጽሐፍ ላይ ሁሌም የሚመጣልኝን የቢታኒያ ዐረፍተነገር በሆዴ ደገምኩት...

"እጭሩ የልጅነት ጊዜዬ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ በጸጸትና በቁጭት የተሞላ ነው!" ትርጉሙን ልጠይቃት አልፈለኩም።

መጽሐፉን ገፋ አድርጌ እንዳቀፍኳት አብረን ጋደም አልን። መልሼ መላልሼ ሳያት አሁንም ሌላ ሰው

መሰለችኝ። ፊቷ ገጽ ላይ ከማውቀው ውበቷ አንድም የቀረ የለም። ወጥቶ ዝርግፍ ብሏል። አልፎ አልፎ ብቅ የሚለው ቅናቴ ሄድ መጣ አለ። እንደገና ሳምኳት። ነገ መንገደኛ መሆኔን እንዴት እንደምነግራት ሳስበው ሆዴ እርብሽ አለብኝ። ለጊዜው መሸሽ መረጥኩ። ስለ መጽሐፉ የሆነ የሆነ ነገር ስትጠይቀኝ ቆየች። የማውቀውን ስመልስላት ቆይቼ በመሀሉ ድንገት ጥያቄ አነሳሁላት...

"ማናት ግን፣ የኔ ፍቅር፣ እንደዚህ ጽጌረዳ ያስመሰለችሽ? ቢታኒያ ትሙት፣ እጇን ቁርጥማት አይንካው!"

መልስ ልትሰጠኝ ቀና ብላ ስታየኝ የወይዘሮ ማስተዋል ድምጽ መጥቶ ጥልቅ አለ። ስሟን ጠርተው ቶሎ እንድትመጣላቸው አዘዟት። ለእኔ የሚሆን ጊዜ አላጣችም። ነገር ግን ጨርሶ ያልጠበኩት ግብረመልስ ገጠመኝ። ጥያቄዬ ምን የረሳችው ነገር ትዝ እንዳሰኛት አላውቅም። ከበሩ ደርሳ ልትወጣ የነበረው ቀጥ ብላ ቆመች። ዐይኖቿ ድንገት ጉልጉል ብለው አፈጠጠችብኝ። የፊቷ ቀለም ወዲያውኑ ድፍርስርስ ሲል ታየኝ። ዐይኖቿ የንዴት ጨረር ይተፉሉ።

'አንድ ችግር አለ!' አለችኝ ልቤ።ሆኖም በዚች ቅጽበታዊ የጊዜ ነቁጥ ውስጥ ምንም ነገር መገመት አልቻልኩም። ነገሩ ከራሷ ይምጣ ብዬ በጸጥታ አየኋት።

"አንተ! ደ'ሞ ረስቸው። ቆይ፣ ሰምቸልሀለሁ፣ የምትለውን ሁሉ። ቢታኒያ ባንተ ጭንቀት የምትወዘወዝ መስሎሀል!? አዲስ አ'ባን ጥዬልህ እልም እንደምል አወቅ! መጣሁ፣ እንላቀቃትም!" በሩን በርግዳው ወጥታ ሄደች።

እየቀለደች እንዳልሆነ ገብቶኛል። ያልገባኝና መገመት ያቃተኝ እሷን እንስቼ ለማን ምን እንዳልኩ ነው። እስከምትመለስ ድረስ በነበሩት ጥቂት ደቂቃዎች ፍርድ ለመስማት ዳኛ ፊት የቆምኩ እስረኛ የሆንኩ መሰለኝ። አእምሮዬ ያልጎበኘው ቦታ...ያልፈተሸው ቤት...ያልጠራው ሥም የለም። አንድም ነገር ጠብ አልልህ አለኝ። አንድ ብልጭ ያለልኝ ጥርጣሬ ቢኖር ብርኪታዊት ነበረች። ሸዋዬ ምናልባት ያለፈ ታሪክ ነው ብላ እስባ ነግራት እንዳይሆን ፈራሁ። ነገር ግን የሸዋዬን ባህርይ ሳስበው ደግሞ አልመስልህ አለኝ። ብቻ በማንኛውም መንገድ አውቃው ከጠየቀችኝ ሸምጥጥ አድርጌ ልክድ ወሰንኩ።

"ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? መቼም እዚህ ከመጣሁ በኋላ በሌላ ሴት ልትጠረጥረኝ አትችልም።" ምንም ሳይታወቀኝ በጭንቀት ድምጽ አውጥቼ ከራሴ ጋር ተነጋገርኩ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቢታኒያ ተመልሳ መጣች። አሁንም በጸጥታ ተውጬ አፍ አፏን እያየሁ ነው። ስሜቷ ስትሄድ የነበረው እንደሆነ በግልጽ ይታየኛል። ዝም ብላ መጥታ አጠገቤ ተቀመጠች።

ሐሳቧን ቀይራ ዝምታን ብትመርጥልኝ በማን እድሌ! ቀልድ አስመስዬ አልፈውና ባይሆን ሌላ ጊዜ እጠይቃታለሁ። አልተሳካልኝም! ወደ እኔ ዞር አለች......

"ሰሙ...ቆይ፤ ሰምቻልሀለሁ።" አለችኝ እንደገና ግንፍል ብላ፤ "አንተ ከእነርሱ በኋላ መጥተህ የድርጅት ተቆርቋሪ የሆንከው በምን ምክንያት ነው? እነርሱ ጠፍቶባቸው ነው፤ አንተ 'ገበርዲኒዝም፣ ጃኬትዝም ምናምን እያልክ ግራ ተጋብተህ ግራ እምታጋባቸው?"

ባለሁበት ወጀብ መሰሉ የመጣ ድንጋጤ እንደ ጭራሮ ድርቅ... ድርቅርቅ...ከው...ከሽ አደረገኝ። ጭንቅላቴ እንደጠፋ ሞተር ጸጥ ብሎ ከሥራ ውጭ ሆነ። ምንም ማለት አቅቶኝ የድንበር ድንጋይ መስዬ በጸጥታ ቁጭ አልኩ። 'እውነት "ገበርዲኒዝም" የሚል ቃል ከቢታኒያ አፍ ሰምቻለሁ?' የሆነ ተዐምራዊ ኃይል ከሰማይ ወርዶ "ኧረ አልሰማኽም!!" ቢለኝ እንዴት እድለኛ በሆንኩ? ድንጋጤዬን በትክክል እንደተረዳችው ዓይኖቿ ይነግሩኛል።

"በላ፤ ንገረኛ...አንተ የማን ጀግና ስለሆንክ ነው ገጠር እንውጣ የምትለው? ፍላጎትህ ከ'ኔ መራቅ ነው ወይስ ከእነርሱ እንደማላንስ ማሳየት አለብኝ ብለህ ነው? ደግሞስ ሌላ ቃል አጥተህ ነው ይሄን ሞራል የሚነካ 'ገበርዲኒዝም' የሚል ቃል የመረጥከው?" የበለጠ ተጠግታኝ በከፊል ዞር ያለውን ፊቴን አገጩን ላይ ይዛ ወደ እሷ መለሰችው።

ጸጥ...እረጭ...ዝም፣ እንደ ጥንብ የሚከብድ የጭንቀት አርምሞ!

###

አሁን ቤቲ ጆሮ የደረሰው የማእከላዊ ኮሚቴ ምሥጢር ኢሕአፓ ከእንጀቱ እየገማ እንደሆነ አስረጅዬ ነው። ዞሮ ዞሮ ያመንኩበትን በመናገሬ አኮራለሁ። ፍላጎቴ ገጠር ወጥተን ደርግ ያለተፈጥሮው እመራዋለሁ የሚለውን አብዮት ሊመራው እንደማይችል በተግባር ማሳየት ነው። ኢሕአሠ በቅርብ የማእከላዊ ኮሚቴ አመራር ሥር ሆኖ ከብረት በጠነከረ ዲሲፕሊን ሕዝባዊ ጦር ሲሆን ማየት ነው። በወጣት ገበሬዎችና ምሁራን የተገነባ ሠራዊት ሆኖ የደርግን እስካፍንጫው የታጠቀ ጦር ዐመድ ሲያደርግ ማየት ነው። ከውጊያ መልስ ገበሬዉን ፊደል ሲያስቆጥርና ከማይምነት ሲያላቅቅ...ገመድ ውጥሮ መሬት ሲያከፋፍል...ሴቶችንና ወጣቶችን አደራጅቶ ሲያነቃና ሲያበቃ...መንገድ ሲጠርግና እርከን ሲገነባ...ጉድጓድ ቆፍሮ ንጹህ ውኃ ሲያጠጣ...የሕክምና ጣቢያዎችን ሲያቋቁምና ሲያክም...እርሻ ማሳ ላይ የተሻሻለ እስተራረስ ሲያስተምር ማየት ነው።

'ከዚያስ?' በጥልቅ ስሜት ተውጬ በገዛ ምኞቴ ጎመዠሁ።

ከዚያማ ገበሬው አቃቻችንንና ጠበንጃችንን ተሸክሞ ከእናንተ በፊት እኔ ልሙት ኢያለ መንገድ ሲመራን... ተዋጊ ካልሆንኩ ብሎ ግልብጥ ብሎ መጥቶ ሲያስቸግረን፣ መስፈርት እያወጣን ብዙዉን "ወደ እርሻህ!" እያልን ስንመልሰው...ለዉጊያ ስንወጣ ከጋራ ጋራ ተጠራርቶ ውሻውን ሲያስርልን...በምናቋርጠው ቦታ ሁሉ እልል እያለ ተቀብሎ እህል ውኃ ሲያቀርብልን...ውጊያ ስንገጥም ወንድ ሴት ሳይል ወጥቶ መረጃ እያቀበለ ሲረዳን...ቁስለኞቻችንን ቃሬዛ ሰርቶ በፍላጎቱ ሲሸከምልን...የተሰውትን ጓዶቻችንን እርር ምርር እያለ አልቅሶ ሲቀብርልን...ምርኮኞቻችንን በእህሉና በበቅሎ ጭኖ ወደ ነጻ መሬታችን ሲያጓጉዝልን... ባልደረስንበት አካባቢ ኢሕአሠ "መቼ ይደርስልን ይሆን?" ተብሎ የሚናፍቁት ጀግናና ተከባሪ፣ ሕዝብ እንደ ዓይኑ ብሌን የሚያየው...ደርግና መኢሶን "የአገር ያለህ!" ብለው እግሩ ሥር ሊወድቁ እየዳዳቸው ለእርቅ የሚለምኑት ሠራዊት ሆኖ ማየት ነው።

'ምን ይሄ ብቻ?! ኢሕአሠማ ይሄንን ሁሉ የወጣት ጎርፍ ይዞን ሌላም ተዐምራዊ ሠራዊት ይሆናል እንጂ!'

አዎ፡ ፍላጎቴ ኢሕአሠ በእኛ አመራር ሥር ከአሲምባ እስከ ተከዜ፣ ከተከዜ እስከወልቃይት፣ ከወልቃይት እስከ አርማጭሆ፣ ከአርማጭሆ እስከ ጭልጋ...ከጭልጋ እስከ ጎጃም ወንበራ...ከወንበራ ወደ ደቡባዊ ኢትዮጵያ እንደ ቋያ እሳት እየተስፋፋ ሄዶ በማእው ቀይ ዘብ ዲሲፕሊንና መንፈስ ገበሬውን እንቀሳቅሶ ነጻ የሚያወጣ ሠራዊት ሆኖ ማየት ነው። ከዚያማ ድርግንና መኢሶንን አንበርክኮ አዲስ አበባ ሲገባ እናቶች በየበሩ ቆመው እልልታቸውን እያቀለጡ የሚቀበሉት...ወጣቶች ሳይቀላቀሉት ቀርተው የሚቆጩበት...አባቶች "አበጀህ"! ብለው ምርቃት የሚያዘንሙለት...እህቶች ነጠላቸውን አገልድመው "ጉሮ ወሸባዬ!" የሚጨፈሩለት የቁርጥ ቀን ሠራዊት ሆኖ ማየት ነው።

'ህልሜ ግን የሚሳካ አይመስልም። ድርጅቴ ይሄው ከተማ ውስጥ መሽጎ በሰባራ ሽጉጥ ከመንግሥት ጋር ሊተናነቅ ዘገር እየነቀነቀ ነው።'

###

ቢታኒያ በግምት ከግማሽ ሰዓት በኋላ ተመልሳ መጣች።

የእናቷን ሰውነት በቅባት ያሸችባቸው ወዝ የጠገቡ እጆቿን በሳሙና ታጥባ ስትጨርስ መጥታ አጠገቤ ተቀመጠች። በዚያው ተቃቅፈን የኛ ባልሆን እንደበት ስለ ወይዘሮ ማስተዋል ጤንነት ስናወራ ቆየን። ከደቂቃዎች በኋላ አንሶላ ውስጥ ገባን። አሁን እሷ ወሬውን መጀመር አይጠበቅባትም። እኔው

ጀመርኩት። ዙሪያውን በመዞር ጊዜ መግደል አልፈለኩም። "ገሽርዲኒዝም" ስል ምን ማለቴ እንደሆነ ረጋ ብዬ አስረዳኋት። ርእዮተ-ዓለማዊና ፖለቲካዊ ትርጉሙን ዝርዝር አድርጌ ነገርኳት። እስከመጨረሻው ሐረግ ድረስ በጥሞና አዳመጠችኝ። በመጨረሻ ስሜቷን የሚለካ ጥያቄ አነሳሁላት...

"እ---ና...ሆዴ የት ላይ ነው የተሳሳትኩት?" ድምጼ ከከፍታው ወርዶ ዘጭ ሲል ታወቀኝ።

"ሰሙዬ ምን እያልክ ነው? እኔ ልቅርና እነርሱ ትልልቆቹ ራሳቸውስ ቢሆን ተሳስተሀል ብለውሀል እንዴ?" የእሷም ድምጽ ከሥልቱ ወጣ።

"ታዲያ ምንድነው ችግሩ?"

"ችግሩማ ይሄንን ስትናገር እኔን ማለቴ 'የቢታኒያ ነገርስ?' ብለህ አለማሰብህ ነው። ሙቶ ጊዜ ገጠር ገጠር ስትላቸው ገጠር ይወዳል ብለው እሲምባ ቢልኩህስ?" ከተጋደምኩበት በቅልጥፍና ቀና ብላ አተኮረችብኝ።

# 22

ልክ ከጠዋቱ 11:30 ሲሆን ጉዞዬን ጀመርኩ።

ገመድ መስሎ መንገዱን የዘጋብኝን የኑረዲን ዳቦ ቤት ረጅም ሰልፍ ጥቂት ደቂቃዎች ታግሼ አለፍኩ።

አዲስ አበባ የማታይ የማትሰማ መስላ በጭልሊታ ተውጣለች። አሥራ ሁለት ሰዓት ሆኖ የመነኸሪያ ግርግርና ከኢትዮጵያ ሬዲዮ የብርኪታዊት ድምጽ እስከሚሰማ ድረስ ጸጥታው ይቀጥላል። ብርኪቲን አሁን አሁን በነገር ብዛትና በቢታኒያ ፍቅር ምክንያት እየረሳኋት መጥቻለሁ። ጸጸቱም በርዶልኛል።

'ኢሕአፓ በዐይኔ እያየሁት የቁልቁለት መንገድ ሲይዝ እንዴት አይበርድልኝ? እንዴት አይወጣልኝ?!' የምሽቱ ንዴት መጣብኝ።

መናኸሪያ ስደርስ የጎብተጊዮርጊስ ድልድይን አቅጣጫ ያዝኩ።

እኔም ሆንኩ ቢታኒያ እስከ ሌሊቱ አስር ሰዓት አካባቢ እንቅልፍ አላየንም። መንገደኛ ሆኜ ተልእኮ የተሰጠኝ በምንም ተንኮል አለመሆኑን አሳመንኳት። አሁን የመሄዱ ነገር ፖለቲካዊ መሆኑ ቀርቶ ማኅበራዊ ሆነ። ከተገናኘን ጀምሮ ተለያይተን አናውቅም። አሁን ለቀናት ልንለያይ ነው። በጣም ቅር አላት። ከዚያማ ከአልጋዋ ተነሽታ ወደ ቀናው ቤት፣ ከዚያ ደግሞ ወደ እኔ ተመላለሰች። ለዓመት የሚወጣ ዘማች እንደሆንኩ ሁሉ ኮስተር ብላ የስንቅ ዝግጅት ጀመረች።

"ቢቲዬ፣ ምን ነካሽ? የጥቂት ቀናት ጉዞ ነው'ኮ...ሌላ ነገር አታድረጊው እንጂ...እስሬ እየተነካሁ ብለምናትም አልሰማች።

ቋንጣ ነሽ፣ ፍትፍት ነሽ፣ በሶና ጨጨብሳም አልቀረ። እስሬ ጥ! ጥ! እያለች እያማረረች እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ደፋ ቀና አለች። በመጨረሻ የሰማይ ስባሪ የሚያክል አገልግል ቋጠረችልኝ። ጭንቀቷን ሳይ እንጀቴ ተንሰፈሰፈ።

ከዚያ በኋላ ጋደም ስንል ደግሞ እረፍት ራቀን። የፍቅር ጨዋታ ግፊት ከውስጣችን ዘጭ ብሎብን ድርጅታዊ የቅሬታ ወሬ ጀመርን። ሳወራት ያመሸሁት የድርጅታችን ድክመት ገብቷታል። በደንብ ሲታያት የምሯን ከፋት።

"ሰሙዬ፣ እናንተ ካልተደማመጣችሁ ታዲያ መጨረሻችን ምን ሊሆን ነው?" በየመሀሉ እያቋረጠች ትጠይቀኛለች።

"እኔንም ያሳሰበኝ እሱ አይደል!" በተደጋጋሚ እመልስላታለሁ።

ጭንቀታችንን ለማቃለል የነበረን እድል አንድ ነው። የዲሲፒለን ገደብ ችላ ብለን የተቻለውን ያህል በግልጽ መወያየት።ይህንኑ ለማድረግ ሞከርን። ብዙውን ድርጅታዊ ምሥጢራችንን ዝርግፍ አድርገን ተነጋገርን። ፍቅር የበላይነቱን ሲይዝ ጊዜ አልፈጀበትም። ፖለቲካና ድርጅታዊ ማንቆ ከፒራሚዱ እናት ላይ ወርደው ቦታውን አስረከቡት።

በእኔ በኩል ለማእከላዊ ኮሚቴ አባልነት መታጨቴን አጫወትኳት። የማንንም ሥም ግን በስህተት እንኳን አላነሳሁላትም። እሷ ደግሞ ከዮሴፍ አዳነ ባለቤት ጋር በአንድ ጥናት ከበብ ውስጥ እንደሚሳተፉ ነገረችኝ። ከወጣቱ ሊግ ወጥታ ፓርቲውን መቀላቀሏንም እንዲሁ። ስለ "ገብርዲኒዝም" ግን እንደነገራት ግን እኔም አልጠየኳት፣ እሷም አልነገረችኝ። የአሁኑ ጉዞዬ ኢሕአሠ የወልድያን ንግድ ባንክ ለመዝረፍ ሞክሮ ከእቅዱ አፈጻጸም ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን ደበኳት። በእሷ በኩል "የአካል እንቅስቃሴ" እያለች የምትሄደውን ነገር እንድታብራራልኝ ነከሼ ያዝኳት። እንደ እሱ ያሳሰበኝና የከነከነኝ ነገር የለም። መልሷ ግን አሁንም የድሮው መሀላ ሆነ። ያም ሆኖ ስንነጋገር ትንሽ ቀልል አለን።

የኮተቤን መንገድ ፉት ብዬ ወደ ሰንዳፋ ተጠጋሁ። ጠበቅ ያለ ፍትሻ ጠበቀኝ። ብዙም አልተጨነኩለት። በቀላሉ አልፌው ጉዞዬን እንደገና ጀመርኩ። አስፋልቱን ስከንፍበት አእምሮዬ በሐሳብ ነጎደ...

ከፍሉ ታደሰ ትዝ አለኝ። ከፍሉ በተራው መስፍን ሐብቱን፣ ሰዓሊውን ቫን ጎሕንና "የሱፍ አበባ"ን ከነታሪኳ ይዞልኝ መጣ...

የሱ——ፍ እ----በ----ባ! መስፍን ሐብቱ! ቫን ጎ--ሕ! ከድርጅቴ ጋር እንዴት እንደተገናኙብኝ ለኔ ለራሱ ገርሞኛል።

መስፍንንና ቫን ጎሕን ለጊዜው ከምስሉ አስወጣኋቸው። የሱፍ አበባ ራሷ ላይ ጥምጥም አልኩባት። ወይም ራሷ መጥታ ተጠመጠመችብኝ ብል ይቀላል። አካሏን ከላይ ከቢጫዎቹ አበባዎቿ ጀምሬ እየዘረዘርኩ ወረድኩ። አበቦቿ የከበቡትና ዳቦ የሚመስለው የሱፍ ምርቷ ሙዳይ፡ የሱፍ ጥሬዋ ከነገለባው፡ ሙዳዩን ደግፎ የቆመው ረጅም የአገዳ ቅልጥሟ፡ ሥራ ስሮቿ...። ከሌሎች ተክሎች የተለየ ተዐምር የላትም። ባሕርይዎቿን ለመዘርዘር ስሞክር ቀድሞ ከች ያለብኝ ከፀሐይ ጋር ያላት ተፎጥሯዊ ትስስር ነው። አበባዋ የፀሐይን እንቅስቃሴ ተከትላ መንቀሳቀስ በተፈጥሮ የተሰጣት የማይቀየር ድርሻዋ ነው። ትሸስራቸው እንደ አዲስ ነገር አስደመመኝ...

'እ----ዎ፣ የሱፍ አበባ ለህልውናዋ ስትል በፀሐይ ላይ ጥገኛ ነች። የመኖሯ ምሥጢርና የጉልበት ምንጯ ፀሐይ ነች። ያ ማለት ፀሐይ ብዙውን ጊዜ በሌለችበት የሰሜን ቀዝቃዛ አካባቢ የሱፍ አበባ አትበቅልም ማለት ነው። ፀሐይ ግን ከሱፍ አበባ ጥገኝነት ነጻ ናት። ሆኖም ለሱፍ አበባ የኃይል ምንጭ በመሆን በኩል ከመጠን በላይ ለጋስና ቸር ነች...'

አሁን ከድርጅቴ ጋር የማያይዝበትን ገመድ ፈለኩ። ውስብስብ ቢሆንም መሞከር አለብኝ። ጭንቅላቴን የበለጠ አንቀሳቀስኩት...

'እ---ዎ፣ የሱፍ አበባዋ ድርጅቴ ኢሕአፓን ትወክላለች። ኩብ ሠርተው የቆሙት የአበባዋ ቅጠሎች በቁጥራቸው ጥቂቶች ናቸው። ስለዚህ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላትና ፖሊት ቢሮው ናቸው። የሱፍ ጥሬው በቁጥሩ እጅግ ብዙ ነው። የአበባዎቹን አቅጣጫ ተከትሎ ነው የሚንቀሳቀሰው። ሱፍ ጥሬው ስለዚህ መላውን የኢሕአፓ አባላት ያመለክታል። ተክሏ የቆመችበት አገዳና ሥራ ሥሮቿ ደግሞ ከኢሕአፓ ጀርባ የቆመው ደጋፊ ነው። የፀሐይ·ብርሃን ደግሞ ዋናው የኢሕአፓ ጉልበት ምንጭ የኢትዮጵያ ገበሬ ነው። አፈርና ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች ሠራተኛውን ይወክላሉ። ጎ------ሽ!'

አሁን አንድ ተግባር ብቻ ይቀረኛል። የሱፍ አበባንና የኢሕአፓን ዋነኛ ገዳይ በሽታ መለየትና ማመልከት።

'የሱፍ አበባ ታዲያ እንዴ አዲስ አበባ ዘመድ ጥየቃ ሄደች። ያልጠበቀችው ተዐምር ጠበቃት። ከተማውን እንቁጣጣሽ ያስመለሰ የኤሌክትሪክ መብራት ይንቦገቦጋል። በጣም ተገረመች። ተገርማ አልቀረችም፣ የህልውናዋን ምሰሶ የፀሐይ ብርሃንን ትታ ከኤሌክትሪክ ብርሃን ጋር ተጣበቀች። ውሳኔዋ ትክክል አለመሆኑ ቢነገራትም ወይ ፍንክች... ።

ኢሕአፓ ድርጅቴም ልክ እንደሱፍ አበባ ገጠር አልወርድም ከከተማ ጋር በፍቅር ወድቋል...'

###

ደብረሲናን አልፈ የእጣየን መንገድ ስይዝ ርሀብ ሞረሞረኝ። እመት ቦታ ፈልጌ ከመንገድ ወጣ አልኩና አንድ ዛፍ ሥር ቆምኩ። አገልግሉን ከፍቼ አልጫ ፍርፉሩን አወጣሁ። ቅቤው መጥቶ እውድ ሲያደርገኝ የምግብ ፍላጎቴ ከፍት አለ። ዐይን ህሊናዬ ቢታኒያን አምጥቶ አጠገቤ ቁጭ አደረጋት። ደሴን እስከማቋርጥ ድረስ ድርጅቴና ፍቅረኛዬ ተፈራረቁብኝ...

"የልጅነት ታሪኬ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ በጸጸትና በቁጭት የተሞላ ነው።" ነበር ያለችው ቤቲ።

የኢትዮጵያ ታሪክ እንደማንኛውም ሕዝብ የተቃራኒ መደቦች ትግል ታሪክ መሆኑን እቀበላለሁ። ነገር ግን ከዚህ የትግል ታሪክ የምንማረው ብዙ ነገር እንዳለም ማወቅ ተገቢ ነው። ድርጅቴ ኢሕአፓ አሻፈረኝ አለ። ቤቲዬ በ20 ምናምን ዓመቷ ቁጭ አድርጋ የምታስተምረው ድርጅት ሆኖ አረፈው። ጸጸት ቤቱን እንዳይሠራብኝ የምለምነው አምላክ የሌለኝ መሆኑ ለሌላ ጸጸት እንዳይዳርገኝ ፈራሁ።

'ወይኔ፣ ተቃጥሎ መሞት!' ጭስስ አልኩ።

አዎ፣ ድርጅቴ በጸጸት ለተሞላው ታሪካችን አስተዋጽኦ አድርጎ ለማለፍ እየተጣደፈ ነው። ቢታኒያ "የጸጸት ታሪክ" ስትል ምን ማለቷ እንደሆነ ለመተርጎም ፍላጎቱ ጨርሶ የለውም፣ ድርጅቴ። የቤቲ የጸጸት ታሪክ በፍካርያዊ ትርጉሙ እንደምን ይገለጻል? ከባድ ጥያቄ ሆነብኝ። ስንቱን አንስተው ስንቱን ይተውታል? ከቅርቡ ታሪካችን ጀምሬ ወደ ሩቁ የአክሱም ዘመነ መንግሥት ድረስ ተጓዝኩ...

"አጼ ኃይለሥላሴ ከአምስት ዓመቱ ሽሽት ሲመለሱ አርበኞችን መተናኮል ያዙ። የጎጃሙን ስመጥር አርበኛ በላይ ዘለቀን ያለምንም ርህራሄ ዙፋኑን ተዳፈረ ብለው በስቅላት ቀጡት። አገር ተደናገጠ። አሳዛኙ ነገር የስቅላት ቅጣቱን ያስፈጸመው የያኔው የክብር ዘብ መቶ አለቃ የወደፊቱ ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ ነበረ። 'ኢትዮጵያ፣ ወንድ አይብቀልብሽ!' አለ በላይ፣ የስቅላት ሽምቀቆው በአንገቱ ሲገባ። የገመዱ ቋጠሮ ማንቁርቱ ላይ በማረፉ አሟሟቱ ስቃይ በዛበት። አትፍረድ ይፈረድብሀል! ይላል የአገሬ ሰው። ጀኔራል መንግሥቱ በመፈንቅለ መንግሥት ሙከራው ምክንያት በላይ በተሰቀለ ልክ በ21ኛው ዓመት እጣው ደረሰው። ሽምቀቆው በአንገቱ ሲገባ ታዲያ 'ቋጠሮውን በማጅራቴ በኩል አድርጉልኝ' ብሎ ተማጸነ። እንዳለው ተደርጎለት ሞተ..."

'የእኔዋ ቢታኒያ የ"ጸጸት ታሪክ" ስትል ይህንን ማለቷ አይደል?'

"ኢትዮጵያ የዐድዋውን ጦርነት በድል የጨረሰችው በሦስት ሰዓታት ውጊያ ነው። አጼ ምኒልክ ቢፈልጉ ኖሮ እስመራን መያዝ ይችላሉ። ራሷን ዐድዋን የመያዝ ያህል ቀላል ነበር። 'ምክንያታቸው በትክክል ይሄ

ነው' ብሎ እስካሁን የጻፈ አልተገኘም። የጦርነቱ መዘዝ የነበረው የውጫሌ ስምምነት አሁን ተሽሯል። ነገር ግን መረብን ሳይሻገሩ ቀሩ። በሽንፈቱ የተሸበረው የጣሊያን መንፈስ ተመልሶ ተንፈስ አለ።ይሄው ዛሬ ሰንኮፉ ለ'ኛ ትውልድ ተረፈ። በ40ኛዉ ዓመት በመርዝ ጋዝ ተለበለብን። ጀብሀና ሕዝባዊ ግንባር ሀርነት ኤርትራ ከተፈጠሩ ወዲህ ደግሞ መጠበስ ከጀመርን 13ኛ ዓመታችንን ያዝን። ዐድዋ ላይ ካለቁት አባቶቻችን በብዙ እጥፍ የሚበልጥ ሕይወት ከፈልን..."

'እዎ፤ ቢታኒያዬ "የጸጸት ታሪክ" ስትል ይሄንኑ ማለትሽ ይሆን...?'

"ቴዎድሮስ በ50ኛ ዓመታቸው ላይ የሞቱ ወጣቱ ንጉሥ ናቸው። ለንግሥና ማእረግ የበቁት በእሳቸው አነጋገር 'ከትቢያ ተነስተው' ነው። ጭልጥ ካለ በርሀ ወደ ከተማ አቅጣጫ እያሌ ውጊያዎችን አሸንፈው ነው። በአገዛዛቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዙ አዳዲስ ነገሮችን አሳዩት። ማእከላዊ አገዛዝ...መሠረተ ልማት...እንድ ለአንድ ጋብቻ...ዝርዝሩ ብዙ ነው። ቤተከርስቲያንን ሲነካኩ ነገር መጣ። 'ለአንድ ደብር ሁለት ቄስ፣ ሦስት ዲያቆን፣ ሌላው ወደ እርሻ!' ያለጊዜው የወሰዱት እርምጃ ነበር። ጎርፍ የነበረው ወታደራቸው ከዳቸው። በአንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ከእንግሊዞች ጋር ዓይንና ናጫ ሆኑ። ጀኔራል ናፒር ሊወጋቸው ሲመጣ አምስት ሺህ ወታደር ብቻ ነበራቸው። ኃይለኛው ንጉሥ በገዛ ሽጉጣቸው ወደቁ።"

'እዎ፤ ቢቲ ፍቅሬ "በጸጸት የተሞላው የኢትዮጵያ ታሪክ" ስትይ ይህንን ማለትሽ አይደል?'

"አጼ ዮሀንስና ራስ አሉላ ለጣሊያን መቼም መቅሰፍቱ ናቸው። ዶጋሊ ላይ አምስት መቶውን ወታደር ሲጥ አደረጉት። አሉላ ከዐድዋ ድል በኋላ ሲገርማቸው ተናገሩ፣ 'እንዲያው እናንተ ጣሊያኖች፣ እናንተ መሸነፍ እኛ ማሸነፍ አይሰለቸንም ልበል?!' አሉት በንቀት እንዱን ምርኮኛ ጀኔራል። በ1881 የጣሊያን ጦር ከምጽዋ ወደ አሥመራ አመራ። አጼ ዮሀንስ ከተት ዐውጀው ሊገጥሙት መረብን ሲሻገሩ ካህናት አማካሪዎች ጣልቃ ገቡ። 'ጃንሆይ፣ ምንም ጣሊያን ጠላታችን ቢሆንኮ እንደ'ኛ ክርስቲያን ነው። እንዴት የክርስቲያን ደም ያፈሳሉ? ይልቅ እስላሙን ጠላታችንን ድርቡሽን አይወጉልንም?' ዮሀንስ አመንትተው አመንትተው ፊታቸውን ወደ መተማ አዞሩ። አልተመለሱም። በድርቡሽ አልሞ ተኳሽ ጥይት ተመትተው ወደቁ። ከሞቱ በኋላ ደግሞ አንገታቸው ተቆርጦ አምድርሀማን ገባ..."

'ታዲያ ቢታኒያ "የጸጸት ታሪክ" የምትለው ይሄንን አይደል?'

"16ኛውና 17ኛው ክፍለዘመናት ለኢትዮጵያ የመከራ ጊዜያት ነበሩ። ኢትዮጵያውያን ሰይፍ መዘው እርስ በእርስ የተራረዱበት ዘግናኝ ጊዜ ነው። ግራኝ አህመድና አጼ ልብነድንግል አገር ባደ ባድማ

እስከምትሆን ድረስ ተላለቁ። መስጊዶችና ቤተክርስቲያኖች ተቃጠሉ። ይህ አልበቃ ብሎ ዘመነ መሳፍንት ሌላ የእልቂት ድግስ ይዞ መጣ። መሀለኞችና ዳረኞች፣ መሀለኞችና መሀለኞች፣ ዳረኞችና ዳረኞች... ተጨፋጨፉ። ይሄ ጋብ ሲል ደግሞ የ'ቅባት'ና የ'ጸጋ' አማኞች መስቀሉን ጥለው ጎራዴውን አነሱ። ጎጃም፣ ጎንደር፣ ሸዋና ትግራይ ጎራ ለይተው ተገዳደሉ። እስከ 16-17ኛው ከፍለ ዘመን ከአውሮፓ ጋር እኩል የተራመደችው ኢትዮጵያ ቀጥ ብላ ቆመች። ዳፋው አሁንም አለ።"

'ቤቲ ፍቅሬ ትክክል ናት። የጸጸት ታሪክ ስትል ከዚህ ውጭ ሌላ ምን ይሆናል!?'

"አከሱም ጽዮን ማርያም ቤተክርስቲያን 10ኛው ከፍለዘመን ላይ የንግሥተ ሳባ ወርቅ ጫማ ተሰረቀባት። ከተማዋ በአሰሳ ታመሰች። ካህናት አንድ ቆሎ ተማሪን ጠርጥረው ሲይዙት መስረቁን አመነ። 'ለምን ሰረቅህ? ለማንስ ሰጠኸው?' መረመሩት። ዮዲት ከምትባል አንዲት የፈላሻ ቆንጆ ፍቅር ይዞኝ አምጣልኝ ስትለኝ ጊዜ ሰርቄ ሰጠኋት' መለሰ። ወጣቷ ዮዲት ተይዛ ለፍርድ ቀረበች። የቀኝ ጡቷ ተቆርጦ ከአገር እንድትባረር ተወሰነ። ሲራራ ነጋዴ ሲና በርሀ ወስዶ ጣላት። ዮዲት 40 ሺህ ጦር አሰልፋ ከዓመታት በኋላ ተመለሰች። አከሱሞች ስለረሷት በጭፈራ ተቀበሏት። ልክ የአከሱምን መሬት ስትረግጥ ሰይፏን ከአፎቱ አወጣችው። ምድርን ቁና አደረገቻት። አከሱም ጉልበት ከዷት በአፍጢሟ ተደፋች። ገናናው ሥልጣኔያችን ወደቀ..."

'ቤቲዬ ይህንን ማለቷ ከሆነ ምን እንከን ይወጣላታል? ምንም!'

ወደ ድርጅቴ ኢሕአፓ ስመለስ ድንጋጤዬ ሸቀብ ናረ። የዓለም ሁሉ ፍርሀት እንደ ግሪሳ ሀውውው... ብሎ መጥቶ ሰፈረብኝ። ድርጅቴ የፍቅረኛየን ያህል ከዚህ መራራ የጸጸት ታሪካችን ለመማር ፈቃደኛ አይደለም። ከዚህ ሁሉ ታሪክ ጀርባ ተቃራኒ ተዋንያን አሉ። ከእነርሱ ጀርባ ደግሞ ሕዝብ አለ፣ የኢትዮጵያ ገበሬ አለ።

"በገበሬ አገር የፖለቲካ ኃይል ሚዛን ሁሌም የሚለወጠው በገበሬው ብቻ ነው።"

ተራ አነጋገር አይደለም።ድርጅቴ ይሄንን ሐቅ መዋጥ አምቢ አለው። እንደ እብድ ከተማን ሙጥኝ ብሎ አዲስ የጸጸት ምዕራፍ ሊከፍት እየተዘጋጀ ነው። የድርጅት አባላት ብዛት የሕዝብ ብዛት መስሎ ታየው። መሬትን በአራሽነት የያዘውን ሕዝብ ያልያዘ ድርጅት የተደፋ ውኃ አያቃናም። የዐድዋ ድል የገበሬ ድል፣ የማይጨው ሽንፈት የገበሬ ሽንፈት፣ የጃንሆይ ውድቀት የገበሬ እምቢ ባይነት... መሆኑ እንዴት አይታየውም? የሉፍ አበባ የማታ ማታ እዳው የራሷ ነው። ኢሕአፓም የዘራውን ያጭዳል፣ ፍቅረኛዬና እኔም አብረን ልንወቃ ነው..."

ኡኡኡኡ......ብል በወደድኩ። ችግሩ ግን ማን ሊሰማኝ?

የታሪካችን ችግር በጸጸት መሞላቱ ብቻ አይደለም። በተቃርኖ ትስስሮች የተተበተበም ነው። አጼ ኃይለሥላሴ የፈረስ ስማቸው "አባ ጠቅል" ነው። ማእከላዊ መንግሥትን የማጠናከርና የአገሪቱን የመሬት ግዛት ማስፋፋት ወይም ማስመለስ ታሪካዊ ትልእኮ አድርገው ለተነሱት ንጉሥ የሚመጥን ስም ነው። ስመጥሩውን የኢድዋ ጀግና ባልቻ አባ ነፍሶን ማኪያቬሊያዊ ሊባል የሚችል ሴራ ጎንጉነው አዋርደዋቸል። በአንድ ጀንበር ሠላሳ ሺህ ጦራቸውን በተንኮል እንዲያጡ አድርገዋቸዋል።

ጃንሆይ ይህንን ነውር ለመሥራት ያነሳሳቸው የማእከላዊነት ስስታቸው ነው። ታዲያ እኝህ ንጉሥ ጭንቅላታቸውና ደማቸው ውስጥ ኖሮ የማያውቀውን "የኤርትራን ፌዴሬሽን" ፈርመው እንዲያስተዳደሩ ተደረገ። እተር ሽንብራ ይሆን ዘንድ እንደመመኘት ነው። የፌዴሬሽን ሎጅክ ሊገባቸው አለመቻሉ አንድ ነገር ነው። ከብረነከ ሆኖ ስላገኙት ፌዴሬሽን የሚባል ቃል አባ ጠቅልን እንደ ሀሞት ጎመዘዛቸው።

"እንዴት በአንድ ደብር ሁለት መምህር ይኖራል? እንደምን አንድ ጎራ በሁለት አውራ ይገዛል?" ብስጭት አሉ።

10 ዓመት ሙሉ ወጥተው ወርደው ያመጧት ኤርትራ ተመልሳ የጭን ቁስላቸው ትሆን ጀመር። እንደ ከልብ ውሻ ፍርት አድርገው ፈሯት። ምክንያቱም ለግዙፉ የኢትዮጵያ ግዛታቸው መዘዝ ይዛባቸው ልትመጣ ሆነ። እያ በሬ በሬ ሳሩን እየሀና ገደሉን ሳታይ...ኤርትራውያን የፌዝ ተረት የተረቱባቸው ሲመስላቸው ከንፈሮቻቸውን ንክስክስ አደረጉ። ይህ ጥላቻቸው የፈጠረውን እዳ ይኼው እኛ በመክፈል ላይ ነን።

የኤርትራ ነገር ሁለት የተለዩ ሰዎችን አስታወሰኝ። የዛሬ ዓመት ደርግ ከረሸናቸው 60 የቀድሞ ባለሥልጣናት መካከል ናቸው። እቶ አክሊሉ ሐብተወልድና እቶ አበበ ረታ። አክሊሉ ኤርትራን ለማምጣት በመጨረሻው እልህ እየሠሩ ነው። እቶ አበበ በዚህ ደስተኛ አልነበሩም። ጃንሆይ ከሽሽት መልስ በማግስቱ ስለኤርትራ ፖሊሲያቸው ምክር የጠየቁ ቀን ነው። እቶ አበበ በጥሞና ሲያዳምጡ ቆይተው ሲፈቀድላቸው ተናገሩ...

"ጃንሆይ፣ ኤርትራን 'ማስመለስ' የሚባል ቃል አልተመቼኝም። ከፈለገች ራሷ ትመለስ። እናስመልስ ከተባለም መጀመሪያ ኢትዮጵያ በእጃችን መግባቷን በደንብ እናረጋግጥ። አዲስ አበባን ዞር ዞር ብሎ የተመለከተ ሰው ይመስከር። ጣሊያኖች ሰንኮፍ ተከለውብን ሄደዋል። ሰው ነጻነቱን ይወዳል። ነገር

ግን አይቶት የማያውቅ ብዙ አንግዳ ነገር አይቷል። ይሄን አምፖሉን_ይሄን ስሩልን_እስከዛሬ የት ነበር ያኖራችሁን? ብሎ መጠየቁ አይቀርም። ብዙ ቦታም የቆየ ባህላችን ተቃውሟል። ይህ ሁሉ ተግባር ከራታችን ተዘርግቶ አሻግረን ኤርትራ ትምጣ ብለን ብንሟገት ይሄን የሚሠራልን የለም። ግዴለምትም፣ በዚያው ትቆይ!"

መካር የሌለው ንጉሥ ያለ አንድ ዓመት አይነግስ! አለ አገሬ። መካር ኖሮ ሰሚ ጆሮ ማጣትም አለና!

የድርጅቱ ኢሕአፓ ደግሞ ይባስ! ከታሪክ መመከር ባለመፈለጉ ድቀት መንገዱን ይዞ ይሄው እኔንም ሊያሳብደኝ ነው። "በገበሬ አገር የላባደር መሪ ፓርቲ ነኝ" ብሎ ነበር?! ይህ ተቃርኖ ብቻ ሳይሆን ሶሽሎጅካዊ ዟልትም ጭምር ነው።

ብሔራዊ የማስተማር ግሊጋሎቱን የሰጠሁት ወሊጋ ውስጥ ግምቢ ከተማ ነው። የኢኮኖሚ እድገት ታሪክ ሳስተምር ምዕራብ አውሮፓንና ሰሜን አሜሪካን አነሳሁ። ተማሪዎቼ አፋቸውን ከፍተው ያዳምጡኝ ነበር።

"ካፒታሊዝም በእነዚህ ቦታዎች አሸናፊ የሆነው እንዴት ይመስላችኋል?" ብዬ ተንደርድሬ መልሱን እኔው ራሴ ሰጠሁ፣ "አዎ፣ ካፒታሊዝም ለድል የበቃው ከንደብርቱ የገበሩ ነሥታትን በአብዮታዊ ለውጥ አፈር ድሜ አስግጦ ነው። ይህ ማለት ዘመናዊው ካፒታሊዝምና ትውፊታዊው ንጉሣዊ አገዛዝ ጨርሶ የማይተዋወቁ የሁለት ዓለማት ከስተቶችና ሁለት የተለያዩ የኅብረተሰብ እድገት ደረጃዎች ናቸው።"

ይሄንን ተናግሬ ጥያቄ ያለው ተማሪ ይኖር እንደሆነ እድል ሰጠሁ። አንዱ እሳት የላሰ ተማሪ ጠየኝ ማለዘን በኩል እጁን አወጣ። እንዲናገር ሲፈቅድለት ያው የተለመደው የቃላት ጥያቄ እንደሚሆን እየገመትኩ ነበር። መናገር ጀመረ...

"ጋሼ! ታዲያ እንደዛ ከሆነ ማለቴ ዘመናዊው ካፒታሊዝምና አርጌው ንግሥና የማይጣጣሙ ከሆነ በእኛ አገር ካፒታሊዝም በንጉሥ አገዛዝ ለመፍጠር እየተደረገ ያለው ነገር ተቃራኒ አይሆንም?" ያልጠበኩትን ጥያቄ አነሳልኝ።መልሴ አጭር ነበር...

"ትክክል ነህ። የእኛ አገር ዶናልድ ሌቪን እንዳለው በመጥፎም በጥሩም ሁሌም የጉድ አገር ናት!" ከፍሉ በሳቅ ፍንዳታ ተናወጸ።

ኢሕአፓ ድርጅቱ ከታሪክ ተምሮ እንዲህ ዓይነት ጉዳትድ ተቃርኖዎችን ሳይመሠረት አለመጠንቀቁ

እንደገና እርር ድብን አደረገኝ።"ኤ---ጭ...ሰን ኦብ ኤ ቢ-----ች!! ድሮስ የማን ዘር ጎመን ዘር..." ድምጽ አውጥቼ ጮኽኩ።

###

በሐሳብ ስጓዝ አልታወቀኝም፤ ለካስ ብዙ ርቀት ነድጃለሁ!

ወልድያ ከተማ ከሩቅ ብቅ አለች። ኾኖም ወደ ከተማዋ እየተጠጋሁ አንድ ጠመዝማዛ መንገድ ላይ ስደርስ ሁለት ወንድ ወጣቶች ድልድይ ላይ ተቀምጠው ታዩኝ። አላማሩኝም። እየቀረብኳቸው ስሄድ ደግሞ የመረበሽ ስሜት ዐየሁባቸው።ዝግ እያልኩ ነድቼ ስጠጋቸው ተነስተው ቆሙ። ከፊት ለፊቴ አንድ ቦቴ እንደ ኤሊ ሲጎተት ከሩቅ ይታየኛል። ከኋላዬ ምንም ነገር የለም። ጥርጣሬ አደረብኝ። ወደ መንገዱ ፊት ለፊት ዐየሁ። ትልልቅ ድንጋዮች አስቀምጠው መንገዱን ለመዘጋት ሞክረዋል። ቶሎ ብዬ እጆቻቸውን ዐየሁ። አንደኛው ወጣት መጥረቢያ ይዟል። ኋደኛው ደግሞ ትልቅ ቆመጥ። አስቀመው ሊዘርፉኝ እንደተዘጋጁ ተገለጠልኝ።

'የምወስደው እርምጃ በያዙት መሣሪያ ይወሰናል። ቆመጥና መጥረቢያ ብቻ ከሆነ ቀላል ነው...' ራሴን አጠናከርኩት።

መቶ ሜትር ያህል ሲቀረኝ ቆምኩ። ማንም እንደማያየኝ ገምቼ ሽጉጥ አውጥቼ ወረድኩና ወደነርሱ ገሰገስኩ። ተደናገጡ መሰለኝ ገና ሽጉጡን ወደ ፊት ሳልደግነው ሁለቱም ወጣቶች እንደ ጉም በነው ጠፉ። ድንጋዩቹን አንስቼ ወደ መኪናዬ ተመልሼ ጉዞዬን ቀጠልኩ።

# 23

ወልድያ ከተማ ስገባ የእጅ ሰዓቴ 11:00ሰዓት ያመለክታል።

ጥሩ በሚባል ፍጥነት ነው የነዳሁት። ትልልቅ ተራሮች ሥር የተሸጎጠችው ወልድያ ከተማ ስትዋከብ አገኘኋት። የጭነት መኪናዎችና የነዳጅ ቦቴዎች ረጅም ሰልፍ መንገዶቿን አጨናንቆታል። አልፎ አልፎ ደግሞ ሸራ የለበሱ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች ይታዩኛል። የትግራይና የኤርትራ መዳረሻ መሆኗ የፈጠረው ትርምስ ይመስላል። ከመኪና መንገዱ መሀል እዚህም እዚያም የሚነሳው የአቧራ ማእበል ደግሞ አይጣል ነው። ነዋሪዎቿን መድረሻ ያሳጣቻቸዋል። የፖለቲካ አለመረጋጋቱና ግራ መጋባቱን እንደ ሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ወልድያንም አልማራትም። የሚዝናና፣ የሚስቅ ሰው አልታይህ አለኝ።

"መጭው ነገር ትሻልን ሲድጂ ትብስን አመጣሁ እንዳይሆን እንጂ..." በሰው ሁሉ ግንባር ላይ የማነበው መልእከት መሰለኝ።

የተነገረኝን መስመር ይዤ መሀል ከተማ ስደርስ ወደ ግራ ታጠፍኩ፤ ወልድያ ሆቴል። ያስመረረኝ የሕጻናት ከበባ እዚህ ብዙም አልገጠመኝም። መኪናዋን ወደ ግቢ አስገብቼ፣ አልጋ ይዤ ሰውነቴን ታጠብኩ። ፕና ጋደም ከማለቴ እየቀረበ የሚመጣ የእግር ኮቴ ድምጽ ተሰማኝ። ወዲያው ኮት የለበሰ ቀጭን ጎልማሳ ከበሩ አቅጣጫ ብቅ አለ። ለዐመል ያህል በሩን አንኳኩቶ ገባ። ገና ሳየው አይነ-ውኃው የእኛ ሰው መሆኑን ሹከ አለኝ።

'እላምረው 1326 ነህ?"

"አንተ ደግሞ ይግዛው አራት በአራት ነህ!?"።

ቀታዬን ለብሼ ተያይዘን ወጣን። ወደ ግራ ታጥፈን በባህርዛፍ አጥር የተከበቡ ቤቶችን አቋረጥን። ውኀብ የሚበጥስ ድንጋያማ ዳገት። የይግዛው ቤተሰቦች መኖሪያ ቤት...

ሰፊ ግቢ ነው። የሞተር ወፍጮ! የመኪና ኢቃዎችና ጎማዎች ወዳድቀው ይታዩኛል። በሩን አልፈን ስንገባ ከእናቱና ከእህቱ ጋር አስተዋወቀኝ ሲያበቃ ምግብ እንዲመጣልን አዘዘ። ከዋናው ቤት ጀርባ ወደ ራሱ መኖሪያ ከፍል ወሰደኝ። ለብቻው የቆመና ሁለት ከፍሎች ያሉት ቤት ነው። ለመነጋገር በጣም አመቺ ሆኖ አገኘሁት።

"በጣም አሳዛኝ ውድቀት ነው የደረሰብን።" ብሎ ጀመረልኝ ይግዛው፤ "ሪፖርቱን 'በኢንተር ዞን' ኮሚቴው በኩል በጽሑፍ አዘጋጅተነዋል። ከምግብ በኋላ እሰጥሀለሁ፤ ወታደሮች ስላልሆን ሪፖርቱ በቂ ላይሆን ይችላል። ተልእኮው ግን ሙሉ በሙሉ ከሽፏል። አራት ጋንታ ኃይል ነው ለጥቃቱ ቀጥታ ከአሲምባ የመጣው። ወደ ሀምሳ ስድስት ጓዶች ተሳትፈው ነበር። ሲመለሱ ሠላሳዎቹ የት እንደደረሱ አይታወቅም። እስከ አሁን ያወቅነው አስር ጓዶች በገበሬዎች ተይዘው መንግሥት እንዳሠራቸው ነው። ሦስት ደግሞ ከገበሬዎች ጋር ሲታኮሱ ተሰውተዋል። በመሀል ገበሬዎች ማርከው በየቤታቸው ያስቀመጧቸው ጓዶች መኖራቸውንም አሁን ከደቂቃዎች በፊት መረጃ መጥቶልናል። አንድ ቀላል ቁስለኛ እዛው እነ ይግዛው ቤት ተደብቋል...

ወኔዬ ፍርክስክስ አለ። ከምግብ በኋላ የጽሑፍ ሪፖርቱን ተቀብዬ ማንበብ ጀመርኩ። ቀጥዬ ቁስለኛውን አግኝቼ ቃለ ምልልስ ማድረግ ነበረብኝ። በጀርባ በኩል ባለ በር ወጥተን ጭልምልም ወዳለ ኩሽና መሰል ቤት ገባን። በግራ በኩል ትልቅ መደብ ላይ ብርድ ልብስ ለብሶ የተኛ ሰው ታየኝ።

'እንደኛው የድርጅቴ ዝርክርክ አቅድ ሰለባ ይሄ መሆኑ ነው...' ቅሬታዬን ከራሴ ጋር ተነጋገርኩ።

ቁስለኛው ድምጽ ሲሰማ ተነስቶ ቁጭ አለ። ይግዛው ቀደም ብሎ ሄዶ ማንነቴን ከነገረው በኋላ እንደጠጋው በጥቅሻ ምልክት አሳየኝ። ስለጤንነቱ ትንሽ ተነጋገርን። ግራ ትከሻው ላይ የበረደ ጥይት እንደመታው ዐወኩ። ለከፋ የሚዳርግ አይደለም። በነጭ ፋሻ ተሸፍኖ መድኃኒት ተደርጎበታል። የተጎሳቆለ ፊቱ የዘመቻውን ከባድነት ይመሰክራል። ወደ ጥያቄዬ አለፍኩ...

"የድርጅት ስምህንና የነበረህን ኃላፊነት ብትነግረኝ..." አንሾካሾኩ።

'ገረመው ነው የምባል። የሁለተኛው ጋንታ ኮሚሳር ነኝ።" ብሎኝ አቀማመጡን አስተካከለ።

"ገረመው፡ ኮሚሳር ከሆንክ ከእቅዱ ጀምሮ እስከ ውድቀቱ አብረህ ነበርክ ማለት ነው። እስቲ የነበረውን ሁኔታ ለውድቀቱ መንስኤ ነው እስከምትለው ችግር ድረስ ዘርዝር አድርገህ አስረዳኝ..."

ቁስለኛው የነበረውን ሂደት ከ "ሀ" ጀምሮ እስከ "ፐ" ሲዘረዝርልኝ የእኔ ጭንቅላት ደግሞ ማጠቃለያ እየሰጠ ትንተና ይሠራል። መልከ መልክ እያስያዝኩ ለዘርው ከህሸን በማስረዳበት አኳኋን አደራጀሁት።

"ሲጀምር የወልድያን ንግድ ባንክ የመዝረፍ እቅድ አሲምባ በኢሕአሠ የተጠነሰሰ አልነበረም። የኢ.ሕ.አ.ፓ ማእከላዊ ኮሚቴም በቀጥታ የሚያውቀው አይደለም። በፖለቲካ ቢሮው የታቀደ ነው። እቅዱን ለማስፈጸም ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ አሲምባ ገብቷል። እዛ በቆየበት ጊዜ ጉዳዩ ወታደራዊ ምሥጢር በመሆኑ ወልድያን አላነሳም። በእርምት ንቅናቄና ከኤርትራ ግንባሮች ጋር በተደረገ ውይይትና በተደረሰ ስምምነት ላይ አተኩሮ ነው የሰነበተው። ከዚህ በኋላ ኢሕአሠን ሰበሰበ። ሠራዊቱ አንድ ወታደራዊ እንቅስቃሴ እንደሚያደርግ ገለጸለት። ከትግራይ ወደ ሰሜን ምሥራቅ ጎንደርና ወደ ምሥራቅ ወሎ ዘልቆ የሙግባት ዘመቻ መሆኑን አብራራ።" አዲስ የመንቀሳቀሻ ወታደራዊ መሠረት ወይም ቤዝ ፍለጋ መሆኑ ነው።

እስከዚህ ድረስ ምንም ችግር እንደሌለ ማየት ችያለሁ።

"የኢሕአሠ ጋንታዎች ትግራይን ለማቋረጥ ከአሥራ ሁለት ቀን በላይ ፈጀባቸው። ወደ ራያ መሀል ሲገቡ ሠራዊቱ ከሁለት ተከፈለ። አንደኛው ወገን የምእራብ አቅጣጫ ይዞ ተጓዘ። ዶክተር ተስፋዬ አራት ጋንታዎች ከያዘው ሌላኛው ኃይል ጋር ተነጥሎ ወደ ምሥራቅ ወሎ አመራ። ሁለት ሳምንት ያህል ተጉዘው ወልድያ ከተማ ሲጠጉ ሠራዊቱ ተሰበሰበ። አዛዦቹ አንድ የጥቃት እቅድ መኖሩን ገለጹ። የወልድያን ንግድ ባንክ መዝረፍ። አንደኛው ጋንታ ባንክ ቤቱን ይወራል። ሁለተኛው ጋንታ ፖሊስ ወደ ባንክ ቤቱ እንዳይሄድ የማገጃ ተኩስ ይከፍታል። ሦስተኛውና አራተኛው ጋንታዎች ከዘረፋው በኋላ ለሚያመልጡት ሁለት ጋንታዎች ሽፋን ይሰጣሉ። በመጨረሻ ሁሉም አንድ ቦታ ተገናኝተው ወደ መጡበት ይመለሳሉ..."

ይህንን ስሰማ ጨጓራዬ ተቃጠለ። ኢሕአሠ የሰፈር ልጆች የሚጫወቱትን ሌባና ፖሊስ የተጫወተ መሰለኝ። ችግሬ በእንደዚህ ዓይነት ወታደራዊ ዘመቻ ጊዜ ውድቀት ስለማያጋጥም አይደለም። ሊያጋጥም ይችላል። የዚህን ተልእኮ ውድቀት የተለየ የሚያደርገው ግን ተራ የአካባቢ ሚሊሺያ ኃይል እንኳን የማይሠራው ስህተት ሆኖ ሳገኘው ነው። ቻል አድርጌው ቀጠልኩ...

"ሠራዊቱ ወደ ከተማው እንደተጠጋ መብራት ድንገት ድርግም ብሎ ጠፋ። ወልድያንና አካባቢዋን

ድቅድቅ ጭለማ ዋጥ አደረጋት። ሁሉም ጋንታዎች በያላችሁበት ቦታ ቁሙ ተባሉ። ለሰዓታት ድምጻቸውን አጥፍተው ተለዋጭ ትእዛዝ ተጠባበቁ። ብዙም ሳይቆይ የጋንታ አዛዦች ትእዛዝ ደረሰ። 'ዘመቻው ተሰርዟል፣ የመልስ ጉዞ ወደ አሲምባ!' በዚህ ሞራሉ የተነካው ታጋይና አዛገሮቹ ንትርክ ውስጥ ገቡ። በመልስ ጉዞ ላይ መደማመጥ ጠፍቶ ጭቅጭቅ ነገሰ። አዛገሮቹ በመጣንበት እንመለስ ሲሉ ሠራዊቱ በሌላ መንገድ ይላል። 'ተንቀሳቀስ!' ሲሉት 'እረፍት' ብሎ በገዛ ውሳኔው ቁጭ ይላል።"

'መንጋ ሊ---ጥ!' ብስጭት አልኩ፣ ማንን እንደምወርድበት ግን አላውቅም።ወደ ሚቀጥለው ነጥብ ተንደረደርኩ...

"ጉዞው እንደምንም ሲቀጥል ጸጉረ-ልውጥ መሆናቸውን ያየ ገበሬ ማነህ? ይላቸዋል። የሆነ ምክንያት እየሰጡ ሲያልፉ ቆዩ። አንድ ቦታ ሲደርሱ ግን መንገድ ተዘግቶ ተኩስ ተከፈተባቸው። የተወሰኑ ጓዶች ሙትና ቁስለኛ ሆኑ። ያንን እንደምንም ተከላክለው አለፉ። ትንሽ እንደሄዱ ደግሞ ፖሊስ ገበሬዎችን አስተባብሮ ከጀርባቸው ደረሰ። እየተከላከሉ ማምለጥ ብቸኛው ዘዴ ሆነ። በጣም ከባድ ሆነባቸው። ቀስ በቀስ ቁጥራቸው እየተመናመነ ሄደ። በመከራ ወደሚቀጥለው ግባቸው ሲጠጉ አሁንም በጎን በኩል ሌላ ተኩስ ተከፈተባቸው። እዚህ ላይ ዋናው አደጋ መጣባቸው። መበታተን፣ መማረክ፣ መቁሰል፣ መሰዋትና መሰወር የብዙዎቹ እጣ ፋንታ ሆነ። ጥቂቶች ብቻ ወደ ትግራይ ተሻገሩ። እነርሱም የኢዲዩው ራስ መንገሻ ሰዩም ተዋጊዎች መሆናቸው እየተናገሩ ነበር ሕዝቡ የሚያሳልፋቸው..."

'በሞ--ት--ኩ--ት! ኢሕአሠ የቀዩ ጦር ጥንስስ በውጊያ ታክቲክ ስህተት ምክንያት ይሄንን ለማለት ተገደደ?!' ነደድኩ።

አሁን የተፈጸመው ጅላጅል ስህተት ከሞላ ጎደል መንስኤው ግልጽ ነው። ዘርዑ ከፊት ለፊቴ የቆመ ያህል ቃላቴን ሳልኳቸው...

"አንደኛ፣ የዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ በዘመቻው ላይ መገኘት ስህተት ብቻ ሳይሆን ወታደራዊ ድንቁርናም ጭምር ነው። የባንክ ዘረፋው ውሳኔ ፖለቲካዊ ሲሆን ዘመቻው ግን ወታደራዊ ነው። ወይም የትጥቅ ትግሉ ኮማንደሮች ሥራ ነው። እቅዱን ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ መንደፍና ማስፈጸም የነበረባቸው እነርሱ ናቸው። ለምሳሌ እጥቂዎቹ ተመርጠው ልዩ ሥልጠና መውሰድ ይገባቸው ነበር። በጣም ረጅም ጊዜ ተወስዶ በአሸዋ ገበታ ላይ በቂ ልምምድ መደረግ ነበረበት። ተስፋዬ ይሄንን ተግባር ላእነርሱ መተው ሲገባው ለምን ያለ ችሎታውና ሥምሪቱ ዘመቻ ውስጥ ገብቶ ፈተፈተ? ይህ ዘመቻውን በትክክለኛ ወታደራዊ ሳይንስ መርሆዎች ከመምራት ይልቅ በጅብደኝነት እንዲካሄድ አደረገው።

ፖለቲከኛዉና ወታደሩ ያለ አግባብ ተቀላቀሉ።"

ወደ ሁለተኛው ስህተት ተሻገርኩ...

"ሁለተኛ፣ ኢሕአሠ የአንድ ወር ጉዞ የኳተነው በማያውቀው መሬትና ሕዝብ መካከል ነው። ይህም ማለት ያቋረጠው ካድሬዎች ቀድመው ያልተሰማሩበትና ያላዘጋጁት ነጭ መሬት ነው። በቻይናው የማኦ ሽምቅ ውጊያ ልምድ ይህ ራስን በራስ የማጥፋት ውሳኔ ነው። ነጭ መሬት ማለፍ ግድ ሲሆን ደግሞ እንድም ይህ ተግባር ቀድሞ መሠራት አለበት አለያም ከፍተኛ ወታደራዊ ኃይል ያስፈልጋል። ኢሕአሠ ረመጥ ውስጥ ጉብቶ የተጠበሰው ሁለቱም ቅድመ ተግባራት ሳይፈጸሙ ነው። ይህ በወንጀልም ያስጠይቃል። ሦስተኛ፣ እንዲህ ዓይነት ዘመቻ የሚደረገው ህልውናን የሚፈትን አደጋ ሲፈጠር ብቻ ነው። የቻይናው 'ረዥሙ ጎዞ' ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ይሄ የእኛው ዘመቻ የተደገረው ግን ባንክ ለመዝረፍ ነው። የህልውና ጉዳይ አይደለም..."

እዚህ ነጥብ ላይ ስደርስ ነበር ጊዜው መምሸቱ ትዝ ያለኝ። ቢታኒያ በጥፍሮቿ ቆማ ስልኬን ስትጠብቅ ታየኝ። ዘርዐንም አግኝቼ ተለዋጭ ተልእኮ ካለ መጠየቅ ነበረብኝ። ደንገጥ ብዬ ወደ ይግዛው ዞር አልኩ...

"ወደ አዲስ አበባ ስልክ ይኖራል፣ አይደል?"

"ኧረ እንኳን በዚህ ሰዓት ቀንም ቢሆን የማዞሪያ ስልክ ከቀናት ቀጠሮ ውጭ አይታሰብም!"

ወሽመጤ ብጥስ አለ...

***

በአራተኛው ቀን ማታ በመከራ ስልክ አገኘሁ። ደስታውን አልቻልኩትም። ዘርዐን ሁሌ በሚያመሽበት በዮሴፍ አዳን ቤት አገኘሁት። ወልድያ መምጣቴና ሪፖርት መቀበሌ ሀቁን የበለጠ እንዳውቀው አድርጎኛል። ይህ በቀራው ስሜቴን ሦስት አራቴ ጎድቶታል። በፖለቲካ ቢሮው ላይ የቋጠርኩት ቅሬታ አሁን ሻኛና ደንደስ አውጥቷል። 'እንክፍ፣ የከተማ አርበኛ ሁላ!' አልኩት በሆዴ ያ ቀጭን ድምጹ ጆሮዬ ሲገባ።ዘርዐ ያ ረጅም ቁመናው አጥሮ፣ ቀይ የፊቱ ቀለም ወይቦ፣ የጎፈረው ጸጉሩ ተንጨፍሮ ታየኝ። በተመሰጠረኮድ ተነጋገርን። ወደ መቀሌ ሄጄ የኢሕአፓን መጻሕፍት ቤት አስተዳዳሪ እንዳገኘው አዘዘኝ። እጥር መልእክት ነው። የተልእኮውን ዝርዝር የማገኘው መቀሌ ሄጄ ነው ማለት ነው።

ትእዛዙን መቀበሌን አረጋግጬለት ስልኩን ዘጋሁ።

እጄ እየነዘረኝ ወደ ቢታኒያ ደወልኩ። ቤቲ ተጠራጥራለች መሰለኝ ዢ በአንድ ጥሪ ስልኩን ብድግ አደረገችው። አዲስ አበባን ከለቀኩበት ደቂቃ ጀምሮ ስልኩን ቤቷ እንደምታስገባው ነግራኛለች።"አቤ-------------ት!" ብላኝ ጣፋጩ ድምጿ ጆሮዬ ሲደርስ ተቃራኒ አቅጣጫ ይዘው ሲገፋፉ የሰነበቱት ነፍስና ስጋዬ ተፈላልገው ተሳሳቡ፣ ተጨባበጡ፣ ተጣበቁ፣ ተዋሃዱ...።

"ቤቲዬ ሆዴ...የእኔ ውብ..." ስሜቴ በጣም ከመናሩ የተነሳ የልቤን የምገልጽበት ቃል አጠረኝ።

"እእእ፣ ሰመረ በእኔ ላይ እንደዚህ አይጨከንም። አራት ቀን ሙሉ አይጨከንብኝም..." ስሜታዊ ሆና ድምጿ እርግብግብ ብሎ ማልቀስ ጀመረች። ላባብላት ስል ደግሞ በጩኸት አቋረጠችኝ።

"እናትዬ፣ በደንብ ተረጅኝ። ወልዲያ የቀጥታ መስመር ስልክ የለም። አሁንም ያገኘሁሽ በማዞሪያ በኩል ነው። ለዚያውም አራት ቀን ሙሉ ወረፋ ጠብቄ። ችግሩ ደግሞ በማዞሪያ ደወልኩ ማለት እንደልባችን መነጋገር አንችልም ማለት ነው። ሰላም ልልሽ ብቻ ነው የደወልኩት..." ላስረዳትና ላሳምናት ሞከርኩ።

"እሺ፣ መቼ ነው ደምትመጣልኝ?" ቢታኒያ ማለት የፈለኩት ገባት መሰለኝ ንጭንጭ ብላ ጠየቀችኝ።

"ከነገ ወዲያ!" አልኳት እፎ እንዳመጣልኝ፣ መረጋጋቷን ብቻ ስለፈለኩ።

'መቼ ማለት ነው ከነገ ወዲያ?" ልክ ዐቅሉ የተረበሸ ሕጻን ልጅ ይመስላል ድምጿ።

እስከሚገባኝ ድረስ ቢታኒያ እንዲህ የተጨነቀችው በተራ የፍቅር ግፊት ብቻ አይደለም። ለጥቂት ቀናት መለያየት ተዐምር ስለሆነባትም አይመስለኝም። እኔም ሆንኩ እሷ በሆነ ጊዜ፣ አይደለም አገር ውስጥ፣ የውጭ ጉዞም ልናደርግ እንችላለን። ያስጨነቃት የድርጅት ተልእኮ ይዤ የተሠማራሁ መሆኔ ነው። የሆነ አንዱ የደርግ ፖሊስ ተኩሶ ሲገድለኝ ህልም እንደሚታያት ደጋግማ ነግራኛለች። እኔ ደግሞ ቢታኒያ ከብርከታዊት ጋር ስትገናኝ፣ እኔን እያነሱ ሲያወሩ፣ ሲያወግዙኝ፣ ሲማማሉብኝ... ያላለምኩበትን ቀን አላስታውስም። ያው ልነግራት ስለማልችል በውስጤ ይዤዋለሁ። አሁን አሁን ደግሞ ይሄ ቂላቂል የከተማ አመጽ በሚሉት እቅዳቸው እንዳያስገድሉብኝ እፈራለሁ።

"ሆድዬ፣ ሐሙስ መሆኑ ነው። እንደምንም ለመድረስ እሞክራለሁ። እሺ ቤቲዬ? በጣም በጣም እወድሻለሁ። ልቤ ሁሌም ካንች ጋር ነው። በደህና ጠብቂኝ!" ስስት እንደበቱን አንዘፈዘፈው።

አጸፋውን ከኔ በባሰ ሆደባሻነት መልሳልኝ ተሰነባበትን።ረፋድ ላይ ነዳጅ ምልቼ የመቀሌ ጉዞዬን ጀመርኩ። የተሰባበረው የጠጠር መንገድ መኪናዬን ሰማይ አድርሶ ሲያፈርጣት የአርሜኒዲዩን ኡኡታውን ታቀልጠዋለች። የብረትና የቆርቆሮ ዘር ይንጫጫል። የተሻለ መንገድ ሳገኝ ወደ ቢታኒያና ወደ ጭንቀቷ ምክንያቶች የሐሳብ ቀዘፋዬ ተመለስኩ...

ከፋቱ ደግሞ ደ፣ግ ሰሞኑን በኢሕአፓ ላይ ተደጋጋሚ የከስ መግለጫ እያወጣ ነው። የትላንት ምሽቱ ማስጠንቀቂያ አዘል ክስ በተለይ ጠንከር ያለ ነበር። ብርከታዊት ነበረች ማታ ከዜና አወጀ በኋላ ያነበበችው። ድምጿ ከወትሮው ተስሎ ተሰማኝ...

"አናርኪስቶች ሕገወጥ የሠራተኞች አድማ በመጥራት፣ ያ ሲከሽፍባቸው ደግሞ የሥራ መሣሪያዎች እንዲሰባበሩና እንዲዘረፉ መመሪያ በመስጠት፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ገቢን የሚጎዱ ተግባራት በመፈጸምና በሌሎች ዘዴዎች በብሔራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ ጥረታችን ላይ ይህ ነው የማይባል የኢኮኖሚ አሻጥር እየፈጸሙብን ይገኛሉ።"

ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም "አብዮታዊ ሰደድ" ብለው ያቋቋሙት ድርጅት አላቸው። በዚሁ ስም የሚጠራው የድርጅቱ ጋዜጣ ታዲያ ቁጥር አንድ ኢላማው ኢሕአፓ ነው። ጋዜጣውን ዮሴፍ አዳነ ከሻለቃ ሽታዬ ደስታ ተቀብሎ ያመጣልናል። ለጸረ-ፕሮፓጋንዳና ለምርምር ሥራ ይጠቅማል። ምድር ቤት ባለው "አደፍርስ" ቅጅ እናደርገዋለን። የመኢሶኑ"የሰፊው ሕዝብ ድምጽ" ጋዜጣም በዚህ ወር ከዚህ ሌላ የጻፈው ነገር የለም። "ኢሕአፓ ከፖለቲካ ውኅንብር ወደ አኮኖሚ አሻጥር..." የሰሞኑ ተከታታይ ርእሰ-አንቀጹ ነው። ዞሮ ዞሮ ለእኔም ሆነ ለፍቅረኛዬ የደኅንነት ስጋቱ ያለው እዚሁ መሀላችን ነው። በቀጥተኛ አነጋገር በዘርዐ ክህሸን ማስታወሻ ደብተር ውስጥ ነው...

"ኢሕአፓ ራሱን ከደርግ/መኢሶን ጥቃት ለመከላከል መዘጋጀት አለበት። የከተማው ትጥቅ ትግል የገጠሩ ትጥቅ ትግል አካል ነው። ስለዚህም ሲያጠቁን ዝም ብለን እንመለከትም..."

አለማስታወስ ይሻለኛል እንጅ ሳስታውሰውማ ለደቂቃዎች ሰላሜን እጣለሁ። ምክንያቱ ግልጽ ነው። ድርጅቴ "በሉፍ አበባ አባዜ" ተጠምዶ በራሱ ላይ ቢላዋ እየሳለ ነው። የዘርዑና የዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ከርከር እንግዳ ነው። ነገር ግን ይሄንን የምለውጥበት ዐቅም አላገኘሁም። የብርሃነመስቀልና የጌታቸው ማሩ ተቃውሞም ብዙ አልረዳኝ። መነሻው ላይ ብንግባባም መድረሻው ላይ ግን ርቀታችን የሰማይና የምድር ያህል ሆነ።

ኡ-------------ፍፍፍፍፍ! ኩኃ ከተማን አቋርጬ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ላይ መቀሌ ገባሁ።

###

የሐምሌ ዝናብ እንደ ጉድ ይወርዳል። የኢሕአፓ መጻሕፍት ቤት ከዋናው ቴሌኮሚኒኬሽን መሥሪያ ቤት አጠገብ መሆኑ ተነግሮኛል። መቀሌዎችን ቆም እያልኩ እየጠየኩ ወዲያው አገኘሁት። የመጻሕፍት ቤቱ አስተዳዳሪ ከባልኮኒ ጀርባ አዳዲስ መጻሕፍትን ከአሽጋቸው እያወጣ ሲደረድር አገኘሁት። ብቻውን ሆኖ ሳገኘው ደስ አለኝ። ብን አድርጎ ያበጠረው ጎፈሬ ጸጉሩ ዋነኛ ምልክቱ ነው። ልክ የተደፋ እንሥራ የተሸከመ መስሎ ታየኝ። በትክክለኛ ስሙ መምህር ጸጋይ ተክለብርሐን ይባላል። በኢሕአፓ የተሰጠው ሥም ደግሞ ካልአዩ ነው። ገብቼ በአማርኛ ሰላምታ ስሰጠው ነቃ ብሎ አየኝ። ከመሰላል ወርዶ እጆቹን እያራገፈ መጣ። የተሰጡንን ኮዶች ተለዋወጥን። ከተጨባበጠን በኋላ በሩን ዘጋው። በሰሀን ተቋጥሮ የመጣለትን ምርጥ ምጥን ሽሮ ጋብዞኝ አብረን በላን።

"ካልአዩ፣ ትግራይ የፖለቲካ ሁኔታው እንዴት ነው?" በለሆሳስ የመነሻ ጥያቄ አቀረብኩለት።

"ዋእ፣ በጣም ውስብስብ...በጣም አስቸጋሪ...በጣም አደገኛና አስፈሪ ነው።" የትግርኛ ተጽእኖ በተጫጫነው አማርኛ መለሰ፣ "እዚህ የኛ ድርጅት አለ፣ ተሓህት አለ፣ ኢደዩ መጥቷል፣ ደርግና መኢሶንም አሉ። ሌላ ደሞ ትግራይን እገነጥላለሁ የሚል አክራሪ ስብስብ 'ትጥቅ ትግል ጀምሪያለሁ' ይላል። ከተማ ውስጥ የምታየው ነገር በሙሉ ሽኩቻና ትንቅንቅ ነው። በተለይ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ከተቋቋመ ወዲህ ብሶበታል። ማን ከየትኛው ድርጅት ጋር እንደተሰለፈ አታውቅም። እኛ፣ ተሓህትና መኢሶንማ ተወው። ተሓህቶች እኛን 'የታላቋ ኢትዮጵያ ጠበቆች' ይሉናል። እኛ ደግሞ 'ጠባብ፣ ጎጠኛ፣' ምናምን እንላቸዋለን። ፍትጊያው ታይቶ የማይታወቅ ነው..." አለኝ፣ በእጁና በዐይኖቹ የሽኩቻውን አስከፊነት እያሳየኝ።

ብዙም አልተገረምኩም። መኢሶን በደርግ ካባ ተጠልሎ መጥቶ እዚህ ጨዋታ መጀመሩ ግን አበሳጨኝ።"ይሄ መኢሶን የሚሉት አሽከላ ለመሆኑ ምን ምን እያደረገ ነው ያለው?" አሁንም ድምጼን ዝቅ አድርጌ ጠየኩት።

"ዋእ? ምን የማይሠራው አለ?! የትግራይን ወጣቶች ከእኛና ከተሓህት የማስኮብለል ተልእኮ ይዞ ነው የመጣ። ስሞኑን የተወሰኑ ልጆችን 'የትግራይ ቀይ ወጣቶች' ብሎ መልምሎ ሲያበቃ የፖለቲካ ሥልጠና እየሰጠ ነው። የሚስቴ ትንሽ ወንድም ተቀላቅሏቸዋል። እሱ ነው የሚነግረኝ። በተለይ አስመራ የሚኖሩ የትግራይ ልጆችን አተኩሮባቸዋል። ኤርትራውያን 'አጋሜ' ምናምን እያሉ ስለማገሯቸው ይሄ ለመኢሶን መና አወረደለት። በሰፋት የመለመለው ከእነርሱ ነው። ስልጠናቸውን እንደጨረሱ ወደ ሌሎች ክፍለሐገሮች በካድሬነት ሊያስማራቸው ነው። ተሓህት በበኩሉም ሌላ ሽኩቻ ውስጥ ገብቷል። ሲያቀብጠው የፖለቲካ ዓላማዬ 'የትግራይ ሪፖብሊክ'ን መፍጠር ነው አለ።፡ በጉባኤ ያልጸደቀ፣ ማን

እንዳወጣው የማይታወቅ ነገር ነው። በዚህ ምክንያት እየተበጣበጡ ነው።"

ኢትዮጵያ አገሬ ልክ እንደ ሰው አሳዘነችኝ።

መምህር ጸጋይ በጣም ጠቃሚ የሚባሉ መረጃዎችን ለየ። በወረቀት፣ በቴፕ ከርና በሸክላ የተጻፉና የተቀረጹ ናቸው። በአንድ ካርቶን ውስጥ በጥንቃቄ አስገብቶ ከነ ቴፑ ሰጠኝ። ምሽት ላይ አዛው አካባቢ አልጋ እስይዞኝ ሲያበቃ ስልክ ተደዋውሎ ሲመለስ የሚቀጥለውን ተልእኮዬን ነገረኝ።

"አዲግራት ትሄድና የሚጠብቅህን ሰው ወልዱ ስባጋድስ ሆቴል ታገኘዋለህ።አሲምባ አድርሶ ይመልስሃል። አሲምባ እግረ መንግድህን አስር ሽህ ብር ይዘህ ትሄዳለህ። ጓድ ጸጋዬ ገብርመድህንን ታገኘዋለህ። ትሰጠውና የሚልህ ነገር ካለ ትሰማውና ትመለሳለህ። እኔ ብሩን እዚህ ለመሰብሰብ ሦስት ቀን ያስፈልገኛል። ምግብ ምናምን ምንም ችግር የለም። መደወል ከፈለክ መጻሕፍት ቤት የቀጥታ ስልክ አለ..."

ኡሁሁሁሁ......! በርግጋ ሽቅብ ልትበር የነበረችው ነፍስያዬ መለስ አለች፣ ስለኢሲምባ ጉዞዬና ስለስልኩ ሲነግረኝ። አ—ሲ—ም—ባ! ይሄ ተራ ጉዞ አይደለም። የኢትዮጵያን ወጣት ትውልድ የተስፋ ምድር ዐይቶ የመምጣት ቅዱስ ተልእኮ ነው።

ብሩ እስከሚሰበሰብ የቆየሁበት ጊዜ እንደፈራሁት አልነበረም። በነበረኝ የሦስት ቀናት ጊዜ ለደቂቃም ቢሆን ሥራ አልፈታሁም። መምህር ጸጋይ የሰጠኝን ውድ መረጃዎች በጥንቃቄ ስመረምር አሳለፍኩ። በአማርኛ ቋንቋ ከተዘጋጁት መካከል አንድም የቀረኝ የለም። የትግርኛዎቹን እሱ እንዲተረጉምልኝ ማድረግ አልፈለኩም። ጊዜም አልነበረውም። አዲስ አበባ ከኢሳያስ ጋር የምንከርምበት ይሆናል። ከቢታኒያም ሳልርቅ ነው ያሳለፍኩት። በየምሽቱ እየደወልኩ አብሬያት ያለሁ ያህል እስኪሰማኝ ተጫወትን።

***

ጉዞ ወደ አሲምባ...

የሚመራኝ ወጣት ገበሬ ምሽት ላይ ወልዱ ስባጋድስ ሆቴል መጣ፣ አዲግራት። የሚታጠፍ ሳንጃ ያለው አልቤን የሚባል ጠመንጃ ይዟል። አማርኛ በደንብ ይረዳል፣ በመጠኑም ይናገራል። በቱታና በቆዳ ጫማ ሲያየኝ ደስ አላለውም። ቢያንስ ጫማ እንድቀይር መከረኝ። ወዲያው ተስማማሁ። እሱ ያደረገውን

ፕላስቲክ ጫማ ዓይነት በሦስት ብር ገዝቶልኝ መጣ። እሱም እዛው ቡና ቤቱ ውስጥ ፍራሽ ተዘርግቶለት አደረ። ሌሊት ፲፩:00 ሰዓት ሲል ተነስተን ጉዞ ጀመርን። ከተማዋን ወደቀኝ እየተውን ተጓዝን። መሄድ ብቻ ነው። ጆሮዎቼ ኮሽ የምትል ድምጽም ብትሆን በአራቱም አቅጣጫ በንቃት ይከታተላሉ።

"አዲግራት ያለው የደርግ መድፈኛ ሻለቃ አልፎ አልፎ ወታደሮችን ለቅኝት በአካባቢው ያሰማራል። በንቃት እየተከታተልክ መጓዝ አትርሳ! ተሐህቶች ካጋጠሙህ ከርክር ምናምን እንዳትገጥም። ታጋይ ነኝ ብቻ ብለሃቸው እለፍ!" መምህር ጺጋይ በቁምነገር አስጠንቅቆኛል።

ረፋድ አራት ሰዓት አካባቢ ከአዲግራት ብዙ ርቀናል። ላቤ ከግንባሬ እየተቀዳ መንቆርቆር ጀመረ። ለመሪዬ ደካማነት ወይም የከተሜ ቅብጠት ላሳየው አልፈለኩም። የምጓዘው በእልህ ነው። አንድ የገጠር መንደር ስንደርስ እረፍ አልን። በአንድ ገበሬ ቤት ያገኘነውን ነገር ቀማምሰን ቀጠልን። አሁን ከተማዋን ከሩቅ ቀስ በቀስ ከጀርባችን እየተውናት ብዙ ሄደናል። መሪዬን ስጠይቀው ትክክል ነኝ። ረጅምና እጅግ አድካሚ ድንጋያማ ሜዳ አቋርጠን ጀንበር ጠለቀች። ስጓዝ ብዙም አይሰማኝም። መከራው እረፍት አድርጌ እንደገና ጉዞ ስጀምር ነው። ጭኔ ተላልጦ ይጠዘጥዘኝ ጀመር። እጅ መስጠት የለም! ጥርሴን ነክሼ በማግስቱም ቀጠልኩ። ረፋድ ላይ ግን ሰውነቴ የእኔ አልመስልህ እያለኝ መጣ።

"እህ፣ እንዴት ነው፣ ዛሬም እንገባ?" የሚያበረታታ ነገር ፍለጋ መሪዬን ጠየኩት።

"ዛሬማ የግድ ነው። ጀንበር ከመጥለቋ በፊት እንደርሳለን። አሲምባ ማለት'ኮ ያ ጉም የሸፈነው ተራራ ነው። ይታይሃል?" ብሎ የበሬ ቀንድ የመሰሉ ከፍተኛ ቦታዎችን በዱላው እየታገዘ አመላከተኝ።

ቅርበትና ርቀቱን በጭራሽ መገመት አይቻልም። ብቻ እየደረስኩ ነው ብዬ ራሴን አጠናከሬ ቀጠልኩ። መሪዬ መርቶ ካደረሳቸው ሰዎች ሁሉ ጎበዝ መሆኔን ደጋግሞ ይነግረኛል።

"ዋእ! እንዳንዱማ 'ግደሉኝ እንጂ ከዚህ በኋላ ንቅንቅ አልልም' ብሎ ለጥ ይላል!" ሳቀ።

የምገምተውም በልጅነቴ ጀምሬም የማውቀው ነገር ነው። ይህች ጉዞ ለገበሬዎች ምንም ማለት አይደለችም። ሽርሽር ማለት ናት። ለዚያውም በጠበንጃው ላይ የእኔን እቃ ደርቦ ተሸክሞ። ድርጅቴ ኢሕአፓ ይሄንን ጥንካሬ ነው እያጣ ያለው። ቻይናዊው ኮንፊሽስ ያለው ነገር ትዝ አለኝ። "ጥበብን ከተግባር መማር ጥሩ ነው። ነገር ግን ረጅምና መራራ ነው። ጥበብን ከሰው በመኮረጅም መማር ይቻላል። ነገር ግን ይህ ቀላልና ርካሽ ነው። ጥበብን በልቦና ምርምሮ መማር ከባድ ነው። ነገር ግን ከዘዴዎች ሁሉ እጅግ የተከበረው ዘዴ ነው።" ድርጅቴ ልቦናውን ደፍኖ ከተግባር መማርን መርጧል።

'እኛ አባላቱና መሪዎቹም የትምህርቱን መሪነት መንገዱት ያምኑበት ወንዱ ጥሉን እንዳያዜሁ ታገልኩ።

ከቀኑ ስምንት ሰዓት ሲል እንደ ምሶሶ ቀጥ ያለ ተራራ መውጣት ጀመርን። በደን ውስጥ እያለፍን ሲያዳልጠን ምናምኑን ይዘን እየቀረን ከእንዱ ቋጥኝ ወደሚቀጥለው እየተንፏቀቅን በመሀል ተነስ እረፍ እያልን ወጣነው። መሪዬ ዳገቱን ከምንም አይቆጥረውም። ጠብ ጠብ እያለ ይወጣዋል፣ እንደ በጎ ላይ ቆሞ ይጠብቀኛል። አስር ሰዓት ሲል እንዱን ተራራ ጨርሰን ሀ ያቋኛውን ተያያዝን።

"ጓዱ፣ እያየህ! አሁን እሰጋበን ረግጠሃል። ይህች መንደር ጋራቢኖ ትባላለች። በቃ፣ እሲያሚ ከዚህ ጀምሮ ነው!"

እሲምባን መርገጤን ሳውቅ እንግዳ ስሜት ደርሶ ውርር አደረገኝ። "ትግላችን መራራ ድላችን የማይቀር ነው!" ልቢ አፍ አውጥታ ቀረርቶውን አቀለጠችው። አዲስ አበባን አስታወሺ በእነ ዘርዐ ጨኋረዬ እንዲላጥ አልፈለኩም። ፍቅረኛዬ ድቅን ስትልብኝ ብቻ ተመልሺ የምንገራትን ታሪክ እእምሮዬ ውስጥ እየመዘገብኩ ቀጠልኩ። ጋራቢኖ ትንሽ የገጠር መንደር ናት። መሪዬ ከሚያውቀው አንድ ቤት ገብተን ትንሽ እረፍ አልን። ምግብ ቀማምሰን ነጣቱ ሻሽ የመሰለ የማር ብርዝ ጠጣን። አሁን ጉልበቴ ጨመረ። ወዲያው ተነስተን እንደገና መሄድ ጀመርን።

"ቢቃ! ይህች የደረስንባት መንደር "እዎዎ" ትባላለች። ጓዶች ያሉት እዚህ ነው!" እንደ ዛፍ ሥር እረፍት እንዳደርግ ነግሮኝ ሄደ።

የከበበኝን የተራራ ሰንሰለትና ወጣ ገባ ምድር ሳየው ከዓለም የወጣሁ መሰለኝ። መሬት ከእጅ እግሯ የወደቀች ሸከላ ትመስላለች። ቅዝቃዜው ደግሞ ልክ እንደአለንጋ ይጋረፋል። ያ ሁሉ ሆኖ ራሴን እሲጋባ አፈር ላይ በማግኘቴ ከልብ ደስተኛ ነኝ። አካሌ በድካም ዝሏል፤ መንፈሴ ግን ከመጠን በላይ ንቁ ነው። ጀንበር ጠልቃ ምሽቱ እየወደቀ ነው። በግምት ከሃያ ደቂቃ በኋላ መሪዬ ከአንድ ድንጋይ ቤት ጀርባ ወጣ። በፉጨት ካነቃኝ በኋላ በእጁ "ና" የሚል ምልክት አሳየኝ። ቀስ ብዬ ተነሳሁ እንከስ እያልኩ ሄድኩ።

"ና፣ እዛኛው ቤት ግባ። ጓድ አምሀን ታገኘዋለህ..."

"ጓድ አምሀ" ማለት ጸጋየ ገብረመድህን (ደብተራው) መሆኑ ነው። የኢሕአሠ ዋና ኮማንደር፤ በዕድሜው የእነ ብርሃነመስቀል ትውልድ ነው። አዲስ አበባ እያለ እንዴ ብቻ ተገናኝተናል። ለበይነቀጠናው የተላኩ "እያፍርስ" ማባዣና ሌሎች የጽሕፈት እቃዎችን ሲያስረክበኝ ነው የተዋወቅነው። ከዚያ በፊት ደግሞ

አዲሳባ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ በስም ዐውቀዋለሁ። ዝና ባተረፈበት አንድ ፖለቲካዊ ቅኔው ነው ስሙን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት...

ቀን በቀን ቁማር ተጫውቼ፣

ተበልቼ ገባሁ ተረትቼ።

ምንኛ ዕድሌ በሰመረ፣

ዘውዱን ገልብጨው በነበረ!

ጸጋዬ አሁን ያስተውሰኝ ወይም ይረሳኝ እንደሆነ አላውቅም። አልፈው ከምሄደው ከወዲህኛው ቤት የተሟሟቀ ወሬ ይሰማኛል። የኢሕአሠ አባላት እንደሆኑ አልተጠራጠርኩም። ጸጋየ ደብተራው ከእነርሱ ተለይቶ ለብቻዬ ሊያገኘኝ እንደፈለገ ገባኝ። ትክክል ነው። እኔ የፓርቲው አመራር አባል እንጂ የኢሕአሠ አባል አይደለሁም። እነርሱም ምናልባት በግልባጩ። ጸጋየ ግን የሁለቱም አባል ነው። ሌላም ምክንያት ሊኖር ይችላል። የወልድያ አፕሬሽን ውድቀት ብዙ የሠራዊቱን አባላት እንደወጡ አስቀርቷቸዋል። የተረፉትና ቤዝ ላይ የነበሩትም ሞራላቸው ተጎድቷል። በዚህ የስሜት ዐውድ ውስጥ ሆነው እንዳያገኙኝ ፈልጎ ይሆናል። በቀስታ ሄጄ ገባሁ...

"ጓድ አላምረው፣ እንኳን ደህና መጣህ!" ብሎ ከተቀመጠበት ተነስቶ ሲስመኝ በማስታወስ ችሎታው ተገረምኩ።

ድሮም ቀርጫማ የነበረ ሰውነቱና የፊቱ ገጽ የበለጠ ቅርጭምጭም ብሏል። መነሳቱሉ ረጅም ፊቱን መፐረቢያ አስመስሎታል።አብረን አፍ ለአፍ ገጥመን ስናወራ አመሸን። ያላነሳነው ጉዳይ የለም። ስለ ወልድያው የኢሕአሠ ውድቀት ግን አንድም ቃል ሳነሳለት አልፈለኩም። እንጀቴ ነፍሯል። ከዘመቻው ከተመለሱ ገና ሳምንት እንዳልሞላቸው ሲነግረኝ ብቻ ተነስቷል። ራት ቀርቦ አንድ ሁለቴ እንደጎረስን ደግሞ አብዲሳ አያና መጣ። የአሲንባው ኢሕአሠ ዋና ኮማንደር ነው። በትክክል አላስታውሰውም እንጂ ከብርሃነመስቀል ጋር አውሮፕላን ከጠለፉት ሰባቱ ተማሪዎችም አንደኛው ነው። ፊቱ አዲስ አልሆነብኝም። የጠለፋው ቀን ከጀርባዬ የኦሮምኛ ቅላጼ በተጫነው አማርኛ ማስጠንቀቂያ ይሰጥ የነበረው እሱ ነበር ማለት ነው። እስከ እኩለ ሌሊት አወራን። ትንሽ ቆይቶ ሌሎች ሁለት ታጋዮች መጡ። የወሬው ርእስ አንድ ብቻ ሆነ። "ኢሕአፓ ረስቶናል..."

ብሩን አስረከቢያቸው በማግስቱ ወደ አዲግራት ተመለስኩ።

ከአዲግራት ወደ መቀሌ...ከመቀሌ ወደ አዲስ አበባ...

# 24

አዲስ አበባ በኃይለኛ ዝናብ ስታነፈርቅ አገኘኋት።

ወደ መሀል ከተማው ስገባ ዝናቡ ቀንሶ ወደ ካፊያነት ተለወጠ። ብርዱ፣ ድካሙ፣ ርሀቡ...ከቢታኒያ ጋር ስንተቃቀፍ እልም እንደሚል ዐውቃለሁ። የኑረዲንን ዳቦ ቤት አልፌ ወደ ጋራዥ ስታጠፍ ናፍቆቴ ጨመረ። ወዲያው ሚካኤለ በዋናው ቤት መስኮት በኩል ብቅ ብሎ አይቶኝ ጥልቅ ሲል ዐየሁት። ሮጦ ሄዶ ቢታኒያን ሲነግራት ታየኝ። በእሷ መደሰት እሱም ይደሰታል። ጋራዡ ሁሉም ሠራተኛ ለምሳ ስለወጣ ኦና ሆኖ ጠበቀኝ።

'የሱ----ፍ አበ---ባ! ፀሐይን እምቢ ብላ የከተማ አምፖልን አመለከች! የዚህ ውጤት የማታ ማታ ምን ይሆን? ይሄ አርምሞ ያን ጊዜ ምን ይመስል ይሆን?' ጭልልታው ሲከብደኝ በውስጤ እንዲሁ ጮኽኩ።

ከቢታኒያ ቀጥሎ ለሚቀጥሉት ቀናት እጅግ የምፈልገው ሰው ኢሳያስ ነው። መረጃዎቹን መርምረን ማዘጋጀት ይኖርብናል። ሳስበው ኢሕአፓ በትርኪ ምርኪ የየዕለት ሥራዎች በመዋጡ እየረሳው የመጣው ድንቅ ባህል ነበረው። እንድን ችግር ወይም ከስተት በርእዩተ-ዓለም መነጽር ብጥር አድርጎ የማየት ልምድ። አሁን አንድ ቦንብ የሆነ ጽሑፍ በማዘጋጀት ይህንን ባህል ነፍስ ልዘራበት ወሰንኩ። የጽሑፌ ርእስ "ሱፍ አባባዊነት" ወይም "ሰን ፍላወሪዝም" የሚል እንደሚሆን ገና መቀሌ ሳለሁ ነው የወሰንኩት።

በምሥጢራዊው በር ወጥቼ በስስት ወደ ቀዩ በር ስማትር ገርበብ ብሎ ታየኝ። 'ማን ከፈተው?' በመገረም ዙሪያ ገባውን እያየሁ ስጠጋ ቢታኒያ ብቅ አለች። ከጀንበር የብርሀን ቦቃታ የሚሮካከር ፈገግታ ተለዋወጥን...'

"ምናባህ፣ በዚያው ተመልሰህ የሄድከ መስለህ የምታስደነግጠኝ?" በውሸት ኩርፊያ ስስት ያደፈረሳቸውን ዐይኖቿን በለጠጠቻቸው።

"ይሄማ እንዴት ይታሰባል፣ ፍቅሬ?" የያዝኩትን እቃ አስቀምጬ ተጠመጠምኩባት።

ወይዘሮ ማስተዋልን ሶፋ ላይ ጋደም ብለው አገኘኋቸው። አቀባበላቸው የውስጥ ስሜቴን እንደ ፊኛ ወጥሮ ሊያፈነዳው ምንም አልቀረው። ጉንጭና ጉንጬን ይዘው አገላብጠው ሳሙኝ። ተለይቼ የቆየሁባቸው ቀናት በትክክል እውነተኛ ዝምድናችንን እንደገለጡት ገባኝ። ቢቃ፣ ከልጃቸው ጋር ሥነ-ሥርዓቱን ችላ ብለን ባልና ሚስት ሆነናል።የምን ሰማኒያ፣ የምን መሀላ፣ የምን ቀለበት? ለመጀመሪያ ጊዜ አብረናቸው ለምሳ ተቀመጥን።

ወዲያው ሙሴ ባልዲ፣ የመሳለሚያ ቁጥር አንድ ወሮበላ፣ ድምጹን ከፍ አድርጎ ሰላምታ እየሰጠ መጣ። ማመን አልቻልኩም። ከየትኛው ደመና ዱብ እንዳለ ገረመኝ። ወደ ቤት ሲገባ አፈጠጥኩበት። መካከለኛ ቁመት፣ የተንሳቆለ አካል፣ በሲጋራ ተጠብሶ ሳምባ የመሰለ ከንፈር፣ በጢስና በመጠጥ ብዛት የጎሸ ዓይን...ጭፍርር ያለ ጸጉር...። ሁለመናው ያስፈራል። እንግዳ ነገር ሆኖብኝ ወይዘሮ ማስተዋልንና ቢታኒያን በግራ መጋባት ተራ በተራ አየኋቸው። ታሪኩን ነገሩኝ።

ከሳምንት በፊት ሰተት ብሎ ወደ ግቢው ገባ። እግራቸው ሥር ወድቆ ይቅርታ ጠየቀ። እናትና ልጅ ይቅር! ብለውት አሁን የቤተሰቡ ባለሟል ሆኖ አገኘሁት። ዋና ጉዳይ አስፈጻሚና የደህንነት መኮንን። ትህትናው አስገራሚ ነው። እኔንም ሲያይ መጥቶ ጉልበቴን በይቅርታ ሊስም ተገለገለ።

"ይቅርታ አድርጌልሀለሁ!" ስለው ተመልሶ ተቀመጠ።

ማስተዋል የልጆቻቸውን ያገለገሉ ልብሶችና ጫማዎች ሰጥተውታል። ይሄንንን ለብሶም የተጎዳ አካሉ ራሱን ሊደብቅለት አልቻለም። በጣም ተሸሎት አይቼው መሆን አለበት። ወሬው በጣም አስቂኝና ግልጽ ነው። ብቆይ ደስ ይለኝ ነበር። በዱርየነት ጊዜው የሠራውን ወንጀል እያወራ በሳቅ ፍንድት አደረገን። ለመሄድ የቢታኒያ ስምምነት ያስፈልገኛል። ወደ እሷ አየሁ...

"እርፈህ ቁጭ በል፣ የትም መሄድ የለም!" ለመሄድ ስቁነጠነጥ በዐይኖቿ መልእክት አስተላለፈችልኝ።

ቡና ቀርቦ አቦሉ እስከሚጠጣ ድረስ ቆየሁ። ኢሳያስን በተቻለ ሁሉ ፍጥነት ማግኘት አለብኝ። ምን ተፈጥሮ እንደከረመ መስማት ይኖርብኛል። ልመለስ ቃል ገብቼላት ወደ ጋራዥ ሄድኩ።

የሱፍ አበባዊነት ጽሑፌን በፍጥነት መጀመር አለብኝ!

ከመቀሌ ያመጣሁትን መረጃ ከላንድሮቨሯ አውርጄ በምሥጢራዊው የጀርባ በር በኩል ወጥቼ ወደ ምድር ቤቴ ሄድኩ።ሸዋዬ መጀመሪያ ሳንኳኳ አልከፈተችልኝም። ድንገት ስለሚሆንባት ላይሰማት ይችላል። ደግሜ ሳንኳኳ ግን ፈጠን ብላ ቦግ አደረገችው። የተለየና ሞቅ ያለ ፈገግታ አሳይታኝ ወደ ጀርባዋ ዞራ...

"ጓድ አላምረው ነው። ኢሱ! ንገራቸው፤ ጓድ አላምረው ነው..." አለች በሩን ከጀርባዬ እየዘጋች።

የፖሊት ቢሮ አባላት ዉስጥ እንዳሉ ገመትኩ። ትክክል ነኝ። ዘርው ከሀሸንና ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ አሉ። እንሶላ ስለለበሱ ልክ አሁን ገና ከመስክ የተመለሰ ገበሬ ይመስላሉ። ዘርውማ የተቆራረጠች የሰሌን ባርኔጣ አድርጎ ምኑም አይለይ። ተስፋዬን ምናልባት በመነጽሩ መለየት አይከብድም።ስንተያይ እየሳቁ አውጥተውት የነበረውን ሽጉጣቸውን ወደ ወገባቸው መለሱ። ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋወጥን። ደጀኔ የለም። እሱ ስለሌለ ይሆናል ጥቢቃ ያላቆሙትና በሩ ሲንኳኳ የደነገጡት።

"ጓዶች፤ የጠላት ከበባ መስሏችሁ ነበር፤ እንዴ?" ተራ በተራ እያየሁ ጠየኳቸው።

"ታዲያስ! በእውነት ነው የምለው... አላምረው የሚባል የኛ ሰው በዚህ ሰዓት ያንኳኳል ብዬ ጨርሶ አልጠበኩም! ሰሞኑን ስላልነበርክ ነው መሰለኝ ረስቼሃለሁ..." ዘርው እየሳቀ መለሰልኝ።

"እንኳን ደህና መጣህ! የተሳካ 'ሚሽን' እንደነበር ዐውቄያለሁ።" ዶክተር ተስፋዬ እንደገና እጄን ጨበጠኝ።

ሊወጡ ሲሉ እንደደረስኩ ሁኔታቸው ነገረኝ። አጭር መረጃ ተለዋወጥን። ሪፖርቴን በጽሑፍ አዘጋጅቼ እንደማቀርብ ነገርኳቸው። እስከ መጭው የማእከላዊ ኮሚቴ ፕሊነም እንዲደርስ አሳሰቡኝ። እነርሱ ደግሞ የደርግ/መኢሶን አፈና እየጠነከረ መምጣቱን አስታውሰውኝ ሁላችንም ጥንቃቄ ለንድ፣ያደርግ አደራ ብለው ተሰነባበትን።

'የእኛዎቹ የሰፋ፡ አበባ ደራሲያን!'

ቅሬታዬ በተለይ ዶክተር ተስፋዬን ላይ ማንፍል ሊልብኝ ፈለገ። በኢሕአሠ ላይ ግፍ ሠርቶ እሱ ግን ትንሽ ጭረት ሳያገኘው፣ ሳይደማ፣ ሳይሞት ሾልኮ እንደመጣ ተሰማኝ። ዘርው ደግሞ የሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል መንፈስ መስሎ ታየኝ። ሻለቃ መንግሥቱን ግደሉልን እያሉ አዋከበው ወደ ስህተት እየመሩት ያሉት እሳቸው ናቸው። ያም ሆኖ የማታ ማታ ተጠያቂው ዘርው ራሱ ነው።

###

"እውር ሸፈተ በጓሮው!" ኢሳያስ እንግዶቹን ከሸኘ በኋላ ሲጋራውን እያቦነነ ተንደርድሮ ወደኔ መጣና አቀፈኝ።

ጊዜ ማባከን አልፈለግንም። ወደ መረጃ ልውውጣችን ገባን። እኔ ባልነበርኩባቸው ቀናት እሱ የትም ንቅንቅ አላለም። አንድ የማእከላዊ ኮሚቴ አስቸኳይ ስብሰባና ሁለት የፖሊት ቢሮ መደበኛ ስብሰባዎችን ተካፍሏል። በኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ አባላትና በስድስቱም የአዲስ አበባ በይነቀጠና ኮሚቴዎች መካከል በየአርባ አምስት ቀናት የሚካሄደው ምክክር ሲደረግ ኢሳያስ ከዮሴፍ አዳነ ጋር በረዳትነት ተመድቦ ቀጠና ስድስት ሄዷል። የስብሰባዎቹ ዋና ዓላማ ምን እንደነበረ አስረዳኝ...

"ቃለ ጉባኤውን አምጥቸዋለሁ። ሸዋዬ ትስጥሀለች፣ አንብበው። የፖለቲካ ቢሮው የደርግ/መኢሶንን ጭፍጨፋ ለመቋቋም አዲስ ስልት ነድፈያለሁ ብሎ መጣ። ስልቱን 'እያጠቁ መከላከል' የሚል ስም ሰጥቶታል። 'ከመሞታችን በፊት ገድለን ራሳችንን ማኖር' የሚል ትርጉም አለው። ደርግና መኢሶን አካባቢ ያሉ ቁልፍ የአመራር ሰጭዎችንና ፖሊሲ አውጭዎችን ኢላማ ማድረግ ፈልገዋል። በግለሰብ ደረጃ እየተከታተሉ መግደል ነው ፍላጎታቸው። በጣም አጨቃጫቂ የደህንነት ሥልት ነው የነደፉት። ሥልቱ ፈጽሞ ትክክል አለመሆኑን አጥብቄ ተከራከሬ ነበር። ካንተ ጋር የተነጋገርንባቸውን ነጥቦች በሙሉ አንስቻቸዋለሁ።"

ረስቶት የቆየውን ሲጋራ እየት አድርጎ ማግ ማግ አደረገው። ቁራጩን መሬት ላይ ጥሎ ከረጋገጠ በኋላ ቀጠለ...

"ሥልቱ፣ በዘርዐ ከህሸን አነጋገር፣ 'ደርግና መኢሶን ኢሕአፓን ለማጥፋት ለነደፉት እቅድ መልስ ነው።' በጣም ደካማና በጥርጣሬ ላይ የቆመ ክርክር ነው።ለ'ኔ ግን የሥልቱ ትርጉም ሌላ ነው። ያም 'ኢሕአፓ በርእዩተ-ዓለም መመራቱ ቀርቶ በ'ኢምፕሪሲስት' ስሜታዊነት (በአቦሰጡኝነት) መወሰን የመጀመሩ ትልቅ ውድቀት ነው...' ብዬ ተከራከርኩ።ይህ ሥልት ሌላው ቀርቶ ራሺያ ውስጥ በ1880ቹ ከተከሰተው 'ናሮድኒክ' እንቅስቃሴ ጋር ሲነጻጸር በጣም የዘቀጠ መሆኑን አስረዳሁ። በማርክሳዊ ሌኒናዊ የትግል ዶክትሪንም አያስኬደንም። ምክንያቱም አብዮታዊ ትግሉ የመደብ አሰላለፍን በመለወጥ ላይ ማተኮር አለበት እንጅ ግለሰቦችን በግድያ መበቀል ሕዝባዊ መሠረት የለውም። ከድርጅታዊ ፍላጎትና ጥያቄ ያፈነገጠ ግለሰባዊ ቂም በቀለኝነት ይሆንብናል አልኳቸው..."

"ኢሱ፣ ለመሆኑ እነ ብርሀነመስቀል የት ሄደው ነው አንተ ብቻህን የተከራከርከው?"

"ዋእ! ስመሬ፣ ማእከላዊ ኮሚቴው'ኮ የሰካራሞች ቤት እየሆነ ነው የመጣው። የሐሳብ 'ኢንተግሪቲ' ብሎ

ነገር እየጠፋ ነው'ኮ። ብርሃነመስቀልን ውሰድ። በ'ሕብረት ግንባር ጥሪ' ጉዳይ በወሰደው 'ፖዚቲቭ' አቋሙ ምክንያት የገዛ ራሱ እስረኛ ሆኗል። ምን ልበልህ፣ በኢሕአፓ ውስጥ የተተከለ የመኢሶኖች የትሮይ ፈረስ ተደርጎ እንዲታይ አድርገውታል። ሲጨንቀው 'እያጠቁ መከላከል' ያሉትን የልጆች ጨዋታ 'በጥንቃቄ እስኪተደረገ ድረስ አልቃወምም' ብሎት ሀረፈው።"

"እውነትከን ነው እየቀለድክ?" የሕጻናት ተረት የሚሰማ ልጅ ሳልመስል አልቀረሁም።

የውድቀታችን ፍጥነት በጣም እያስፈራኝ ኢሳያስን ሌላ ጥያቄ አነሳሁለት ፣"ኢሱ፣ ጌታቸው ማሩና አበበ ዋቅጅራ አልነበሩም ማለት ነው?"

"በጣም የሚገርምህ የ'ሕብረት ግንባር' ጉዳይ ተነስቶ ነበር። ጌታቸው የሐሳቡ ዋናው አቀንቃኝ ሆኖ ነው የምናውቀው። ብርሀነመስቀልና አበበ ተከራከረው ተከራከረው በተወሰኑ ቅድመ-ሁኔታዎች ኢሕአፓ የሚሰጠው አዎንታዊ መልስ ቀረበልን። ረጅም ክርክር ነው'ኮ። ጌታቸው አንድም ቃል ሳይተነፍስ ቀረ። ይሄንን ከወሰኑ በኋላ ነው እንደገና 'አጥቅቶ መከላከል' የሚል ሥልት ለውይይት ያቀረቡት። እንዴት በአንድ ጭንቅላት ሁለት ተጻራሪ ዐውዶችን ማስተናገድ እንደቻሉ ገረመኝ። በመጨረሻ፣ የፖለቲካ ቢሮው የሥልቱን የዕለት ተዕለት አፈጻጸም በበላይነት እንዲከታተል ሥልጣን ሰጡት። ሥልቁ ጸደቀ ማለት ነው። በሚቀጥለው ፕሊነም የሚገደሉ ሰዎችን ዝርዝር እንዲያመጣ ተወስኖ ሰብሰባው አበቃ።"

ኢሳያስ በንዴት ሌላ ሲጋራ ለኩሶ በእኔ ላይ ያተኮረ ወሬ ጀመረልኝ...

"ስብሰባው ላይ አንተ ትኖራለህ። ምንም ማድረግ የምትችል ግን አይመስለኝም። በድምጽ ብልጫ ጭጭ ያደርጉሀል። በዚህ ላይ የተለየ ሐሳብ ማራመድን በጣም አደገኛ እንደሆነ ነገር እያስመሰሉት ነው። ያንተን 'ገቨርዲኒዝም' ክርክር ፊት ለፊት መንቀፍ አልቻሉም። ውስጥ ለውስጥ ግን ደስተኞች አይደሉም። ከፍሉ ታደሰና ዘርዑማ የተሰደቡም ሳይመስላቸው የሚቀር አይመስለኝም። ብቻ፣ ሰመሬ፣ ኢሕአፓ ውስጥ የፍትህ ደረጃችን አጠያያቂ እየሆነ ነው። ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ለምሳሌ ከኤርትራ ተዋጊዎች ጋር በማእከላዊ ኮሚቴው የማይታወቅ ስምምነት አድርጓል ብለው አንዳንዶቹ ከሰውታል። ታያለህ፣ በመጨረሻ ምንም አይሆንም። ሌላ ሰው የሆነ ስህተት ሲሠራ ግን 'ትሪቡናል' አቋቁመው ቁም ስቅሉን ያሳዩታል።"

ይሄንን ሲነግረኝ በወልዲያ ኦፕሬሽን ውድቀት ግምገማየ ገረመው የነገረኝ ነገር አስታውሼ አጫወትኩት...

"ጸጋዬ ደብተራው የሠራውን ልንገርህ... ኢሕአሠ ወሎ እንዲት ትንሽ ከተማ ውስጥ አረፍት አድርጎ ነበር።

ጸጋዬ በቆየበት ቤት ወይም ሌላ ቦታ ሽጉጡን ይጥላል። ከተማዋ በአሰሳ ቁም ስቅሏን ዐየች። ሽጉጡ አልተገኘም። ጉዞ ላይ እያሉ ታዲያ አንዳንድ ጓዶች ጸጋዬ እንደማንኛውም ታጋይ ሊቀጣ እንደሚገባ አጉረመረሙ። ለካስ ደብተራው የራሱን ሰላዮች አሰማርቶ ኑሮ እነማን ምን እንዳሉ ልቅም አድርገው ነገሩት። ከዚያ ተናገሩ የተባሉ ሰዎችን እየጠራ ምን እንዳላቸው ታውቃለህ? 'ምንም ሳትፈጥሩ ነገር ራሳችሁን እደጋ ላይ ጣላችሁ!' ጸጋዬ በዚህ አባባሉ 'ኢሕአፓ የኔ ነው፣ እናንተን አይመለከታችሁም...' እንዳላቸው ነው የሚገባኝ። በጣም ያናድዳል።" ብዬው ከመስከ ያመጣኋቸውን በአማርኛና በትግርኛ የተጻፉ መረጃዎችን ከፋፍዬ ሰጠሁት።

ኢሳያስ በተለየ ፍላጎት ሰፍ ብሎ ተቀበለኝ። በትግርኛ ለተዘጋጀው መረጃ ቅድሚያ ሰጥቶ በፍጥነት ማገበብና ካሴቶችን ማድመጥ ያዘ። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ በሚሰማው ነገር ከት ብሎ ይስቅ ጀመር።

ባገኘሁት ፋታ አእምሮዬ ወደ ኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴና ፖለቲካ ቢሮ ተመለሰ...

"እጥቅቶ መከላከል" የሚባል ሥልት የፖለቲካ ልዩነት በጎላባቸው የኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ እንዴት እንደሚፈጸም...ጽንሰ ሐሳቡን ከየት እንዳመጡት...ከወታደራዊ ሳይንስ እንጻር ትርጉሙ በትክክል ምን ማለት እንደሆነ...በአፈጻጸም ሂደትና ከፍጻሜው በኋላ ስለሚያመጣው ትርፍና ኪሳራ...እባዘትኩ። አንድም ነገር አልገለጽልህ አለኝ። ግለሰብ ላይ ያተኮረ ጥቃት መሆኑ ደግሞ የበለጠ አሳሰበኝ ፡ በሌሎች አገሮች ተሞክሮ እንደነበረ ያነበብኩበት ቦታ አለ። ነገር ግን ኮሚኒስት መሪዎች "ፎኮይዝም" ወይም ተራ ነፍስ ገዳይነት ነው ብለው አስቁመውታል። በአንዳንድ የምእራቡ ሊብራል አገሮች ተበደልን የሚሉ ግለሰቦች መሪዎችን ገድለዋል ወይም ለመግደል ሞክረዋል። ፕሬዚደንት ሊንከን፣ አንድሬይ ጆንስተን፣ ጆን ኤፍ ኬኒዲ በነፍስ ገዳዮች ተገድለዋል። ግን ምን ተፈጠረ? ምንም!

'አዎ! የርእዮተ-ዓለም፣ የታሪክና የፖለቲካ ድጋፍም የለው!' ብዬ ለራሴ ቀጠልኩ።

ማእሴቱንግ የኮሚንታንጉን አገዛዝ መሪ ፕሬዚደንት ሱንያተሰንን ከድሉ በፊትም ሆነ በኋላ ተከታትሎ ማስገደል ይችል ነበር። አላደረገውም። ይህንን ያደረገው ጠላት ስላልነበሩ ወይም ፈርቶት አይደለም። የኮሚኒስት ፓርቲውና የማእ ትኩረት የሥርዓቶች ሹምሽር ማድረግ ላይ ብቻ ስለነበረ ነው። ፊደል ካስተሮ ሩዝና ቼ ጉቬራ የተዋጉትን የባቲስቱታ አገዛዝ አምርረው ይጠሉታል። የኪውባን ሕዝብ በማደህየትና በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም "ቡችላነት" ይከሱታል። የምንካዳን ጥቃት በድል ሲፈጽሙ ግን ትኩረታቸው አብዮቱ ነበር። ባቲስቱታን በግሉ ሊያድኑት ወይም ሊበቀሉት አልፈለጉም።

'ታዲያ ኢሕአፓ ከየት አመጣው?' ጭንቅ አለኝ።

ዮሥልቱን ደካማነት በ"ሱፍ አበባዊነት" ጽሑፌ ላይ እንዴት እንደምተነትነው ማብሰልሰል ስጀምር ኢሳያስ ከት ብሎ ስቆ ትኩረቴን ቀለበሰው። በትግርኛ የሚሰማውን መረጃ ትርጉም አንድ በአንድ ይነግረኝ ጀመር። ኢሕአፓ አባላቱን በትግራይ ሽምቅ ተዋጊዎች መካከል አስርጎ አስገብቷል። እነርሱ ያመጡትና በደንብ የተደራጀ የድምጽ መረጃ ነው።የመግቢያ ገለጻውን የሚያደርገው ራሱ መምህር ጸጋይ ነው። ቃል በቃል ተረጎመልኝ...

"የትግራይ ሓርነት ሕዝቢ ግንባር (ተሓሕት) 'የትግራይ ሪፖብሊክን መመስረት' የሚል የፖለቲካ ፕሮግራም ነድፏል። በዚህ ሸከላ አንድ ከፍተኛ የድርጅቱ ካድሬ በጉዳዩ ላይ ከሕዝብ ጋር ያደረገውን ውይይት በተለይም ታላላቅ የአገር ሽማግሌዎች የሚናገሩትን እንሰማለን። አቦይ መረሳ ይባላሉ። አዲግራት አካባቢ የአንድ ገጠር ነዋሪ አዛውንት ናቸው። እሳቸውን ሳስቀድም..." ብሎ መምህር ጸጋይ መቅረጸ-ድምጹን ቀጭጭ አድርጎ ከፈተው።ቁልጭ ብሎ የሚሳማ የወንድ አዛውንት ድምጽ መጣ...

"ጥሩ፤ መቼስ ድርጅታችን መገንጠልን ያለ አንዳች ምክንያት አላቀደችውም። እኛም ይሁን ብለን ተቀብለን። እየቆየን ስናስበው ግን ችግር ገጠመን። ታግለን ታግለን በመጨረሻ ትግራይ ተገነጠለች ብለን እንውሰድ። ከዚያ በኋላ 'ኢትዮጵያ' የሚለውን ሥም ማንኛችን ነን የምንጠራበት? እኛ ወይስ የተውናቸው ሌሎቹ? እኛ እንዳልል ተገንጥለናል። እነርሱ እንዳልል ኢትዮጵያን ሀ ብለን የጀመርናት እኛ ነን። እንግዲህ እኔ ሳወቀው ሰው እንጀራ ጋግሮ፣ ወጥ ሰርቶ፣ ጠላ ጠምቆ...ሌሎች ጎረቤቶቼን ብሉልኝ ጠጡልኝ ማለት የቆየ ባህላችን ነው። አገርን ያህል ነገር ፈጥሮ፣ ባንዲራን አቁሞ፣ ድንበርን አጽንቶ... ሌሎችን እንኩ ውሰዱልኝ ሲባል ግን ሰምቼም አላውቅ..."

ጫጫጫጫጫ!! የሚል ድምጽ ተሰምቶ የመምህር ጸጋይ አጭር ትችት ቀጠለ...

"እነሆ የትግራይ አባቶችና ልጆቻቸው መገንጠልን በሚቃወመው የአዛውንቱ ንግግር እርካታቸውን ለመግለጽ አጨበጨቡ። ተሳህቶች ተደናገጡ። ችግሩ ግን ማን ጽፎ እንዳሰራጨው የሚታወቅ ነገር የለም። አረጋዊ በርሔ ሲጠየቅ ወደ አባይ ፀሐዬ ጣቱን ይቀስራል። አባይ ሲጠየቅ ደግሞ በግልባጩ። መለስ ዜናዊ እንዳይባል ይህንን ያህል ትልቅ የፖሊሲ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የለውም። ሕዝቡ ተቃውሞውን ያሰማው እዚህ ብቻ አይደለም። አንድ የታወቁ የአክሱም ካህን ነገሩን አንድ ስብሰባ ላይ አነሱት። እንሰማቸው......" መምህር ጸጋይ ቴፑን ነካክቶ የአክሱሙን ካህን ድምጽ አመጣው...

"ይሄን ትሓህት ይዛው የመጣችውን 'እንገንጠል' የሚል ነገር በበኩሌ አልወደድኩትም። ሙግት አገጥማለሁ ብዬ ማን እንደጠነሰሰው ለማወቅ ሞክሬ ነበር። የሚነግረኝ አጣሁ። እንዲህ ያለ ነገር የኋላ ኋላ የሚፈጥረውን ችግር በሃይማኖታችን እናውቀዋለን። 'የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናችን ጳጳስ ከግብጽ አገር መምጣት አለበት' የሚል ቀኖና ለብዙ ጊዜ ተተክሎ ኖሯል።" ካህኑ መምህር ጸጋዬ ያልተረጎመው

አንድ አባባል በግእዝ ቋንቋ ተናግረው ቀጠሉ፣ "ጽሑፉ በአራተኛው ክፍለዘመን አከሱም ጳጳሳት ቤተክርስተቲያን መቅደስ ውስጥ ተገኘ። አባቶቻችን ግራ ተጋቡ። ማነው የጻፈውና እዚህ ያስቀመጠው? ብለው ጠየቁ። እኔ ነኝ የሚል ሰው ጠፋ። ሲጨንቃቸው 'ይሄማ ከላይ የወረደ ነው' ብለው ቀኖና አደረጉት። ይሄው 1500ዓመት ሙሉ ግብጽ ድረስ በጉልበታችን ተንበርክከን እየለመን ጳጳስ ስናመጣ ኖርን። የተጻፈ ነገር መዘዙ ብዙ ነው። አሁንም ይሄ 'አንገንጠል' የሚል ጽሑፍ ለትውልድ ሳይተላለፍ በያለበት እንዲቃጠል ይደረግልን..."

ጫ.ጫ.ጫ.ጫ.ጫ.!!

"እ-----ይ...ግራ የተጋባው የኢትዮጵያ ግራ ኃይል እንዴት ያሳዝናል!?" ብዬ ወደ ኢሳያስ ቀና ስል ሸዋዬ ደረጃው ላይ ታየችኝ።

"አላምረው! አላምረው! እንዴ በጣም ትፈለጋለህ!" የምፈለገበትን የፍጥነት ደረጃ በእጆቿም በዐይኖቿም አሳየችኝ።"ምን መጣ?" .. በቅልጥፍና ብድግ ብዬ ተንደረደርኩ፣ 'ቢታኒያ ትሆን የፈለገችኝ?'

"ቤቲ፣ ቢታኒያ...እ...ምራቁ ሳይደርቅ...አሁኑኑ ይምጣ ብላሀለች!" ብላኝ እየተጣደፍኩ አልፌያት ስሄድ ትከሻየን ያዝ አድርጋ አስከበሩ ድረስ ሸኘችኝ።

'ፍቅሬን ምን አደጋ ገጠማት?' አእምሮዬ ርብሽብሽ እንዳለ የሩጫ ያህል እየከነፍኩ ሄድኩ። ቀዩ በር ደርሼ በደመነፍስ አንቅስቃሴ ከፈትኩት። ወደ ቢታኒያ ቤት ሳይ ሙብራት በርቷል። አለች ማለት ነው። ሄጄ ስገባ ከሁለተኛው ከፍል በርግጋ መጣች...

"ሰሙዬ፣ አለህልኝ አይደል?" አንገቴ ላይ ጥምጥም አለች። "አሁን ስልክ ነበረኝ። ደርጎች ዮሴፍ አዳንና ኢንጅነር ዑስማንን አሁን ያዟቸው። አብረህ ትኖራለህ ብዬ ፈርቼ ነበር...በቃ፣ ሆድየ፣ ንቅንቅ እንዳትል..."

"ዩሲ----ፍ አዳ---ነና ኢንጅነ--ር ዑስማ---ን?" ድንጋጤውን መሸከም አቅቶኝ... ራሴን መደገፍ ሲሳነኝ አልጋው ላይ በቁሙቴ ልክ ዘፍ አልኩ።ጉሽትሽት ባለው ዐይነህሊናዬ አንድ ጉልህ ምስል መጥቶ ድቅን አለብኝ። አንድ ቅጠሏ ተገንጥሎ የበረረና ጥርስ-ወላቃ የመሰለች የሱፍ አበባ ተክል! ያሲያዛቸው ሰሞኑን ሹልክ ብሎ ከመሀላችን ጠፍቶ ወደ ደርግ ጎራ የገባው ሻለቃ ሽታዬ ደስታ መሆን አለበት። በሆነ አንዳች ግርግር ሳልተቀዋወቀው ቀርቻለሁ። ብተዋወቀው ኖሮ ይሄኔ የእኔም እጣ ያው ነበር።

የሱፍ አበ-------------ባ መርገፍ ጀመረች!!

# 25

እርብ ምሽት ከማእከላዊ ኮሚቴው ስብሰባ የደረስኩት 2:00 ሰዓት ላይ ነበር። በግምት አንድ ሰዓት ያህል ዘግይቻለሁ። የጎንደር ዞን በይነቀጠና ኮሚቴ ጸሐፊ ከመሸ ነው አዲስ አበባ የገባው። ከአውቶቡስ ተራ ተቀብዬ ወደ ስብሰባው እንዳመጣው ዘርው መድቦኛል። ዘግይቶ ቢደርስም ያለምንም ችግር ተቀብዬ አደረስኩት።የስብሰባው ቦታ በላይ ዘለቀ አካባቢ ነው። በጣም ጽዱና ጸጥ ያለ ቆንጆ ቪላ ቤት። ለእንዲህ ዓይነት ከቅጡ ላለፈ ድርጅታዊ ሕቡዕ ስብሰባ በጣም የተመቼ ነው። "ገቨርዲኒዝም" እንደ ቤቱ ሁሉ ፐዘፎ ታየኝ። ብንታደል ኖሮ እልም ባለ የገጠር ሜካ ዛፍ ሥር ወይም ዋሻ ውስጥ መደረግ የነበረበት ስብሰባ ነው። የቤቱ ባለቤት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አስተማሪ የሆነው እንግሊዛዊው የኢሕአፓ አባል ሞርቶን ነው።

"የውጭ አገር ዜጋ ለዚያውም እንግሊዛዊ የኢሕአፓ አባል? የተለመደ ነገር አይመስለኝም።" ኢሳያስ ሲጠይቀኝ ትዝ ይለኛል።

"አዎ፣ ልክ ነህ ኢሱ፣ ያልተለመደ ነው። ይህ ስሜት የመጣው ግን ይሄ ዘመናዊ መንግሥት የሚሉት ተቋም ዘመናዊ ዜግነትን ይዞ ከመጣ ወዲህ ነው። ቀደም ሲል የዓለም አብዮተኞች የብሔራዊ ድንበር ገደብ አልነበረባቸውም። የ1789ን የፈረንሳይን ቡርዣ አብዮት ከመሩት አብዮተኞች አንዱ ሮብስፒየር በጣም ታዋቂው ነው። በትውልዱ ግን አሜሪካዊ ተራማጅ ነው። ጉዳዩ የአመለካከት ጉዳይ ነው..."

"እውነትከን ነው። እንግሊዛዊ ስለሆነ ብቻ 'ያንኪ' ልንለው አንችልም..." ጭንቅላቱን በአዎንታ ነቀነቀልኝ።

"ሚስተር ሞርተን ኢሕአፓን የተቀላቀለው በቅርብ ጓደኛው በዮሀንስ ብርሀኔ በኩል ነው። ዮሀንስ

ባለፈው አእ ባልተገኘሁበት ምርጫ ማእከላዊ ኮሚቴዉን በአባልነት ተቀላቅሏል። ባለፈው ከዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ጋር ካገኘሁት ወዲህ ተገናኝተን አናውቅም። አሁን ስብሰባው ላይ መኖሩን ያየሁት ዐይኔ ደብ ያለውን ደብዛዛ የኤሌክትሪክ ብርሀን ከተለማመደው በኋላ ነው። ነጣ ያለ ቆብ አድርጎ በብርሃነመስቀልና በጌታቸው ማሩ መካከል ተቀምጧል። ሁሉም ሰው የተቀመጠው በመመገቢያ ከፍሉ ውስጥ ዙሪያውን በተደረደሩ ፕላስቲክ ወንበሮች ላይ ነው። በበሩ በኩል ተስፋይ ደበሳይና ከፍሉ ታደሰ ይታዩኛል። ከእነርሱ በቀኝ በኩል ሁሌ ለይቼ ላውቃት የተቸገርኩባት ሴት አባል አለች። ጉትቻዋ ብልጭ ሲል ብቻ ነው ጾታዋን የምለየው።

'ማን ትሆን ይህች ልጅ? ከወር ምናምን በፊት ቢታኒያ ስትሸኛት በቀዳዳ ያየኋት ትሆን?' መገመት ከበደኝ።

ከብርሃነመስቀል አጠገብ በነበረ ከፍት ወንበር ላይ ተቀመጥኩ። ዮሴፍ አዳነ ያልተገኘበት የመጀመሪያው ስብሰባ ነው። 'ምን ተባብለው ይሆን?' ራሴን ጠይቄ ወዲያው ትኩረቴን ወደ ስብሰባው መለስኩ። አጀንዳው ያው የጠበኩት ነው። የኤርትራው ሕዝባዊ ግንባርና ኢሕአፓ በዶክተር ተስፋዬ በኩል ህዳር ወር ላይ የተፈራረሙት ስምምነት ሕጋዊነት ጥያቄ ነበር። ስብሰባው በተጀመረ ገና በደቂቃዎች ውስጥ ውጥረት የነገሰበት መስሎ ታየኝ።

ተስፋዬ ማእከላዊ ኮሚቴው ሥልጣን ሳይሰጠው ለምን "ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት" ብሎ እንደተፈራረመ በማስረዳት ላይ ነው። ጆሮዎቼንና ዐይኖቼን ወደ እሱ መለስኩ። ቀስ ብሎ በተረጋጋ እንደበት ይናገራል...

"ጆን ሳርቴር 'አለመወሰን በራሱ መወሰን ነው' ይላል። አቋም አለመውሰድ በራሱ አቋም ነው። ኢሕአፓ የኤርትራን ጥያቄ አንድም የቅኝ ግዛት ነው አለያም የብሔር ጥያቄ ነው ብሎ አቋም መያዝ አልቻለም። በዚህም የንጉሡንና የደርግን 'አንዲት ኢትዮጵያ!' መፈክር ተጋርተናል ማለት ነው። በዚህ መቀጠል ግን የምንችል አልመሰለኝም። ይህንን ለመለወጥ ትክክለኛ እርምጃ መውሰዴ ነበር በበኩሌ። ይህንን ያደረኩት ደግሞ ረጅም ውይይት ካደረኩ በኋላ ሦስት አሳማኝ ምክንያቶች ታሳቢ አድርጌ ነው።"

ምክንያቶቹን ለመመዝገብ ይመስላል አብዛኛው ሰው ማስታወሻ ለመያዝ አቀረቀረ።

"አንደኛ፣ ከአስተሳሰብ ዘዴ አንጻር ሲታይ የኤርትራን ጥያቄ ይዘት፣ ስፋትና ጥበቱን የሚወስነው ማነው? ግልጽ ይመስለኛል። ወሳኞቹ ጥያቄውን ያነሱት ኤርትራዉያን ራሳቸው እንጅ እኛ ኢትዮጵያውያን ልንሆን አንችልም። በእነርሱ እምነት 'ዓላማቸው በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ የተፈጠረውን አዲስ ማንነት

"ሰለመለስ' ነው። ይህም ማለት ዘጠኝ ብሔሮች በአንድ ኤርትራ ሥር ያነሱት ጥያቄ ነው። 'በጣሊያን የተፈጠረው ማንነታችን በኢትዮጵያ ተነጠቀ' ነው የሚሉት። ይህ የብሔር ጥያቄ ሳይሆን የቅኝ ግዛት ጥያቄ መሆኑን እቀበላለሁ።"

"ሁለተኛ፣ ጉዳዩ በእነርሱ በኩል ከላይ ያልኩት ከሆነ በእኛ በኩልስ ምን መምሰል አለበት? ደርግና መኢሶን የንጉሡን ፖሊሲ ይዘው ቀጥለዋል። ኢሕአፓስ፣ ለጥያቄው የማያዳግም 'ተራማጅና አብዮታዊ መፍትሄ' የመስጠት ግዴታ አለብን። ይህንን ጥያቄ መቀበልና አዎንታዊ ነው ብሎ ማመን ኤርትራን የመጥቀም፣ ኢትዮጵያን ደግሞ የመጉዳት ጉዳይ አይደለም። ማኅበራዊ ቅራኔዎችን በሙሉ የመፍታት ግዴታ ነው። ተራማጅ ማለትም ከነበረው አሮጌ አስተሳሰብ ነጻ መሆን ማለት ብቻ አይደለም፣ አዲስ የመፍትሄ ሐሳብ ማመንጨትና በድፍረት መጋፈጥም ማለት ነው። ለድርጅታችን የሚያዋጣው መስመር ይህ ነው።"

"ሦስተኛው ምክንያቴ 'ሪል-ፖለቲክ' ወይም ወቅታዊው የፖለቲካ እውነታና ጥቅም ነው። ይሄንን በምንነጋገርበት ወቅት ኢሕአሠ አሲምባ ነው ያለው። ኢሕአሠ ራሱን ማኖር የሚ·ስችለው እንቅስቃሴ እንዲያደርግ ፈቅደንለታል። ይህም ማለት የሻእቢያን ድጋፍ በብዛት ይፈልጋል። እነ ኢሳያስን ሳነጋግራቸው የሰጡኝ መልስ አሳሳቢ ሆነብኝ። 'ዛሬ ጥያቄያችን የቅኝ ግዛት መሆኑን ያልተቀበለ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ደግፈን ነገ ሥልጣን ሲይዝ እንዲወጋን አንፈልግም...' ከእነርሱ አቅጣጫ ሲያየው ትክክል ናቸው። በዚህ ምክንያት ኢሕአሠ ችግር እንዳይገጥመው ስላልፈለኩ ባሉት ሐሳብ ተስማምቻለሁ..." ብሎ አጠቃለለ።

ዘርዑ አጭር ማብራሪያ ሰጥቶ ሐሳብ ይሰጥበት ዘንድ መድረኩን ክፍት አደረገ...

ብርሃነመስቀል የመናገር እድሉን ቀድሞ አገኘ። ፊቱን በተቃውሞ ከስክሶ አድርጎ ተስፋዬን ተነሳበት።

"ሁለት ግልጽ ጥፋቶች ተፈጽመዋል። የመጀመሪያው ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ አንድ ድርጅት ነው። ኤርትራን በሙሉ የሚወክል መንግሥት አድርጎ መውሰድ ትክክል አይደለም። ሻእቢያ ፍላጎቱን ገልጿል። ጥያቄዬ የቅኝ አገዛዝ ጥያቄ ነው ብሏል። ይህንን ጥያቄ ዘጠኙም ብሔሮች እንስተውታል ለማለት የተስፋዬ መረጃ ምንድነው? አንድ በአንድ እየዞረ አነጋግሯቸዋል? ይሄ ከመሆኑ በፊት ቅኝ ግዛትን እንደ ጥያቄ መቀበል አደጋው ለእኛ ብቻ አይደለም። ለሌሎቹ የኤርትራ ብሔሮች ጭምር ነው።ሁለተኛ፣ ዋናው የጥያቄው ባለቤት የኤርትራ ሕዝብ ነው ከተባለ የእኛ ተራማጅ አቋም ምን መሆን አለበት? ቢቃ፣ የኤርትራ ሕዝብ ነጻና ዲሞክራሲያዊ መድረክ ተከፍቶለት በነጻነት ማንነቱን ይወስን! ተስፋዬ የሠራው ግን ከዚህ የሚጋጭ ነው።"

እንደ አደል ሆኖ ወይም ሥር በሰደደ ቁርሾ ምክንያት ብርሃነመስቀል የሚናገረው ሁሉ ለእነ ዘርዑና ከፍሉ ታደሰ አይዋጥላቸውም። አሁን ግን የእነርሱን ድጋፍ አገኘ። "በዚህ ውሳኔ ኢሕአፓ የቆየውን ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት በጸጥታ ተቀብሏል ማለት ነው።" የሚለውና እኔም የደገፍኩት የዶክተር ተስፋዬ መኮንን ውድቅ ተደረገ። ሙሉው ክርክር በቃለ ጉባኤ ተይዞ ተረኛው ጸሐፊ ጸሎተ ሕዝቅያስ በንባብ አሰማን። በሚቀጥለው ስብሰባ ለፊርማ ይቀርባል ተባለና ወደ ሁለተኛው አጀንዳ "የአጥቂና መከላከል" ሥልት ኢላማዎችን ማጽደቅ ተሻገርን።

ዘርዑ ለድርጅታችን ህልውና ቁጥር አንድ አስጊ ናቸው የተባሉ ግለሰቦችን ዝርዝር አቀረበ። እርምጃ የሚወስድባቸው ዝርዝር መሆኑ ነው..

'ደርግ ይሁን መኢሶን...የተኮሰብን ይሆን ጠቋሚ ያስያዘን..የዘረፈን ይሁን የዘለፈን...ከበደ ይሁን አየለ... ማንም ይሁን ማን ግድ የለኝም። ግለሰቦችን በሥም ጠርቶ "እንግደላቸው" የሚለው ይህ ሐሳብ ከጸደቀ "ታላቁ ኢሕአፓ"ትንሹ ሽፍታ ሆነ ማለት ነው። ስህተት ብቻ አይደለም። በሕግ ዐዋቂዎች አነጋገር ኢሕአፓ ተቋማዊ ወንጀል ፈጸመ ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ታላቁን የውድቀት ጉዞ ጀመረው ማለት ነው!' እስከመጨረሻው ልፋለም ቆረጥኩ፤ 'ለፎኮይዝም ፊቴን ፈጽሞ አላሳይም!'

ዘርዑ ወደ ሥም ዝርዝሩ ገባ። ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም፣ ሻምበል ተካ ቱሉ፣ ሻለቃ ጌታቸው ሽበሽ፣ ኃይሌ ፊዳ፣ ፍቅሬ መርእድ፣ ተስፋዬ ታደሰ፣ ዶክተር ከበደ መንገሻ፣ ወይዘሮ ንግሥት አዳነ፣ አብዱላሂ የሱፍ፣ ሰናይ ልኬ፣ መሥፍን ካሡ..። ዘርዝሮ ሲጨርስ ወደ ተሰብሳቢዎች ዞሮ ተመለከተ...

ብርሃነመስቀል ቀድሞኝ በተቃውሞ እጁን አወጣ።

"በበኩሌ ያቀረብከውን የፖሊት ቢሮ 'ፕሮፖዛል' ጨርሶ አልቀበለውም። ለተቃውሞዬ አራት መሠረታዊ ምክንያቶች አሉኝ። አንደኛ፣ ከርእዩተዓለም አንጻር ሐሳቡ ከማርክሳዊ ሌኒናዊ አብዮታዊ የትግል ሥልቶች ያፈነገጠ ብቻ ሳይሆን በቀጥታ የሚጻረር ነው። ሁለተኛ፣ ከፖለቲካ አንጻር ሳየውም የሚያስኬድ አይደለም። የመንግሥት ባለሥልጣናትን በተለይ እንደ ሻለቃ መንግሥቱ ዓይነትን ግራ ኃይል መሪ ሠማይል 'ፑሰሽዚም (መፈንቅለ መንግሥታዊነት) ነው። በዚህ መንገድ ሥልጣን ለመያዝ ታስቦ ከሆነ አደገኛ ስህተት ነው። አካሄዱ ሕዝብን ያላሳተፈ ጸረ-አብዮታዊ ድርጊት በመሆኑ..."

ብርሃነመስቀል ባኮረፈ ሰው ዓይነት አተያይ ድንገት ወደ እኔ አቅጣጫ ዞር ብሎ አየት ካደረገ በኋላ ክርክሩን ቀጠለ...

"ባለፈው ጓድ አላምረው ያቀረበውን ጽሑፍ ላስታውስ። 'ማንኛውም መፈንቅለ መንግሥት ሥር የሰደደ የሌላ ፖለቲካዊ ቀውስ ውጤት ነው። ስለዚህ የችግሩ እንጅ የመፍትሄው አካል የመሆን ተፈጥሯዊ እድል የለውም...' ብሎ ነበር። ያኔ አንድም ሰው ሲቃዎም ትዝ አይለኝም። ተቀብለነዋል ማለት ነው። አሁን ምን አዲስ ነገር ተገኘና ነው ወደ መፈንቅለ መንግስታዊነት የምንገባው? ሦስተኛ፣ አሁንም ጓድ አላምረው ባለፈው 'ገቨርዲኒዝም' ጽሑፉ ላይ አንስቶ መልስ የሰጠበት ጥያቄ አለ። 'ግለሰቦችን የመግደል ግፊት የሚፈጠረው ከየት ነው? አንድም ሕዝባዊ አብዮታዊ ጠርነትን የመምራት ርእዩተዓለማዊ ብቃት ሲጎድል ነው። አለያም ቂም በቀለኝነት የፖለቲካ አስተሳሰብ ሲሆን ነው።' ሙሉ በሙሉ የምቀበለው ሐሳብ ነው_።"

የድምጹ ቅላጼ እየተሳለና እያፈረጠመ ሲመጣ በስብባው ድባብ ላይ ለውጥ የማስከተል እድሉ እየጨመረ መሆኑ ተሰማኝ_

"አራተኛ፣ የሌሎች ኮሚኒስት ድርጅቶች ልምዶች የሚያሳዩን ምንድነው? ግለሰቦችን በመግደል የተሳካ አብዮት ታይቶ አይታወቅም። ከዚህ ሁሉ በኋላ ግን አንድ ጥያቄ ላንሳ። በየትኛውም መንገድ የሚደረግ ወቅታዊ የአገራችን ፖለቲካ ግምገማ በትክክል የሚያሳየን ከመንግሥት ጋር ተባብሮ የመሥራትን ብሔራዊ ኃላፊነትና ግዴታ ነው ወይስ ግለሰቦችን ከጀርባቸው እየተከተሉ መግደልን? ለመሆኑ ሶማሊያ የምታደርገው የወረራ ዝግጅት ኢሕአፓን እያሳሰበውም? አገር ከሌለ አብዮት አለ እንዴ? እየከፋ የመጣው የአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እኛን አይመለከትንም? በዚህ ላይ የበኩላችንን ለማገዝ የሕብረት ግንባር እንዲፈጠር መጫን ሲገባን ሰው መግደልን ምን አመጣው? " ብሎ አጠቃሎ አቀማመጡን አስተካከለ።

ዘርው እንደሁሌው ነው። የብርሃንመስቀል ከርከር አንዳልተመቸው ፊቱ ገጽ ላይ ቁልጭ ብሎ ይነበባል። ምናልባትም የብዙኃኑን ቀልብ ስቦ ሊሆን እንደሚችልም ሳይጠረጥር አልቀረም። የይስሙላ በሚመስል ፈቃደኝነት ተጨማሪ ሐሳብ ስለመኖሩ ጠየቀ። ፈጠን ብዬ እጄን አወጣሁ። እድሉን ሰጠኝ። በ "ሱፍ አበባዊነት" ጽሑፌ መነሻዎች ላይ አተኩሬ የግድያ እቅዱን አምርሬ ተቃወምኩ_

"በበኩሌ ግለሰቦች የፖለቲካን አቅጣጫና ፍጥነት በመወሰን በኩል ሚና የላቸውም የሚል አቋም የለኝም። ነገር ግን ይህ ማለት ከጠቅላላው ሕዝብ ድምር ችሎታ የሚበልጥ ዐቅም አላቸው ማለትም አይደለም። እንደማንኛውም ግለሰብ በጊዜና በቦታ የተገደቡ ፍጡራን ናቸው። ግለሰቦች ታሪክን በማራመድ የራሳቸው ሚና እንዳለቸው ሁሉ ታሪክን ለማዘግየትም ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። ሻለቃ መንግሥቱ ሚናው የትኛው ነው? ብትሉኝ መልሴ አጭር ነው። የታሪክ እርምጃን በማዘግየት ሚና

አመድበዋለሁ። ይሁንና ይህንን ሰው በግድያ የምናስወግደው ለኢሕአፓ ሕልውና አደገኛ ስለሆነ ነው ወይስ የታሪክ እርምጃን የሚያዘገይ ስለሆነ?"

ለአፍታ ቆና ብዬ ተሰብሳቢዎችን አየሁ። ጌታቸው ማሩ ጭንቅላቱን በአዎንታ ሲነቀንቅ ተመለከትኩ። ወኔዬ ግንፍል ብሎ መናገር ቀጠልኩ...

"ሻለቃ መንግሥቱ ለኢሕአፓ አደገኛ ስለሆነ ካላችሁ ይህ አያስኬድም። እዚሁ መሀል ከተማ አደጃፋ-ሥር ቁጭ ብለን አደገኛ ሆነብን ብንል ትርጉሙ ምን ይሆናል? ትርጉሙ 'አዲስ አበባ ለመቀመጥና ግዙፍ ፓርቲ ለማንቀሳቀስ መብት ያለን እኛ ኢሕአፓዎች ብቻ እንጂ ሻለቃ መንግሥቱ አይደለም። ስለዚህ አዲስ አበባን ይልቀቅልን፣ ካልሆነ ግን እንገድለዋለን...' የሚል ይሆናል። 'ሻለቃው የታሪክ እርምጃን ስለሚያዘገይ ነው የምንገድለው' ካላችሁም ይሄም አያስኬድም። የታሪክ እርምጃን ማዘግየት በራሱ ለእኛ አብዮታዊ ሁኔታ ነው። ሕዝቡን አሰባስበን ለሕዝባዊ ጦርነት የምናነሳሳበት አጀንዳ አገኘን ማለት ነው።"

"ከዚህ ውጭ ሰውየውን ብንገድል ያለምንም ጥርጥር በሌላ ታሪክን በሚቀለፍ ግለሰብ ይተካል። እኛ የምንገድለው ሽጉጥና ክላሽን በያዙ ፈቃደኛና አብዮታዊ አባሎቻችን ነው። ሰውየው ቢሳት ወይም ቆስሎ ቢተርፍ ግን አጸፋውን የሚመልስልን በጀት በተመደበለትና መግደል የሙሉ ጊዜ ሥራው በሆነ ታንከኛና እግረኛ ጦር ነው። ሌላው ችግር ምንድነው...እኛ ሕቡዕ ነን፣ የምንገድላቸው ሰዎች ገሀድ ናቸው። ስለዚህ እኛ የምንገድላቸውን ሰዎች እናውቃለን። እነርሱ ግን እኛን ገዳዮቻቸውን አያውቁም። ይህ ምን ማለት ነው? አፍሮ ያበጠረ ወጣት ሁሉ ኢሕአፓ ይሆንና ትውልዱን ለጭፍጨፋ አዘጋጀነው ማለት አይደል? በጣም አደገኛ ስህተት ነው የምንሠራው። መፍትሄ ካላችሁ አንድና አንድ ነው፤ አዲስ አበባን ለቀን ወደ ኢሕአሠ!"

አሁን ብርሃነመስቀልም ሳይደግፈኝ አልቀረም። ዞር ብሎ አይቶኝ በቅንደቦቹ የአዎንታ ምልክት ሰጠኝ። የስብሰባውን መንፈስ በሱፍ አበባዊነት አቅጣጫ መለወጤን ግን እርግጠኛ አይደለሁም።

ዞርው የእኔን መጨረስ ሲያረጋግጥ ሌላ እድል ሰጠ። ጌታቸው ማሩ እጁን አወጣ...

"እኔ የጓድ አላምረው ሐሳብ በከፊልና የጓድ ረዘነ ሐሳብ የወቅቱን የአገራችንን ሁኔታ በትክክል የሚገልጽ ይመስለኛል። እንዲያውም እኔ ከመከላከልና ከመግደል እርምጃው ይልቅ የሕብረት ግንባሩን እንደ ደህንነት ዋስትና እመለከተዋለሁ። ግለሰብን ከሕዝብ በላይ ዐይቶ እንግደል ማለት በበኩሌ ግልጽ ፎኮይዝም ነው..."

ዘርው የተበሳጨ ይመስላል። በደምፍላት ጌታቸውን ገለማመምጠት ሲያበቃ አቋርጦት ጥያቄ አነሳለት፣ "ምንድነው እያልክ ያለኸው? በፖለቲካ ቢሮው ድምጽ ሲሰጥበት ደግፈኸ አይደለም እንዴ በሙሉ ድምጽ የጸደቀው? ያኔ ለምን ተቃውመህ ከርክር አላደርክም?" አፈጠጠበት።

ጌታቸው ጠይም ፊቱ ልውጥውጥ አለ። ሲቆጣ ሁሌ እንደሚሆነው አፍንጫው ሜፍ ላይ የላብ እንክብሎች ፍስስ አሉ፣ "ማ፣ እኔ? በጭራሽ 'እንግደል' የሚል ሐሳብ ደግፌ አልተናገርኩም፣ አልተከራከርኩም፣ ድምጽም አልሰጠሁም። በ'ፎኮይዝም' እምኔ አ...ቅም..." ድምጹን የበለጠ ከረር አድርጎ ተጽእኖ ለመፍጠር ሞከረ።

"እንዴዴ? ምን ነካህ? ቃለ-ጉባኤው'ኮ አሁን ሁሉንም እልያገዙትም አንድ ከ'ኔ ጋር አለ። አንድም የድምጽ ልዩነት ሳይኖር ነው የጸደቀው..."

ከፍሉ ታደሰ ጌታቸውን በመቃወም ጣልቃ ገብቶ ከነቀፈው በኋላ በቢጫ ከላስር የተያዘ ትልቅ ፋይል ከአጠገቡ አንስቶ ገጾችን እየገላለጠ መበርበር ጀመረ። የሁላችንም ትኩረት ቃለ ጉባኤው ላይ ሆነ...

"በጭራሽ!" ጌታቸው የመናገር እድል ሳይጠይቅ በስሜት ጮኸ፣ "ጥሩ፣ ቃለጉባኤው ይምጣና ይታይ! አሁን ግን የጀመርኩትን ሐሳብ ልጨርስ። 'ቼርማን' እድሉን ለእኔ ስለሰጠ'ኸኝ ልቀጥል..." ሌላ ድምጽ አቋረጠው።

"እዚህ እኔ ሐሳብ አለኝ፣ በ'ፕሮሲጀር ላይ..." ሳሙኤል ብርሀኔ ጣልቃ ገብቶ እድል እንዲሰጠው ሲጠይቅ ዘርው ፈቀደለት።

"በፖ'ሊቲካ ቢሮው አባላት መካከል እንዲህ ዓይነት ልዩነት ካለ ለማእከላዊ ኮሚቴው ከርክርና የውሳኔ አሰጣጥ ጥሩ አይሆንም። ቃለጉባኤው በሙሉ ወይም በከፊል ካለ መታየት አለበት። የጓዱ ልዩነት ምን እንደነበረ ወይም እዛ ደግፎ መጥቶ እዚህ አቋሙን ለምን እንደለወጠ አጣርተን ነው መቀጠል ያለብን። እዚህ የተሰበሰብነው ፖሊት ቢሮው የወሰነውን ለማጽደቅ ወይም ለመሻር ነው። እንጂ የሐሳብ ልዩነቶችን አዳምጠን ፍርድ ለመስጠት አይመስለኝም..."

ዘርው "ቃለጉባኤው ይታይ" የሚለው ሐሳብ በግሉ የሳበውን ያህል የሁሉም ስምምነት እንደነበረ ከሁኔታው ሳይገነዘብ አልቀረም። ለውሳኔ ሲያቀርበው እንደተጠበቀው የሁላችንም ፍላጎት ሆኖ አገኘው። ወረቀት ፍሊጋው ቀጠለ...

ዮሀንስ ብርሀኔ ወደ ሌላ ክፍል ገብቶ በራድ የሚያክል የእጅ ባትሪ አመጣ። ቃለጉባኤውን የያዘው ክፍሉ ታደሰ ቢጫውን ከላስር መሬት ላይ አስቀምጦታል። ሲቷ አባል፣ ዮሀንስ፣ ፍስሀ ገብርሚካኤልና ክፍሉ ተዘራ ክብብ አድርገውት ብርበራውን ቀጠለ። "በዚህ ቀን ፈልገው...በአጀንዳ ቅደም ተከተል ብትፈልገው ይሻላል...ኖኖ በወሩ ብትፈልገው ይቀላል..." ሲባባሉ ክፍሉ ዝምብሎ አቀርቅሮ ገጾችን መገልበጥ ቀጠለ። ሌሎቻችን ተመልካች ብቻ ሆነን በጸጥታ እንመለከታለን።

በግምት ከግማሽ ሰዓት በኋላ ቃለጉባኤው ተገኘ። ክፍሉ መዘዝ አድርጎ ሲያወጣው ዘርው ስብሰባውን እንደገና አስጀምሮ "ወደ ውሳኔ ገጽ ሄደህ አንብበው!" አለው። ገጹን ሲያገኘው ክፍሉ በባትሪው ብርሀን እየታገዘ መዞ አወጣው። ጌታቸው ማሩ በራሱ እጅ የጻፈውንና በኮድ ስሙ የፈረበመትን አጭር ቃል ለራሱ ጭምር እያሳየ አነበበው...

"የተዘጋጀው የሥም ዝርዝር ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል። እኔም ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲደረግ የገለጽኩ ሲሆን የተዘጋጀው ዝርዝር 'እያጠቁ መከላከል' ከሚለው አዲሱ ሥልት ጋር የሚጣጣም መሆኑን አምኘበታለሁ። ፊርማ የማይነበብ..."

ሊጽፍ ያሰበውና የጻፈው እንደተጋጩበት ገብቶኛል። ያም ሆነ ይህ ጌታቸው ማሩ ተረታ...

ሁኔታው ግራ መጋባትም ግርምትም መፍጠሩ አልቀረም። በተለይ በዘርውና በአውቶማቲክ ተቀናቃኙ በብርሃነመስቀል አእምሮ ውስጥ ሊፈጠር የሚችል የተለየ ስሜት መኖሩ አያጠራጥርም። ለመገመት ሞከርኩ። ዘርው የፖሊት ቢሮውን ትክክለኛነትና የጌታቸው ማሩን የአቋም መዋዠቅ ችግር ማእከላዊ ኮሚቴው በሚገባ አስተውሎታል ብሎ ዐስቦ ይሆናል። በመሆኑም በሌሎቹ ላይ ምናልባት ተፈጥሮ ሊሆን የሚችለው ጥርጣሬ ተወግዷል ብሎ ያምናል። ብርሃነመስቀል በበኩሉ ጌታቸው በግድያው ተስማምቶ ከመጣ በኋላ በእሱ ክርክር ተመስጦ አቋሙን እንደቀየረ ሊያስብ ይችላል። የትኛው ግምቴ ትክክል እንደሆነ ለማየት ጓጓሁ። ነገር ግን ፈጽሞ ደስ ያላለኝ ብቻ ሳይሆን ቅሬታዬ እየጠለቀ የሄደበት ገመድ ጉተታ ነበር።

ዘርው ወደ መድረኩ ተመለሰ። ነገር ግን ሌሊቱ በመንጋቱ ስብሰባው አበቃ። ምግብ ነገር ቀማምሰን እስከ እኩለ ቀን ድረስ ከተኛን በኋላ ተመልሰን ልንቀጥል ተስማምተን ስብሰባው ተዘጋ። ኢጋጣሚ ካገናኘኝ ከጌታቸው ማሩ ጋር አንድ ፍራሽ ተጋርተን ተኛን። ሁለታችንም ደክመናል፣ የወሬ ፍላጎት አልነበረንም። ጎኔ ገና ፍራሹን ሲነካ የኖሕ እንቅልፍ ይዞኝ ጥርግ አለ...

***

በማግስቱ የተዘጋጀልንን ግሩም ሽሮና ድንች ወጥ ምሳ በልተን ስብሰባውን እንደገና ጀመርን። አቀማመጣችን ከሞላ ጎደል የትላንተናው ነው። የስብሰባው ክፍል በቢሮ መጋረጃ ሸፍንፍን ብሎ ብርሀኑ ደብዝዟል። ብቸኛዋ የሴት አባል በቀኝ ማእዘን በኩል ተቀምጣለች። ብቻዋን አንድ ክፍል ውስጥ ስላደረች በደንብ አላየኋትም። አሁንም የዘርዑ ወፍራም ረጅም አካል ስለከለላት በደንብ አትታየኝም። ትኩረቴን ወደ ስብሰባው አደረኩ።

ክርክር እስከሚጋጋል ድረስ ብዙዎቻችን በተደበተ ስሜት ውስጥ መቆየታችን የተለመደ ነው። አብዛኛው ሰው አሁንም እያዛጋ መንጠራራት…ማፏሸክ…አይኑን ዘጠኝ ጊዜ ማሻሸት…ቁንጥንጥ ማለት ይታይበታል። በጣም የገረመኝ አንድ ከስተት ቢኖር ብርሃነመስቀል ከእንደዚህ ዓይነት ስሜት ፈጽሞ ነጻ መሆኑ ነው። 'እንተኛ' ወይም 'እረፍት አድርገን እንመለስ' ሲል አንድም ጊዜ ሰምቼው አላውቅም። ስብሰባው ውሎ ቢያድር ከወንበሩ ንቅንቅ አይልም።

"ኢሱ፣ ምን ዓይነት ጽናት ነው 'ባከህ?"

"ብርሃነ ሌላ ሕይወት የለውም። መላ ትኩረቱ ኢሕአፓ፣ ስብሰባውና ክርክሩ ነው፣ ወዳጄ!"

ለነገሩ እንዴት እንዲህ አይሆን! እንደቂጣ በእጁ ጠፍጥፎ የፈጠረው ድርጅት ዛሬ ከእጁ ወጥቷል። በሌላ በኩል ኢሕአፓ ዛሬ እሱ ሲፈጥረው የነበረው ድርጅት አይደለም። እንደ ተራራ የዘፈ የሰው ማእበል ሆኗል። የእያሌ ንብረት ባለቤትና የመጭው ጊዜ ባለራእይ ባቡር መሆን ችሏል። ነገር ግን ይህ ቧቡር ሐዲዱን ለቅቄ ካልወጣሁ ብሎ እየተገለገለ ነው። በዚህ አጅግ ፈታኝ ጊዜ የባቡሩ የመጀመሪያ ጠቅላይ አርኪቴክት ብርሃነመስቀል በመሪ ቦታ ላይ የለም። በቁጭት ቁጭ ብሎ ይመለከታል።

'ም----ስ---ኪ----ን! የመጀመሪያው የኢሕአፓ ኩነኔ ሰለባ!' በልቤ አዘንኩለት።

ብርሃነመስቀል እንዴ በሕገ ደንብና በአሠራር፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በንድፈሐሳብ ብልጫ የቀድሞ ተፈላጊነቱን ለማስመለስ ሲሞክር በትክክል ታዝቤያለሁ። ነገር ግን እንኳን ሊሳካለት እንዲያውም በየቀኑ ወደ ድንበር እየተገፋ ነው። ዘርዑ፣ ዶክተር ተስፋዬና ክፍሉ ታደሰ በተለይ ለእሱ የሚራራ አንጀት የላቸውም። ሌሎቻችን ጭምር ሳይታወቀን በስጋት እንድንመለከተው አሉታዊ የሥነልቦና ጫና ሳያደርጉብን አልቀሩም። በበኩሌ መቼም ጊዜ የኢሕአፓ ዋና ጸሐፊ ሆኖ ሲመራን አይታየኝም። በዚህ ላይ እሱም ራሱ ከወፋፍራም ስህተቶች ሊያመልጥ አለመቻሉን አምናለሁ። ከ 'ገሸርዲኒዝም' ደራሲያን ግንባር ቀደሙ አድጌዋለሁ ።

ኧረ ምን ይሄ ብቻ! ብዙ ታሪካዊ ሊባል የሚችል ስህተትም ሰርቷል እንጂ_' ቅሬታዬ መልሶ አገረሸ።

ብርሃነመስቀል በአጓጉል ትምኒታዊነት ወይም "ብላይንድ አፕቲሚዝም" እየተመራ የደርግን ትክክለኛ ተፈጥሮ በማድበስበሱ በአመራሩ መካከል ጥርጣሬ አጭሯል። አሊምባ በቆየበት ጊዜም ከዚህ ወንጀል አላመለጠም። "እርፋችሁ ተቀመጡ!" በሚል መመሪያ እግር ከወርች አስሮ የኢሕአሠን የጦርነት መንፈስ ሽባ አድርጎታል። የሠራዊቱን ሥነ ልቦና "ሪትሪት" በሚል ማእከላዊ አስተሳሰብ ገርቶ አብዮታዊ ግለቱንና ቁርጠኝነቱን አሽመድምዶታል። ከደርግና ከመኢሶን ጋር አንድ ስምምነት ላይ ይደረስ ይሆናል በሚል ላም አለኝ በሰማይ ዓይነት ሞኛ ሞኝ እምነቱ ኢሕአሠን ለውጊያ ሳይሆን ወንጌል ለመስበክ የተሰማራ የሚሽነሪዎች ጓድ እንዲመስል አድርጎታል_

'እሉ——-ጫ!' ብልጭ አለብኝ።ከንዴቴ ለመውጣት ጭምር እንደገና ወደ ተጀመረው ክርክር ትኩረቴን መለስኩ። ጸሎተ ሕዝቅያስ የመናገር እድል ተሰጥቶት አስተያየት መስጠት ጀመረ_

"በ 'አጥቅቶ መከላከል' ሥልታችን አርምጃ እንዲወሰድባቸው የተመረጡት ሰዎች ለድርጅታችን ሕልውና አደገኛ መሆናቸውን እቀበላለሁ። ይህ ከሆነ መወገድ አለባቸው በሚለውም 'ፕሮፖዛል' ላይ ብዙ ችግር የለብኝም። 'ሎጅካል' ነው። ነገር ግን ጓድ ረዘነ (ብርሃነመስቀል) ያነሳውና የሚያሳስበኝ ነጥብ ደግሞ አለ። ለሰላማዊ ትግል ድርጅታችን ያለው ጽናትና ለሕብረት ግንባር ጥሪው ያሳየው ቀና ፍላጎት በቂ ነው ብዬ አላስብም። ወደ እርምጃ ከመግባታችን በፊት ለዚህ ፍላጎታችን አንድ የመጨረሻ እድል መስጠት ይኖርብናል..." አለ።

ዘርዑ የመናገር እድሉን ለሌላ ሰው ከመስጠቱ በፊት አንድ ማሳሰቢያ ሰጠ_

"ጓዶች፤ ሐሳብ ስትሰጡ አንድ ነገር አትርሱ። ለሰላማዊ ትግልና ለሕብረት ግንባር ኢሕአፓ በቂ ጥረት አላደረገም ካላችሁ ያላደረግናቸውን ጥረቶች አብራችሁ ብትጠቅሱልን ይጠቅመናል።" ብሎ የሚቀጥለውን እድል ለጌታቸው ማሩ ሰጠው።

"አዎ፤ ያልተጠቀምንባቸው ብዙ እድሎች አሉ። ለምሳሌ፤ እንዲያውም ትልቁና ዋናው እድል ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ኢሕአፓን ለማነጋገር ፍላጎት እንዳለው አረጋግጫለሁ። ይሄን በማንኛውም መስመር በኩል አጣርታችሁ ልትደርሱበት ትችላላችሁ። የመነጋገሪያ ፕሮሲጀሩ ላይ ከተስማማን እሱ ለውይይት ዝግጁ ነዉ!" በጋለ ስሜት ተናገረ።

'የምን ተዐምር ነው የሚያወራው? ወይስ እየቃገሩ?' በሆዴ ያልኩትን ግርምት በእርግጠኝነት ሁሉም

ፊት ላይ ቁልጭ ብሎ ተጽፎ አየሁት። እርስ በእርሳችን ለበርካታ ሴኮንዶች በዝምታ ተያየን። 'በትክክል ምንድነው የሰማነው ነገር?'

"ከየት ነው መረጃውን ያገኘሽው?" ዘርው በመገረም እያየው ጌታቸውን ጠየቀው።

"ከደርግ አባሉ ወንድሜ ነው። ከፈለጋችሁ በማንኛውም ዘዴ ማጣራት ትችላላችሁ።" ፊርጠም አለ።

እንደገና የጸጥታ ደመና መጥቶ ቤቱን ልብ----ስ አደረገው። ጸጥታው የተገሰሰው ብርሃነመስቀል ተፈቅዶላት መናገር ሲጀምር ነው። ሁኔታው ልውጥውጥ ብሎ በድል አድርጊነት መንፈስ አንድ ውሳኔ እንዲተላለፍ አበክሮ ጠየቀ።

ዘርው ምንም ማድረግ የቻለ አይመስልም። ጉዳዩን የሚያጣራና ካስፈለገ ከሻለቃ መንግሥቱ ጋር የሚገናኝ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ልዑክ እንዲሰየም በቀረበው ሐሳብ ተስማማ። ፍስሀ ገብረሚካኤልና ኢሳያስ ተመረጡ። ቀጥሎ ውይይቱ በሚደረግበት ሥነሥርዓትና መሳካት አለመሳካቱ በሚመዘንበት ጉዳይ ላይ የጦፈ ክርክር ተጀመረ። በበኩሌ ቅልጥ ያለ ኮሜዲ ድራማ የምመለከት ነው የመሰለኝ። "እንግደል" የሚሉት የገናን በዓል ጠብቀው በእንቁር ጨዋታ ጊዜ የሚደባደቡ ጎረምሶች መሰሉኝ። "እንወያይ" የሚሉት ደግሞ ከጉድጓዳቸው ወጥተው ከድመት ጋር ለመታረቅ ጉዞ የጀመሩ አይጦች መስለው ታዩኝ። ሁለቱም በየራሳቸው ከልል በፀሐይ ላይ ያመጹትውንና አንድ ቅጠሏ የበረረውን የሱፍ አበባ መንገድ መያዛቸውን ማሳመን አልቻልኩም።

'የሱ-----------ፍ አ-----በ-----ባ! መጨረሻሽ ምን ይሆን?'

እዚህ ነጥብ ላይ ስደርስ ፍላጎቴ ጠፍቶ አእምሮዬ ከሁዲዱ ወጣ። ቢታኒያ በዐይኖቼ ላይ ው--ል አለችብኝ። የመጨረሻው ውሳኔ ሲወሰን ብቻ ነቃ አልኩ። "አጥቅቶ መከላከል" ሥቲቱ ኢላማ ያደረጋቸው ሰዎች ዝርዝር በመርሕ ጸድቋል። ለተፈጻሚነቱ ፍሰሐ ገብረሚካኤል ከሻለቃ መንግሥቱ ጋር ተነጋግሮ የሚያመጣው ሪፖርት ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ይሆናል። ፍስሀ ሻለቃውን እንደማያገኛቸው ልቤ ያውቃል። "ሊያነጋግሩኝ አልፈቀዱም" ወይም "ላገኛቸው አልቻልኩም" የሚል መልስ ይዞ ይመጣል። በማግስቱ ኢሕአፓ ግድያ ይጀምራል...

'ታ---ላ---ቁ ስ---ሀ---ተ--------------ት! ሁለተኛ-----ው ኩነ----ኔ'

በሆዴ እ-እ-እ... ብዬ ሞኸኩ። የኖሕ የጥፋት ውኃ እንደገና አራት ሺህ ዓመታት ቢዘንብ...የእየሱስ

ክርስቶስ ምጽዐት ቢታዎጅ...የአርማጌዲዮን ውጊያ የሚያፈሰው የደም ጎርፍ ፈጥሮ ቢጎርፍ...ቀይ ባሕር ወንዝ ሆኖ ቢፈስ...ፈጽሞ ሊያጸዳው የማይችለው ታላቁ ስህተት ተፈጸመ። ኡኡኡ...! ልቤ ከሁለት ተከፍሎ ስብሰባውን ቀጠልኩ። አጭር የሂስና የግለ ሂስ ፕሮግራም ተከፈተ። ግለሂስ ሲባል ብርሃነመስቀል የመጀመሪያ ሆነ። ያልተለመደ በመሆኑ ሁላችንም ምን እንደሚያወራ ለመስማት በግራ መጋባት እንጠብቀዋለን።

"ከሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር ኢሕአፓ የሚደራደርበት ሁኔታ መፈጠሩ አስደስቶኛል። ድርጅታችን አብዮቱን በመምራት በኩል የራሱን ድርሻ ለመወጣት እድል አግኝቷል ብዬ አምናለሁ። እዚህ ደረጃ ለመድረስ የሄድንባቸው መንገዶች ነበሩ። አንዳንዶቹ በትክክለኛውና ሕጋዊው መስመር የተካሄዱ ናቸው። በተቃራኒው የተሄደበት ጊዜም አለ። በዚህ በኩል መጋቢት ወር ላይ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጣውን የሕብረት ግንባር ጥሪ የሚደግፍ ርእሰ አንቀጽ እንዲታተም ያደረኩት እኔ ነኝ። ለድርጅቴ ጥቅም ብዬ ያደረኩት ቢሆንም ከመስመር በመውጣቴ ስህተት ሠርቻለሁ።"

ለእኔ አዲስ አይደለም። ለሌሎቹ ግን ሌላ እንቆቅልሽ...ሌላ ግራ መገባት...ሌላ ቅኔ...ሌላ ሰምና ወርቅ! ብርሃነመስቀል ምን ነካው? ዘርዑን አፍጥጩ ሳየው እሱም አየኝ። የነገሩን ሥር ማየትም መያዝም አቅቶታል! ከዚህ አዚም መሰል ድብት የገላገለን ሳሙኤል ብርሀኔ ነው።

"ጥያቄ አለኝ፣ 'ቼርማን'" ሲል ዘርዑ ፈቀደለት፣ "ብርሃነመስቀል ይሄንን ማድረግህን ለፖለቲካ ቢሮው አሳውቀሀል? ፖለቲካ ቢሮው ዐውቆ ከሆነስ ለእኛ ያልገለጸልን ለምንድነው?"

ዘርዑ ለሁለተኛው ጥያቄ ቅንድቡን ከስክስ አድርጎ መልስ ከሰጠ በኋላ ሌላ ጥያቄ አነሳ፣ "የፖለቲካ ቢሮው የሚያውቀው ነገር የለም። ጓድ ረዘነ ይህንን ለምን እንዳላደረከ ልታስረዳን ይገባል።" ብርሐነስቀልን ትኩር ብሎ ተመለከተው።

"አሳውቄያለሁ። የውጭ ኮሚቴውንና የማእከላዊ ኮሚቴውን ከፖለቲካ ቢሮው ጋር ለሚያገናኘው ጓድ ጌታቸው ማሩ ነግሬዋለሁ፣ ጽሑፉንም ሰጥቼዋለሁ..." ሲል ጌታቸው ቱግ ብሎ አቋረጠው።

"መቼ ነው የሰጠኸኝ? እኔ ምንም የማውቀው ነገር የለም!" የሰሁብትም በሚል መልእክት እጆቹን ብድግ አደረገ።

"የማውቀው ነገር የለም ነው የምትለው?" ብርሃነመስቀል በመጨረሻው ንዴት ከመቅጽበት ደም የለበሱ ዐይኖቹን እንደ ተቆጣ ነብር አፍጥጦ ሸቅብ እያየው፣ "ጨሽ—ታም! ቀጣ—ፊ!!" በጩኸት አጓራበት።

"ውሸታምማ ራስህ ነህ_" ጌታቸው አጸፋውን መለሰ።

ብርሃንመስቀል ራሱን መቆጣጠር አልቻለም። ከወንበሩ ተወርውሮ ብድግ አለ። እጆቹን በፍጹም ደመፍላቱ እንቅስቃሴ በምህንስ ብርሃኔ ጭንቅላት ላይ አወናጭፎ የጌታቸውን አንገት አንቆ አደረገው። የህንስ መንገል አልቻለም። ጌታቸው አንገቱን ለማስለቀቅ ባለ በሌለ ጉልበቱ ሲፍጨረጨር ብርሃንመስቀል ወደ ፊትና ወደ ኋላ ወዘወዘው። ዘርዐ ሄዶ እጁን ሲይዘው "ውሸታ—ም" ብሎ ጮኾ ለቀቀው። ጌታቸው በተራው አጸፋውን ሊመልስ ሲል እሱንም ያዘው_

እእእ—ውኡ! ታላቁ_ቀዳሚው_ግዙፉ_ግራውና ግንባር ቀደሙ ኢትእጋ ሆይ! ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም! ነብዩ ዳዊት በመስኮት በኩል ብቅ ብሎ የተናገረ መሰለኝ።

ከሳምንት በኋላ ሐሙስ ምሽት ልንገናኝ ተወስኖ ስብሰባው አበቃ።

***

ሐሙስ ምሽት ከስብሰባው ቦታ የደረስኩት ልክ በሰዓቱ ነው። ዛሬ ኢሳያስም አብሮኝ አለ። በሐዘኑ ምክንያት በቤተሰብ ተጽእኖ ይመስለኛል ጥቁር ቆብ አድርጓል። ግቢው ውስጥ ስንገባ ቀድመን ያየነው ከፍሉ ታደሰን ነው። በረንዳው ላይ በነጠላ ጫማ ቁጭ ብሎ ሲጋራ ያጤሳል። በሐሳብ እልም ብሎ ጠፍቶ መሬት ላይ አቀርቅሯል። የሚወደውን ዘመድ አስከሬን ቤት ውስጥ አስቀምጦ የሩቅ ዘመዶቹ እስከሚደርሱለት የሚጠብቅ ሐዘንተኛ ይመስላል። እንዴ ብቻ ቀና ብሎ ዐይቶን መልሶ አቀረቀረ_

"ምን ተፈጠረ?" ከኢሳያስ ጋር በጭንቀት ተያየን። መኪናዋን ቦታ አስይዤ ስመለስ ኢሳያስም ከከፍሉ የበለጠ ደንግጦ በትካዜ ቆሟል። ሲጋት ገባኝ። ሄጄ ስቀላቀል ምን እንደተፈጠረ እየተጣደፍኩ ጠየኩት_

"ፍስሀ ገብረሚካኤል በደርግ እጅ ወደቀ"

# 26

እኔና ኢሳያስ ጋራዡን ለቀን የትም ንቅንቅ እንዳንል በዘርዑ ከህሸን ታዘናል። እጅግ ጥብቅ ትእዛዝ ነው። ለምሳ እንኳን አልወጣንም። እዛው ቁጭ እንዳልን ቢታኒያ በሚካኤለ በኩል የላከችልንን ምሳ በላን። ከሰዓት በኋላ ዶክተር ተስፋዬ ስልክ ደወለና በኮድ የተመሰጠረ ትእዛዝ አስተላለፈልን...

"ሁለት የመኪና ሰሌዳዎች በግል መኪና ኮድና ቀለም በአስቸኳይ እንዲዘጋጁ። ሁለት ፒከ አፕ መኪናዎች ይመጣሉ፤ ታርጋው እንዲገጠምላቸው። የፊትና የኋላ የፍሬቻ መብራቶች አምፑሎቻቸው በአረንጓዴ ቀለም እንዲቀቡ። ቶዮታ ሐይሉከሷ ሸራ እንድትለብስ። ያረጁ ወይም ብዙ ያገለገሉ ጎማዎች በአዲስ እንዲተኩ..."

ትዕዛዙን ለመፈፀም መረባረብ ጀመርን። ጎይቶም ለባሲና አምስት ጓደኞቹ ቁራ አካባቢ ወደሌላ ጋራዥ ከተዛወሩ ሳምንት ሆኗቸዋል። በጎይቶም ምትክ ሌላ ጀማል የሚባል ኤርትራዊ ልጅ እንዲሠራ አድርጌያለሁ። ችግሩ ጀማል አረብኛ እንጂ አማርኛ በደንብ አይችልም። በዚህ ላይ በጣም ዝምተኛ ነው። ትእዛዙን ለመፈጸም ታዲያ የእቃ ግዥ ያስፈልጋል። ጀማል መሥራት የሚቻለውን ሁሉ ከሁለት ጓደኞቹ ጋር በመሆን መሥራት ጀመረ።

ኢሳያስን አንድ ሽህ ብር ሰጥቼው መርካቶ ሄደ። እስካሁን አንደኛዋ መኪና ብቻ ናት መጥታ እየተሠራች ያለችው። ባጋጣሚ ከመኢሶኖች መኪና አጠገብ ቆማለች። ብዙ ጊዜ ዶክተር ተስፋዬ የሚይዛት አዲስ ጃፓን ሰራሽ ቶዮታ ፒከ አፕ ናት። ሁለተኛዋ ስትመጣ ዛሬና ነገ ሙሉ ሥራችን ይሄው እንደሚሆን

ዐውቃያለሁ።

"ይሄ ሁሉ ጥድፊያ ምንድነው?" ደጀኔ ተለይቶኝ ወደ ምድር ቤታችን ሲሄድ እንደቀልድ ጠየኩት።

"እኔ እንጃ...ለእኔ የነገሩኝ ነገር የለም። ምናልባት ከፍለሀገር ይሄዱ ይሆናል።" ብሎኝ በምሥጢራዊዋ መንገድ አለፈ።

###

ዘመን መለወጫ በዋለ በአራተኛው ቀን ምሽት ላይ ይመስለኛል። ዘርዑ ከህሸን ለአስቸኳይ ተልእኮ ጠርቶኝ ጉለሌ ሄጄ ነበር። የማላወቃቸው ሁለት እንግዳ ሰዎችን ከሰበታ አምጥቼ መሿለኪያ የሆነ ቤት እንዳደረሳቸው ነገረኝ። ተልእኮዬን ጨርሼ ሦስት ሰዓት ላይ ተመልሼ ጋራዥ ደረስኩ። ምን እንደገፋፋኝ አላውቅም! ወደ ምድር ቤቴ መሄድ ትቼ በቀጥታ ወደ ቢታኒያ አመራሁ። የቤቷን በር ከፍቼ ስገባ ያልጠበኩት ነገር ገጠመኝ...

ልብስ ስትቀይር አገኘኋት። ገና ወደቤት መግባቷ ነበር። እንደዚህ አምሽታ ስትገባ አጋጥሞኝ አያውቅም። ድከ—ም ብሏታል። የቀኝ እጇን ጣቶች በፋሻ ጨርቅ አሥራቸዋለች። የሆነ ነገር ልትዋሸኝ እንደፈለገች ከንፈሯ ቅልብልብ ሲሉ ገመትኩ...

"ምናባህ ታፈጥብኛለህ? የት ቆይቼ የመጣሁ መስሎህ ነው? ይልቅ ሰሙዬ! ነጠላ ጫማዬንና ቢጃማዬን አቀብለኝ..." በይሉኝታ ሳቅና በቀልድ መካከል ሆና ርብትብት አለች።

"ቤቲ! ይህ ምሽት የመጨረሻ መተያያችን እንዳይሆን ከፈለግሽ የት ልከውሽ፣ ምን አድርገሽ እንደመጣሽ ልትነግሪኝ ይገባል!" መላ ሰውነቴ እንደ ምጣድ ከመቅጽበት ጋለ!...ከንፈሮቼ አምልጠውኝ የሚወድቁ እስኪመስለኝ ድረስ ተንዘፈዘፉ።

"ኪድ እዛ! ሞርገ! ማን እባቱ ነው ቢታኒያን እንደ አሽከር ብድግ ብሎ የሚልካት!? ዓላማረብህም፣ ይልቅ ዝምብለህ ጫማዬን አምጣልኝ!" በውሸት ቁጣ ግልምጥምጥ አደረገችኝ።

አላመንኳትም፤ እኔም በቀላሉ አለቀኳትምም። ነገር ግን የፈጠርኩት ነገር የለም። ዓይኔን ግንባር ያርገው! ብላ ቀረች።

###

ከትላንትና ወዲያ ምሽት የኢሕአፓ ታጣቂ አሀዶች የሰንዳፋን ፖሊስ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት የመሣሪያ ግምጃ ቤት ባዶውን አስቀሩት።በእኛ በኩል የተሰዋ አለመኖሩ ደስ ብሎናል። በመንግሥት በኩል አንድ ሀምሳ አለቃ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ይዘው ገድለውታል። ዘመቻው የተሳካ ቢሆንም በበኩሌ ጠብ የሚል ኩራት አልተሰማኝም። ሁሉም ነገር የተፈጸመው በኩዩባ ምንካዳ ዓይነት የጀግንነት ገድል አይደለም። እልም ባለ አሻጥር ነው። ማሰልጠኛው ውስጥ በነበሩ አባሎቻችን ሙሉ ድጋፍ የተፈጸመ ነው።

"ኢሱ፤ እኔ ይሄንን ነገር ኢሕአሠ ቢያደርገው ኖሮ ወገቤን አሸርቅጬ እስክስታ በወረድኩ ነበር። ያ አለመሆኑ ስኬታችንን ከዘመቻ ይልቅ በር ሰብሮ የመግባት ተራ ዘረፋ አስመሰለብኝ።"

"ይሁን፤ ግዴለም። የጠላትን ዐቅም በአንዲትም ጥይት እስካዳከመ ድረስ እንቀበለው። እኔን ያሳሰበኝ ግን ይሄ ሁሉ መሣሪያ ለከተማ ውጊያ ያዘጋጁት አንጂ አሲምባ የሚሄድ አለመሆኑ ነው። ተመልሶ ሲማረክ እንጅ ስንገድልበት አይታየኝም።"

የኢሳያስ መልስ አዲስ ስጋት ለቀቀብኝ። ስጋቴ ግን 'ይሄ በከፉ ቀን የገዛሁት ጋሻ እንዳያስገድለኝ አንጂ...' ያለው ፈሪ ዓይነት ፍርሀት አይደለም። በርእዩተዓለማዊ ትንተና ላይ የተመሰሠረተ ስጋት ነው። ያም ሆኖ ሁለታችንም ለራሳችን የመለገም ወይም የመሰላቸት ፊት አላሳየነውም። የተዘረፈውን መሣሪያ ከየተደበቀበት ቦታ እየጫን ለበይነቀጠና ኮሚቴዎች አከፋፈልን። በማናወቀው የአዲስ አበባ ጉራንጉር ሁሉ ነፍሳችንን ሸጠን ትእዛዙን ፈጸምን። አንድም ቦታ ላይ "ማነህ?" ያለን አልነበረም።

በዚህ ሁሉ ሥራ ደጀኔ አልተለየንም። ሙፎም ከሰኔ ወር በተለይ ደግሞ ከ "አጥቅቶ መከላከል" ፖሊሲ መጽደቅ ወዲህ ኢሕአፓ ሙሉ በሙሉ ወታደራዊ ተቋም ሆኗል። በፖለቲካ ክፍሉ ያለነው እኔና ኢሳያስ ተረስተናል። እነ ደጀኔ ደግሞ ዋነኛ ተፈላጊ ሰዎች ሆነዋል። ትላንት ምሽት ላይ እኔና ኢሳያስ ከሸዋዬና ከደጀኔ ጋር ነበርን። ሸዋዬ ያበሰለችልንን ቦቆልት እየበላን ወሬ ጀመርን። በጣም ሲጨንቀን ደጀኔን ስለፖሊሲው ምንነት ጠየቅነው...

"ደጀን፤ በተማርከው ወታደራዊ ሳይንስ 'አጥቅቶ መከላከል' የሚባል ጽንሰሐሳብ አለ? እኛ ያላገላበጥነው መጽሐፍ የለም። አንድም የሌሎች ማርከሲስት ድርጅቶች ልምድ ማግኘት አልቻልንም..."

"እእእ...በወታደራዊ ሳይንስ..." መልስ መስጠት የቸገረው ይመስላል፤ ፊቱን ጭምድድ አድርጎ ለማስታወስ ከታገለ በኋላ፤ "በወታደራዊ ሳይንስ ማጥቃትና መከላከል የተለያዩ ጽንሰ ሐሳቦች ናቸው። የዘመቻ አቅዳቸውና ሥልታቸውም የተለያየ ነው። የሚጠይቁት ወታደራዊ ዝግጅትና ሥነልቦናም

እንዲሁ የተለያየ ነው። በሁለት የተለያዩ የአእምሮ ሁኔታዎች የሚሠሩ ተግባራት ናቸው። ስትከላከል አንተ ምሽግ ቆፍረህ ሊያጠቃህ የሚመጣን ጠላት ትመከታለህ። ጠላትህ ከአንተ የሠራዊት ቁጥር አነሰ ከተባለ በሦስት እጥፍ መብለጥ አለበት። በተለይ በከባድ መሣሪያዎች የተጠናከረ ጠላት ነው። አንተ ቦታህን ላለመልቀቅ ስትዋጋ ጠላትህ ቦታውን ለመንጠቅ ይዋጋል። ስታጠቃ አንተም የምታደርገው ይሄንኑ ነው..."

"እ---ሽ? ግ--ን ወታደራዊ ኮሚሽኑ አማከሯችሁ ነበር?" ኢሳያስ በጥሞና ሲያዳምጥ ቆይቶ ቅልብልብ ብሎ ሲጠይቀው ሁላችንም ሳቅን።

"አይ ኢሱዬ፣ እስቲ ቆይ መጀመሪያ የጠየቃችሁትን ይመልስላችሁ!" አለች ሸዋዬ ከሳቋ መለስ እያለች።

ደጀኔ ፈገግ ብሎ ከቆመበት ነጥብ ቀጠለ...

"ማጥቃትና መከላከል፣ የትኛው ይጠቅማል? ብለህ የምታወዳድራቸው ነገሮች አይደሉም። በአንድ ጦርነት ውስጥ ሁኔታው አስፈላጊ የሚያደርጋቸው የአንድ ውጊያ ሁለት ገጽታዎች ናቸው። አፈጻጸማቸው በጦርነቱ ዓይነትና ግብ ይወሰናል። በሁለት አገሮች መካከል የሚደርግ መደበኛ ጦርነት ሊሆን ይችላል። ወይም የጎሬላ ውጊያ። ያም ሆነ ይህ በአንድ ጦርነት ውስጥ አንደኛው ወገን ተሸናፊ ሌላኛው አሸናፊ ሊሆን የግድ ነው። አንድን ቦታ ከጠላት ጥቃት ተከላክሎ ሳይለቁ መቅረት የመከላከል ውጊያ ድል ነው። አጥቅቶ የጠላትን ይዞታ መንጠቅ ደግሞ የማጥቃት ድል ነው።"

ደጀኔ ትንሽ አሰብ አድርጎ እንደገና ቀጠለ...

"በሁለቱም ዓይነት ውጊያዎች አሸናፊና ተሸናፊ አለ። በጎሬላ ውጊያ ጊዜ አንድን ቦታ አጥቅተህ ይዘህ ቆይተህ መልሰህ በውጊያ ወይም ያለውጊያ ልትለቅ ትችላለህ። ይህ ግን በጽንሰ ሐሳቡ ልዩነት ላይ ለውጥ አያመጣም። በመከላከል ወይም በማጥቃት ጦርነት ቦታ ወሳኝ ነገር ነው። ልክ ኳስ ጨዋታ ላይ እንደምታየው ነው። ስትከላከል በራስህ ግብ በር ላይ ነህ። ስታጠቃ የተቃራኒውን ቡድን የግብ ይዞታ መውረር አለብህ..." ብሎ የተማረውን ወይም ከልምድ ያገኘውን እውቀት ከተናገረው ጋር ለማመሳከር ይመስለኛል መሬት መሬት እያየ ዝም ሲል ጥያቄ አነሳሁለት።

"ስለዚህ እያልከን ያለኸው ወይ ማጥቃት ወይ መከላከል እንጂ በአንድ ጊዜ 'አጥቅቶ መከላከል' የሚባል ወታደራዊ ሥልት የለም ነው፣ አይደል?"

ጉዳዩ እንደአስጨነቀው ፊቱ ላይ የሚታወቅበት ኢሳያስ ሲከነክነው የከረመ ሌላ ጥያቄ አነሳለት...

"በጦርነትም ይሁን በኳስ ጨዋታ ጊዜ ወገንን ከጠላት ወይም ከተጋጣሚህ መለየት አለብህ። ቦታ እንዳልከው አንዱ መለያ ነው። የደንብ ልብስ፣ አርማ ወይም ባንዲራ፣ የትጥቅ አይነቶችን ምናምን ትጠቀማለህ። በከተማ ሽምቅ ውጊያ ጊዜ ጠላትህን እያጠቃኸው ይሁን እየተከላከልከው በምን ታውቀዋለህ?"

ኢሳያስ በተናገረው ቁም ነገር ሳይሆን በተናገረበት አኳኋን ሦስታችንም ፍርፍር ብለን ሳቅን።

ደጀኔ የድርጅት ፖሊሲ ጉዳይ ስለሆነበት ይሁን ወይም ስላልተዘጋጀበት መልስ ለመስጠት ተቸገረ። እኔም በበኩሌ ከዚህ አልፌ መሄድ አልፈለኩም። ደጂኔን በጥያቄ እያዋከብን የድርጅቱን ተልእኮ እንዲጠራ ማድረግ ሆኖ ተሰማኝ። ያ ደግሞ የአንጃ ምልክት እንዳይሆንብን ሰጋሁ። ያም ሆኖ ግን አሁን አንድ ብዥታዬ ግፍፍ ብሎልኛል። "አጥቅቶ መከላከል" የሚባል ወታደራዊ ጽንሰሐሳብ የለም። አዲስ ሐሳብ ፈጠርን ብለው ከሆነ ደግሞ አልጨረሱትም ወይም በሚገባ አልተብራራም። ይህ ሳይደረግ ዘርዑና ዶክተር ተስፋዬ ወደ ተግባር ሊገቡ እየታጣደፉ ነው።

"እጭሩ የልጅነት ሕይወቴ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ በጸጸትና በቁጭት የተሞላ ነው!" የቢታኒያ አባባል ነፍስ ዘርቶ መጣብኝ።

# 27

ቢታኒያ ካልመጣች መተኛት አልችልም። እሷም የባሳች ናት። የማአከላዊ ኮሚቴ የስብሰባ ቀናትን "እንቅልፍ አልባ ሌሊቶች" ነው የምትላቸው። ገና እንደምሄድ ስነግራት ጭንቀት ይይዛታል።

በመስተንግዶ ሲዋከብ የዋለውና ያመሸው ግቢ ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ጀምሮ ጸጥ አለ። ቢታኒያ ዋናው ቤት ስለነበረች ብቻዬን ሁለተኛው ክፍል ውስጥ ፍራሽ ላይ ቁጭ ብያለሁ። አልፎ አልፎ ብቻ የገጠር እንግዶች ሽንት ቤት ሲሄዱና ሲመለሱ ይሰማኛል። ዳግላስ ሲጮኽባቸው ጸጥታው ለአፍታ ይደፈርሳል።

ቢታኒያ በገጠር ዘመዶቿ ወሬ እየሳቀች መጣች። ገና ሳትቀመጥ ያሏትን ነገር በቃለምልልስ መልክ እየነገረች እኔንም አሳቀችኝ…

በአባቷ በኩል የእናቷ ታናሽ እህት፣ "እንዲያው የከተማ ኮረዶች ነገራችሁ ምንድነው፣ ራቴ?"

"እንዴት ማለት፣ አስካልየ?"

"እህ፣ ሲያይዋችሁ አበባ፣ አዲስ ልቃቂት፣ ቆንጆ…ግን ጎጆ ሳትወጡ ከእናት ከአባት ጋር ተዳብሎ ቁጭ… የቁንጅናው ወራት ታለፉችሁ ወዲያ፣ እሙች እውነቴን ነው፣ ዛዲያ ሰርግ ቢሉት ከበሮውም እሽ ብሎ እሚመታ አይመስለኝ…"

"አስካልየ፣ እናንተምኮ ያው የትምህርት ችግር ምናምን ስላለ ነው እንጅ ቀስ ብላችሁ…ተምራችሁ…

አካላችሁ ሲጠነክር...ትንሽ ሐብትና ንብረት ስታፈሩ ነው መዳር የነበረባችሁ። ጭራሽ እኛንም አግቡ ብላችሁ ትመክሩናላችሁ ደ'ሞ?"

"ጉ---ድ ፈላ! ሐብት እስተማፈራ ልቆይ ካልኩማ ቁሜ መቅረቴ አይደል! ተዚያ ወዲያ ጋለሞታ ተብዬ ማን ወንድ ዞር ብሎ ያየኛል? ነው ወይስ በውሽማ ቆይ እያልሽኝ ነው?"

"እንደሱ አይደለም። ወንዱም ይሄን የምልሽን ነገር ይለማመደዋል። ከፈለግሽም ውሽማ ምናምን ሳይሆን ጓደኛ...እእእእ...ጮኛም ይዘሽ መቆየት ትችያለሽ። እሱም አይቸኩልብሽም..."

"እይይይ...ይሄማ ያው ዞሮ ዞሮ መወሻሸም አይደል! እንዲያው ለመሆኑስ አንቺ አሁን ጮኛ አብጅተሻል ማለት ነው?"

"እዎ፣ እስካልዬ... ቃል ተገባብተን የሚኖር ጮኛ አለኝ።"

"ታለሽማ ዛዲያ ከዛሬ ወዲያ ምን ቀን አለ? ምነው መጥቶ አላየነውምና?"

"ዉይ እስካልየ፣ ሳላስተዋውቅሽ ቀርቼ ነው እንጅ ነበረ። አራት ሆነው መጥተው አሁን ከመኼ ከሄዱት መካከል ነው። ያ ጠይሙ እዛ ተቀምጦ የነበረው...አይተሽዋል? ሲያጎርሰኝ የነበረው፣ ቁታ የለበሰው..." ስላት፣ "በጉ——ዶ ወጣ---ሁ! እሱማ አውታንቲ መስሎኝ፣ የዚታ የምናምን!"

ቢታኒያ ገና አሁን እንደሰማችው ሁሉ ከት ከት ብላ ሳቀች። እኔም ሳቋ ተጋባብኝ።

አውታንቲ ማለት የጭነት መኪና ሾፌር ረዳት መሆኑን ዐውቃለሁ። ዝቅ ተደርጎ የሚታይ ሥራ ነው። የገጠር ሰዎች ቅንነትና ልበ ገራገርነት ከልጅነቴ ጀምሬ የማውቀውና የሚስበኝ በረከታቸው ነው። በችግር ጊዜ ደግሞ መንፈሰ ጠንካራ ናቸው። ድርጅቴ ኢሕአፓ የመሬት ዐዋጁ መልስ ስለሰጣቸው ማሕበራዊ መሠረታችን ሊሆኑ አይችሉም ብሎ ችላ ያላቸው እነዚህን ሚሊዮኖች ነው። እንደገና ቅር አለኝ። ሌላ ያላቃትን ቢታኒያ እየመረጠች ስታወራኝ ቆይታ ወደ እኔና እሷ ጉዳይ ተመለሰች...

"በእንድ በኩል'ኮ እከስቴ እውነቷን ነው። የወደዱትንና የፈለጉትን በፈለጉ ጊዜ ማግባት ከወንድ ይልቅ ለሴት ይከብዳታል። ዛሬ ነገ ሲባል ደግሞ እንዳንዱ ወንድ እንዳ'ጉተ ሞሮን ነው። ሁኔታውን ዐይቶ እጥፍ ይላል።" ብላ ስትስቅ አብሬያት ልስቅ ቀና ስል፣ "ግን ሰሙዬ፣ ሰርቼልሀለሁ...እርግዣለሁ!" እለችኝ ቃላቱን ረገጥ አድርጋ።

የተደበላለቀ ስሜት ተሰማኝ።

"እንደዚያማ ከሆነ እኔ ነኝ የሠራሁልሽ፣ ቤቲዬ?"አልኳት።

ድንገት የወሬውን አቅጣጫ ቀይራ ከተጋደመችበት ጭኔ ላይ ብድግ አለችና ለሴኮንዶች ትክ ብላ አየችኝ። በረጅሙ ተንፍሳ ጸጉሯን ቆፈር ቆፈር አድርጋ እንደገና አተኮረችብኝ። የሆነ አንግዳ ነገር ልትነግረኝ ወይም ልትጠይቀኝ እንደፈለገች ገብቶኛል።

"ሰሙዬ፣ እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅህ፣ የምሬን ነው፣ ቀልድ እንዳይመስልህ..."

"እኮ ጠይቂኝ፣ እሱ ምንድነው?"

"አሁን ሰሙዬ፣ በሆነ ምክንያት ድንገት ሞት ከእጠገብህ ንጥቅ ቢያደርገኝ ምንድነው የምትለው? እኔ ልንገርህ... እናቴ፣ አባቴ ዘመዶቼ ምናምን አልልም። ሞቼ ሲለቀስልኝ ማየት ብችል ኖሮ አንተን ነው ማየት የምፈልገው። አንተ ሞሮን፣ መቼም ቁሉ ነህ፣ በሞትኩ በማግስቱ የሴት ባት ማየት ትጀምር ይሆናል እኮ ይሄኔ..."

ምንም አላልኩም። በዐይኖቼ ጠርዝ ሳያት ኮስተር ብላ ታየኛለች። አእምሮዬን ትንፋሽ አጠረው...

'ቢታኒያ መቼም ሕጻን ልጅ አይደለችም። ሕግን በመጠኑ የተማረች፣ ፍልስፍናን ድቅቅ አድርጋ ያነበበች፣ በዲያሌክቲካዊ ክርክር በደንብ የተገራች፣ ዐዋቂ ሴት ናት። ይሄ ልሰማው የማልፈልገው ወሬ እንደሆነ አሳምራ ታውቃለች። ወሬውን የምጠላው በሟርትነቱ ወይም ይደርስባታል ብዬ በመሳቀቅ አይደለም። በቃ፣ ሲጀምር በፍቅር መሀል የሚሰነቀር ርእስ መሆን የለበትም። ስለመኖርና በሕይወት ውስጥ ድል አድራጊ ሆኖ ስለመውጣት ነው መነጋገር ያለብን...' ቁጣዬ ግንፍል ብሎ ሊመጣብኝ ሲል እንደምንም ታግዬ መለስኩት።

ምንም መልስ ሳልሰጣት የቅሬታ ትንፋሽ ለቅቄ ሮመር ሰዓቴን እያፀዳዳሁ ዝም አልኩኝ። ዝምብላ ዓይን አይኔን ማየት ስትቀጥል ደግሞ ፈራሁ።

"ምናባህ ነው የምትዘጋኝ፣ ሞሮን?!" ብላ ራሷን ችላ ከተቀመጠች በኋላ፣ "ሰሙዬ፣ ቅር አለህ እንዴ? ስለምወድህ ነው የኔ ጌታ...ደግሞም ሰዎች ነን፣ ሞት አይመጣም ብለህ ብዙ አትዘናጋ...ለማንኛውም ከሞትኩ አደራ!" ብላ አንገቷ ላይ የነበረውን የወርቅ ሐብል አውጥታ አንገቴ ላይ አጠለቀችው፣"ሰሙዬ፣ ፍቅሬ...ከሞትኩ በዚህ አስታውሰኝ..."

አሁን ጨረቃ በፀሐይና በመሬት መካከል ተሰንቅራ ምድር በግርዶሽ ተዋጠች። የኃያላን መንግሥታት የጦር ግምጃ ቤቶች ተከፍተው አቶሚክ ቦንቦች ፈነዱ። የቴርሞ ኒኩሌር ውጊያው የቀሰቀሰው የጢስ ማአበል ምድርን ሙተንፈሻ አሳጣት...።

'አንድ ነገር አለ! እነ ዘርው በማይሆን ጅላጅል እቅዳቸው ከራሴ አስበልጨ የማያትን ፍቅረኛዬን ሊያስገድሉብኝ ነው። አንድ ጥቃት ላይ እንድትሳተፍ አዘዋታል ማለት ነው...' ጭል ጭል ብላ ትታየኝ የነበረችው ብርሀን ድርግም አለች። ጤነኛ ስለመሆኔ እርግጠኛ አይደለሁም። ብቻ የያዝኩትን ሮመር ሰዓት በመጨረሻው ጉልበቴ ወደ ግድግዳው ወረወርኩት። ከግድግዳው ጋር ተጋጭቶ ቁልቁል ወረዶ ወለሉ ላይ ተበትነ።

"እህህ? ሰሙ———ዬ፣ ምን እያ——ደረክ ነው? ቀልድ አታውቅም፣ እንዴ?" የቢታኒያ ድምጽ ዋናው ቤት መድረሱ አይቀርም ብዬ ለማሰብ የተፈጠረብኝ ደምፍላት አልፈቀደልኝም።

ሰዓት በመሰበሬ ብቻ አልረካሁም። የሚንተከተከው የሆዴ ውስጥ ገሞራ አልወጣልህ አለኝ። ግን ምንድነው የማደርገው? ምንም ነገር ማድረግ እንደማልችል ሳውቅ በደመነፍስ ብድግ አልኩ። ፍላጎቴ፣ ወጥቶ ወደ ምድር ቤት መሸሽ እንደሆነ ትንሽ ትንሽ ዐውቃለሁ። ቱታዬን ብድግ ሳደርግ ቢታኒያ እንደ ጭልፊት ተወርውራ ነጠቀችኝ።

"ምናባህ፣ የት ልትሄድ? ቀልድ አታውቅም፣ እንዴ?" እንደገና የምሯን ጮኸች።

አንድ ቃል አልተናገርኩም። ቱታውን ለቅቄላት የእሷን ነጠላ ጫማ አደረኩ። በሙታንታዬና በኬኒትራዬ ብቻ ወደ መሀለኛው በር ተንደረደርኩ። በዚህ የቁጣና የእብደት መጠን ዐይታኝ እንደማታውቅና እንደደነገጠች ገብቶኛል። በርግጋ ተነስታ ተከተለችኝ። ግድ አልነበረኝም። ከመሀል በሩ ደርሼ መጋረጃውን ለመግለጥ እጄን ስሰድ በጀርባዬ በኩል ሆዴን ጥምጥም አድርጋ ያዘችኝ...

"አትሄዳትም! አለቅህም! ማሚ ትሙት! ሰመረ ይሙት!" በመጨረሻ ጉልቢቷ ብትይዘኝም ልታስቀረኝ ይከብዳታል፣ እጆቿን ላላቅቅ ስሞክር፣ "ኡኡኡ...ብዬ ማማሚን ልጥራት ነው! ሰሙዬ ልታስጮኸኝ ነው!"

እንደማታስቆመኝ ሲገባት ትከሻየ ላይ በንክሻ አንቅ አደረገችኝ። የውስጥ እልህ ግፊት እሱንም ተቋቋሚ ወጥቼ እንድሄድ አበረታታኝ። እጇንም ጥርሷንም አስለቅቄ ላመልጣት ትንሽ ሲቀረኝ ወደ ጎን ገፍትራኝ ቀድማኝ ተፈተለከች። "እንዲያውም ራሴን አጠፋለሁ!" ስትል ሰምቻታለሁ። ትርጉሙን ለመረዳት ግን አእምሮዬ በሩን ጥርቅም አደረገው። ከመጀመሪያው ክፍል ገብታ ወደ እልጋው ራስጌ ውልብ ስትል

ዐየኋት። ተከትያት መጋረጃውን ገልጪ ወጣ ስል ፊቷን ወደ እኔ አዙራ ቆማለች። ቀኝ እጇን ብድግ ስታደርገው ጥቁረቱ ናፍታ የመሰለ አዲስ ሩሲያ ሰራሽ ማካሮቭ ሽጉጥ! አፈሙዙን ጭንቅላቷ እስነክታ ደግናዋለች...

"ቤቲ—የ...!" ድምጼ እምልጦኝ እንደ መርዶ ነጋሪ ጮኽኩ።

ጭለማው አሁን የተሟላ ሆነ። የቆምኩባት ምድር እግሬ ሥር ስትሽከረከር በቆምኩበት ልቀመጥ ልውደቅ ትዝ አይለኝም።ትንሽ ቆይቼ የቢታኒያ እጆች መላ ደረቴን ሰንነብ እንስ ግንባሬ ሲመላለሱበት ተሰማኝ። ቀስ ብዬ ተነሳሁ። ወደ ፍራሹ ሄጄ በደረቴ ; ደፋሁ። አጠገቤ አብራኝ ጋደም አለች። ትንፋሿ አንገቴን...የአንገቴን ሥር...ጉንጮቼን ሲያሞቃቸው ተሰማኝ። እስከ ዶሮ ጩኸት ድረስ ተጨማሪ እንዲትም ቃል ትንፍሽ አላልኩም። ደጋግማ ልታግባባኝ ሞከራ በድን ስሆንባት አሷም ዝም አለች። መነጋገር የለ፣ ምን የለ። ተልእኮዋ የትና መቼ እንደሆነ አላውቅም። 'የሱፍ አበባዋን ሊቀነጥሱብኝ ነው!' ብቻ መልእከ ሞት ሲያንገብብን አድሮ ንጋት ሆነ። እንቅልፍ ሸለብ አድርጓታል። እንባዬ እየተናነቀኝ ግንባሯ ላይ ስሜያት ወጥቼ ሄድኩ...

***

ውሎዬ ዉሎ ተብሎ የሚመዘገብ አይደለም። በጋራዡና በቢታኒያ ቤት መካከል እንደ ዝሀ አዝጊ ስመላለስ ዋልኩ። አስር ጊዜ ይሆናል ዐይቻት የተመለስኩት። እስካሁን አለች። በተያየን ቁጥር ትርጉሙን የማላውቀው ፈገግታ ታሳየኛለች።ብቻዋን ካገኟኋት አንቅ አድርጋ ይዛ አልጋው ላይ በጀርባዬ ትጥለኛለች። በአንገቴ ሥር ቅርቅር ትልና ትልሰኛለች። የምጓጓለትን አንድ ነገር ግን መስማት አልቻልኩም።

"ሰሙዬ ሆዴ፣ ቀልዴን ነው፣ የትም አልሄድም!" ከአፏ አልወጣልኝ አለ።

ፊቴ በቅሬታ የሞላ አቁማዳ መስሎ እንደተነፋፋ ወጥቼ እሄዳለሁ። አላስችል ብሎኝ እንደገና እመለሳለሁ፣ ለውጥ የለም። የማደርገው ሲጠፋብኝ ወደ ምድር ቤት ሄጄ ደጀኔና ሸዋዬ የሚያውቁት ነገር ይኖር እንደሆን መጠየቅ ፈለኩ። በነሐሴው መዘዘኛ የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባችን ውሳኔ የዘመቻው ኃላፊነት በሙሉ የፖሊቲካ ቢሮው ነው። ስለዚህ ምንም ፍንጭ ማግኘት አልቻልንም። ኢሳያስም ምንም የሰማው ነገር የለም። መኪናዎቹን በማዘጋጀት ሥራ ቀልቡን ስቶ ተወጥሯል። ቀጥ ብዬ ወደ ምድር ቤት ሄድኩ። ሸዋዬ በር ከፍታልኝ የኢሳያስን ከፍል ሳቋርጥ ድምጽ ተሰማኝ። ወደ ደጀኔ ቤት አማተርኩ። አራት ሰዎች መሬት ላይ በጥፍሮቻቸው ጫፍ ላይ ቁጢጥ ብለው ተቀምጠው ይታዩኛል። በደብዛዛው ብርሀን

ውስጥ ዝቅ ባለ ድምፅ የደራ ምከከር ይዘዋል። ከርከር ይሁን አይሁን ግን መለየት ከበደኝ...

'እነ ማን ናቸው? የምንስ ድግስ ነው የያዙት?'

ከመካከላቸው የፖሊት ቢሮ አባላት እንደሚኖሩ አልተራጠርኩም። ደብዛዛው ብርሀን እየፈካ ሲሄድ ሌላም ነገር ታየኝ። ወለሉ ላይ ትልቅ የካርታ ወረቀት ዘርግተዋል። የአዲስ አበባ ይሁን የአሲምባ አላውቅም። ለነገሩ እነርሱ ለአሲምባ ምን ጉዳይ አላቸውና! አሲምባ ለእነርሱ ፀሐይ ለአመጸኛዋ የሱፍ አበባ ማለት ነው። በጣም በጣም ሆዴን ከፋው። አሁን ደግሞ ማንነታቸውን ለየሁት። ዘርው ከሀሸን፣ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ፣ ደጀኔና ጎይቶም ለባሲ ናቸው። እነርሱን አቋርጬ በመሄድና በሽዋዬ ሙተላለፊያ በኩል ወደ ምድር ቤት ለመውረድ ሳመነታ ዘር ዘር ብለው አዩኝ።

ዘርው "ጓድ አላምረው..." ብሎ ሲጠራኝ ሁሉንም አንድ ላይ እጄን አወዛውዤ ሰላምታ ሰጠኋቸው። ሥራቸውን የጨረሱ ይመስለኛል፤ ዶክተር ተስፋዬና ጎይቶም ከተቀመጡበት ተነሱ። ደጀኔ ካርታውን ጠቅልልሎ አነሳው።

'ገበሬን የካደው የድርጅቴ ኢሕአፓ አመራር! በፀሐይ ላይ ያመጸችው የሱፍ አበባ ተምሳሌቶች!' ልቤ መከፋቱን እያጉረመረመ አጃቸውን ተራ በተራ ጨብጬ ወደ ምድር ቤቴ ወረድኩ።

ምድር ቤቴ እንደ ቀድሞው አና ሆኖ አልጠበቀኝም። ሦስት ራሳቸውን 'ካሞፍላጅ' ያደረጉ ሴቶች አሉ። በታይፕ መጻፊያዎች ላይ አቀርቅረው ይሄን ጽሑፍ ይሉታል። እኔ ቀድሞውኑ ስለተመሳሰልኩ አታውቅ ይሆናል ብዬ አልተጨነኩም። ከጀርባቸው እየት ሳደርጋቸው ለአፍታ ዘር ዘር ብለው አዩኝ። አተኩሮ ማየት በኢሕአፓ ባህል ደስ አይልም። ወደ ሥራቸው ተመልሰው ታይፕ መጻፊያውን ያንጫጩት ጀመር። ወደ አልጋዬ መሄድ አልፈለኩም። ወረቀት የምፈልግ መስዬ የአንዱን ቁም ሳጥን ኪሶች በረበርኩ። እስከአሁን እነ ዘርው ሄደው እንደሚሆን ዐሰብኩ። ረስቼው ሰዓቴን ላይ እጄን አነሳሁ። ሮመፋ የለም።

ተመልሼ ሄጄ ደረጃውን ወጣሁ።

ግምቴ ትክክል ነው። ጥርግርግ ብለው ሄደዋል። ወደ ኢሳያስ ክፍል ጉብቼ ቁጭ ከማለቴ ሽዋዬ መጣች። ስንባ ዐይታኛለች ማለት ነው። በጣም የምወደውን ስንዴ ቂጣ በሳህን አድርጋ ከሻይ ጋር አመጣችልኝ። እሱን እየቆረጣጠምን ወሬ ጀመርን። ቅሬታ የለዋወጠውን ፊቴን በደንብ አንብባዋለች። ከቢታኒያ ጋር ተገናኝተው እንደሚሆንም አገምታለሁ። በጣም መሠረታዊ የድርጅት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር

በማሕበራዊ ኑሯችን ምሥጢር የሚባል ነገር ገና ድሮ ነው የተውነው። በተለይ እኔ፣ ሸዋዬና ደጀኔ አብረን ከመኖር ብዛት ቤተሰብ ሆነናል...

"አንተ አላምረው፣" ድምጿን በጣም ዝቅ አድርጋ ወደ ጆሮዬ ተጠጋች፣ "እኔ ካንተ የተሻለ እውቀት የለኝም። አባካችሁ፣ አባካችሁ፣ ይሄ 'አጥቅቶ መከላከል' የሚሉት ነገር እስከሚያልፍ ድረስ አፋችሁን ዝጉ። በተለይ አንተና ኢሳያስ። እኔ፣ እዛ ማእከላዊ ኮሚቴና ፖሊት ቢሮ አካባቢ ስትባባሉት የምታድሩትን ነገር በጨረፍታ ስሰማው አልተመቸኝም..." ትከዝ አለች።

"ሸዋ፣ ደጀኔ ሲነግረን ሰምተሽ የለ? 'አጥቅቶ መከላከል' የሚባል ነገር የለም። ያለው 'አድብቶ መግደል' ነው። ይሄንን ተይውና ይልቅ ዛሬ ምን ሊያደርጉ እንዳሰቡ የሰማሽው ነገር አለ?" የሆነ የምሥራች እንድታሰማኝ እየተመኘሁ ጠየኳት።

"ምን ዐውቅላቸዋለሁ? 'ቁጭራ ባንክን መዝረፍ' ምናምን ሲሉ ነበር።"

"ባንክ?"

ነገሩ ሁሉ ወዲያው ተምታታብኝ። ቢታኒያ ሰው ከመግደል በባንክ ዘረፋ ብትሳተፍ የሚሻል መሰሎ ታየኝ። ደግሜ አሰብ ሳደርገው የባንክ ዘረፋ ከሆነ በእርግጥም ይሻላል። ያው በአብዛኛው በአሻጥር የሚፈጸም ነው የሚሆነው። ልክ እንደሰንዳፋ መሣሪያ ዘረፋ የውስጥ አባሎቻችን አመቻችተው የሚሠራ ነው። በመጠኑም ቢሆን ቅልል ብሎኝ ዘና አልኩ።

'አዎ፣ አድብቶ ከመግደል ይሻላል!' የቀረችኝን ሻይ ጨልጬት ተነሳሁ።

***

ወደ ጋራዥ ስመለስ ሰዓቱ ተንቀዥቅዥ ሄዶ አሥራ ሁለት ሆኗል። ሠራተኞች ወጥተዋል። ዋናው መግቢያ በር ግን አልተዘጋም። ሸዋዬ የነገረችኝ ዜና ጭንቀቴን ተንፈስ እደረገው መሰለኝ ወደ ቢታኒያ የመሄድን ሐሳብ አዘገየሁት። ቢሮዬ ገብቼ ቁጭ አልኩ። ገና ሳልደላደል ወደ ጋራዡ የሚገቡ ሰዎች የእግር ኮቴ ተሰማኝ። ብድግ ብዬ ሄጄ አየሁ። ደጀኔና ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ናቸው።ተስፋዬ ካኪ ካፖርት ልብሶ ስለተመሳሰለ በመነጽሩ ነው የለየሁት። ከመኢሶኖች መኪና አጠገብ በቆሙትውና በተጠገነችው መኪና ላይ ተሳፈሩ። ዶክተር ተስፋዬ በአሽከርካሪዉ ወንበር ላይ ሲቀመጥ ደጀኔ እንደገና ወርዶ በእግሩ ወደ በር ሄደ። መኪናዋ ቀስ ብላ ወደ ኋላዋ ሄዳ ወጣች። ተመልሼ ወንበሬ ላይ ቁጭ ስል ደግሞ ሌላ ድምጽ መጣ። የእነ ቢታኒያ የጀርባ ቀይ በር ሲከፈት ተሰማኝ። ልቤ በሆነ ድንጋጤ ትርትር አለች...

'ይሄ ቀይ በር ያለእንዳች ምክንያት አይከፈትም። ከእኔና ከኢሳያስ በስተቀር ቁልፍ ያለው የለም።' በርግግ ብዬ ተነስቼ ለበሩ ትይዩ ወደሆነ ትልቅ መስኮት ሄጄ በስንጥቁ በኩል ወደ ውጭ አጮለኩ።

ትክክል ነኝ። ቢታኒያ በሩ ላይ ብቻዋን ቆማለች። እንደዚህ ምሽት አምራና ደምቃ አይቻት አላውቅም። ከአግሯ ቅልጥም ሲደርስ የሚቆም ርዝመት ያለው ነጣ ያለ ካኪ ሱሪ ለብሳለች። ከላይ ዥጉርጉር አጅጌ ጉርድ ሸሚዝ አድርጋለች። ጥቁር መነጽሯን ጭንቅላቷ ላይ አለ። ሱልልታ የሄድን ጊዜ ይዛው የነበረውን ትልቅ ቢጫ ቦርሳ አንግባለች። ቦርሳውን የክፉ ነገር ምልክት አድርጌ መውሰድ የጀመርኩት ከዛ ቀን ጀምሮ ነው። ትላንት ሌሊትም አልተወኝ። ያን ጽልመት የመሰለ ሽጉጥ መሸርጣ ያወጣችው ከዚሁ ቦርሳ እንደሆነ ገብቶኛል። በሽዋዬ ዜና ስከኖ የነበረ መንፈሴ እንደገና ደፈረሰ...

'የት ሊወስዱብኝ ነው? እውነት ቤቲ ለባንክ ዘረፋ ታስፈልጋቸዋለች? እንደዛ ከሆነ ዶክተር ተሰፋዬ ምን ጣለው? በዚህ የአመራር ቦታ ላይ ሆኖ ዘመቻ ውስጥ አይገባም። ግን በወልድያው ዘመቻ ላይ ነበረ አይደል!' አእምሮዬ አንድ ቦታ ላይ ማረፍ ተስኖት አየር ላይ ተንሳፈፈ።

ቢታኒያ ወደ ፊት ለፊት እያየች በጥቅሻ ስትነጋገር አየኋት። ከደጀኔ ጋር መሆን አለበት። በከንፈሮቿና በእጆቿ የምትጠይቀው ነገር አለ። ስትደግምለት የምትለው ነገር በደንብ ገባኝ። "ሰመረ አለ ወይ?" "ቢሮ ውስጥ አለ!" ሳይላት አልቀረም። ደንገጥ ብላ ወደ ቢሮዬ አቅጣጫ ገልመጥ ካለች በኋላ ወደፊት እየተንደረደረች ሮጠች።

'ወይኔ፣ ፍቅረኛዬን ሊያስገድሉብኝ ነው!' ወደ ዋናው የጋራዡ በር ተጣደፍኩ።

በትንሿ በር በኩል አንገቴን ወደ ውጭ አሰገኩ። የዶክተር ተሰፋዬ መኪና ፊቷን አዞራ ቆማለች። ደጀኔ ከጀርባ ወንበር በግራ በኩል ቁጭ ብሏል። ቢታኒያ በዚያው ፍጥነት ሄዳ የገቢናውን በር ከፍታ ከተሰፋዬ አጠገብ ተቀመጠች። የአንገት ሰላምታ ብቻ ስትሰጠው አየኋት። እይተዋወቁም ማለት ነው...!። ...ሁሉም ነገር ቅዠት መስሎ ታየኝ። ከመቅጽበት ውስጤ ባዶ ሆነ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ ለማብሰልሰል ጊዜ አላገኘሁም። ስድስተኛው ህዋሴ ሹክ ብሎኝ መንገዱን መራኝ...

'ሰመረ፣ ልብ በል! ቢታኒያ አንድ ቦታ ላይ እርዳታህ ያስፈልጋት ይሆናል። ለጊዜው ትክክልም ባትሆን የራሱ ጉዳይ! ቢታኒያ አይደለችም፣ እንዴ? መኪና ያዝና ከሥር ከሥር ተከተላቸው።'

***

የፈረንጆቹ ፊያት 127 መኪና አንድ ቁልፍ ኪሴ ውስጥ አለ። ፍጥነት! ፍጥነት! ፍጥነት! እየንዳሁ ወጥቼ አስፋልቱን ስይዝ ወደ ቀኝ አቅጣጫ ተመለከትኩ። የእነ ተሰፋዬ መኪና ገና የኑረዲንን ዳቦ ቤት ማለፏ ነው። ተከተልኳት። አውቶቡስ ማረፊያ...አዲስ ከተማ...ጎንደር በረንዳ...ሐብተጊዮርጊስ ድልድይ...እቡነ

ጼጥርካ፡፡ እዚህ ሲደረስ እንደ ልማዴ ወደ ግራ ዞር ብዬ ወደ ሬዲዮ ጣቢያው ተመለከትኩ፡፡

"ወ—ይ እጋጥሚ!" አልኩ ድምጽ አውጥቼ፡፡ ብርከታዊት ሙሉ ጥቁር የከረምት ካፖርት ለብሳ ጃንጥላዋን እያጠፈች ሄዳ መኪና ላይ ተሳፈረች፡፡ በድንገቱ ተገረምኩ፡፡ ይሄኔ ብፈልጋት ኖሮ በእግር በፈረስ ብዬም አላገኛት ነበር፡፡ ፈጠን ብዬ ወደ ምኒልክ አደባባይ ነዳሁ፡፡ የተስፋዬ መኪና ወደ ግራ ታጥፋ አደባባዩን ዞረችና የእፍንጮ በርን አቅጣጫ ይዛ ሮጠች፡፡ ዳገቱን ወጥታ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሳትደርስ ወደ ቀኝ ታጥፋ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ያዘች፡፡ ወደ ሰባ ደረጃ የሚወስደውን መንገድ ይዛ ሄዳ ወደ ግራ ታጠፈች፡፡ አለቀኳትም፡፡

ዮት ነው የሚሄዱት?' ፍቅረኛዬን ሲያስገድሉብኝ ዝም ብዬ ማየት አለብኝ? የነዳጅ ቆጣሪው 'እያለቀብህ ነው!' ምልከት አሳየኝ፡ 'ችግር የለውም፡ ከዚህ በኋላ ቢያንስ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ያስኬደኛል!'

የተስፋዬ መኪና ወደ ቅድስተ ማርያም ቤተክርስቲያን ሄዳ አራት ኪሎ ዋናው አስፋልት ገባች፡፡ እሱንም አቋርጣ ወደ ማንፍሌ ሄዳ እንደገና ወደ አራት ኪሎ በወወከማ በኩል ተመለሰች፡፡ አራት ኪሎ አደባባይን ዞራ ወደ ግራ ታጠፈች፡፡ አርበኞች ሕንጻ ስትደርስ ለደቂቃዎች ቆመች፡፡ እየመሸ ነው፤ የመንገድ መብራት በርቶ የሰውና የታከሲው ግርግር ጨምሯል፡፡ ትንሽ ቆይታ የተስፋዬ መኪና ወደ ፊት ተንቀሳቀሰች፡፡ የፊት በርን አቅጣጫ ይዛ ሮጠች፡፡ ተከተልኩት፡፡ እድል አልፈቀደችልኝም፡፡ ፓርላማ ፊት ለፊት ያለው መብራት ያዘኝ...

"ስ—ቀ—ፒ--ድ!" የመኪናዋን መሪ በቡጢ ነረትኩት፡፡

ከዚህ በኋላ በየት በኩል እንደምሄድ አላውቅም፡፡ አረንጓዴው ሲበራ ቀጠልኩ፤ በአዲስ አበባ ትራፊክ ፖሊስ በኩል ወደ ስቴዲየም ወረድኩ፡፡ የተስፋዬ መኪና አሁን ደብዛዋ የለም፡፡ በለገሐር በኩል ወደ ቴክኒክ ኮሌጅ ሜክሲኮ ነዳሁ፡፡ አደባባዩን ዞሬ ወደ ጀርባዬ ከተመለስኩ በኋላ ወደ ሶማሀር ስጣጋ እንግዳ ድምጽ ተሰማኝ፡፡ ተኩስ! ካካካካካ... ዲዲዲዲዲ... ድው ድው ድው ድው ድ፡ጥ፡...ምድር ቀውጢ ሆነች፡፡ 'ግድያ ነው! ግድያ! ፍቅሬን አስገደሉብኝ! ወ—ይ—ኔ!! ቢታኒያ፤ ወ—ይ—ኔ ፍቅሬ! እኔ ደፋ ከንብል ልበልልሽ...'

ከርቀት ሰው ሲተረማመስ ይታየኛል፡፡ የመኪናው ጅረት ስቴዲየም አካባቢ ቀጥ አለ፡፡ የምሄድበት ቦታ አልም ብሎ ጠፋብኝ፡፡ ወደ ግራ ታጥፌ እንደገና ወደ አራት ኪሎ ከወጣሁ በኋላ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ወደ አብዮት አደባባይ መጣሁ፡፡ ምንም ነገር አይታየኝም፡፡ በስቴዲየም በኩል ወደ ፒያሳ ነድቼ መዘጋጃ ቤት ስደርስ ነዳጁ ቀጥ አለ፡፡ አጠገቤ የነዳጅ ማደያ አይታየኝም፡፡ መኪናዋን እየገፋሁ ከመንገድ አውጥቼ አቆምኳት፡፡ ጀርካን ይዤ ወደ ጊዮርጊስ ቶታል ሮጥኩ፡፡ ወረፋው ዘንዶ መስሎ ጠበቀኝ፡፡ ከአንድ ሰዓት በላይ ጠብቄ አልደርስ ሲል መታወቂያ አሳይቼ በመከራ ቀዱልኝ፡፡

'ወይኔ፣ ቤቷን አስገደሉብኝ ማለት ነው?' ነፍሴን ስቼ ሮጥኩ።አእምሮዬ ሥዕሉን አመጣው። ራቅ ራቅ ብለው በቆሙ ፖሊሶች መሀል ቤቲ በጀርባዋ መሬት ላይ ተዘርራ...ረጅም ጸጉሯ ከጀርባዋ መሬቱ ላይ ተነስንሶ...ሁለቱ እጆቿና እግሮቿ በየአቅጣጫው ዝርግትግት ብለው...ከአንገቷ አካባቢ የሚፈስ ደም አስፋልቱን አቅልቶት ቁልቁል እየወረደ...ቦርሳዋ አጠገቧ ወድቆ...አላፊ አግዳሚው ከርቀት አይቷት "ጽም! እየ ጉ-----ድ፣ ያለጥርጥር የቤት ልጅ ናት...ቁንጅና መና...ውበት ብላሽ...ይሄኔ እናትሽ ቢኖሩ ምን ይሉ ነበር?! ኧረ ፈጣሪ በዚህ በቃችሁ በለን!" ሲባባል እንደፈልም ታየኝ። ሕሊናዬን ልስት ምንም አልቀረኝም። የምሠራውንና የማደርገውንም አላውቅም።

'እኔ ልደፋልሽ፣ ቤትዬ፣ ፍቅሬ!' በረርኩ።

ሙቼም ሲቸኩሉት ነገር አለው። ፊያት 127ቷ ከኋላና ከፊት በወታደሮች መኪና ታጥራ አገኘኋት። በኢሕአፓነቴ የሚያስፈራኝ ምንም ነገር የለም። ችግሬ ሾፌሮቹ በአካባቢው አለመኖራቸው ነው። መላወሻ ቦታ የለም። ነዳጁን ቀድቼ ሾፌሮቹን ግማሽ ሰዓት ያህል ጠበኩ። ብቅ አላሉም። ምንም ማድረግ ሲያቅተኝ ሰው ለምኜ በግፌ መኪናዋን ወደ መንገድ አስገባሁ።

ተመልሼ ጋራዥ የደረስኩት 2: 45 ሲል ነው። ቢታኒያ ተገድላ ግቢው ውስጥ ለቅሶ ይጠብቀኛል እያልኩ ነው የደረስኩት። ምንም ድምጽ ሳልሰማ ቀረሁ። መሬቱን ስመህ ፈጣሪህን አመስግን የሚል ግፊት መጣብኝ። ማርክሲስትነቴ አዛው! ግን ማልቀስ ተከልክለው ቢሆንስ? አይደለም! አይደለም!

'ፍቅሬ ተርፋልኛለች ማለት ነው! ግን፣ ግን ምን አድርገው ነው የመጡት? መጀመሪያ እሷን ላግኛት!' ወደ ቢታኒያ ሮጥኩ።

በሯን በርግጀው ገባሁ። በሕይወት አገኘኋት። ቢጃማዋን ለብሳ ሬዲዮ ስትጎረጉር ደረስኩ። ከመጠን በላይ ተረባብሻለች። ፊቴ ላይ ወይም ከአኳኋኔ ምን እንደተረዳች አላውቅም። መጥታ ተጠመጠመችብኝ። ለበርካታ ሴኮንዶች እንደተቃቀፍን ቆየን። የተላቀቅነው ወንድ የሬዲዮ ጋዜጠኛ "አድማጮቻችን፣ አሁን የደረሰን ዜና አለ!" ሲል ነው። ሄዳ ሬዲዮውን አንስታ ይዛው ቆመች። ጋዜጠኛው ንባቡን ጀመረ...

"ጸረ-አብዮትና ጸረ-ሰላም ዓላማ የሚያራምደው ኢሕአፓ የተሰኘው አናርኪስት ቡድን ቅጥር ነፍሰገዳዮች የደርጉን ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያምን ለመግደል በከፈቱት ተኩስ ምክትል ሊቀመንበሩ ቆስለው ሆስፒታል መግባታቸውን የደርግ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ። ይሁንና አደጋው ለሕይወታቸው አስጊ አለመሆኑን ሐኪሞች አረጋግጠዋል።"

ቢታኒያ የያዘችውን ሬዲዮ ወለሉ ላይ ፈጠፈጠችው...

# 28

ከሁሉም ትልቁና መራራው ፈተና የማያምኑበትን ተልእኮ በፈቃደኝነት መፈጸም ነው።

የቢታኒያ ሕይወት አደጋ ላይ መውደቅ እንደ እሬት ጎመዘዘኝ። ሻለቃ መንግሥቱ ሞተ፣ ኖረ፣ ቆሰለ፣ ደማ...ለእኔ ምኔም አይደለም። የእኔ ጭንቀት ርእዩተዓለማዊ ጥቅምና የኢሕአፓ ሕልውና ናቸው። እድብቶ የመግደል ዘመቻው እንዳች ጥቅም ቢያመጣ ኖሮ እኔው ራሴ ለምን እሁኑኑ ድብን አልልም?!

ይሄው በሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ላይ የግድያ ሙከራ ከተደረገ አንድ ሳምንት አለፈ። የሙከራውን ፖለቲካዊና ወታደራዊ እንድምታ ለመተንተንና ጊዜው ገና ቢሆንም አንድ ግዙፍ ውጤት እንደሚኖረው መገመት አይከብድም። በበኩሌ ሰባራ ሳንቲም ታክል ስሜት የሰጠኝ ከንውን አልነበረም። ባደኩበት አካባቢ በልጅነቴ እሰማው የነበረውን "የደም ምልልስ" ታሪክ ነው ያስታወሰኝ።

'ኢሕአፓን የሚያከል ግዙፍ ድርጅት በግለሰብ መሞትና መኖር ጉዳይ ሲጨነቅ መዋል ነበረበት?' ትከን አልኩ።

የድርጅታችን አብዛኛው አባሎች ከእርምጃው በስተጀርባ ያለውን ሎጅክ ከመመርመርና ትምህርት ከማግኘት ይልቅ የሻለቃ መንግሥቱን መሞት ወይም መትርፍ ልክ እንደ አንድ የመጨረሻ ፖለቲካዊ ግብ አድርገው እንዲወስዱት አድርጓቸዋል። ቢታኒያ በማግስቱ ሙሉውን ቀን ምግብ አልበላም፣ ውኃ አልጠጣም፣ ሰው አያናግረኝ... ብላ ነበር የዋለችው።

"ኧረ ባክሽ፣ ቤቲዬ... ድሮውንም በሳይንሳዊ ትንተና ላይ ያልቆመ ውሳኔ ነው። ብትሞች ኖሮ ዕድሜ ልኬን ሲያቃ------ጥለኝ የሚኖር ጸጸት ትተሽብኝ ትሄጅ ነበር። አሁን ቁጭቱን ትተሽ እንደድሮው ሁኚልኝ!" እንባ እየተናነቀኝ ለምኖት ነው ለአመል ያህል እችን ታህል የቀመሰችው።

በምን ምክንያት ተልእኮው እንደከሸፈ ልትነግረኝ ግን አልፈቀደችም። ደጀኔም በሙከራው ማግስት ልክ እንደእሷ ሆኖ ነው ያሳለፈው። ሲነድ ሲበርድ ውሎ ምሽት ላይ በሸዋዬ ምክርና ተጽእኖ ትንሽ መለስ ሲልለት በጫወታ ጫወታ ስለ ኦፐሬሽኑ እንዲነግረን ወተወትነው። እያማጠ፣ ጀመር ተወት እያደረገ ይተርክልን ገባ...

"በሦስት ተከፍሏል..."

"ምኑ?"

"ኦፐሬሽኑን የሚፈጽመው ታጣቂ ኃይል"

"እ..ሺ!"

"አብሪ ጓድ የመጀመሪያው ነው። ጥገና በተደረገላት ቶዮታ ሐይሉከስ ተሳፍሮ የሻለቃ መንግሥቱን መምጣት ይጠባበቃል። ይህ ከንፍ በፍቅሬ ዘርጋው ይመራል።

ባለፈው ሳምንት እድሳት ስናደርግላት የነበረችው ሐይሉከስ ቶዮታ ትዝ አለችኝ።

"ሁለተኛው ክፍል «መች ጓድ» ነው። ምልክቱን አይቶ በሻለቃው ላይ ተኩስ የሚከፍት እግረኛ ቡድን። ጎይቶም ለባሲ የዚህ ቡድን መሪ ነው። የተመደበውም ስቴዲየም አካባቢ ነው። ምክንያቱም መንግሥቱ ከየትም አቅጣጫ ይምጣ ስቴዲየም የግድ የሚያቋርጠው መንገድ ስለሆነ ነው።

ለአፍታ ቆም ብሎ በቁጭት ከንፈሩን ነከሰ

"ሦስተኛው ጓድ ደግሞ መችው ኃይል ግድያውን ከፈጸመ በኋላ ችግር እንዳይገጥመው የማደናገሪያ ሽፋን የሚሰጥ ነው። በኔ ነበር የሚመራው። ዶክተር ተስፋይ ደበሳይ ደግሞ ጠቅላላውን ኦፐሬሽን ይመራል።"

ሦስተኛው ጓድ የኔዋ ቢታኒያ የነበረችበት መሆኑ ገባኝ። እሷ ሾፌራቸው ተስፋዬ ደበሳይ መሆኑን በጭራሽ አላወቀችም። ገቢና እንድትቀመጥ የተደረገው መኪናው የቤተሰብ ወይም የፍቅረኞች እንዲመስል ነበር። ለማንኛውም በሚል ግን ሽጉጥ እንድትታጠቅ ተደርጓል።

ደጀኔ ትረካውን ቀጠለ...

"ከዚያ ልክ መንግሥቱ ከቤተመንግሥት ሲወጣ ለሙችው ኃይል ምልክት የሚሰጠው ጓድ ተንቀሳቀሰ፡፡ እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ችግር የተፈጠረው፡፡ ሙቺው ኃይል እንድም ጥይት ሳይተኩስ የመንግሥቱ መኪና አለፈች፡፡ እኛ ይሄንን ስናይ የምናደርገው ጠፋብን፡፡ ምክንያቱም እኛ ሙቺ ኃይሉ ከተኮሰ በኋላ ነው የማደናገሪያ ተኩስ እንድንከፍት የታቀደው፡፡ ከሙቺው ኃይል አዲስ ነገር ሲጠፋ ዝምብለን መቀመጡ ደግሞ እጅግ አሳፈረን፡፡ በዚያ ላይ ለድሉ ዜና እጅግ ጓጉተናል፡፡ በዚህ ጊዜ መንግሥቱን የያዘችው መኪና እያለፈች ነበር፡፡ ቢታኒያ መኪናዋ ስታልፈን ድንገት 'ምንድነው ይሄን ያህል መንቦቅቦቅ፣ በአገሩ ወንድ የለም እንዴ?' ስትል ጮኸች፡፡ እውነቱን ለመናገር የርሷ ስሜት ሁላችንም ውስጥ ስለነበረ በቃ፣ ከአቅድ ውጭ፣ ለሽፋን የተመደበው የኛ ቡድን ከመንግሥቱ መኪና ጀርባ ደርሶ በዘፈቀደ ተኩስ ከፈተ፡፡ አራተኛ ከፍለ ጦር ግቢ ደርሰን ስለነበረ መንግሥቱን እልመን ልንመታው ግን አልቻልንም፡፡ ከዚያ በኋላ አብሪው ጓድ ለምን ምልክት እንዳላሳየ ተጠየቀ፡፡ 'አሳይቻለሁ፣ ነገር ግን ከፊት ለፊቴ መኪና ገብቶ ከለለኝ' አለ፡፡ ሙቺው ጓድ ሲጠየቅ ደግሞ 'ምልክት የሚያሳየኝ አጣሁ' አለ፡፡ በቃ፣ እምስተኛው ሙከራችን እንዲህ ሆኖ ከሸፈ፣ ምን ታደርገዋለህ...፡፡" ቁጭት እንገበገበው፡፡

"ኤዲያ፣ መንጋ ቦጭቧጫ! ፈርቼ ነው ቢል ሊዋረድ ሆኖ ነው?!" ሽዋዬ ንድድ ብሏት ጣልቃ ገባች፡፡

ነገሩ በዚህ ቢያበቃ ባልከፋ ነበር፡፡ ይህ በፓርቲ ደረጃ የተደረገ ሙከራ መክሸፍ የኢሕአወሊን አመራር አበሳጨ፡፡ የሊጉ ታጣቂ ከንፍ በሦስተኛው ቀን ለሌላ ግድያ ተንቀሳቀሰ፡፡ "የአዲስ አበባ ሕዝብ አደባባይ ወጥቶ የግድያ ሙከራውን አወገዘ" በተባለ በማግስቱ መሆኑ ነው፡፡ አራት የመኢሶን ወጣት ሊግ መሪዎችን በጠራራ ፀሐይ ድባን አደረጋቸው፡፡ ታጣቂው እንድም እባሉ ጉዳት ሳይገጥመው ተመልሶ መጣ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ ግድያ የፖርቲያችን የሙሉ ጊዜ ሥራ ሆነ፡፡

"እስቲ ተመልከት፣ ኢሱ..." አልኩት ኢሳያስን በዚያው ቀን ምሽት፣ "...ጓድ ተስፋዬ ፍልስፍና ነው ያጠናው፡፡ ዘርው ደ'ሞ ኢኮኖሚክስ፡፡ 'እንዴት ግለሰቦችን እድነብቶ በመግደል ወደ ሥልጣን መውጣት ይቻላል' ብለው አሰቡ?"

"ተወው ሰመሬ፣ ከእነርሱማ መሀንዲሱ ጌታቸው ማሩ ተሻለኝ፡፡ የፖለቲካ ቢሮውን ድርሳን ብታየው የሐሳብ ልዩነት አስመዝግቧል፡፡"

"ምን ብሎ? 'ከደርግ ጋር ተባብረን መሥራት አለብን' የሚለውን ጅላጅል ከርከሩን እንዳይሆን..."

"አይደለም፣ አይደለም...ልክ የእኔንና የአንተን አቋም ነው ቃል በቃል ያስመዘገበው፡፡ 'የፓርቲውን አመራር ጨምሮ የከተማ ታጣቂ ከንፉ ወደ ገጠር መውጣት አለበት' ብሎ ነው የጻፈው፡፡ ግን ምን ዋጋ

አለው! በጣም የዘገየ ከርከር ነው። በዚህ ላይ የጌታቸው ተደማጭነት አሁን አፈር በልቷል።"

ኢሳያስ እውነቱን ነው። ጌታቸው "ትኩረት ለገጠሩ ትጥቅ ትግልና ለኢሕአሠ ይሰጥ!" ብሎ በራሱ እጅ ነው የጻፈው። ችግሩ ጌታቸው በተለይ ለፍስሀ ገብረሚካኤል መታሰር የዋህ ሰበብ በመሆኑ እኔን ጨምሮ ሌሎችም ቅር ተሰኝተንበታል። ከዚህ አልፌ "ምናልባት መኢሶን ጠልፎት ይሆን?" የሚለውን የአንዳንዶቹን ጥርጣሬ ግን አልቀበለውም። ይህ አንድም ጌታቸው ማኅሩን አለያም መኢሶንን ጠንቅቆ አለማወቅ ነው። ይህ ብቻም አይደለ። ጌታቸው ይህንን ቢያደርግ ኖሮ ማናችን ነን አሁን በሕይወት የምንገኘው?

###

የኢሕአወሊ ታጣቂ ከንፍ የመኢሶንን ወጣት ከንፍ መሪዎች በገደለ በሁለተኛው ቀን ሌላ ፈተና ገጠመኝ።

አሥራ አንድ ሰዓት ሲሆን የገቢ ድርሻቸውን ለመስጠት ወደ ወይዘሮ ማስተዋል ሄድኩ። ቢታኒያና ሚካኤለ ከእናታቸው ጋር ዋናው ቤት ነበሩ። ገብቼ ከማስተዋል አጠገብ ሶፋ ላይ ተቀመጥኩ። ወደ ቢታኒያ ሳይ ዓይኖቿ ቅልብልብ ሲሉ ዐየሁ።

'የሆነ አንድ እኔን የሚያበሳጭ ነገር ልታደርግ ነው ማለት ነው!' ስጋት ገብቶኝ እንደገና ሳያት ከሚካኤለ ጋር ወሬ ይዛለች።

ብሩን እያስረከብኳቸው እያለ ሙሴ ባልዲ መጣ። ሞቅ ያለው ይመስላል። እንደገባ ተወርውሮ የወይዘሮ ማስተዋልን ጉልበት ሳመ። እኔንና ቢታኒያን ደግሞ እጆቻችንን ግልብጥ እያደረገ ሳመ። ገና ቁጭ ብሎ ወሬ ሳይጀምር መሳሳቅ ተጀመረ። ቤቲ ምግብና ጠላ አመጣችለት። ገና መመገብ ሳይጀምር ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ቅልስልስ እያለ ወደ ወይዘሮ ማስተዋል ተጠጋ...

"ማዘር፣ ዛሬ በቁም ነገር አንድ ውለታ እንዲውሉልኝ ልለምንዎ ነው የመጣሁት።"

"እንዴት ያለ ውለታ፣ ሙሴ ባልዲ? ቁጭ ብለህ እየበላህ ካልነገረከኝ ግን አልሰማህም..."

"ግዴለም፣ማዘር...አጭር ነገር ናት። እሽ ሲሉኝ እቀመጣለሁ። ዛሬ በቀበሌ ሥራ የሌላችሁ እየቀረባችሁ ተመዝገቡ ተብለን ሄጀ ነበር። 'አብዮት ጥበቃ ለሚባል ሥራ ልንቀጥራችሁ ነው አሉን። ግን 'በቀበሌው ነዋሪ መሆናችሁንና በመንግሥቱ ኃይለማርያም ላይ የተሞከረውን ግድያ አውግዛችሁ

ሰልፍ መውጣታችሁን ሦስት የታወቁ የአካባቢውን ሰዎች ካስመሰከራችሁ ነው መመዝገብ የምትችሉት ተብለናል።' ጋሽ ገረመውንና ኑረዲን ዳቦን ለምን እሽ ብለውኛል። እርስዎ ሦስተኛ ሆነው እንዲመሰክሩልኝ ልለምንዎ ነው የመጣሁ..."

'እሆሆ...እንድ ነገር አለ፣ ጠንቀቅ በል ኢሕአፓ!'

ሙሴ ባልዲ ሲናገር ከወይዘሮ ማስተዋል ይልቅ ቆቅ ሆኜ ጆሮዬን የቀሰርኩት እኔ ነበርኩ። ወዲያውኑ ወደ አእምሮዬ የመጣልኝ የሻለቃ መንግሥቱ የሚያዚያ ወር ንግግር ነው። "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደሞክራሲያዊ አብዮት መሰስተኛ ፕሮግራም"። ብርክታዊት ደግማ ያነበበችው ጊዜ ቃል በቃል ሰምቼዋለሁ። አንቀጽ 13 ይመስለኛል...

"በዘኔው ክፍል በአብዩቱ ተጠቃሚ የሚሆንበትና መልሶም አብዮቱን የሚጠቅምበት ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል።"

የነገሩ መነሻ ዋነኛ ምንጭ የካርል ማርከስ "የመገለል" ሀልዮት (ዘ ቲዩሪ ኦቭ አሊኔሽን) ነው። በማርከስ እምነት "የሕብረተሰብ እድገት ታሪክ ከጥንታዊው የጋርዩሽ ሥርዐት በኋላ ሥርነቀል ለውጥ አሳይቷል። የግል ሐብት ባለቤቶችና ሐብት አልባ ድሆች የሚፈጠሩበት አዲስ ክስተት ሆኗል። ሰው የተፈጠረው በሥራና ለሥራ ሆኖ ሳለ ጥቂቶች ብዙዎችን ከሥራ ሂደት እየገፉ ያገለሉበት ታሪክ ነው። ይህ በካፒታሊዝም ከፍተኛ ደረጃ ይደርስና ሥራ እጥ ሠራዊት ይፈለፍላል። ችግሩን የሚፈታው ሶሻሊስት አብዮት ነው።" ሲል ይከራከራል። ደርግና መኢሶን ይሄንን ችግር በዚህ ፕሮግራም መፍታታቸው ነው። ሻለቃ መንግሥቱ ሐሳቡን ከኃይሌ ፊዳ ወስዶት መሆን አለበት።

'ነ--ገ--ር መ---ጣ!' አልኩ ለራሴ በውስጣዊ ሲጋት ከመጠን በላይ ተውጬ።

ሌላም ምክንያት አለኝ። ፋሽዝም በኢጣሊያና ናዚዝም በጀርመን ወደ ሥልጣን የመጡት በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ነው። ለድላቸው ትልቁን አስተዋፅኦ ያደረገላቸው ይህ ደርግ "ቦዘኔ" ያለው የሕብረተሰብ ክፍል ነው። የካፒታሊዝም የተንሸዋረረ እድገት በሁለቱም አገሮች ቦዘኔውን እንደ አረም አባዝቶት ነበር። ሂትለርና ሞሶሎኒ ሕይወቱን ሊለውጡሉት ቃል ገቡለት። ከልብ ደገፋቸው ብቻ ሳይሆን ከፊት ለፊት ሆኖ ተዋደቀላቸው። በዚህ ቀመር ስንሄድ የደርግ ፕሮግራም ቦታው የት ነው? ከካርል ማርክስ ይልቅ ለፋሺዝም በእጅጉ የተጠጋ ነው። በሌላ የሥራ ፈጠራ መስከ ሊፈታ ይገባ የነበረው ችግራቸው ጠበንጃ ይዘው ምንዳ እንዲያገኙ ተደርጎ ሊፈታ እየተሞከረ ነው። ኢላማው ያለጥርጥር ኢሕአፓ ነው። ይህ ነበር ሲጋት የለቀቀብኝ።

"እይ ሙሴ፣ ይሄማ ምን ችግር አለው? አንተ ለቁም ነገር ብቃ እንጂ እኔ እናትህ ማለት ነኝ። አንድ አፍታ ብቅ ብዬ መስከረልህ እመጣለሁ።... ነገ ከቤተክርስቲያን እንደተመለስኩ መጥተህ አስታውሰኝ።" አሉት ወይዘሮ ማስተዋል።

ሙሴ ባልዲ በደስታ ጉልበታቸውን ሳመ። በሀያ አራት ዓመት ዕድሜው ገና ከልጅነቱ ጀምሮ በ "ዱርየነት" ያሳለፈውን ውጣ ውረድ ይነግረን ጀመር። የሐሽሽና የቁማር መዘዝ...የሲጋራ፣ጫትና መጠጥ ሱሱ...የስርቆት ኑሮው ስቀቀን...እስር ቤት መመላለሱ...የፖሊስ ጥፊና ስደፍ...የፍርድ ቤት ዘለፋና ቅጣት...ከሌሎች ሴቦች ጋር እርስ በእርስ መካካድና መደባደቡ...የቀረው የለም። አንዳንዱ በሳቅ ፍርስ ያደርገናል።

"አሁን ዕድሜ ለመንግሥቱ ኃይለማርያም አስታዋሽ አገኘን። ይህችን ለዕለት ጉርሴ ካገኜሁ፣ ማማ ማስተዋል፣ ዱርየነት ደህና ሰንብት። ሁሉንም ከፉ ለማዶቼን ጠብ አርግፍ አድርጌ ትቼ በትዳር መኖር..."

ሙሴ እያወራ የእኔ ጭንቅላት ግን አሁንም በደርግና በመኢሶን አደገኛ ፕሮጀክት ትንተና ላይ ነው። ሥራ አጥ ከመሆን አልፎ በዐዘኔነት ያደገው ወገን እንኳንስ ለአብዮት ጠባቂነት ይቅርና ለጉልበት ሥራ ቢፈለግ እንኳን መጀመሪያ መሠራት ያለበት ትልቅ ተግባር አለ። ጥልቀት ያለው የሰብአናና የሥነልቦና ተሀድሶ ትምህርት። "ተገልሎ በችግር የቆየ ነው" ማለት ሌላ ማለት አይደለም። ሕብረተሰቡ የራሱ አካል አድርጎ አይመለከተውም ነበር ማለት ነው። ያለበቂ ሥልጠና ይሄንን ወገን መሣሪያ ማስታጠቅ "የበደሉህን ተበቀል" ከማለት ውጭ አይሆንም። የድርጅቴ መሪዎች ስለጉዳዩ መረጃ ይኑራቸው አይኑራቸው አላውቅም። እንደምነግራቸው በልቤ ማስታዋሻ ያዝኩ።

"ማዘርዬ፣ የቆንጆዋ የቢታኒያ እናት! እግዜር ይጠብቅልኝ!" ሙሴ የምግብ እቃውን ወስዶ ትልቅ ገበታ ውስጥ አስቀመጠ።

በአነጋገሩ ቢታኒያ እንድታሳስቀኝ አንገቴን አስግጌ ተቀምጣበት ወደ ነበረው ቦታ አየሁ። ወንበሯ ላይ የለችም። ከጣሪያው የወረደ ድንጋጤ ዝም ብሎ ጓ አደረገኝ። ብድግ ብዬ ወጥቼ ወደ ቢታኒያ መኖሪያ ከፍል ሄድኩ። በሩ ገርበብ ብሏል፣ ከፍቸው ገባሁ። ደብዛዋ የለም። ሽቶ ነገር ያውደኛል። ለብሳው የነበረውን የአረፍት ልብስ ቀይራ አልጋው ላይ ትታዋለች። ያን መዘዛኛ ትልቅ ቢጫ ቦርሳ በዐይኔ ፈለኩት። በዘውትር ቦታው ላይ የለም። ተመልሼ ስወጣ ሚኬኤለ ወደ እኔ እየመጣ በሩ ላይ ተገጣጠምን።

"ቤቲ የት ሄደች?" እሱ ጥፋተኛ እንደሆነ ሁሉ እፈጠጥኩበት።

"እኢ...ስመረ ከጠየቀህ ቀጨኔ አካባቢ ሄጃለሁ በለው ብላኛለች።"

"ቀ–ጨ–ኔ?" ለዓመታት አሳምሬ የማውቀው ቦታ ከአእምሮዬ መዝገብ ሊሰወርብኝ ፈለገ።

ወደ ጋራዥ ከነፍኩ። ላንድሮቨሯን አስነስቼ ስወጣ የመኪናው ውስጥ ሰዓቱ 12፡10 ይላል። ቀጨኔ ሰፊ ነው። የት ብዬ እንደምፈልጋት አላውቅም። በደመነፍስ እንዲሁ ወጥቼ አስፋልቱን ያዝኩ። የኑረዲንን ዳቦ ቤት ሳልፍ ደጀኔ ከተቃራኒ አቅጣጫ በሞተር ብስክሌት አልፎኝ ሄደ። ግድያ ካለ እሱ እዚህ የተገኘበት ምክንያት አልገባህ አለኝ። ነገር ግን የገዳይ ቡድኖችን አደረጃጀት በደንብ አላወኩም። የማወቅ ፍላጎቱም የለኝም። ንጭንጭ አልኩ...

'ወይኔ፣ ፍቅረኛዬን የእሳት እራት አደረጉብኝ!' ፍጥነቴን ጨመርኩ።

ቀጨኔ ደርሼ ቢታኒያን በሆነ ተዐምር ባገኛት እንኳን ምን እንደማደርግ አላውቅም። ጣልቃ ገብቼ ከተልእኮ ባስወጣት ቀጥታ አንጀኝነት ይሆንብኛል። አይቼ እንዳለየሁ ዝም ብል ደግሞ ልትሞትብኝ ነው። አስከሬን ፍለጋ የምሄድ ሆኖ ተሰማኝ። የድርጅቴ "አድብቶ መግደል" ብዬ የሰየምኩት ጥቃት ጭንቀት የለቀቀባትን አዲስ አበባ እያቅራረጥኩ ቀጨኔ ደረስኩ። ያልገባሁበት፣ ያልወጣሁበት፣ ያልተሽከረከርኩበት...ውስጣ ውስጥ የለም። ሳስበው ቢታኒያ የሄደችበትን ቦታ በትክክል ትነግረኛለች ብዬ ማሰቤ ማም ቂሎ እንደሆንኩ ዓይነት ሆኖ ተሰማኝ። ቀጨኔን ለቅቄ ወደ ስድስት ኪሎ ስነዳ በደንብ መሽቶ የመንገድ መብራቶች በርተዋል። አልፎኝ የሚሄደውን መኪና ሁሉ ቢታኒያን የጫነ እስኪመስለኝ ድረስ አይኖቼ ይንከራተታሉ።

"ዛሬ ቀፎኛል፣ ፍቅሬ በሰላም የምትመለስ አይመስለኝም..." አልኩ ድምጽ አውጥቼ።

እቅሌን ከመሳቴ የተነሳ መንገድ የምዘጋባቸው ተሽከርካሪዎች ጥሩንባቸውን ያስጮሁብኛል። የካቲት 12 ሆስፒታል ጀርባ ስደርስ በአስከሬን መውጫው በኩል ለቅሶ ላይ ያሉ ሰዎች ታዩኝ። ወደ አራት ኪሎ ታጠፍኩ፣ ቢታኒያ ዘሯ የለም። ስናውዝ አምሽቼ ተስፋ ስቆርጥ ወደ መሳለሚያ አመራሁ። ጋራዥ ገብቼ አንድ ደቂቃ እንኳ አልቆየሁም። እየተንደረደርኩ ቀዩን በር ከፍቼው ገባሁ። የቢታኒያ ቤት መብራቱ በርቶ በሩ መለስ ብሏል።

'ቤቲ ሆዬ...ቤቲ ፍቅሬ...አለች ማለት ነው! አለች ማለት ነው!' እግሮቼ እስርስር ሊሉብኝ ፈለጉ።በሩን ከፍቼው ስገባ ከመጀመሪያው ክፍል አልጋ ላይ ጋደም ብላ አገኘኋት። ቆሜ ሳፈጥባት በቅልጥፍና ብድግ አለች...

"ሰሙዬ፣ ሆዴ፣ እንዳትቆጣኝ...ና ልሳምህ...ዛሬ የፍቅር ሌሊት ነው..." ብላኝ እጄን እየጎተተች ወደ አልጋው ጎተተችኝ።

***

ጉለሌ...

የመግቢያ ኮዴን ለዘበኛው ነግሬው ገባሁ። የቪላ ቤቱ የፊት ለፊት በር ሁሌም ዝግ ነው። በጀርባ በኩል ስሄድ ድምጽ ተሰማኝ። ዘርዑና ከፍሉ ታደሰ በበረንዳው ደብዘዝ ያለ የአምፖል መብራት ይታዩኛል። ዘርዑ ጠረጴዛ ተደግፎ ቆሟል። ከፍሉ ደግሞ ዱካ ላይ ቁጭ ብሎ ሲጋራ ያጤሳል። ዘርዑ ድምጹን ዝቅ አድርጎ በስሜት የሚያወራው ነገር አለ። ሞቅ ባለ ሰላምታ ተቀብለውኝ ከዘርዑ አጠገብ ባገኘሁት ታጣፊ የእንጨት ወንበር ላይ ተቀመጥኩ።

"አላምረው፣ ስለ ሻለቃ መንግሥቱ የሰማነውን እያወራሁት ነበረ።" አለኝ ዘርዑ ሳቁን እየታገለ።

"ም-----ን፣ አዲስ ነገር አለ እንዴ?" 'ሕክምና ላይ እያለ ሕይወቱ አለፈ የሚለኝ' መስሎኝ ዓይን ዐይኑን ዐየሁት።

"መንግሥቱ ደርግ ስበሰባ ላይ መቼም ተራራን ታግሎ የሚገፋ የጀግና ጀግና ሆኖ ነው እሚያወራላቸው። የቆሰለ ዕለት ከመኪና ሲወርድ ያዩት ሰዎች ግን አፈሩ። የመኪናውን በር ሲከፍቱለት እንደ ጨርቅ አጥፍጥፍ ብሎ ወንበር ሥር አገኙት። ሽጉጥ አልያዘ ምን አልያዘ።ሽጉጡ የወደቀበትን ቦታ ፈልገው ሾፌሩ እግር ሥር ነው ያገኙት። እና ፊቱ በፍርሀትና በድንጋጤ አመድ ወርሶት ደግፈው ሲያወርዱት 'ሞቻለሁ፣ አልሞትኩም?' እያለ ይጠይቃቸው ነበር አሉኝ..." ከት ብሎ ሳቀ።

ከግድያ ሙከራው የፖለቲካ ትርጉም አንጻር ሳየው የዘርዑ ወሬ ተራና ተልካሻ ሆነብኝ። ምናልባት እንደድሮው ቢሆን ኖሮ በአድርባይነት አብሬ መሳቄ አይቀርም ነበር። ፈገግም አላልኩ። እንዲያውም መሪዎቼ ምን እያደረጉ እንደሆነ አልገባ ብሎኝ ለራሴ ጥያቄ አነሳሁ። 'በዚህ ዓይነት "አጥቅቶ መከላከል" የሚሉት ነገር ትርጉሙ ቀልድ ሆኗል ልበል? በቃ፣ ዋና ትርጉሙ እንዱ ደርግ ወይም የመኢሶን ካድሬ በእኛ ጥይት ተመትቶ እንዲህ ሲሆን ማየት ነው ማለት ነው?' ሀዘኑ ከበደኝ።

የድርጅታችን የአስተሳሰብ ደረጃ ዘቅጦ ታየኝ። ሁኔታው ያስታወሰኝ ደራሲ ጀምስ ዊሊያምን ነው። እሱ እንደሚለው፣ "በጣም ብዙ ሰዎች ጭንቅላታችንን እሠራነው የሚሉት ለሌሎች ሰዎች ያላቸውን

የውስጥ ጥላቻ ሲያብሰለስሉ ነው።"

'እዎ፣ በእነ ዘርዑ አመራር ኢሕአፓ የጥላቻና የበቀል ተቋም ሆነ!' ውስጤ ጋየ።

ቢታኒያ በዐይነህሊናዬ ታየችኝ። 'በንጹህ ህሊና ለድርጅቷ ደፋ ቀና የምትለው፣ ነገር ግን፣ ከተፈጥሮ የሕልውና ምንጪ እፈንግጣ ያመጸችው የሱፍ አበባ ህያው ተምሳሌት!' ብቻ እንኳን አልሞተችብኝ። ሐቁን አንድ በአንድ ዝርዝር አድርጌ እነግራታለሁ። መሪዎቻችን በትክክል የፎኮይዝምን መንገድ ተከትለው በድርጅቱ ላይ ምድር ተገረፌ መቅሰፈት እየጠሩ መሆኑን እሳምናታለሁ። ከመሪዎቼ ጋር አብሬ መቆየት ይቅርና መገናኘታችንም ራሱ ሊያስጠላኝ ተፈታተነኝ።

"የዛሬን ገቢ ልሰጥህ ነው የመጣሁት..." አልኩት ከፍሉን በድርጅት ስሙ ጠርቼ።

አንድ ጠንካራ ጎን አላቸው። መኮፈስና መጀነን አልፈጠረባቸውም። ብሩን ቆጥሬ ሰጥቼው ውልቅ አልኩ። መሳለሚያ እስከምደረስ ይሄንኑ እያነሳሁ እየጣልኩ ነዳሁ። ኦረዲን ዳቦ ቤት ስደርስ ከዳቦ ቤቱ ፊት ለፊት ሽራ ማክ የወታደር መኪና ቆሟል። የጉልበት ሠራተኞች ይሯሯጣሉ። በኩንታል በኩንታል የታሰረ ፉርኖ ዱቄት ከዳቦ ቤቱ እያወጡ መኪናው ላይ ይጭናሉ። ከማክ መኪናው ጀርባ ትንሽ አለፍ ብሎ ያለው ቦታ ጭለማ ነው። የመንገድ መብራቱ ተበላሽቷል። ግርግሩን ሳይ አዛው ቆምኩ...

'ይሄ ረብሻ የለመደ ቦታ...'

ቀበቶ የሌለው ወታደራዊ ቁታ የለበሰ ጎልማሳ በሰዎች ተከቧል። መለዮ ስላልደፋ የጭንቅላቱ በርሀ ይታየኛል። በግራ እጁ የሆነች ሴትን ቀኝ እጅ ግጥም አድርጎ ይዟል። በረጅም ቁመናው ስለከለላት ሴቷ በደንብ አትታየኝም። የዳቦ ቤቱ ባለቤትና ሌሎች ሠራተኞቻቸው አብረው አሉ። ከሁኔታቸው ሽምግልና የያዙ ይመስላል። ጆሮዎቼን ወደዚያው ቀሰርኩ...

"በምንም ተዐምር አለቃትም። የመንግሥት ንብረት ሳታስረክብ ጠፍታ ባለ እዳ አድርጋኛለች። ወንጀለኛ ናት!" ይጮኻል።

"በሕግ አምላክ! የትም አላውቅህም፣ ልቀቀኝ!" እጇ የተያዘው ሴት ትመልሳለች።

ዝም ብሎ ቅፍፍፍ አለኝ። የሴቷን ድምጽ የማውቀው መሰለኝ። ከመኪና ወርጄ ወደ ግርግሩ ትንሽ ጠጋ አልኩ። ግምቴ ትክክል ነው። ሽዋዬ ዳቦ ልትገዛ መጥታ እያለች ተይዛለች። ወደ ማክ መኪናው ዐየሁ። ሾፌሩ በጸጥታ ተቀምጦ እንደማንኛውም ሰው ትርኢቱን ይመለከታል። የሸዋዬን እጅ የያዘው ወታደር

ጤነኛ አይመስልም። ሳይጠጣ አልቀረም። ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ሳብሰለስል ከሥጋ ቤቱ በር በግራ በኩል ከነበረ ደብዘዝ ያለ ቦታ አንድ ሰው ወደ እኔ ሲመጣ ታየኝ። ትኩር ብዬ ሳየው በአካሉ ቅርጽ ዐወኩት። ደጀኔ ነው። ወዲያውኑ ደኅንነት ተሰማኝ።

"አላምር፤ የመኪናህን የጀርባ በር ከፍተህ ተወው!" ሹክ ብሎኝ ተመለሰ።

ምን ማድረግ እንደፈለገ አላውቅም። ሄጄ ከፍቼ መሪ ወንበሬ ላይ ቁጭ አልኩ። ደጀኔ በየት በኩል ሄዶ ወታደሩን እንደመታው አላየሁም። ወታደሩ መጋኛ እንደመታው ሰው በደረቱ ተዘረረ። የከበበው ሰው በርግጎ ቦታውን ሲለቅ ደግሞ ደጀኔና ሽቀዬ የት እንደተሰወሩ አላየሁም። ከጀርባየ ድምጽ ሲሰማኝ ብቻ ዘወር አልኩ። በሰላም ደርሰው ተሳፍረዋል። መኪናዋን አዞሬ ወደ መናኸሪያ አቅጣጫ ተፈተለኩ…

# 29

አዲስ አበባ መስከረም ከጠባ ጀምሮ ያጣችውን ሰላም መልሳ አላገኘችም። በቀላሉ የምታገኘውም አትመስልም። ለዚህ ብዙም የማይጨነቅ የሚመስለው ጊዜም ወደፊት እየቀዘፈ መሸምጠጡን ቀጥሏል። መስከረም የመጨረሻ ሳምንቱን በር እያንኳኳ ነው። ባለፈው ሳምንት ሻለቃ መንግሥቱ የኢሕአፓ ጥይት ያልጎዳቸው መሆኑን በቴሌቪዥን ለሕዝቡ ገልጸዋል። ይህ የቀሰቀሰው የሕዝብ አስተያየት አሁንም አየር ላይ ነው። ሙከራው መደረጉ ካልቀረ አስተያየቱ ለእኛ ጠቃሚ ነበር። በጥቃቅን ሥራዎች በመዋጣችን ግን ሳይሠራ ጊዜው እያለፈ ነው። ይሄንን ሳስብ ትዝ የሚሉኝ ወይዘሮ ማስተዋል ናቸው። ማታ ቡና እየተጠጣ እያለ የሻለቃ መንግሥቱ ምስል ቴሌቪዥን ላይ ብቅ አለ...

“በጣም ደህና ነኝ። አነስተኛ ጉዳት ነው የደረሰብኝ። ብሞትም እንኳን እኔ አንድ ግለሰብ ነኝ...” አሉ ቆመው።

“እንተማ ምን ታደርግ?!” ማስተዋል ግልፍ ብሎባቸው መናገር ጀመሩ፣ “የተኮሱብህ ይሄ ከስከርቢቶ በስተቀር ጠበንጃ ጨብጦ የማያውቅ መንጋ ቂጣ እጅ ሁሉ ነው። እንዴት አትተርፍ፣ ትተርፋለህ እንጂ...። እንኳን ሰው ከር በውርርድ የሚበጥሰው የመርሐቤቴን ጀግና ቢጥልብህ ኖሮ እንዲህ ለማለት አትበቃትም ነበር። እ——ይ፣ ተ—ማ—ሪ!” አማረሩ።

ጉዳቸውን ስለማያውቁ ቢታኒያ በሳቅ እየተንከተከተች ትስማቸዋለች።

እኔና ኢሳያስ ምሽት ላይ ከጋራዥ ወጣን። ሸዋዬ ሁለታችንም የምንወደውን ቦቆልት አዘጋጅታልናለች። ብቻችንን በእሱ መኖሪያ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብለን በቆልቱን እየበላን እንሠራለን። ደጀኔ እንደሰምኑ ውሎው አሁንም የለም። በኔ በኩል ባለፈው ሳምንት የጀመርኩትን የፖሊት ቢሮውን ድርሳን የአርትኦት ሥራ ተያይዤዋለሁ። ኢሳያስ ደግሞ የመኢሶንን “የሰፊው ሕዝብ ድምጽ” ጋዜጣ የወቅቱን እትም በተመስጦ ያነባል። ጋዜጣውን አላነበብኩትም። ትኩረቱ ምን እንደነበረ ግን ነግሮኛል። በሻለቃ መንግሥቱ ግድያ

ሙከራና በመኢሶን ወጣት ሊግ መሪዎች ግድያ ላይ አተኩሯል። በብስጭት ኢሕአፓዎችን ጥንብ እርኩሳችንን እያወጣ እንደ ጉድ አብጠልጥሎናል።

"ፎኮይዝምን ማራመዳችን እውነት ከሆነ ይሄ እንዴት ይነሰን?" አልኩት መልሼ።

"ትክክል ነህ፣ ይሄው በግድያ ሙከራው የኃይል ሚዛኑ እየተለወጠ ነው። የኪውባ፣ የጀርመን፣ የሩማኒያና የሶቪየት ኮሚኒስት ፓርቲዎች እኛን አውግዘው ሻለቃ መንግሥቱን 'አጋራችን ነህ' ብለውታል።" ጎላ ብሎ የተጻፈውን የዜናውን ርእስ አሳየኝ።

በመሀሉ ሸዋዬ ከማብሰያ ቤቷ ደርደር ብላ መጥታ ገባች። በቀኝ እጇ እፈሙዙ ቁልቁል የተዘቀዘቀ ማካሮቭ ሽጉጥ ይዛለች። ጊዜ ሳትሰጠን "ምድር ቤት፣ ምድር ቤት ሂዱ!" በከፊል ትእዛዝ አዋከበችን። እርስ በእርሳችን ተያይተን ወደ ምድር ቤት ወረድን። ወዲያው ከጀርባችን በሩ ተንኳኳ። ሽጉጥ ለማውጣት ጊዜ ሳናገኝ ደረጃው ላይ እንደደረስን በደጀኔ ከፍል ውስጥ ድምጽ ተሰማን። ሳናስበው ሁለታችንም ቀጥ ብለን ቆምን። 'አንድ ነገር አለ!' በዐይኖቻችን መልእክት ተለዋወጥን። ወዲያው የሸዋዬ ድምጽ ተሰማን። መታገስ አልቻልንም፣ ተመልሰን ወደ ኢሳያስ ከፍል ሄድን...

የመጣው ሰው ጌታቸው ማሩ ነው። ሲስቅ ከማወቃችን በስተቀር ድንገት በማየት መለየት አይቻልም። አለባበሱን ቀይሮ የስልሳ ዓመት አዛውንት መስሎ ነው የመጣው። በጣም ችሎብታል። ከሰላምታ በኋላ አንድ ሁለት የበቆሎት ፍሬዎችን አንስቶ ወደ መጣበት ጉዳይ ገባ...

"ጓዶች፣ እንዴት ነው የድርጅታችንን ነገር እያያችሁት ያላችሁት?" ተራ በተራ ዐይኖቹን አፈራረቀብን።

"እንዴት ማለትን" ልቤ እያወቀ በይሉኝታ ብቻ መልሼ ጠየኩት።

"ይሄ 'እጥቅቶ መከላከል' ብለው የጀመሩትን ቀልድ ገፉበትኮ። የእናንተን አቋም ስለማውቅ በግሌ እንመካከርበት ብዬ መምጣቴ ነው። መኢሶኖች እኛን እያጠቁ ያሉት የእኛዎቹ ሰዎች እጋነው የሚያወሩትን ያህል አይደለም። ለዚያውም የእኛ አባላት በየስብሰባውና በየሰልፉ ለሚቀሰቅሱት ረብሻ በቂ አጸፋ አልሰጡም። እየተነኮስናቸው ያለነው እኛ ነን። አሁን ደግሞ የመኢሶን አመራሮች መርካቶ በሚያደረጉት ስብሰባቸው ላይ በቦንብ አንድ ላይ ሊያጠፏቸው እያሴሩ ነው።"

እኔ፣ ኢሳያስና ሸዋዬ በድንጋጤ እርስ በእርስ ተያየን። ለአፍታ የሰፈነውን ጸጥታ የገሰሰው ኢሳያስ ነበር...

"ምንድነው ይሄ ሁሉ ነፍስ ግድያ? ለመሆኑ ብርሃነመስቀል ያፈጠር ያለው ፍርድ ሰጭ አካል ተቋቁሞ ነው የሚወስነው ወይስ ወታደራዊ ኮሚሽኑ ብቻውን ገፋበት? ምንድነው ያደረጋችሁት?"

"ሆሆሆ... ው፣ የምን ፍርድ ቤት... የምን ኮሚሽን አመጣህ? እስከ አሁን በኮሚሽን ስም ውሳኔውን

የሚሰጡት ሁለት ግለሰቦች ናቸው። ጓድ ተስፋዬና ጓድ ዘርዐ ብቻ። ከበቀደም ወዲህ ደግሞ ሥልጣኑን ለበይነቀጠና ኮሚቴ ሰጥተውታል። 'ከአሥራ አምስት ቀን በፊት ዐሳውቃችሁ እርምጃ መውሰድ ትችላላችሁ' አሏቸው። አንዳንድ በይነቀጠናዎች ትእዛዙን አከበሩ። ሩቅ የሆኑት ግን ምንም ሳያሳውቁ እየገደሉ ነው። ጎንደር ሰባት ሰዎች...ወሎ አራት...ሲዳሞ ስድስት ሰዎች ተገድለዋል...።"

"ለመሆኑ የግድያው ምክንያት እኛ ስለተጠቃን አጸፋ መመለስ ነው ወይስ ከእኛ የተለየ ሐሳብ ያለው ሁሉ ጠላታችን ነው ማለታቸው ነው?" መጭው ጊዜ ሲያስፈራኝ እንዳልነበረ ሰው ሁሉ ጌታቸውን የጭንቀት ጥያቄ አነሳሁለት።

"ይሄማ ግልጽ ነው'ኮ፣ አላምረው። ፎክይዝም እየዋለ እያደረ ሲሄድ የሚከተል ባህርይ ነው። ሰላማዊ ሰዎችን 'ለምን ገላመጣችሁኝ' ብሎ መግደልም ይመጣል። ከዚህ ሁሉ መዘዝ ያመጣብናል ብዬ የፈራሁት ግን የነገውን ግድያቸውን ነው። አሥራ አራት ሰዎች መኢሶን ስለሆኑ ብቻ በአንድ በጉብ ሲገደሉ ነው። እና እናንተ ዝም ብለን እንይ የሚል አቋም ነው ያላችሁ?" ጠበቅ አድርጎ ጠየቀን።

"ምን አማራጭ አለ ታድያ? የራሳችንን ታጣቂዎች 'ተው' ብንል ድርጅታዊ ሥርዐት አልበኝነት ይሆንብናል። መኢሶኖችን በቦታው አትገኙ ብንል አሻጥር ወይም አንጃኝነት ይሆናል። ግድያው ይፈጸም አይፈጸም ተከራክረን በድምጽ ብልጫ ስለተሸነፍን አማራጭ የለንም። ትክክልም ባይሆን ዝም ብለን ማየት ነው ያለብን..." አሳያስ መለሰለት።

ሸዋዬ በጭንቀት ተውጣ ቆይታ ከወሬያችን ወጣ ያለ ነገር አነሳች...

"ኢሱ፣ በመርሕ ትክክል ነህ። ነገር ግን ግድያው በሚያመጣው ውጤት የማንጠቀም ከሆነ ለምን አንድ ነገር አናደርግም? ለምሳሌ፣ ለመኢሶኖች ዝርዝር መረጃ ባንሰጥ እንኳን ሌላ ዘዴ አለ። በከንቱ የሚገደልና የምናውቀው ሰው ካለ በደፈናው 'አትሂድ' ማለት ማንም አይከለክለንም። ይሄ ማኀበራዊ ጉዳይ ነው፣ ፖለቲካ አይደለም..." ፈርጠም አለች።

የሸዋዬ መፍትሄ ብዙ አላረካኝም። አንድ ነገር እንዳስታውስ አደረገኝ። ብርከታዊት ትኖርበት ይሆን? ፍርሀት ደርሶ ሰፈረብኝ። አሁን ከጌታቸው ጋር የምንነጋገርበት መንፈስ በራሱ የአንጃኝነት ምልክት እንደሆነ አላጣሁትም። አንጃኝነትን በፍጹም የማልደግፈውና የማልሞክረው ጉዳይ ነው። ብርከታዊትን ሳስታውስ ግን የአንጃኝነትን ትርጉም የመከለስ ዝንባሌ አደረብኝ። 'የመኢሶን አባል ስለሆነች ብቻ ለምን ትገደላለች?' ጥያቄዬ መልሱንም ጭምር ይዟል። በረጅሙ ተንፍሼ ጌታቸውን ትኩር ብዬ እያየሁ ድንገተኛ መሆኑ በደንብ የሚታወቅ ጥያቄ አነሳሁለት...

"የሚገደሉትን ሰዎች በሥም ዝርዝር ታውቃቸዋለህ?"

"የመኢሶን መሪዎች ካልከ የሥም ዝርዝር አያስፈልግም። በአርግጥ እነ ዘርዑ ለግድያው የቋመጡት መስፍን ካሱ አብሮ ይገኛል ስለተባለ ነው። የሚገርምህ የጠቀሱበት ወንጀል አስቂኝ ነው። 'ኢሕአፓን ለማስመታት እቅድ ያወጣው እሱ ነው' ካሉ ይሄ በቂ ነበር። የሚሉት ግን 'መኢሶንን ለመጀመሪያ ጊዜ ከደርግ ጋር ያስተዋወቀ እሱ ስለሆነ ይመታ' ነው። ነገሩ ከቁጥጥር ወጥቶ ትክክለኛ ፎኮይስት መንገድ ይዟል የምላችሁም ለዚህ'ኮ ነው።" የጌታቸው ድምጽ በቅሬታ ቁልቁል ወረደ።

"እውነትከን ነው?" የራሴ ባልሆነ ድምጽ ጮኺ ወደ ሸዋዬ ዞር አልኩ፣ "በዚህ ዓይነትማ እነ ብርክቲንም አይለቋቸውም ማለት ነው'ኮ! ይሄማ ከፎኮይዝም ጭምር ወርዶ ተራ ነፍሰ ገዳይነት ነው!"

"ብርክታዊት የትኛዋ ናት? ጋዜጠኛዋን ናት?" ጌታቸው እንደቀልድ ሲጠይቀኝ "አዎ" አልኩት፣"እሷንማ እዚህ አናንተ ግቢ ያለችው ቆንጆዋ ልጅ አንድ የአሥራ አራት ዓመት ልጅ ይዛ ሄዳ ተራማጅ መጻሕፍት መደብር ውስጥ አስገድላት ተመለሰች አይደል እንዴ?!" አፉን አመለጠው።

ከሰማይ ድንገት የወረደ የዲን ዝናብ ምድርን አጨለማት። መርዶው የፈጠረብኝ ድንጋጤ ልቆጣጠረው የምችለው አይደለም። እቅፌ የሳምኩትና የተጣበኩበት የብርክቲ ንጹህ ገላ መጣብኝ። የምድር ሁሉ ትላትል ሰፍረው አመድ ሲያደርጉት...ቀስ በቀስ ሲጋዋ እየረገፈ አጥንቶቿ ባላ መስለው ሲቀሩ...ጥቁር ጸጉሯ በአፈር ተውጦ ሲበጣጠስ...ቁልጭ ብሎ ታየኝ። በአሳት ላይ ቤንዚን፣ የድሮዋ ፍቅረኛዬ የተገደለችው በአሁኗ የገዛ ፍቅረኛየ ጥይት መሆኑ ድራማ እንጂ እውን አልመስልህ አለኝ። ውስጤ ባዶ ሆኖ እንደ በርሜል ተንጓጓ። ሸዋዬና ኢሳያስ ግራ ተጋቡ። ጌታቸው የተናገረውን መርዶ የሚያስቀይሩበት ብጣሽ እድል አጥተው በድንጋጤ ያዩኛል። ጭንቅላቴ ከሥራ ውጭ ሆኖ አዞረኝ...

"ጓዶች፣ ምድር ቤት ወርጄ ትንሽ አረፍት ላድርግ..." ብድግ ብዬ እግሬን ማዘዝ አቅቶኝ ስወላገድ ሸዋዬ ደግፋ ይዛኝ ወረደች።

###

ባለፈው ሳምንት ቀጨኔ ሄጃለሁ ብላ ስታንከራትተኝ ያመሸሁበት ቀን...የካቲት 12 ሆስፒታል ለቅሶ... እጥፓት ስመለስ ቢታኒያ ዘና ብላ ያደረገችልኝ አቀባባል...ግጥምጥም አሉብኝ። ያ መዘዘኛ ቢጫ ቦርሳዋ መጣብኝ።

እንጀቴ ከሁለት በሦስት እጥፍ ጉምድምድ አለ። ይህ ልቦለድ ታሪክ የመሰለ ድርጊት የተፈጸመው በመቶ ሽህ የሚቆጠሩ ነዋሪዎች ባሉባት አዲስ አበባ ነው። "ጨርሶ የማይተዋወቁት ፍቅረኞቼ ተገዳደሉ" ብዬ ብናገር እስቲ አሁን ማን ያምነኛል? ፖለቲካ እንደ እስማት ነው። እጥፊንና ጠፊን ከየትም ከየትም አምጥቶ ያገናኛል። ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያምንና ጀኔራል አማን እንዶምን የውትድርና ዘመናቸው

አገናኛቸው። ፖለቲካ ገዳይና ሟች አደረጋቸው። ቢታኒያ እንኳን ብርኪቲን ሻለቃ መንግሥቱን ለመግደልስ ሄዳ ነበር አይደል?!

"ድርጅት ስጡንና ራሺያን እንገለባብጣታለን!" ሌኒን ጥሩ ብሏል። ኢሕአፓን በዚህ እምነት ተቀላቀልኩትና ወደድኩት፤ አሁን ግን፤ኢሕአፓ፤ "ድርጅት ስጡንና ኢትዮጵያ ን እንበጣብጣታለን!" ሆኖብኝ አረፈው።

የለውጡ ሂደት ሁለት ጉልህ ልዩነቶችን አሳየኝ። የመጀመሪያውና "ኢትዮጵያን ሊገለባብጥ" የተነሳው ኢሕአፓ የብርሃነመስቀል ኢሕአፓ ነው። ሁለተኛውና "ኢትዮጵያን ሊበጠብጥ" የተነሳው ኢሕአፓ የዘርዑ ክሕሸን ኢሕአፓ ነው። 'የመጀመሪያውን ኩነኔ የፈጸመ አእምሮ የሚቀጥሉትን ኩነኔዎች ቢፈጽም ድርሻው ነው። የሚገርም አይሆንም።' ሀዘኔ ከበደ።

ምን ያህል ጊዜ አልጋዬ ላይ እንደቆየሁ አላውቅም። ስገምት ግን ከአንድ ሰዓት ተኩል በላይ ይሆናል። ቢታኒያ በር በሩን እያየች መቅበጥበጥ ጀምራለች ማለት ነው። የመሄድ ፍላጎቴ ከዳኝ። አእምሮዬ ቢታኒያን ማሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ አሰፈራው። ይሄኔ እሷ ደግሞ ቀረ ብላ አያበደች ይሆናል። የፈራሁት ነገር አልቀረም፤ሸዋዬ እየተንደረደረች ስትመጣ ኮቴዋ ተሰማኝ።

"አንተ አላምረው፤" ትከሻዬን ይዛ ስትወዘውዘው ቀና አልኩ፤ "ትልቅ ሰው አይደለህ እንዴ? ፖለቲካ ምን እንደሆነ አዲስ ነገር ሆነብህና ነው ተመልሰህ ሕጻን ልጅ የምትሆነው?" በቁጣ ጮኸችብኝ።

"እ----ይ፤ ሸዋ... ትንሽ ልረፍ ብዬ ነው። ምነው ችግር አለ?" ዓይኖቼን እያሻሸሁ ተንተባተብኩ።

"ደ'ሞ 'ችግር አለ ወይ?' ትለኛለህ? ልጅቱን ወይ ቀድመህ 'አልምጣም' አላልካት፤ ተረበሸችኮ። አሁን ለሦስተኛ ጊዜ ነው 'ሳይረን' ያስጮኸችው። ይሄ ጊዜ ያመጣብን ፈተና ነው። የምትችው ሞታለች፤ ያለችውን አታስቃያት..."

ሸዋዬ ትክክል ናት። ብርኪታዊትና ቢታኒያ የት ይተዋወቃሉ? ያገናኛቸው ጠማማው ዐድርጅቴ ፖሊሲ ነው። ቢታኒያ ተልእኮዋን ተወጣች እንጂ ሕይወት አላጠፋችም። ራሴን አሳምኜ ከአልጋዬ ተነሳሁ። አንድም ቃል አልናገራትም፤ እንዲያውም ፍንጭም አላሳያት። ባይሆን ከዚህ በኋላ ከግድያ ተልእኮ የምትወጣበትን ጥያቄ እንድታቀርብ በብዙ መንገድ ላሳምናት እሞክራለሁ። ተነስቼ ወደ ላይ ቤት ወጣሁ። ጌታቸው ሄዷል። ኢሳያስ አልጋው ላይ ተጋድሞ ጋዜጣ እያነበበ ሲጋራ ያጤሳል። ተሰናብቻቸው ልወጣ ወደ በሩ ሳመራ መዝጊያው ከውጭ ተንኳኳ። ቆም አልኩ። ሸዋዬ በቅልጥፍና ከማብሰያ ከፍሏ ወጥታ መጣች.

"ደጀኔ ነው፤ ደጀኔ!!" ኮገራን ሄዳ ከፈተችው።

ደጀኔ ሲገባ ሌላ ሰው መስሎን ሁላችንም ደነገጥን። መላ ሰውነቱ በአመድ ተውጧል። የግራ ከንዱ በጀርባ በኩል ቢደም ተሸፍኗል። ሱሪው ከሁለት ተገንጥሎ ሙታንታው በከፊል ይታያል። እንደገባ ለዐመል ያህል ብቻ ሰላም ብሎን ወደ ማደሪያ ቤቱ ገባ። በግራ መጋባት ተውጠን ተከተልነው። 'አንድ ችግር አለ! "የአጥቅቶ መከላከል" ፖሊሲ መዘዝ...' የሁላችንም ልብ ይህንኑ እንደምታዜም ሳንነጋገር ተግባብተናል። ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ግጥም አድርጎ ይዞ መሬት ላይ አቀርቅሮ አገኘነው። ሸዋዬ አጠገቡ ተቀምጣ ታነጋግረው ጀመር...

"ደጄኑ፤ ሰላም አይደለህም፤ እንዴ? ምን ተፈጠረ?"

"ባከሽ፤ ተልእኮ ይዘን እየሄድን ነበር። በመሀል ፍቅሬ መርእድ የሚባለውን መኢሶን ሳናስበው የሆነ ቦታ አጋጠመን። ልናልፈው አልቻልንም። እሱን ገድለን ለማምለጥ ስንሞክር ቦታውን አናውቀውም። ዝም ብለን በደመነፍስ ወደ አንዱ ሰፈር ሮጥን። ምን የሚያከል ግንብ ከፊት ለፊታችን ተገትሮብን ቁጭ። ያው እኔ እንደምንም አመለጥኩ፤ ይትባረከ ሕዝቅያስን ግን ያዙት..."

"ይ---ትባ----ረከ ሕዝቅ---ያስ?" ሸዋዬ ከው አለች።

ይትባረከን ሁላችንም እናውቀዋለን። አንዳንዴ የዲሞክራሲያን ቅጽ ለመውሰድ ይመጣል። የኢሕአፓ የማእከላዊ ኮሚቴ አባል የሆነው የጸሎተ ሕዝቅያስ ወንድም ነው። በድርጅቱ ጥሪ ከአሜሪካ ከመጣ ስድስት ወር ይሆነዋል። ልባችን ተሰበረ...

'የሱ----ፍ አበ--ባ!! ተፈጥሮ የደለደለችላትን የህልውና ምንጯን ፀሐይን አሻፈረኝ በማለቷ እበቦቿ መርገፍ ጀምረዋል። ዮሴፍ አዳነና ፍስሀ...። ጉልበቷም እየደከመ መጣ። እናም ይሄው የሱፍ ጥሬዎቿ ጢር ጢር እያሉ እየወደቁ ነው።'

"አጥቅቶ መከላከል" ሥልት እጅና እግር የሌለው የእውር ድንበስ እቅድ እንደነበረ አንድ ማረጋገጫ መምጣቱ ነው። ደጀኔ፤ ፍቅሬ መርእድን አጥቅቶ መግደል ችሏል። ይትባረከን ግን መከላከል አልቻለም። ይህ የእሱ ድክመት አይደለም። የሥልቱ ስሜታዊነት ውጤት ነው። ደርግና መኢሶን በበኩላቸው ፍቅሬ ሲገደል ተጠቁ። ይትባረከን ግን በመከላከል አርምጃቸው ያዙት። ብርሃነመስቀል አሁን ትዝ አለኝ...

"መከላከል አደረግን የሚባለው በምንጠቃበት ጊዜና ቦታ አጸፋውን ስንመልስ እንጅ ሰው ለመግደል ድምጻችንን አጥፍተን ከጀርባው ስንከተለው አይደለም..." በጣም ትክክል ነው። የእሱ ቀንዳም ሰይጣን ብቅ የሚለው ከዚህ በኋላ መናገር ሲቀጥል ነው፤ "ከደርግ ጋር አንተባበር..."

# 30

ቁርስ ላይ ወደ ምድር ቤት አመራሁ።

ሸዋዬና ኢሳያስ በድልህ የታሸ የስንዴ ቂጣ በወተት እየበሉ አገኘኋቸው። ደጀኔ የለም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የደጀኔን ቤት መሆን ወይም መውጣት የፖለቲካ ሙቀት መለኪያ አድርጌዋለሁ። ሳይኖር ሲቀር በሆነች የአዲሳባ ቀበሌ አንድ ነፍስ እየጠፋች እንደሆነ እንዳስብ ስለምገደድ ቅፍፍ ይለኛል። የደረስኩት ስለ ብርከቲ መገደል እያወሩ ሳለ ነበር። ርእሱን ሳይቀይሩት ቀጠሉ። ሸዋዬ ወደ እኔ አተኩራ እያየች ታናግረኝ ጀመር...

"አላምር፣ አንተ በእኔ የምትመከር ሰው አይደለህም። አንድ ብለህ የብርከታዊትን ነገር ለቢታኒያ እንዳታነሳ። እኔ አዲስ አ'ባ ድንበር የሌለው ሰፊ ውቂያኖስ ነበር የሚመስለኝ። ለካስ ጠባብ ነው። 'የድሮ ፍቅረኛዬን ያስገደልሻት አንቺ ነሽ' ብትላት ቢታኒያ ጨርቋን ጥላ እንደምታብድ እወቅ!" አበክራ አስጠነቀቀችኝ።

"ምን ማለትሽ ነው! ስመሬ ሕጻን አደረግሽው እንዴ?" ኢሳያስ ስጋቷን አጣጣለው።

"ኢሱ፣ ይሄ'ኮ 'ዲያሎግ'፣ ሎጅክ፣ ምክንያታዊነት ምናምን የለውም። ስመረ፣ ብርከታዊትን የተለያት በጥል አይደለም። በድርጅት ትእዛዝ ነው። ይህ እንኳን ብርከታዊት ስትሞት ይቅርና እንዲሁም ቢሆን እየዋለ ሲያድር ጸጸት ይፈጥራል። አሁን በፍቅር ላይ ያለው አስገደለቻት ከተባለችው ከቢታኒያ ጋር ነው። ቤቲን ደ'ሞ ልቧ ድረስ ዘልቄ ዐውቃታለሁ። ለፍቅር ሟች ናት። በሆነ አንድ ስሜታዊነት ድንገት ከአፉ ቢያመልጠው በንቡ ፈነዳ ማለት ነው..." ሸዋዬ ስጋቷን አጠናከረች።

ትክክል መሆኗን ልቤ ይነግረኛል። ሞትና መታሰር እየጨመረ ሲመጣ ሆድ ባሰን መሰለኝ እንነፋፈቃለን።

በተለይ የደጀኔ ነገር ከልብ ያሳስበናል። ሸዋዬ አንድም ጊዜ መጨረሻው ጥሩ እንደማይሆን ከመናገር ተቆጥባ አታውቅም።

"መንግሥቱ ኃይለማርያም ቀስሉ ተሽሎት ቢሮ ተመልሶ የገባ ቀን ነው!" ለሞኑን ትደጋግመዋለች።

"ከሁለት ቀን በፊት ገብቷል አሉ፣" ኢሳያስ ሲጋራ እየለኮሰ ጣልቃ ገባ፣ "አሁን ባለው ሥልጣን ምንም ማድረግ የሚችል አልመሰለኝም። እርፎ ቁጭ ይላል ብዬ ግን አላምንም። መፈንቅለ መንግሥት ሊያስብ ይችላል። በደርግ ስብሰባ ላይ መሣሪያ ታጥቆ መግባት ተከልክሎ ነበር። እሱ ከቆሰለ በኋላ ግን እንደገና ተጀመረ ብለው ነገሩኝ።

'እኔ ግን ነገሩ ዓላማረኝም' ስጋቴን ገለጽኩ።

"ጓድ ዘርዑን ስነግረው ግን ምንም የሚያሳስብ ነገር የለም አለኝ። እንግዲህ ዝም ብሎ ማየት ነው..."

ሸዋዬ ለኢሳያስ ስጋት የሆነ መልስ ልትሰጠው ስትል ጣውላው በር ተንኳኳ። ጆሯችንን ወደ በሩ አቀናን። እኔና ኢሳያስ ከራሳችን በስተቀር የሌሎችን ኮድ የአንዱንም አናውቅም። ስለመጣው ሰው የምትነገረን እሷ ናት። ዓይን ዓይኗን ዐየናት...

"ደጀኔ ነው!" ሄዳ ከፈተችለት።

ሰላማዊ ረፋድ እንዳሳለፈ መገመት አልተቸገርንም። ሸዋዬ ቁርሱን እስከምታመጣለት እኛ ያስተረፍነውን ቂጣ መብላት ጀመረ። ሻይ ቀድታለት ስትቀመጥ ወሬ ተጀመረ...

"ደጀኑ፣ እህ... እንዴት ነው? የዛሬ ጧት ተልእኮ ወይ ከሽፏል ወይ በደንብ ተሳክቷል። ከመስከረም በፊት የነበረውን መረጋጋት ነው ይዘህ የተመለስከ። ትክክል ነኝ?" ፈገግታ እያሳየችው ጠየቀችው።

ደጀኔ የኮረኮሩትን ያህል ከት ብሎ ሳቀ፣ "ሸዋ እንዴት ዐወቅሽ?" ከሳቁ ጋር እየታገለ ጠይቋት መልስ ሳይጠበቅ ነገረን፣ "የመኢሶን ሥራ አስፈጻሚ መርካቶ ይሰበሰባል ተብሎ ሄደን ነበር። ጭቃ ልናረጋቸው ስንደርስ ባዶ አዳራሽ ጠበቀን። ደውለን ኮማንደሩን ስንጠይቀው መረጃ ሳይደርሳቸው አልቀረም አለን።"

ሦስታችንም አንድ ዓይነት ደወል ሳናስበው የጮኸብን ነው የመሰለነው። ዞር ዞር ብለን በብርቱ ግራ መጋባት በዐይኖቻችን እርስ በእርስ ተጠያየቅን፣ "መረጃ ደረሳቸው? ጌታቸው ማ----ሩ????" ለአፍታ በጥልቅ ጸጥታ ተያየን። ቀጭን የስጋት፣ የጥርጣሬ፣ የፍርሀት...ወጀብ እንቀጥቅጦን አለፈ። በደጀኔ ፊት

ምንም ነገር መነጋገር አልፈለግንም። እንዲሁ በየግላችን ስናስበው ግን ከጌታቸው ማሩ ትከሻ መውረድ ተቸገርን።

በመሀሉ ትኩረታችንን ያስቀየረ ኃይለኛ የጫጫታና የኡኡታ ድምጽ ከቅርብ ርቀት ተሰማን። "ኡኡኡኡኡኡ............ ዋይ! ዋይ! ዋይ! ኡኡኡኡኡኡኡኡ..."

"ምንድነው? ከየት ነው?" ድምጹ የሚመጣበትን አቅጣጫ መለየት ተቸግረን።

"ይሄ ነገር ከእነ ቢታኒያ ግቢ ነው!" ደጀኔ ተስፈንጥሮ ብድግ አለ።

"ቢታኒያ??" እንዴት እንደተነሳሁ...የቁርስ እቃውን እንደዘለልኩት...ከበሩ እንደደረስኩና ከፍቾው እንደወጣሁ ትዝ የሚለኝ ነገር የለም። እንደጭልፊት እየበረርኩ ቀዩን በር ከፍቼው ገባሁ። ደጀኔ ትክክል ነው። ቢታኒያና ወይዘሮ ማስተዋል በብዙ የጎረቤት ሴቶች ተይዘው መሬት ላይ ካልወደቅን፣ ካልፈረጥን፣ ካልደማን...ሲሉ ደረስኩ። ቢታኒያን በሰላም ማግኘቴ ግን ድንጋጤዬን አላስቀረልኝም። ዋናው ቤት በሰው ግጥም ብሏል። ሙሴ ባልዲ አዲስ ወታደራዊ ዩኒፎርምና ጫማ አድርጎ ከወዲያ ወዲህ ይሯሯጣል። ምን አደጋ እንደተፈጠረ ለማወቅ ከእሱ የተሻለ የምጠይቀው ሰው የለም። ወደ እሱ ሮጥኩ፣ "ሙሴ፣ ምንድነው? ንገረኝ ምንድነው? ማን ምን ሆነ?"

"ሚኪኤለን..."

"ሚካኤለ ምን ሆነ...?"

"...ትምህርት ቤት መኢሶኖንና ኢሕአፓ ተጣልተው በመሀል በጩቤ ወግተው ገደሉት!"

# 31

የጥቅምትና የህዳር ወራት እስከ አጋማሹ ድረስ ያለው ጊዜ ብዙም ለውጥ አላመጣም። የፖለቲካ ገሞራው የመስከረሙን ዝንባሌ ይዞ ቀጥሏል። የእያንዳንዱ ቀን ምሽት የሞት ሲቃ ይዞ ይመጣል። የእያንዳንዱ ቀን ማለዳ የለቅሶና የዋይታ ድምጽ ያጅበዋል። ጸጥ ብሎ የዋለው ቀን ጸጥ ብሎ አያመሽም። አዲስ አበባ በጥይት ጣጣታና በመትረየስ ድምድምታ ትናጣለች። የሚችና የገዳይ ጥምረትም ያው የመስከረሙን ቅያስ አልቀቀም። ኢሕአፓ ከጀርባ አድብቶ ይተኩሳል፣ ደርግና መኢሶን ይወድቃሉ። ከኢሕአፓ ሰኳድ አባላት የሚያዘው ይይዛል፣ የሚያመልጠው ያመልጣል። ሞትና ለቅሶ መደበኛ የዕለት ውሎ እየሆኑ እስከመለመድ ደርሰዋል።

"ኧረ ምንድነው ጎበዝ...ኧረ የምን እልቂት መጣብን?" እናቶችና አባቶች በየቤተክርስቲያኑ፣ በየገበያው፣ በተገናኙበት ቦታ ሁሉ ይጠያየቁና የሚያረካ መልስ ሳይለዋወጡ ከንፈራቸውን እየመጠጡ ይለያያሉ፣ ጭም፣ ጭም!

የድርጅቱ 'አድብቶ የመግደል' እርምጃ ቀስ በቀስ መልኩን እየለወጠ መጣ። ሕቡዕ የሲቪክ ማኅበር የምንለው ኢላአማ በራሱ ታጣቂ አሀዶች ግድያውን ተቀላቀለ። ለደርግና ለመኢሶን ወገኑ የተባሉ የኢሰአማ መሪዎችን ኢላማ አደረገ። ቢሯቸው ውስጥ ቁጭ እንዳሉ ግንባር ግንባራቸውን ብሎ ገደላቸው። ታጣቂዎቹ ተዋህደው በአንድ የፓርቲ አመራር ሥር ሲገቡ ደግሞ ኢላማዎቹ ላይ ለውጥ ተደረገ። ከፍተኞችና ቀበሌዎች መታመስ ጀመሩ። ከመስከረሙ በላቀ ቁጥር በርካታ ሰዎች ወደቁ።

"እግዚኦ ማሕረ------ነ፣ አድህነነ ከመዐ----ቱ!" ቤተክርስቲያናት የምልጃ ጸሎት አስተጋቡ።

ግድያው በቀጠሉት ወራት ሌላም ለውጥ አሳየ። የመገዳደሉ ወረርሽኝ ከአዲስ አበባ ወጥቶ ወደ ክፍለሐገር ከተሞች ተዛመተ። ጎንደር፣ ደሴ፣ አስመራ፣ ሐረርና ሌሎች ከተሞች በመገዳደል ትርኢት ተጨነቁ፣ ግቢ ነፍስ- ውጭ ነፍስ አቃሰተ። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮና አዲስ ዘመን ጋዜጣ የሞት ዜና ማሰማት የተለመደ ተግባራቸው ሆነ። የሟቾች ፎቶግራፍ ይታይና የሕይወት ታሪካቸው ይነበባል። የአዲስ አበባ ሟቾች ለ"አብዮታውያን ሰማእታት" በተዘጋጀው የቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ልዩ ቦታ ይቀበራሉ። ሕዝቡ በተለይ ወጣቱ የኢሕአፓ ስኳዶች ሰው የገደሉበትን ቴክኒክ አስገራሚነት ይነጋገራል። የደርግ/የመኢሶን ባለሥልጣናት፣ ካድሬዎችና ደጋፊዎች መውጫ መግቢያ አጡ...

"እንዴት ነው፣ በቃ፣ በአገሩ መንግሥት የለም ማለት ነው?"

ሕዳር ላይ በሕዝቡ መካከል የሚነሳው ጥያቄ ቅላጼው ተቀየረ። ቀበሌዎችና ከፍተኞች ሕዝቡን እየሰበሰቡ "እዩልን...ስሙልን...ልብ በሉልን..." ማለቱን ተያያዙት። በአንዳንድ ቀበሌዎች የድርጅታችን ስኳድ አባላትና መሪዎች በጥቆማ ተያዙ። በሻለቃ መንግሥቱ ግድያ ሙከራ መቺ ጓድ ሆነው ከተሰለፉት አምስት ሰዎች አራቱ ተይዘዋል። ጎይቶም ለባሲና መምህር በላይነህ ሊያመልጡ አልቻሉም። ጎንደርና ባሌ ጎባ ከጥቆማ አልፎ በድንገተኛ አሰሳና በአፈሳ ማሰርና በሞቁዘገንን ጭካኔ መመርመር ተጀምሯል። ደርግ አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ በመከላከል ጥረት ላይ ነው።

የሱ----ፍ አበ--ባ!! እያሌ የሱፍ ጥሬዎቿን አጣች።

መሳለሚያ የእኛ ጋራዥ ያለበት ቀበሌ ከትላንትና ወዲያ ሰላማዊ ሰልፍ ጠራ። ኢሕአፓንና የግድያ ዘመቻውን ለመቃወም መጠራቱ በግልጽ ተነግሯል። ቢታኒያን አስተኝቼ እኔም ተገኘሁ። የተጻፉት መፈክሮች አስፈሪ ነበሩ...

"አስታጥቁን፣ አታስፈጁን! ዲሞን በዲሞትፈር!"

እኔና ኢሳያስ ጉዳዩን ለፖሊት ቢሮው አሳወቅን። ዘርዑ ከሕሸንን በመከራ ጉለሌ አግኝተን ነገርነው። በመርበትበትና በመሸበር አልነበረም የነገርነው። የተተነተነ ሐሳብና ስለ ሰልፉ ውጤት የመሰለንን መላምት በሥርዐት ይዘን ነው የሄድነው። አብዛኛውን የውውይቱን ጊዜ የያዝነው እኔና ዘርዑ ነበርን። ትንሽ ቆይቶ ዶክተር ተስፋዬ መጣ። ውይይት ብለን የጀመርነው ነገር ወደ ተጧጧፈ ክርክር ተለወጠ። ኢሳያስ እስከመጨረሻው የእኔን ሐሳብ ደግፎ ቆመ...

"እመኑኝ፣ ደርግና መኢሶን በገንዘብና በማስፈራራት ከሚያስወጡት ስብስብ ውጭ ከሕዝቡ ኢሕአፓን

ለመቃወም እምኖበት የሚወጣው ሰው ከአስር ሰው ሊበልጥ አይችልም። ታያላችሁ..." ዘርዑ ድርቅ አለ።

የማነጋግረው ሰው ያ ድሮ የማውቀውና የማከብረው ዘርዑ ከሕሾን አልመስልህ አለኝ። ያቺ ችኮላዬ ብቅ ብላብኝ ተሳስቼም እንዳይሆን ሰጋሁ። የሚያሳምን ነገር ደግሞ አልሰማሁም። ሲገባኝ መረዎቻችንን "መሥራቾች፣ አንጋፋዎች......" ምናምን እያልን የማይሆን መንገድ አስይዘናቸዋል።ድርጅታችን የያዘውን የቁልቁለት መንገድ አብረን ማፋጠናችን ተሰማኝ። አድርባይነት ምን ያህል እንደጎዳን ያወኩት"እጥቅቶ መከላከል"ሥልት በድምጽ ብልጫ የጸደቀች ዕለት ነው። ብልጭ አለብኝ። በዝምታ የማልፍበት ጊዜ አንድ ቦታ ላይ በተለይ ደግሞ አሁን መቆም አለበት ብዬ በውስጤ ወሰንኩ...

"አይይ...ጓድ ዘርዑ፣ ያልከው ነገር ጨርሶ የማያሳምን ነው። አንተ የምትለው ዓይነት ስሜት አይደለም በሕዝቡ መካከል እየተንሸራሸረ ያለው። ራስን ማታለል እንዳይሆንብን ሰጋት አለኝ..." ፈርጠም አልኩ።

ቃላቱ እንደዚህ ይከራሉ ብሎ የጠበቀ አይመስለኝም። የፊቱንም መለዋወጥ ሳያጤነው አልቀረም። ዞር ብሎ አተኮረብኝ...

"እና ሕዝቡ ኢሕአፓ በቀንደኛ ጠላቶቹ ላይ እርምጃ መውሰዱን ከልብ ይቃወማል ብለህ ነው የምታምነው፣ ጓድ አላምረው? እስቲ አስረዳኝ!" እሱም ጠንከር አለ።

"እንዴዴ! ምን ማለትህ ነው፣ ዘርዑ? እኔ የኢትዮጵያ ታሪክ ከኢሕአፓ ይጀምራል ብዬ አላምንም። ሕዝቡ በዘመናት የጦርነት ትዝታዎች ተኮትኩቶ ያደገ ሕዝብ ነው። ስለ ጦርነትና ሰላም ያዳበራቸው እሴቶችም አሉት። ጦርነት ለትክክለኛ ፍትህ ሲሆን የሚዘምት ሕዝብ ነው። ጀግናን ያደንቃል፣ ያወድሳል፣ ይታዘዛል። ጀግና የሚለው ግን ጠላትን ፊት ለፊት ገጥሞ የሚያቸንፈውን ነው። የፈለገ የፖለቲካ ልዩነት ይኑር። ጧት ሰላምታ ሰጥቶ የሸኘው ጎረቤቱ ምሽት ላይ ከጀርባው በጥይት ተመትቶ ሲወድቅ እንደ ፍትሀዊ ጦርነት ያየዋል ብትለኝ አላምንም። ይልቁን የፈሪ ዱላ አድርጎ ነው የሚያየው..." ትኩር ብዬ ዓይን ዐይኖቹን እያየሁ ተናገርኩት።

"ሰመሬ የሚለው ትክክል ይመስለኛል፣ ጓድ ዘርዑ። ካስፈለገ የሕዝብ አስተያየት ዳሰሳ ማድረገም ይቻላል።" ኢሳያስ ደገፈኝ።

ዘርዑ ይናገራል ብዬ ስጠብቅ ለመናገር ብዙም የመቅደም ልምድ የሌለው ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ቀደመው...

"ጓድ አላምረው፣ ይሄ ሕዝብ'ኮ ከሁለት ዓመታት በፊት አብዮት አካሂዶ ሥርዐት የለወጠ ሕዝብ ነው። እሁን አብዮቱ በደርግና በመኢሶን ተጠልፎበት ባዶ እጁን ቁጭ ማለቱን የማያውቅ ሕዝብ ነው ብዬ አላስብም። ደርግን ጠልቶ ኢሕአፓን የሚደግፈው በምርቃን አይመስለኝም። የዚህ ቁጭት ውጤት ነው። ኢሕአፓ ይህንን የተጠለፈ ድሉን ለማስመለስ መቆሙን በሚገባ ያውቃል ብዬ አገምታለሁ። ጠላፊዎቹ መገደላቸውን ከፖለቲካ አንጻር 'ዋጋቸውን አገኙ' ይል እንደሆነ እንጅ 'ኢሕአፓን ለመውጋት አስታጥቁን' ብሎ ይነሳል ብዬ አላስብም። ቢኖሩም ወይ የሟች ዘመዶች አለያም ጥቂት የደርግ ደጋፊች ናቸው..."

"እኔም የማስበው እንደዚህ ነው። ኢሕአፓም የሕዝቡ አካል ይመስለኛል። የገዛ ልጆቹ ናቸው።" ዘርዑ ጨመረ።

ፈጽሞ አልተቀበልኳቸውም። አቀማመጤን አስተካከዬ ዘርዑ ካቆመበት ቀጠልኩ...

"በበኩሌ ሕዝቡ ኢሕአፓን እንደሚደግፍ አልጠራጠርም። ኢሕአፓን ሲደግፍ ግን ግድያን ይደግፋል ብላችሁ እየተረጎማችሁት ከሆነ ስህተት ነው። የቆዩ እሴቶቹን ለጊዜው እንተዋቸው።ሕዝቡ እንደማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ስለመጭው ጊዜ እርግጠኛ ቢሆን አይጠላም። የእኛ የግድያ እርምጃ ይህንን ፍላጉቱን ይጻረርባታል። በዚህ ላይ ግድያችን በጥቂት ግለሰቦች ሊቆም አልቻለም። ሂደት እየሆነ ነው። ግድያው በደርግ/መኢሶን በኩል የበቀል እጸፋን እያስከተለ ነው። እጸፋው እንደገና የእኛን ሌላ እጸፋ ይቀሰቅሳል። መገዳደሉ ሰንሰለት ሆነ ማለት ነው። ይህ መቼም ለሕዝቡ የምሥራች አይሆንም። ወይም የግላዲያተር ባሪያዎች መገዳደል ዓይነት የመዝናኛ ትርኢት ሊሆን አይችልም። ለዚህ ነው ሰልፉን የሚደግፈው..."

ከሁኔታችን ሁላችንም በዚህ ሰዓት መተማመን ላይ እንደማንደርስ የተግባባን ይመስለኛል። ከሳምንት በኋላ የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ሐሳባችንን ልናቀርብ ተስማማን። እኔና ኢሳያስ ሳምንቱን በሙሉ ስንዘጋጅ ከረምን። ልዩነታችንን የምናቀርብበት ትክክለኛ ቀን ደርሷል።

"ጨከነን መፋለም አለብን!" ከኢሳያስ ጋር በልባችን ቃል ተገባባን።

###

የማእከላዊ ኮሚቴው ስብሰባ ዛሬ ምሽት በላይ ዘለቀ ትምህርት ቤት አካባቢ ይደረጋል። ምናልባት ሌሊቱን በሙሉ። ስብሰባ እንደሚኖረኝ ለቢታኒያ መንገር አስፈርቶኛል። ደግነቱ ያን ቢጫ በርሳ ይዛ

መንከልከል እርግፍ አድርጋ ትታለች። "ትሞትብኛለች" ከሚለው ጭንቀቴ ወጥቼ ነው የከረምኩት። የሚካኤለ በመኢሰን ደጋፊዎች መገደል ይህንን መረጋጋቷን ለውጦ ለበቀል ያነሳሳት ይሆናል ብዬ ሰግቼ ነበር። የሚካኤለ ሞት ከዝምድናው በተጨማሪ ሐዘኗን የሚያባብስበት ምክንያት ነበረው።

ወይዘሮ ማስተዋልማ አብደት ጫፍ ደርሰው በመከራ ነው የተመለሱት። እየተረጋጉ የመጡት የቢታኒያን ማምረር ሲያዩ ይመስለኛል። ቤቲ ጸጉሬን ካልተላጨሁ ብላ አስቸግራ ነበር። በጭራሽ የማይሆን ነገር ነዉ ለእሳቸው። በብዙ ሽምግልና ነው ሐሳቧን የቀየረችው። ሙሉ ጥቁር ልብስ ብቻ ለበሰች። እሷ ስትረጋጋ ካዩ በኋላ ግን ሐዘኑ ተመልሶ ይጠብሳቸው ገባ። ፎቶግራፉን፣ ልብሶቹን፣ የመማሪያ ደብተሮቹን...ሲያዩ ይቀሰቀስባቸዋል። ቤቱ ሲያስጠላቸው ወደ ኮተቤ ዘመዶቻቸው ይሄዳሉ። አንዳንዴ ሳምንቱን እዛው አሳልፈው ይመጣሉ።

"ማሚ፣ ይሄ መጥፋት አልበዛም?" ቢታኒያ ነገሩ ሲያሳስባት ጠየቀቻቸው።

"ምን ላድርግ ብለሽ ነው፣ ቤቲዬ? በሰው እጅ የተገደለ ዘመድ ኖሮኝ ስለማያውቅ ነው መሰለኝ መልመዱ ከበደኝ። ከእንግዲህ እንኳን አልጠፋም። አሁን ትንሽ ቅልል ብሎኛል፣ ..."

እንድም ቀን ከጎኗ ተለይቼ አላውቅም። በአንድ በኩል የሚካኤለ ሞት እኔንም ከእንጀቴ አሳዝኖኛል። ልካፈላት ይገባኛል። በሌላ በኩል ሞቱ ለበቀል አላነሳሳትም። ሙሉውን ጊዜዋን ቤት ነው የምታሳልፈው። ከተጽናናች በኋላ ይሄን መጽሐፍ እያከታተለች ትፈልጠዋለች። ከግድያ ተልእኮ መውጣቷ እንደሆነ ገባኝ። በምን መንገድ እንደወጣች ግን አላውቅም፣ ልጠይቃትም አልፈልግም። አንድም የእኔ ምክር አሳምኗት በራሷ ጊዜ እምቢ ብላለች። አለያም የታጣቂ ከንፉ በራሱ ምክንያት አስቁሟት ታል። ወይም በራሷ ጥያቄ ለመተው ተፈቅዶላታል። እምቢ ያለች ግን አልመሰለኝም። ሥራ ቀይራ እያየኋት ነው። በጣም ብዙ ሰነዶች ነው የምትመረምረው።

'በፈለገው መንገድ ይሁን፣ ዋናው ግልግሉ ነው!' እውነተኛ ሰላሜን አገኘሁ።

በሚካኤለ ሞት ምክንያት ከልቡ ያዘነው ሌላው ሰው ሙሴ ባልዲ ነው። ከትላንትና ወዲያ እዚህ ነበር ያመሸው። ባጋጣሚ ወይዘሮ ማስተዋል ከአየር ጤናዋ እህታቸው ጋር መጥተው ቡና እየተፈላ ነበር። ሙሴ ነጣ ያለ ካኪ የደንብ ልብስ ለብሷል። በተለይ ለአዲስ አበባ ከተማ የአብዮት ጥበቃ አባላት የተዘጋጀ መሆኑን ዐውቀናል። በቁመቱ ረዘም ያለ አንድ በአንድ የሚተኩስ ጠበንጃ ይዟል። አፈሙዙ ቀጠን ብሎ ይወጣና ጫፉ ላይ ሲደርስ ሰፍቶ የቱልቱላ ቅርጽ ይይዛል። ሙሴ ባልዲ የቀድሞ ሰውነቱ ተመልሶ ጸዳ ብሏል። ጸጉሩ በደንብ አጥሮ በወጉ ተበጥሯል። ከንፈሮቹ ፈካ ብለው ጥርሶቹ ነጽተዋል።

አተላ ይመስሉ የነበሩት የጣቶቹ ጥፍሮች በሙሉ ተከርክመዋል...

"ሙሴ ባልዲ፣ አሁን ጎበዝ ሁን። እንዲህ አምሮብህ እንደድሮው ቂጥህን ጥለህ መንገላወድ የለም። ሚስት አግባ፣ ቆንጆዋን...እ...ሽመል የመሰለችውን መርጠህ...አግባ። ውለድ፣ ከበድ፣ ቁምነገረኛ ሁን..." ወይዘሮ ማስተዋል መከሩት።

"ማዘር፣ ሁሉም ነገር በእርሰዎ ላይ የሆነ ነው። የወለደች እናት የማታደርገውን ነው ያደረጉልኝ። ምሥከር ያጡት ጓደኞቼማ ፖሊስ ሆነው ከፍለሐገር ተላኩ። በሦስት ወር ሥልጠና አንደኛ ዙር ብለው አስመርቀው ላኳቸው። ችግሩ በሄዱበት ቦታ ሁሉ ሕዝቡ ዱሩየዎች የነበሩ መሆናቸውን ወሬውን ቀድሞ ሰምቶ ጠበቃቸው። ሥራ ሲጀምሩ እንዴት እድርጎ ይመናቸው? በዚህ ላይ ያው ሙቼም ባህርይ አይለቅም፣ እነርሱም ዱርየነቱ አምቢ ሳይላቸው አልቀረም። መልከስከሳቸውን አልተውም። የኢግዜቢት ገንዘብ ሲገኝ ላስ ያደርጉታል። ጎንደርማ ስም አወጡላቸው። 'ሸዋ አረፈ፣ ጎንደር ተገረፈ...' እሉን ብሎ አንዱ ጓደኛችን ለሥራ መጥቶ ነገረን..."

ወይዘሮ ማስተዋል የጎንደሮችን አባባል አስደግመውት ሲነግራቸው የሐዘን ፈገግታ ፈገግ አሉ። ቢታኒያ ሌላ ጥያቄ አነሳችለት...

"ሙሳ ባልዲ፣ ለመሆኑ ምን ዓይነት ጠበንጃ ነው የሰጡህ? አፉ የአረቄ መጠጫ የመሰለ ነገር ነው። እንዳያሳስትህ እንጂ..."

ሙሴ ባልዲ ከት ብሎ ሳቀ። የየዋህነት አባባሏና የጠበንጃው አፍ ቅርጽ ከአረቂ መጠጫ እቃ ጋር መመሳሰሉ ሲገጣጠምበት የምሩን ሳቀ። "አይ ቢታኒያየ! የአረቂ መጠጫ አልሽኝ?" እያለ ሲስቅ ቆይቶ መልስ ሰጣት...

"ቤቲ፣ ጠበንጃየ ዲምትፊር ይባላል። አሥራ ሁለት ጥይት ጎራሽ ነው። እስካሁን አልተኮስኩበትም። 'አናርኪስቶችን ምቱ ስንላችሁ ያኔ ትተኩሳላችሁ' ስላሉን ዝም ብለን መወልወልና ሥልጠና መወሰድ ነው ሥራችን..." ካለ በኋላ የሆነ ነገር ትዝ ብሎት ወደ ወይዘሮ ማስተዋል ዘወር አለ፣ "ማዘር፣ ሳልነግራችሁ፣ በዚህ ሦስት አራት ቀን ውስጥ የጦር መሣሪያ አሰሳ ልናደርግ ነው። ከእናንተ ቤት እንኳን የሚገኝ ነገር አይኖርም። ግን የዘመድ ጠበንጃ፣ ሽጉጥ ምናምን ካለ ጥንቃቄ አድረጉ..."

እኔና ቢታኒያ ሰረቅ አድርገን ተያየን። "ሹኬ የሚል ዘመድ አያሳጣ!" የተለዋወጥነው ድምጽ አልባ መልእክት ነው። ሁለታችንም በየመስመራችን ለድርጅታችን ሪፖርት አደረግን። የገረመን ነገር መረጃው

ለኢሕአፓ አመራር ከእኛ በፊት ሳይደርስ ማግኘታችን ነው። የመረጃና ደህንነት መዋቅሩ ተጠሪ ከፍሉ ተዘራ ምን ይሠራል? መልሱ ለእኔና ለቤቱ አሁን በጣም ቀላል ነው። የገበርዲኒዝምን ሽማ ያዳውራል። የከተማ ሕይወት ወከባ ነው። ምን ጊዜ አገኘና! በተቻለ ፍጥነት ጥንቃቄ የማድረግ ሥራ ሠራን። የቢታኒያን ሽጉጥ ተቀብዬ ምድር ቤት አስቀመጥኩት።

ሰዓቱ ወደ ምሽቱ አሥራ ሁለት እየተጣደፈ ነው። ከጋራዥ ቢሮየ ወጥቼ ወደ ቢታኒያ አመራሁ። ልሄድ ነው ስላት በእነዚያ ሰይፍ ዐይኖቿ እንደ ቱባ ትርክክ ስታደርገኝ ታየኝ። ነገር ግን የምቀርበት ስብሰባ አይደለም። በዚህ አስቸጋሪ ፀጥታ ሁኔታ የማይገኝ እድል ነው። "የሱፍ አበባዊነት" እንብሮየን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር አሻሽዬ ባቀርበው ደስ ይለኛል። እድል ሳገኝ ግን አይታየኝም። ያም ባይሆን ስብሰባውን መካፈል አስፈላጊ ነው።

ቤት ስደርስ ግቢው ጭር ብሎ ቢታኒያ ቤቷ በር ላይ ቁጭ ብላለች። ሽታው እንደ ዮርዳኖስ ጢስ ከሩቅ የሚሸት ቅባት እየቀባች ጸጉሯን ስታበጥር አገኘኋት። ጸጉሯን ከሁለት ከፍላ በግራና በቀኝ በኩል ቁልቁል ትለገዋለች። አጠገቧ ደርሼ እንደቆምኩ በድንጋጤና በጥርጣሬ አፈጠጥኩባት...

"ምናባህ፣ ሞሮን...የት እምሄድ መስሎህ ነው የምታፈጥብኝ?" ቀና ብላ አየችኝ።

"እኔ ምን ዐውቅልሻለሁ፣ አንቺ ንገሪኛ!" ድምጼ የራሴ አልመሰልህ አለኝ።

"ማማቢ ትሙት፤የትም አልሄድም። ሰ--መ---ረ--የ ይሙት! ምናባህ፣ ሲነግሩህ አታምንም?"

ሁኔታዬ እንዳልተመቻት ያስታውቃል። አመንኳት። አጎንብሼ ከንፈሮቿን ፈልጌ ሳምኳቸው። እሷም በተራዋ ልትቀጣ ነው። እንዴት እንደምጀምርላት ግራ ገባኝ። ለመዋሸት እየተገደድኩ እንደሆነ ተሰምቶኛል። መቼስ አፍ ወድቆ አይሰበርም። እያመነታሁ እስከ ምሽት የሚያቆይ ሥራ እንደገጠመኝ ነገርኳት። ከመቅጽበት ከንፈሯ አምልጧት ዱብ ሲል አየሁት።

"ይሄን ልትነገረኝ ነው የመጣኸው? ከሄድክ ጥርግ ነው። ካመሸህ ሰዓት አላፊው እንዳይደርስብህ በዚያው እደር። ኮሽ ባለ ቁጥር እየባተትኩ ተሳቅቄ አልሞትም!" ንጭንጭ አለች።

ለደቂቃዎች ቆሜ በሰሰት ግንባሯን ስሜ ወደ ጋራዥ ተመለስኩ። ከዚያ ወደ በላይ ዘለቀ ትምህርት ቤት አካባቢ...

***

የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ዘርዘር ብለው ሰፋ ወንበሮች ላይ ተቀምጠዋል። የባሉት መብራት ሆን ተብሎ ስለጠፋ ከእቃ ቤት በሚመጣው የፍሎረሰንት መብራት ቦቃታ ነው የምንተያየው።

ዘርዐ በቀኝ በኩል መሀል ላይ ተቀምጧል። ወቅታዊው የፖለቲካ ሁኔታ ግምገማ የመጀመሪያው አጀንዳ መሆኑን ይናገራል። ኢሳያስ ከፍት ወንበር ሲያመለከትኝ ሄጄ ተቀመጥኩ። በቀኝ በኩል ጸሎተ ሕዝቅያስ አጠገቤ ተቀምጧል። በግራ በኩል ቤቷ አባላችን አለች። አሁንም የፊት ገጿን ዙሪያውን ስለሸፈነችው በደንብ አትታየኝም። ቢታኒያ ጋር እንዳየኋት የተፈጠረብኝ ጥርጣሬ አለቀቀኝም።

ዘርዐ ተናገሮ ሲጨርስ የመናገር እድሉን ለከፍሉ ተዘራ ሰጠው…

"የከተማው ታጣቂ ኃይላችን በተወሰኑ የደርግ አባላትና በመኢሶን ከሀዲ ምሁራን ላይ እርምጃ መውሰዱን ቀጥሏል። የአጥቅቶ የመከላከል እርምጃችን በብሔራዊ የኃይል ሚዛኑ ላይ ለውስጥ ስለሚያስከትሉ ምልከቶችን እያየን ነው። በመኢሶንና በሌሎች ደርግን ከበው በተኮለኮሉ ድርጅቶች መካከል አለመግባባቱ ተካሯል። በደርግና በኢማሌድህ መካከል የተቆሰቆሰውን ግጭትም ከፍተኛ ደረጃ ላይ እድርሶታል። በደርግ አባላት መካከልም ለውጥ አለ። ከድርጅታችን ጋር ግልጽ ውይይት ተደርጎ አንድ ዓይነት የሰላም ስምምነት የመፈረም ግፊት እየጨመረ ስለመምጣቱ መረጃዎች አግኝተናል። በዚያው ልክ የደርግ/መኢሶን አክራሪ ወገን አጸፋ መስጠቱን ቀጥሏል። እስከአሁን አዲስ አ'ባ ውስጥ ብቻ 132 አባሎቻችን እየታደኑ ተይዘው ታስረዋል…"

'እዎ! ጓድ ከፍሉ ከቀልድከ አይቀር እንዲህ ነው መቀለድ! 132 የሱፍ ጥሬዎች ጠብ ጠብ እያሉ መሬት ላይ እየወደቁ ነው። ተመልሰው ያሽታሉ እንዳይባል የወደቁት አስፓልት ላይ ነው! እልም ያልከ ውሸታም ክሆ' ጨጓራዬ መጤስ ጀመረ።

ከዚህ በኋላ የተናገረውን አልሰማሁትም። ዘርዐ ሌላ የሁኔታ ግምገማ እድል የመስጠት ፍላጎት የለውም። በዚህ ላይ በተበላሸው የጸጥታ ሁኔታ ምክንያት ጥድፊያ ይታይበታል። የስብሰባውን መንፈስ እንደመርግ የከበደ ጋግርት ተጫጭኖታል። ቀጥሎ ስብሰባው ስለተጠራበት ሁለተኛውና ዋናው አጀንዳ አኮ። ጌታቸው ማሩ ፈጸመ የተባለው መሠረታዊ የኢሕአፓ ሕገ ደንብ ጥሰት። ሀሞቴ ፍስስስስስ አለ። ወደ ጌታቸው አቅጣጫ ዐየሁ። እጆቹን ደረቱ ላይ አጣጥፎ በጸጥታ ያዳምጣል። ሠራቸው የተባሉ ወንጀሎችን ዘርዐ አንድ ሁለት እያለ መዘርዘር ጀመረ…

"የፖለቲካ ቢሮውንና የማእከላዊ ኮሚቴውን የማገናኘት ኃላፊነት የጓድ ጌታቸው ነው። ይሄንን ድርሻውን በሚገባ እንዳልተወጣ በብዙ መረጃዎች አረጋግጠናል። በነሐሴው ስብሰባችን ላይ ከጓድ ረዘነ (ብርሃነመስቀል) ጋር ግጭት ውስጥ መግባታቸው የምናስታውሰው አንድ ምስከር ነው። ሁለተኛ፣

ጌታቸው በዚሁ በነሐሴ ስብሰባችን ላይ ሌላም የደንብ ጥሰትና ክህደት ፈጽሟል። ፖሊት ቢሮው በሙሉ ድምጽ ያጸደቀውን የ 'አጥቅቶ መከላከል' ሥልት 'እኔ የለሁበትም' ብሏል። በዚህ ምክንያት በመካከላችን እስካሁን ጸንቶ የቆየው መተማመን አደጋ ላይ እንዲወድቅ አድርጓል..."

አሁንም ሳልፈልግ ዓይኔ ወደ ጌታቸው አማተረ። ምንም ንቅንቅ ሳይል ዘርዑን በጥላቻ እየተመለከተ ያዳምጣል...

"ጓዱ! የማእከላዊ ኮሚቴውን ከአዲስ አበባ የወጣቶች ሊግ ኮሚቴ ጋር የማገናኘት ኃላፊነት እንደተሰጠው ታስታውሳላችሁ። በዚህ የሥራ ድርሻው የነሐሴ/መስከረም ውሳኔዎችን ማስተላለፍ ሲኖርበት ይህንን አልፈጸመም። በዚህ ምክንያት የድርጅቱንና የሊጉን እንቅስቃሴ ማቀናጀት አስቸጋሪ ሆኖብን ብዙ ውጣ ውረድ እንድናልፍ ምክንያት ሆኗል። የጓዱ ሕገ ደንብ ጥሰት በዚህ ቢያበቃ መልካም ነበር። በጥቅምት/ሕዳር የፖሊት ቢሮው ውሳኔ መሠረት የቢሮውን ድርሳን እንዲሁ ሳያስተላልፍ መቅረቱ ተረጋግጧል። በዚህ ምክንያት ለበርካታ የፖሊሲና የርእዩተዓለም ጥያቄዎች የሰጠናቸው ማብራሪያዎች በጊዜው አልደረሱም..."

ዘርዑ የማስታወሻ ደብተሩን ፈካ ወዳለው የብርሀኑ ክፍል ከፍ አድርጎ ዐይቶ ቀጠለ...

"ጓዱ፣ የተጣለበትን ኃላፊነት አለመወጣቱ አንድ ነገር ነው። ነገር ግን ከዚህም አልፎ ሌሎች የድርጅቱና የወጣቱ ሊግ አባላት ተልእኮቸውን እንዳይወጡ ጣልቃ እየገባ ሲያውክ ተደርሶበታል። በመዋቅር፣ በሥራ ድርሻና በተልእኮ የማይገናኙ አባላትን ነው ሥራቸውን እንዳይሠሩ ጣልቃ የገባው። ለምሳሌ፣ በመኢሶን መሪዎች ላይ እርምጃ ሊወስዱ የተሠማሩ አባላትን እንዳይሠሩ ለማድረግ መሞከሩ ታውቋል..."

'ጉ----ድ ፈ---ላ!' ኢሳያስን ለማየት ሞከሬ አልቻልኩም።

ዘርዑ ወደ ማጠቃለያው መጣ...

"የጌታቸው ማሩ ጥፋቶች የድርጅቱን ሕገደንብና የዲሞክራሲያ ማእከላዊነት መርሆ በግልጽ የሚጥሱ ሆነው አግኝተናቸዋል። ስለዚህ ጉዳዩ ተጣርቶ በጉባኤ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የፖለቲት ቢሮው ከፖሊት ቢሮ አባልነቱ እንዲታገድ ውሳኔ አስተላልፏል። ማእከላዊ ኮሚቴው እንዲያጸድቀው ለውይይት ቀርቧል። ሐሳብ መስጠት ይቻላል..."

በበኩሌ ጌታቸው "የአጥቅቶ መከላከል" ሥልትን ከፖሊት ቢሮው ውይይት ጀምሮ መቃወሙን ከልብ አደግፋለሁ። መደገፍ ብቻ ሳይሆን አደንቃለሁም። ሥልቱ ፖሊሲ ሆኖ እንዳይወጣ እስከመጨረሻው

መከራከሩንም ወድጀለታለሁ። በድምጽ ብልጫ ከጸደቀ በኋላ ግን እንዳይፈጸም ጣልቃ መግባት አልነበረበትም። ይህ ስህተት ብቻ ሳይሆን አልም ያለ የፖለቲካ ከህሎት ማጣትም ነው። የተሰጠውን ኃላፊነት እንዲያውም በበለጠ ትጋት እየተወጣ ተቃውሞውን መቀጠል ነበረበት። ሥልቱ በተግባር ውጤት አልባ መሆኑን በማስረጃ እያቀረበ ግድያው እንዲቆም መታገል ይገባው ነበር። ምናልባት ሰው እየሞተ ይሄንን ማድረግ ሀሊናው አልፈቅድለት ብሎ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህ ፖለቲካ ወይም የፖለቲካ መጥፎ ጎኑ ነው። ማንም ምንም ማድረግ አይችልም። በብልጠት ማነስ ችግር ውስጥ ገብቶ ፖሊት ቢሮውንም ችግር ውስጥ እንደጣለው ገብቶኛል።

'አይ የሱፍ አበ----ባ! በራስሽ ላይ በፈጠርሽው ችግር ትታመሽ ገባሽ! ይህ ቀውስ ያለምንም ጥርጥር ፀሐይ ላይ አምጾ አምፖልን የማምለክ የሱፍ አበባዋ ስትራቴጅክ ስህተት ውጤት ነው።' ሀዘኔ ሲጠልቅ ተሰማኝ።

የጌታቸው ማሩ ስህተት የፖሊት ቢሮውና ማእከላዊ ኮሚቴው ነሐሲ ላይ የሠሩትን ወንጀል በሌላ ወንጀል ለማረም መሞከሩ ነው። "አጥቅቶ መከላከል" መዘዙ በአጭር ጊዜ እየታየ መሆኑን ግን የዘርው-ተስፋዬ--ክፍሉ ሦስት ማእዘን አመራር ሊያጤነው አልቻለም። ንዴት እንደ እግር እሳት ለበለበኝ። ትኩረቴን ወደ ስብሰባው የመለስኩት ብርሃነመስቀል እድል ተሰጥቶት መናገር ሲጀምር ነው...

"የፖሊት ቢሮው በጓዱ ላይ ያቀረበው ክስና የወሰደው እርምጃ ሁለት የፕሮሲጀር ግድፈቶች ያሉበት ይመስለኛል። አንደኛው፣ ቢሮው አንድ ጓድ ጥፋት ተፈጽሟል ብሎ ሊያምን ይችላል። ነገር ግን ከፖለቲካ መሪነት ሥራው ወጥቶ ራሱ ከሳሽ፣ ራሱ ውሳኔ ሰጭም ሊሆን አይገባም። አንድ ነጻ የዳኝነት አካል ሊያየውና ሊወስንበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ድርጅታችን የኦዲት ኮሚሽን ሊኖረው ሲገባ እንዳይቋቋም ያደረጋችሁት እናንተ ናችሁ። ይህ ለእንዲህ ዓይነት ጣልቃ ገብነት እድል ሰጥቷችኋል። ሁለተኛው፣ በእኔና በጓዱ መካከል ነሐሲ ላይ የተፈጠረው ችግር ነው። ችግሩ የጌታቸው ስህተት ከሆነ ከሳሽ መሆን ያለብኝ እኔ ብቻ ነኝ እንጂ ፖሊት ቢሮ እኔን ወክሎ ሊከስልኝ አይችልም። ክሱ ትክክል አይደለም።"

'በጣ----ም ት----ክክል!' በውስጤ ጮኽኩ።

ብርሃነመስቀልን ደግፌ ለመናገር እጄን አወጣሁ። ዘርው አላየኝም መሰለኝ እድሉን ለዘውዱ በላይ ሰጠው። ዘውዱና ጌታቸው በደንብ ይተዋወቃሉ። ኢሕአፓን ከመቀላቀላቸው በፊት የአብዮት ቡድን አባላት ነበሩ። በጓደኝነታቸው የተነጋገሩት ነገርም ይኖራል። ዘውዱ፣ ጌታቸው ከድርጅት ፖሊሲና አሠራር ውጭ ለ'ሱ ይነገረው የነበረውን ምሥጢር ዝክዝክ አደረገው። እሱ ሲጨርስ ዮሀንስ ብርሀኔ

ቀጠለ...

"በድርጅት ወሬ መሀል ጌታቸው 'እኛም እጃችንን አጣጥፈን እንመለከትም...' ብሎናል። እኔንና ከፍሉ ተዘራን። ይህንን ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ያብራራልን።" እንቶ ያዘው።

ጌታቸው መልስ ለመስጠት እድሉን አገኘ። የሥራ ብዛትንና የጊዜ እጥረትን ዋና ጉዳይ አድርጎ ራሱን ለመከላከል ሞከረ። አልተሳካለትም። የፖሊት ቢሮውን የውሳኔ ሐሳብ ተቀበልነው። ከፖለቲካ ቢሮውና ከማእከላዊ ኮሚቴ አባልነቱ ታገደ። አጀንዳው አልቆ ወደ ማጠቃለያ ስናመራ ሳሙኤል አለማየሁ እጁን አወጣ። ከብርሃነመስቀል ጋር ሙቼም ዓይንና ናጫ ናቸው።

"ጌታቸው ላይ የቀረቡት ክሶች ብርሃነንም ይመለከቱታል..." የሚል ሐሳብ አቀረበ።

ብርሃነመስቀልን ከማእከላዊ ኮሚቴ አባልነቱ የማገድ ውሳኔ ብዙም ክርክር አልተደረገበትም። ኢሕአፓ፣ እምጦ የወለዳት የገዛ ልጇ ጎኑን ወጋቸው። መጀመሪያ ወንበሩን ነጠቅነው። ቀጥላ ተደማጭነቱንና ተጽእኖውን። አሁን ደግሞ መቀመጫ መደቡን። "ጅል ከመውለድ ይሻላል ማስወረድ!" ብሎ እንደሚሆን ገመትኩ። ከዚህ በኋላ የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ምንድነው? በቃ፣ ጥይት የሌለው ጠበንጃ። እውነት ብርሃነመስቀልም በሰኩሉ ያለ ስብሰባ መኖር የሚችል አይመስለኝም። በሚቀጥለው የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ክሱን ያዳምጣል። ውሳኔውንም ይሰማል። የዐድዋ ማርያም ትርዓው፤ እንዳልል ማገርከሲት ነኝ። በትካዜ ተውጬ እየሁት...

'ኦ------ው፣ የሱፍ አበ-----ባ! እስከአሁን አንድ አበባሽን በደርግ አጣሽ። ሁለት አበቦችሽን እነሆ በገዛ እጅሽ! ነገስ ምን ይዞልሽ ይመጣ ይሆን?' ፍርሀት እንደ አዲስ ነገር ውርርር አደረገኝ። ስብሰባው ያለልማዳችን በሰዓታት ውስጥ አለቀ።

ከኢሳያስ ጋር ወደ መሳለሚያ ጋራዥ ተመለስን።

# 32

ወደ ቢታኒያ ከመሄዴ በፊት ሰውነቴን ታጥቤ፣ ፎጣ አገልድሜ ሽቦ አልጋዬ ላይ ጋደም እንዳልኩ አእምሮዬ ብርቱ ሥራ ያዘ። ያለፉትን ሁለት ወራት ክራሞታችንን መበርበር ጀመርኩ። የእኔ፣ የፍቅረኛዬና የእናቷ፣ የምድር ቤት ጓዶቼ፣ የድርጅቴ፣ የአዲስ አበባና የአገሬ ክራሞት። ጨዓራህ ይላጥ ሲለኝ ቢታኒያ ቴሌቪዥናቸውን ከዋናው ቤት ወደ ቤቷ አምጥታዋለች። ወይዘሮ ማስተዋል፣ ሚካኤለ ከሞተ ወዲህ ምንም ነገር ማየትም መስማትም አይፈልጉም። እኔው ሳልወድ እንዲሁ እየዋለሁ። አንዳንዱ ዓይን ያወጣ የደርግ/መኢሶን ውሸት ደሜን ያፈላውና ድቅቅ አድርገው የሚል ሰይጣን ይመጣብኛል።

"ቤቲዬ፣ መንግሥት ከዋሼ'ኮ አገሪቱ አደጋ ላይ ናት ማለት ነው። ብሔራዊ የሞራል ምሰሶቿን እየተናደ ነው።" ጉዳዩ በጣም ሲያሳስበኝ አንድ ሁለቴ ብያታለሁ።

"ሆዴ፣ በኢትዮጵያ ጉዳይ ተስፋ አልቆረጥክም ማለት ነው? ከሆነ በጣም ጠንካራ ነህ!" ትመልስልኛለች።.

ሙቀት እየተሰማኝ ሲሄድ ወደ ጀመርኩት ሐሳብ ተመለስኩ...

በገበያ መወደድ ምክንያት ለዛውን ያጣው የገና በዓል ካለፈ ሦስተኛ ሳምንቱን ይዟል። እነ ቢታኒያ ቤት ግን ዐውደ ዓመቱ የቀድሞ ወጉን ይዞ ነው የተከበረው። ትዝታው አሁንም ድረስ አለ። እኔ፣ ሽዋዬና ኢሳያስ 12 ሰዓት ገብተን ከምሽቱ 6:00 ሰዓት ነበር የተለያየነው። የወይዘሮ ማስተዋል ግብዣ ልግስና የበዛበት ነበር። ሙሴ ባልዲም አብሮን ነበር ያመሸው። የቀበሌያችን አብዮት ጥበቃ ኮሚቴ ጸሐፊ ሆኖ መሾሙን ነግሮናል። ባህርይው ከድሮው ትንሽ ለወጥ ብሎ ኮስታራ ለመሆን እየሞከረ ነው። የማስተዋልን የከረመ ድፍድፍ ጠላ ሲጠጣ ግን አልዘለቀበትም። የድሮው ሙሴ ባልዲ ወዲያው ከች

አለ። የቅርብ ጊዜ ማኅበራዊ ገጠመኞቹን እያነሳ በሳቅ ልባችንን ፍርስ ሲያደርገው አመሸ...

"ማዘር ማስተዋል 'ሚስት አግባ' ብለው የመከሩኝ ሰሞን ልቤ ተነሳስቶ ነበር።" ብሎ ጀመረልን፡"ትንሽ ምግብ ምናምን ሳሻሽል ጊዜ ደ'ሞ ሴት አምጣ አምጣ አለኝ። በኋላ ማንን ላግባ? እያልኩ ስጨነቅ ማደር ጀመርኩ። ካገባሁ አይቀር ደ'ሞ በገንዘብም በኑሮም የምታግዘኝ እንድትሆን ፈልጊያለሁ። ወገቤን ታጥቄ ፍለጋ ወጣሁ..."

"እዚህ እኛ ቀበሌ ነው ወይስ ገጠር ሄደህ?" ቢታኒያ ጣልቃ ገብታ ስትጠይቀው ቤት ውስጥ ሳቅ ፈነዳ። እሱ ራሱ ሳይቀር የምሩን ሳቀ።

"ቤቲዬ፣ አንዳንዴ ጥንቁልና ትሞክሪያለሽ ይሆን?" ለአመል ያህል ጠይቋት ወደ ወሬው ተመለሰ፣ "እናላችሁ ይሄን ቤቲዬ ያለችው ይደርሳል ብዬ ፈርቼ ራቅ ብዬ ሄድኩ። አንድ የፈረንጅ ከብት የሚያረቡ ትልቅ ሰውዬ አሉ። አብራቸው የምትኖር የዘመድ ልጅ እንዳለች ድሮ ኪስ አውላቂ እያለሁ ዐውቃለሁ። ትንሽ ልጅ ነበረች። ሁልጊዜ ጧት አንድ ሰዓት ላይ የወተት እቃ ታከሲ ላይ ጭና ወደ ቤት ስትሄድ እያታለሁ። ከዚያ ማዘር በጥሩ ጊዜ ያለበሱኝ ጅንስ አለ። እሱን ለብሼ ዝንጥ ብዬ ጠበኳት..."

"ውሎቱን አድርሳ ስትመለስ ነው ገና ሳትመጣ?" ሸዋዬ እየሳቀች ጠየቀችው።

"ገና ሳትመጣ፣" ሙሴ ባልዲ ቀጠለ፣ "ጠብቂያት ስትመጣ ቀብረር ብዬ ሄጄ አነጋገርኳት። መጀመሪያ አፍራኝ ዝም ብላ ሄደች። ስትመለስ እንደገና ያዝኳት። ትንሽ ተስፋ አየሁ። ሳምንት ሙሉ ተመላልሼ ጭቅጭቅ አደረኳት። በመጨረሻ ለትዳር መሆኑን ስነግራት በደንብ አናገረችኝ። አንድ ሳምንት ምናምን አሳልፈን 'ሽማግሌ ላክ' አለችኝ። የቀበሌውን ሊቀመንበር አስር አለቃ ረታንና ሁለት ሰዎችን ለመንኳቸው። እሺ ብለውኝ የዛሬ ወር አካባቢ ሄዱልኝ..."

"አይ ጉዳችን! ምን ብለው መልሰዋቸው ይሆን?" አሉ ወይዘሮ ማስተዋል።

"ልነግረዎት አይደል፣ ማዘር?" ሙሴ ሳቁ እያፈነው ቀጠለ፣ "ሰውየው 'አሁንማ ጥድፊያ አደረጋችሁብኝ። ቢያንስ ቢያንስ ሁለት ሳምንት ስጡኝ። ከእሷ ከልጅቱ ጋር፣ ከወላጆቿም፣ ከባለቤቴም ጋር መምከር አለብኝ..' ሲሏቸው ሁለት ሳምንት ሰጧቸው። በመሀል ለካ 'ሙሴ ሰለሞን የሚባል ሰው ታውቃላችሁ ወይ?' እያሉ ሲያጠያይቁ ከርመዋል። ብለው ብለው ሙሴ ሰለሞን ሙሴ ባልዲ መሆኑን ደረሱበት። ማዘርየ፣ ምናለ ዝምብለው 'ልጄን አልሰጥም' ቢሉ። ይሄ የትልቅ ሰው ወግ ነው። እሳቸው ምናሉ፣ 'ቆዩ፣ መጀመሪያ ከብቶቼንና የወተት ባልዲዎቼን ልሸጥና ከዚያ በኋላ አነጋግሩኝ...' አይሉም መሰለዎት!"

ካካካካካካ.........ቀቀቀቀቀ.......ካካካካ...ሁላችንም ሳቅን።

ሙሴ ባልዲ ከዚያ ወዲህ እንዲሁ አንድ ሁለቴ መጥቶ አዝናንቶን ሄደ። አግረመንገዱንም በየዋህነት መረጃ ጣል ያደርግልናል። ባለፈው ሕዳር ወር ላይ የተካሄደውን የጦር መሣሪያ አሰሳ ጉዳይ አነሳልን። ኮሎኔል መንግሥቱ በሂደቱና በውጤቱ አልተደሰቱበትም። "ብረት ላይ ብቻ ያተኮረ አሰሳ ስለሆነ በቂ ውጤት አላስገኘም" ማለታቸውን ነገረን። ሌላ በሰውም ጭምር ላይ ያተኮረ ትልቅ አሰሳ ለማድረግ አቅደው እንደገና ኮሚቴ ተቋቁሞ ጥናት እየተሠራ መሆኑንም አጫወተን።

'ጠንቶቅ በል ኢ.ሕ.አ.ፓ!' በስጋት እርስ በእርሳችን ተያየን።

በማግስቱ የእኛን ጨምሮ በአራት ከፍተኛዎች ሕዝባዊ ስልፎች ተካሄዱ። "አስታጥቁን! አታስፈጁን!" ደምቆ የሚሰማ መፈክር ሆኖ መዋሉን ታዘብን። ከሁለት ቀናት በኋላ ታደሰ ከፍሉና ዘርዐ ከሕሽን ከሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል ጋር መጥተው ነበር። ኢሳያስና እኔ በእኛ ቀበሌ ያስተዋልነውን ትርኢት ነገርናቸው። በጥሞና ሲያዳምጡን ቆይተው የተሰማቸውን አንድ ባንድ ነገሩን። ሻምበል ሞገስ ቀደሙ...

"ኮሎኔል መንግሥቱ የበጀት፣ ሠራዊት የማንቀሳቀስ፣ የመሳሰሉት ሥልጣኖች አሁን የሉትም። አብዛኛው ከእሱ ተቆርሶ ለጀኔራል ተፈሪ ተሰጥቷል። ይሄንን ያደረግነው ባለፈው ወር እሱ ራሱ ጭምር ባጸደቀው ዐዋጅ ነው። እግርና እጁን ቀፍድደን ቁጭ አድርገነዋል። ይሄንን ማድረግ አይችልም። ይሄንን እያደረገ ያለው መኢሶን ነው። አሁን በደረሰበት ጥቃት መደበቂያ ዋሻ አጥቷል። ጅምላ ጭፍጨፋ ለማድረግ አቅዶ እንደነበር ሰምተናል። ፖሊስና መከላከያ ጣታቸውን እንዳያስገቡ ታዘዋል።" ብለው አስረዱን።

ኢሳያስና እኔ የሻምበሉ አነጋገር ትንሽም ጠብ አላለንም። እርስ በእርስ ተያይተን መናገር ወደጀመረው ከፍሉ ታደሰ ዞርን...

"ሻምበል፣ ያ ትክክል እንደሆነ እያየነው ነው። ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ ግን ኮሎኔል መንግሥቱን ተስፋ አስቆርጦ ሌላ ተንኮል እንዲያውጠነጥኑ አይገፋፋቸውም ብለህ ታስባለህ?" ከፍሉ በኢሳያስና በእኔ ልቦች ውስጥ የነበረውን ጥያቄ ነው ደረቱ ላይ የመታው። መልሱ አጓጊ ነው። ፊታችንን ወደ ሻንበሉ ስንመልስ ዘርዐ ቀድሞ የራሱን መልስ ሰጠ...

"ተንኮል ማሰቡማ የት ይቀራል!? ነገር ግን በአሠራርና በሕግ ከተያዘ በጣም ይከብደዋል። ባጭር ጊዜ ሊሠራው የሚችለው ነገር የለም። በመሀል እኛ መተንፈሻ ጊዜ ልንሰጠው አይገባም።"

ዘርዐን በጥርሴ ብነክሰው በወደድኩ። አነጋገሩ በራስ ከመተማመን ይልቅ ተራ ጀብደኝነት ሆኖ

ተሰማኝ። ዝም ብለን ልናሳልፈው አልፈለግንም። በደርግ ውስጥ ያለው የኃይል ሚዛን ከኢሕአፓ ይልቅ አዛው ባለው የውስጥ ግብ ግብ እንደሚወሰን አጥብቀን ተከራከርን። እንደ ሁሌው መተማመን እንደሚያስቸግረን ተግባብተን ተለያየን።

'የሱ---ፍ አበባ፣ ካፈርኩ አይመልሰኝ...አቋሜን ገፋሁበት!'

የፖሊት ቢሮው የአንቅልፍ እንከብል እንደዋጠ ሰው እልም ባለ ስመመን የገባባቸው ወራት እያለፉ ነው። እዳው ለእኛ ሁሉ መትረፉ አልቀረም። የደርግ/መኢሶን ጥምረት በመከላከል ጥረቱ እንደተወሰነ ነው። ነገር ግን እንደምንም ብሎ በሆነ ቀን ወይም በሌላ ጊዜ በመጨረሻ ዐቅሙ ይናደፋል። ስለዚህ አንዳንዴ አንዱ መዋቅራችን ላይ ጠንከር ያለ ምት ማሳረፍ አልከበደውም። በዚህ አንድ ምት ብቻ አርባ ሀምሳ ንቁ አባላት ይያዙብናል። መያዛቸው የግንኙነት መስመሮች እንዲቋረረጡ አደረጉብን። ግንኙነት ሲጠፋ ደግሞ በሽህ የሚቆጠሩ አባሎቻችንን አደጋ ላይ ይወድቃሉ። በደርግ ጸጥታ ኃይሎች ይደረስባቸው አይደረስባቸው ለማወቅ እንኳን በሩ ድርግምግም ይልብናል። በዚህ ጊዜ ፖሊት ቢሮው ይጮኻል...

"ጓድ ኢሳያስ፣ ጓድ አላምረውንና ጓድ ሽዋዬን ይዘኸ አሁኑኑ እንድትመጣ!" የዘርው ስልክ እረፍት ነስቶን ከረመ።

ሁላችንም የማእከላዊ ኮሚቴ አባላትና ተለዋጮች በሥራ መተንፈሻ አጣን። የተቋረጡ መስመሮችን በአዲስ መልክ እንቀጥላለን። የተነቃባቸውን አባላት ወደ አዲስ አበባ የቅርብ ገጠሮች አድርሰን እንመለሳለን። ቀኑን ሙሉ። ከዐቅም በላይ ሲሆን ቢታኒያም ገባችበት። ጋራዥ ውስጥ ከቆሙና በቀላሉ ልንጠግናቸው ከቻልናቸው መኪናዎች ሥራ የፈታ የለም። ጥገናው ከተጀመረው የመኢሶኖች ሽፍን ኒሳን በስተቀር ሁሉንም አንቀሳቀስን። ቢታኒያ አድራሻቸው የጠፋውን የፈረንጆቹን ፊያት 127 መኪና ይዛ ሰነበተች። በመከራ ለምኛት ብዙም እስጊ ያልሆነውን የዱከም መውጫ ያዘችልኝ። ገና በዚህ ሳምንት እረፍ አልን።

"ስሙዬ፣ በጣም አደንቅሀለሁ፣ እወድሀለሁ፣ አከብርሀለሁ!" አለችኝ ስሜታዊ ሆና።

"እንዴት፣ እናትዬ...ምን አዲስ ነገር አይተሽ ነው?"

"በቃ፣ 'ገቨርዲኒዝምና የሱፍ አበባዊነት' ያልከው ክርክርህ ገና አሁን ነው በደንብ የገባኝ። እኛም ድርጅቱም አደጋ ላይ ነን። ገጠር ብንገባ ኖሮ እንኳን ትልቅ ድርጅት ይዘን እስር ሆነንም እንበቃ ነበር። ማሚ ስትነገረኝ አንድ የመርሐቤቴ ሽፍታ ብቻውን ሆኖ ዱር እያደረ መንግሥትን እስከ አሥራ አምስት

ዓመት ያንቀጠቀጣል! የእኛ መሪዎች ጉድ ነው የሠሩን..." የቀኝ እጄን ጣቶች በቁጭት አንጣጣቻቸው።

በጣ---ም ብትዘገይም እውነቱን ስለተረዳችልኝ ደስ አለኝ። ችግሩ ቀውሱ አሁን ከድጡ ወደ ማጡ እየገባ ነው። የፖሊት ቢሮው በውስጣዊ አመራር ቀውስ መታመሱን ቀጥሏል። ከትላንትና ወዲያ አጭር የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ አድርገን ነበር። የሁኔታ ግምገማ ጊዜውም አጭር ነበር። የክፍሉ ተዘራን ሪፖርት ብቻ ነው ያዳመጥነው...

"...እስከአሁን 'አጥቅቶ መከላከል' ፖሊሲው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ኢሕአፓና ኢላአማ ወደ 170 የደርግ/መኢሶን ሰዎችን ለቀብር አብቅተዋል። ወደ 30 የግድያ ሙከራዎች ሳይሳኩ ቀርተዋል። ከዚህ ውስጥ የደርግ ደህንነት መዋቅር መሪ የሆኑትን ኮሎኔል ተካ ቱሉን ለመግደል የተደረገው ሙከራ ይገኝበታል። ሻለቃ ጌታቸው ሽበሽንም መግደል አልተቻለም። ደርግና መኢሶን በወሰዱት የመከላከል እጸፋ ከ40 በላይ አባሎቻችን ተገድለዋል። 235 አባሎቻችን በስድስት ከተሞች ተይዘዋል። 160 የሚሆኑትንና የተነቃባቸውን አባሎች ወደ ገጠር ማሸሽ ችለናል። ከአደጋ ግን ነጻ አይደሉም። አንዳንድ ከተሞች ላይ ተይዘው የታሰሩ አሉ። መኢሶን በፋብሪካዎች ውስጥ የማጋለጥ ዘመቻ ለማካሄድ የሥነ ሥርዓት መመሪያ እያዘጋጀ ነው..."

"ኤጭ፣ መንጋ ተልባ እጅ ሁሉ!" ወይዘሮ ማስተዋል ትዝ አሉኝ።

ንድድ እድርጎ ያናደደኝ ደግሞ በተካ ቱሉ ላይ የታቀደው ግድያ የከሸፈው በሕዝብ ትግል መሆኑ ነው። ታጣቂዎቹን የሰፈሩ ሕዝብ ከበባ አድርጎ መድረሻ አሳጣቸው። ደጀኔ ቦንብ አፈንድቶ ሽፋን ባይሰጣቸው ኖሮ ሁሉም አልቆላቸው ነበር። ሕዝቡ የተፋለመው ግን ለቆየ ባህሉ መከበርና ለሰላሙ ሲል ነው። የየትኛውንም የኢትዮጵያ ብሔረሰብ ወግ እንፈትሽ።"አድብቶ መግደል" የሚጨበጨብለት ጀግንነት አለመሆኑን ደጋግሜ ተናግሬያለሁ። በዚህ ላይ የአዲስ አበባ ሕዝብ በተለያዩ የፖለቲካ ፍላጎቶች የተኸገረገረ ሕዝብ ነው። ነፍስ ያወቀ ሰው ሁሉ የኢሕአፓ ደጋፊ ነው ብሎ ማሰብ ራሱ ከደርግ ድንቁርና የባሰ ድንቁርና ነው። ሰሚ አላገኘሁም።

'ዘርዑና ዶክተር ተስፋዬ አሁንስ ምን ያስቡ ይሆን?' ራሴን ጠየኩት።

ወደዱም ጠሉም ይህ ቅልብጭ ያለ ድርጅታዊ ውድቀት ነው። ነገር ግን ድርጅቱ ዐይኑን ጨፍኖ ዐይቶ እንዳለየ አሳለፈው። እንደበቀደሙ ስብሰባ ያስጠላኝ ነገር የለም። ኢሕአፓ በዚህ የብረት ጉጠት ታንቆ ተይዞ የማእከላዊ ኮሚቴው ትኩረት ግን ሌላ ቦታ ነበር። ብርሃነመስቀል ረዳና ጌታቸው ማሩ። በወረቀት ተጽፎ ቀደም ብሎ በተላከላቸው ክስ ላይ ስንነዛነዝ አመሸን። ጉዳያቸው የአንጃኝነት ማስረጃ ተገኘበት። ጉዳዩን መላው የፓርቲው ኮሚቴዎችና አባላት እንዲያውቁት ተወሰነ። አንጃኝነት የከራሞታችን አፍ

መፍቻ ቃል ሆነ። ከዚያ በጸጥታው ቀውስ መባባስ ተሳቦ ስብሰባው አለቀ።

'ብርሃነመስቀል፣ ገና ዓይኑን ሳይገልጥ ጀምሮ ጡጦ እያጠባ ባሳደገው ነብር ተነከሰ!' መንፈሱ ስብርብር ብሎ ሳየው አሳዘነኝ።

***

ቢታኒያ እንደ ሁሌው የድርጅት ሥራ ይዛለች። ቴሌቪዥኑን ድምጹን ዝቅ አድርጋ ከፍታው የምሽት ፕሮግራሙን ማስጀመሪያ የተለመደውን የሰሜን ተራሮችን ምስል ያሳያል። እንገቷን አቀርቅራ ነው የምትጽፈው። አዲሱ ሥራዋ ከጭንቀት የገላገለኝ ሥራ ስለሆነ ከልብ አወደዋለሁ። ከእኔ ጋር አውሏታል።

ቁጣዋን ለማብረድ የሁሌውን ዘዴ መጠቀም አለብኝ። ቀስ ብዬ በጸባይ አጠጋትና በጸጥታ ቀጭ አላለሁ። እግዛት ስጀምር ታዲያ መለስ ትልልኛለች። ዛሬም ይህንኑ አደረኩ...

"ምሮን፣ እኔን ማናደድ ነው የሚያስደስትህ? እስቲ ለእኔ ብለህ እንጦሮጦስ ግባ!"

አሁን ሰላም ወረደ። ብዙም ሳንቆይ ተሰብስበው የተከመሩ ወረቀቶችን ማገበብ ጀመርኩ። ከሕዳር ወር ጀምሮ ምርር አድርጎ ያስመረረኝ ጉዳይ ሆኖ አገኘሁት። ብርሃመስቀል ረዳና ጌታቸው ማሩ። በቅደም ተከተል ጓድ "ሀ" እና ጓድ "ለ" የሚል የተመሰጠረ ስም ተሰጥቷቸዋል። ስፋት የተባሉት ወንጀል ተዘርዝሮ "እንጀኝነት" በሚለው ቃል ታስሯል። የድርጅታችን የወቅቱ ከፍተኛ አደጋ መሆኑ ተሰምሮበታል።

"ቤቲዬ፣ በፍጹም በፍጹም ትክክለኛ መደምደሚያ አይደለም።" አልኳት በወረቀቱ የመጨረሻው ገጽ ላይ እንዳተኮርኩ።

"እንዴት? የሠሩት ሥራ መቼም ትክክል ነው ብለህ የምትከራከር አይመስለኝም።"

"ኖኖ...አባባሌ እነርሱ አልተሳሳቱም አይደለም። 'ዋናው የድርጅታችን አደጋ' ናቸው' የሚለውን ግን አልቀበልም። ለ'ኔ ዋናው የድርጅታችን አደጋ የገዛ ራሳችን የሉፍ አበባዊነት አባዜ ነው። ዋናው አደጋ ከዚህ የተዛነፈ አስተሳሰብ የበቀለው 'እያጠቁ መከላከል' ሥልት ነው። ብርሃነመስቀልንና ጌታቸው ማሩን የፈጠራቸው ይሄው በሽታ ነው።" ስሜታዊነት ገነፈለብኝ።

ቢታኒያ በጸጥታና በጭንቀት ተውጣ ታዳምጠኛለች። በረጅሙ ተንፍሳ ስታበቃ ጥያቄ አነሳችልኝ...

"ምን ዓይነት ናላ አሚያዞር ነገር ነው የገጠመኝ፣ አምላኬ! አሁን እየመጣ ያለው የጥያቄ ጎርፍ'ኮ 'ማነው

ጥፋተኛ?' ከመባሉ በፊት 'አንጃኝነት' ራሱ ምን ማለት ነው? ቡድንኝነትስ? ለዚህ መልስ መስጠት የኔ ግዴታ ነው። ይህንን ግልጽ ካደረኩ በኋላ ጥፋተኛውን መለየት የአባላት ጉዳይ ነው። እስቲ በደንብ አድረገህ አስረዳኝ፣ ሰሙዬ..." ጭንቅንቅ አለች።

" ምን መሰለሽ...አንድ ማርከሳዊ ድርጅት ልክ እንደ ሰው በሆነ ስህተት ወይም ጉድለት ምክንያት ጤናው ሊታወክ ይችላል። በዚህ በኩል ሁለት ጉዳይ የበሽታ ምንጮች ወይም አደገኛ ቁራጭ መጋዞች አሉ። 'የአመራር ቡድንኝነት' (ከሊክ) እና አንጃ (ፋክሽን) ናቸው። 'ቡድንኝነት' ከፖለቲካዊና ርእዮተዓለማዊ መሰፍርቶች ውጭ በሌላ ማኅበራዊ ገመዶች መተሳሰርን ያመለክታል። የጋራ ጎጥ፣ ሃይማኖት፣ ብሔር፣ ሞያ፣ ጾታ ወይም ሌላ ትስስር። ቡድንኝነት የብዙኃን ድምጽ ብልጫ ሥርዓትን ሽፋን አድርጎ ምክንያታዊነትና ሳይንሳዊነት የሌለው ስሜት ሙጥኝ ማለት ነው። ገባሽ፣ የኔ ፍቅር?"

"ጉብቶኛል፣ ጨርስልኝ..."

"አንጃ ደግሞ ለቡድንኝነት የሚሰጥ ግብረመልስ ነው። በዚህ ምክንያት ትክክል የሚባል አንጃ ሊኖር አይችልም። አንጃ 'ቡድንኝነት' ተፈጥሯል' በሚል መሠረት የሌለው ስጋትም ሊፈጠር ይችላል። 'የያዝኩት ከርከር እውነት ሆኖ ሳለ በድምጽ ብልጫ ተሸነፍኩ። ስለዚህ የሚደግፉኝን ይዤ በራሴ መንገድ መጓዝ አለብኝ' የሚል ግፊት አንጃን ይፈጥረዋል። አንጃ በአንድ ጉዳይ ትክክል ነው ተብሎ ቢገመት እንኳን ከችግር ሊጸዳ አይችልም። ምክንያቱም 'አብዛኞቹ ትክክል አይደሉም' ብሎ በተስፋ መቁረጥ የሚመጣ የመነጠል ዝንባሌ ነው። ከዚያ በድርጅት ውስጥ ድርጅት የመፍጠር እንቅስቃሴ ይከተላል።"

"ትክክል ነህ፣ ሎጅካል ንጽጽር ነው ያደረከው፣ ሆዴ። ጨርስልኝና ጽፌ እነብልሃለሁ..."

"ቡድንኝነት የጠቀላላው ድርጅት አደገኛ ሕመም ነው። ነገር ግን በብርቱ ትግል ሊፈወስ ይችላል። አንጃኝነት ደግሞ ድርጅታዊ እጢ ነው። ተቆርጦ ካልተጣለ ቀስ በቀስ ሁሉንም አካል ሽባ ያደርጋል። ትልቅ ጋን በትንሽ ጠጠር ሊደገፍ ይችላል። በዚያው ልክ ደግሞ ትልቅ ጋን በትንሽ ጠጠር ሊሰበርም ይችላል። ወይም ትልቅ ዛፍ በራሱ ሊወድቅ የመቻሉን ያህል በትንሽ መጥረቢያም ሊቆረጥ ይችላል። ቡድንኝነት ጋንና ዛፍ ማንም ሳይነካቸው በራሳቸው ችግር የሚወድቁበትን ሂደት ይወከላል።" ቀና ብዬ ዐይቻት ቀጠልኩ፣ "አንጃኝነት ደግሞ በትንሽ ጠጠርና መጥረቢያ የሚወድቁበትን ሁኔታ ያመለክታል። አንጃኝነት ተደርቦ የሚበቅል እጢ ስለሆነ አከሞ ማዳን ከባድ ነው። አንጃ በምንም ተዐምር የድርጅቱን አመራር ሊቀማ አይችልም..."

ቢታኒያ አስከርቢቶዋን ከወረቀት ጋር ልታገናኝ እጇን ሰደድ ስታደርግ ቴሌቪዥኑ ርእሰ ዜና ማሰማት

ጀመረ። የመጀመሪያው ርእስ ዜና በመግለጫ ተደግፎ ቀረበ። ድምጽ አልባ የማርሽ ባንድ ቅንብር ቀደመ። መግለጫ አንባቢው የአዲስ አበባ ሕዝብ እንደ እድር መርዶ ነጋሪ የሚያየው አሰፋ እያና ነው። ያለ አንዳች ብርቱ ነገር ድምጹ አይሰማም። ያንበለብለው ጀመር...

"ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የተሰጠ መግለጫ! የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! በደምህ የዋገርህለት አብዮትህ የበግ ለምድ ያጠለቁ የውስጥ ቀልባሾችን በመደምሰስ ራሱን ከቅልበሳ አድኗል። ደስ ይበልህ! ታሪክና አብዮቱ የጣለባቸውን አደራ በልተው ከአብዮትህ ጠላቶች ጋር በመመሳጠር ጠልፈው ሊጥሉህ የነበሩ ሰባት የደርግ አባላት አብዮታዊ እርምጃ ተወስዶባቸዋል። እነርሱም ጀኔራል ተፈሪ በንቲ፣ ሙቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ፣ ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል..."

"ሻ----ምበ----ል ሞ---ገ----ስ?"ጮኼ ጭንቅላቴን ያዝኩ።

###

ዐይኖቼና ጆሮዎቼ ላይ የብራ መብረቅ የመሰለ ቅጽበታዊ ነጎድጓድ ቀድሞ አስተጋባ። ሳይታሰብ ፈንድቶ በተቀመጥንበት ሁለታችንንም በድን አደረገን። ምን እንደገፋው የማይታወቅ ግዙፍ መርግ ከቋጥኝ ቋጥኝ እየተጋጨ ማረፊያው ላይታወቅ ቀጥ ብሎ መጣብን። በተቀመጥንበት ጭቃ ሊያደርገን ተምዘገዘገ።

ከመርጉ ጀርባ ኮሎኔል መንግሥቱ የተቆጣ ጋኔል መስሎ፣ እንደ ከሰል የጠቆረ ፈረስ እየጋለበ፣ጥርሱን እያፋጨ፣ አይኖቹን ጉልጉል አድርጎ፣ ወጋግራ የሚያክል የተሳለ ሰይፍ በቀኝ እጁ እየነቀነቀ፣ አፈሙዙ የተከፈተ በርሜል የሚያክል ዲሞትፈር በግራ እጁ ወድሮ፣ ግዳዩን ለመጣል ያንንም ይሄንንም በሚቃብዙ ዓይኖቹ እያየ፣ ከንፈሩን ንክስ አድርጎ... ንሥር አሞራ መስሎ ወደ ምድር ሲምዘገዘግ...ዓይነ ህሊናየ እንደፎቶ ቀጭ አደረገው...

ቤቲ ዜናው ከኔ በላይ አደንዝዟታል። ወደ ራሷ ስትመለስ ከፊት ለፊቷ የተከመረውን ወረቀት በእጆቿ አንድ ላይ ጭምድድ አድርጋ በመጨረሻው ኃይሏ ወደ ግድግዳው ወረወረችው። ነጥሮ ሲመለስ ወለሉ ላይ ብትንትን ብሎ አደይ አበባ መሰለ።

እነ ሻምበል ሞገስ በፈራ ተባ አላልተው ያሠሩት ጨካኝ ተኩላ ሰንበለቱን በጥሶት ወጣ። እና ከዚህ በኋላ ድርጅታችን ኢሕአፓ ምንድነው? ምንም አይደለም። በቃ፣ በኢትዮጵያ የጸጸት ታሪክ ላይ የተጻፈ የድሮ ትዝታ! አሁን ደግሞ እግሮቹ ታስረው ለኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም እርድ የቀረበ የቆሌ ዶሮ ሆነ!

መግለጫው የተገደሉቱን መኮንኖች ወንጀል ዘርዝሮ ሲያበቃ የይርጋ ዱባለ ዜማን አስከተለ...

የፍየል ወጠጤ ትከሻው ያበጠ ልቡ ያበጠበት፣

እንዋጋ ብሎ ለነብር ላከበት።

የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች፣

ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች።

ኢትዮጵያስ ከዚህ በኋላ ምንድናት? አገር? ወንዝ? ቀዬ? ተራራ ሜዳ? አይይይ...ሌላ ምንም አይደለችም። በቃ፡ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ተንበርክካ አምጣ የወለደቻቸው፣ ወልዳ በመከራ ያሳደገቻቸው፣ አሳድጋ ያስተማረቻቸው... የገዛ ልጆቿ መካነመቃብር ናት! የቤተክርስቲያን ጓሮ! ነብዩ ሙሴ መቃብሬን ለማንም እንዳታሳዩ ብሎ ነበር። ይህ ለአሁኗ ኢትዮጵያ ትንቢት ሳይሆን ቀልድ ነው። ሩቅ መሄድ አያስፈልግም። ይሄው እኔና ፍቅረኛዬ፣ የትውልዱ ለውጥ ዘማሪዎች፣ አስፓልት ላይ የሚታየው አፍላ ወጣት ሁሉ... ከሞት ጋር ተቃቅፈናል። ሞትና ቀብር የአደባባይ ምሥጢር የሚሆኑበት ቀን ደረሰ።

'ትምህርት ብላሽ! ወጣትነት ብላሽ! ድርጅት ብላሽ!' ጆሮዬ የሚያመጣው ጩኸት እረፍት ነሳኝ።

ቢታኒያ እንደምንም ታግላ ቀና ብላ አየችኝ። አንድ የሆነ ስጋቷን ወይም ብሶቷን ልትነግረኝ የፈለገች ትመስላለች። ዐይኖቿ ስሜቷን ሁሌም አይደብቁላትም። በትካዜ ተውጬ መልሼ ዐየኋት። 'ምን ይሻለናል? የት ነው እምደብቅሽ? የት ነው የምሰውርሽ? ከእንች በፊት ያድርገኝ!'

"ብቻ----------ልጄን ሳላየው..." ዐይኖቿ እንባ አቀረሩ።

"ልጄ---ን ሳላ----የው??"ጆሮዬ በትክክል ይህንን ቃል ሰምቷል ወይስ ህልም ነው?

ቢታኒያ በዚህ ሰዓት የምትቀልድ ጅል አይደለችም። በፍጹም አትቀልድም፤ በትክክል ጸንሳለች። ፍላጎቷ እንደነበር በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደጋግማ ነግራኛለች። የልጅ አባት አድርጋኝ ኖሯል። ልጅ! ል--ጅ! ል-----ጅ! ልቤ ተነስታ ፈረጠች።'ፍቅረኛዬ በድርጅቴ ስህተት ልጄን ይዛ አትሞትብኝም! እኔ ሞቼ እሷ በልጄ ታስበኝ!' ጨርሶ በማላውቀው ፍጹም እንግዳ ስሜትና የውስጥ ግፊት አፈፍ አድርጌ ጥምጥም አልኩባት፣ የልጄን እናት!

# 33

የሌተናል ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም የተሳካ መፈንቅለ መንግሥት ከተካሄደ ሦስት ቀናት ማለፋቸው ነው። ቢታኒያ ገና በማለዳ ከእንቅልፌ ቀሰቀሰችኝ። ሽሮ ሜዳ አሜሪካን ኢምባሲ አጠገብ ወዳለው የሴቶችና ሕጻናት ክሊኒክ እንድወስዳት ነበር። በዚያውም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስድስት ኪሎ ግቢ ጎራ ብላ በሚቀጥለው መንፈቀ ዓመት ትምህርቷን ለመቀጠል ማመልከቻ ታስገባለች። እንደማይሆን ልቧ እየነገራትም መሞከሩን መርጣለች። ወይዘሮ ማስተዋልን ለማስደሰት ብቻ ያደረገችው እንደሆነ አውቃለሁ።

"ከእንግዲህ ዲግሪዬ ልጄ ነው። መነሳንሴ ደግሞ ባሌ ሰመረ ማንደፍሮ..." ቤቲ ለሸዋዬ ነግራት ሸዋዬ ለኔ ነግራኛለች።

ልክ እንደነቃሁ ወዲያው ትዝ ያለኝ የኮሎኔሉ ድርጊት ነው። ሰውየው በማግስቱ ጭፍጨፋ አለመጀመራቸው አስገርሞኛል። የዝግጅት ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው ግን አላጣሁትም። ዝግጅታቸውም ጥቂት ቀናት ግፋ ቢል ሳምንታት ሊወስድ እንደሚችል ገመትኩ። አንድም ተስፋ አይታየኝም። የትንፋሻችን መቆየት የቀናት ጉዳይ ነው።

'ማምሻም ዕድሜ ነው። ለ'ኔ ችግር የለም። ጭንቀቴ ለፍቅረኛዬና ለልጄ ነው...' ተነስቼ ልብሴን ለባበስኩ።

ዛሬ የኮሎኔል መንግሥቱ ቡድንና መኢሶን የድጋፍ ሰልፍ መጥራታቸውን ሙሴ ባልዲ ትላንት ምሽት መጥቶ እንደቀልድ ነግሮናል። ስለጭፍጨፋ ዝግጅቱ ጭምር ፍንጭ ሰጥቶናል። በተለይ መኢሶን ወገቡን ታጥቆ ለበቀል ሽር ጉድ ማለቱን ተያይዞታል። ሙሴ ባልዲ የአንድ ቀን ሙሉ ሥልጠና ወስዶ ሲመለስ ነበር ወደ እኛ ጎራ ያለው። "አናርኪስቶችን" መንጥሮ መደምሰስ በሚቻልበት ሥልት ላይ

ያተኮረ ስልጠና ነበር። ጎራዴው እየተሳለ እንደነበር ገባኝ።

የወንድ ልጅ እናት ታጠቂ በገመድ፣

ልጅሽን እምራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ!

የዛሬ ዓመት የተለቀቀው የአያሌው መስፍን ዜማ ምንም ስሜት አይሰጠኝም ነበር። አሁን አሁን ስሰማው ግን ትርጉም ይሰጠኝ ያዘ። ይህ በተራው ፍርሀት ይለቅብኝ ጀመር። እነ ቀን አያውቁ ኢሕአፓና ማእከላዊ ኮሚቴው አሁንም አዲስ አበባ ናቸው። ባለፉት አራት ቀናት በከባድ ድንጋጤ በመመታታችን ይህ ነው የሚባል ግንኙነት አላደረግንም። የተሰጠ አጸፋም ይሁን የተሠራ ሥራ የለም። ለነገሩ ኢሕአፓ አሁን የፖለቲካ ፓርቲ መሆኑ ቀርቷል። ሙሉ በሙሉ ወታደራዊ ተቋም ሆኗል። ልቤ ተሰበረ።

'አጥቅቶ መከላከል! ባዶ ራስ ያፈለቀውን ባዶ ሥልት ይኸው ውጤቱን እየነው...' መጸዳጃ ቤት ሆኜ ብስልስል አልኩ።

ፊቴን ታጥቤ ስወጣና ስልኩ ሲንጫረር አንድ ሆነ። ደስ የማይል ስሜት ተሰማኝ። ሁለቴ እንደተንጫረረ ቢታኒያ ስታነሳው ይሰማኛል። አጭር ነገር ተነጋግራ ወደ እኔ ተጣደፈች። "ስሙዬ፣ ያንተ ነው..." ስትለኝ እሷም ደስ አላላትም። በዚህ ቀውጢ ጊዜ የሚደወል ስልክ ለበጎ እንደማይሆን ተሰምቶናል። ሄጄ አነሳሁት። የዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ድምጽ መጣ። ሰላምታ መለዋወጥ፣ የኮድም ይሁን የይፋ ሥም መጠራራት፣ መልካም ምኞት መሰጣጣት...የለም። ትንፋሽ የት አለና! አጭር በምሥጢር የተሰወረ መልእክት ነግሮኝ ስልኩን ዘጋ። እንደቆምኩ ወዲያው ተረጎምኩት...

"ልክ ሰባት ሰዓት ሲሆን በሳሪስ መንገድ ስብስቴ ነጋሢ ፲ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትሄዳለህ። እዛ ስትደርስ መኪናህን አቁመህ ውረድ። ፊት ለፊት ነጭ ኖራ የተቀባ መኖሪያ ቤት አለ። በጀርባ በኩል አንድ የዘይትና የቅባት ሱቅ አለ። እዛ ስትገባ ትንሽዬ ሴት ልጅ 'አላምረው' ነኝ ስትላት ትቀበልሀለች። አብረሀት ወደ ውስጥ ሂድ..."

ትእዛዙን እንደ እንኩብል ዋጥ አደረኩት። ለምን? እንዴት? ብሎ መጠየቅ የኢ.ሕ.አ.ፓ ባህል አይደለም። ያለ መሪ የቀረው ኢ.ሕ.አ.ሠ ግን ትቶታል! እርግጥ ለዶክተር ተስፋዬ ያለኝ ክብር በጣም ቀንሷል። ሁለት ምክንያታዊ ይሁኑ አይሁኑ ያላሰብኩባቸው ምክንያቶች አሉኝ። በሰኔው የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ዶክተር ተስፋዬ አሲምባ ሄዶ ስለነበረ አልተገኘም። "ገሸርዲኒዝም" ጽሑፌን አቀረብኩ። ቅድበታዊ ተጽእኖ አሳድሮ ለውጥ አስከተለ። ለድርጅቴና ለአገሬ አንድ ትልቅ ሥራ እንደከወንኩ ተሰምቶኝም

ነበር። ሙሉ ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ውሳኔ ስንሄድ ይህ ነው የሚባል ክርክር አልገጠመኝም...

"ማእከላዊ ኮሚቴውና ዋና ዋና የፓርቲ ኮሚቴዎች ወደ አሲምባ ይወጣሉ። የድርጅቱ ስትራቴጅካዊ ጥቅም ያላቸው ንብረቶችና ጥሬ ገንዘብ በሙሉ አብሮ ይጓጓዛል። የዚህን ውሳኔ አፈጻጸም አጥንቶ የሚያቀርብ አንድ ኮሚቴም በዛሬው ዕለት ሰይመናል..."

ኢሳያስና እኔ ከስብሰባ መልስ ምድር ቤታችን ስንደርስ ከሸዋዬና ከደጀኔ ጋር እቅፍቅፍ ብለን ደስታችንን አበሰርናቸው።"ኢሱ፤ ሸዋ፤ ደጀን...ብዙ ታግለን ተሳክቶልናል። ደስ ይበላችሁ! ትክክለኛው 'ፋኖ ተሰማራ' ይህ ነው!" ፍንድቅ አልኩ።

"ሰመሬ፣ ተስፋ አለመቁረጥን ስላስተማርከኝ እወድሀለሁ!" ኢሳያስ ጀርባዬን እየጠበጠበ አወደሰኝ።

"እራታችንም ቢታኒያን ጨምረን ወደ አርማጭሆ ውልቅ ነው። በፍጹም መለያየት የለብንም!" ሸዋዬ ጨመረች።

ቢታኒያን ስነግራት አንድ ቅድመሁኔታ ከተሟላላት ደስተኛ መሆኗን ነገረችኝ። "ከባሌ ጋር እስካልተለያየሁ ድረስ..." ተስማማች። ጋራዥ ውስጥ የቆሙ መኪናዎችን በሙሉ ጠግነን ለማዘጋጀት ተስማማን። የመኢሶኖችን መኪናም አንተዋትም። በደረስችበት ቦታ ትተናት እንሄዳለን እንጂ እዚህ አቁመናት እንሄድም። ቃላችን ነው።ጌታቸው ማሩ፤ ጸሎተ ሕዝቅያስና ኢሳያስ ናቸው በኮሚቴንት የተመረጡት። ጥናታቸውን ሲሰሩ ኢሳያስ ወሳኝ ሚና ነው የተጫወተው። ሥራቸውን ጨርሰው ለነሐሴው የማእከላዊ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ አቀረቡ። ዶክተር ተስፋዬ ከትግራይ መልስ በዚህ ስብሰባ ላይ ተገኝቷል። እንደሁሌው በጸጥታ ተውጦ ጥናቱን በጥሞና ያዳምጣል...

ጌታቸው ገለጻውን ቀጠለ...

"የማእከላዊ ኮሚቴው ጽሕፈት ቤት አሲምባ ይሆናል። አዲስ አበባ ያለውን የፓርቲ ሥራ የሚያስተባብር አንድ አገናኝ ኮሚቴ ይዋቀራል። ኮሚቴው የሚሠራቸው ተግባራት ዘጠኝ ይሆናሉ። መረጃ፣ ገንዘብ፣ ምልመላ፣ ሥምሪት..." ሁሉንም ዘረዘረ።

ሲጨርስ ዘርዑ መድረኩን ለውይይት ክፍት አደረገው። እኔ ይቃወማል ብዬ የጠረጠርኩት ብርሃነመስቀልን ነበር። ልቡ ወደ "ሕብረት ግንባር" ካደላ ወዲህ አሲምባ የሚል ቃል መስማት እንደማይፈልግ ዐውቃለሁ። ክርክሩን ሳጠቃልለው "የኢሕአሠ ዘመን አከትሟል" በሚል ወስጃዋለሁ።

ተቃውሞ የመጣው ግን ካላሰብኩት አቅጣጫ ከዶክተር ተስፋዬ ነው። ቀድሞ እጁን ሲያወጣ ድጋፍ መስሎኝ ቅብጥብጥ ብዬ ነበር...

"የማእከላዊ ኮሚቴው ወደ አሲምባ መውጣትና አዲስ አበባን በአገናኝ ኮሚቴ መምራት የበርሊኑ የኢሕአፓ መሥራች ጉባኤ ካጸደቀው ደንብ ጋር ይቃረናል። አንድም ደንቡ መቀየር አለበት፤ አለያም እቅዱ መሰረዝ አለበት።"

ገነባሁት ያልኩት ቤት በአንዴ ፍርስ ፍርስርስ አለ። ከርከሩ ጨርሶ አላሳመነኝም። "የማእከላዊ ኮሚቴውን ጽሕፈት ቤት ቦታ መወሰን የኮሚቴው መብት እንጂ በጉባኤ የሚጸድቅ መሆን የለበትም" ብዬ ተከራከርኩ። ነገሩ በተለይ ለፖሊቲካ ቢሮውና ለአንዳንድ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ድሮውንም ከአንገት በላይ እንደነበረ ቁልጭ ብሎ ታየኝ። በአንዴ መንፈሳቸው ቅይርይር አለ። "ወደፊት በሚደረግ የፓርቲው መለስተኛ ጉባኤ ይታያል" ብለው ዘጉት። አሁን ሳስበው ዶክተር ተስፋዬ የሰፍ አበባን ኮቱ ኪስ ሰኩቶ ያየሁበት ቀን ነው ያ ቀን።

ሁለተኛው ምክንያቴ ያው "አጥቅቶ መከላከል"ን ተስፋዬ ልክ እንደ ሃይማኖት ሙጥኝ ብሎበት ማየቴ ነው። ይሄው ዛሬ የዘራነውን እያጨድን ነው። ያም ሆኖ እምነቱንና ጽናቱን አደንቅለታለሁ። ትእዛዙንም ያለማመንታት የመቀበል ግዴታ አለብኝ።

ቢታኒያ እስከምትዘገጃጅ ድረስ የተወሰነ ጊዜ አለኝ። የዘወትር ልምዴን ተከትዬ ወይዘሮ ማስተዋልን ሄጄ ስለጤንነታቸው ጠየኩ። በጣም ተሽሏቸዋል። አርባ ጾምን በሙሉ ሱባኤ ለመግባት ወደ ደብረሊባኖስ የጎዞ ዝግጅት መጀመራቸውን ዐውቄያለሁ። በዚህ ሁኔታ ሲሆን አይታየኝም እንጅ አድርሻቸው የምመጣውም እኔ ነኝ። ምርቃቴን ተቀብዬ ወደ ምድር ቤቴ ሄድኩ። ሸዋዬና ደጀኔ አጠገብ ለአጠገብ ተቀምጠው ቁርስ እየበሉ አገኘኋቸው። ኢሳያስን ዘርዐ አስጠርቶት መሄዱን ነገሩኝ። ከሁኔታቸው ስለ አንድ ብርቱ የድርጅት ጉዳይ እያወሩ እንደነበር ጠርጥሬያለሁ...

"ሸዋ፣ ደጀኑ፣ ምንድነው፣ ችግር አለ እንዴ?" ቅልብልብ ያልኩባቸው መሰለኝ።

"አየ አላምር፣ ችግራችን ከችግርነት አልፎ ውድቀት ከሆነ ሰነባበተ አይደል፣ እንዴ?!"

"እሱስ ልክ ነህ...አሁን ደግሞ ምን መጣ ብዬ..." ከትንፋሽ በሳሱ ቃላት ተናገርኩ።

"ብርሃነመስቀልንና ጌታቸው ማሩን ከነአንጃው አባሎቻቸው ጋር በቁጥጥር ሥር እንዲናውል ታዘናል።"

ደጀኔ ይህን ተናግሮ አንገቱን አቀረቀረ።

አርምኛው እንደማይቀርላቸው ዐውቃለሁ። ፖሊት ቢሮው ወደዚህ ውሳኔ የደረሰበት አጣዳፊ ግፊት ምን እንደነበረም ሰምቻለሁ። በተለይ ብርሃነመስቀል ጉድ ሠርቷቸዋል። በሥርጭት ላይ የነበሩ ጦር መሣሪያዎችን ከመስመር አስወጥቶ እንዲሰወሩ አድርጓል። በጣም አሳሳቢ አርምኛ ነው የወሰደው። ይሁን እንጅ እንዲያዙ ሲወሰን ያነሳሁት የጥያቄ ጅረት አለ።

"የት ነው እስር ቤቱ? ፖሊሱስ ማን ነው? ስንት ቀን ነው የሚታሰሩት? የሚቀርቡበት ፍርድ ቤትስ የት ነው? 'አንታሰርም' ብለው በራሳቸው ታጣቂዎች አጸፋ ቢሰጡስ ምንድነው የሚደረገው? ቅለባቸውስ እንዴት ነው የሚቀርብላቸው?"

መልስ ይሰጠኛል ብዬ የምጠብቀው ሰው የለም። ሸዋዬ ይበሉት ከነበረው የስንዴ ቅንጬ ለእኔም አቀረበችልኝ። በሻይ እያወራረድኩ በላሁ። የምንነጋገረው ሁሉ የውድቀትና የመርዶ ዜና ሲሆንብኝ በረሀ ጥፋ ጥፋ የሚል ግፊት መጣብኝ። በልቼ ጨርሸ ሳህኑን ስመልስላት የሸዋዬ ደወል ተቅጨለጨለ። ቀና ቀና ብለን ተያየን። ቢታኒያ መሆኗን መነጋገር አላስፈለገንም። ቻው! ብያቸው እየተጣደፍኩ ውጥቼ ሄድኩ። ጋራዥ ገብቼ ፊያት 127ቷን መኪና ይዤ ቤቷን በር ላይ አሳፍሪያት የመነሀሪያን መንገድ ተከትየ ነዳሁ።

"ሰሙዬ፤ አሁን ትንሽ ቀደም ብሎ ሙሴ ባልዲ ቁርስ ስጡኝ እያለ ቤት መጥቶ ነበር።" ቢታኒያ ፈገግ ብላ ጀመረችልኝ።

"እ----ሸ፤ አዲስ ነገር ይዞ መጥቷል?" የመባነን ያህል ሰፍ ብዬ ጠየኳት።

"ልነግርህ አይደል? ምግብ ሰጥቼው እየበላ ወሬ ጀመረ። 'ቤቲዬ፤ እውነት ሰመረ ባልሽ ነው?' ብሎ ጠየቀኝ። 'አዎ' ስለው፤ 'ሁለት ቆንጆዎች ባጋጣሚ የተገናኛችሁ አትመስሉም። ኮከብ ቆጣሪ ያስተዋወቃችሁ ነው የመሰለኝ...' ብሎኝ ወዲያው አጥፍ ብሎ፤ 'እደራችሁን፤ እነዚህ አናርኪስቶች ነካከተዋችሁ ትዳራችሁ እንዳይናጋ' ብሎ መከረኝ..."

ኑሪዲን ዳቦ ቤት ከወትሮዉ የተለየ መዐት ሰው ሰልፍ ይዟል። አገር የፈረሰ መሰሎ ታየኝ። የአዲስ አበባ ገበያ የፖለቲካ ትኩሳቱን የሚለካ መሣሪያ ከሆነ ቆይቷል። እያደር በመበላሸት ላይ ነው። ደርግ የኢኮኖሚ ሥራ አመራር ግንዛቤውና ብቃቱ ደካማ መሆኑን አፍ አውጥቶ ይናገራል። ወደ አውቶቡስ መነኸሪያ ስንወጣ የድምጽ ማጉያ ጩኸትና የቀበሌ ተመራጮች ግርግር ተቀበለን። ሕዝቡ የኮሎኔል

መንግሥቱን መፈንቅለ መንግሥት ደግፎ እንዲሰለፍ በመቀስቀስ ላይ ናቸው። ዓይኖቻችን የሚያርፉበት ነገር ሁሉ አስፈሪና ለጭንቀት የሚጋብዝ ነው።

"ግ--ን፣ ፍቅሬ፣ ለከፋም ለደጉም ቀለበት ብናስር አይሻልም?" ድንገት ከአሬ ሹልክ አለ።

"ሰ--ሙ፣ አንተም ማርክሲዝም ሌኒንዝምን ትተህ እንደ ማሚ....!?" ከት ከት ብላ ስቃ፣ "ማሚ ከፋሲካ ማግስት ልትድረን ጌሾና ቅቤ መግዛት ጀምራለች። ደስ ይበላት ብዬ ዝም አልኳት..." እንደገና ሳቀች።

ማርክሲስት ከሆንኩ ወዲህ ለጀመሪያ ጊዜ ፈጣሪዬን አመሰገንኩ። በመሀል ሰይጣን አንድ ሳንካ ይዞብን እንዳይመጣም በልቤ ጸለይኩ። ማርክሲዝም ሥር የሰደደን እምነት መጋፈጥ መቻሉን ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠራጠርኩ። ከልብ ደስ አለኝ።

###

ወደ አብዮት አደባባይ የሚጎርፈው ሕዝብ ለጉድ ነው።

ሽሮ ሜዳ ስንደርስ መንገዱ ተዘግቶብን ትንሽ ቆምን። የሰላሌና የአካባቢው ፈረሰኛ አንድም የቀረ አይመስልም። ረድፍ ሰርቶ እየጋለበ፣ ሹግ መስሎ ቆም፣ ሄድ... እያለ ይተማል። ጭፈራውና ሆታው ይቀልጣል። ከቢታኒያ ጋር መጀመሪያ ፍቅር ስንጀምር የጋለብነው ፈረስ በመካከሉ ሊኖር እንደሚችል አሰብኩ። ታላቁ የሠርጋችን ቀን ለእኔ ያ ረፋድ ነው። እየቀለድኩ አይደለም። እንደ ሞኝ ያንንም ይሄንንም ፈረሰኛ እያየሁ ፈለኩት፣ ቤቲ "ሰሙዬ!" ብላ እስከምትጠራኝ ድረስ...

"ሰሙዬ፣ በኦሮምኛ ምን እያሉ እንደሚጨፍሩ እየሰማኻቸው ነው?" ትከሻዬን ነቀነቀችኝ።

"ኧረ አልሰማኋቸውም። ምን እያሉ ነው?" ጆሮዬን በመስኮት በኩል ደቀንኩ።

*ያ ኬኛ ተፈሪ በንቲ፣*

*ምቱማ ኬኛ ያ ተፈሪ በንቲ!*

ከቤቲ ጋር ተያየን። መሳቅም...ማልቀስም...መጮኽም...መተከዝም...አልቻልንም። የሰላሌ ገበሬዎች የጀኔራል ተፈሪ በንቲን መገደል አላወቁም። በእሳቸው የተጠራ ስብሰባ መስሏቸው ነው ግልብጥ ብለው የመጡት። ከልብ አሳዘኑኝ። የአገሬ ፖለቲካ እንደዚህ ቀን ጥል---ት አድርጎ አስጠልቶኝ አያውቅም። አእምሮዬ ጥያቄዎችን አነሳ...

'ተፈሪ በንቲ የመገደላቸውን ዜና እንዴት ይሄ ሁሉ ሕዝብ አልሰማም? ሬዲዮ ስለሌለው? ሚዲያ ስለማይሰማ ወይስ የቋንቋ ልዩነት ችግር ፈጥሮባቸው? ለሰልፉ ያንቀሳቀሷቸው የአካባቢው የደርግና

መኢሶን ባለሥልጣናትስ እንዴት አልነገሯቸውም?'

የገበሬ ቅንነት እንዲህ ነው። መንግሥትን ጨዋና ርሕሩህ አድርጎ ይመለከታል። ድርጅቴ ኢሕአፓ በራሱ ስህተት ከኢትዮጵያ ገበሬ ያጣው ሙቀትና ጉልበት ይህ ነው። ድርጅቴ ችላ ያለው የብሔር ጥያቄም ይህንን ያህል ብርታት አለው። ግን ለማን ይነግሩታል? መብከንከን ብቻ!

መንገዱ ሲከፈት ወደ ክሊኒኩ ነዳሁ። ክሊኒኩ ተከፍቶ ሥራ ጀምሯል። ቢታኒያ ወርዳ ሄዳ ገባች። አንድ ሰዓት ያህል ልትቆይ እንደምትችል ነግራኛለች። መኪና ውስጥ ቁጭ እንዳልኩ አጠብቃት ጀመር። ማቹ ተፈሪ በንቲና የሰላሌ ገበሬዎች ተመልሰው ወደ አእምሮዬ መጡ።

'እነዚህ የዋህ ገበሬዎች በዚህ ወኔ አብዮት አደባባይ ደረሱ። ቦታቸውን ይዘው ወደ ሰገነቱ ይመለከታሉ። ያኔ በጀኔራል ተፈሪ ወንበር ላይ መንግሥቱ ኃይለማርያም ተቀምጦበታል። ምን ይሉ ይሆን? ከዚያ መንግሥቱ ተነስቶ ጀኔራሉን እያወገዘ ሲደነፋባቸው ምን ይመስላቸው ይሆን? ከሞቱ አሟሟቱ! የደርግ/መኢሶን ዓይን ያወጣ የክህደት ክህደት!'

በመገረም እንዲን እንስቼ ሌላውን ስጥል ቢታኒያ ተመልሳ መጣች። ፊቷ እንደ ጀንበር ፍክት ብሏል። በዐይኗ ጠርዞች የጎድን ስታየኝ ደግሞ ፈገግታ ልብስ አደረጋት። በሩን ዘግታ እንደተቀመጠች በእጇ የያዘችውን ቢጫ ካርድ ወረቀት ሰጠችኝ። በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀ የቅድመ ምርምራ ውጤት ቅጽ ነው። ክፍት ቦታዎች ላይ ከሙሉ ስሟ ጀምሮ በእስከርቢቶ የተሞሉ ነገሮችን እያነበብኩ ወረድኩ። "ኬዝ" ከሚለው ደረስኩ።"የነፍሰጡርነት ጤና ምርመራ..." ልቤ ስንጥቅ ብላ መልሳ ግጥም አለች፣ "የወላጅ አባት ሙሉ ስም...ሰመረ ማንደፍሮ...የጽንሱ ዕድሜ...46 ቀናት...የጤንነት ሁኔታ...ሙሉ ጤነኛ...የጾታ አመልካች...ገና ምልከት አልሰጠም..." ስሜቴ ልውጥውጥ ብሎብኝ እንገቷን ይገኤ ሳምኳት። የምለው ነገር አጥቼ እንደበቴ ቁልፍልፍ አለብኝ።

"ሆድዬ፣ ስም አውጣ፣ በጣ------ም ቆንጆ ሥም!!" በጉጉት ጥድፍ አለች።

ትንሽ አሰብ አድርጌ ወደ እሷ ዞር አልኩ...

"ልጃችን ወንድ ከሆነ...አአአአ......አ--ሲ--ም--ባ! ሴት ከሆነች ደግሞ እ---ር--ም--ት! እንላቸዋለን..."

"ወ----ይ--ኔ ሰ---ሙ---የ፣ አሁን እንደተመለስን ዳቦ እንቆርሳለን፣ ማሚ ትሙት!"

'የእርምት ወይም የአሲንባ አባት!' በረጅሙ ተነፈስኩ።

# 34

ሸዋዬ፣ ደጀኔና ኢሳያስ ቆቅ መስለው ሬዲዮ ያዳምጣሉ። ኮሌኔል መንግሥቱ በመርሐብሄርነታቸው ይፋዊ ንግግር በማድረግ ላይ ናቸው። ንግግሩ ግን ጠብ የሚል የተለመደው ኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ትህትና የሚሰማበት አይደለም። እልም ያለ ድንፋታ...ዛቻ...ፉከራ...ቀረርቶ...ውረድ እንውረድ... ይለይልን...። ፍርሀት ብቻ አይደለም፣ ለራሴ፣ ለሕዝቤ፣ ለትውልዱ፣ ለአገሬ ጭምር...ፕልቅ ሐዘን ተሰማኝ።

"...ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! አብዮትህ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋግሯል።...ለምሳ ያሰቡንን ቁርስ አደረግናቸው...ለአናርኪስቶች የውስጥ አርበኛ ሆነው ሲያስወጉን የነበሩ ከሀዲዎች ተገቢ ፍርዳቸዉን አግኝተዋል..."

ምን ምልከት እንዳሳዩ ወይም እንዳደረጉ አላውቅም። ሕዝቡ በንግግራቸው መሀል አቋርጦ አንድ ሁለቴ እንደ አሳተ ገሞራ የሚፈንዳ ጭብጨባ አሰማ። መንግሥቱ ንግግራቸውን ሲጨርሱ ከእንቅልፍ የመንቃት ያህል ብንን ብለን እርስ በእርስ ተያየን።

"እኪልዳማ፣ ኢትዮጵያ  ከእንግዲህ ምንድናት? የደም መሬት!" ገጻችን ላይ በትክክል የሚነበበው መልእከት ነበር።

እንደ ዕለት ሐዘንተኛ አንገቴን አቀርቅሬ ቆይቼ ልሄድ ብድግ ስል ኢሳያስ ጠራኝ። ተመልሼ ቁጭ አልኩ። አብሮኝ ካደገ የእናቴ ልጅ የበለጠ ጠንቅቄ የማውቀው ኢሳያስ የተቆረጠ ቅጠል መስሎ ዐየሁት። የጠወለገች የሱፍ አበባ! ሸዋዬና ደጀኔ ከመፈንቅለ መንግሥቱ ወዲህ ነገሩ ያማራቸው አይመስልም። ሙሉ ትጥቃቸውን ቀኑን ሙሉ አድርገው መዋል ጀመርዋል። ሦስቱም ወደ እኔ ዞረው

ወሬ ጀመርን። ኢሳያስ ያላሰብኩት ጥያቄ አነሳልኝ...

"ሰመሬ! እነ ሻምበል ሞገስ የተገደሉ ቀን የወጣውን የደርግ መግለጫ በደንብ አዳምጠህ ነበር?"

"ቃል በቃል ላላስታውሰውም እንጂ አዳምጬዋለሁ። ምን......አዲስ ነገር ተገኘበት?" መልሼ በጥንቃቄ ጠየኩት።

"እረ ባክህ ማመን የሚከብድ ፈተና ነው የገጠመን። ትዝ ይልህ እንደሆን በነሐሴው የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ መንግሥቱ ኃይለማርያምን የመግደል ሐሳብ ሲጸድቅ ብርሃነመስቀልና ዘርዑ ተቆጥተው ነበር። ብርሀነ፣ 'በኮሎኔል መንግሥቱ ላይ ያለኝ ቅሬታ ዲሞክራት ባለመሆናቸው ነው እንጂ ተራማጅነታቸውን አልጠራጠርም። ይሄ ድክመታቸውን አብሮ በመሥራት ማስተካከል ይቻላል። ተራማጅ ነን ካልን ተራማጅ መሪን ማገዝ ነው እንጂ መግደል የለብንም...' ሲል ዘርዑ መልስ ሰጠው። 'መንግሥቱ ተራማጅም ዲሞክራትም አይደለም። እጁ በደም የተነከረ አምባገነን ብቻ ነው። መወገድ ነው ያለበት። ደርግ አካባቢ ያለው የእኛ ኮሚቴ ያረጋገጠልንም ይሄንኑ ነው። "እኛ ከላይ ስንጫናቸው እናንተ ከታች ምቷቸው..." የሚል ምክር ሰጥተውናል። ይሄንን ነው ተግባራዊ ማድረግ ያለብን...' አለ።"

"አዎ፣ ትዝ ይለኛል። ይሄንማ ሻምበል ሞገስ እዚሁ እኛ ቤት እኔና አንተ ባለንበት አይደል እንዴ ሲነግሩት የሰማነው። በአማርኛ ተርጉመኸ የነገርከኝም አንተ እኮ ነህ። ረሳኸው...?"

"አ--------------ዎዎ፣ አስታወስኩት፣ ትክክል ነህ፣ ትክክል ነህ!" አለኝ ኢሳያስ ትከሻዬን እየጠበጠበ።

"እና ምን ተፈጠረ ነው የምትለኝ?" ኢሳያስን ስጠይቀው ደጀኔ መልሱን ሊሰጠኝ ጣልቃ ገባ።

"የደርግ መግለጫ 'ሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል ከኢሕአፓ መሪዎች ጋር እንዲህ ዓይነት ስምምነት ማድረጋቸው ተረጋግጧል' ብሎ አንድም ቃል ሳያዛንፍ ራሱን አነበበው..."

"እትለኝም!?" በድንጋጤ ከሰል ከመምሰሌ የተነሳ የከረመ ሽከላ ሳልመስል አልቀረሁም፣ "ምሥጢሩ ከእኛ ሰዎች ወጥቶ ነው ወይስ ሥርጎ ገብ ተልኮብን?" ደጀኔን ላብ ላብ እያለኝ ጠየኩት።

"እኛም የጨነቀን ይሄ አይደል?" ሸዋዬ ደጀኔን ቀድማ ጣልቃ ገባች፣ "እኔ ግን፣ ምላሴ ይቆረጥ፣ ይህንን መረጃ ያቀበላቸው ወይ ጌታቸው ወይ ብርሃነመስቀል አለያም ሁለቱም ናቸው። በትክክል እንጃ ፈጥረዋል። ከመኢሶን ጋር መረጃ እየተለዋወጡ ሊያስፈጁን ነው። ሌላ ማንም ማንም ሊሆን

አይችልም። ኢሕአሠ የትም የትም ብሎ የእነዚህን ሁለት ከሀዲ ሰዎች ምላስ መቁረጥ አለበት! በቃ፡ አሁንኮ እኛም አራታችንም በሕይወት አለን ማለት አይቻልም። መርተው ሲያመጧቸው ይታየኛል..." እርር አለች።

የምጨምረው...የምቀንሰው...የማምነው...የምጠራጠረው...የማጣጥለው...የማዳንቀው ነገር አልነበረኝም። አፍ ይጸውዑ ለሞት! ድርጭት መስየ በጸጥታ ቁጭ አልኩ። የድርጅቴ የኢሕአፓ ባቡር ከሀዲዱ በመውጣት ላይ የነበረው መጀመሪያ ከጊዜ ጊዜ ነበር። ቀጥሎ ደግሞ ከወራት ወራት ሆነ። ትንሽ ቆይቶ ከሳምንት ወደ ሳምንት ወረደ። አሁን ከቀን ቀንና ከሰዓት ሰዓት በአስደንጋጭ ፍጥነት ወጣ። የእኛ መትረፍ አለመትረፍ ነው ጥያቄው። የባቡሩ መገልበጥ የማይቀር እውነት ነው። ጭንቅላቴን እየወዘወዝኩ ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ትቻቸው ወጣሁ። ወደ ፍቅረኛዬና የልጄ አሊምባ ወይም እርምት እናት፣ ቢታኒያ...

"ሰሙዬ፣ ና፣ና...ና ተመልከት የመንግሥቱ ኃይለማርያምን እብደት!" አለችኝ ቢታኒያ ስገባ ዓይኖቿ ቴሌቪዥኑ ላይ ሰክታ።

"ምን እያደረገ ነው?" ፈጠን ብዬ ወደ ቴሌቪዥኑ ዞርኩ።

የረፋዱን ምስል በድጋሚ እያሳየ ነው። ኮሎኔል መንግሥቱ ነጣ ያለ ወታደራዊ የደንብ ልብስ ለብሰዋል። ሽቅብ ሾጠጥ ያለ መለዩ አድርገው በግራ ከንዳቸው ላይ ወታደራዊ ገመድ አስረዋል። የሸሚዛቸው እጅጌዎች ተጥቅልለዋል። እጠገባቸው ከመሬት ላይ ጠርሙሶች እያነሱ ወደ መሀል አስፋልቱ ይወረውራሉ። ጠርሙሶቹ አየር ላይ እየተምዘገዘጉ ሄደው ምድር ሲነኩ ኳ! ከሽ! ብለው የሰባበራሉ። ከተሰባበረ አካላቸው ቀይ ቀለም ቷ! ቡልቅ! ብሎ ይፈስና አስፋልቱን ያቀላዋል። ኢምፔሪያሊዝምን፣ ፊውዳሊዝምንና ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝምን ዐመድ አደረጓቸው። የውስጥ ከሀዲዎችንና ተባባሪዎቻቸውንም አወገዙ። ይህንን ሲያደርጉ ጩኸታቸው አይጣል ነው።

"ይው----ደ----ም!!" ሕዝቡ ይቀበላቸውና ያስተጋባዋል፣ "ይው---ደ---ም!" ጭብጨባ።

"እውነትም እብደት! በተንኮልና በአሻጥር የተገኘ ድል ሲያሰክር እንዲህ ነው።" እጅግ እጅግ ተኳረምኩ።

የሰማሁትን የምሥጢራችንን መውጣት ጉድ ለቤቴ አልነገራትም። ምክንያቱም 'አትወጣም አትገባም' ብላ እስረኛ ታደርገኛለች ብዬ ሰጋሁ። ነገር በውስጤ እያንቀራቀርኩ ከምሳ በኋላ ጋራዥ ነኝ ብያት

ሄድኩና ላንድሮቨሬን አስነስቼ ወጣሁ፣ ወደ አየር ጤና...

###

አዲስ አበባ ከሰልፍ በሚመለሰው ሕዝብ ከጫፍ ጫፍ ታቃስታለች።

ዘግየት...ቆም...ፈጠን... እያልኩ ጊዮርጊስ ደረስኩ። በቸርቺል ጎዳና በኩል መንገድ እያሳበርኩ ሄጄ ሜክሲኮንና ስቴዲየምን ካለፍኩ በኋላ የሳሪስን መንገድ ያዝኩ። ጥሩ ሄጄ ሄጄ ቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ስደርስ መንገዱ ተያዘብኝ። ሴት የፋብሪካ ሠራተኞች በሁለቱም አቅጣጫ መንገዱን ዘግተው እየጨፈሩ ነው። ከሰልፍ መመለሳቸው ነው። በዝግታ ስለሚሄዱ ከግማሽ ሰዓት በላይ እንደሚያቆዩኝ ገመትኩ...

'ምን ይ-ሻ-ለ-ኛ-ል?' ብዬ ራሴን ስጠይቅ አንድ ያላሰብኩት ፍላጎት ጭንቅላቴ ውስጥ ብልጭ አለብኝ፣ 'በዚህ አጋጣሚ የብርከታዊትን መቃብር ማየት አለብኝ!' መኪናዋን በፍጥነት ከመንገድ አውጥቼ መካነመቃብሩ በር አጠገብ አቆምኳት።

ኢሕአፓ የገደላቸው የደርግ/መኢሶን ሰዎች በተዘጋጀላቸው ልዩ ቦታ እዚህ እንደሚቀበሩ ዐውቃለሁ። ሰተት ብዬ ገባሁ። በታጣቂዎች ይጠበቅ ይሆናል ብዬ ሰግቼ ነበር። መጽሐፉስ "እግዚአብሔር የህያዋን እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም ይል" የለ!? ምንም ነገር አላጋጠመኝም።:ብዙ መቃብሮችን አቋረጥኩ። የሻምበል አበበ ቢቂላን መቃብር አልፌ ወደ ተከለለው መቃብር ገባሁ። የሙታን ሰፈር ጭር ብሏል። ከግራ ወደ ቀኝ ቀጥ ያለ የመቃብር ሰልፍ...እሜጭር ሐውልቶች...ጉርድና የቁመት ልክ ፎቶግራፍ... የደረቁና በመጠውለግ ላይ ያሉ የአበባ ጉንጉኖች...። ፍለጋየን ቀጥዬ ከሦስተኛው ረድፍ መሀል ላይ የምፈልገውን አገኘሁ።ብርከታዊት አዳነ ዋሲሁን...

በቁም ከተነሳችው ትልቅ ፎቶግራፏ ጋር ስፋጠጥ ነፍስ የዘራች መሰሎ ተሰማኝ። ሙሉ ትውፊታዊ ጥበብ ቀሚስ ለብሳለች። ነጭ ቆዳ ጫማ አድርጋ በግራ ጎኗ ትልቅ ቦርሳ አንግባለች። ፎቶውን አውቀዋለሁ። እምና በገና ዋዜማ አብረን እንበሳ ግቢ ሄደን የተነሳችው ነው። ውስጤ እንደ እውሎ ነፋስ እየጋለበ በደረሰ የፍርሀት ማእበል ተናጠ። ዐይኖቿን ሳይ መልሰው አፈጠጡብኝ። እንደ ጦር ተወርውረው ደረቴን ስንጥቅ የሚያደርጉት መሰለኝ። ብርከቴ ልትናገረኝ እየፈለገች ነው...

"አንተ ከሀዲ፣ በሕይወት እያለሁ ጠፍተኸ አሁን ስሞት ፈለከኝ፣ አይደል? አንተ ጉዳም! በል፣ እዚህ የሚያስጥልህ ማንም የለም። ቢታኒያም ብትሆን። ባመጣ እግርህ ተመልሰህ ውልቅ በል!" ከንፈሮቿ ሲንቀሳቀሱ ያየኋቸው መሰለኝ።

በእውነት ፎቶግራፍ እንደዚህ ቀን አስፈርቶኝ አያውቅም። ትክ ብዬ ባየኋት ቁጥር ፍርሀቴ፣ ጸጸቴ፣ ሐዘኔ፣ ትካዜዬ...ጨምሮ እንባዬን ጠራው። ስለ ሕይወትና ሞት በቂ ፍልስፍና አለኝ ብዬ አምን ነበር። አሁን ሳስበው ግን ውሸቴን ነው። ወደ ኋላ ሳፈገፍግ የብርኪቲ ዐይኖች የምራቸውን ተከተሉኝ። አንደገና አንድ ሁለት እርምጃዎች ተመልሼ ፎቶዋን ተጠጋሁት...

“ብርኪቲዬ፣ አንድ ቀን እሞታለሁ ብዬ ባለማሰብ ለሠራሁብሽ በደል ይቅርታሽን እለምናለሁ! ይቅር በይኝ፣ የኔ ቆንጆ!” ሰው ይኑር አይኑር ግድ የለኝም፣ ድምጽ አውጥቼ ከልቤ ለመንኳት።

ይቅርታ ልታደርግልኝ የፈለገች አልመሰለኝም። ድንገት ዞር ብዬ ከፊቷ ጠፋሁ። ካሁን አሁን የሆነ ኃይል ሊይዘኝ ሲከተለኝ እያለምኩ ቀብሮ እንዳየች በግ በፍርሀት ብን አልኩ። “ሟቹ ባሌ ነበር ገዳዩ ወንድሜ!” የትግራዩ በዝብዝ ካሳ እሁት ትዝ አሉኝ።

ተመልሼ ዋናውን በር አልፌ ወደ ስብስቴ ነጋሢ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነዳሁ።

ከአንዲት ልጅ ጋር ኮድ እንደተለዋወጥን እየመራች ወደ ሱቁ ጀርባ ወሰደችኝ። ግቢው ከጥበቱ የተነሳ ጭንቅንጭ ያለ የጭቃ መኖሪያ ቤት ነው። ጣውላ በሩን ከፍታልኝ ስገባ ጭለማ ዋጠኝ። ሙብራት አብርታ የሌላ ክፍል በር አመላከተችኝ። ሄጄ አንኳኩቼው ገፋ አድርጌው ገባሁ። ዘርዑ ከሕሸንና ጸሎተ ሕዝቅያስ ወንበሮች ላይ አጠገብ ለአጠገብ ጉብ ብለው አገኘኋቸው። ከዚህ በፊት ባየሁት ማመሳሰያ አለባበስ ገጽታቸውን ለውጠውታል። ዘርዑ ደንበኛ የእህል በረንዳ ነጋዴ፣ ጸሎተ ደግሞ የተቀጣለት የበረንዳው ደላላ መስለዋል። አጭር ሰላምታ ተለዋወጥን።

“ዘገየሁ ይሆን?” ዘርዑን ትክ ብዬ እያየሁ በትህትና ጠይቄው ከፊት ለፊታቸው በነበረ ፕላስቲክ ወንበር ላይ ቁጭ አልኩ።

“ኧረ አልዘገየህም። ይልቅ እኛ አጣድፈንህ እንዳይሆን...” ካለኝ በኋላ ቀጥ ብሎ ወደተፈለኩበት ምክንያት ገባ፣ “ጓድ አላምረው፣ ያው አንተም የጸና አቋም እንዳለህ ዐውቃለሁ። የኢሕአሠ ጥያቄም እየጨመረ ስለመጣ ሁለታችን መስከ መውጣታችን ነው። የምንመለስ አይመስለኝም። በቀጥታ ወደ አርማጭሆና አሲምባ ነው የምንሄደው...”

‘በ--ቀ---ጥ--ታ ወ--ደ አ---ር---ማ--ጭ--ሆ--ና አ----ሲምባ? የምራቸውን ነው ወይስ ድራማ እየሠሩ?’

ሐሳቤን ከመቅጽበት አደራጅቼ ማመን የከበደኝን ዜና ጭንቅላትና ጅራት መለየት ቸገረኝ። ትርምስምስ

አለብኝ። በአንድ በኩል የከተሞችን በተለይ ግን የአዲስ አበባን እጅግ ብዙ ወጣት እሳት ከማገዱ በኋላ ሽሽት የጀመሩ መሰለኝ። የኮሎኔል መንግሥቱ መፈንቅለ መንግሥት በተለይ ዘርዑን አረፍት እንደሚያሳጣው ግጥም አድርጌ ዐውቃለሁ። "የእጥቅቶ መከላከል"ን ታላቅ ሥልታዊ ውድቀት እንዲሠራ ግፊት ካደረጉ ሰዎች አንደኛውና ዋናው ሻምበል ምገስ ወልደሚካኤል ነው። አሁን የኮሎኔሉ ሰይፍ በልቶታል። ይህ ዘርዑ በመሪነት ሚናውና በፖለቲካ ሥነልቦናው ላይ ጫና እንደሚፈጥርበት አልጠፋብኝም።

'የሆነ ሆኖ በዚህ ቀውጢ ሰዓት ወደ መስክ ሊወጣ የወሰነው በዚህ ጭንቀት ምክንያት ወይስ በፖሊሲ ለውጥ?'

ይህ ከሆነ በእርግጥም በጫረው ቋያ እሳት ውስጥ ማግደን መሄዱ ነው። ይሄንን ይዤ መቀጠል ግን አልቻልኩም። በበጎ ገጹ ሳየው ተስፋ ሊታየኝ ዳር ዳር አለኝ። በጣ----ም የዘገየ እርምጃም ቢሆን ፖሊት ቢሮው የፖሊሲ ለውጥ አድርጓል ማለት ነው። ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መስክ እየወጣ ከሆነ ይሄ ታላቅ የምሥራች ነው። በእርግጥ የሱፍ አበባዋ ቆስላለች። የሞት አደጋን ግን አመለጠችው ማለት ነው። አሲምባ እንደ አዲስ አበባ አይደለም። ያለምንም ጥርጥር በቂ የማገገሚያ ጊዜ ታገኛለች። እኔም ራሴ የምወጣበት ቀን በጣም ቀርቦ ታየኝ። ይህንን ማለትም ደግሞ አልቻልኩም። ዘርዑ ዋና ጸሐፊውን ይዞ ወይም ለሌላ ሰው አስረክቦ እየሄደ መሆኑን ለይቼ ማወቅ አለብኝ።

"ፓርቲው እንዳለ ነው የሚወጣው ወ--ይ---ስ...?" የሚሰጠኝ መልስ ገና ለገና ሲቃ ፈጥሮብኝ ጥያቄዬን አንጠለጠልኩት።

"እ---ይ፣ ለጊዜው ወታደራዊ ኮሚሽኑ ነው የሚወጣው። ኢሕአሠን ከከተማው የትጥቅ ትግል ጋር የማቀናጀት 'ኢመርጀንሲ' ስለተፈጠረ ነው ሁላታችን የምንወጣው። አመራሩ እዚሁ ይቆያል።"

ወገቤ ከሦስት አራት ቦታ ትርክክ ብሎ ተደቆሰ። ኢሕአፓ የያዘው ቧልት ነው። በዚህ ጊዜ እንኳን የወረሰውን የ"ገሽርዲኒዝም" ትቢያ ማራገፍ አልቻለም። ብስጭትጭት አልኩ። ቅሬታዬን ፊቴ ላይ እንደሚያነቡት እገምታለሁ። ውሳኔው አዲስና አስደንጋጭ የሆነብኝ በፖለቲካ ቢሮው ብቻ ስለተወሰነ ነው። ኢሳያስ የኃላፊነት ሽግሽግ ሳያደርጉ እንደማይቀሩ ፍንጭ ሰጥቶኝ ነበር። ሽግሽግ የተባለው እንግዲህ ይህ መሆኑ ነው።'ይሄ እልም ያለ ሽሽት እንጂ ፈጽሞ ሽግሽግ አይደለም።' ሆዴን በጣም ከፋው።

"የፖሊት ቢሮው የተሻለ ሥልት ነው ብሎ ካመነና ከሆነ ጥሩ። እኛ ያው ሌሊትና ቀን መሥራታችንን

እንቀጥላለን። አሁን የተፈለኩበት ተልእኮ ምንድነው?" በንዴት ድምጼ ተለዋውጦ ጠየኩት።ብስጭቴን ያጢኑት እያጢኑት አላውቅም። ጸሎተን ፈገግ ሲል ሳየው ግን የተግባባን መሰለኝ። ዘርዐ ለጥያቄዬ መልስ መስጠት ሲጀምር ወደ እሱ ዞርኩ...

"ጥሩ! ጓድ አላምረው...አሁን አንተን የፈለግንህ ለሁለት ተልእኮዎች ነው። የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ተልእኮዎች ናቸው። ባጭር ጊዜ ይሄንን ማስታወሻ ጉለሌ ትወስድና ለተስፋዬ ትሰጠዋለህ። እዛ በጀንያ ታስረው የተቀመጡ እቃዎች አሉን። እነርሱን ጭነህ ከተስፋዬ ጋር ሆነህ እንጦጦ በሚያሳይህ ቤት ታራግፍልናለህ። ከዚያ መመለስ ነው ወደ ሥራህ።ሁለተኛ፣ ልክ የዛሬ ሁለት ሳምንት ለረጅም ጉዞ ትወጣለህ። ጎንደር በለሳ አካባቢ አብናት የምትባል ከተማ ትሄዳለህ። ተስፋዬ የሚሰጥህና ለኢሕአሠ የሚደርስ ብዙ ገንዘብ አለ። ከዚያ በፊት ግን አብናት ስትደርስ እዛ አንድ የጀብሀ ጓድ የተመሰጠረ መልእክት ይሰጥሀል። ዐረብኛ ነው የሚናገረው። መልእክቱን ተቀብለህ ወደ አዲስ አበባ ትልከዋለህ። ወደ ጎንደር ትመለስና ማይጸብሪ የምትባል ከተማ ትሄዳለህ። እዛ እኔን ታገኘኛለህ።" ብሎ ስሜቴን እንድነገርው ፈለገ መሰለኝ ዓይን አይኔን አየኝ።'

"ይሄን ሁሉ የምሠራው ብቻዬን ነው ወይስ...?" ግንባሬን ከስከስ አደረኩት።

"ኖ----ው! ሁለት ሰዎች ይኖራሉ። አንዱ እዛው አንተ ጋ ያለ ልጅ ነው። ጀማል የሚባለው ጀብሀ አለ...ዐረብኛ ስለሚችል ነው አብሮህ የሚሄደው። ከአብናት መልስ ወረታ ላይ በዚያው አድርጎ ወደ አገሩ ይመለሳል። ሌላውን ግን ለመመሳሰልና ለደህንነት የምትወስደው ነው። ከፍሉ ተዘራ ይሄንን ሰው እንዲያዘጋጅልህ ተነግሮታል። ወንድ ቢሆን ይሻላል ወይስ ሴት? የሚለውን መወሰን ተቸግሮ ነው እንጂ የመደበውን ሰው ይነግርሀል። ከጀብሀው ጓድ የምትቀበለውን መልእክት ወደ አዲስ አበባ የምትልከው በዚህ ሰው በኩል ነው። ባህርዳር አድርሰሽው አንተ ወደ ጎንደር ትመለሳለህ። አትስጋ!በቂ ዝግጅት መደረጉን ስታረጋግጥ ነው የምትወጣው።" ትከሻዬን ይዞ ነቀነቀኝ።

ጨርሶ ደስ አላለኝም። የምሄደው "ሰው በላው" ብሎ ሕዝብ ወደ ሰየመው ሻለቃ መላኩ ግዛት ነው። እጅግ አደገኛ ጉዞ ነው። ተልእኮውን በቅንነት ማየት ከበደኝ። በእንጀኝነት ጠርጥረውኝ ማስረጃ ስላጡ ብቻ ሊያስገድሉኝ ያቀዱ ነው የመሰለኝ።አይሆንም አይባልም። ኢሕአፓ እንደሆነ ዘቅጦ ዘቅጦ አስፈሪ ሽፍታ ሆኗል። የቁንም ያህል ብጠራጠር ግን ተልእኮውን አልቀበልም ልል የምችልበት ቀዳዳ የለም።

"ጥሩ! ተቀብዬዋለሁ። መልካም መንገድ ይሁንላችሁ..." ተሳስመን ስናበቃ ተለይቻቸው ሄድኩ።

###

ላንድሮቨሯን አስነስቼ በሐሳብ እየተብሰለሰልኩ ወደ ጉለሌ አመራሁ። ዘርዑን ልቡ ድረስ ዘልቄ መረዳት አልቻልኩም። ብልጭ ብሎልኝ የነበረው ቢፓርቲ ደረጃ አዲስ አበባን የመልቀቅ ተስፋም አሁን በቦታው የለም።

ኢሕአሠም ልክ እንደ ከተማው ታጣቂ ክንፍ ሰው ይዞ እየረሸነ መሆኑን ብርሃነመስቀል ነግሮኛል። አሲምባ ከአስኳሉ ሠራዊት ጋር ያልተገባባበት አንዱ ልዩነትም ይሄው ነበር። ሌሎቹ ሕዝብን በቀጥታ ማስተዳደር ይፈልጋሉ። ብርሃነመስቀል ደግሞ ሕዝቡ ራሱን በራሱ ያስተዳድር አለ። ጸጋዩ ደብተራው ሲሄድ የሕዝቡ አምባገነን ቁጭ ቆንጣጭ ሆኖ ቁጭ አለ። የወልድያና የመቀሌ ሪፖርቱን አስታወስኩ። የደርግ ሰላይ ናችሁ ብሎ ያስገረፋቸው ሰዎች እንዳሉ መምህር ጸጋይ ነግሮኛል። ያም ሆኖ ዘርዑና ጸሎተ አሁን መሄዳቸው ጥሩ ነው። ይሄ ሁሉ ስህተት እርምት ይደረግበት ይሆናል። የሚገጥማቸው ፈተና ግን ቀላል አይሆንም።

'ለማንኛውም መንገዱ አልጋ በአልጋ ይሁንላቸው!' ተመኘኹላቸው ጉለሌ ደርሼ ከመኪና ወረድኩ።

ከዶክተር ተስፋዬ ጋር ብዙ አልተነጋገርንም። ጀንያዎቹን ጭነን ከተባለው ቦታ አደረስን። መንገድ ላይ ተፈሪ በንቲን እያወደሱ የገቡት የሰላሌ ገበሬዎችን አገኘናቸው። አሁን ጭፈራ የለም፣ ውዳሴ የለም። ሞራላቸው እንክትክት ብሎ ብትንትን ብለው በጸጥታ ነው የሚመለሱት። "ያ ኬኛ ተፈሪ በንቲ!" ያሉለት ሰው አሁን ትላትል ሰፍረው የሚነከሱት ሬሳ ነው። ገጠመኙን ለዶክተር ተስፋዬ ስነግረው የእውነቱን አዘነ። ለረጅም ጊዜ ጭንቅላቱን በትካዜ ነቀነቀ...

"በጣም ቀፋፊ ምስል ነው። በእነ አጼ ቴዎድሮስ ዘመን እንኳን እንዲህ ዓይነት ውንብድና አልተሠራም!" አለኝ።

ጉለሌ ተመልሰን ከሁለት ሰዓት በላይ አብረን ቆየን። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ከፍሉ ተዘራ መጣ። ስለ ጎንደር ጉዞዬ ዝርዝር ነገር ነገረኝ። የሐሰት ሰነዶች ለሦስቱም ተጓዦች በጥንቃቄና በፍጥነት እየተዘጋጀልን ነው። አብራኝ የምትሄደው ሴት እንድትሆን ተወስኖ ማስመሰያዋ እየተሠራላት ነው። ልንሄድ አንድ ቀን ሲቀረን ሩፋኤል ቤተክርስተያን በኮድ እንገናኛለን። ግባችን ስንደረስ የምንጠቀምበት የተመሰጠረ ቋንቋም እየተሠራልን ነው። ትልቅ ጥንቃቄና ድፍረት የሚጠይቅ ተልእኮ መሆኑን መገመት ቀላል ነበር። አመሻሽ ላይ ወደ መሳለሚያ ተመለስኩ። ቢታኒያ ትዝ ስትለኝ ፍርሀት ቀፍድዶ ያዘኝ...

'ወ---ይ ጣጣ! እስቲ እንዴት አድርጌ ነው ለሳምንታት አብሬሽ አልኖርም' ብዬ የምነግራት?'

የኑረዲንን ዳቦ ቤት አልፌ ወደ ጋራዥ ታጠፍኩ። ጠባቧ መተላለፊያ መሀል ላይ ደጀኔ ታየኝ። ሞተር ብስክሌት ተደግፎ ቆሟል። የሆነ አንድ ሰው አብሮት አለ። አንድ ጥበቃ የሚያደርጉለት የፖሊት ቢሮ አባል በአካባቢው እንዳለ ገመትኩ። ከዶክተር ተስፋዬ ጋር አብሬ ስለቆየሁ እሱ ሊሆን አይችልም። ከፍሉ ታደሰ ወይም እነ ዘርዑ በሌላ መንገድ መጥተው እነርሱ መሆን አለባቸው። መንገዱን ለቀውልኝ ጋራዥ ስገባ ግን የገጠመኝ ሌላ ትርኢት ነበር።

"እንዴ------------------ዴ???" ማመን አልቻልኩም።

ጌታቸው ማሩና ሌላ አንድ ሰው ነው። አብዬ ኤርሳሞ ይመስለኛል። አብዬ "ሰው መግደል የለብንም" በሚለው አቋሙ ጸንቶ አንጃውን ተቀላቅሏል። ሁለቱም እጆቻቸው የፊጥኝ ታስረዋል። ዐይኖቻቸው በአራፊ ጨርቆች ተሸፍነዋል። ሁለት ራሳቸውን ካሞፍላጅ ያደረጉ ወጣቶች ከአንድ ፒክ አፕ መኪና አወረዷቸው። በአጀብ ወስደው ሌላ ሽፍን መኪና ላይ ጫኗቸው። እስረኞቹ ምንም አላንገራገሩም። በሮቹን ዘጋግተው አልፈውኝ ወጥተው ተፈተለኩ። ዝግን----ን አለኝ። ለቢታኒያ እንዴት እንደምነግራት አላውቅም። ሐዘን እየናጠኝ ወደ እሷ አመራሁ...

# 35

የጥቅምት ወር የመጀመሪያ ሳምንት ማብቂያ...

እንደ አርማጌዲዮን በጭንቅና በፍርሀት ሲጠበቅ የቆየው የእሳት ዲን መዘነብ ያዘ። የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም የበቀል ሰይፍ ማፏጨት ጀመረ። አዲስ አበባ በጥይት ካኪታና በሙትረየስ እሩምታ ተናጠች። ከአራት ኪሎ ቤተመንግሥት የሚለቀቀው እሳት ረመጥ ሆኖ መሬት ወረደ። ደም ደምን እየጠራ እልቂቱ ተጀመረ። የኮሎኔሉ የበቀል በትር ሦስት አንጓዎች አሉት። ከላይ ደርግና መኢሶን ማእከል ላይ አሉ። መሀል ላይ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር። ከሥር ከፍተኞችና ቀበሌዎች ዘምተዋል። ሦስቱም አንድ ግንባር ፈጥረው ማጥቃቱን ተያያዙት። የአዲስ አበባ አየር በባሩድ ሽታ ታጠነ።

"ኢሎ—ሄሄ...ላማ ሰብቀታ——ኒ!!" ኢትዮጵያ እንደ ራሄል፣ አዲስ አበባ እንደራማ ዋይ ዋይ አሉ።

የመጀመሪያው ሌሊት ወይዘሮ ማስተዋልን ደብረሊባኖስ አድርሼ የተመለስኩበት ቀን ነው። ቀን ላይ ቢታኒያን ጊዮን ሆቴል ወስጃት ነበር። አርግዝናዋ ጸባይዋን ቅይርይር አድርጎብኛል። ለደቂቃዎች እንድለያት አትፈልግም። ትንሽ ቆይታ ደግሞ 'ይዘሽኝ ውጣ' ትለኛለች። ይዣት ስወጣ ምን ለማድረግ እንደወጣን ይጠፋባታል። እዚህ ውሰደኝ...እዛ አቁምልኝ...እዚያ መልሰኝ ትለኛለች። ጊዮን አምሽተን መጥተን ቤት ስንደርስ ሙሴ ባልዲ እየተዋከበ መጣ። ለምግብ እንኳን ጊዜ አልነበረውም።

"ቤቲ፣ ሰመረ...ሌሊት ላይ ተኩስ ይከፈታል...የትም ንቅንቅ እንዳትሉ!" አስጠንቅቆን እየሮጠ ሄደ።

"ቢቃ፤ ጭፍጨፋው ሊጀመር ነው..." አልኳት በስጋት ተውጠን ስንተያይ።

ከንጋቱ 11:00 ሰዓት ሲል ቢታኒያ ቀሰቀሰችኝ። ሙሴ እንዳለው ነው። በብዙ አቅጣጫ የጥይት እሩምታ ይወርድ ጀመር። ዷ.ዷ.ዷ...ጓ...ግም...ዷ... "ዲሞን በዲሞትፊር!" ሙሴ ባልዲ እንደገና ትዝ አለኝ። የደርግ/መኢሶን መፈክር ዘርውና ዶክተር ተስፋዬ እንደተነበዩት "ባዶ ቱማታ" ሆኖ አልቀረም። መሪዎቹን ሳስታውስ ቁጣዬ ተቀሰቀሰብኝ። 'ባዶ ቱማታ ሆኖ የቀረውማ ሰንካላው "የአጥቅቶ መከላከል" ሥልት ነው። በመሀሉ አእምሮዬ አንድ የሚከነከነኝ ጥያቄ አነሳ...

'ለመሆኑ በዚህ የጥይት ውርጅብኝ እየተገደሉ ያሉት እነማን ናቸው?' የሥም ዝርዝር ማውጣት ቸገረኝ።

ዘርውና ጸሎተ በመጨረሻዋ ሰዓት የከህደት ያህል ጣል አድርገውን ሸሽተዋል። በቢታኒያ ትዝብት "በመጨረሻ የኢሕአፓ ወሬ ነጋሪ ሆነው የሚተርፉት እነርሱ ናቸው..."። የኢትዮጵያ ገበሬ እሳልፎ እንደማይሰጣቸው ይታወቃላ! እኔና ቤቲም ቤታችን ነን። ቢታኒያ በሁለት የግድያ ሙከራና በአራት የተሳካ ግድያ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተሳትፋለች። የብዙ ደርግ/መኢሶን አንገቶችን የቀላው ደጀኔም ምድር ቤት ውስጥ አለ። ሸዋዬና ኢሳያስም እንዲሁ።

'እና እየታጨደ ያለው ማነው?' ደግሜ ራሴን ጠየኩት።

ቀድሞም የገመትኩት ነው። የኢሕአፓ አባላት ግንባራችን ላይ ምልክት የለም። ስለዚህ እየተጨፈጨፈ ያለው የተጠረጠረ የአዲስ አበባ ወጣት ሁሉ ነው። ይህ ነው የኢሕአፓ ሕቡዕነት ትሩፋት። በተለይ ጸጉሩን አፍሮ ያበጠረ...... ሌቪን ጅንስ የለበሰ... በተናገረ ቁጥር የእንግሊዝኛ ቃላትን የሚሰነቅር...መልከና ቁመናው ዓይን የሚስብ...መኢሶንን ያልተቀላቀለ ሁሉ በደርግ/መኢሶን ዓይን "ኢናርኪስቷ ኢሕአፓ" ነው። ባጭሩ እየተመተረ ያለው ትውልዱ ነው። የሕቡዕነታችን መዘዝ ግን ይሄ ብቻ አይደለም። የደርግ መርማሪዎች አንዱን ተጠርጣሪ ከሌላው መለየት ሲያቅታቸውና ሰንሰለቱ ሲረዝምባቸው ዘግናኝ የምርመራ ዘዴዎችን ፈጠሩ። አንድም ነገር ሳይቀር ከስታሊኒስት ሩሲያ ግልብጥ አድርገው ያመጡት ነው...

"ወፌ ኢላላ የመጨረሻው ዘግናኝ ግርፋት ነው።" በዮሴፍ አዳነና በኢንጅነር ዑስማን ላይ የተፈጸመውን ግፍ ዐውቃለሁ፤ "ሁለቱም እጅ ሰዓት ማሰሪያ ላይ በገመድ ተጠፍሮ ይታሰራል። ጉልበት ይታጠፍና እጅ በጉልበት ይገባል። በመሀል ባለው ቀዳዳ ወፍራም እንጨት ይሰነቀራል። አፍ ውስጥ የተጠቀለለ ድሪቶ ጨርቅ ይወተፋል። ከዚያ በኋላ እስረኛ ሆይ... እንደፈለጉ የሚያገላብጡት እቃ ነው። በጀርባው ያስተኙትና የውስጥ እግሩን በቆመጥ ይደበድቡታል። እስኪደከማቸው ድረስ። አረፍ ይሉና በአፉ

ይደፉታል። ድብደባው ይቀጥላል። እግር እንደ ቲማቲም እየተተለተለ ደም ይተፋል..."

ደርጎች ጭካኔ አብሯቸው የተወለደ ባህርያቸው ነው። የኢሕአፓ ሕቡዕነት ለዚህ ጭካኔ ሽፋን ሆናቸው። ዝርዐና ጸሎት ድርጊታቸው ከግራ ኃይል የማይጠበቅ ሽሽት ነው። ያም ሆኖ በፀሐይ ላይ ያመጸችው የሱፍ አበባ ወደ ህሊናዋ ተመልሳ አርቅ የመፍጠሯ ምልክት ሆኖ ታየኝ። አሁንም ፖሊት ቢሮው አዲስ አበባ ተረፋቁል።የሄዱት በጣም በጣም አስቀኑኝ።

ተኩሱ ከጆሯችን ጋር እየተለማመደ ሲመጣ ቢታኒያ እንቅልፍ መልሶ ሸለብ አደረጋት። ሲነጋጋ ደግሞ ተኩሱ ጋብ አለ። ለባብሼ ወደ ምድር ቤቱ በረርኩ። ሽዋዬንና ኢሳያስን አገኘኋቸው። ሽዋዬ በሩን ስትከፍትልኝ ዐይኗ በለቅሶ ብዛት ደም መስሷል። ሙሉ ትጥቅ ይዛለች። ኢሳያስ መኖሪያ ክፍሉ ውስጥ እንገቱን ደፍቶ ተቀምጦ አገኘሁት። የደጀኔን አለመኖር ሳይ ተደናግጬ ሽዋዬ ላይ አፈጠጥኩ...

"ያዙት ልትይኝ ነው?"

"አይ ደህና ነው። ለተልእኮ ወጥቶ ነው። ሞተር ብስክሌት ይዞ ስለሄደ አይቆይም፣ ይመለሳል..." አለችኝ እንባዋን እየጠራረገች።

"ኢሱ፣ እስካሁን ከምናውቃቸው ጓዶች የተሰዋ ሰው አለ?" አጠገቡ ስቀመጥ ጠየኩት።

"ምን የቀረ ሰው ይኖራል ብለህ ነው? እስቲ ደጀኔ ይምጣና ደግሞ በስም ይነግረናል።" አለኝ ከላሽን ጠበንጃውን ከአንዱ ትከሻው ወደ ሌላው አዙሮ እያስደገፈ።

ኮሎኔል መንግሥቱ ፈትተው የለቀቁት ድራጎን መቼ እኛ ጋ እንደሚደረስ አላውቅም። እንደሚመጣ ግን ምንም አልጠራጠርም። አሁን ሞት አዲስ አበባ ውስጥ የተራ ጉዳይ ነው። ሽዋዬ ቁርስ ስታቀርብልን እጃችን ዳቦ መቁረስ አልቻለም። እንዳይቀር ብቻ ቆረስ አያደረግን እንጎርሰና ከሻይው ማግ እናደርጋለን። በግምት ከአርባ አምስት ደቂቃ በኋላ ደጀኔ መጣ። ድፍረቱ ከልብ አስገረመኝ። የማለዳ ዳቦ አከፋፋይ መስሎ አዲስ አበባን ፈታትሿት ተመልሷል። መርዶውን ይነግረን ጀመር...

"ዮሴፍ አዳነና ኢንጅነር ዑስማን ከሀያ ሁለቱ የአዲስ አበባ ኢሕአወሊ ኮሚቴ አባላት ጋር ከእስር ቤት ተወስደው ከግንደበረት ራቅ ባለ ቦታ ላይ ተረሽነው አንድ ጉድጓድ ውስጥ ተቀብረዋል። ማረጋገጥ አልቻልኩም እንጂ ፍቅሩ ዮሴፍና መምህር በላይነህ ከመኪና ላይ ዘለው አምልጠዋል የሚል መረጃ ደርሶኛል። ካመለጡም መልሰው ይይዟቸዋል። ሌሎቹን ግን በጅምላ ጨፈጨፏቸው..."

ሐዘኑና ድንጋጤው ተባብረው ጀርባዬ ቀዝቃዛ ላብ አመነጨ። የጅምላ ግድያና ቀብር የመጨረሻው ጭካኔ ብቻ አይደለም። "ዘር የማጥፋት" ወንጀል መሆኑን ጭምር ቢታኒያ ወንጀለኛ መቀጫ ሕጉን ጠቅሳ ነግራኛለች። "አንድን በፖለቲካ አስተሳሰብ የተሳሰረን ቡድን መፍጀት" የሚል ዐረፍተ ነገር እንዳነበበችልኝ ትዝ ይለኛል። ነገሩ በዚህ ብቻ አይቆምም። ዮሴፍ አዳነና ኢንጅነር ዑስማን ወደ ዓይነህሊናዬ መጡ። ከቅርብ ዐውቃቸዋለሁ፣ ከሦስት ዓመታት በላይ። አስብ...

...ተመሳሳይነትም ልዩነትም አላቸው። ሁለቱም ወጣቶች፣ የልብ ጓደኛሞች፣ ኢሕአፓዎች፣ ባለሙያዎችና ኢትዮጵያውያን ናቸው። በሃይማኖት ይለያያሉ። ዮሴፍ በቤተሰብ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን፣ ዑስማን ደግሞ ሙስሊም ነው። የሁለቱም ሃይማኖታዊ ቀኖናዎች አንድ የሃይማኖቱ ተከታይ ሲሞት ምን መደረግ እንዳለበት የተለያየ ደንብ አላቸው። ጸሎተ ፍታታቸውና የመቃብር አቆፋፈራቸው ሳይቀር የተለያየ ነው። ይህ አልተከበረም። ሁለቱም በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ተቀበሩ። የደርግ/መኢሶን ምክንያት ባይናገሩትም ይታወቃል። 'ኢሕአፓ ሰው አይደለም፣ ዜጋ አይደለም፣ የሚከበርለት ወግ የለም።' አ—-ሪሪሪ በይ ኢትዮጵያ!

ካቀረቀርኩበት ቀና ብዬ ወደ ደጀኔ ተመለከትኩ። ልክ እንደ መነባንብ ይተርክልናል...

"ኃይቶም ለባሲና አምስት ጓደኞቹ ተገድለዋል። ሌሎች አሥራ ሁለት አባሎቻችንም አብረው ተገድለዋል። አስከሬናቸው ከሜክሲኮ አደባባይ አካባቢ ጀምሮ እስከ አብዮት አደባባይ ድረስ ከመንገዱ ግራና ቀኝ ተጥሏል። ይትባረክ ሕዝቅያስም ተገድሎ አምስት ኪሎ አካባቢ አግረኛ መንገድ ላይ ጥለውታል። ሁሉም ያለጫማ ነው የወደቁት። እግራቸው በድብደባ ቆስሎ በሰነበተ ፋሻ ጨርቅ ተሸፍኗል። ምኒልክ ሆስፒታል አካባቢ የእኛ አባል ያልሆኑ ሰምንት ሰዎች ተገድለው ተጥለዋል። እነርሱ ከነጫማቸው ናቸው። ስጠይቅ የይህዋ ምስክሮችና ከዋጋ በላይ የሸጡ የመርካቶ ነጋዴዎች ናቸው አሉኝ..."

"እ----ግ---ዚ---አ!! ግድያው ከበቀልም ያልፋል ማለት ነው?" ሸዋዬ አንገቷን ደፋች።

የኢሳያስን አላውቅም። የእኔ አእምሮ ግን በግድያው ትውፊታዊና ሃይማኖታዊ ዐውድ ላይ አተኩሮ ነበር። በሕግ ውሳኔ ሰዉ በስቅላት ሲገደል ከልጅነቴ ጀምሬ ዐውቃለሁ። ከዚህ የበለጠ ግን ቢታኒያ ብዙ ነገር ብጥር አድርጋ አስተምራኛለች። ከቃላቷ አንዱም አይረሳኝም...

"በሕግ የሚገደል ሰው ሕዝብ እንዲማርበት ተብሎ በገበያ ቦታ ይቀጣል። ሕጉ ከስቅላቱ ገመድ ውፍረትና ቅጥነት ጀምሮ እስከ ቀብር ሥርዐቱ ድረስ በዝርዝር ይደነግጋል። ያም ሆኖ ሕዝቡ ሬሳ እንዳያይ መደረጉ ሰብዓዊነት የጎደለው ነው የሚል ክርክር ተነሳ። አጼ ኃይለሥላሴ ሕጉን ለማሻሻል

ደፋ ቀና ሲሉ ደርግ ቀድሞ በላቸው። የምዕራባውያን የቅጣት ባህል ደግሞ ከዚህም ጠበቅ ይላል። ሞት የተፈረደበት ወንጀለኛ ቅጣቱ የሚፈጸምበት አዛው ወህኒ ቤት ውስጥ ነው። አስከሬኑን ሕዝብ እንዲያየው አይፈቀድም። አገዳደሉም ብዙ ስቃይ የሌለበትና ሰብዓዊ ክብርን የማያዋርድ መሆን አለበት። አሁን አሁን በሞት መቅጣትም ራሱ ተቃውሞ እየገጠመው ነው። 'ዓላማ የለሽና ስሜት አልባ' ነው እያሉ ተቃወሙት። እና አንዳንድ አገሮች ከልከለዋል..."

ይህ በደርግና በድርጅቴ ኢሕአፓ ኢትዮጵያ ውስጥ አዬዬም ሲደላ ነው ዓይነት ቅንጦት ነው። ግን ደግሞ ጸንቶ የኖረ የሕዝብ ወግና ማኅበራዊ ደንብ አለ። "ሙሽራና አስከሬን አንድ ናቸው። ሁለቱም ክብር ይፈልጋሉ..." ሙሽራ የአዲስ ዓይነት ሕይወትና ኃላፊነት መግቢያ በር ነው። ሞት ደግሞ ከሕይወት መውጫ በር። ልክ እንደ ሙሽራ ሁሉ አስከሬንም ሽልም ግምጃ ይለብሳል። አልጋ ላይ አርፎ ሕዝብ ያጅበዋል። በክብር ወደ ቀብር ጉድጓዱ ይሸኛል። ምንም ያጥፋ ምን አንድን ሰው ገድሎ አስከሬኑን መንገድ ላይ መጣል ለኢትዮጵያ ሕዝብ አልም ያለ ነውረኝነት ነው። አረመኔያዊ ባህርይ ነው።

'ታሪክ ኢትዮጵያ ውስጥ የኃሊት እየጋለበ ነው...' በቢታኒያ አነጋገር ደግሞ "ሌላ የጸጸት ምእራፍ እየከፈተ ነው!" ልቤ አስር አሥራ አምስት ቦታ ስብር ስብርብር አለች።

እንደገና ወደ ደጀኔ ዞርኩ።

"ጦር ኃይሎች አካባቢ ደግሞ የእኛ አባል የሆኑ አሥራ ሁለት ልጆች ተገድለው ተጥለዋል። አራቱ ከወልዲያ የባንክ ዘረፋ ሙከራ የተማረኩ የኢሕአሠ አባላት ናቸው። ስምንቱ ግን የዚያው አካባቢ ልጆች ናቸው። የኢሕአፓ ሁለተኛ ዓመት የልደት በዓል ሲከበር ቀለም ሲቀቡ እጅ ከፍንጅ የተያዙ ናቸው። እዚህ ለየት የሚል ነገር አድርገዋል። አስከሬኖቻቸው የተጣሉት ከወላጆቻቸው መኖሪያ ቤት ፊት ለፊት ነው። ወላጆች ለለቅሶ እንዳይቀመጡ የአብዮት ጥበቃዎች ከልከለዋቸዋል። እንዲያውም 'በጸረ-ሕዝብ ልጆቻቸው መገደል የተሰማቸውን ደስታ እንዲናገሩ' እያስገደዷቸው ነው አሉኝ..."

በምሰማው ቅጥ የሌለው ትራጀዲ ነፍሴ ተጨንቃ መድረሻ አጣች። "ታሪክ ወደ ኋላ!" አልኩኝ እንደገና። ሞትኮ ለማንም የማይቀር የወር ተራ ነው። የዛሬ ገዳዮች ነገ ማንም ባይገድላቸው እንኳን ዕድሜ ራሱ ይሸኛቸዋል። ሞት በጣም አስፈሪ የሚሆነው ደግሞ እየኖሩ ሲያስቡት ነው። የሞተማ ሞቷል፤ የዘላለም እንቅልፍ አሸልቧል። ስለዚህ ማንም ሰው ለሞተ ዘመዱ ሲያለቅስ ለራሱም ጭምር እያለቀሰ ነው። ለቅሶ ደግሞ ልክ እንደ ንጥሻ ወይም ሀቅታ ስሜታዊ ግብረመልስ ነው። ልንቆጣጠረው ይከብደናል። ይህ ግልብ ስሜት እንዴት በመንግሥት ደረጃ "እታልቅሱ" ተብሎ ይከለከላል?

ሠመጮው ዘመን ያለምንም ጥርጥር የጥልቅ ምሬትና የብርቱ ጸጸት ዘመን ነው! ታሪክ ወደ ኋላ! በረጅሙ ተነፈስኩ።

ደርግ ትላንት ከሥልጣን አውርዶ ከገደላቸው አጼ ኃይለሥላሴ እንኳን ፍጭጭ የምትል ነገር አልተማረም። አጼው ጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ ከከሀደትም በላይ ብዙ በድሎኛል ብለው ያምናሉ። ተይዞ ፍርድ ቤት ቀረበና ሞት ተፈረደበት። ቅጣቱ ተፈጻሚ ሆነ። ቤተሰቡ ድንኳን ጥለው ሲያለቅሱ አጼ ኃይለሥላሴ ሳይታሰቡ ድንገት ከች አሉ። በሀበሻ ወግ ሐዘን ተካፍለው ተመለሱ። የድርጊታቸው ፖለቲካዊ ትርጉም ግልጽ ነው። "በእኔ ላይ ለሠራው በደል ሕግ ቀጣው እንጂ በግሌ አልተበቀልኩትም። አብሮኝ ላሳለፈው ጊዜ ማስታወሻ ሐዘን ልደርስ ይገባኛል።" በኋላ የመጡት ደርግ/መኢሶንና ኢሕአፓ ይህ ብልጠት በልቦናቸው ውስጥ የለም።

'እንዴት በድን ለሆነ መዋቲ ለቅሶ ይከለከላል?' የበቀለኝነታችንና የጨካኝነታችን ደረጃ በእጅጉ አስፈራኝ።

ፊቴን ወደ ደጀኔ አዞርኩ። ፋታ ለማግኘት ፈልጎ ይሁን ወይም ወሬዉን ስለጨረሰ ዝምብሎ መሬት መሬት ያያል። ቅሬታዬን አምቄ መቀጠል አልቻልኩም። የድርጅታችን ታይቶ መጥፋት የማይቀር መሆኑ ሲታሰበኝ ደፈር ደፈር አልኩ...

"ይሄ ሁሉ የእኛ መሪዎች ስህተት ነው። ስህተት ብዬም አላልፈው። ወንጀል ነው።"

"ኧረ ራሱ በግድያ አፕሬሽን ላይ የሠራነው ስህተት ብዙ አለ።" ደጀኔ ወደ ወሬው ተመለሰ፣ "ተስፋዬ ታደሰ የሚባለውን የቤቶች ሚኒስትርና የመኢሶን አመራር ልንገድል ሄደን ልክ እሱን የሚመስል ሰው አጋጠመን። ቁርጥ አንድ ናቸው። ያለ ኃጥያቱ ንጹሁን ሰውዬ ገድለነው መጣን። አንድ የኢሕአወሊ አባል በሠራው ትንሽ ስህተት ትልቅ ወንጀል ተሠራ..." እንደገና አቀረቀረ።

"ያሳዝናል! ደርግም በበኩሉ ኢሕአፓን ገደልኩ ብሎ ስንቱን ንጹህ ሰው ጨፍጭፎት ይሆናል ይሄኔ!?" አለች ሸዋዬ።

"ቢያንስ ከዚህ በኋላ ምን አለ የእኛ ግድያ ቢቆም!!?" ስልና ሸዋዬ ማብሰያ ቤት የቢታኒያ ደወል ሲንጫረር አንድ ሆነ። እንደቆየሁባት ገብቶኛል። ሂድላት! እስከሚሉኝ ድረስ አልጠበኩም። ዐይኖቿን በቁጣ ጨቤ አስመስላ እንዳትጠብቀኝ ብድግ ብዬ ቱር አልኩ። ወደ ደጅ ስወጣ ጆሮዬ እንዲሁ በባዶው የጥይት ተኩስ ያሰማኛል። ቢታኒያ ጋ ስደርስ አልተቆጣችም። እንዲያውም ደጅ ዱካ ወንበር አውጥታ

ተቀምጣለች፣ በጥልቅ ትካዜ ስትቆዝም አገኘኋት። የሰማችው አንድ አሳዛኝ ነገር እንደሚኖር ገመትኩ። ትኩር ብዬ እያየኋት ጠየኳት...

"ባክህ ሰሙዬ፣ ሙሴ ባልዲ አሁን ሙጥቶ የሚያሳዝን ነገር ነግሮኝ ሄደ..." ፍልስልስ ያለ ጸጉሯን አንድ ላይ ለማሰር እየታገለች።

"ምን ተፈጠረ? ምን ብሎሽ ነው?" ጉልበቶቿን ይገፍ ከፊት ለፊቷ ቁርጢጥ ብዬ ቆሜ አልኩ።

"የኑረዲን ዳቦ ትልቁ ልጃቸው አድሪስ የሚባል ነበረ። እስከ አስረኛ ክፍል አብረን ነው የተማርነው፣ አዲስ ከተማ። ለኢሕአፓ የገንዘብ መዋጮ ሰጥተሀል ብለው አስረውት ነበረ። ገድለውት አደሩ። እዛው ከዳቦ ቤቱ አለፍ ብሎ አስከሬኑ ወድቋል አለኝ። ልጆች እያሉ አድሪስ ገንዘብ ይሰጠው ነበር። በጣም አዝኗል። እና ዳቦ ቤቱን ዘግተው ሌላ መዘዝ እንዳያመጡ አባቱን 'ይከፈቱ' ብሎ ሊነግራቸው ሄዶ ነበር። ጋሽ ኑረዲን 'ከፈለጋችሁ እኔንም ግደሉኝ እንጅ አልከፍትም' አለ አሉ።"

"እና አሰሯቸው ማለት ነው?" እንጀት እያረቀኝ ጠየኳት።

"ማሰር አለብን ብለው ነበር። ሙሴ፣ እውነቱን ይሁን የውሸቱን አላውቅም፣ 'እኔ አይሆንም ብዬ እንዳይታሰሩ አደረኳቸው' አለኝ።" ብላ አንድ ላይ የሰበሰበችውን ጸጉሯን በፕላስቲክ ገመድ አሰረችው።

"አይ ቤቲዬ፣ ጭፍጨፋው'ኮ ገና መጀመሩ ነው። ታያለሽ፣ አይደለም የአንድ ሰፈር አብሮ አደጎች ይቅርና አባትና ልጅ ወይ ወንድምና ወንድም ተገዳደሉ ሲባል እንሰማለን። የሽብር ውጤቱ ይሄ ነው!"

"ሰሙዬ፣ በኢድሪስ ላይማ እኔም ግፍ ሰርቼበታለሁ። አስረኛ ክፍል እያለን ፍቅር ያዘኝ ብሎ በየቀኑ የደብዳቤ መዐት ይልክልኝ ነበር። ደብዳቤውን ታዲያ ከጓደኞቼ ጋር እያነበብን መዝናኛ አድርገነው ነበር። በጣም ይፈራኝ ነበር። ጨከኖ ደብዳቤ መጻፍ ሲያቆም ጓደኞቼ ዳቦ ቤት እንሂድና ታይው ይሉኛል። ገና ብቅ ስንል መድረሻ ያጣል። ዘወር ከማለታችን ጽፎ ይልክልኛል። እንሳሳቃለን። በመጨረሻ ትምህርቱንም መማር አልቻለም፣ እኔን ላለማየት ጉራጌ አገር ሄዶ መኪና ገጨው። አሁን ሳስበው ብልግና ነበር የሠራንበት። ይቅርታ! ሳልለው ለዚህ በቃ..." ሐዘኗ ከልብ ነበር።

እስከ አስር ሰዓት አንድ ሁለቴ ጋራዥ ብቅ ብዬ ከመመለሴ በስተቀር ሳልለያት ዋልኩ። አስር ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች እንዳለፉ ስልኩ ጠራ። ቀልቤ የእኔ ጥሪ መሆኑን ነገረኝ። ዘርው ከሕሸን ትሄዳለህ ያለኝ ጉዞ ይሰረዝ ይቅር ማወቅ አልቻልኩም። ፖሊት ቢሮውና ማእከላዊ ኮሚቴው በጭፍጨፋው መጀመር

ምክንያት እንደ ጨው ዘር ተበትነናል። እርግጠኛ ሳልሆን ደግሞ ቢታኒያን መንገር አልፈለኩም። የእኔ ስልክ ከሆነ ከዚህ ሌላ ጉዳይ እንደማይሆን ገመትኩ። ፈጠን ብዬ አነሳሁት። "አ----ቤ--ት!" ስል የዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ ድምጽ መጣ። አጭር የተመሰጠረ መልእክት ነግሮኝ ዘጋው...

"ጉለሌ ድረስ በአስቸኳይ እፈልግሀለሁ!"

ቢታኒያን "ጋራዥ ነኝ!" ብያት ሹክክ ብዬ ወጣሁ...

***

አዲስ አበባ የታጠቀና ትእቢት የተሞጫጨነው ሠራዊትና ቅስሙ በደቀቀ ሕዝብ መሀል እንደ አንጋሬ ተወጥራለች።

ከመሳለሚያ እስከ ጉለሌ ድረስ መንገዱ እረጭ ብሏል። እዚህም እዛም የሚታዩኝ የፖሊሶችና የአብዮት ጥበቃ ታጣቂዎች እንቅስቃሴ ብቻ ነው። እስከሬን በሙሉ ተነስቷል። በሰው ፊት ላይ የማየው መንፈስ በጠቅላላ ብሔራዊ ጭንቀትና ፍርሀት ነው። ጸጥታዋ አዲስ አበባ በአንድ ሌሊት ብቻ ከመቶ ሰው በላይ ገድላ የቀበረች አትመስልም። ለቅሶ የለ እርግዶ...ሙሾ የለ ማንዘተ ጸሎት...የእድር ለፋፊ አይሰማ ምን የለ። እርምምም ብቻ! ሐብተጊዮርጊስ ስደርስ ብቻ ተይዘው የሚነዱ በርከት ያሉ ወጣቶችን አይቻለሁ።

'የእነ ዘርዐ ኩሕሸን "እጥቅቶ መከላከል ዉጤት!' ሀሞቴ ተንተከተከ።

አሁን ባለው ሁኔታ ለእኔና ለቢታኒያ አደጋ የሚሆን ነገር አይታየኝም። እነ ጎይቶም ለባሲ ሲገደሉ ዋናው አደጋ አለፈ። ጋራዡ አንደኛው የኢሕአፓ ታጣቂ ከንፍ ማዘዣ ጣቢያ መሆኑን ሳይናገሩ ሞተዋል ማለት ነው። እኛን አሁን የሚያሰጋን የእርስ በእርስ መጠቋቆም ነው። በፖሊት ቢሮና በማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ምንም ጥርጣሬ የለኝም። በምድር የመጨረሻው ስቃይ ቢደርስብን ሞታችንን እንመርጣለን እንጅ የምንጠቋመው ሰው አይኖርም። ዮሴፍ አዳነ የሞተውን ሞት መሞት አይከብደንም።

የጴጥሮስ አደባባይን ዞሬ ወደ ግራ ሁለት ኪሎሜትር ያህል ከነዳሁ በኋላ ደረስኩ...

ዶክተር ተስፋዬን ሳገኘው በሥራ ብዛት ነፍሱን ሊስት ምንም አልቀረውም። ከአንዱ ከፍል ወደ ሌላው የሩጫ ያህል ይመላለሳል። የሆነ ነገር ይጽፋል፣ ሌላ ወረቀት ኣንስቶ ያነባል፣ ማስታወሻ ይይዛል፣ ይቀዳል...። ለእኔ በጣም አጭር ጊዜ ብቻ እንደሚኖረው ሁኔታው ይነግረኛል። እጅ ለእጅ ተያይዘን በጀርባ በኩል ወደ በረንዳው ወጣን...

"ጓድ አላምረው፣ የፈለኩህ ስለጉዞህ አንዳንድ ነገር ልንገርህ ነው።" ብሎኝ ከኮቱ የውስጥ ኪስ ቁራጭ ወረቀት አወጣ፣ "ልክ የዛሬ ሳምንት ሰኞ ዕለት ትወጣላችሁ። አብናት ከተማ በሦስተኛው ቀን ትገባላችሁ። በማግስቱ ሐሙስ ጧት ቀደም ብላችሁ አብናት ከሊኒክ ትሄዳላችሁ። በምሥራቅ የክሊኒኩ ግድግዳ ቁጭ ትላላችሁ። ልክ ሦስት ሰዓት ላይ አረንጓዴ ካኪ ሸሚዝና ቁምጣ ሱሪ ያደረገ አንድ ወጣት ይመጣል። ። በቀኝ እግሩ አውራ ጣት ላይ ነጭ ፋሻ ጠምጥሟል። በዐረብኛና በአማርኛ ሰላምታ ሰጥቷችሁ አጠገባችሁ ይቀመጣል። ሸሚዙን አውልቆ ይቀመጥበትና ሌላ ሸሚዝ ይለብሳል። ከአሥራ አምስት ደቂቃ በኋላ ተነስቶ ይሄዳል። ሸሚዙን አንስታችሁ ቦታውን ትለቃላችሁ። መልእክቱ ኮሌታው ውስጥ ነው ያለው..."

ለአፍታ ቆም ብሎ ቁራጪን ወረቀት ዐይቶ ወደ እኔ ዞረ...

"ከዚያ በኋላ ወደ አዲስ ዘመን ከተማ ትመለሳላችሁ። ከዚህ ቀጥሎ የምትሠሩት በሙሉ ጓድ ዘርዑ እንደነገረህ ነው። አንድ ለውጥ ብቻ አለ። ከባህርዳር ወደ ማይጸብሪ አትሄድም። ከጎንደር ወጣ ብሎ አምባ ጊዮርጊስ የምትባል ከተማ አለች። ማርያም ደብር የሚባል ቤተክርስቲያን አላት። እዛ ነው የምትገናኙት። ሊዘገይብህ ይችላል። እስከመጨረሻ ትጠብቀዋለህ።"

"እስከመጨረሻ ትጠብቀዋለህ።" ምን ማለት እንደፈለገ አልገባኝም፣ ጠየቅኩት።

"በፍጹም ሊቀር አይችልም ማለቴ ነው። በአመራር ደረጃ ባለን ሰዎች ብቻ የሚደረግ የሞት የሽረት ግንኙነት ስለሆነ ነው እንደዚያ ያልኩህ። ምንም ዓይነት የደህንነት ሥጋት አይኖርም። አብራህ የምትሄደው ጓዲት አበበች እንደምትሆን ወስነን ነበር። እኛ የቁጥር መጓደሉን ፈራን። እሷ ደግሞ ሁለት መሪዎች አንድ ላይ መሆናችሁን አልወደደችውም። ሌላ ሰው እያፈላለገች ነው፣ ካልተገኘ ራሷ ትሆናለች የምትሄደው። ብቻኝነት አይሰማህም፣ ቢያንስ ወደ ጎንደር እስከምትሄድ..." ብሎኝ ፈገግ አለ።

አላመንኩትም። ዝም ብዬ ሳስበው የምሄደው ወደ ሻለቃ መላኩ ተፈራ ግዛት ነው። በጠላት ጥይት እንድወገድላቸው ሤራ ሸረቡብኝ? ጥርጣሬዬ አገረሸ። የመጣ ቢመጣ እንደየአመጣጡ መጋፈጥ ነው። በዚህ ላይ ዘርዑና ጸሎተ ኢሕአሠን መቀላቀላቸው አበረታቶኛል። ፓርቲውም ሊከተል ይችላል የሚል ተስፋ አሳድሮብኛል። እንደዚያ አስበው ከሆነ ለድርጅቴ አስር ጊዜም ብሞት ግድ የለኝ።

"ጥሩ፣ የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ!"

በሽራ የተጠቀለለ የብር ከምር ሲሰጠኝ ተሰናብቼው ወጣሁ...

# 36

ጉዞዬን ለመጀመር ሦስት ቀናት ቀርተውኛል።

ኢሳያስን ወደ አዋሳ ሸኘኹ መመለሴ ነው። የፖሊት ቢሮውን የሽምቅ ውጊያ የበታ መረጣ ጥናት ለመጨረስ ነው የሄደው። ቋቅ ሲለኝ ምንም አልቀረውም። ኢሳያስም ጭምር እንዳለፈው ጊዜ "አውር ይሸፍታል በጓሮው!" ብሎ አጣጥሎታል።

"ቤቲዬ፣ ለአንድ አስቸኳይ ሥራ ባህርዳር ደርሼ ልመጣ ነው። ከሁለት ቀን በላይ አልቆይም_" ሲያስጨንቀኝ የነበረውን ዜና ተነፈስኩ።

አላስጨረሰችኝም። ተልባ የመሰለው ጠይም ፊቷ ማበሻ መስሎ እንደ ፋስ በተጠረቡት ዐይኖቿ ግልምጥምጥ አደረገችኝ። ቃላት መረጣ ወይም ተቃውሞዋን በምክንያት የማስደገፍ ትግል ጊዜ ሳይወስድባት አልቀረም። የተሳካላት አይመስለኝም። ከንፈሮቿ ተንቀጠቀጡ_

"ማን ነው የሚልክህ?"

"ያ----ው፣ ለድርጅት ሥራ ነው የምሄደው። በጣም አስቸኳይ የሞት የሽረት_" ስንተባተብ አቋረጠችኝ።

"በአገሩ ያለኸው የድርጅት አመራር አንተ ብቻ ነህ እንዴ? ደግሞስ እኔን ከታጣቂ ከንፍ ያስወጣኸኝ ምክንያት ፈጥረሽ አመልክቺ ብለህ አይደለም? ጉዳዩ አንተ ላይ ሲደርስ ይህንን ማድረግ ያቃታህ ለምንድነው?"

ዝም አልኩ።

# 35

የየካቲት ወር የመጀመሪያ ሳምንት ማብቂያ...

እንደ አርማጌዲዮን በጭንቅና በፍርሀት ሲጠበቅ የቆየው የእሳት ዲን መዝነብ ያዘ። የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም የበቀል ሰይፍ ማፏጨት ጀመረ። አዲስ አበባ በጥይት ካካታና በመትረየስ እሩምታ ተናጠች። ከአራት ኪሎ ቤተመንግሥት የሚለቀቀው እሳት ረመጥ ሆኖ መሬት ወረደ። ደም ደምን እየጠራ እልቂቱ ተጀመረ። የኮሎኔሉ የበቀል በትር ሦስት እንጓዎች አሉት። ከላይ ደርግና መኢሶን ማእከል ላይ አሉ። መሀል ላይ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር። ከሥር ከፍተኞችና ቀበሌዎች ዘምተዋል። ሦስቱም አንድ ግንባር ፈጥረው ማጥቃቱን ተያያዙት። የአዲስ አበባ አየር በባሩድ ሽታ ታጠነ።

"ኢሎ——ሄሄ_ላማ ሰብቀታ——ኒ!!" ኢትዮጵያ እንደ ራሄል፣ አዲስ አበባ እንደራማ ዋይ ዋይ አሉ።

የመጀመሪያው ሌሊት ወይዘሮ ማስተዋልን ደብረሊባኖስ አድርሼ የተመለስኩበት ቀን ነው። ቀን ላይ ቢታኒያን ጊዮን ሆቴል ወስጃት ነበር። እርግዝናዋ ጸባይዋን ቅይርይር አድርጎብኛል። ለደቂቃዎች እንድለያት አትፈልግም። ትንሽ ቆይታ ደግሞ 'ይዘኸኝ ውጣ' ትለኛለች። ይዣት ስወጣ ምን ለማድረግ እንደወጣን ይጠፋባታል። እዚህ ውሰደኝ...እዛ አቁምልኝ...እዚያ መልሰኝ ትለኛለች። ጊዮን አምሽተን መጥተን ቤት ስንደርስ ሙሴ ባልዲ እየተዋከበ መጣ። ለምግብ እንኳን ጊዜ አልነበረውም።

"ቤቲ፣ ስመረ...ሌሊት ላይ ተኩስ ይከፈታል...የትም ንቅንቅ እንዳትሉ!" አስጠንቅቆን እየሮጠ ሄደ።

"...መልሱን ዐውቀዋለሽው፡ ከአንተ አልጠብቅም። ለእኔ ደንታ ስለሌለህ ነው። ሂድ። ግን ወይ ድርጅትህን ወይ እኔን መርጠህ እቅጩን ነግረኸኝ ነው የምትሄደው። 'አሳማኝ ምክንያት' ምናምን ብለህ እንዳትንዘባዘብ። ኢሕአፓ የሰው እጥረት የለበትም..." ከመቅጽበት እሳት ሆነች።

'ጉ---ድ ፈ—ላ!'

ምሬቷ ውስጤን ባዶ አደረገው። ቁጣዋም ይሁን ክርክሯ ምክንያታዊ እንዳልሆነ እሷም ይገባታል። አሁን ለዚህ ግድ አልነበራትም። "እስከዛሬ የምትነውና የደማነው ይበቃል" ዓይነት ስሜት ሠሰለኝ ተቃውሞዋ። የኢሕአፓን የመስመር ስህተት በብዙ ክርክር ካሳመንኳት ወዲህ ለድርጅቱ የነበራት ስሜት በጥያቄ ተሞልቷል። ጭንቅ አለኝ...

"ቤቲዬ፣ በዚህ አስጨናቂ ጊዜ ወጣ ማለቴም አይከፋም። እንደምታይው ጓዶች እንደ ቅጠል እየረገፉ ነው..." አሁንም ተናግሬ ለመጨረስ እድል ልትሰጠኝ አልፈለገችም።

"ሰ---ሙ፣ በቃ አፍክን ዝ----ጋ! ሐሳብህ ገብቶኛል። ቢታኒያ ያንተን ልጅ በሆዷ ይዛ እዚህ አዲስ አበባ ደፋ ከንብል ትበል። ሰመረ አገር ሲረጋጋ ለተዝካር ይመጣል። ይህንን አይደል የምትለው?!"

"ኧረ እኔ ደፋ ከንብል ልበልልሽ! ለምን አሁን..."

"ው—ሸ---ት—ህ!! ውሸትህ!!" ብላ ጮኻብኝ በተቀመጥኩበት ጥላኝ ወደ እልጋዋ ሄድ ሽፍ፡ንፏን ብላ ተኛች።

'ምን ይሻለኛል?' በረጅሙ ተነፈስኩ።

ድርጅታችን በሚሠራው ስህተት የበርካታ አባላቱ የግራ ዘመምነት ወኔና ጽናት እየተፈተነ ነው። ቀውሱ ቀስ በቀስ ጊዜውን ጠብቆ እኔንም እየነካኝ ነው። ጭልምልም ብሎብኝ የማደረገው ሳጣ በማግስቱ ወደ ሽዋዬ ሄድኩ። በሽምግልና ሄዳ ቢታኒያን እንድታሳምንልኝ ጠየኳት። በአሳቻ ሰዓት መጥታ ሳይታሰብ ተሰውራ ከምትሄደው የሴት እንግዳዋ ጋር አገኘቻት። አሁን አሁን የማእከላዊ ኮሚቴ አባሏ አበበች በቀለ መሆኗን እርግጠኛ እየሆንኩ መጥቻለሁ። ሽዋዬ ስለ አካሏ ምስል ስትነግረኝ ደግሞ የበለጠ አመንኩ።

'እሷ መሆን አለባት ስብሰባ ላይ የምናገረውንና የምይዘውን አቋም እየመጣች የምትነግራት!'

ሽዋዬ በሚቀጥለው ቀን ጧት ሄደች። ቢታኒያን አሁንም ልጅቱን ሸኝታ ስትመለስ አገኘቻት። ገና ነገሩን ስታነሳላት አስቆመቻት...

የኛን መኪና እየሰራችሁልን ነው። ደስ ይላል። በቅርብ ጊዜ እወስዳታለሁ ማለት ነው?" ብሎ በቀኝ እጁ ወደ መኪናዋ አመለከተኝ።

አሁን በደንብ አስታወስኩት።የመኢሶኖች መኪና ሾፌር ነው። የተለየ ስጋት ወይም ጥርጣሬ...ብቻ ምንም ዓይነት ስሜት አልተፈጠረብኝም። እጁን ይዤው ወደ መኪናዋ ሄድን። የጥገናዋን ደረጃ አስረዳሁት...

"የቀራት አንድ ትንሽ እቃ ማሟላት ነው። ከውጭ የሚገባ እቃ ስለሆነ ብቻ ነው የዘገየው። የእቃው አስመጭ ድርጅት ጅቡቲ መድረሱን ነግሮናል። ከሦስት ሳምንት በኋላ መኪናህን ጨርሰን እናስረክብሀለን። እኔ ራሴ እደውልለሀለሁ።" በጣም አርግጠኛ ሆኜ ቃል ገባሁለት።

እሱን ሸኝቼ ወደ ቢታኒያ ከመሄዴ በፊት ወደ ምድር ቤት አመራሁ። ሸዋዬንና ደጀኔን በድል ስሜት ሲጨባበጡ አገኘኋቸው። ከተሳካ አንድ የግድያ ኦፕሬሽን ተመልሶ መምጣቱን ገመትኩ። ምን እንደተገኘ ጠይቄያቸው አጠገባቸው ተቀመጥኩ።

"አንድ አረመኔ የፖሊስ መርማሪ ነበር፣ ሻምበል ጣሰው የሚሉት። አንዲት ጓዳችንን አስሮ ወፌ ይላላ ሊገርፋት ሲል ነፍሰጡር ሆና አገኛት። እንዳይተዋት ጭካኔውን በምን ያርካ? ዐስቦ ዐስቦ ማንም ከሴት የተወለደ ሰው የማያደርገውን ግፍ ሰራባት። የጡቶቿን ጫፎች በፒንሳ አጣብቆ ብልቷ ውስጥ በርበሬ ጨመረባት። ሦስት ሌሊትና ቀን ደም እንባ አልቅሳ በአራተኛው ቀን በብዙ ልመና ገላዋን እንድትታጠብ ፈቀደላት። የከፍተኛ አሥራ ሁለት ሕዝብ ኡኡኡ... ብሎ ነው ያለቀሰው። አሁን እሱን ጠብ አድርገውት መምጣታቸውን እያጫዎተኝ እያለ ነው አንተ የመጣኸው።"

የሰውየው ድርጊት ዘግንኖኛል። እንደተለመደው ከርእዮተዓለም አንጻር ሳየው ግን ስሜት አልሰጠኝም። የራሳችን ድርጅት ድክመት ያስከተለው መዘዝ ነው። የኮሎኔል መንግሥቱ የጭፍጨፋ ዘመቻ በየቀኑ አዳዲስ የጭካኔ ተዋናዮችን በመፍጠር ላይ ነው። የአራት ኪሎዎቹ ግርማ ከበደና ብርሁኑ ከበደ ግንባር ቀዳሚዎቹ ናቸው። በቀናት ውስጥ ከኮሎኔል መንግሥቱ እኩል ታዋቂ "ሰዉ አራጆች" ተብለው ለሁሉም ዘንድ መነጋገሪያ ሆነዋል።

'ይሄም ቢሆን የገዛ ድርጅቴ "አድብቶ የመግደል" ፖሊሲ ውጤት ነው!' አልኩ ለራሴ።

ደጀኔ ብርሃነመስቀልን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ሄደው ብርሀነ እንደተሰወረባቸው ነገረን። መልሼ መላልሼ ሳስበው ድርጅታችን በገባበት ጥልቅ ማጥ አዘንኩ።ሸዋዬ ብርሃነመስቀልን በጣም ጠልታዋለች። እሱ ሲነሳባት ሁሌም ደስ አይላትም። ብድግ ብላ ሄዳ በቆልት ይዛልን መጣች። አቅረባልን መብላት ስንጀምርም የወሬው አጀንዳ አልተቀየረም። እኔ ጭንቅላት ውስጥ ተሰንቅሮ የቀረው ሐሳብ ግን ሌላ ነው። የሱ---ፍ አበ----ባ! በየቀኑ እየጫጫች...እየገረጣች...አካሏ እየከዳት...ገጿ ጉስቁልቁል እያለ

ሲመጣ በዓይነህሊናዬ ታየችኝ። ከዚህ በኋላ ተመልሳ ያሸተች ተከል ለመሆን እድሏ ተሟጦ ታሰበኝ። ከሆነ ደግሞ አንዲት ትንሽ ቀዳዳ አለች። የፖለቲካ ቢሮውና ማእከላዊ ኮሚቴው ዘርዑንና ጸሎተን ተከትለው ከወጡ ብቻ ትንሽ ተስፋ ይታየኛል። ሸዋዬ ስትጠራኝ በርገግ ብዬ ሐሳቤን አቋርጬ ወደ እነርሱ ተመለስኩ...

"አንተ አላምር፣ አሁን በቤቲ በኩል ነው የመጣኸው?"

"አይ ቀጥታ ነው የመጣሁት። ምነው፣ ችግር አለ እንዴ?" ጠየኳት።

"ምንም ችግር የለም። እንዲያውም የሚያዝናና ነገር ነው። አትንገሪው ብላኛለች።" ከፍ ባለ ድምጽ ከልቧ በሳቅ ተንከተከተች።

አንድም ብልጭ ያለልኝ ነገር የለም። ችግር ከሌለ ምንም ቢሆን ግድ የለኝም። ደጀኔ ነገም ለሌላ የግድያ አፕሬሽን እንዲወጡ መታዘዛቸውን ሲነግረኝ ጋዝ ጋዝ አለኝ። የጎንደር ጉዞዬ አሁኑኑ ቢሆን እመርጥ ነበር። ብረር ብረር የሚለኝ ነገር መጣ። ኢሕአፓን በተቀጣለት የእርምት እንቅስቃሴ እናስተካክለዋለን የሚል ተስፋ ነበረኝ። አሁን አሁን ግን ይህ ጅላጅል ምኞት ሆነብኝ። ትንሽ ተሟውተን ወደ ቢታኒያ ለመሄድ ተነሳሁ። እስካሁን ደወል አለማሰማቷም ገርሞኛል። ሸዋዬ ያዝናናል ያለችኝን ነገርም ለማየት ተቻኩያለሁ። ቀዩን በር ከፍቼው ገባሁ።

'ከሁለት ቀናት በኋላ ከሚስቴ ጋር ረዥም ጉዞ ልወጣ ነው!'

ገርበብ ያለውን የቢታኒያን ከፍል በር ለዐመል ያህል አንኳኩቼው ገባሁ። በመጀመሪያው ከፍል ሶፋ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ ጠበቀችኝ። ልቅም ያለች የገጠር ውብ ወይዘሮ። ጸዳ ያለ ረጅም ትውፊታዊ ቀሚስ በቀጭን ነጠላ አጣፍታ ለብሳለች። ጸጉሯን በጥቁር ሻሽ ግጥም አድርጋ ሸፍና አሥራዋለች። ግንባሯ፣ አገጯና አንገቷ በንቅሳት ተዥጎርጉሯል። የእጅ አንባርና የእግር አልቦ አድርጋለች። ትኩር ብዬ ሳያት ፊቷን ለማዞር ገልመጥ ስትል የወሊድ ቀኗ የደረሰ የስምንት ወይም የዘጠኝ ወር እርጉዝ ናት። በቃ፣ ተመችቷት ያደገች ያንድ የገጠር ባላባት ልጅ ወይም የልጁ ሚስት።

"እ----ህ፣ ቤቲ-----የ ነሽ ወይስ----" ሸዋዬ ያለችኝን ሁሉ እርስት አድርጌው የእውነት ግራ ገባኝ።

¨ ·ሏ ስቆም ረጅም ሳቋን ለቀቀችው። የገዛ ፍቅረኛዬ ቢታኒያ መሆኗን ያወኩት ሳቋን ስሰማ ነው። የተሳካ የማመሳሰል ጥረት ነው። የዛሬውን አያድርገውና ኢሕአፓን በዚህ በኩል የሚስተካከለው የለም። የጉዟችን ዝግጅት አካል መሆኑ ነው።

"ቤቲዬ፣ ይሄ ለወሊድ የተቃረበ እርግዝና የምር ነው ወይስ ቀልድ?" ይበልጥ እየተደነኩ ጠየኳት።

ሳቋን መቆጣጠር እያቃታት ቀሚሷን ሽቅብ ሰብስባ ሆዷን አሳየችኝ። ከቆዳዋ ቀለም በጭራሽ የማይለይ በጥንቃቄ የተነፋ ባዶ ፕላስቲክ ሆኖ አገኘሁት። ማንም ሊጠራጠረው የሚችግረው እምብርት ሁሉ አለው። በጀርባዋ በኩል አልፎ በፕላስቲክ ከሰውነቷ ጋር ተያይዟል። ቀሚሷን መልሳ ስትለቀው ቁጭ የደረሰች እርጉዝ!

"ሰሙዬ፣ አንተና ኢሕአፓ በአንዴ ሁለት ልጅ አስረገዛችሁኝ! ካካካ..." በሳቅ ፍርስ አለች።

\###

ከአራት በኋላ እስከ ሌሊቱ ሰባት ሰዓት የእሷን የድርጅት ሥራ እየተጋገዝን ሠራን።

ከአዲስ አበባ የኢሕአፓ በይነቀጠና ሁሉም ቀጠናዎች የተሰበሰበ የማብራሪያ ጥያቄ ከምር ነው። ከሰባ አምስት በመቶ በላይ የሚሆነው ጥያቄ በአንድ አንኳር ጉዳይ ላይ ያተኩራል...

"ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም በድርጅታችን ላይ እንደዚህ ያመረረ እርምጃ ይወስዳል ብሎ አመራሩ አልጠበቀም ወይ? ሰውየው ድርጅታችንን እንዴት እንደሚመለከተው ፖሊት ቢሮው በትክክል እውቀት ነበረው ወይ? የሚያውቅ ከሆነ በዝርዝር ይግለጽልን። አሁንስ ቢድርጅታችንና በጓዶቻችን ላይ ይህንን ያህል ጥፋት ከደረሰ በኋላ የትግል ሥልታችን ምንድነው የሚሆነው? የሥልት ለውጥ ይደረጋል ወይስ በዚሁ ነው የምንቀጥለው?"

አጅግ ፈታኝም አሳዛኝም ጥያቄ ነው። አባላት ድርጅታችን በየቀኑ እግሩና እጁ እየተቆረጠ አካለ ጎደሎ ሆኖ ሲያዩት በጣም ተረብሸዋል። የግንኙነት መስመሮች መቆራረጣቸው የብዙዎችን ሕይወት አደጋ ላይ ጥሎታል። ሁለታችንም ጭንቀት ገባን። ቀና ብለን ተያየን...

"ሰሙዬ፣ ምን ማብራሪያ እንስጣቸው?" ትከት ብሏት ጠየቀችኝ።

ዐስቤ ዐስቤ የመሰለኝን መልስ አእምሮዬ ውስጥ አደራጀሁ። በሰፊው አቀርብላትና እሷ መርጣ ማስታወሻ ትይዛለች። ከፖሊት ቢሮው ድርሳን ጋር መጣጣሙን አረጋግጣ ትለቀዋለች። ማስታወሻ ስታዘጋጅ ቀስ ብዬ እነግራት ጀመር...

"ይሄውልሽ ቤቲዬ፣ ኮሎኔል መንግሥቱ በትክክል ኢሕአፓን ከየትኛውም ጠላቱ በላይ ይጠላዋል። በበኩሌ አራት ምክንያቶች አሉት ብዬ አምናለሁ። ሲጀምር የእኛ የመሪዎቹና የአብዛኛው አባላቱ የብሔረሰብ ስብጥር ጨርሶ አይመቻቸውም። ከሰማኒያ በመቶ በላይ የሰሜን አማርኛና ትግርኛ ተናጋሪ

ተረማጆች ነን። በዚህም ምክንያት በአንድ በኩል የወደቀው የሸዋ አማራ ገዥ መደብ ቅጥያ አድርገው ይመለከቱናል። በሌላ በኩል በኤርትራ ጥያቄ ላይ የሻአቢያና የጀብሀ ተልእኮ አስፈጻሚዎች ብለውናል። ይህ እሱ በግሉ ወይም እንደ አንድ የደርግ አባል ፈጠርነው ከሚሉት 'የኢትዮጵያ ትቅደም' መርሆ ጋር ይጻረራል። በዚህ ምክንያት አምርረው ጠሉን...

"ሁለተኛ፣ የኢሕአፓ የፖለቲካ መስመር ለኮሎኔል መንግሥቱ ገዳይ ፖለቲካዊ መርዝ ነው። መንግሥቱ ደርግንና መኢሶንን ተጠቅሞ የሥልጣን መሰላሉን ሽቅብ እየወጣ ነው። በመሀሉ የእኛ መፈከር ብቅ አለ። ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት። ከየትም አቅጣጫ ያልመጣበት ፈተና ነው። ይህ ለእሱ ምን ማለት ነው? መፈከሩን ሕዝቡና ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ቢደግፉት የኮሌኔል መንግሥቱ የሥልጣን ሩጫና ጥረት ገና በማለዳው ፖለቲካዊ ሞቱን ሞተ ማለት ነው። የመሪነት ሙብት የለህም ነው ያልነው። ሥልጣኑን በሕዝብ ለተመረጠ ሸንጎ አስረከቦ ወደ ሐረር ሊመለስ ነው። ይህ የማይታሰብ መራራ ውሳኔ ነው። በዚህ ምክንያት ከየትኛውም ተቃዋሚ ይልቅ እኛን ልክ እንደ ግል ጠላት ይመለከተናል።"

"ስሙዬ፣ በጣ--ም እወድሃለሁ። ቀጥልልኝ..." ቢታኒያ ደስ አላት።

ትንሽ እረፍ ብዬ አእምሮዬን ከበረበርኩ በኋላ ወደሚቀጥለው ነጥብ እመራሁ። ቢታኒያ በፍጥነት ትጽፋለች...

"ሌላው የተግባር ምክንያቱ ያው በመንግሥቱ ላይ የተደረገው የግድያ ሙከራ ነው። ከመጠን በላይ አደናግጦታል። መራራ ቂም እንዲይዝም አድርጎታል። ነገር ግን ለመበቀል አቅዶ የፈለገውን ያህል ነጻነት አላገኘም። እዛው ያሉ ተቃዋሚዎቹ የመዋቅር ለውጥ አድርገው አዳከሙት። እነርሱን ለማስወገድ የቆረጠውም 'ኢሕአፓ ላፈሰሰው ደሜ እውቅና አልሰጡትም' ብሎ በመቆጨት ጭምር ነው። በቃ፣ ሰባቱን ጓደኞቹን ሲገድል የተረፉት ደንቆሮ ደርጎች 'ቆራጡ መሪያችን' አሉት። ይህ ወደ አዲስ የፖለቲካ ሥነልቦና ደረጃ አሸጋገረው። ፊቱን ወደ እኛ ድርጅት አዞረ። መግደልን 'የቆራጥ መሪነት' መስፈርት አደረገው። ያው በሳልሽው ተመተሪ ነው ነገሩ፣ በገዛ ስህተታችን የመሞቻችንን ቢላዋ አቀበልነው..."

በመሀሉ ሌሊቱ መግፋቱን ረስተነዋል ወይም በልምድ ችላ ብለነዋል። ከቅርብ ርቀት የመትረየስ ጥይት ተንፈቀፈቀ። ዷዷዷዷ......! ካካካካካ......! ድምድምድምድምድም!የሱፍ አበባዋ ሱፍ ጥሬዎች ያለምንም ርህራሄ ምጣድ ላይ ተደርገው መቆላት ጀመሩ።

# 37

ከሌሊቱ ፲፩:30 ሲል ቢታኒያ፣ ጀማልና እኔ ሆነን ከጋራዥ ወጣን።

ላንድሮቨሩን ጀማል እንዲነዳት አድርጌያለሁ። ቤቲ በጉዞ ዝግጅት ምክንያት ትላንት ሙሉ ሌሊት እንቅልፍ አላየችም። በተቻለ መጠን ሆቴል ምግብ ገዝተን እንዳንበላ ስትል ምግባችንን ስታዘጋጅ አደረች። ሽዋዬና ደጀኔ ሳይቀሩ መጥተው አገዟት።

ጉዟችን ፖለቲካዊና ወታደራዊ ግብ ስላለው ጥንቃቄ ይጠይቃል። ለዘርዑ ከሕሽን የምሰጠው ገንዘብ በተለይ በምንም ተዐምር ሊደረስበት አይገባም። ጀማል አዲስ ነገር የመፍጠር ችሎታውና ፍጥነቱ የሚገርም ነው። ትላንት ምሽት አንዱን የጋራዥ የመፍቻ እቃ የብረት ሳጥን በሦስት ክፍሎች ቆርጦ አዘጋጀው።

ኤርትራውያን መቼም የጋራዥ ሥራን ያመልኩታል። ጥቂት የአስመራ ሰዎችን የሚመለከት የቅኝ ግዛት ውርስ አድርገው አይደለም የሚመለከቱት። የአዲሱ ኤርትራዊ ማንነታቸው ኢኮኖሚያዊ መገለጫ አድርገውታል። "ከኢትዮጵያውያን እንበልጣለን" ሲሉ ጋራዥ ሞልቶናል ማለታቸው እንደሆነ በቀላሉ መረዳት ይቻላል። የሚገርመው ተማሩ የሚባሉ ልሂቃን ሳይቀሩ እንደዛ ያስባሉ። በበኩሌ የኤርትራን ጥያቄ ከዚህ ገጽ ስለምመለከተው ሁሌም አቋሜ አንድ ነው፣ "ሌት ዘም ጎ!" እላለሁ።

ጀማል አማርኛ በደንብ ስለማይችል ይመስለኛል፣ ብዙ ጊዜ ጭምት ነው። ያዘዝኩትን ሁሉ ሳያመነታ ይፈጽማል። ከአንድ መቶ ሽህ ብር በላይ የገመትኩትን የድርጅት ገንዘብ ሦስተኛው ሳጥን ውስጥ አስቀመጥነው። ዝምብዬ ሳስበው ግራ ዘመምነት ምን ዓይነት ባህርይ እንደፈጠረብን እገረማለሁ። ይህንን ሁሉ ገንዘብ ይዘን ምንም መስሎ አይታየንም። በቃ፣ የሆነ ጠቃሚ ቅጠል...ወረቀት...

ካርቶን። አምስት ሳንቲም የማንሳት ፍላጎቱም ጥያቄውም የለንም። ይሄኔ አንዱ ሊብራል ቀኝ ዘመም ቢሆን ኖሮ ይሄንን ያህል ብር ይዞ ብን ብሎ ከጠፋ በኋላ ስለሚኖረው የቅንጦት ሕይወት ነበር የሚወዘወዘው።አእምሮዬን ወደ ጀማል መለስኩት...

'እ------ይ ጉድ! ከእነ ጎይቶም ለባሲ ጋር ሰባት ሆነው መጡ። ስድስቱ በአንድ ወር ውስጥ አልቀዋል። ጀማል ብቻ ተርፎ ይሄው ወደ ኤርትራ ለመመለስ መብቃቱ ነው።' ከጀርባው ቂጭ ብዬ ሳየው ሐዘን ተሰማኝ።

ቢታኒያ አንቅልፍ አንድትተኛ ስል ከኋላ ወንበር ተቀመጥን።ወንበሩ እንዲመቻት በጨርቅና በሸራ ደልድየዋለሁ። ዋናውን አስፋልት ይዘን ወደ ኑረዲን ዳቦ ቤት ስናመራ ጭኔን ተንተርሳ ጋደም አለች። ለእሷ ይህ ጉዞ ከፖለቲካ ይልቅ ማኅበራዊ ተልእኮ አለው። ከእኔ ጋር ነው የምትጓዘው። በትላንቱ አለባበሷ ናት። ባየኋት ቁጥር መላመድ አቅቶኝ በሳቅ ቡፍ እላለሁ። "ምናባህ ያስቅኻል፣ ምሮን!" ብላኝ እሷም ትስቃለች። ለመለማመድ ገና ብዙ የምቸገር ይመስለኛል። ወይዘሮ ማስተዋልን ደብረሊባኖስ አንድ አፍታ ቆም ብለን ለመጠየቅ ፍላጎት ነበረን። የእሷ አለባበስ ምቾት አይሰጣቸውም ብለን ሰጋን።

"አ---ው እንደሱማ አይሆንም፣ ማስቴ በጣም ጠርጣራ ናት። የሆነ ምሥጢር እንዳለኝ አይጠፋትም። ከዚያ እንቃ ይዛኝ አለቅም ነው የምትለው!" ስትለኝ አልፈናቸው ለመሄድ ተስማማሁ።

አዲስ አበባን እያቋረጥናት ሄደን አውቶቡስ ማረፊያ ስንደርስ የግራ አቅጣጫችንን ያዝን። እስካሁን ተገድሎ የተጣለ የ"አናርኪስት" አስከሬን አይታየኝም። ምናልባት ተረኛው ከፍተኛና ቀበሌ ሌላ ሊሆን ይችላል። ከግድያው ጎን ለጎን የደርግ/መኢሶን ያለፉት ቀናት ትኩረት ትምህርት ቤቶች ሆነዋል። ሰፊና ተከታታይነት ያለው የማጋለጥ ዘመቻ ጀምረዋል። ተማሪዎችንና መምህራንን ሰብስበው መዝሙር ያስቀድሙና በሥነልቦና ጫና ራሳቸውን እንዲያጋልጡ ያዋክቧቸዋል...

ያጋለጠ አመለጠ፣

ያልወጣ ራሱን አጣ!

መግቢያ ቀደዳ የሚያስከፍቱበትም ዘዴ ቀይሰዋል። አንድ የሌላ ቀበሌ ነዋሪ የሆነ ተጠርጣሪ ኢሕአፓ ይፈልጉና ስሙን ይጠሩታል። ከእሱ ጋር የተነጋገሩ ወይም አብረው የሠሩ ዋስትናና በራስ መተማመን እንዲያጡ ያደርጓቸዋል። ዘዴው አንዳንድ ቦታ ሰርቶላቸዋል። ይህ ካልሠራ ሌላ ዘዴ ይጠቀማሉ፣ "ወላ ሳታውቁት ወይም ያለፍላጎታችሁ ዲሞክራሲያ ጋዜጣ መሬት ወድቆ አንስታችሁ ያነበባችሁም

ቢሆን እናውቃችኋለን። ምህረት የሚደረግላችሁ ግን ራሳችሁ በፈቃዳችሁ ካጋለጣችሁ ብቻ ነው።" ይሏቸዋል።

ከዚህ የሚያመልጥ ስለሌለ ብዙ ሰው ይግተለተላል። ፖሊሶችን አሰማርተው እያንዳንዱ ሰው ቃል እንዲሰጥ ያደረጉታል። ቀጥሎ የሦስት ሳምንታት የርእዮተዓለም ትምህርት እንዲወስድ ይደረጋል። በጣም የተሳካው ዘዴያቸው ግን የእኛን ወዶ ገቦች መጠቀም መቻላቸው ነው። ጥቆማ እንዲሰጡ ያድርጉና የተወሰኑትን በአፈሳ ይይዛሉ። ከዚያ ወዲ ይላላ ይገለብጧቸዋል። በዚህም ምክንያት አዲስ አበባ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ግዙፍ እስር ቤትነት በመለወጥ ላይ ናት።

ላንድሮቨሯ የእንጦጦን ዳገት ተያያዘችው። ሐሳቤ መፍሰሱን ቀጥሎ ሙሴ ባልዲን ድንገት ጠለፈው።

ሙሴ ትላንት ከምሳ በኋላ ቤት መጥቶ ነበር። በመጠኑ ተረጋግቶ ትልቅ ሰው ለመሆን እየጣረ ነው። የድሮው የዋህነቱ ግን እንዲህ በቀላሉ የሚለቀው አይመስልም። ወይዘሮ ማስተዋልን በተደጋጋሚ መጥቶ ስላላገኛቸው ቅር አለው።

"ቤቲዬ፣ ሰመረ፣...ሹመት ያዳብር! በሉኝ እንጂ። የከፍተኛው አብዮት ጥበቃ ኮሚቴ መች ግብረኃይል ሰብሳቢ ሆኜ ከቅላንት ወዲያ ጀምሬ ተሹሜያለሁ'ኮ።" ሲለን ስለ ሥራው ባናውቅም እሱ ደስ ስላለው ብቻ ተነስተን ጨበጥነው።

"ሰማ እንጂ ሙሴ፣ ይሄ የሚያዘውንና የሚገደለውን ሰው እናንተ ናችሁ እንዴ የምታስሩት? እኔማ ጨነቀኝ'ኮ። ይሄ ሁሉ ሰው ኢሕአፓ ከነበረ ምን የተረፈ ሰው አለ ይባላል?" ቢታኒያ፣ ዝም እንድትል ሳፈጥባት ሳታየኝ ቀርታ፣ ጠየቀችው።

ሙሴ ባልዲ ምግቡን እየበላ...በመሀሉ ጉርሻውን እጁ ላይ ይዞ ለሴኮንዶች እረፍ እያለ...እንደገና እየጎረሰ ያኘውተን ገባ። አንድ ቃል በነገረን ቁጥር ታዲያ አንድ ምክር ጣል ያደርግልናል። ጥያቄዋን መነሻ አድርጎ በቢታኒያ የዋህነት ፈገግ ካለ በኋላ ቀጠለ...

"ቤቲዬ፣ ሰመረ፣ ልንገራችሁ።ጊዜው በጣም ጥንቃቄ የሚፈልግ ጊዜ ነው። ቢታኒያ እንዳልሽው አንዱን ሰው ከሌላው ምን እንደሆነ መለየት መንግሥትን በጣም ከብዶታል። ወይ የውጭ ጠላት አይባል። ንጹህ ሰው አብሮ ተጎዳ። ሲጨንቀን ባለፈው ሳምንት አለቆቻችንን ጠየቅናቸው። እንዴ ምን አለን መሰላችሁ? 'አናርኪቶችን ብዙ ጊዜ የምትለይዋቸው በሚናገሯቸው ቃላት ነው። እኛ "እናሸንፋለን!" ስንል ኢሕአፓዎች ግን "እናቸንፋለን!" ይላሉ' አለን። እኔ አልተቀበልኩትም። እጄን አወጣሁና፣

አናርኪስትን ምኝ አደረክው እንዴ ተይዞ "እናቻንፋለን!" የሚልልህ?" ብዬ ሰውን አሳኩት። በኋላ ግን ዝም ብዬ ሳስበው ሰው እያለቀ ያለው እውነትም በንግግር አለማወቅ ነው። አደራችሁን፣ አፋችሁን ቆጡ!" ምክሩ በእውነት ከልብ ስለነበረ ከቢታኒያ ጋር ስንተያይ ውለታ እንደተሰማን ተግባብተናል።

ሙሴ ስለ ደርግ መኢሶን የሙጭው ጊዜ እቅድ የሚያውቀውን መረጃ ዝርዝር አድርጎ ተረከልን። ወዲያው አስተላለፍነው።

እንጦጦ ደርሰን ለፍተሻ ቆምን። የፍተሻው መዐት ጨርቅ እስፐሎ ያሳብዳል። አካል ላይ የበቀለ ጸጉር ወይም ቡግር ነገር የሚፈልጉ ነው የሚመስሉት። ደግነቱ መረጃዎቻችንና መመሳሰላችን አጅግ የተዋጣለት ነው። ሁሉንም ኬላዎች በራስ መተማመንና መረጋጋት ሳይለየን እየተፈተሽን ለማለፍ ተነጋግረናል። ዋናውን ፍተሻ በቀላሉ አለፍን። ቢታኒያ ተመልሳ ጋደም አለች። በመንገዳችን ላይ ነፍሰጡር ሴት ማየት የሌለባት ነገር ሊያጋጥመን ይችላል። በእንድም ከፉ ትርኢት እንድትረበሽ አልፈልግም። መተኛቷን የምፈልገው ለዚህ ነው። ረጅሙን የሸዋ ሜዳ ስንያያዘው ሐሳቤ ወደ ሙሴ ባልዲ ተመለሰ...

እፍ ያመጣል አዳ! ይላሉ አበው። ለዚህ አስቸጋሪ ጊዜ የሚስማማ እውነት አለው። ፈረንጆች በራሳቸው መንገድ ይገልጹታል፣ "ሕይወትና ሞት በምላስ ሥር ናቸው።" በእኛ በኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴም ይሁን በደርጎች በኩል ምላስ ሞትንና ሽረትን እየወሰነች ነው። ቃላት የድርጊት ነጸብራቅ ሆነው እንገት የሚቀላበትን ሰይፍ እስከመሳል ድረስ ጠንክረዋል።

ጌታቸው ማሩ ከዮሀንስ ብርሀኔና ከጸሎተ ሕዝቅያስ ጋር ቁጭ ብሎ ሲያወራ አንድ ነገር እንደቀልድ ተናገረ። "በሉ፣ እናንተም ግፉበት፣ እኛም እጃችንን አጣጥፈን አንቀመጥም!" መጀመሪያ ችላ ተባለ። ጠቡ ሲፋፋም ግን ማስረጃ ሆኖ ተጠቀሰበት። ይሄው በእጁ ላይ ሰንሰለት ታሰረበት። የኢሕአፓ ፖሊት ቢሮ አስረኛ ይዞ የሚያስቀምጥበት ወህኒ ቤት የለውም። ጌታቸውን እስካሁን እነ ደጀኔ በገመድ ሲጥ አድርገውት ይሆናል። በዚህ በኩል በጣም ጠንቃቃ የሚባለው ተናጋሪ ብርሃነመስቀልም ከምላስ ወለምታ አላመለጠም። አንዱ ጓደኛው፣ "እዚህ አዲስ አበባ አለህ እንዴ? ለመሆኑ ምን እየሠራህ ነው?" ብሎ ጠየቀው። ብርሀነ፣ "የማእከላዊ ኮሚቴ አስረኛ ሆኜ ይኸው ተቀምጫለሁ።" ብሎ መለሰለት። የግጭቱ እሳት ሲነድ ተጠቀሰበት።

በደርጎች በኩልም ምላስ ሞትንና ሕይወትን መወሰኗ አልቀረም...

ባለፈው ሕዳር ወር ላይ ነው። ደርግ የመዋቅር ለውጥ አድርጎ ዐዋጁ ወጥቷል። ዐዋጁ የኮሎኔል መንግሥቱን ዋና ዋና የተባሉ ሥልጣኖች ለጀኔራል ተፈሪ በንቲ ሰጥቶባቸዋል። አንድ ስብሰባ ላይ

ጀኔራል ተፈሪ መድረኩን ይመራሉ። መንግሥቱ እጃቸውን ያወጡና "ኢሕአፓ ከፍተኛ የኢኮኖሚ አሻጥር እየሠራችብን ነው። ገቢ እያሳጣችን ነው። በሥራ መሣሪያዎች ላይ ጉዳት እያደረሰችብን ነው።" ብለው አማረሩ። ጀኔራል ተፈሪ እየቀለዱ ይሁን የምራቸውን ይናገሩት አይታወቅም። "መንግሥቱ፣ ውኃ ውኃ አሰኝታህ ሳለ ኢሕአፓን ለምንድነው ዘጠኝ ጊዜ «እንቺ እንቺ» ይምትላት?" ከሰሙት ሁሉ የደነገጠ እንጂ የሳቀ አልነበረም።

"አፍ ይጸውራ ለሞት!" ይላል መጽሐፉ። (አፍ ሞትን ይጠራል!) ጀኔራል ተፈሪ የሞቱት ያለጥርጥር ያን ቀን ነበር።

ለጥ ያለውን የሸዋን መስክ አቋርጠን አባይ በርሀ ደረስን። እሱንም ወጥተን ጎጃም ገባን። የጀማል አነዳድ ግሩም ነው። እንደምንም ሄደን ከመሼ ባህርዳር ገብተን አደርን። እዚህም የፖለቲካ አየሩ ከአዲስ አበባ የተለየ አይደለም። ጥቁር ደመና አርግዞ ሕዝቡን በጭንቀት ይንጠዋል። የምናየው ሰው ሁሉ ቆም ሙሾ ሲደረደር የተሰማን መሰለን።

"እነሆ በዚያን ጊዜ ሰው በሰው ላይ ይነሳል። 'አንተም ተው አንተም ተው!' የሚል ዳኛም አይኖርም።" የሆነ ቦታ አንብቤዋለሁ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ግን የትንቢቱ አፈጻጸም ትንሽ ለየት ይላል። የሚገዳደለው ሰው እርስ በእርሱ አይደለም። መንግሥት ነው የገዛ ሕዝቡን የሚረመርመው። ዳኞችም ያለፈቃዳቸው ሥራ ፈት ተደርገዋል። በኮሚቴ አሠራር ስለተተኩ ቢሯቸው በር ላይ ቆመው ጥርሳቸውን ሲፍቁ ነው የሚውሉት። እነ ሻለቃ ተካ ቱሉ የገቡትን ፖሊሳዊ ቃለመሀላ ቆረጣጥመው በልተው ግድያ የሚወስኑት በእጅ ድምጽ ነው። ግን ምን ማድረግ ይቻላል? ድርጅቴ ኢሕአፓም ከታሪክ ተጠያቂነት እያመለጥም። ቤቲ የምትወደውና የምትደጋግመው የቤንጃሚን ፍራንክሊን ጥቅስ መጥቶ ጥልቅ አለብኝ...

"የጠብን ፍም የሚያራግብ በሚፈጠረው ፍንጣቂ ቢቃጠል ማማረር አይኖርበትም!"

ይሄው ፍንጣቂው ቋያ እሳት ሆኖ አገር ምድሩን እየለበለበው ነው። ቤንጃሚን ፍራንክሊን ሌላም ድንቅ አባባል አለው። "ከሞትክ በኋላ ቶሎ ላለመረሳት ከፈለክ፣ አንድም የሚነበብ ነገር ጻፍ፣ አለያም ሊጻፍ የሚችል ታሪክ ሥራ!" ኢሕአፓዎች ለሁለቱም አማራጭ አልታደልንም። ሕቡእነታችን ከመጠኑ በማለፉ ታሪክ አልባ ሆነን እያለፍን ነው።

"አጭሩ የልጅነት ዘመኔ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ በጸጸት የተሞላ ነው!" ቢታኒያ ትንቢት የተናገረች

መሳሉ ተሰማኝ።

ባህርዳር አድርገን በዉኃት ጉዞ ጀመርን። አበይ ድልድዩን ስንሻገር ጠርቅ ያለ ፍተሻ አካሄዱን። እንዲ ፖሊስ ቢታኒያ ላይ አፍጥጦ ዐይኖቹን አልነቅል አለ። አመለካከቱ እንደ ብር ሸንተ ባለመሆኑት ሁኔታው ተለወጠ። "ካልሸፈናችሁ ቀኙ እኛ ስሁ" ብሎ ትንሽ አስቸገረ። ለንድድርጊ የሮጎትን ሜዳ ቶት ብላ ወረታን አልፈን ወደ ይፋግ ከሚወስደው መገንጠያ ስንደርስ ያለስበነው ፍተሻ አጋጠመን። ፖሊሶቹ በጣም ብዙ ናቸው። ጸጥ ብለው እዚያና እዚህ ቆመዋል። ብርብር አድርገው ፈተሹን። ደግነቱ ቢታኒያ ላይ ያፈጠጠ የለም እንጂ ጉቦ ለመስጠትም አመቻ አልነበረም። ጉዟችንን ስንቀጥል መንገዱ ሁሉ ታላቅ ነው። እነ ጎይቶም ለባሲ ተገድለው መንገድ ላይ የተጣሉ ቀን ያየሁት ዓይነት ትርኢት ተመላከትኩ።

ከፋቱ ደግሞ ቢታኒያ ነቅታ ቁጭ አለች። ላስተኛት ስል ውኃ ጠማኝ አለች። እንድም ነገር ማግኘት የለባትም። አዲስ ዘመን ከተማ መግቢያ ላይ ጀማልን አስቆምኩት። ተሯሩጦ ቀዝቃዛ ውኃ ሳመጣላት ግጥም አድርጋ ጠጥታ ጋደም አለችልኝ። ወደ መሀል ከተማው ስንገባ ግምቴ ትክክል ሆኖ እያየሁት ሰው ሆኜ መፈጠሬ አስጠላኝ።

ወደ ጎንደር መገንጠያ ላይ ትንሽ አደባባይ አለች። በላይ በኩል ዳገቱ ላይ አራት ያህል ፖሊሶች ቆመዋል። ከአደባባይዋ ቢታች በኩል በጥይት የተገደለ አስከሬን ወድቋል። ውባት ሴት ናት። የለበሰችውን ቀላል ቀሚስ ነፋስ ገልቦታል። ቀይ ሙታንታዋ ይታያል። ወፈር ያለውና ፍም የመሰለ ቀይ ገላዋ እንደጧፍ ይንተገተጋል። ስፖርት ስትሠራ ቆይታ እረፍት ያደረገች ትመስላለች። አጭርና አፍሮ ዘርቢ የተቆረጠ ጸጉሯ መሀል ላይ ጥይት ጭንቅላቷን ፈረካክሶታል። መቼም ልረሳው አልችልም። አንጀቴ ተንሰፈሰፈላት። አእምሮዬ ድንብርብር ብሎብኝ ወደ መሀል ከተማው ገባን። ከአውቶቡስ ማረፊያው አለፍ ብሎ የወንድ አስከሬን ወድቋል።

'ከዚህ በኋላ ግራና ቀኝ አላይም!' ቁልቁል አቀረቀርኩ።

ባደኩበት አካባቢ ባህል ሴት ልጅ ምንም ይሁን በደም ምልልስ አትገደልም። ሚስት ትሁን እናት ወይም ልጅ። ድርጅቴ ኢሕአፓና ደርግ ከዚህ ትውፊታዊ ወግ ቢታች ቁልቁል ዘቅጠው ታዩኝ። በነፍስ ገዳይነታቸው ሁለቱም ያው ናቸው። ብርክታዊትንስ የገደሏት በዚህ የጭካኔ መንፈስ አይደል?! ሁለቱም ጣሉኝ። ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል የምትታየኝ አሁን ዘርዑ አዲስ አበባ ስለሌለ እርምት ለማድረግ ይመች ይሆናል። በድርጅት ደረጃ የአገር ሽማግሌ አቁም ኃጢያቱን መናዘዝ አለበት። ለሥራው ወንጀል ሁሉ በይፋ ይቅርታ መጠየቅ አለበት።

'ችግሩ ግን ማነው ከሞት ተርፎ የአርምት ንቅናቄውን የሚያደርገው?' ብልጭ ያለችው ተስፋዬ መልሳ ድርግም አለች።

አዲስ ዘመን ከተማን ካለፍን በኋላ የሲአል ጉዞ ሆነብን። በወጉ ያልተጠረገው ሰበርባራ መንገድ እያነሳ ያፈርጠን ጀመር። ቢታኒያን ጠበቅ አድርጌ እየያዝኩ እንደምንም ገፋነው። የምሳ ሰዓት አለፍ እንዳለ እብናት ከተማ ገባን። የከተማው ሕጻናት ልክ እንደተጠራሩ ሁሉ ግልብጥ ብለው መጥተው ከበቡን። ከሰማይ እንደወረደ የሌላ ዓለም ፍጡር አፍጥው በአግራሞት ያዩናል። ሰው እንዳንገጭ እንደምንም ተጠንቅቀን አለፍን። ዐዋቂዎችን እስከምናገኝ እግር መጣያ አጣን።

አንድ ምግብ ቤት አሳይተውን እዛ አቁመን ገባን። በቅል የተያዘ ንጹህ ማር በር ላይ ፀሐይ ላይ ተሰጥቶ ዐየን። ብርዝ አስበጥብጠን እየጠጣን ቁጭ አልን። ከምግቡ ይልቅ ብርዙ ቢታኒያን ተስማማት።

"ሆድዬ፣ አይዞሽ፣ ነቃ በይልኝ!" ስላት "አታስብ ሰሙዬ፣ በጣም ደህና ነኝ!" ትለኛለች።

የምግብ ቤቱ ባለቤት ከወይዘሮ ማስተዋል ጋር የሚመሳሰሉ በሳል ሴት ናቸው። ቡና አፍልተውልን ቅልጥ ያለ ወሬ ጀመርን። ስለ አዲስ አበባ ይጠይቁናል፣ እንመልሳለን። ቀስ በቀስ እየተግባባን ስንመጣ ወደ ፖለቲካ አዘነበሉ።

"እውነት ልጅ ያላት የአዲስ አበባ እናት አለች?" በመገረም ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው ጠየቁን።

"ያው መቼስ ሁሉም ተገድሎ አያልቅ..." ብዬ ቢታኒያ ስታፈጥብኝ 'ላፉከ' ብዬ ዝም አልኩ።

እንደአብዛኛው የገጠር አካባቢ ሰው ጥሩ አቀባበል አደረጉልን። ትንሽ ቆይተን የእብናት ክሊኒክን የሚያሳየኝ ሰው ይኖር እንደሁ ጠየኳቸው። አንዱን ሕጻን ልጅ ጠርተው አስመጡልኝ። ቢታኒያና ጀማል አብረውኝ እንዲሄዱ አልፈለኩም። መንጋጋቱ የደርግን ትኩረት ይስብ ይሆናል ብዬ ስጋሁ። ሕጻኑ እየመራ ሲወስደኝ አልፈነው በገባንበት መንገድ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል እንኳን አይርቅም። ከመንገዱ ዳር ነው። በአካባቢው የተሻለ ሕንጻ ነው። እንደነገሩ በሆነ የጭራሮ አጥር ታጥሯል። በደንብ አይቼው ወደ ጠጅ ቤቱ ተመለስኩ...

# 38

በማግስቱ ጧት ቁርስ በልተን ሦስታችንም ወጣን፣ ወደ አብናት ክሊኒክ። መኪናዋን እዛው ጠጅ ቤቱ ግቢ ትተናት ነው የወጣነው። ከሰው አተያይ እንደተረዳነው ወዞ-ልውጥ መሆናችን በደንብ ይታወቃል። በተለይ ሕጻናትና እናቶች አተኩረው ይመለከቱናል። የገረመኝ አንድ ነገር የሚያተኩሩት እንደፈራሁት ቢታኒያ ላይ አይደለም። ሆዷን አንገፍጣዋለች። አካሄዷም ድንቅ ድራማ ነበር። በእርግዝናዋ የተሰላቸች ሴት መስላ ፊቷን ከፍት አድርጋዋለች። ይህ ችሎታዋ ዓይን ውስጥ እንዳትገባ እንደረዳን አልተጠራጠርኩም። ትኩረቱ በእኔና በጀማል ላይ ነው። ፈተና ከገጠመኝ በቢታኒያ ነው የሚለው ጭንቀቴ አሁን አብሮኝ የለም።

'ግልግል!'

ክሊኒክ ስንደርስ ግቢው በህሙማን ጭንቅንቅ ብሎ ጠበቀን። በትክክል የምንፈልገው ነገር ነው። ከእንጨትና ከቅጠል በተሠራ ቃሬዛ ላይ የተኛ፣ በሰዎች ግራና ቀኝ ተደግፎ የተቀመጠ፣ የክሊኒኩን ግድግዳ ተደግፎ አረፍ ያለ... የበሽተኛ መዐት። በአንቀልባ ታዝለው የመጡ ሕጻናትም ዋይ! ዋይ! እያሉ ያለቅሳሉ። በቅሎዎችና ፈረሶች ኮርቻቸውን ጀርባቸው ላይ እንደሆነ በአጥሩ ዙሪያ ታስረው ሳር ይግጣሉ። ለምሥጢራዊ ተልእኮ አጅግ የተመቸ ትእይንት ነው። ቀስ ብለን ከሕሙማኑ ጋር ተቀላቅለን ወደ ግራው ግድግዳ ሄደን። በተባልነው ቦታ ላይ ቆሞ ይግጥ የነበረ ፈረስ አሰለቅቀን ቁጭ አልን። ቢታኒያ ሰዓቷን አየች።ከረፋዱ 2፡ 30።

ተልእኳችንን ፈጽመን ከተማዋን ልንለቅ ሠላሳ ደቂቃዎች ይቀሩናል። የምናገኘውን ሰው ምስል በአእምሯችን በጠር በጠር አደረግነው። ቀጭን፣ አጠር ያለ፣ በሀያዎቹ መጀመሪያ የዕድሜ ክልል የሚገመት ወጣት፣ አረንጓዴ ካኪ ሸሚዝና ቁምጣ ሱሪ የለበሰ፣ የቀኝ እግሩ አውራ ጣት ባደፈ ነጭ ፋሻ

የተጠቀለለ...።

ደቂቃዎች ከንፍ አውጥተው በረሩ። ለሦስት ሰዓት አምስት ደቂቃ ሲቀረው ትንፋሼ ቁርጥርጥ እያለ ዐይኔ ዙሪያውን መቃበዝ ጀመረ። እንድም ቃል መነጋገር ተሳነን። የሰዓቱ ዘንጎች 3፡00 ቁጥርን መቱ። በሁሉም አቅጣጫ የምንጠብቀውን ዓይነት ሰው ብቅ አላለም። ልቤ ድው ድው ማለት ጀመረች። ሦስታችንም ነገሩን ለመተርጎም ተቸግረን በጭንቀት ተያየን...

"ስሙዬ፣ እንዴት ነው ነገሩ?" የቢታኒያ ዓይኖች መልእክት አስተላለፉልኝ።

ደቂቃዎች ግልቢያቸውን ቀጥለዋል። 3፡20። አሁንም ዐይናችን ውስጥ የገባ፣ የተጠጋን፣ ያነጋገረን ወይም ምልክት የሰጠን ሰው ዝር አላለም። ተስፋ ላለመቁረጥ የሞት ሞቴን ታገልኩ። በደህንነት ደንብ ከዚህ በኋላ ያለው ሰዓት አደገኛ ነው። መልእክተኛው ተይዞ የሚደርስበትን ስቃይ ለማምለጥ መርቶ ሊያሳይ ይችላል። ወይም የደርግ የደኅንነት ሠራተኞች እንድ ቦታ ተደብቀው እስከምንገናኝ እዘግይተውት እያዩን ይሆናል። ለእኔ ችግር የለውም። ጭንቀቱ ለነፍሰጡሯ ፍቅረኛዬ ነው። 3፡40 ሲል ሦስታችንም መረበሽ ጀመርን። በቡድን መሪነቴ ትእዛዝ መስጠት አለብኝ።

"ቤቲዬ፣ ጀማል...ተነሱ እንሂድ!"

ጀማል ወዲያው ፈጥኖ ተነስቶ ቆመ። ቢታኒያ ግን በጣም ቅር አላት። እንድ ነገር ሳይሳካላት ሲቀር ሁሌም እንደዚሁ ናት። አንዳንዴ ቁጭቷን ለሰዓታትና ለቀናት አትረሳውም። ስታመነታ ራመድ ብዬ ሄጄ እጇን ይዤ አነሳኋት። በታውን ለቀን ትንሽ ሜትሮች ራቅ ብለን ቆምን። ሌላ ሠላሳ ደቂቃ አለፈ። ጠብ ያለ ነገር የለም።

ከክሊኒኩ ግቢ ወጥተን መንገዱን ተሻገርን። ትንሽ አለፍ ብሎ ድከምከም ያለ ቡና ቤት ነገር ታየን። ሄደን ገብተን በጠፍር ወንበር ላይ ቁጭ አልን። ፔፒሲ ኮላ ለቢታኒያ አዘዝኩላት። ጠርሙሱን እቧራ የዋጠው ፔፕሲ ከሚንጫጫ የእንጨት መደርደሪያ አውርደው ሰጧት። አልጠጣችውም። ዐይናችን በበሩ በኩል አሁንም ክሊኒኩ ላይ ነው።

4፡10.........4፡40፡...... 5፡20.........6፡00... 7፡00...

አሁን የሚያጠራጥር ነገር የለም። ያንን ሁሉ ውጣ ውረድ ያየንበት ከፍተኛ የድርጅት ተልእኮ ከሸፏል። ሀቁ ምንም ያህል መራራ ቢሆን እምኖ መዋጥ ነው። የመከሸፉን ምክንያት መላምት እያስቀደምኩ

የምመረምርበት ጊዜውም ቀልቡም አልነበረኝም። የቢታኒያ የፊት ገጽ አሁንም በቅሬታ እንደተዋጠ ነው። ጭንቀቷ ከሞላ ጎደል ይገባኛል። የተልእኮው መከሸፍ ከፈጠረባት እልህ በተጨማሪ ሌላ ስጋትም አለባት። አብራኝ ለመሄድ ተልእኮውን ስትቀበል አበበች የሰጠቻት መመሪያ አለ።ፍቅረኞች መሆናችንን ስለምታውቅ እየሳቀች በቀልድ መልክ እንደነገረቻት አገምታለሁ...

"የሰመረን እያንዳንዱን እንቅስቃሴውን ተከታተይው!"

ቤቲ፣ አሁን መመሪያውን ቃል በቃል እያስታወሰች ቀልድ አለመሆኑን እያሰበች ይሆናል። ባዶ እጃችንን መመለሳችን አዲስ አበባ ከእነ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይና ከፍሉ ታደሰ ጆሮ ይደርሳል። ያኔ ውድቀቱ የሚፈጥረውን ስሜት እኔም መገመት አይከብደኝም።"ጓድ አላምረው በትክክል አንጃውን ተቀላቅሏል!" ይህ ከተባለ ደግሞ የሚቀጥለው እርምጃ ብዙም የሚያወዛግብ አይሆንም። የጌታቸው ማሩ ጽዋ እኔንም ይደርሰኛል። በበኩሌ ሰባራ ሳንቲም ቦታ የምሰጠው ጉዳይ አይደለም።

"ጓድ አላምር፣" ሽዋዬ መጥታ ድቅን አለችብኝ፣ "ጓድ አላምር፣ ሁላችሁም እንዴ ስሙኝ። መስዋእትነት ይቀርልናል ወይም ሞትን በሆነ ብልሀት እናመልጣለን ብላችሁ እንዳታስቡ። አሁንም በሌላ አንድ ነገር እርግጠኛ ነኝ። በፍጹም በፍጹም የውሻ ሞት አንሞትም። ዓይንህን ጨፍን...ተንበርከክ...በደረትህ ተኛ! ተብለን ጭንቅላታችን ተፈርክሶ ስንገደል አይታየኝም..." እንዳንገዴ ሟርት ይመስለኝ የነበረው የሽዋዬ ትንቢት አሁን እውነትነቱ ተሰማኝ።

በኢሕአፓ ታሪክ የተልእኮ መከሸፍ ወይም መደናቀፍ አዲስ ተዐምር አይደለም። በሻለቃ መንግሥቱ ላይ ስምንት የግድያ ሙከራ ታቅዶና ተደርጎ ሁሉም ከሽፏል። የወልድያ ንግድ ባንክ ዘረፋ እቅድ... የብርሃነመስቀልና የጌታቸው ማሩ አንጃኝነት...። ኢሕአሠ በራሱ የውድቀት ቋት ነው። በአንጃኝነት መጠርጠሬ የዚህ ውድቀታችን ማሳያ አንድ ምሳሌ ነው። ከምንም አልቆጥረውም። ቢታኒያን የሚወዘውዛት ስጋት እንደሚሆን ግን አላጣሁትም። ምንም ነገር መነጋገር አልቻልንም።

እንዲሁ ተጎልተን ውለን ለዘጠኝ ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩ ወዳረፍንበት ጠጅ ቤት ተመለስን። ባለቤቷ ገና እንዳዩን ሰፍ ብለው ተቀበሉን። ጠፍተን በመዋላችን ችግር ገጥሟቸው ይሆናል ብለው ዐስበዋል። ቅሬታችንን እንደምንም በውስጣችን ቀብረን ልናጫውታቸው ሞከርን። ዋናው ጠጅ ቤት እንደትላንትናው ነጻ አልነበረም። መሸተኞች ሲጫጫሁ ተሰማን።

"በሉ፣ ኑ። ከእኔ መኝታ ቤት አረፍ በሉ። የሰው አገር ሰዎች ምሳ ሳትበሉ በዚያው እልም ትላላችሁ?" ብለው ይዘውን ገቡ።

የምግብ ነገር እንኳን ይቅር። ሆዳችን ከፍት ብሎ ልንበላ ይቅርና እንዲሸተን ራሱ አንፈልግም። ቢታኒያ የቋጠረችውን አገልግል ማየትም በበኩሌ አስጠላኝ። ጀማል ሥጋ ንክኪ ነገር አይበላም። ጨጨብሳ ስትሰጠው ግጥም አድርጎ በላ። እሱ ሲበላ ስናየው ትንሽ ተነቃቃን። የጠጅ ቤቱ ባለቤት አገልግል ለመክፈት ጊዜ አልሰጡንም። ሠራተኞቻቸው የእጅ ማስታጠቢያ እቃ ይዛ ቀረብ አለች። መግደርደርም ይሁን እምቢ ማለት አልተፈቀደልንም።

"በሉማ፣ ታጠቡ...በ'ኛ ባህል ምግብ ቀርቦ መግልገል ነውር ነው። ታጠቢ፣ የ'ኔ ልጅ...በይ!" የቁጣ ያህል ተሜኑን።

እንዲህ ዓይነቱ የበዛ ልግስናና ደግነት አዲስ የሚሆነው ምናልባት ለቢታኒያ ነው። ይሉኝታና የውለታ ብዛት አሳቀቃት። እኔና ጀማል ገጠሩን ስለምናውቅ አልተገረምንም። እንጀራው በትልቅ ዝርግ ሳህን ከፊት ለፊታችን አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ ቀረበ። የሞሰቡ ክዳን ሲነሳ ንድፍ ጥጥ የመሰለ ነጭ ጤፍ እንጀራ። በወይዘሮ ማስተዋል ቤት የምንበላው እንጀራ የንጣት መጨረሻ ይመስለኝ ነበር። ይሄ ይበልጣል። ደንዝዞ የነበረው ወስፋቴ መንጫጫት ጀመረ። አገልግል የሚያከለው ድስት ሲከፈት በንጹህ ጥናቡግ ዘይት የጎደደ የድንች ወጥ ሽታ አፍንጫችንን ቆርጦ ሊጥለው ደረሰ። ቢታኒያ "እሽ" ብላ በእጇ አትበላልኝም። አንድ ለእሷ አንድ ለእኔ እያጎረስኩ ግጥም አድርገን በላን።

"እስቲ ይሄ ሁሉ መስተንግዶ ምን ልናደርግላቸው ነው? ነገ መሄዳችን አይደል?" ቤቲ በጭንቀት አየችኝ።

"ሆዴ፣ የገጠር ሰዎች ውለታ ከፈለጉ ዝምድናውን ማትረፍ ነው። አለያም ግፋ ቢል አዲስ አ'ባ ለሚኖር አንድ ዘመዳቸው ማር ወይም ቅቤ ውሰዱልን ይላሉ። ገንዘብ ላይ ብዙ አይደሉም። ፍላጎታቸው ሰው ነው..." ግራ ዘመምነቴ የውስጥ ግፊቴን ሽቅብ እያናረው አስረዳኋት።

የምግብ እቃው ሲነሳ የእውነት እርካታ ተሰማኝ። የተልእኳችንን መከሸፍ ሁለተኛ ጉዳይ አድርጌ ለማሰብ ግን ከበደኝ። ቢታኒያማ በየመሀሉ ሐሳብ ድንገት ዥ---ው አድርጎ ይወስዳታል። ውድቀቱ ማለፍ ያለበትን የጊዜ እርዝመት ገና አላለፈም። ተልእኮው በውድቀት ጎዳና ላይ የነበረውን ድርጅታችንን ሊታደግ የሚችል ነው ተብሎ የተነገረን መሆኑ ትካዜያችንን ሳያባብሰው አልቀረም።

'የዶክተር ተሰፋዬ መዝረክረክ ሳይሆን አይቀርም ዋናው ምክንያት። እዛ ከተማ ላይ ተጎልቶ ሁሉንም ልሥራው ብሎ ሲንደፋደፍ አንድ ያላቀናጀው ነገር ይኖራል እንጂ እንዲህ ዓይነት ውድቀት አይመጣም ነበር!' አልኩ ለራሴን መሬት መሬት እያየሁ።

የጠጅ ቤቱ ባለቤት ሠራተኛ የቡና እቃ ሲታቀራርብ ዐይኔ ያያታል። ልቦናዬ ግን አላስተዋላትም። ሃሳታችንም ተመልሶ መጥቶ ከሰፈረብን ስመመን ብንን ብለን የነቃነው በመስኮቱ በኩል እንደ መድፍ የሚጮህ ድምጽ ስንሰማ ነው።

"ስ—ማ ብለ—ው ሀ—ል! ስ—ማ ብ—ለ—ው ሀ—ል!! ማንኛውም የእብናት ከተማ ነዋሪ የሆናችሁ ሁሉ! የእብናት ወረዳ ጽሕፈት ቤት ማንኛውም ሰው ከአሁን ሰዓት ጀምሮ በአዲስ ገበያ እንዲገኝ ብለዋ---ል!"

ቢታኒያና ጀማል በድምጹ ግራ ተጋብተው እኔን አተኮሩብኝ። በትንንሽ የገጠር ከተሞች ድምጽ ማጉያ የለም። የስብሰባ ጥሪ የሚደረገው በዚህ መንገድ ነው። ይሄንኑ ስነግራቸው ተረጋጉ። እኔን ያልገባኝ ግን ከቀኑ ፲፱:00 ሰዓት ላይ የሚጠራ ስብሰባ ትርጉም ነው። በዚህ ላይ ብን ብን የሚል ካፊያ ሲወርድ በመስኮቱ በኩል ይታየናል። ሳቁ ሊመጣብኝ ፈለገ። መቼም የደርጎች ነገር ብዙ ቦታ ሰውን ግራ እያጋባው ነው። ትእዛዙን የሚያሰማው ድምጽ ትንሽ ሄድ ብሎ እንደገና ጠራ። በመሀል የጠጅ ቤቱ ባለቤት መቀነታቸውን እያጠባበቁ መጡ...

"ማዘር፤ በዚህ ሰዓት ምንድነው ስብሰባ? እውነታቸውን ነው?" ፈገግ ብዬ በእንግድነት ድምጸት ጠየኳቸው።

"እእእ_ደመላሽ እንተነህ ነው እሉ የጠራው። እሱ ከሆነ ቀልድ የለም። ከሚጠባ ልጅ በስተቀር ደፍሮ የሚቀር የለም። እናንተ ግን ወንዶቹ ከሄዳችሁ አብረን እንሂድ። እሷ አይሆንላትም።" ወደ ቢታኒያ እያመለከቱ።

የእኔ እእምሮ ቀጥ ብሎ ቆም። የቀረው ግን ከሰማነው ስም ጋር ነው። ደመላሽ እንተነህ? ደመላሽ እንተነህ? ደመላሽ እንተነህ? ሴትዩዋ ልክ እንደምናውቀው አድርገው ነው የነገሩን። እኔና ጀማል ወደ ስብሰባው ብንሄድም ባንሄድም የማወቅ ፍላጎቴ ብድግ አለብኝ። ልጠይቃቸው ወደ እሳቸው ዞር ስል መጥተው መሀላችን ተቀመጡና ራሳቸው በጥያቄ አነሱልን...

"ደመላሽ እንተነህን በዚያ በአዲስ አበባ አታውቁትም ወይ?" ተራ በተራ እያዩ ጠየቁን።

"ኧረ እንደዚህ የሚባል ሥም አዲስ አ'ባ ውስጥ ሰምተን አናውቅም።"

"ደመላሽን አናውቅም ካላችሁማ በአገሩ የላችሁም ማለት ነው።" ካሉ በኋላ ድንገት ሐሳባቸውን ቀይረው፤ "ለነገሩ አዲስ አ'ባ ዱር ነው። ስንቱ ይታወቃል? እኛም ሰውየው ከብዶ የታየን ገጠር ስለሆን ይሆናል።" ብለው የጸጉር ሻሻቸውን አጠባበቁ።

"ለመሆኑ ደመላሽ አንተነህ ማለት የዚህ አካባቢ ባለሥልጣን ነው?" ቢታኒያ ድምጿን ቀንሳ ጠየቀቻቸው።

"ኧረ ምኑ ታውቆ፣ ልጄ? ሲባል ነው የምንሰማ።" ድምጻቸውን ከእስካሁኑ የበለጠ ዝቅ አደረጉት፣ "የመጀመሪያ ሥሙ ሌላ ነው ይላሉ የሚያውቁት ሰዎች። ማእረጉም ኩርኔል ነዉ ይባላል። እና መንግሥቱ ኃይለማርያም ራሱ ነው እሱ ጠርቶ ሥሙን ቀይሮ ሹመት የሰጠው። 'ጎንደር አስቸግሮኛል፣ ሄደህ ደሜን መልስልኝ።ሌላ ሰው የለኝም፣ ደምመላሼ አንተነህ' ብሎ ላከው ይባላል። ይሄውላቸው ይጠፋ ይጠፋና በሦስት በአራት ወር አንዴ ብቅ ይላል። ምድር ትሸበራለች። የፈለገውን ሰው ብረ ፀን ገፎ፣ አስሮ፣ ገርፎ፣ ደብድቦ፣ ገድሎ...የፈለገውን ሰው ደግሞ አስታጥቆ፣ ሹሞ፣ ሸልሞ ይሄዳል።"

'ወ—ይ፣ አገሬ! ትክክለኛው ፖሊሳዊ መንግሥት ማለት ይህ ነው። ጠበንጃና ፖለቲካ ሲዋሃዱ... ማንም ባለጠበንጃ ብድግ ብሎ አገረ ገዥ የሚሆንበት...ፈላጭ ቆራጭነት እንደ መንጃ ፈቃድ ለጥቂቶች የሚታደልበት...ሲቪል ዜጋ መሆን ወንጀል መስሎ የሚታይበት...መንግሥት ለሚመራው ሕዝብ ጠበቃ ሳይሆን የደኅንነት ስጋቱ ምንጭ የሚሆንበት...' በጣም አዘንኩ።

"ሥልጣኑ የደርግ አባል ይሁን ሌላ ምንም ነገር አይታወቅም?" ቢታኒያ ሌላ ጥያቄ አነሳችላቸው።

"ሥልጣኑ ይህ ነው ተብሎ አይታወቅም፣ መምጫው ጊዜ አይታወቅ! ግማሹ ተነቃናቂ ደርግ ነው ይላል፣ ግማሹ ደግሞ ወታደር። መጀመሪያውኑ ማን ጠይቆት ብለሽ!? ይሄውላቸሁ፣ ቀን አገሩን ሲያሸብር ይውልና ማታ ጠጅ ቢጋን አስወርዶ ሲጠጣ ያመሻል። ዛሬም ከማን መሸታ ቤት እንደሚያመሽ አይታወቅም። እናንተን መኪና አምጡ ብሎ እንዳይተናኮላችሁ መኪናችሁን በማር አቁማዳ ሸፍኛታለሁ። እስረኛ ካለው ማድረሻ ብሎ የማንንም መኪና ይነጥቃል። ያን ያህልም ደግሞ አትስጉ! አንችም እርጉዝ መሆንሽ ጥሩ ነው። መቼስ ቆንጆ ሆኖ መገኘት አሁን አሁን ነገር በምን ይምጣብኝ ማለት አይደል? ወንዶቹ ስብሰባ ካልሄዳችሁ ከቤት አትውጡ።" ብለው ነጠላቸውን ደርበው ወደ ተጠራው ስብሰባ ሲሄዱ ከመኝታ ክፍላቸው ወጡ።

የምንሰማውን አምነን መቀበል ተቸግረን እርስ በእርሳችን ተያየን። ጭራሽ ይሄም አለ? መኪናችንን ግድ የለም። ቢታኒያን ቢነካ ግን ሞቴን የሚከለክለኝ ማንም ሊኖር አይችልም። ፍርሀት'ኮ ዋና ምንጩ ተፈጥሯዊ የመኖር ጉጉት ነው። በቃ፣ ይሄን ችላ ማለት ነው የጀግንነት መጀመሪያ። ጀግንነት ማለትም የውስጥ የፍትህ ስሜት ሞትን ቀላል አድርጎ ሲያሳይ ማለት ነው።

"እኔና ጀማል እዚህ ብንገኝ ጥሩ አይደለም። ዝም ብለን ዳር ቆመን ሰምተን እንምጣ። መቼም የምሽት

ስብሰባ ሊያመሽ አይችልም።" አልኳት ቢታኒያን በጣም ፈራ ተባ እያልኩ።

አስባበት ስላልነበረ ነው መሰለኝ ግራ ግብት አላት። መሄዳችንን አልወደደችውም። ቀርተን እዛ ፖሊስ ቢይዘን ደግሞ መዘዙ ብዙ ነው። በጣም የተገረምንበት ደግሞ ሲንሚሚ የነበረው መሸተኛ የአንዱም ድምጽ አይሰማም። ሁሉም ጥርግርግ ብሎ ሄዶ ቤቱ በአንዴ ጭር አለ። ሰውየው የዋዛ እንዳልሆነ አመለከቱን።

"እኔ...ሰሙዪ ምን ይሻለኛል?" ንጭንጭ ብላ ከቆየች በኋላ፣ "እሽ ቶሎ ደርሳችሁ ኑ!" እየጎመዘዛት ፈቀደችልን።

***

አስተናጋጃችንን በጥቂት ሜትሮች ራቅ ብለን እየተከተልን ሄድን።

እናቶች ነጠላቸውን ጣል አድርገው፣ ጎልማሶችና አዛውንቶች ጋቢያቸውን ደርበው፣ ወጣቶች ደግሞ የተጋጋለ ወሬ ይዘው የከተማው ነዋሪ ግልብጥ ብሎ ወጣ። ካፍያ መኖሩ የሚያተኩርብን ሰው እንዲቀንስ ያደረገው ይመስለኛል። የሚያፈጥብን ሰው አይታየኝም። ድቅስቁስ ባለና የእግር መተላለፊያ ብቻ ባለው ሰፈር ውስጥ ለውስጥ ሄደን ገበያ ከተባለው ቦታ ደረስን። ቀድሞ የደረሰው ሰው ሰልፈኛ መስሎ ቆሟል። ሁሉም ጀርባውን ሰጥቶን ወደ ፊት ለፊት አቅጣጫ ያያል። ብዙው ሰው የተቀመጠው በትልልቅ ድንጋዮች ላይ ስለሆነ ዕይታችንን ከለለው። በቁመት ከጀማል ስለምሻል ደጋግሜ አሰገኩ። ማየት አልቻልኩም። የእሱን ትከሻ ተንጠላጥዬ በጥፈሬ ቆሜ አንዴ ለማየት ሞከርኩ...

"ምንድነው ነገሩ?" የባሰ ግራ ገብቶኝ እንዲሁ ጠየኩ።

መደዳውን ተጠጋግተው የተደረደሩ ጭቃ ቤቶች ይታዩኛል። የሁሉም ቤቶች በሮችና መስኮቶች ተዘግተዋል። አንደኛው ቤት ተዛነብ ላይ አንድ ወጣት ከአንገቱ በላይ ታየኝ። በሁለት ታጣቂዎች መሀል ግድግዳውን ተደግፎ ቆሟል። እጆቹ የፊጥኝ የታሰሩ ይመስላል። ጉንጮቹ ላይ የሚያርፉ ዝንቦችን ጭንቅላቱን ወዲያና ወዲህ እያወዛወዘ ያባርራል። ገጹ ላይ ምንም የተለየ የመረበሽ ምልክት ማየት አልቻልኩም። ከእሱ ወደዚህ ከፍት በሆነች ቦታ ላይ ከብብ ብለው የቆሙ ሰዎች አሉ። በታጠቁ አጃቢዎች ተከበዋል። ብዙዎቹ በጋቢያቸው ላይ ወታደራዊ ፊልድ ጃኬቶችን ለብሰው ከዘራ ይዘዋል። የጦፈ ወሬ ይዘው ይሳሳቃሉ።

"ኧረ ምንድነው ነገሩ?" ምንም ነገር መገመት አልቻልኩም።

ጆሮዬን አጠገቤ ወደነበሩ ወጣቶች ጣል አደረኩ። አንዴ በሌላው ትከሻ ላይ ቆሞ ለሴኮንዶች ሲመለከት ቆየ። ወዲያው ዱብ ብሎ ወርዶ ያየውን ነገር ለጓደኞቹ ነገራቸው...

"ራሱ ደመላሽ ነው። የሚገደል ሰው አለ መሰለኝ። እጁ ታስሮ የቆመ ሰው አለ።" ጥድፍድፍ እያለ ነገራቸው።

እንደገና በጀማል ተከሻ ላይ ተንጠላጥዬ ተንጠራራሁ። አሁን ለውጥ አለ። ቀይ፣ በጣም ረጅም፣ ጸጉረ በርሀ፣ ወርቅ ጥርሱ የሚፈልቅ፣ ከዘራ የያዘና በጋቢው ላይ ጃኬት የደረበ ጎልማሳ ነው። ከሌሎቹ ነጠል ብሎ ወደ ሕዝቡ መጣ። በጩኸት መናገር ጀመረ። ከዘራውን አየር ላይ እያወናጨፈ...ጥርሶቹን እያንገጫገጨ...ወደ ጀርባው ወዲያው ወዲያው እየተገላመጠ...በኃይለኛ ስሜት ይናገራል። ከቃላት ያለፈ ትርጉም የሚሰጥ ነገር አልሰማ አለኝ፣ "ሌባ...መንደፈራ...ሐረርጌ...ጠበንጃ ሰርቆ..." የሚሉ ቃላት ብቻ ጆረዬ ደረሱ። ሁኔታው በጣም ያስፈራል። ጠበንጃ ግን አልያዘም።

'ደመላሽ አንተነህ ማለት ይሄ መሆን አለበት!'

ሌሎቹ ጓደኞቹ አሁን ጸበል ለመረጨት ከጳጳስ ፊት የቆሙ መስለው ተደርድረዋል። ሁሉም ጸጥ ብለው ይመለከቱታል። ሰውየው ድንገት ተወናጭፎ ወደ ጀርባው ዞር አለ። "ስቀለው፣ ይሄን ሌባ!" እስካሁን ባልነበረ ድምጽ ጮኸ። ታጣቂዎቹ መሀላቸው የነበረውን ወጣት እየገፉ ወደፊት አመጡት። የእግር ኳስ ግብ የመሰለ የመስቀያ ምሰሶ መኖሩን ያጤንኩት አሁን ነዉ። የሚንከባለል በርሚል ድምጽ ተሰማኝ። የሚሰቀለው ወጣት አሁን ከትከሻው በላይ ታየኝ። አንገቱን በኑጭ ገመድ ሸምቀቆ ውስጥ አስገብተውለት ታጣቂዎቹ ከበርሚሉ ወረዱ። በርሚሉን ገፋ ሲያደርጉት ወጣቱ በጩኸት የሆነ ነገር ተናገረ። በመጨረሻ እስትንፋሱ ነው የጮኸው። ጩኸቱን ተከትሎ የጀማል ፊት ልውጥውጥ አለ። በመሀሉ ጀማልን ምን እንዲህ እንዳስደነበረው አላውቅም።

"መጣ፣ አላሙሮ!" ብቻ ብሎኝ ከስሬ ሾልኮ በሕዝቡ መሀል እልም አለ።

ታጣቂዎቹ በርሚሉን በእግሮቻቸው ገፋ አደረጉት። ወጣቱ የተሰቀለበት ገመድ ብጥስ ብሎ ሲወድቅ ታየኝ። ወዲያው ደመላሽ አንተነህ ከጓደኞቹ መካከል ፈንጠር ብሎ ሲወጣ ጭንቅላቱ ይታየኛል። ወደ መስቀያው ቦታ ተንደረደረ። ዱ....................!! አየሩ ላይ የጭንቅላት ፍልጥላጮች የእሳት ፍንጣሪ መስለው ብትንትን አሉ።

ስብሰባው ተበተነ።

ዐይኖቼን እዚህና እዚያ እየወረወርኩ ጀማልን ፈለኩት። ዐይታየኝም። ሲጋት ገብቶኝ እንደቆምኩ ሕዝቡ ጥርግርግ ብሎ ሄዶ ጥቂት ሕጻናትና ወጣቶች አስከሬኑን ከበው ቆመው ታዩኝ። ጀማል ከዳር አጎንብሶ አስከሬኑን ለማየት ይታገላል። እኔም ሄጄ ለማየት የሆነ ደመነፍሳዊ ግፊት እያጣደፈ አንደረደረኝ። ስደርስ ሦስት ወጣቶች ባዩት ነገር ዝግንን ብሏቸው ቦታውን ሲለቁ ዕይታዬ ከፍትፍት አለልኝ።

በአፍጢሙ ተደፍቶ ጭንቅላቱ የፈረሰ ወጣት..አረንጓዴ ካኪ ሸሚዝና ቁምጣ ሱሪ...የቀኝ እግሩ አውራ ጣት በፋሻ ጨርቅ የተጠቀለለ...። ልቤ አንድ ነገር ጠረጠረ። ደነገጥኩ። ከግቡ ያልደረሰው የኛው የኢሕአፓ መልእክተኛ ነው! ራሱ ነው! እሱ ነው! ህሊናዬን ልስት ምንም አልቀረኝ!

ጀማል ከጎኔ መጥቶ እጄን ሲይዘኝ የደመላሽ እንተነህ መንፈስ ደርሶ ብጥብጥ አደረገኝ። በድንጋጤ በርግጌ አፈጠጥኩበት። ጀማል ከኔ በባሰ ሁኔታ ፊቱ ተረብሿል።

# 39

እንቅልፍ አልባው ሌሊት እንደምንም አለቀ።

የመልእክተኞችን ተደራ መዝገብ በምን ተዓምራዊ ግምገማሽ እንደተረዳሽው ብርቱ እንቆቅልሽ ሆነብን። ጀማል፡ ግጥሙ ንጉሡን ሲያጠልቁለት ተሰሊቶችን የጻደቡትን ምሥጢር ሲነግረኝ ደግሞ ሆድ ባሰኝ።

በአረብኛ "ራስኢ...ራስኢ...ዘበር...ዳኺል...ሱትራ..." እያለ ነበር የሚሸው። ጀማል ሲተረጉምልኝ እንደተረዳሁት "ገኝ ሰዎች ካላችሁ ስሙኝ! መሪአቱቁ ጃኬቴ ጀርባ ኪሲታዬ ውስጥ አለ" ነው ያለው። ለእኛ የተላለፈ የመጨረሻ ጉዳ መሆኑ ነው። በሌሊት ጃደን መቃብሩን የመቆፈር ሐሳብ ብልጭ ብሎልኝ ነበር። ምሽት ላይ በወሬ መሃል አንድ ነገር ስንቅር አደረኩ። አስተናጋጃችንን ሌላ ሽፋን ሰጥቼ ምን አይነ ሊኖር እንደሚችል ጠየኳቸው። በእሳት የመጫወት ዓይነት ድፍረት ነበር፤ ማጠየቁ በራሱ። የሰጡኝ ማልስ በረዶ ለቀቀብኝ...

"ነገ ሌሊት ተገርሰው የሚገኙት እምነት የዚህ ከተማ ሰዎች አሁን ከመሸ ከጎንደር መጥተዋል። ሌላም የዚህ አካባቢ ልምድ አለ። ዘመዶቻቸው የሞቱባቸው የአካባቢው ሰዎች ወረፋ ገብተው መቃብራቸውን ይጠብቁታል። ምክንያቱም ዕውጭ የሚባል ዕውሬ አለ፤ ትኩስ አስከሬን ቆፍሮ አውጥቶ የሚበላ። ሌሊቱን በሙሉ እሱን ሲጠብቁት ያድራሉ..."

ምንም ማድረግ አልቻልም። ይሄንን ቀን በቀስ ስንላመደው ደግሞ ሌላው ችግር ተተካ። የሌሊት ግድያ

ጥይት ድምጽ መፈንዳት ጀመረ። "አምስት ኢሕአሠ ወደሚንቀሳቀስበት ቆላማ ቀበሌ ሄዳችሁ ልብስ ሸጣችኋል ተብለው በሻለቃ መላኩ ሞት የተፈረደባቸው ምስኪን ልብስ ሰፊዎች የጎዳና ላይ ርሸና ነበር የተካሄደው!" ስቅጥጥ አለኝ።

***

በንጋት ተነስተን ፊታችንን ወደ መጣንበት አዞርን።

እንደጠረጠርኩት አስተናጋጆችን መልእከት ጫኑብን። አዲስ አበባ ለምትኖር እህታቸው ቅቤ፣ በርበሬና ማር ጫንኩላቸው። ከመጠን በላይ ደስተኛ ሆኑ። መኪናዋን እኔ እየነዳሁ በተከፈለ ልብ እብናትን ለቀቅን።

ስንመለስ መንገዱ የተሻለ ሆነልን። ቁልቁለትና ደልዳላ ቦታ ይበዛዋል። ቢታኒያ ከኋለኛው ወንበር እጥፍጥፍ ብላ ተኛች። ለአካል እረፍት ያህል ብቻ ነው የተጋደመችው። አዲስ ዘመንን አልፈን ወረታ ከተማ ስንደርስ ጀማልን ወደ አገሩ ሸኘነው። ከልብ ቅር የተሰኘንበት መለያየት ነበር። በታዘዝኩት መሠረት 40 ብር አውጥቼ ሰጠሁት።

"በጣ—ም ይወዶችኋል...! ዳህና ሁ——ኖ...ጀዛከ አላህ !!" ስብርብር ባለ አማርኛ ተሰናበተን።

ረፋድ ላይ ባህርዳር ገባን። እንደ ርችት የሚፈንዳዳ የፖለቲካ እሳተገሞራ ተቀበለን። የድምጽ ማጉያ ግምግምታ...የተቃውሞና የድጋፍ ሰልፍ...የሕዝብ ስብሰባ...የመፈከር ወጀብ...። "እናርኪስቷን ኢሕአፓን እንመነጥራለን!" "ሞት ለውስጥና ለውጭ የአብዮታችን ጠላቶች!" "እናሸንፋለን!" የአብዮት ጥበቃ አባላት ጀብ ጀብ...ፍተሻ...ምንጠራ...እሥራት...ዛቻ...እንደገና ስብሰባ።

ለሁሉም ነገር እንዲመቸን እዛው አውሮፕላን ማረፊያው አካባቢ እያልነሽ ሆቴል አልጋ ያዝን። ቢታኒያ ወደ አዲስ አበባ የምትመለሰው በአየር ነው። የፈለጉትን ይበሉ፣ የማይለወጥ ውሳኔዬ ነው። ገንዘቡን የማወጣው ከግል ኪሴ ነው። የተሻለ አልጋ አገኘን። ሙቀቱ እይጣል ነው። ሰውነታችን ተጣጥበን ጋደም አልን። እሷ ማስመሰያውን ስታወልቀው በጣም ቅልል አላት። የድሮዋና ጽጌረዳ አበባዋ ቢታኒያ መኮንን ተመልሳ ከች አለች።በትከከለኛው እርግዝናዋ ሳያት ሆዷ ላይ ንብ የነደፈው ዓይነት እበጥ ብሏል። ደስታዬ ግንፍል ብሎ በስስት ዐየኋት። ከዚህ የግርግር ማእበል ቶሎ እንድትሄድልኝ ፈለኩ...

"እናትየ፣ በጊዜ ሄጂ የአውሮፕላን ትኬት ልቁረጥልሽ። እረፍ ብለሽ ጠብቂኝ..." ተነሳሁ።

"በ---ል፣ አርፈህ ተቀመጥ፣ ሰሙዩ...እንዳንጣላ!" ፊቷ ልውጥውጥ ብሎ ባፈጠጠቻቸው ዐይኖቿ ገረፈችኝ።

ጉዱ ፈላ! "አብሬህ ጎንደር እሄዳለሁ..." ልትለኝ ነው። ሰማይና ምድር በአንዳች ገድል ቢጣበቁ እንኳን የማይሆን ሐሳብ ነው። ችግሩ ግን እንዴ ከአፏ ከወጣ ወጣ ነው። አሳምኖ ማስቀየሩ ዳገት ነው። ምኑ ሰይጣን ሹክ ብሏት እንዳደረ አልገባኝም። የድርጅት ተልእኮ መሆኑን በደንብ እያወቀች ነው የመጀመሪያውን እቅድ ለማስለወጥ የተነሳቸው። ብሞት ወደ ሻለቃ መላኩ ግዛት ይዣት አልሄድም። ግን እንዴት አድርጌ? በኃይለ-ቃል መከራከር አያዋጣም። እያሳዘኑ ማባባልን መረጥኩ...

"ቤቲዬ፣ ጎንደርም እሄዳለሁ እያልሽኝ ከሆነ አብረን ብንሄድ ደስ ይለኛል። ግን በችግር ላይ ችግር ብቻ ነው የምናተርፈው..." በደምፍላት አቋርጣኝ ብድግ አለች።

"እንጃባህ! እንጃባህ! ምርጊ! አትቅለስለስብኝ...አንድ ምክንያት ብሎ ነገር አልሰማም..." ጆሮዎቿን በእጇ ደፈነች።

በተስፋ መቁረጥ በረጅሙ ተንፍሼ እንደገና ኃደም አልኩ። አንድ በድንጋጤ ወከክ አድርጎ ወዲያውኑ እንድታምነኝ የሚያደርግ ምክንያት ማግኘት እንዳለብኝ ተሰማኝ። እንዳናግራት ግን አልፈለገችም። ፊቷን በትራሱ ሸፍና ዝም አለችኝ።ቀና ብላ እስከምትቀመጥልኝ ድረስ ጭንቅላቴን እያሠራሁ በትእግስት ጠበኳት። ከሴኮንዶች በኋላ ተቃንታ ወደ እኔ ዞር አለች...

"ቤቲዬ ስሚኝ፣ አብረሽኝ ጎንደር ከሄድሽ አለቀልኝ። 'ይሄ አንጀኛ ከሚስቱ ጋር ብራችንን ይዞ ወደ ሱዳን ሊጠፋ ሊሄድ ሲል አገኘነው' ብሎ የጎንደር ኢሕአፓ ኮሚቴ ወዲያውኑ እንደሚያስገድለኝ ምንም አትጠራጠሪ!"

የቢታኒያ ጠይም የፊት ገጽ ከመቅጽበት ዐመድ ለበሰ። ጨርሶ ባላሰበችው መንገድ ነው የሄድኩባት። ቅንድቦቿን በሽንፈት ስሜት ከስከስ አደረገቻቸው። ምክንያቴን የሚፈታተን ነገር ሳታመጣብኝ ሌላ የበለጠ የሚያሳምን ነገር መጨመር አለብኝ...

"ሆዴ፣ ልብ በይ...ፖሊት ቢሮው ወደ አብናት ስሄድ ስላይ መደበልኝ። ወደ ጎንደር ስሄድ ግን ይሄንን ሁሉ ገንዘብ ይዤ ስላይ አልመደበልኝም። ይሄ በድንገት የሆነ አይምሰልሽ። የጎንደር ታጣቂ ከንፍ ስለሚከታተለኝ ሆነ ብለው ያደረጉት ነው።" የስሜት ለውጧን ለመለካት ትኩር ብዬ ዓይኖቿን እየሁ።

በደንብ አሳምኛታለሁ።

በጸጥታ ተውጣ ግድግዳውን እንዲሁ ትመለከታለች። አሁን የአየር ትኬቷን መቁረጥ እችላለሁ። ቱታዋን ለብሼ፣ መታወቂያዋንና ገንዘብ ይገኙ ስወጣ ከንፈሯን ሳምኳት። "የት ነህ?" አላለችኝም። የአየር ትኬት ቢሮው እዛው አሊጋ ከያዝንበት ፊት ለፊት ነው። ወረፋ ግጥም ብሎ ጠበቀኝ። እንደምንም ተንኳትቼ ተራዬ ደረሰ። ዛሬ ምሽት ወይም በማግስቱ ለመብረር ወንበር የለም። ከሁለት ቀን በኋላ ረፋድ ላይ በመከራ አንድ ወንበር ተገኝቶ ቆረጥኩላት። ተመልሼ ስሄድ ቀዝቃዛ ሌ፣ ባበል አደረገችልኝ። እንደዚህ ቀን ተጨንቃ ዐይቻት አላውቅም። በሞት ምክንያት የምንለያይ ያህል ትክ---ዝ አለች። የማይቻል ሆኖ እንጂ ስቃዬ እኩል እኔንም ተሰምቶኛል። ምሳችንን ስንበላ ትንሽ መለስ ብሎላት ወሬ ጀመርን...

"እስቲ አሁን እዛ ብቻዬን እንዴት አባቴ ነው ቀኑ የሚሄደው? በዚህ ላይ 'አዲስ ሥራ ላይ ትመደቢያለሽ' ብለውኛል። በዚህ ቀውጢ ጊዜ አንድ ቀንም ቢሆን ያላንተ ምኑን ከምን እንደማደርገው አላውቅም።" መሬቱ ላይ አቀረቀረች።

"ምን ዓይነት ሥራ? ይሄ ታጣቂ ከነፍ ምናምን የሚሉት እቃ እቃ ጨዋታ እንዳይሆን ብቻ..." ስጋት አጣደፈኝ።

"እ---ይ፣ አይደለም። የአዲስ አ'ባ ቀጠና አንድ ነው መሰለኝ ኮሚቴ ጸሐፊው እንጃውን ተቀላቅሏል። እና ከሌሎች ስድስት ሰዎች ጋር ከኮሚቴው አግደውታል። ቦታው ክፍት ሲሆን ጊዜ በጊዜያዊነት እዛ ትቆያለሽ ብላኛለች፣ ጓዲቷ።"

ቅፍፍ አለኝ። የምትነግረኝ ስለ አብዩ ኤርሳሞ ነው። ብርሃነመስቀልን ደግፎ "አጥቅቶ የመከላከል" ሥልትን በጥብቅ ተቃውሟል። ከሰንዳፋ የተዘረፊውን መሣሪያ ያስረከብኩት እኔ ነኝ። ተቀብሎ ሊታጣቂ ከንፉ ሳያስረከብ ቆሞ አድርጎት ተገኘ። አስረክብ ሲባል ደግሞ ይዞት ጠፋ። ይህ ቀጠና እጅግ አስቸጋሪ ቦታ ነው። ሆን አንድ ማለት የእሷ መኖሪያ ቤት፣ ጋራገዶና የዓድር ቤታችን የኢሕአፓ መዝገብ ቤትና የማንኙነት ማእከል የሚገኝበት መሳለሚያ አካባቢ ነው። በጣም በርካታ አባላት ብቻ ሳይሆን የድርጅቱ ንብረት የሚገኝበትም ቦታ ነው።

'ምን ይሻለኛል?' ጭንቅ ጥብብ አለኝ።

ቀጠና አንድ በአንድ በኩል ኢሕአፓ እንጃውን የሚታገልበት ቀበና መሆኑ የባሰ አደገኛ ያደርገዋል። በአባሎቻችን መካከል መጠቋቆምና ማስያዝ የተጀመረውም እዚሁ ነው። በሌላ በኩል የደርግ/መኢሶን

ትኩረት ያረፈበት አካባቢ ነው። የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎችን ቀድመው ያዋቀሩትና ተከታታይ ሥልጠና መስጠት የጀመሩትም እዚህ ነው። የተበጣጠሰውን መስመር መቀጠል ራሱ ከባድ ሥራ ነው። ሙሴ ባልዲ የሚመራው ግብረኃይል ያለበት ከፍተኛ መሆኑ ነው። በአመራር ቦታችን ምክንያት ብዙም ተሳትፎ አልነበረንም። ለጥርጣሬ ብዙም ያልተጋለጥነው ለዚህ ነው። አሁን ግን ዓይን የሚጋብዝ መንከልከል ሊበዛ ነው። የማማከራት ነገር አልም ብሎ ጠፋብኝ። ዝምብዬ ሳያት ቆይቼ አደጋውን የበለጠ ለመመዘን ሞከርኩ...

"ማርየ፣ ለነገሩ አሁንኮ ድርጅታችን አዲስ አ'ባ ውስጥ ሽባ ሆኗል። በተለይ የፖለቲካና የርእዩተዓለም ሥራው ዜሮ ሆኗል። እንዲያውም 'ኢሕአፓ እውነት አለ ወይስ የለም?' የሚል ጥያቄም እየተነሳ ነው። የድሮውን ያህል ውጣውረድ የሚኖር አይመስለኝም።" ራሴን ለማጽናናትም ጭምር ውስጤ በተቃራኒው እየታገለኝ ላቃልለው ሞከርኩ።

"ጥያቄውንማ፣ ሰሙዬ አይተኸው የለ፣ በቀደምለት? የብዙ አባል እየጨመረ የመጣው ጥያቄ 'መገዳደሉን ማን ነው የጀመረው?' የሚል ነው። ትክት ብሎ የታከተኝ ጥያቄ ነው። አሁን አሁን ደግሞ የደርግ ፕሮፓጋንዳ እየሠራ መጣ መሰለኝ፣ ጥያቄው ከድርጅት ወጥቶ ወደ ሕዝቡ ገብቷል። የአብናቷ ባለጠጅ ቤት ሳይቀር አንተ ከሊኒኩን ለማየት የወጣህ ጊዜ ይህንኑ ሲነግሩኝ ነበር። 'እነዚህ ኢሕአፓ የሚባሉ ወይ ሙትተው ላያደሙ የድሀውን ልጅ አስጨረሱት' ብለው ምርር አሉ..."

ሁለታችንም ፈገግ የምንልበት ጥርስ አልነበረንም። አእምሮዬ እዚያና እዚህ ሲረግጥ ቆይቶ ወደ ጥያቄው ተመለሰ። "መገዳደሉን ማን ጀመረው?" አባሎቻችንም ሕዝቡም ተጠያቂውን ለይቶ ለማውጣት በቂ መልስ ይፈልጋሉ። ከሁሉም የሚያሳስበው ግን ታሪክ እንዴት እንደሚመዘግበው መጨነቁ አይቀርም። ሐሳብ ለማሰባሰብ ያህል ለአፍታ አረፍ ብዬ ወደ ቢታኒያ ዞርኩ...

"ጥያቄው በጣም አስጠሊታ ነው። መልሱ ግን ሊሰጥ ይገባል። ትዝ ይልሽ እንደሆን የፖሊት ቢሮው ድርሳን ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ ያደረገው ደርግ/መኢሶንን ነው። እነርሱ ደግሞ እኛን ይሉናል። በበኩሌ የምቀበለው ክርክር አይደለም። ይሄ ድንጋዩ ነው ውኃውን የሚያስጮኸው ወይስ ውኃው ነው ድንጋዩን የሚያስጮኸው... ዓይነት ሙግት ነው..." ስላት አቋረጠችኝ።

"ሰሙዬ፣ አንዱ ወገን ጀማሪ መሆን አለበት ብዬ ነው እኔ የማምነው። ዲያሌክቲካል ማቴሪያሊዝም የሚለውም ቢሆን'ኮ ይህንኑ ነው። አንድ ጀማሪ ድርጊት ይኖራል፣ ድርጊቱ ሌላ ግብረ-መልስ ድርጊት ያስከትላል። ሁለቱ ሊነጣጠሉ አይችሉም ወይም ሁለቱም በአንዴ ጀማሪ ሊሆኑ አይችሉም። አንደኛው

ተጠያቂ የማይሆን ከሆነ ለእርምት እንቅስቃሴም አመች አይሆንም። እኛ ነን ጀማሪዎቹ ካልን ደግሞ ነገሩ የበለጠ ይወሳሰባል። አይመስልህም?" ጸጉሬን እየደባበሰች ጠየቀችኝ።

"አይመስለኝም፣ ቤቲዬ። ለምን መሰለሽ? ሦስት ምክንያቶች ልስጥሽ። ሲጀምር ጥያቄው ከመገዳደሉ ጀርባ ያሉ ጥልቅና ውስብስብ የሥነልቦናና የፖለቲካ ሰሮችን የዘነጋ ግልብ ጥያቄ ነው። የትም ቦታ ብትሄጅ የፖለቲካ ግጭት ቅልብጭ ተደርጎ የሚገለጽ ሂሳባዊ ቀመር አይደለም። መነሻውንና መድረሻውን በቀላሉ ለመለየት የሚያስቸግር ሂደት ነው። የፖለቲካ መገዳደል እንደኳስ ጨዋታ ግጥሚያ በፊሽካና በአንድ ቡድን የሚጀመር ሜካኒካል ድርጊት አይደለም። ማለቴ ጥይት ከመተኮሱ በፊት ምላጭ መሳብን የሚገፋፋ የሥነልቦና ሁኔታ መኖር አለበት። ይህ ነው መገዳደል የሚጀምርበት ቦታ። እና ይህ ከእኛ ወይስ ከደርግ ጋር ነው የነበረው?"

"እ—ሽ ሰሙ ሆዬ፣ አሁን ጥሩ መጣህ። ሁለተኛውን ምክንያት ንገረኝ..." ፍላጎቷ ብድግ አለ።ወደ ሁለተኛው ምክንያቴ አለፍኩ...

"ሌላው መገዳደሉ ርእዩተአለማዊ ማብራሪያ የሌለው መሆኑ ነው። ይህ 'ማን ጀመረው?' የሚለውን ጥያቄ መልስ ከባድ ያደርገዋል። እኛም ሆን ደርግና መኢሶን ስንፈጠር አንድ የጋራ አዝማሚያ ይዘን ነው የተፈጠርነው። ሦስታችንም ማሌዎች ነን አልን። እና አብዮታዊ ለውጥን ኃይል ከመጠቀም ውጭ አስበነው አናውቅም። ሦስታችንም 'ሥልጣን ከአፈሙዝ ይመነጫል' ብለን የምናምን ማአይስቶች ነን። እንደኛችን ሌላውን "ጸረ-አብዮት" ስለምንል ኃይል የመጠቀም መብት የኔ ነው ማለታችን አይቀርም። ስለዚህ 'መገዳደሉን ማን ጀመረው?' ከሚለው ጥያቄ በፊት 'መገዳደሉን ማን ነዉ ርእዩተዓለማዊ መልክ የሰጠው?' የሚለው ጥያቄ መመለስ አለበት። እየተረዳሽኝ ነው?"

"በጣ—ም! ቀጥልልኝ፣ ቀጥል"

"ሦስተኛው ከመገዳደሉ ጀርባ ያሉ እሴቶች ናቸው። ትዝ ይልሽ እንደሆነ ወይዘሮ ማስተዋል 'በአሁኑ ጊዜ ሰው መግደልን ኃጢያት የሚያደርግ ፈሪሀ እግዚአብሔር መጥፋቱ ነው ደም እያፋሰሰ ያለው' ብለውናል። እኛም ሆን ደርግ ማርክሲስቶች ነን ስለምንል የቆዩ የሕዝቡን ጥሩ ጥሩ እሴቶች ከደናል። መኢሶንና ሌሎቹም እንደዚያው። በብርሃነመስቀል አነጋገር ደግሞ 'ማርክሲዝም ሌኒንዝም በደንብ ያልገባው ኃይል ቀድሞ የሚተኩሰው እሱ ነው።' ያ ኃይል ማለት እኛ ነን፣ ደርግ ወይስ መኢሶን? እኛና መኢሶን ከተማሪዎች ንቅናቄ የወረስነው ጀብደኝነትና ደመፍሉነት አለብን። ደርግ ደግሞ ሲፈጥረው ጠበንጃ አምላኪ ኃይል ነው። ስለዚህ ማን ይጠየቅ? እኔ የሚመስለኝ ተጠያቂው ትውልዱ ነው።"

"ወ—ይ ጣ—ጣ! ሜካኒካል አይደለም አልኩ!?" ስትል ወደ ማጠቃለያዬ መጣሁ።

"እና ፍቅሬ ምን መሰለሽ? በእኛ ድርጅት እርምት ከተደረገ አይቀር አንድ መታመን ያለበት ነገር አለ።ወደድንም ጠላንም ከወንጀሉ እናመልጥም። መጉዳደሉን የተሟላ ቅርጽ በመስጠት ትልቅ ስህተት ሠርተናል። ቀጥሎ ግለሰቦች መጠየቅ አለባቸው። ከእኛ በኩል ዘርዑ ከሕሸን፣ ዶክተር ተሰፋዬ ደበሳይና ከፍሉ ታደሰ ሕዝብን ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው። ደርግና መኢሶን ደግሞ ለፍርድ መቅረብ አለባቸው። በተለይ ኮሎኔል መንግሥቱና ኃይሌ ፊዳ!"

ምሽት ላይ ከአልጋ ከፍላችን ወጣን። በግድ ልብሴን አስቀይራ ጅንስ አስለብሳኛለች። ፍቅር ከጀመርን ለመጀመሪያ ጊዜ በሙሉ ነጻነት ተቃቅፈን ረጅም ጎዳና ላይ በዝግታ ተራመድን። በእውነት የማይጠገብ ገጠመኝ ሆነብን። መሸትሸት ሲል ደግሞ ስልክ ቤት ሄድን። እሷ ለአበበች፤ እኔ ለተሰፋዬ ደበሳይ ደወልን። አበበች ቁርጥ ያለ ቃል ነገራቻት።

"በተቻለ ፍጥነት ወደ አዲስ አበባ እንድትመጭ!"

ቢታኒያን በሦስተኛው ቀን ስሸኛት እንባዋ ይወርድ ነበር። አውሮፕላኑ መሬት ሲለቅ ደግሞ የእኔ እንባ ፈሰሰ...

***

ነጋጅ በሌሊት ቀድቼ ወደ ጎንደር ነዳሁ።

ቢታኒያን ለሴኮንድ ከአእምሮዬ ማውጣት ቸገረኝ። ልቤ እየተንተተ ረጅሙን መንገድ አቋራረጥኩት። ጎንደር ከአዲስ አበባ የተሻለ ሆኖ አይታየኝም። ሻለቃ መላኩ ከሳምንታት በፊት ከተሞከረበት ግድያ አምልጧል። የበቀል ሰይፉን ግን ከዚያ ቀደም ብሎ መዞ ጎንደርን በደም አበላ ማጠብ ጀምሯል። አሁን የበለጠ እንደሚከፋ አጠብቃለሁ። ማክሰኝት ከምትባል ትንሽ ከተማ ስደርስ የዞኑን የኢሕአፓ ኮሚቴ ጸሐፊ አገኘሁት። ዶክተር ተሰፋዬ ቀደም ብሎ ስለደወለለት አሳቻ ቦታ ቆሞ እየጠበቀኝ ነበር። ቁርጥ አናጺ ሆኗል፣ በአለባበሱና በያዛቸው ቁሳቁስ።

'አይ፣ ድርጅቴ ኢሕአፓ! ሕዝባዊ ጦርነቱ ተረስቶ እንደ አይጥ መሹለክለክ ብቻ!' ንዴቴ ግንፍል ሲል መልሼ እንቅ አደረኩት።

"እህ፣ ጓዱ_ጎንደር እንዴት ናት?" መግቢያ ለመስጠት ያህል ጥያቄ አነሳሁለት።

"የጎንደርን ነገር ተወው ባከህ! የአስከሬን አውድማ ሆናለች። ሻለቃ መላኩ ባልተወለደ አንጀቱ እየመተረን ነው።"

"በየቦታው ብዙ መላኩዎች ተፈጥረዋል...ብዙም አይግረምህ" አለመደነቁን ልገልጽለት ሞከርኩ።

"ኖ ኖ! የጎንደሩ ይለያል፤ እመነኝ። የሚገርምህ መላኩ የደብረታቦር አካባቢ ሰው ነው። አንድ ደጃዝማች አጎቱን የአውራጃው አስተዳዳሪ አድርጓቸዋል። ደብረታቦር ከተማ ላይ አንድም የተገደለ የኛ አባል የለም። እየተጨፈጨፈ ያለ እዚህ ያለው ወጣት ነው። ሲጨንቀን የተጋለጡ አባሎቻችንን ወደዚያው ወደ ደብረታቦር እየላከናቸው ነው። ኢሕአሠን መድረስ የተቸገሩትን ማለቴ ነው።" ቁጭት ብክንክን አደረገው።

የምሰጠው አስተያየት የለኝም። ፈረንጆች እንደሚሉት መስታወት ቤት ውስጥ የተቀመጠ ሰው ጠጠር ለመወርወር የመጀመርያ መሆን የለበትም። የነሐሴው መዘዘኛ የማእከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ እንደተሳለ ቢላዋ መልሶ መታረጃችን ሆኗል። ወ---ይ ጉድ! ጎንደር የነገሥታት አገር... የአርባ አራቱ ታቦታት መቀመጫ... የፋሲል ግንብ ባለቤት...የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ ድርሳን...። ጎንደር ከተማ ከአክሱም ዘመን የከፋ እያሌ ጦርነቶችን አሳልፋለች። ብዙ ግፍና የእርስ በእርስ ደም መፋሰስ ዐይታለች። ነገሥታትና መሣፍንት...መሣፍንትና መሣፍንት...ነገሥታትና ሕዝብ...የቅብዐትና የጸጋ እምነቶች... ድርቡሽና አገሬው...ተራኩተውባታል። በዚህ በ21ኛው ክፍለዘመን ግን እረፍት ማግኘት ነበረባት። አልተሳካላትም። ሻለቃ መላኩን የመሰለ ችኩል፣ ጥራዝ ነጠቅ፣ ቀልቃላ፣ የደም ጥማቱ የማይረካ... ገዥ ጣለባት። የት ይደርሳሉ የተባሉ ለግላጋና ወጣት ልጆቿ እየተቀጠፉባት ነው። ደርግና ኢሕአፓ ወፍጮና መጅ...ምረድና ካራ...ጦርና እንጨት ሆነው እያደቀቋቸው ነው። ሆዴን ከፋው።

"ወደ እምባጊዮርጊስ ያለው መንገድ እንዴት ነው?" ወደ ራሴ ጉዳይ ተመለሼ ጠየኩት።

"እስካሁን ምንም ችግር የለም። ከሁለት ሳምንት በፊት እንደዚህ በኢዲዩ ተወራ ነበር። አሁን ደርግ መልሶ ከጁ አስገብቷታል። ምንም ስጋት የለም።" ብሎ ለዘርዐ የሚላክ በካኪ ፖስታ የታሸገ የወረቀት መልእክት ሰጠኝ።

ቸቸላ ሆስፒታሉ አካባቢ ስንደርስ ወረደ። እኔ ወደ መሀል ከተማው ገባሁ። አጼ ፋሲል ትምህርት ቤት አካባቢ ተጥሉ የነበረ አስከሬን ሲነሳ ዐይቼ ምንም አለመደንገጤ አስገረመኝ። መከራም ለካ ይለመዳል! ፒያሳም እንዲሁ አስከሬኖች ተነስተው ፖሊሶችና የአብዮት ጥበቃ አባላት ወደየሥራቸው እየሄዱ ነው። ብልኮ ስደርስ ለእፍታ እረፍ ማለት አሰኘኝ። የተለየ ፍላጎት የለኝም። ለቢታኒያ ስልክ የመደወል ግፊት

ነው ያስቆመኝ። ሄጄ እዛው አካባቢ ወደነበረ ስልክ ቤት ገባሁ። ተመዝግቤ ግማሽ ያህል ሰዓት ጠብቄ ኦፕሬተሯ መነጋገሪያ ክፍል እንድገባ ነገረችኝ። መነጋገሪያውን አንስቼ ሀሎ! ስል ለዓመታት የተለየኝት የመሰለኝ ቢታኒያ ድምጿ ጆሮዬ ደረሰ...

"ሰሙ ... ዬ፣ ፍቅ ሬ...ሙቹ ነው የምትመጣል...ኝ፣ ሆድዬ?" ድምጿን የለቅሶ ሳግ ተፈታተነው።

"...በሰላም ገባሽል...ኝ?" የኔም ድምጽ እየረገረገ ጠየቅኳት፣

"አልቆይም፣ ቶሎ እመጣልሻለሁ..." የሚቀጥለውን ለመናገር ልሳኔ ዝግት አለብኝ።

ብዙ መነጋገር አልቻልንም። ኦፕሬተሯ በትዝብት ፈገግ እስከምትል ድረስ ተነፋፍቀናል። እምባጊዮርጊስ ስደርስ እንደምደውልላት አስቤ ተለያየን። ስለቢታኒያ እያብሰለሰልኩ ጉዞዬን ቀጠልኩ። 'እስካሁን በሕይወት መኖራችን ትልቅ እድል ነው። ወደፊት ምን እንደሚመጣ ዐላውቅም። ድርጊት የአገሩን ወግ ከጠበቁ ነፍሰጡር መሆኗ አንድ የደኅንነት ዋስትና ነው። ፍቅረኛዬና ልጄ ከተረፉልኝ የእኔው ችግር የለውም። ብቻ አሟሟቴ ሸዋዬ እንዳለችው ይሁን። "የውሻ ሞት እንሞትም!"

እርባ ኪሎሜትሩን የጠጠር መንገድ ጨርሼ እምባጊዮርጊስ ከተማ ገባሁ። መንደር ብትባል ይቀላል። አጥንት የሚሰነጥቅ ብርድ...የእቧራ ማእበል...ጭንቅንቅ ብለው የተሠሩ ጭቃ ቤቶች...ለጥ ያለ ሜዳ። ከተማዋን አቋርጬ ልክ እንደተነገረኝ ወደ አስመራ መውጫ በኩል ሄድኩና ቡና ቤት መኝታ ያዝኩ። ምሳ ለመቀማመስና በዚያውም ለቢታኒያ ለመደወል ከተማ ወጣሁ። አስተውዬ ስመለከት የኢዴዩ ጦር ከተማዋን ምስቅልቅሏን አውጥቷታል። ስልክ የለ ምን የለ። በተለይ ስልክ አለመኖሩ አስደነገጠኝ። ወደ ጎንደር ልመለስ አልችልም።

'ምን ዓይነት ጣጣ ነው፣ ባካችሁ?' ባንዴ ምርር አለኝ።

የከተማዋ አብዛኞዎቹ የእህል ወፍጮዎች እልጋ በያዝኩበት አካባቢ ናቸው። ሥራ ላለመፍታት ከባለቤቶቹ ጋረ ተነጋግሬ አንድ የተበላሸ ወፍጮ ጥገና ጀመርኩ። ጨርሼ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ሥራ አስጀመርኩት። 35 ብር አስከፈልኳቸው። ወዲያው እምባጊዩርጊስ ማርያም ደብር ቤተክርስቲያን ጀርባ ጎራ አልኩና እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ጠበኩ። ዘርው ሳይመጣ ቀረ። በማግስቱም እንደዚያው። ከሦስተኛው ቀን በኋላ የቢታኒያ ናፍቆት ይጠብሰኝ ገባ። በዐይኔ ላይ መመላለስ ጀምራ እለቅህ አለችኝ፣ መለማመድ ተሳነኝ። አራት...አምስት...ስድስት...ሰባት...። ቀናቱ እንደቅንበርስ ተንተቱብኝ።ምንም ማድረግ አልችል ብዬ አስረኛ ሆኜ ቁጭ አልኩ!

"ቤቡላት እጅ ሊያስገድሉን ይፈልጋሉ" የሚለው ጥርጣሬዬ ዳግም ተመለሰ። ደግነቱ ዘርዐ ከሕሸን በአሥራ ሁለተኛው ቀን ከአምስት የኢሕአሠ ጓዶች ጋር መጣ። በደንብ ተመሳስለዋል። ዘርዑማ ጭራሽ የተመቸው የገጠር ባላባት መስሏል። ቁመቱ የበለጠ የረዘመ መሰለኝ። ሁለታችንም ጥድፊያ ላይ መሆናችንን ተረድተናል። መልእክቱን አስረከቢው አንድም ትርፍ ቃል ሳልተነፍስ ወደ ጎንደር ጥር እልኩ...

ምናልባትም ከዘርዑ ጋር ከዚህ በኋላ በዐይነ ሥጋ እንገናኝ ይሆናል። አልከፋኝም።

# 40

ተመልሼ ጎንደር ስገባ አስር ሰዓት ሆኗል።

ለአንድ ደቂቃ እንኳን መቆየት አልፈለኩም። በከተማዋ ሰማይ ላይ የነገሰው መልአከሞት ጨርሶ ሰላም አይሰጥም። ብልኮ አደባባይ ስደርስ አስደንጋጭ ትእይንት ገጠመኝ። የእናቱን ዘንቢል ይዞ ከጀርባዋ ኩስ ኩስ እያለ ወደ ገበያ ይሄድ የነበረ የአሥራ አራት ዓመት ልጅ ነው። እሱም ሆነች እናቱ ነጻ እርምጃ መጀመሩን አላወቁም። ከቅርብ ርቀት ጸጥታ ሠራተኞች በተኮሱት ጥይት ተገድሏል። እናቱ ኡኡኡ... ትላለች። ገዳዮቹ መጥተው ግንባሯ ላይ አፈሙዝ ደግነው ዝም አሰኟት። አስከሬኑን ቢጋሪ ይዛ ወደ ቤቷ ውልቅ አለች። ፍጥነቴን ጨመርኩ። አዘዞ ስደርስ ትንሽ ቅልል አለኝ።

ስልክ ቤት ባጋጣሚ መንገድ ላይ ሳይ ለቤቲ መደወል አማረኝ።

ስልክ ቤቱ ውስጥ ከሁለት አሮጊቶች በስተቀር ሰው የለም። ስልኩ የተበላሸ ሁሉ መስሎኝ ነበር። ቀይ፣ ቀፍራምና በሰል ያለች ኦፕሬተር ተቀበለችኝ። ስልክ ቁጥር ስጥቻት ብዙም ሳልጠብቅ እየጠራ መሆኑን ነገረችኝ። ቀልጠፍ ብዬ ሄጄ የመነጋገሪያ እጀታውን እየተንደፋደፍኩ ሰፍ ብዬ አነሳሁት። ስልኩ ይጠራል፤ የቢታኒያ ድምጽ ግን የለም። 'የት ሄዳ ነው?' ፍርሀት መገጣጠሚያዎቼን ሊያንዘራቸው ዳር ዳር አለኝ።አስራ አምስት ደቂቃ ያህል ቆይቼ እንደገና ሞከረችልኝ። ለውጥ የለም። ፊቴ ሲለዋወጥ ታዘበች መሰለኝ ኦፕሬተሯ ልታረጋጋኝ ሞከረች...

"አንድም ወጣ ብላ ይሆናል። ወይም አልፎ አልፎ ስልኩ እየጠራ ድምጹ ግን የማይሰማበት ጊዜ አለ። ያም ሊሆን ይችላል።"

በኀማሽ ልቤ ብቻ ነው የሰማኋት። የስልኩ ችግር ከሆነ እድለኛ ነኝ። ነገር ግን ይህ የመሆን እድሉ ጠቦ ጠቦ ታየኝ። ባህርዳር ስደርስ መደወልን መፍትሄ አደረኩት። ሁለቱንም ችግር የሚፈታልኝ መስሎ ተሰማኝ። በተከፈለ ልብ መኪናዬን እስነስቼ መንዳት ቀጠልኩ። ቢታኒያ ፍቅሬ! ወደ መቶ ሐምሳ ኪሎሜትር ሰኮዳ ለሰከንድ ከአእምሮዬ ላወጣት አልቻልኩም። ባህርዳር እንዳች ዓይነት ተዐምራዊ መፍትሄ እንደሚፈጠኝ ብቻ ደጋግሜ ዐስባለሁ። እየመሸ ስለነበር እንደደረስኩ ቀድሜ ባገኘሁት ሆቴል አልጋ ያዝኩ። በጣም ከመጣደፌ የተነሳ መኪናዋን ይዤ ነው ወደ ስልክ ቤት የሄድኩት። እስከ ምሽቱ 2:00 እንደሚሠራ ዐውቃለሁ። አንድ ሰዓት ሲል ደርሼ ተመዘገብኩ። ከግማሽ ሰዓት በኋላ መነጋገሪያ ከፍል ግባ ተባልኩ።

'ኧረ የቶር ወሬ ያለህ!' ትንፋሼ ቁርጥርጥ አለብኝ።

ስልኩ ይጠራል! ነገር ግን አሁንም መልስ የለም። አሁን ጉልበቴ መንቀጥቀጥ ጀመረ። አንድም በጎ ነገር አልታይህ አለኝ። ቢቃ፣ በመከራ ያቆየኋትን ፍቅረኛዬን አስገድለውብኛል! ተስፋዬ አልም ድርግም አለ። ኦፕሬተሮቹ እስከሚወጡ ደጋግሜ ሞከርኩ። የቢታኒያ ድምጽ ምጽዐት ሆነብኝ። ከአንዱ ጥሪ ወደ ሌላው ጥሪ እየተረበሽኩ መሄዴን ያየች አንዷ ኦፕሬተር መከረችኝች።

"ስልክ ደውሎ የፈለጉትን ሰው ማግኘት'ኮ ሁሌ የሚሳካ ነገር አይደለም..." ምክሯ እውነት ነው። እምነ የምቀበልበት ሀሊናና ዝግጁነት ግን የለኝም። ዘግተው ሊወጡ እስከሚነሱ ስልክ ቤቱን አለቀኩም። የመከረችኝ ኦፕሬተር ሁኔታዬ ሳያሳዝናት አልቀረም። በመስኮቱ በኩል በእጇ ጠቀሰችኝ...

"የት ነው አልጋ የያዝከው?"

"ገዳም ሆቴል...ገዳም...አዎ፣ ገዳም ሆቴል ነው።" እርብትብት አልኩ።

በአንዴ ዐወቀችው። ዞር ብላ ስልክ ደወለች። ለአንድ ሁለት ደቂቃዎች አነጋግራ ወደ እኔ ዞረች። "ቢታኒያ ቀርባለች!" ብላ እንድታበስረኝ ተመኘሁ። ምኞቴ አልያዘልኝም። የሆቴሉ ባለቤቶች ሁለት ብር ከፍያቸው የፈለኩትን ሰው እስከማገኘው ድረስ መሞከር እንዲፈቅዱልኝ እንደነገረችልኝ ነገረችኝ። ከልብ አመሰግኛት ወጣሁ። ረጅሙ ሌሊት ቢያንስ በሙከራ የሚያልፍ መሆኑ ትንሽ ተስፋ ሰጠኝ።

ወደ አልጋዬ በረርኩ። ሆቴሉ ውስጥ እስከምሽቱ አምስት ሰዓት ድረስ በየአሥራ አምስቱ ደቂቃ ሞከርኩ። ምንም ነገር የለም።

ብቻ፡ ፍቅረኛሁ ወደ ሰተምራቸው ወይ ተብሎሃቸው፡ ለማንን እንደምትመልሰው ጨንቆኛል።

ከአምነቱ ሰዓት በኋላ በለኒቱ ይሉኝታቸው ሲሰፋ፡ በተዋት ሁኔታው ከዚህ ያለፈ እንደምትይፈቅሁላቸው ሲነግሩኝ ተቀብለኛቸዋለ። ትንሽ ቆይተው ደግሞ በእሱነ ጭምር ቆሳሬው ገበያው ተኑ። መብኝት ይቅርና መንገዱም እንኳን የሚታሰብ ቅዥት አይደለም። ቢታይ በጨለማ ፓኪንግ እጅ ገቡት ትታየናለች። ከዕርስኩ መሀል ቢታዩቅ ሴሳ ዘዴ ይፈልጋሉ። የሆምበል ጫማውን በርገራ ያመጣሉ። ይነበንበባታል። እልልልል… የግብር ድምጿ መጣብኝ፡ እንዴት ልረፍ?

ጊዜ ከእሱ ጋር እሰህ ገናም እንደዚህ ቀን ቢሊዮን አሳልቶብናልም ወይም አንተዋዋኝ አይመቅም። ቢቻ፡ ሰዓቱ ፊስ እንደምሄው ገድቤ ቀን ብሎ ተንተረ። ያለምንም ሥራ ብዙ በረንዳው እየመጣሁ። ትንሽ ቆይቼ ተመልሼ እየገባሁ። ሲሊሴ ንትንቶ አይፈልም። ከ10–30 ሰዓት ድግሞ ከተማ መሐሪ በእግሮም ይሁን በተሽከርካሪ መንቀሳቀስ አይቻልም። የት ያለሁ ጊዜ እንደሆንኩ አላውቅም። ስለዚ፡ ሰውነቴ፡ ለንበረከክ፡ ሰፊም ቅዳሜ በመስኮ ሰሚና ድምጽ ሰማሁ…

እ—ዩ—ዩ! ከእሱ ከፍሌ ወተቴ ሄደ ምግር አለብህ።

የሆቴሉን ግቢ ሰፊት ስጋረመቅ የተኖሬሽ ያለሁ ነው የተሰበሰቡ። ገና እሱ መቅረጽ ነው። የሪሳ ጉዳይ፡ ቢታንያን የበላ ጅብ ይብላኝ። የኢፎሰ አባቱን መኪና ይዞ በመጫወቻው ፍተሻ ተፈተሻል። ተንቀሳቃሽ አምብዛም ነው። በዚህ ሰዓት ትራፊክ ጉዳይ ፍተሻ ነው። ከገና አውቶቡሱ በረረኝ። ቀስ በቀስ እእምሮዬን የሚያንቀሳቅሰው ጥያቄ መልሱን ሰጠኝ።

ቢታንያን ችግር እንደገጠማት መጠራጠር አልቻልኩም። ከር ቀን የት ነው ችግር? አሰሪዎች ደሆኑ ገድለዋት ይሆን?

ጥያቄው በዚህ አልቆምልህ አለኝ። ገድለዋት ከሆኑ እነዚ… የሞቱ ሰውን እርምጃ እና ሰዶሰ እያሰብሁ። አሰረዋት ከሆነስ? ስለሚደርገው ነገር ማሰብ አልቻልኩም። ድንጋጤ ጨለማ ይወጠኛል። በመጨረሻ የሞት ድግስ እንደሚጠብቀኝ ራሴን ደጋግሜ አሳመንኩት። ስለኛውንም መንገድ ይገድ ሳይገባ ወሲድ ወሰዶ የሚያደርሰኝ ከባለ መቃብሬ ነው። ይሆንኝ ሰንቱ ሳይ የምትለውን ቀን ነው የምጠብቀው።

***

9:20 እንቅልፍ ደረሰኩ።

ፍተሻውን ለማለፍ ግን ትእግስት አጣሁ። አስር ብር ጉቦ ከፍዬ አመለጥኩ። አዲስ አበባ ጥቁር ማቋን ተከናንባ ፍራሽ ላይ የተቀመጠች ሐዘንተኛ መስላ ጠበቀችኝ። የማየው ነገር ሁሉ ጠበንጃ፣ እሥራት፣ እልፎ አልፎ ደግሞ ተኩስ። እያንዳንዱ የጥይት ድምጽ ቢታኒያ ስትገደል የሚጮኸ መሰለኝ። ጭንቅላቷ ፍርከስ ሲል ይመጣብኛል። የኑረዲንን ዳቦ ቤት ሳልፍ ወደ ቤታችን ሀየሁ። ሐዘንተኛ ዐይታየኝም። ለቅሶም ተከልክሎ ሊሆን ይችላል። ጋራዥ ደርሼ ስቆም ሞተር ላጥፋ አላጥፋ ትዝ አይለኝም። ወደ ቀዩ በር ሮጥኩ። ዘልዬ ገብቼ ወደ ቢታኒያ መኖሪያ ከፍል ተምዘገዘኩ። 'ወ----ይ--------------------ኔ!' ጭንቅላቴን በእጆቼ ይዤ ቁጭ አልኩ።

በሩ በውጭ በኩል በቁልፍ ተጠርቅሟል። ወደ ምድር ቤት። ሸዋዬና ደጀኔም ሞተው ሊሆን ይችላል። ሰውነቴን እንደበድን እየገፋሁ ጣውላው በር ደርሼ አንኳኳሁ። በሩ እንደተከፈተ ሸዋዬ መጥታ ጥምጥም አለችብኝ። በግማሽ ልቤ ሳያት ሙሉ ትጥቋን ይዛለች። መምጣቴ እንዳስደሰታት ግን የማጤንበት አእምሮ አልነበረኝም። ወዲያው ደግሞ ደጀኔ ከመኝታ ከፍሉ ወጥቶ መጣ። እሱም ሙሉ ትጥቁን ይዟል። ስንሳሳም መርበትበቴ በደንብ ይታወቃል፣ "ቢታኒያ...ቤቲ...እእእ...ቢታኒያ! ገ--ደ--ሏት አይደል?" መልስ ሳጣ እደጋ እንደገጠማት ስለገባኝ ዐቅሌን ስቼ ኩልትፍትፍ አልኩባቸው።

"ጓድ አላምረው!" ሸዋዬ ትከሻየን እንቅ አድርጋ ይዛ አስቀመጠችኝ፣ "ጓድ አላምረው፣ መቅበጥበጡን ተውና በደንብ ተረጋግተህ የምንልህን ስማ!" ቆፍጠን ያለ ትእዛዝ ሰጠችኝ፣ "በቃ! ቢታኒያ በጠላት እጅ ወድቃለች። ሚስትህ ጀግና ናት! አንተም መርበትበቱን ትተህ ጀግንነት እንሥራ። በድርጅት ተልእኮ ላይ እያለች ይዘዋታል። የዳእሮ ነጋሽን ግድያ የሚቃወም ሰልፍ ሕቡዕ ገብታ ስታስተባብር ነው የያዟት። ልትኮራ ይገባሃል። ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ እራት ኪሎ አካባቢ ነው ያለችው። የምንወያየው አሁን ስለመያዟ አይሆንም። እንዴት ነጻ እንደምናወጣት ነው። ወይ ነጻ እናወጣታለን፤ አለያም የከብር ሞት እንሞታለን። ተረጋግተህ እያዳመጥከኝ ከሆን ልቀጥል..."

በድን ከመሆን ብዙም ባልዘለለ ስሜት ውስጥ ነኝ። ትንሽም ተስፋ አይታየኝም። ነገር ግን ነገ ሀፍረት የሚሆን ባህርይ ላለማሳየት ደመነፍሴን ራሴን ነግሬ ለመረጋጋት ታገልኩ። ደግሞም መረጋጋት ነው ያለብኝ፤ 'የታሰረችው ቢታኒያ እያለች?' በዚህ ላይ ጓድ ዳእሮ ነጋሽን ዐውቃታለሁ። የስምንት ልጆች እናት ነበረች። የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የነቃችና በፖለቲካ ጉዳይ እንደ ንብ የምትለፋ ጽኑ ሴት ነበረች። ፍርሀት ብሎ ነገር አልፈጠረባትም። ኢሰማ (የሠራተኞች ማህበር) ሕቡዕ ገብቶ የተቋቋመው እሷ ቤት በተደረገ ምሥጢራዊ ጉባኤ ነው። ከዶክተር ተስፋዬ ጋር በአስረጅነት ተገኝቻለሁ። ዳእሮ ነጋሮማ ከበደ የተገደለችው ልትወልድ ጥቂት ቀናት የቀሯት የዘጠኝ ወር እርጉዝ ሆና እያለ ነው።

እንዲህ ዓይነት የወንጀል ወንጀል...የበደል በደል...የግፎች ሁሉ ግፍ ይሰራባታል ብዬ አልጠበኩም። ቢሆንም አንድ ቀን በቅጽ በቅጽ የሚጻፍ ታሪክ ትታ ይሄደች የጀግና ጀግና ናት። ስለዚህ ከሁሉቱ የሴት ጀግኖች ተምሬ መረጋጋት እንዳለብኝ ተሰምቶኛል።

"በደንብ እየሰማሁሽ ነው፣ሸዋ።"

ደጀኔ፣ "አሁን የዘመቻ እቅዳችንን ዝርዝር አድርገሽ ንገሪው!" ብሏት ወደ መኝታ ክፍሉ ተመልሶ ሄደ። ሸዋዬ ቀጠለች...

"አንደኛ፣ አሁን አዲስ አ'ባ እናንተ ስትሄዱ የነበረችው አይደለችም። ግርግር በግርግር ሆና ማን ከማን አይለይም። ልብ ያለውና የደፈረ ማንም ሰው የፈለገውን መሥራት ይችላል። ቢታኒያን ነጻ ለማውጣት በጣም ምቹ ነው። ይሄን ከልብህ እመንበት። ሁለተኛ፣ ቀኑን ነው የማናውቀው እንጂ ሁላችንም መስዋእት እንሆናለን። የውሻ ሞት ግን በፍጹም አንሞትም። ቢታኒያን ለማስለቀቅ ስንል ሞትን ወይም ተይዘን ሞትን ልዩነት የለውም።ሦስተኛ፣ ለዘመቻችን በቂ ማስመሰያ አግኝተናል። የመኢሶናች መኪና በእጃችን አለች። በደንብ አዘጋጅተናታል። መኢሶኖች ብቻ የሚለብሱት የኩባ ቱታም እዛው መኪናዋ ውስጥ አግኝተናል። ሙሴ ባልዲ ዋናው ቤት መጥቶ ረስቶት የሄደው የአብዮት ጥበቃዎች ቆብም በእጃችን አለ። ሙሉ ትጥቅ አለን። አንድ የኛ ኮማንዶ አግኝተናል። እየሰማኸኝ ነው፣ አላምር?"

"በደንብ እየሰማሁሽ ነው።"

"አንተ ከዚህ በኋላ የመኢሶን ከፍተኛ ባለሥልጣን ነህ። ሁሉንም ነገር አዘጋጅተንልሀል። እኛ አጃቢዎችህ ነን። መሽትሽት ሲል ቀጥ ብለን እየነዳን እንሄድና ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ድንገት እንደርሳለን። ወርደን ከጀርባህ ጀብ ጀብ ስንል ያለጥርጥር ፖሊሶቹ ባለሥልጣንነትህን ይቀበላሉ። የፈለገው ደፋር ሰው ቢሆን ይህንን ያደርጋል ብለው ሊገምቱ አይችሉም። ዋናው መሣሪያችን ግን መኪናዋ የመኢሶኖች መሆኗ ነው። እንኳንስተራ ፖሊሶች ማንም ባለሥልጣን ቢሆን መኪናዋን ሲያይ ካድሬዎች እንደመጡ ያምናል። እኔና አንተም ብንሆን!"

"በጣም ትክክል ነሽ፣ ሸዋ!" የሆነች ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል ታየችኝ፣ "ልበሙሉነት ይጠይቃል እንጂ እሥራኤሎች በየቀኑ የሚሠሩት ጀብድ ነው፣ ይሄ። ምንም የሚያስፈራ ነገር የለም!" ድንገት ወኔዬ ተንተከተከ ቆፍጠን አልኩ።

"ተግባባ—ን!" ሸዋዬ ደስ ብሏት ቀጠለች፣ "ነገር ግን ፖሊሶቹ በሆነ ምክንያት ቢጠራጠሩስ? ግፋ ቢል

ለአለቆቻችን እናስታውቅ ይላሉ። የዚህ አድል ግን ወደ ዜሮ የተጠጋ ነው። ከዚያ ምን ታደርጋለህ? ሰሚን ከማስታወሻ ደብተር ዐይቼ ስነግርህ ቢታኒያን ታስጠራታለህ። ስትመጣ በቁጣ መዐት ትወርድባትና በጥፊ ትላታለህ። 'ነፍስጡር ባትሆኝ ኖሮ አደፋሽ ነበር!' ትላትና የፖሊሶቹን ተረኛ ዘብ ታስጠራዋለህ። ምንም ሳታመነታ ፈርጠም ብለህ 'ልቀቃት!' ትለዋለህ። እኛ እንደሄድን ቤቷ ትወጣለች ማለት ነው። ወዲያው አክስቷ በመኪና ይዛት ውልቅ ትላለች። አክስቷ ስልኩ አልመልስ ሲላቸው ጊዜ እዚህ መጥተው ነበር። በደንብ አዘጋጅተናታል። ይህ ሁሉ ሳይሆን ቀርቶ ቢነቃብንስ? በቃ፣ ረፍርፈነው ወይ እናመልጣለን ወይ እንሞታለን! ምን ይመስልሃል?"

"ሸዋ፣ ትጠይቂኛለሽ እንዴ? በደንብ አምንበታለሁ!"

ሸዋዬ በትልቅ ብርጭቆ አርጎ አመጣችልኝ። አሁን ልተወው አልፈለኩም። ጭልጥ አድርጌ ጠጣሁት። ሰውነቴን ልገታጠብ ወደ ምድር ቤት ስወርድ ሸዋዬ የደጀኔን ጸጉር መላጨት ጀመረች። አሁን ልቤ በሞትና በሕይወት መካከል እያወዛወዘች እንድትረብሸኝ አልፈለኩም። የዘመቻ እቅዱ በትክክል ሊፈጸም የሚችል ነው። ሸዋዬ ከበቂ በላይ አሳምናኛለች...

'ስለዚህ...' አልኩት ራሴን፣ 'ስለዚህ ማሰብ ያለብኝ ስለከሸፈ ዘመቻና ሞት መሆን የለበትም። ስለፍትህና ነጻነት ነው። የጀግና ጉልበት የሚቀዳው ከተራ ድፍረት አይደለም። ሌሎችን ከመናቅና የውጊያ ዘዴ ከማወቅም ብቻም አይደለም። ከጠበንጃ ብልጫና ከሥፍራ አያያዝ ብቃትም አይደለም። የጀግና ጉልበት የሚመነጨው ወደ ውጊያ ካስገባው ምክንያት ፍትህዊነት ነው። ጀግንነትና ፍትህ መቼም አይነጣጠሉም። ቢታኒያ በዳእሮ ነጋሽ ሞት ፍትህን ፍለጋ ስትማስን ተያዘች። እኔ ደግሞ ፍትህ ላጣችው ፍቅረኛዬ ነጻነት ልዘምት ነው!

"ለፍትህ መኖርም መሞትም በስንት ጣእሙ!" ከልቤ ራሴን በደንብ አሳምኜ የጀብደኝነት ግፊት በውስጤ እንደሌለና ብዙ ጊዜ ስህተት የምታሠራኝ የችኩልነት ችግሬ አብራኝ እንደሌለች እርግጠኛ ሆንኩ።

ስመለስ ሸዋዬና ደጀኔ ሁሉንም ነገር ጨራርሰው ሲጠብቁኝ ደረስኩ። እሷ የፖሊስ ፊልድ ጃኬት በአዲስ አረንጓዴ ወታደራዊ ቱታ ለብሳ የአብዮት ጥበቃ ሰማያዊ መለዩ ደፍታለች። የሙሴ ቆብ መሆኑ ነው። በቃ፣ ሌላ የማላውቃት ሰው ሆናለች። ደጀኔም የኩባ ዥጉርጉር ወታደራዊ ቱታ ለብሶ በተላጨ ጸጉሩ ላይ ቢጫ መለዩ አድርጓል። "ከስከስ" የሚሉትን የወታደር ጫማም ተጫምቷል። እንዲህ በተሳካ መመሳሰል ሳያቸው ልቤ የተስፋ ደም መርጨት ጀመረች።

"ጓድ አላምረው፣ ና ተቀላቀል። አይዞህ! ይሄን ገድል ሠርተን ከሚስትህ ጋር ትገናኛለህ። ደንባራው ድርጅታችንም የማይረሳ ትምህርት ማግኘት አለበት።" ሽዋዬ የቀኝ እጇን ዘርግታ ሽቅብ ቀሥራ ቁርጠኝነቷን አሳየችኝ። "ዘመቻ ዳዕሮ ነጋ---ሽ ብዬዋለሁ!" ፈገግ አለች።

"ዘመቻ ዳእሮ ነጋሽ!!" እኔና ደጀኔ ደገምነው።

ወኔዬ ግንፍል ብሎ በል! በል! አለኝ። ደጀኔ የመኢሶኖችን ቁታ ከፕላስቲክ አውጥቶ ዝርግትግት አድርጎ ሰጠኝ። በጣም የተገረምኩበት የአየር ኃይል መኮንኖች ብቻ የሚያደርጉት ጫማም አዘጋጅቶልኛል። ማኦ ኮፍያ ደፋሁ። ሁሉንም ለባብሼ ስጨርስ ሽዋዬ ጉንጮቼን የሚያጣብቅ ቀለም የለሽ ቅባት ነገር ቀባቻቸው። ተላጭቶ በተዘረጋ ከላሴር ላይ የተቀመጠውን የደጀኔን ከርዳዳ ጸጉር አምጥታ አጣበቀችብኝ። ስትጨርስ መስታዎት አሳየችኝ። ቁርጥ የመኢሶን ካድሬ። ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያን በደንብ ስለምናውቀው የካርታ ጥናት አላደረግንም። ተኩስ ከተከፈተ ብቻ ፖሊሶቹን ጨፍጭፈናቸው በእስር ቤቱ ጀርባ ልናመልጥ ተነጋገርን። ተያይዘን ወደ ጋራዥ...

***

ፀሐይ ጠልቃ ምሽቱ ገብቷል፣ዐይን ግን አይዝም። የመንገድ መብራቶችም በርተዋል። ራስ መኮንን ድልድይን አልፈን ወደ ሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ስንጠጋ ፍርሀቴን በደንብ እንደተቆጣጠርኩት መንፈሴ ደጋግሞ ነገረኝ። "ዘመቻ ዳእሮ ነጋ---ሽ!"

ዘመቻችን የፍትህ ዘመቻ መሆኑን እንደገና አስታወስኩ። የበለጠ ወኔና በራስ መተማመን ተሰማኝ። ደጀኔ ያመጣው ኮማንዶ የመኢሶኖችን ቶዮታ እንደ ጥንግ ያከንፋታል። ከፖሊስ ጣቢያው በር ስንደርስ ሲጢጢጢጢጢጥ አድርጎ አቆማት። ሁሉም ነገር ቅጽበታዊ ነው። ሦስቱም በሮቹን እየበረገዱ ቀድመውኝ ወረዱ። ደጀኔ ወደ እኔ መጥቶ በሩን ሲከፍተው ዱብ ብዬ ወረድኩ። ዘመቻ ዳእሮ ነጋ---ሽ!!

'የጀግንነት ምንጭ ተራ ድፍረት አይደለም። አሳማኝ የሆነ የፍትህ ርሀብ ነው!' ልቤ ድው ድው ማለት ስትጀምር ገሰጽኳት።

ወደ ፖሊስ ጣቢያው በር ተመለከትኩ። የብረት በሩ በሰንሰለት ታስሮ ነው የተዘጋው። አስር የሚሆኑ ፖሊሶች እዚያና እዚህ ቆመውና ተቀምጠው ይታዩኛል። ትልልቅ ካፖርትና ሌሎቹ ደግሞ ብርድ ልብስ ደርበዋል። ተረኛ ጠባቂዎቹ ከበሩ ግራና ቀኝ በትንንሽ ቆርቆሮ ቤቶች ውስጥ ተቀምጠዋል። ሾፌሩ ሄዶ ሰንሰለቱን ሲያንጫጫው ተረኞቹ እየበረገጉ ተነስተው በሩጫ መጡ። ውስጥ ብትንትን ብለው

የቆሙት ደግሞ ርብሽብሽ ብለው ብርድ ልብሳቸውን እያወለቁ ሲጥሉ ይታዩኛል። ተረኞቹ ከሰማይ የወረደ ጉድ እንደሚመለከቱ ዓይነት በጭንቀት ተውጠው ዐይን ዐይኔን ያዩኛል። በመጨረሻው ፍጥነት መሰላሉን አንስተው በሩን ብርግድ አደረጉት። ሾፌሩ ከላሸንኮሩን እንደደገነ በሩ ላይ ቆመ። ሸዋዬና ደጀኔ ቅልብልብ እያሉ በግራና በቀኝ ጎኔ መጡ...

በሩን የከፈቱልኝ ፖሊሶች ወታደራዊ ሰላምታ ሲሰጡኝ መሬቱ ተነጋነገ። ከአንገቴ ቀልበስ ብዬ አጸፋውን መልሼ ሰተት ብዬ ገባሁ። በቀኝና በፊት ለፊቴ በኩል መዐት እስር ቤቶች የሆቴል አልጋ ከፍል መስለው ተደረደረዋል። በረንዳው በጫማዎች ተጨናንቋል። በእስር ቤቶቹ መስኮት የላይኛው ሀዳግ እስረኞች አንዱ በአንዱ ላይ እየተደራረቡ ሊያዩኝ ተተረማመሱ። በግራ በኩል ሁለት ትልልቅ ቤቶች አሉ። የሚታዩኝ ፖሊሶች ሁሉም በተጠንቀቅ ቆመው አፍጥጠውብኛል። ቀጥ ብዬ በግራ በኩል ወዳለው ቤት በረንዳ አመራሁ...

"ማ---ነ--ሀ፣ እስቲ አዛገፉ ካለ አዛገፉን...እሱ ከሌለ ተረኛ መኮንኑን አስጠራልኝ! ካሳሁን ነው በለው..." ለእኔ ቀረብ ብሎ የሚታየኝን አንዱን ፖሊስ ሳዘው ሦስት ፖሊሶች ወደ ግራ አቅጣጫ የሩጫ ውድድር የገጠሙ መስለው ሮጡ።

ወዲያውኑ ተረኛ መኮንኑ መጥቶ ከፊቴ ቆመ። በጣም አጭር...ቦርጬ ዝርግፍ ያለ በጣም ወፍራም... ከሰል የመሰለ ጥቁር...። መርበትበቱን ፊቱ ላይ ሳነበው ጊዜም አልፈጀብኝ። እጁን በሰላምታ ጨብጬ ቁልቁል ዐየሁት...

"ማን ነበር ያልሽኝ?" ሸዋዬን ጮኽ ብዬ ስጠይቃት ማስታወሻ ደብተር እንደገለጠች ሹክክ ብላ መጥታ አጠገቤ ቆመች።

"እዚህ ያለችው ቢ--ታ--ኒ---ያ መኮንን ነው የምትባለው..." አለችኝ ስሟ ያልተነበበላት መስላ እየታገለች።

"ቢታኒያ መኮንን የምትባል እናርኪስት አቅርብልኝ!!" መኮንኑ ገና ተናግሬ ሳልጨርስ ወደመጣበት አቅጣጫ ከነፈ።

ለአፍታ በነበረኝ ጊዜ ዙሪያ ገባውን ቃኘሁ። እስካሁን ምንም ዓይነት ችግር ያልገጠመን መሆኑን ሳይ ቢታኒያ እንጀት የሚሞረሙር ርሀብ ሆነችብኝ። ተረኛ መኮንኑ ወደሄደበት አቅጣጫ ገልመጥ አልኩ። ቢታኒያ በሁለት የታጠቁ ሴት ፖሊሶች ታጅባ እየመጣች ነው። ሙሉ የሌሊት ልብስ ለብሳለች። ጸጉሯ

እንደነገሩ ተጎንጉኖ ፍልስልስ ብሏል። ቡጢ'ጥ ያለው ሆዷን ሳይ ወኔዬ እንደገና እሳት ሆኖ ነደደ። ባዶ እግሯን ናት። በረንዳውን ጨርሰው ወደ እኔ መጡ። መንገዱ ጠጠር ስለለበሰ እግሯን አልመች ብሏት የማንከስ ያህል ዘንበል ዘንበል አለች። ተረኛ መኮንኑ ከሴት ፖሊሶች ጀርባ አለ። ሮጥ ብሎ ቀድሞ ቢታኒያን ከፊቴ አቀረባት። ዐይኖቿን ዐይኔ ላይ ለማሳረፍ ተቸገረች መሰለኝ መሬቱ ላይ አቀረቀረች። እንዳላወቀችኝ እርግጠኛ ነኝ...

"ቢታኒያ መኮንን ማለት አንቺ ነሽ፣ አይደል?" በጩኸት ጥይቄ አፈጠጥኩባት።

"አዎ፣ ነኝ።" ዐይኖቿ እንባ አለማርገዛቸው ገረመኝ።

"ስሚ፣ አንቺ ደካማ ውርጋ—ጥ! አብዮታዊ መንግሥትን 'እርጉዝ ገደለ' ብለሽ በሕዝብ ለማስጠላት ሞከርሽ። እናስ ተሳካልሽ? በፍጹም በፍጹም አትችይም። እኛም ከእናቶቻችን ማህጸን የተገኘን መሆናችንን ያንች በጸረ-አብዮት ኃይሎች ፕሮፓጋንዳ የረከሰ ጭንቅላት ሊያስታውሰን አይችልም። ሲበዛ ደንቆሮ ነሽ! አንችም ለጸረ-ሕዝቦች መጫሪያ የሆንሽው እርግዝናሽን ተማምነሽ ነው። አብዮታዊ መንግሥት ለነፍሰ-ጡር እናቶች ይቅርና ለሴቶች ሁሉ አክብሮት እንዳለው ስላወቅሽ ነው። ስሚ፣ ሁለተኛ በጸረ-አብዮት ድርጊት ተሳትፈሽ ብትገኚ ምን እንደምናደርግ መገመት አለብሽ። ሁ---ለ---ተ---ኛ!!" ብዬ ወደ ተረኛ ፖሊሱ ዞር አልኩ፣ "አሰናብታት!!" ቀጭን ትእዛዝ።

በዘመቻ እቅዱ መሠረት አንዴ ደህና አድርጌ በጥፊ ማጮል ነበረብኝ። እጄ በጭራሽ አልታዘዝህ አለኝ። ሳልመታት ነጻ እንደምትወጣ ውስጤ እንዲሁ እየነገረኝ ነው። እጅግ ትልቅ ስህተት መሆኑን ይገባኛል። የፈለገ ይሁን፣ አልመታትም።ቢታኒያ አንገቷን እንዳቀረቀረች ከፊቴ ዘወር አለች።

ዘመቻ ዳእሮ ነጋ--ሽ!! እንደኮርማ እየተጀነንኩ ወደ በሩ ተመልሼ ስወጣ ሌላ ሰላምታ ጠበቀኝ። "ደህና ሁኑ!" ብዬ ወጣሁ...

# 41

ራስ መኮንን ድልድይን አልፈን በአቋራጭ መንገድ ሄድን። አሳት አደጋ መከላከያን አልፈን ወደ ፒያሳ። በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በኩል ወደ ጦር ኃይሎች ነዳን። ተመልሰን በጉራንጉር ውስጥ አልፈን አንድ ቦታ አረፍ አልን። ጭለማን ተገን አድርገን ለደቂቃዎች ቆምን። መንገዳችንን ያወሳሰብነው ምንም ዓይነት ክትትል እንደሌለብን ለማረጋገጥ ያህል ነበር።

ጋራዥ ገብተን ስንቆም በደስታ ሲቃ መነጋገር ሁሉ እቃተን። በሕይወታችን መቼም የማንረሳው ገድል ነው። ከመኪና ወርደን ለረጅም ጊዜ ተቃቅፈን ተሳሳምን።

'የሰው ልጅ ለካ ሌላ ምንም አይደለም። ሥነልቦና ብቻ ነው።' የአዲሱ ፍልስፍናዬ ምሰሶ ሲሆን ታየኝ።

ሁላችንም ቢታኒያን እንደማግኘት ያጓጓን ነገር የለም። ሾፌሩን አሰናብተን ወደ እሷ ሮጥን። ቀድማን እንደምትደርስ ግልጽ ነው። ቀዩን በር ከፍተን ስንገባ ግን ቤቷ ልክ እንደ ቀኑ ተዘግቷል። መብራትም አልበራም። በቁማችን የጨው ዐምድ መስለን ቆምን። አእምሮዬ ሙሉ በሙሉ ሥራውን አቁሞ ቀጥ አለ። እንደ ሰካራም ራሴን መሸከም አቅቶኝ ወደ ቀዩ በር ተመለስኩ። መቀርቀሪያውን ልከፍት እጄን ሰደድ ሳደርግ ደጀኔ ከጀርባዬ ጠራኝ...

"ጓድ አላምረው፣ አንዴ ና። ስልክ እየጮኸ ነው።" ሩጫዬ ሩጫ አይደለም። በሩን የከፈትኩበትንም ፍጥነት አላውቀውም። የስልኩን እጀታ ማን እንዳቀበለኝ ትዝ አይለኝም።

"ሰሙዬ፣ የ'ኔ ጌታ፣ ፍቅሬ..." ወድቃ ፍርከስከስ ልትል የነበረችው ነፍሴ ወደ ቦታዋ ተመለሰች፣ "እእእ... እናና—ትየ...እእእ...የ-ት የ—ት ነሽ?" አፌ ገና መናገር እንደሚለማመድ ሕጻን ልጅ እሰርሰር አለብኝ።

"ስሙዬ...አትደንግጥ! በሰላም ወጥቻለሁ። ኮተቤ አክስቴ ቤት ነው ያለሁት..." ስትለኝ አቋርጫት፣ "እሺ፣ እሺ...አሁኑኑ መጣሁ..." ብያት ስልኩን ልዘጋ ስል እንደገና ጠራችኝ።

"ስሙዬ፣ እዚህ አካባቢ ከባድ ግርግር አለ። አትምጣ...ነገ ጧት ነው የምትመጣልኝ...ቤት አትቀመጥ... ወይ መኪና ይዘህ ዞር ዞር በል፤ ወይ ምድር ቤት ሂድልኝ...እሺ?" ጭንቅ እያላት ድምጿ በስጋት ተለዋውጧል። "እሺ!" ብዬ ተሰናበትኳት።

እንደገና ተቃቅፈን ከደጀኔና ከሸዋዬ ጋር ተሳሳምን። እንደተቃቀፍን ወደ ምድር ቤታችን ሄድን። ማመሳሰያዎቻችንን አጽድተን ወደ ቀድሞ ማንነታችን እንደተመለስን ገና አስር ደቂቃ ሳይሞላ ወደ ጋራዥ የሚገባ ድምጽ ተሰማን። "የመጣው ይምጣ፤ እናፋለመዋለን!" መሣሪያዎቻችንን አንስተን ለተኩስ ተዘጋጀን። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ጣውላው በራችን ተንኳኳ። ሸዋዬ ዞር ብላ ዐይታን ፈገግ አለች። የመጣው ሰው ኢሳያስ ነው። ከፍታለት ሲገባ እንገት ለእንገት ተጠማጠምን።ለዓመታት የተለያየን ነው የመሰለኝ። ናፍቆታችንን ለመወጣት ግን ጊዜ አልተረፈንም።

ከጉለሌ የኢሕአፓ ፖለቲካ ቢሮ ጽሕፈት ቤት ሰነዶችን ወደ ሌላ ቦታ በማጓጓዝ ሥራ ተጠምዶ መዋሉን ነገረን። ገና ያልጨረሰው ሥራ ስላለ ነገም በሌሊት ይወጣል። የኢሳያስ መምጣት ልቤን ከሁለት ከፈለው። በመሄድና በመቆየት አማራጮች መካከል አመነታሁ...

"ኢሱ፣ ጓድ ተስፋዬን ወይም ጓድ ከፍሉን አሁን ብሄድ አገኛቸዋለሁ?" ለመወሰን እንዲረዳኝ ጠየኩት።

"በጭራሽ አታገኛቸውም። በስልክ ብትል በምንም መንገድ ብትሞክር የሉም። አንተ ስላልነበርክ ነው፣ ሰመሬ። ነገሩ ቀስ በቀስ የድርጅትን ሕይወት ከማዳን ጉዳይነት ወጥቷል። አሁን የራስን የግል ሕይወት እንዴት ማትረፍ እንደሚቻል ነው ዋና ጭንቀት እየሆነ የመጣው። ያች የሱፍ አበባ ያልካት ነገር በፍጥነት ረግፋ ረግፋ..." ብሎኝ በሐዘን አቀረቀረ።

የተገደሉትንና የታሰሩትን የአዲስ አበባ በይነቀጠናና የየቀጠናው የኢሕአፓ ኮሚቴ አባላትን ሲዘረዘርልን መስማት አቃተኝ። የእኛ ሰፈር መሳለሚያም ነበልባሉ ደርሶታል። ሙሴ ባልዲ ባጭር ጊዜ ስሙ የገነነና በጣም የሚፈራ ውሳኔ ሰጭ ባለሥልጣን ሆኖ መውጣቱን ሸዋዬ ነገረችን። በተለይ ቢታኒያና እኔ እንድንጠነቀቅ መከረችኝ። ምክንያቱ ግልጽ ነው። ቡዳ በወዳጁ ይጠናል!

የምሽቱን ገድላችንን ደጀኔ ለኢሳያስ አነሳለት። ኢሳያስ ሌሊቱን ሁሉ ብንነግረው፣ ብንምልለት፣ ብንሙኸለት አምኖ የሚቀበል አልመስልህ አለኝ። ይሰማ ይሰማና፣ "አረፉ እንጂ! እየቀለዳችሁብኝ

ነው፣ አይደል?" ግራ ተጋብቶ ተራ በተራ ያየናል።

አብሬያቸው ብቆይ ደስታውን አልችለውም። የገጠመኝን ፈተና በድል ማለፌ የፈጠረብኝ ጥልቅ ደስታ በርሀብና በእንቅልፍ ጥማት አብሮኝ ሊቆይ አልቻለም። ሸዋዬ ሽሮ ሠርታ እስከምታቀርብልን ድረስ መታገስ ከበደኝ። በልቼ ቢታኒያ ወደ ሌለችበት ቤትና ሌሊት አመራሁ። የተመኘሁት ዥው ያለ እንቅልፍ ግን አልቀናኝም። የምሽቱ ዘመቻ ህልም ሆኖ እየመጣ ቅዥት ለቀቀብኝ። በቃ፣ ሲከሽፍና ለወሬ ነጋሪ ሳንተርፍ ስናልቅ እየመጣ ድቅን ይልብኛል። ንጋት ሲቃረብ ደግሞ የጥይት እሩምታው በየት ያስተኛኝ። የዛሬው የተለየ ነው። አሁን ስንት የሱፍ ጥሬዎች ወድቀው እንዳደሩ በመጨነቅ አላነጋሁትም።

"ምትም ይለመዳልና! መርዶ መሆኑ ቀርቷል። ዕድሜ ለ'አጥቅቶ መከላከል' ተብዬው ሥልታችን!" ከፍራሽ ተነስቼ ቱታየን ስለብስ ሳይታወቀኝ ድምጼ አውጥቼ ምሬቴን አስተጋባሁ።

ቀደም ብዬ ነው የተነሳሁት። ኢሳያስ ከእኔም ቀድሞ ተነስቶ ነው የሄደው። ቢታኒያን ከኮተቤ ለማምጣት እሄዳለሁ። እግረመንገዴን የምሠራቸውን ነገሮች ዐሰብኩ። ከእብናት ያመጣሁትን መልእክት አደርሳለሁ። ዶክተር ተስፋዬን የማድ ማግኜት ይኖርብኛል። አሁን ጧት ላይ ግን እንደማላገኘው ኢሳያስ ነግሮኛል። ቤቱን ዘግቼ ወደ ጋራዥ አመራሁ።

ላንድሮቨሯን ይገዞ ወጥቼ መጀመሪያ የሄድኩት ሜክሲኮ ነው። የእብናቷን ባለ ጠጅ ቤት መልእክት ካደረስኩ በኋላ ወደ ኮተቤ። የቢታኒያን ዓይኖች ለማየት ከመጠን በላይ ጓጉቻለሁ። እንዲሁ በሕይወት የማገኛት የማገኛት አልመሰልህ አለኝ። እንግሊዝ ኤምባሲን እንዳለፍኩ የተጣለ አስከሬን ዐየሁ። ትንሽ ራቅ ስለሚል ቢታኒያን በወሬ ከያዝኳት ሳታየው እንደምታልፍ ተስፋ አደረኩ።

'ተመልሶ ላያሸት የረገፈ የሱፍ ጥሬ!' በቁጭት የመኪናዋን መሪ በቡጢ ነረትኩት።

###

የቢታኒያን አከስት ቤት ወይዘሮ ማስተዋልን ወደ ደብረ-ብርሀን ስሸኝ አውቀዋለሁ። ደርሼ በሩ ላይ ቆምኩ። ስገባ ቤቷ የዘመናት የእንቅልፍ ሐሳብ የምታወርርድ ያህል ለጥ ብላ አገኘኋት። አከስቷ ቤተክርስቲያን ስለሄዱ መሰለኝ ቤቱ ጭር ብሏል። ትልቅ ሴት ልጃቸው ተቀበለችኝ። በረንዳ ወንበር አውጥታልኝ ቁጭ ብዬ እስከምትነቃ መጠበቅ ጀመርኩ። ብዙም ሳይቆይ አከስቷ መጡ። ከዋናው በር ሲገቡ እንግዳ ሆንኩባቸው መሰለኝ ትኩር ብለው ዓዩኝ። የቢታኒያ ጓደኛ መሆኔን ስነግራቸው ደግሞ በአንዴ ቅይርይር አሉ።

ወንድ...እናትህ የወለደችህ የወንድ ወንድ...የሰው አንበሳ...ከእዞ አፍ የገባ ጥሻ ፈልቅቀህ ያወጣህ የሰው ነብር! እሰይ ልጄ! አንኳን የቢታኒያ ሆንክ! አንኳን የማስተዋል ሆንክ...አንኳን የኛ ሆንክ! ለሰው ቢነግሩት አያምንም!"

ቀከራና ቀረርቶ...ውዳሴና ምርቃት...ቀለጠ። እያገላበጡ ስመው አቅፈው ይዘውኝ ቤት ገቡ። ቢታኒያን በዚያ መንገድ ከእስር ማስለቀቄ ሞትንና ሕይወትን የሚወስን ምሥጢር ነው። አሁን ግን አንኳንስ አከስቷን እኔንም አላስጨነቀኝ። ልጃቸው መጥታ ስትቀላቀለን ደግሞ ቅልጥ ያለ ሠርግና ምላሽ ሆነ። ቢታኒያን ከእስር ቤት ስናስወጣት ሁለቱም ራቅ ብለው ይከታተሉ እንደነበር ነገሩኝ። ስለ ሸዋዬና ደጀኔ ማንነት በጥያቄ አዋከቡኝ። ቢታኒያ ተነስታ ስትመጣ ደግሞ የቤቱ ሀውድ ተለወጠ። በእንባ ሳግ የሚናገሩትን ማጣት መጣብን። አቅፋ አለቀህም አለችኝ። ቁርስ በልተን ወደ መሳለሚያ ለመመለስ ስንነሳ ከሁለት ሰዓት በላይ ቆይተናል።

"እናትዬ፣ በአካልም በመንፈስም ሰላም ነሽ፣ አይደል?" ጉዟችን ላይ ሠላሳ ጊዜ ይሆናል የምጠይቃት።

"ብቻ፣ አንተ ኑርልኝ፣ ሆድዬ! በጣ----ም ደህና ነኝ!"

"ሆዴ፣ መቼም በዚያ መንገድ ነጻነቴን አገኛለሁ ብለሽ ልታስቢ አትችይም። አይደል?"

"በጭራሽ! በኔ ሞት እርግጠኛ ስለሆንኩ አልጠበኩም። አጸልይ የነበረው ባሌን ለአንዲት ሴኮንድ ዐይኑን አይቼው ልሙት እያልኩ ነበር። በተረፈ 'ሚሽኑን' ስላሳካሁ ጸጸት ብሎ ነገር አልነበረብኝም።"

"ስናስጠራሽ ለይተሽ አወቅሽን ወይስ ከተለቀቅሽ በኋላ ነው ያገናዘብሽው?"

"ው...ይ፣ ሰሙ... እየቀለድክ ነው? ሸዋዬን ገና ከሩቅ ሳያት ነው ያወኳት። አንተን ደግሞ መናገር ስትጀምርና ጥርስህን ሳይ ለየሁህ። ደጀኔንና ያኛውን ትንሽ ልጅ ነው ያላወኳቸው። ብቻ አውሬዎቹን ጉድ ሠራችሁልኝ! ሽንታቸውን በቁማቸው ሊለቁት ምንም አልቀራቸው..." የሞት ሞቷን ሳቀች።

"ደግነቱ፣ ሆድዬ...ደርጎችን ሁለቴ ነው ጉድ የሠራናቸው። ዳእሮ ነጋሽን የረሸናት ግርማ ከበደ ያው አንቺ ባስተባበርሽው ሰልፍ ምክንያት ተይዞ ወዲያው ተገድሏል አሉኝ። እሱን ይዘው ግን 'ሕዝቡን ለምን ትሰለፋላችሁ?' ሲሉ ገረመኝ። ሊይዙት አልፈለጉም ነበር ማለት ነው?"

"ማን ነው እንደዚህ ያለው? ውሸት ነው። ደርግ በጓድ ዳእሮ መገደል የሚያዝንበትና የሚጸጸትበት ምን አንጀት አለውና ነው?! ግርማ ከበደ ተይዞ የተገደለው እሷን ስለገደለ አይደለም። አንዷ ሴት ፖሊስ

በሆነ ምክንያት አብራን ታስራ ነበር። ወይ ልትስልለን ይሆናል፡ በሹክሹክታ ስታወራ ሰምቻታለሁ። የፍተሻው ጊዜ የመንግሥቱ ኃይለማርያምን አባት ጠበንጃ ያስረከቡን ብሎ ስለተዳፈረ ነው የገደሉት..." ቁባዋ ተመልሶ ሊቀጣጠል ዳር ዳር አለው።

ያም ሆነ ይህ ሁሉም ነገር አልፎ በሕይወት ተገናኝተን አሁን አንድ ላይ ነን። ሁለታችንም ቅዠት የመሰለውን ክስተት ለማመን ተቸግረናል። ሰው እንደ ቅጠል በሚረግፋባት አዲስ አበባ ድላችን በእርግጥም በተሀምርነት ሊታይ የሚችል ነው።

ቁጭራ ባንክ ስንደርስ መንገዱ ተዘጋብን። ለሁሉም ተሽከርካሪ ስለተዘጋ አልተደናገጥንም። ብዙም ሳይቆይ በግራ መስመር እንድናልፍ ተፈቀደ። ስናልፍ መንገዱ የተዘጋበትን ምክንያት ለማየት በመስኮቱ በኩል ተማተርን። ከባንክ ቤቱ በር ወረድ ብሎ ቶዮታ ሐይሉክስ ቆማለች። ሁለቱም በሮቿ እስከላንቃቸው ተከፍተዋል። ፖሊሶች የውስጥና የውጭ ፍተሻ ያደርጋሉ። አንዳች መብረቃዊ ድንጋጤ ወገቤን ደቃኝ...

"ሆድዬ፣ ...ይታይሻል? የእኛ ጋራዥ መኪና??" ምላሴ እሰርስር አሉብኝ።

"አዎ...አዎ..." ብላኝ ፍጥነት በመቀነሴ ከጀርባዩ የሚንጫጫው የጥሩንባ ድምጽ መድረሻ አሳጥቶኝ ስቸገር፣ "ወ--ይኔ! ኢሳያስን ገደ-- ሉት!" ብላ ቢታኒያ ጮኸች፣ እንባዋ ከመቅጽበት ዠርግፍ አለ።

የመኪና አደጋ ሳይገጥመን መቅረቱ ይገርመኛል። አብድ ሆነን ሙሾውን አቀለጥነው። ቤት ስንደርስ ሸዋዬና ደጀኔ ጆሯቸውን ማመን አቃታቸው። ተሳስተን እንዳይሆን ደጀኔ ሰግቶ ሞተር ብስክሌት ይዞ ወጣ። ሲመለስ ኢሳያስ በትክክል መስዋእት ሆኗል። ሁላችንም ምድር ቤት ጉብተን ለኢሳያስም ለራሳችንም ጭምር እየየው ብለን አለቀስን። አምርረን አዘን።

እንዴት እንደገደሉት አንድም ሐሳብ የለንም። ምናልባት ለፍተሻ እንዲያቆም ሲጠይቁት ፈቃደኛ አልሆን ብሎ እንደመቱት ገመትን።

***

የኢሳያስ ሐዘን ሲሊቱን ሙሉ መንፈሳችንን ሽባ አድርጎታል።

ቃል መናገር እንኳ ኃጥያት መስሎ ተሰማን። እንቅልፍ በዐይናችን አልዞረም። ለዚህ ፋታ ያሳጣው እያሳደዱን ያሉት ጠላቶቻችንና ወልቃይት የገቡት ዘርዑና ጳሎተ ናቸው።

የአስር ሰዓቱ የእሱር ሶላት የቢላል መስጊድ አዛን ሲሰማ ነቅቼ ቁጭ አልኩ። የኢሳያስ ገዳዮች መታወቂያውን ዐይተው ከሸዋአዲስ ጋራዥ መሆኑን ሲያውቁ ይመጡብን ይሆናል የሚል ስጋት ነበረኝ። ደጀኔና ሸዋዬ ልብሶቹን ሲበረብሩ ግን ሁሉም መረጃዎች አሉ። ለምን እንዳልያዛቸው ግራ ገባን።

"አላምረው፣ አትስጋ...ወታደሮቹ ምንም ፍንጭ ሊያገኙ አይችሉም።" የደጀኔና የሸዋዬ በራስ መተማመን እኔንም አረጋጋኝ።

ለማንኛውም ግን ጋራዥ ብቅ ብዬ መመለስ ነበረብኝ። ቀ--ስ ብዬ ተነስቼ ወጣሁ። እንቅልፍ ማጣቴ ብዙም አልጎዳኝም። ብተኛም ቅዠቱ መንፈሴንና አካሌን ድቅቅ ያደርጋቸዋል። አሁን የጎዳኝ ሐዘኑ ነው። ቀዩን በር አልፌ ወጥቼ በምሥጢራዊዋ መግቢያ በኩል ቢሮዬ ገባሁ።

እስኪነጋጋ እዚያው ቆየሁ። ጋራዡ ከሞላ ጎደል ሥራ ሳይፈታ እንደከረመ ተረዳሁ። ባልነበርኩባቸው ቀናት ተወካዩ የሰበሰበውን ገቢ ሒሳብ ሠርተን ለመረካከብ ከአንድ ሰዓት በላይ ፈጀብን። ወደ አሥራ ሦስት ሺህ ብር የሚጠጋ ገንዘብ ቆጥሬ ተረከብኩ። ለማን እንደምሰጠው ወይም ምን እንደማደርገው አላውቅም። አዛው መሳቢያው ውስጥ ተውኩት።

'ኢሕአፓ አሁን የት አለና! ይሄው ምጣድ ላይ አስቀምጦን እየሞተ አይደል!' ኢሳያስን ሳስብ እንባዬ እንደገና መፍሰስ ጀመረ። ለመጀመርያ ጊዜ ይህንን ቢሮዬን ሲያስረክበኝ ትዝ ብሎኝ ዳግም ማንባት ጀመርኩ። የኢሳያስ ሐዘን መቼ ሊወጣልኝ ይችላል? መፍትሄው ሌላ አይደለም፤ እሱ ወደሄደበት መሄድ ነው።

ፊቴን ጠረጴዛው ላይ ደፍቼ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ። የቢሮዬ መስኮት ተንኳኩቶ የሸዋዬ ድምጽ ባይሰማኝ ኖሮ በዚያው መቀጠሌ አይቀርም ነበር። ባልተለመደው የሸዋዬ ጥሪ ደንግጬ ብድግ አልኩ። "አላምር፣ አንዴ ቢታኒያ ጋ እፈልግሃለሁ!" ብላኝ ለጥያቄ እድል ሳትሰጠኝ እልም አለች። የከረመብኝ ድንጋጤና ጭንቀት ገደል አከሎ መጥቶ ጀርባዬን ደቆሰው። ልፍጠን ልዘግይ የማውቀው ነገር የለም። ወጥቼ ከቀዩ በር ስደርስ ሞት በሩን ከፍቶ እጁን ለሰላምታ ሲዘረጋልኝ ብቻ ነው የሚታየኝ። አልፌ ገብቼ ዐይኖቼን ወደ ቢታኒያ ቤት ስወረውር ሸዋዬ በሩ ላይ ቆማ እየጠበቀችኝ ነው። የፊቷ ገጽ እርብሽብሽ ብሏል።

"ሸዋ፣ ሰላም አይደላችሁም...ምን ተፈጠረ?" ሰውነቴ እየተንዘፈዘፈ ተጠጋኋት።

"ና ና...ናማ ና...ይህችን ጥጋበኛ ሚስትህን አንድ አድርግልኝ..." ብላኝ ወደ ውስጥ ስትገባ ተከትያት ገባሁ፤ "አላምር፣ ይሄውልህ፣ ቢታኒያ የምትሠራውን ተመልከት።" መሀለኛው በር ላይ ቆማ መጋረጃውን

ስትገልጠው ቤቷ ከፍራሽ ላይ ቱር ብላ ተነስታ ወደ ጭለማው የከፍሉ ማእዘን ደርደር ብላ ከዐይኔ ስትደበቅ አየኋት። ለአፍታ ሁሉም ነገር ድንብርብር አለብኝ።

"ምንድነው? ምን እያደረገች ነው?" ግራ ገብቶኝ ሸዋዬ ላይ አፈጠጥኩባት።

"የታሰረች ጊዜ 'መርማሪው ፖሊስ ጡቴን ፈትፍቶኛል...ክብሬን ማስመለስ አለብኝ...ተራው በዚህ ሰዓት ነው...ሄጂ ፈረንሳይ ለጋሲዎን መንገድ ላይ አገኘዋለሁ፣ ገድየው እመጣለሁ...'ብላ ሽጉጥ እየወለወለችልህ ነው። እኔ ላስቀራት አልቻልኩም። ይሄ እልም ያለ ቅብጠትና ጥጋብ ነው። አንተ የምታደርገውን አድርግ!" ብላኝ በምሬት ወደ ሁለተኛው ከፍል ገብታ መብራቱን አበራችው።

መብራቱ ሲበራ ይታየኛል። አእምሮዬ ግን ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ተውጦ እንክርዳድ እንደቀመሰ ሰው አዞረኝ። የምጋፈጠው ፈተና ሲደራረብብኝ ሞቴን ጭምር ሳልመኝ አልቀረሁም። ከትላንትናውና ከዛሬው ፈተናዬ በኋላ ግን ቢታኒያ በዚህ መንገድ ትፈታተነኛለች ብዬ ጨርሶ አልጠበኩም። ብስጭትና ተስፋ መቁረጥ ተዳምረው ህሊናዬን እና አደረጉት። በደመነፍስ ወደ ፍራሹ ዐየሁ። ፍራሹ ላይ የእኔ የትንሿ ሽጉጤ ጥይቶች ዝርግፍ ብለው አብለጨለጨብኝ። የእሷን ማካሮቭ ሽጉጥ ባለፈው ተቀብያት እንደያዝኩት ነው። ቢታኒያ ወደ ተደበቀችበት ማእዘን ዞር ስል ቁም ሳጥን ተከልላ ቆማ ጥላዋ ግድግዳው ላይ ታየኝ። የእጇ ፍጥነት እንደጭልፊት አደን ዓይነት ነበር። ማድረግ ያለብኝ ነገር አሁን ቁልጭ ብሎ ታየኝ። ማካሮቭ ሽጉጡን ከሙታንታዬ ስር መዥረጥ አድርጌ አወጣሁት።

"ግንባርሽን ፈርክሸው ጠጥቼ እሞታለሁ!!" እንደ ቋያ እየነደደኩ ጮኼ ሽጉጡን ሳቀባብለው ሽቀቀ---- -ቀቀቀ የሚል ድምጽ አሰማ።

"አላ--ም--ር! አብደሃል!?" ሸዋዬ እከናፍ አውጥታ እጄን ልትይዘኝ እየተንደረደረች መጣች። "ሸዋዬ ተ--ይ---ኝ!!" ድምጼ ናረ።

ቢታኒያ ከጭለማው ውልብ ብላ ስትወጣ አየኋት። እመር ብላ መጥታ ከሸዋዬ ጀርባ እግሮቿ ስር ተገን አድርጋት ቁጭ አለች። ድርጊቴ እንኳን ለእነርሱ ለእኔም ጨርሶ ያልጠበኩት እንግዳ ነገር ነው። በቃ፣ የምሬን አበድኩ። ሰውነቴ እንደ አባዴ ሥጋ ይንዘፈዘፋል። የቢታኒያ ልብ ይሄኔ በድንጋጤ እየነጠረች እንደሚሆን ደመነፍሴ ይነግረኛል። ትክክል ነኝ። ይዛው የነበረውን ሽጉጥ ወደ ፍራሹ ወረወረችው። አልሄድም ማለቷ ነው። በቆምኩበት ላቤ ግንባሬን እያቋረጠ ወረደ። ሸዋዬ ገፋ ገፋ አድርጋ እርቃኝ ስታበቃ ቢታኒያን በደረቷ ከልላ እየገፈተረች ይዛት ወጣች።

የኢሳያስ ምስል ደርሶ አእምሮዬን ወረሰው። ሆድ ባሰኝ። እንባዬ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ መፍሰስ ጀመረ።

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ ደጀኔና ሸዋዬ ቤቲን ይዘዋት መጡ። ድምጻቸውን ስሰማ በጀርባዬ እንዲሁ ከተጋደምኩበት ቀና አልኩ። ቤት ሲገቡ ቢታኒያ ከመሀላቸው ነጠል ብላ በፍጥነት ወደ እኔ መጣች። "ፍቅ----ሬ፣ ይቅር---ታ! ስሙ-ዬ---የ ይቅር--ታ አድርግ---ልኝ..." በስሜት ተውጣ ድምጿን የእንባ ሳግ እየቆራረጠው አንገቴን ጥምጥም አለችብኝ። ይቅርታ መጠያየቃችን አዲስ ነገር አልነበረም። ቅር ያሰኟት ቃላት ተናግሬ ተቆጥታብኝ ታውቃለች። ከአንጀቴ አዝኘ ይቅርታዋን ስጠይቃት ወዲያው መለስ አለችልኝ። የአሁኑ ግን ስሜት ስለተቀላቀለበት ነው መሰለኝ ለየት ያለ ነው።

ቀስ አድርጌ እንዳቀፍኳት እጠገቤ ሳስቀምጣት ሸዋዬ አልቻለችም።ዐይኖቿ ለትውልዱ መከራና ሰቃይ የእንባ እንክብሎችን እንጠባጠቡ...

# 42

ታላቁ የ"መንጥሮ መደምሰስ" አሰሳ!

ኢሳያስ በተገደለ በአምስተኛው ቀን ነው፡፡ ዶክተር ተስፋዬ ወይም ከፍሉ ታደሰን ለማግኘት ያልገባሁበት ጉድጓድ የለም። የውኃ ሽታ ሆኑብኝ። ሁኔታው ከመጠን በላይ አስፈሪ ነው፡፡ ከማእከላዊ ኮሚቴው ሦስት አባላት ብቻ በሕይወት አሉ። እኔ ከተቆጠርኩ አራት። ከፖለቲካ ቢሮው ደግሞ ሁለት ብቻ።

የካቲት ላይ በተደረገው የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ አልተገኘሁም። መጋቢት አጋማሽ ላይ ለመሰብሰብ ቀጠሮ ተይዞ ነበር። መገናኘት ቢቻል ኖሮ ፈጽሞ የማይታለፍ ስብሰባ ይሆን ነበር። የሚቻል ግን አይደለም። ምሽት ላይ ስመለስ ቢታኒያ እኔን ፍለጋ ዙሪያ ገባውን ውሊድ! ትለዋለች። ድንጋጤዋ ፊቷ ላይ ይታወቃል...

"ቤቲዬ፤ ምን ሆንሽ? ምን ተፈጠረ?" ጠየኳት ለቀቅ ያለ የነፍሰጡር ቀሚስ እንደለበሰች ከሸዋዬ ጋር ቀዬ በር ላይ ሳገኛቸው።

"ሆድዬ፤ ናልኝማ ዝምብለህ!" መልስ ሳትሰጠኝ እጄን ይዛ በጥድፊያ እየመራችኝ አብረን ገባን።

"ሆዴ፣ የት አባቴ ልሰውርህ? የት ልደብቅህ? ሙሴ ባልዲ አሁን መጥቶ ነበር። ነገ ከንጋት ጀምሮ ትልቅ አሰሳ አለ አለኝ። የምትጠራጠሩትን ሰው ግደሉ ተብለዋል። እኛን አይመለከተንም ስለው ባልሽ ተጠርጥሯል አለኝ። ጌታዬ፤ የት ልሰውርህ?" ወገቧን በእጆቿ ይዛ ወለሉ ላይ አንነበሰች።

ሸዋዬ ግልፍ ብሎባት ጣልቃ ገባች...

"ቤቲ፣ ምን ነካሽ? ጠንካራ ልጅ አልነበርሽም እንዴ? ሞቶ የተቀበረ አስመሰልሽው'ኮ! አሁን'ኮ ፈተና ለ'ኛ አዲስ ነገር አይደለም። ይልቅ አሁን ይሄን አደጋ እንዴት እንደምናልፈው ነው መነጋገር ያለብን። ቤትሽን ዝጊና ወደ ምድር ቤት እንሂድ። ለጊዜው እዛ ሆነን የሚቀጥለውን ነገር መከታተል ነው የሚሻለን..."

"ሸዋዬ፣ ምን ላ'ርግ ብለሽኝ ነው? ሊነጥቁኝ ነው'ኮ! ሊገሉብኝ'ኮ ነው!" እንዳጎነበሰች መጥታ ጥምጥም ብላብኝ እንባዋን ለቀቀችው።

እየቆየች ግን ሸዋዬ የትእዛዝ ያህል የምትላትን ነገር ሁሉ ማድረግ ያዘች። የሚያስፈልጉንን ሁሉ እየመረጥን ሰብስብ አድርገን ወደ ምድር ቤት ገባን። አነሰ ከተባለ ሳምንት የሚያቆየንን አሰቤዛ አንድም ሳንተው ወሰድን። ፍራሽ ዘርግተን መደዳውን ተኛን። ለምን እንደሆነ በማላውቀው ምክንያት ጠብ የሚል ፍርሀት አይሰማኝም። ሁላችንም ውሳኔያችን ገድለን መሞት ነው። "እጃችን ተይዞ የውሻ ሞት አንሞትም!" እንደገና ቃል ተገባባን። በቂ ጥይት ይዘናል። ደጀኔ 'ርኬ ኤም መትረየስ ፈታቶ ሲያጸዳዳ አደረ። ቦንቦችንም በደንብ አዘጋጅቷል። አሁን አንድ ችግሬ የቢታኒያ ሆድ ብሶትና ለቅሶ ብቻ ነው። በፍጹም ልናሳምናትም ልናጽናናትም አልቻልንም።

"ባልሽ ተጠርጣሪ ነው!" የሙሴ ባልዲን ቃል መርሳት አልሆነላትም። አስጨናቂው ሌሊት አለቀ።

"ሬዲዮ? ሬዲዮ??" ሸዋዬ ላይ-ቤት ሄዳ ሬዲዮዋን ይዛ ተመለሰች።

በማለዳው ዜና "ታላቁ የመንጥሮ መደምሰስ አሰሳ" መጀመሩ ተነገረ። ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት ወዲህ ብቻ ሰባት ከፍተኛ የኢሕአፓ መሪዎች መገደላቸውን አረዳ። በተለይ ቦሌ አካባቢ እንድ ለጥቃት የተዘጋጀ ነፍሰ-ገዳይ ቡድን ተደምስሷል አለ። መሣሪያዎቹም በሙሉ መያዛቸውን ገለጸ። አሰሳው በሁሉም የአዲስ አበባ ከፍተኛዎች መቀጠሉንም አሳወቀ...

እስካሁን በእኛ ቀበሌ ምንም የተፈጠረ ችግር የለም። ተኩስም ብዙ አይሰማን። አንጻራዊ መረጋጋት ተሰምቶን ዘና ማለት ጀመርን። ስድስት ሰዓት ላይ የሸዋዬ ሬዲዮ እንደገና ተከፈተ። አሁን ለውጥ አለ። ጋዜጠኛው የአሰሳ ዜና አስቀደመ...

"በኢቃቂ በኩል ከአዲስ አበባ ከተማ በተሽከርካሪ ተሳፍረው ሊወጡ ሲሞክሩ መታወቂያ እንዲያሳዩ ተጠይቀው ፈቃደኛ ያልሆኑ አራት ሰዎች በተከፈተ ተኩስ ተገድለዋል። እነርሱም ዮሀንስ ብርሀኔ፣ ሞርቶን የተባለ የውጭ ዜጋ..."

አሁንመደንገጥቀርቷል። በቃ፣ለስለትየሰጡትገላእንደማያምሁሉየምትንጻእርተለማመድኩት።ዮሀንስ ብርሀኔ የኢሕአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ አባል መሆኑን ደርግ አላወቀም። አብረውት ያለቁትም በተለያየ አመራር ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎቻችን ናቸው። ደርግ በእርግጥም በለስ ነው የቀናው። የሱፍ አበባ ከቀሯት

አራት ወሳኝ የጠወለጉ አበቦች እንዲ ተቀንጥሶ ወደቀ። ጥቂት የእንባ ዘለላዎችን ረጨሁላቸው።

"አላምር፣ ችላ ማለት ነው። ለስንቱ ይለቀሳል?!" ብላ ሸዋዬ ወደ እውኑ ዓለም መለሰችኝኝ።

ትንሽ ቆየቼ ደጀኔ ወደ ላይኛው ቤት ሄዶ አለመመለሱ ትዝ አለኝ። "ምን ገጥሞት ይሆን?" ተነስቼ ሄድኩ። ደጀኔን ሸዋዬ ማብሰያና ማደሪያ ከፍል ውስጥ አገኘሁት። በምድር ቤቱ ጣሪያ ላይ ሸዋዬ የከፈተቻቸው ሁለት ወደ ውጭ ማጮለቂያዎች አሉ። እነርሱን በቢላዋ እየተረዳ ሲያሰፋቸው ደረስኩ። በአንደኛው ቀደዳ ትይዩ ፒኬ ኤም መትረየሱን ጠምዶታል። በቀዳዳዎቹ ሳጮልቅ እስከ ቢላል መስጊድ ድረስ ያለው ጎድጓዳማ ቦታ ቁልጭ ብሎ ይታያል። በዚያ በኩል የመጡ የደርግ አሳሾች ለወሬ ነጋሪ ሳይቀር እንደ ቅጠል ሲረግፉ ታየኝ። መጥተው እፍንጫችንን እስካልነኩን ድረስ ግን እንደማንተኩስባቸው ተስማምተናል። ትልቁ ተስፋችን በዚያ አቅጣጫ የመምጣታቸው እድል እነስተኛ ነው። አበረታትቼው ተመለስኩ...

"አንተ ጓድ አላምረው፣ እንዴ ፍጠን...ቢታኒያን አሟታል!" ገና ብቅ ስል ሸዋዬ ቢታኒያን አቅፋ ይዛ አንድ እጇን እያወናጨፈች ጠራችኝ።

ምድር ጥብብ ብላ ጠበበችኝ። ደረጃውን ተንደርድሬ ስወርድ ልወድቅ ትንሽ ነው የቀረኝ። ቢታኒያን ከሞት ቀጠና አድርሶ የሚመልስ የሆድ ቁርጠት እያጣደፋት ነው። ፊቷ ልውጥውጥ ብሎ ላቧ ግንባሯ ላይ ይንቆረቆራል። ሸዋዬ ከእርግዝና ጋር የተያያዘ መሆኑን ስትነግረኝ ደግሞ የምሆነውን አጣሁ። ለከፋ የማይሰጥ እክል እንደሆነ ከራሷ ልምድ ልታሳምነኝ ሞከረች። መድኃኒት እንዳለው ከነስሙ ስትነግረኝ ደቂቃ ማባከን አልፈለኩም። በደኀንነት መስኮቷ ልዉጣ ካልኩ ቢታኒያ አትለቀኝም። ወደነበርኩበት ተመልሼ በጣውላው በር በኩል መውጣት ተሻለኝ። ሾከክ ብዬ ከአጠገባቸው ተለይቼ ደረጃውን ወጣሁ። ጣውላው በር ስደርስ የቢታኒያ ድምጽ ከጀርባዬ መጣ።

"ሰ--ሙ--ዬ!! ስመ---ረዬ!! ተሸሎኛ----ል!"

ልታስቀረኝ ቆርጣለች። ዞር ብዬ ማየት አልፈለኩም። ፍጥነቴን ጨምሬ በቀጭኗ መንገድ በኩል ምሥጢራዊውን በር ከፍቼ ጋራዥ ገባሁ። ላንደሮቨሯን አስነስቼ ወደ ዋናው አስፋልት ነዳሁ። መንጥሮ መደምሰስ አለሳው ከኑረዲን ዳቦ ቤት ገና አልደረሰም። ፍጥነቴን ጨመርኩ፤ ወደ ምትኩ ፋርማሲ።

መንገዱ ላይ የሚታየኝ አሰሳ የለም። መኪናዋን ፋርማሲው በር ላይ አቁሜያት ወደ በሩ ሳመራ ፋርማሲው መዘጋቱን ልብ አላልኩም። መድረሻው እልም ብሎ ጠፍቶብኝ ወገቤን ይዤ በጭንቀት ቆምኩ። ወደ መናኸሪያ ከመሄድ ውጭ ሌላ እድል የለኝም። ልክ እግሬን ሳነሳ ከጀርባዬ ስሜ ተጠራ። ከወራት በፊት ዶክተር ተስፋዬንና ዘርዑን ስለ ጅማ ጭፍጨፋ ያነጋገርኩበት ቤት ግቢ ነው። በአጥሩ

ብቅ ብላ የጠራችኝ ደግሞ ጓድ አበበች በቀለ ናት። የማእከላዊ ኪሚቴ ተለዋጭ አባልና የቢታኒያ ጓደኛ!

"እንዴ ና! ሰው ይፈልግሃል። በጣም አስቸኳይ ነው!" እርግብግብ አለች።

ለጥሩ እንደማይሆን ገብቶኛል። ለምንም ቢሆን ግድ የለኝም። በዋናው የግቢው በር በኩል ሄጄ ገባሁ። በቤቱ የጀርባ በር በኩል ሰዘልቅ ከፍሉ ታደሰን አገኘሁት። የመጨረሻ ተረብሿል። ይይዘው ይለቀውን ነገር ጨርሶ አያውቅም። ውስጡ ጥስቅ ብሎ ሞልቶ የድሙት እርጉዝ የመሰለ የገንዘብ ቦርሳ ይዟል። ገንዘብ ይሁን ሌላ ነገር ግን አላውቅም። ሰላምታ ብሎ ነገር የለም። ወለሉ ላይ ሰቆም ወደ እኔ መጣ...

"ጓድ አላምረው፣ በሚገርም እድል ነው ያገኘሁህ። ይሄን ቦርሳ ጓድ ተስፋዬና ጓድ በሪሁን ረስተውት ሄደዋል። የህልውና ጉዳይ ነው። አሁን ነው በበሪሁን መኪና ከዚህ የወጡት። አምባሳደር አጠገብ ኪዳኔ ሕንጻ ከበሪሁን ሚስት ቢሮ ታገኛቸዋለህ። ቢቻል ቀድመኻቸው ድረስ። ካላገኘኻቸው ግን ለበሪሁን ሚስት ሰጥተሃት ና። የሞት የሽረት ጉዳይ ነው..."

"ተስፍሽ አሁንም አዲስ አ'ባ ነው አይደል? ያሳዝናል!" በተሸነፈ ስሜት የመጨረሻ ቃል የሚመስል ነገር ተንተባተብኩ።

"ለምኜው ነበር። 'የ'ኔ ሕይወት ከማን ይበልጣል?' አለኝ። ጠይቀውና ፈቃደኛ ከኾነ፣ ፐሊ---ዝ፣ ጓድ አላምረው፣ እንደምንም ብለህ ወደ አንዱ አካባቢ አሾልከኸው ና፣ 'ፐሊ--ዝ...'ፐሊ---ዝ..."

ከፍሉን እንዲህ ሲንቦጃቦጅ አይቼው አላውቅም። አበበች የቢታኒያን መድኃኒት ገዝታ እንድትጠብቀኝ አደራ ብያት ወጣሁ። ከቀበሌ ቀበሌ መዘዋወር ተከልክሏል። ተሽከርካሪ መቆጣጠር ግን ያስቸገራቸው ይመስለኛል፣ እንቅስቃሴ ይታየኛል። 'የፈለገ ይምጣ!'መኪናዬን አስነስቼ ትንሽ እንደሄድኩ አዲስ አበባ የዘወትር መልኳን ቀየረችብኝ። የደርግ የበር ከበር ፍተሻ ቁም ስቅሏን ያሳያታል። አፏ እስከ ጉሮሮዋና ደረቷ...ሆድ እቃዋ እስከ አንጀቷ...ተከፍቶ ትበረበራለች። ወጣቶችና ወላጆች እጃቸው በሰንሰለት እየታሰረ ይነዳሉ። ምናልባት ነገ ከእኛ ጋራዥ እንደሚደርስ ገመትኩ።

'ማምሻም ዕድሜ ነው! ይላል የአገሬ ሰው።' ሰሞኑን የምደጋግመው ነው።ፍጥነቴን ጨመርኩ።

በፒያሳ በኩል ቸርችል ጎዳናን አቋርጬ አምባሳደር ቲያትር ቤት ደረስኩ። መኪናዋን ከኪዳኔ ሕንጻ አጠገብ በነበረ ላውንደሪ ቤት ፊት ለፊት አቁሜያት ወረድኩ። ወደ ሕንጻው ለማምራት ከርቀት ሳማትር የበሪሁን ሚስት ደረጃውን ወርዳ ስትመጣ አየኋት። ከግቢው በር ሳትወጣ ልሰጣት ራመድ ስል ተቀደምኩ። ከየት እንደመጡ ያላየኋቸው ታጣቂዎች ከፊት ለፊቴ መጥተው አስቁመዋታል። ወደ ላውንደሪ ቤቱ አፈገፈኩ። ዐይኖቼ እሷ ላይ ናቸው። ቦርሳዋን ከፍታ መታወቂያ ስትሰጣቸው ከጀርባዋ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይና በሪሁን ፊትና ኋላ ሆነው ደረጃውን እየወረዱ ነው። በምን ተዐምራዊ ቋንቋ...

በምን ምልከት...በምን ድምጽ ልንገራቸው?! መጥተው ነዲድ እሳት ላይ ቆሙ። ተቀደምኩ። ሁሉም ነገር እንደ ጎርፍ ቅጽበታዊ ነበር...

ዷዷዷ...ካካካካ...ዷዷድም... የጥይት እሩምታ ምድርን አንቀጠቀጣት።

በራሁን ጀርባው ላይ ተመታ። ጥቅልል ብሎ ደረጃው ላይ ሲወድቅ አየሁት። ዶክተር ተስፋዬ አንደኛውን ደረጃ ወጥቶ ሁለተኛውን ሲይዝ የግራ እግሩን ማንሳት አቅቶት እንደምንም እየጎተተው ከዐይኔ ተሰወረ። በተኩሱ የተሸበረው ሕዝብ በየጥጋጥጉ ቦታ ሲይዝ እኔም ዘልዬ ላውንደሪው ቤት ገባሁ። የላውንደሪው ሴት ሠራተኞች ወንበሮች ላይ ቆመው በመስኮት ወደ ተኩሱ ይመለከታሉ። ፊታቸውን ስላዞሩ አላዩኝም። ድምጽ ሰምተው ዘወር ሲሉ መሀል ወለሉ ላይ ቆሜ አዩኝ።

"መግባት አይቻልም! ውጣ! ውጣ! ተመለስ!" አንድ ላይ ጮኹብኝ።

'የመጣው ይምጣ!' ወጥቼ ወደ መኪናዬ ተጣደፍኩ። በመሀሉ ባላሰብኩት ደመነፍሳዊ ግፊት ወደ ኪዳኔ ሕንጻ ዞር አልኩ። ነፋስ ሽቅብ አንስቶ መልሶ ቁልቁል የወረወረዉ ቆርቆሮ ነበር የመሰለኝ። አይደለም። እየተምዘገዘገ የወረደው ሰው ነው። ከሰውም ደግሞ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ! ከአምስተኛ ፎቅ ላይ እየተንሳፈፈ ወርዶ ድንጋዩ ንጣፍ ላይ ሲወድቅ ጧ! የሚል ድምጽ እንደ ጥይት ፈነዳ።

'የኢሕአፓ የወቅቱ ዋና ጸሐፊ ተሰዋ! የሱፍ አበባ ከወገቧ ላይ ተቆርጣ በቁመቷ ልክ ዟ ብላ ወደቀች...'

ተስፋ መቁረጥ የበለጠ በድን አደረገኝ። እንደገና ወደ ሕንጻው በር ተመለከትኩ። የአሳሾቹ ሁኔታ አስፈሪ ነው። እየተሯሯጡ ወደ ግቢው ገቡ።መኪናዬ ላይ ወጥቼ ከፊትና ከኋላ ከበባ መኖር አለመኖሩን አየሁ። መንገዱ ተዘግቷል። አሥራ አምስት ደቂቃ ያህል እንደቆምኩ ለውጥ መጣ።

የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት መኪና ከግራ አቅጣጫ ደረሰች። ኪዳኔ ሕንጻ ስትደርስ በር ላይ ቆመች። ጥቁር መነጽር ያደረገ አጭርና ጠይም ሰው ወረደና አደግድገው የሚጠብቁትን አሳሾች ተቀላቀለ። በደንብ ሳየው የመኢሶኑ ዶክተር ነገደ ጎበዜ ነው። በአጀብ መሀል ሆኖ የወደቀውን ሰው ማንነት ከተመለከተ በኋላ ወደ ጀርባ ዞር አለ። የወደቀው ሰው ተስፋዬ ደበሳይ መሆኑን እንዳወቀ አልተጠራጠርኩም። ትክክል ነኝ። አሳሾቹን በእንኳን ደስ አለን! ፈገግታ እጆቻቸውን እየጨበጠ ሽቅብና ቁልቁል ወዘወዛቸው።

መራሩ ጨዋታ አከተመ!

# ድሕረ-ታሪክ

"ግንበኞች የናቁት ድንጋይ የማዕዘን ራስ ይሆናል!" ወይዘሮ ማስተዋል ይህንን አባባል ይደጋግሙታል። ሙሴ ባልዲ ከደርግ የሞት መንጋጋ ስላወጣን ነው እንዲህ የሚሉት።

ሸዋዬ ቃሏን አክብራ እየተታኮሰች ተሰዋች። ደጀኔ አራቱን የደርግ ፈታሽ ታጣቂዎች ረፍርፎ አምልጧል። የት እንደገባ ሙሴ ጭምር የሰማው ነገር የለም። ቤቲና እኔ ለጥቂት ሞትን አምልጠን እስከ 1969 መጨረሻ ድረስ በሙሴ ቤት ተደብቀን አሳለፍን። ቤቲ እርግዝናዋ እየገፋ መጥቶ ሆዷ ተንጠለጠለ።ነሐሴ 10 ቀን ሴት ልጅ ተገላገለች። እርምቱ ባይሰምርም ሕጻን እርምት ሰመረ ተወለደች። እንደ ወጉ እልልል...አልተባለም።

ሕይወታችን ከእስረኝነት ብዙም የተለየ አልነበረም። ነገር ግን ሞትን ለማምለጥ የምንኖረው ስለሆነ ደስተኞች ነበርን። ሙሴና ባለቤቱ አንድም ቀን ሳይሰለቹን ነው ያስተናገዱን። ዉለታቸውን በምን እንደምንመልሰው አናውቅም። ወይዘሮ ማስተዋል ሌሊት መጥተው አብረውን ይውላሉ። ምሽት ይመለሳሉ። አደጋዉ እየቀነሰ ሲመጣ ጥር መጨረሻ ወደ ቤት ለመመለስ ወሰንን።

ቢታኒያ እየተደፋፈረች ስትመጣ ወደ ጓደኞቿ ስልክ መደዋወልና መረጃ መሰብሰብ ጀመረች። አንድም ደስ የሚል ወሬ ሰምታ አሰምታኝ ግን አታውቅም።አበበች በቀለ ታስራ ቆይታ በኋላም መገደሏን፤ብርሃነመስቀል የተወሰነ የታጠቀ ቡድን ይዞ ሸዋ መግባቱን፤ ዘርዑ ክሕሸንና ሚስቱ ታደለች ኪዳነማርያም (ለምለም) ከኤርትራ ተመልሰው ወልቃይት መሆናቸውን፤ ከፍሉ ታደሰ ደግሞ ጭራሽ የት እንደገባ አለመታወቁን ነገረችኝ። በኢሕአፓ ላይ የሚወሰደው የግድያ እርምጃ "ቀይ ሽብር" የሚል ሥም ተሰጥቶት ቀጠለ። የእኛ ታጣቂ ከንፍ እጁ ዝሎ የአልሞት ባይ ተጋዳይ ጥይት ብቻ ያጮኻል።

"ኢሕአፓ እስካሁን አለ እንዴ?" ቢታኒያ ወደ ዮሴፍ አዳነ ባለቤት ደውላ ጠየቀቻት።

"ኢሕአፓ ከሞተ መንፈቅ አልፎታል። አሁን የምትሰሚው ጥይት እንዳያሳስትሽ። ድርጅቱ መፍረሱን ያላወቁ የዞንና የሪጅን ታጣቂዎች የሚተኩሱት ነው።አንዳንዶቹም ቀደም ብሎ የተሰጣቸውን ትእዛዝ እየፈጸሙ ነው።ቤቲዬ፣ አትጠራጠሪ...ድርጅታችን ፈርሷል!"

ሰኔ ወር ላይ ሕቡእነትን ትተን ወጣን። የሙሴ ድጋፍ አሁንም አልተለየንም። "አናርኪስቶች" አለመሆናችንን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ጽፎ አምጥቶ ሰጠን።አንጻራዊ የሰላም አየር መተንፈስ ጀመርን። ቤቲ ያቋረጠችውን ትምህርት እንደገና ጀመረች። እኔ በጋራዥ ሥራዬ ጥቂት ቆየሁ።

በዚያው ዓመት ኢሕአሠ በህወሓት ሠራዊት ተመትቶ አሲምባን መልቀቁን ሰማን። የተረፈው ሠራዊት አመለጥን ሲል እንደገና በጀብሀ መታገቱን፣ እስከሚለቁት ድረስ ግን የሰው ሏጅ ይቋቋመዋል ተብሎ በማይታመን ችግር ዉስጥ መውደቁን ሰማን። ይህ ሠራዊት ርሀብ ሲጠናበት አባብና ሳር ሳይቀር እየበላ በመጨረሻ ጎንደር መድረሱን ሰማን።

ሌላም ታሪክ ከጆሯችን ደረሰ። እዚያው አሲምባ ነው። ሰንገዶ ላይ ጸጋዬ ደብተራውና አብዲሳ ኢያና በአንጃኝነት የከሰሷቸውን 17 ጓዶች በእስር አቆይተዋቸው በመጨረሻ ረሸነዋቸው ኤርትራ ገቡ ተባለ። ይህንን ዜና ቢታኒያን ስነግራት የተጠቀምኩበት ቃል ለቀናት አፌን ጎምዝዞኝ እንደነበር አስታውሳለሁ...

"ጸጋዬ ደብተራው፣ የሞተን በድን አካል ለሁለተኛ ጊዜ ገድሎ ይፎክር ይሆን?"

በ1971 ሙሉ በሙሉ ሕቡዕነትን ትቼ ይፋ ወጣሁ። አሁን ከተሞች ሙሉ በሙሉ እረጭ ብለዋል። የጋራዥ ሥራዬን ለተቀጣሪ ሜካኒክ አስረክቤ ብሔራዊ ባንክ ተቀጠርኩ። አዲሱ ሥራዬ ላይ እንዳለሁ አዲስ ወሬ ደረሰኝ።ብርሃነመስቀልና ጓደኞቹ በወሎና በሸዋ ድንበር መካከል በደርግ ተይዘው እስር ቤት መግባታቸው። ዐመል አይለቅም፣ አንዲትም ጥይት ሳያጮኹ ነው እጃቸውን የሰጡት አሉ። ክረምት ላይ ደግሞ ብርሃነመስቀልና ሌሎች ሰባት ጓደኞቹ ተመርጠው መረሸናቸውን ሰማሁ። ባለቤቱ ታደለች ኃይለማርያምም ነፍሰጡር ስለነበረች በተአምር ከርሸና መትረፏን ነገሩኝ።

'The game is assuredly over, and he was a poor player!!' ልበል እንጂ በብርሃነመስቀል ሞት የተሰማኝ ሐዘን ጥልቅ ነው። ያ ገና ድሮ አውሮፕላን ዉስጥ ያየሁትን፣ ያ ኢትዮጵያን እንደ ሙሴ እጁን ይዞ ያሻግራታል ብዬ ጽኑ ተስፋ ያደረኩበትን፣ ያ በጽናቱ የምቀናበትን ብርሃነመስቀልን ሳስብ አንድ አባባል እንደ ጭልፊት መጥቶ ጭንቅላቴ ላይ ጉብ አለ።

"አንድ ዛፍ ብዙ ሺህ ክብሪቶችን ይፈጥራል። ብዙ ሺህ ዛፎች ግን በአንድ ክብሪት ይወድማሉ!" ምን ዓይነት ምጡቅ ትዝብት ነው!? 'አንድ ብርሃነመስቀል ረዳ ኢሕአፓን ፈጥሮ ብዙ ሺህ ብርሃነመስቀሎች ተወለዱ። ነገር ግን አንድ ዘርዑ ክሕሸን በሠራው ስህተት ሺዎች ወደቁን። እርስ በእርስ ተበላላን። እነሆ ጌታቸው ማሩ በገዛ ፖለቲካ ቢሯችን እጅ ወደ ዐጽምነት ከተቀየረ ዓመት ከምናምን ሊያስቆጥር ነው። የአሲምባ ክህደትና የከተማ አምልኮ ለምድራዊ ሲኦል ዳረገን። መራራው ታሪክ በግብር ተፈጽሟልና አሁን እንደ ቅገቤት "ሕልም እልም!" ብለው የሚያባርሩት ነገር አይደለም።

ለልጄ እርምት ሰመረ ወደፊት የምነግራት ታሪክ ይኖረኛል።

*ተረት ተረት...*

*የላም በረት....*

*አንድ ኢጅግ ጨብ የሆነች የምታምር የሱፍ አበባ ነበረች።*

*እሺ...*

*ስትኖር...ስትኖር...ስትኖር....ስትኖር....ስትኖር...በግ ብሎ የበራ አንድ የከተማ አምፑል ብርሃንን ወየች፣*

*እሺ....*

*ይሄንን ብርሃን አመለኩችው...*

*እሺ...*

*ስትኖር...ስትኖር..ስትኖር...ከዕለታት አንድ ቀን መብራት ሄደና...አቧም ከሰመች።*

"አንድ ዛፍ ብዙ ሺህ ክብሪቶችን ይፈጥራል። ብዙ ሺህ ዛፎች ግን በአንድ ክብሪት ይወድማሉ!"

አንድ ብርሃንመስቀል ረዳ ኢሕአፓን ፈጥሮ ብዙ ሺህ ብርሃንመስቀሎች ተወለዱ። ነገር ግን አንድ ዘርዑ ክሕሸን በሠራው ስህተት ሺዎች ወደቅን። እርስ በእርስ ተበላላን።

እነሆ ጌታቸው ማሩ በገዛ ፖለቲካ ቢሯችን እጅ ወደ ዐጽምንት ከተቀየረ ዓመት ከምናምን ሊያስቆጥር ነው። የአሲምባ ክህደትና የከተማ እምልኮ ለምድራዊ ሲኦል ዳረገን።

ዋጋ፡- 91.20 ብር ብቻ

Price- 30 USD

Kittmann Books